# ምስጢሩ ሲገለጥ




አዘጋጅ ታሪኩ ተፈራ(MA)

የኮፒ ራይት መብት ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ነው፡፡
All rights reserved.
© Tariku Tefera
የመጀመርያ ዕትም 2012ዓ.ም/2020GC
E-mail – tarikutefera2@gmail.com
ISBN: 9781393104469

## ማስታወሻ

- ምዕራፍ 1 የሳይንስና የፍልስፍና ዕውቀት የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን መረዳት የሚከብደው ሰው ከምዕራፍ ሁለት ጀምሮ ማንበብ ይችላል፤ በተጨማሪም መፅሀፉን ለሰዎች በስጦታ ሲያበረክቱ ሙሉውን መፅሀፍ ማንበብ ለሚከብዳቸው እንዲያነቡ የምትፈልጉትን ምዕራፍ ወይንም ክፍል ለይተው ይንገሯቸው፣
- በመፅሀፉ ውስጥ የተጠቀሱት የዘመን አቆጣጠሮች የቀረቡት በሁለት መንገድ ነው፣ ኢትዮጵያዊ ታሪኮች በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የቀረቡ ሲሆን ዓለማቀፍ ታሪኮች ደግሞ እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር ቀርበዋል፣
- ከመፅሀፍ ቅዱሱ የተጠቀሱት ጥቅሶች የተወሰዱት ከ1954 ህትመት ነው፣ ጥቅሶቹም የቀረቡት በተለመደው ምህፃረ ቃል ሲሆን ማንኛውም ሰው ጥቅሶቹን ከመፅሀፍ ቅዱሱ መመልከት እንዲችል እነዚህ ምህፃረ ቃሎች የሚወክሉትን ምዕራፍ በ"አባሪ-1"/Annex-I/ ክፍል ቀርቧል፣
- የቁርአን ምዕራፎች ቋሚ በመሆናቸው በተለምዶ ከቁርአን ሲጠቀስ የምዕራፉን ቁጥርና የአንቀፅ ቁጥርን በማስቀመጥ በመሆኑ በዚህች መፅሀፍም ከቁርአኑ የተጠቀሱትን ጥቅሶች የምዕራፉን ቁጥርና የአንቀፅ ቁጥሩን በማስቀመጥ ብቻ የቀረቡ ሲሆን የምዕራፍ ቁጥሮቹ የሚወክሉት ምዕራፍ በ"አባሪ-2"/Annex-II/ ክፍል ቀርቧል፣
- መፅሀፍ ቅዱሱን ወይንም ቁርአኑን በአማርኛ ማግኘት ያልቻላችሁ ከኢንተርኔት Download አድርጋችሁ ማንበብ ትችላላችሁ፡፡

መቅድም ....................................................................4
መግቢያ ....................................................................7
ምዕራፍ አንድ
1. ኢአምላኪነት("ፈጣሪ አምላክ የለም" አስተምህሮ) ......................8
ምዕራፍ ሁለት
2. እስልምና........................................................................83
ምዕራፍ ሦስት
3. ከክርስትና በመውጣት ሌላ ሀይማኖት የተከተሉ ....................200
3.1. ከክርስትና ወደ ማህበረሰባዊ ሀይማኖት የተመለሱ............200
3.1.1. ዘመናዊው ዋቂፈና................................................201
3.1.2. ራስ ተፈሪያን ..........**Error! Bookmark not defined.**
3.2. ከመፅሀፍ ቅዱሱ በኋላ በመጣ "ቅዱስ" መፅሀፍ ከክርስትና የወጡ (ባኢ፣ ሞርሞኒዝም፣ ሺንቼአንጂ፣ የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒስትና የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ)..........................................................228
ምዕራፍ አራት
4. ኦርቶዶክስና ካቶሊክ ..........................................................240
ምዕራፍ አምስት
5. በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት ...........390
5.1. የሐዋርያት ቤተክርስቲያን "Only Jesus" .......................391
5.2. የይኾዋ(የጂሆቫ) ምስክሮች (Jhova Witness) ................421
5.3. አድቬንቲስት(Adventism) .......................................451
ምዕራፍ ስድስት
6. ፕሮቴስታንት..................................................................459
ምዕራፍ ሰባት
7. መጪው የአንድ ዓለም አንድሀይማኖትና አንድ መገበያያ ስርአት 500
ማጠቃለያ........................................................................519
አባሪ(Annex)...................................................................520

# መቅድም

የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ፈፅሞ የሚለየው በአንድ ነገር ብቻ ነው “አምላኪነት”፣ ሌሎች የሰው ልጆች ባህሪ ብቻ የሚመስሉን እንደ ፍቅር፣ ርህራሄ፣ ተመራማሪነት ... የመሳሰሉት ባህሪዎች በተወሰነ መጠን ይሁን እንጂ እንስሳቱም ጋር ይገኛሉ ነገር ግን እንስሳቱ ጋር ፈፅሞ የማናገኘው “አምልኮ” የተባለችውን የሰው ልጅ ብቸኛ ባህሪ ነው፡፡

ይህ የሰው ልጅ ብቸኛ ባህሪ ደግሞ በሰው ልጆች መካከል ወጥነት የሌለው፣ የተበታተነ፣ አብዛኛውንም ጊዜ እርስ በርስ የሚቃረንና ሰዎችን እስከ ማገዳደል የሚያዳርስ ሆኖ ይታያል፣ ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ከሶሻሊዝም/ኮሚኒዝም ፍልስፍናና አንዳንድ ሳይንሳዊ ግኝቶች በመነሳት አንዳንድ ቡድኖች ይህን የሰው ልጅ ለዘመናት የኖረበትን ሀይማኖተኝነቱ ትክክል እንዳልሆነና ይባሱኑ [1]“ሀይማኖት የሰው ልጆች እድገት እንቅፋት ነው” ሲሉ ይደመጣል፡፡

ለዚህ መፅሀፍም ዝግጅት ምክንያት የሆነው፣ በዚህ የሰው ልጅ ብቸኛ ባህሪ ላይ ያለው እውነት አንድ ሆኖ ሳለ ሰዎች በዚህ መልክ የመለያየታቸው ምክንያት አንዷ እውነት በተለያየ የውሸት ፍልስፍናና አስተምህሮ በመጋረዷ በመሆኑ፣ ይህንንም ምስጢር በመግለጥ የተሸፈነችውን አንዷን እውነት መግለጥ የሚቻልበት መሠረት መኖሩን በመመልከት ነው፡፡ በዚህም በመፅሀፏ “ፈጣሪ የለም” የሚለውን ኢአምላኪነት እንዲሁም “ፈጣሪ በኛ መንገድ ብቻ ነው የሚገኘው” የሚሉትን የእያንዳንዱን አምላካዉያንን አስተምህሮ በዝርዝር ትመለከታለች፡፡

እዚህ ጋር የአምላካውያን አስተምህሮዎች የተለያዩና ሰፋፊ በመሆናቸው የየቤተእምነቶቹ አስተምህሮም በደንብ ለመመርመር እንዲያመቸን ሀይማኖቶችን በየቡድናቸው እንመለከታለን፣ [2] በሀይማኖቶች ጥናት መሠረት በአለም ላይ ያሉ ሀይማኖቶች በዋናነት በአምስት ይከፈላሉ፣

---

[1] **የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት**፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1978፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ ገፅ 325

[2] https://en.m.Wikipedia>wiki>major religion groups

1. የአብርሃም ሀይማኖቶች - ክርስትና፣ እስልምና፣ ጁዳይዝም ...
2. የህንድ ሀይማኖቶች- ሂንዱይዝም፣ ቡድሂዝም፣ ሲኪዝም፣ ጃኒዝም...
3. የምስራቅ ኢሲያ ሀይማኖቶች - ኮንፊሺያኒዝም፣ ታኦይዝም ...
4. የኢራናውያን ሀይማኖቶች-ያዝዳኒዝም፣ዞሮአስተሪአኒዝም፣ ያርሳኒዝም...
5. በየሀገራቱ ውስጥ የሚገኙ በየማህበረሰቡ የተወሰኑ ባህላዊ ሀይማኖቶች

   በመባል ይታወቃሉ፡፡

ይህ የሀይማኖቶች ብዛት የምንፈልጋትን እውነት እንዳይጋርድብን፣ ለጊዜው የኢአምላኪ/ኢአማኒያንን ፍልስፍናን ትተን፣ በአምላካውያን አዕምሮ ሆነን ከነዚህ የሀይማኖት ቡድኖች ውስጥ ትክክለኛ ሊሆን የሚችሉትን ቡድኖች ለይተን በማውጣት ከኢአምላኪነት ጋር እንመለከታለን፡፡

በዚህም በአምላካውያን አዕምሮ ሆነን ስንመለከት “የሰው ዘር ከመነሻው ዋናውን አምላክ የሚያመልክበት አንድ ትክክለኛ ሀይማኖት ሲከተል ነበረ ነገር ግን በሰይጣን እና በሰው ልጆች ግጭት፣ ክፋት፣ ዝናና ንዋይ ፈላጊነት ... ምክንያት የተለያዩ አስተምህሮን የሚከተሉ የተለያዩ ሀይማኖቶች ተፈጠሩ” በዚህም “ዋናውን አምላክ” በትክክለኛው መንገድ የሚያመልከው አንዱ ሀይማኖት ብቻ ነው፣ ይህ ሀይማኖት የትኛው ነው? ወደሚለው ከመሄዳችን በፊት በአምላካውያን አዕምሮ ሆነን አንድ አጠቃላይ መስፈርት እናስቀምጥ፣

> “ትክክለኛዋ ሀይማኖት <u>የምታመልከው ዋናውን ፈጣሪ</u> ሲሆን በዚሁ አምላክ በሚኖራትም እገዛ ሀይማኖቷ <u>በአንፃራዊነት አለማቀፋዊ ናት</u>”

በዚህ መስፈርት መሠረት ከላይ የተዘረዘሩትን ሀይማኖቶች ስንመለከት፣ በመጀመሪያ ላይ ያሉት ሁሉም የአብርሃም ሀይማኖቶች የምናመልከው “ዋናውን አምላክ ነው” ስለሚሉ እንዲሁም ከሌሎች ሀይማኖቶች በአንፃራዊነት ሲታዩ አለማቀፋዊ በመሆናቸው፣ ሁሉንም የአብርሃም ሀይማኖቶች ለተጨማሪ ምርመራ“ እንወስዳቸዋለን፡፡

በግዝፈት ከአብርሃም ሀይማኖቶች ቀጥለው የሚገኙት የህንድ ሀይማኖቶችን ስንመለከት፣ ሀይማኖቶቹ የሚያመልኩት በስራ ድርሻ የተከፋፈሉ አማልክቶችን እንጂ ዋናውን አምላክ አለመሆኑ እንደዚሁም ሀይማኖቶቹም በህንድ ዘሮች ብቻ የተወሰኑና “ዘር ዘለል” አለማቀፋዊ ሀይማኖቶች ባለመሆናቸው እነዚህ ሀይማኖቶች ለትክክለኛው ሀይማኖት ፍለጋችን መጠቀም አንችልም፡፡

እንደዚሁም የምስራቅ ኢሲያ ሀይማኖቶች፣ የኢራን ሀይማኖቶችና ሀገር በቀል ባህላዊ ሀይማኖቶችን ስንመለከት ከራሳቸው ማህበረሰብ በላይ መመልከት የማይችሉ በመሆናቸው እነዚህን ሀይማኖቶችም ለትክክለኛው ሀይማኖት ፍለጋችን መጠቀም አንችልም፡፡

ከባህላዊ ሀይማኖቶች ጋር በተያያዘ አንዳንድ ባህላዊ ሀይማኖቶች በዘመናዊው ፍልስፍና እየተደራጁና ከላይ የተመለከትናቸውን ሁለቱን መስፈርቶች በሌላ ፍልስፍና ሲያሟሉ ይታያሉ፣ ሁሉንም ማየት ባይቻልም ለምሳሌ እንዲሆነን ከነዚህ ውስጥ ግዙፉንና አሁን በዘመናዊ መንገድ የተደራጀውን ዘመናዊውን ዋቄፈና እንመለከታለን፡፡ በዘመናዊው ዋቄፈና አስተምህሮ “ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ ነው፤ አይሁድ፣ አረብ... ይህንን አምላክ በራሳቸው እሴት እንደሚያመልኩት ኦሮሞም ይህን አምላክ በራሱ እሴት ያመልካል” ይላሉ፣ በዚህም ዘመናዊው ዋቄፈና ከላይ ያስቀመጥናቸውን ሁለቱን መስፈርቶች ስለሚያሟላልን ለዝርዝር ዕይታ እንወስደዋለን፡፡

በዚህም “ፈጣሪ የለም” የሚለው እንዲሁም “ፈጣሪ አለ” ብለው ነገር ግን በተከፋፈለ መንገድ የሚሄዱትን የአብርሃም ሀይማኖቶችንና ዋቅፈናን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

# መግቢያ

በመፅሀፏ ውስጥ ፈጣሪ “አለ” ወይስ “የለም” ከሚለው ፍልስፍና በመነሳት የአብርሀም ሀይማኖቶች ስር የሚመደቡትንና የዋቄፈና ሀይማኖትን አስተምህሮ በዝርዝር እንመለከታለን፣ በዚህም፡-

- “ፈጣሪ አምላክ የለም” የሚሉትን ኤቲዝምና ሂውማኒዝምን
- ጥንታዊዎቹን እስልምና፣ ኦርቶዶክስና ካቶሊክን፣
- ፕሮቴስታንትን፣
- በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተመሰረቱትን ጂሆቫ፣ ሐዋርያትና አድቬንቲስት፣
- ከፊል የአብርሃም ሀይማኖት የሆኑት ባኢ፣ ሞርሞን፣ ሺንቼአንጂ፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒዝም፣ የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴና የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን፣
- “ዋናውን አምላክ በማህበረሰባችን ዕሴት እናመልካለን” የሚለውን ዘመናዊው ዋቄፈናን እንዲሁም “የክርስትናውን አምላክ በራሳችን ዕሴት እናመልካለን” የሚሉትን ራስ ተፈሪያንን፣
- ሁሉንም ሀይማኖቶች በአንድ ዕዝ ስር ሊያጠቃልል የተዘጋጀው መጪውን “የአንድ አለም አንድ ሀይማኖት”

አስተምህሮቶችን በዝርዝር በመመልከት ለዘመናት በሰው ልጆች መካከል ያለውን ሀይማኖታዊ ልዩነት በማያዳግም መልኩ መፍታት የሚቻልበትን መንገድ እንመለከታለን፡፡

መልካም ንባብ//

# ምዕራፍ አንድ

## 1. ኢአምላኪነት(“ፈጣሪ አምላክ የለም” አስተምህሮ)

“ኢአምላኪነት/ኢአማኒነት” የሚባለው “ፈጣሪ አምላክ የለም” የሚል ፍልስፍና ነው፣ የፍልስፍናው አራማጆችም በዋናነት የስነፍጥረት ሳይንሶችና የሶሻሊዝም/ኮሚኒዝም የፖለቲካ መስመር ነው፣ እንደ ሶሻሊዝም/ኮሚኒዝም አስተምህሮ [3] “ኢአማኒነት የመጨረሻውን የማይለወጥ ቅርፁን የያዘው የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና መሠረት በሆኑት በዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁሳካላዊነት ፍልስፍና ነው፡፡”

በዚህ ምዕራፍም ይህን የኢአምላኪነትን አስተምህሮ ከአጠቃላይ እውነታና ከአምላካውያን አስተምህሮ ጋር እያነፃፀርን እንመለከታለን፣ ከአምላካውያን ውስጥ ለዋናው አምላክ ፍለጋችን ትክክለኛ የሚሆነን የአብርሃም ሀይማኖቶችና ዋቄፈናን እንደወሰድነው ሁሉ ከነዚህ ሁለቱ መንገዶች ደግሞ መፅሀፍ ያላቸው የአብርሃም ሀይማኖቶች በመሆናቸው፣ የአብርሃም ሀይማኖቶች ደግሞ የሚመሩት በዋናነት በቁርአንና በመፅሀፍ ቅዱሱ ሆኖ ቁርአኑ ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱን ስለሚቀበል(ቁርአን 2፡136፣ 3፡3, 4፡136, 29፡46 …) ለማነፃፀርያ መፅሀፍ ቅዱሱን እንጠቀማለን፣ በዚህም በዚህ ምዕራፍ ስር፣

- የ“ፈጣሪ አለመኖር” በኢአምላኪነት አስተምህሮ፣
- የኢአምላኪነት የስነፍጥረት ፍልስፍና፣
- የስነፍጥረት ሳይንሱ የፈጣሪን ሀለዎት(ህልውና) የማጥናት አቅም፣
- ከኢአምላካውያንና ከአምላካውያን በተለየ መንገድ የፈጣሪ መኖር አለመኖርን

በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

---

[3] **የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት**፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1978፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ ገፅ 325

## 1.1. “የፈጣሪ አለመኖር” በኢአምላኪነት አስተምህሮ

ኢአምላካውያን አምላክ እንደሌለና ፍጥረታት የመጡት በ1.2 ክፍል በዝርዝር በምንመለከተው በተፈጥሮአዊ ሂደት እንደሆነ ይናገራሉ፣ በኢአምላኪነት በዋናነት የሚታወቁት አስተምህሮቶች ኤቲዝም(Atheism) እና ሂውማኒዝም(Humanism) ሲሆኑ፣ ሁለቱም የፈጣሪን አለመኖርን የሚያስረዱት በተለያየ መንገድ ነው፣ የሁለቱንም አስተምህሮዎች ድካምና ጥንካሬ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 1.1.1. “የፈጣሪ አለመኖር” በኤቲዝም አስተምህሮ

ኤቲዝም የሚመራው በቁስአካላዊነት(materialism) ፍልስፍና ነው፣ ይህ ፍልስፍና ስለነገሮች ትንታኔ የሚሰጠው ሁሉንም ነገሮች በቁስነታቸው በመመልከት ነው፣ ይህ ፍልስፍናም ፈጣሪን በቁሳካላዊነት መንገድ ስለማያውቀው “ፈጣሪ አምላክ የለም” ይላል፡፡

ይሁን እንጂ በቁስአካላዊነት ብቻ ተወስኖ የሚደረግ ፍልስፍና ሙሉ ፍልስፍና አለመሆኑን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ መረዳት እንችላለን፣ አምላካውያን የሚሉትን መንፈሳዊ አለም እንኳን ለጊዜው ትተን ቁስአካላዊ ያልሆኑትን እንደ ሀይል፣ሞገድ፣ ፎቶንስ፣ ህይወት ... የመሳሰሉትን ግምት ውስጥ አለማስገባቱ ይባሱኑም ደግሞ ቁሶች በራሳቸው የነዚህ ውጤቶች መሆናቸውን ስንመለከት በቁስ ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ ስለ ሁሉም ነገር ድምዳሜ የሚሰጠው ቁሳካላዊነት ጎዶሎ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ዘመነኛው ሳይንስ “ኩአንተም ቲዎሪም(Quantum Theory)” የቁስ አካላዊነት የስነፍጥረት ፍልስፍና ትክክል እንዳልሆነ ይናገራል፣ እንደ ኩአንተም ቲዎሪ “የሚታየው ቁስአካል የተሰራው ከማይታዩት ቅንጣቶች `quantas` (electrons, protons, photons ...) ነው፣ እነዚህ ቅንጣቶች ደግሞ ሀይል እንጂ ቁስአካል አይደሉም” ይላል፣ በዚህም ኩአንተም ቲዎሪ “ቁስ የሚባል ነገር የለም፣ ሁሉም ነገር ሃይል ብቻ ነው፣ በዚህም ስለ ስነፍጥረት ሙሉ እውቀት የሚሰጠን ፍልስፍና የማቴሪአሊዝም ፍልስፍና ሳይሆን በማይታየው አለም ላይ የሚደረገው የኩአንተም ፍልስፍና ነው” ይላል፡፡

የቁስ አካላዊነት ፍልስፍናና የኩአንተም ፅንሰ ሃሳቦች ነገሮችን የሚያዩበት መንገድ ላይ እርስ በርስ ቢጋጭም ሁለቱንም አስተምህሮቶች የምንጠቀምባቸው የየራሳቸው አግባቦች አሉዋቸው ይሁን እንጂ የቁስ አካላዊነት ፍልስፍና በቁስ አካላዊነት ላይ ብቻ ተመስርቶ የፈጣሪን መኖርና አለመኖር ለማጥናት መሞከሩ ትክክል አለመሆኑን፣ በዚህም በቁስ አካላዊነት ላይ ተንጠልጥሎ “ፈጣሪ አምላክ የለም” የሚለው የኤቲዝም ፍልስፍና ተአማኒ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 1.1.2. “የፈጣሪ አለመኖር” በሂውማኒዝም አስተምህሮ

ሂውማኒዝም የ“ፈጣሪ አምላክን አለመኖር” የሚያስረዳው በሌላ መንገድ ነው፣ “ሂውማኒዝም” በመጀመሪያ “ፈጣሪ አለ” ይላል ቀጥሎም “የሰው ልጅ ችሎታውን አልተጠቀመበትም እንጂ የመፍጠር ችሎታ አለው” ይላል፣ በመጨረሻም “የሰው ልጅ ፈጣሪ ነው” ይላል፡፡

በዚህ አስተምህሮ እግዚአብሄር፣ ሰይጣን፣ ገነት፣ ሲኦል … የመሳሰሉ መፅሃፍ ቅዱሳዊ ቃላት ቢኖሩም ትርጉማቸው ግን ከመንፈሳዊው አተረጓጎም የተለየ ነው፣ በሂውማኒዝም አተረጓጎም “እግዚአብሄር ማለት መልካም ሀሳብ ማለት ነው፣ ገነት ማለት ደግሞ በመልካም ሀሳባችን የምንኖረው መልካም ህይወታችን ነው” ሲል “ሰይጣን ማለት ክፉ ሀሳብ ማለት ነው፣ ሲኦል ማለት ደግሞ በዚህ ክፉ ሀሳባችን ምክንያት የምንኖረው መጥፎ ህይወታችን ነው” በማለት ይገልፃል፣ በዚህም “ሰው የአለሙ ፈጣሪ ነው፣ አለሙንም የሚፈጥረው በአስተሳሰቡ ነው” ይላል፡፡

ሂውማኒዝም የሰው ልጅ ራሱን በማክበር፣ በማድነቅ፣ በማሞገስ፣ በማመስገን … ፈጣሪነት ድረስ የሚደርስ የከፍተኛ ችሎታ ያለው መሆኑን ያስተምራል፤ እንደ ሂውማኒዝም አስተምህሮ ይህ ፍልስፍና አዲስ አለመሆኑና ብዙ ስኬታማ ሳይንቲስቶች ስኬት የመጣው በዚህ መንገድ በመጓዛቸው እንደሆነ ይናገራል፡፡

እዚህ ጋር “ሰው ፈጣሪ ነው ወይስ አይደለም” የሚለውን ለመመልከት፣ በመጀመርያ ማስተዋል ያለብን “መፍጠር” የሚለው ቃል ሶስት የተለያየ ደረጃ ትርጉሞች ያሉት መሆኑን ነው፣ በመጀመርያ ደረጃ ያለውን የመፍጠር ትርጉም ተፈጥሮ የተፈጠረበት ትርጉም ነው፣ ሁለተኛው የፈጠራ ትርጉም

ደግሞ ቀድሞ በተፈጥሮ ካለ ነገር ግብአቶችን ወስዶ ሌላ አዲስ ነገር የሚፈጠርበት ለምሳሌ የሳይንቲስቶች ፈጠራ፣ ሶስተኛው የ"መፍጠር" ትርጉም ከላይ የተመለከትነው የሂውማኒዝም ትርጉም ነው፣ ይህም "ሰው መልካም በመስራቱ የሚፈጥረው መልካም ሁኔታና ክፉ በመስራቱ የሚደርስበት ችግር"፡፡

በነዚህ ሶስት "ፈጠራዎች" መካከል ሰፊ ልዩነቶችን እንመለከታለን፣ የሂውማኒዝምን የፈጠራ ትርጉምን ስንመለከት ደግሞ ሰው ህይወቱን ለራሱ መቅረፁን ያሳያል እንጂ እንደ ሁለተኛው ትርጉም "የተፈጠረውን በማገናኘት ሌላ መፍጠር" ወይም እንደ መጀመርያው ትርጉም አይደለም፣ በዚህም ሂውማኒቲ ከሶስተኛው ትርጉም ተነስቶ፣ በሁለተኛው ትርጉም ተደግፎ አንደኛው ትርጉም ጋር ሄዶ "ሌላ ፈጣሪ የለም ፈጣሪ ሰው ነው" ማለቱ ስህተት ነው፡፡

በመቀጠል ደግሞ የሂውማኒዝም አስተምህሮ ምሳሌያቸውን የሚያነሳልን ወደ ፈጣሪነት ያደጉ ሳይንቲስቶችን ዛሬ በህይወት ባናገኛቸውም እንኳን በዚህ ዘመን ላይ ያሉት የዚህ አስተምህሮት ደቀመዛሙርቶች (የመፅሀፍቱ ደራሲዎች፣ ተርጓሚዎች፣ ሰባኪዎች …) እንደሚፈላሰፉት ፍልስፍና የሚኖሩ አለመሆኑና የሚኖሩትም ኑሮ እንደኛው አይነት ተራ ኑሮ መሆኑን ስንመለከት ፍልስፍናው ተራ ፍልስፍና መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 1.2. <u>የኢአምላኪነት የስነፍጥረት ፍልስፍና</u>

ኢአምላካዊው ፍልስፍና "ፈጣሪ የለም" እንደሚለው ሁሉ ፍጥረታት ከየት እንደመጡ የሚያስረዳበት የራሱ የስነ ፍጥረት ፅንሰ ሀሳቦች አሉት፣ ከነዚህ ውስጥ ዋነኞቹ፣ አለማቀፍ ተቀባይነት ያገኙትና በዚህም ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያየ መንገድ እየተደገፉ መጥተው አሁን ያለ ተወዳዳሪ ብቸኛ የስነ ፍጥረት ፅንሰ ሀሳቦች የሆኑት፡-

- የዩኒቨርስ/ፅንፈ አለም/መሬት፣ ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት … አፈጣጠርን የሚያስረዳው - <u>የታላቁ ፍንዳታ ፅንሰ ሀሳብ(Big Bang Theory)</u>
- የህይወታዊው ስነፍጥረት አፈጣጠርን የሚያስረዳው - <u>የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብ (Evolution Theory)</u>

ናቸው፣ ከነዚህ የስነፍጥረት ሀሳቦችም ጋር ለነዚህ የስነፍጥረት ሀሳቦች ጥንካሬ ቀኝ እጅ ሆኖ ያለውን “Age Dating” እንመለከታለን፡፡

### 1.2.1. <u>የታላቁ ፍንዳታ ፅንሰ ሀሳብ (Big Bang Theory)</u>

በዚህ ፅንሰ ሃሳብ መሠረት በከፍተኛ እፍግታ፣ እምቅታና ሙቀት ውስጥ የነበረ ፖይንት ማስ (point mass/point particle/infinitely dense point) [4] “ከ13.8 ቢሊየን አመታት በፊት በገጠመው የፍንዳታና የመለጠጥ ሂደት ይህ ዩኒቨርስ(መሬት፣ ፀሀይ፣ ጨረቃ ...) ተፈጠረ፣ የፍንዳታው አካላትም በአንድ በኩል በፍንዳታው ጉልበት በተቃራኒው ደግሞ በግራቪቲ ጉልበት መካከል ባለው መስተጋብር ዩኒቨርሱ ይህንን መልክ ያዘ” ይላል፡፡

ለዚህ ፅንሰ ሃሳብ መነሻ የሆነው ዩኒቨርሳችን በየጊዜው እየተለጠጠ የመሄድበት እውነታ ሲሆን ይንንም የመለጠጥ ሂደት ወደ ኋላ መልሰን(Replay) አድርገን ስንመለከተው ሁሉም ነገር ወደ አንድ መነሻ ነጥብ የሚሄድ መሆኑ ነው፡፡

ፅንሰ ሃሳቡ ስነፍጥረትን ለማስረዳት ይነሳ እንጂ ሙሉ ሆኖ የስነፍጥረትን መነሻ አይገልፅም፣ “ፖይንት ማስ ከየት መጣ?” ለሚለው ጥያቄ ምንም መልስ የለውም ይባሱኑ ስለዚህች ሰማይና ምድርን ፈጠረች ስለተባለች ፖይንት ማስ መጠነ ቁስ ሲገለፅ [5] አንዳንዶች የዩኒቨርስ መነሻ ዲያሜትር ከፕሮቶን ዲያሜትር አንድ ትሪሊዮንኛ እንደሆነ ሲገልፁ ሌሎች ደግሞ ምንም ቁስ አካል እንዳልነበረ(singularity) ይገልፃሉ፣ አልበርት አንስታየን ደግሞ የዩኒቨርስ ዲያሜትር ዜሮ እንደነበረ ይናገራል፡፡

በርግጥ ይህ ውጤት ከፊል መፅሃፍ ቅዱሳዊ ነው፣ ዕብ.11፡3 “... <u>የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ</u> ...” ከሚለው ቃል ጋር በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላል፣ መፅሀፍ ቅዱሱ “የቁሳዊው ነገር መነሻ ቃል እንጂ ቁስ አይደለም” ሲለን፣ ፅንሰ ሀሳቡም ቁሳዊው ፍጥረት የመጣው ቁሳዊ ካልሆነ ነገር መሆኑን ያሳየናል፣ በዚህም የፍጥረት መነሻን የቁአካላዊነት ሳይንስ ሊያሳየን አይችልም፡፡

---

[4] https://en.m.Wikipedia>wiki>Universe

[5] ሰለሞን ዮሐንስ(2007)፣ **የሳይንስ ኑዛዜ**፣ ገፅ 13

ስለዚህ የሳይንሱ የስነፍጥረት ፍልስፍና መነሻ መሆን የነበረበት እንደ መፅሀፍ ቅዱሱ፣ ቁሳዊ አለም እንዲፈጠር ምክንያት ከሆነው ከቁስ አካላዊነት ውጪ ካለው አካል እንጂ ከውጤቱ ከቁሳዊው አለም መሆን አልነበረበትም፣ በዚህ የታላቁ ፍንዳታ ፅንሰ ሀሳብ (Big Bang Theory) ከመነሻው ያልተነሳ ፍልስፍና በመሆኑ ፅንሰ ሀሳቡ የስነፍጥረትን መነሻ መግለፅ አይችልም፡፡

### 1.2.2. የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብ (Evolution Theory)

ኢአምላኪነት ህይወታዊ ፍጥረታት የተፈጠሩት በዝግመተ ለውጥ እንደሆነ ያስተምራል፣ ይህንን የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው ቻርለስ ዳርዊን በ1859 በታተመው “origion of species” በሚባለው መፅሀፉ ነው፡፡

በፅንሰ ሀሳቡ “በመጀመሪያ በአንድ ኩሬ ውስጥ እንደ አጋጣሚ የተገናኙ ማዕድናት አሚኖ አሲድ ሰሩ፣ አሚኖ አሲዶችም እንደ አጋጣሚ በመሰባሰብ በድንገት ሲንግል ሴል ባክቴሪያን አስገኙ፣ ይህቺ ባክቴሪያ በመራባትዋና በዘሮቿ ላይ በሚሊዮን አመታት ውስጥ በተከሰቱት ዝግመተ ለውጣዊ ሂደቶች ምክንያት አሁን የምንመለከታቸው የተለያዩ ህይወታዊ ፍጥረታት ተገኙ” ይላል፡፡

ነገር ግን ፅንሰ ሀሳቡን በዝርዝር ስንመለከት ሙሉ ያልሆነ፣ አሳማኝነት የጎደለው ይባሱኑ የተሳሳተ ሆኖ እንመለከተዋለን፣ ይህም፡-

- ፅንሰ ሀሳቡ ከመጀመሪያ ያልተነሳ መሆኑ
- የህይወት ጅማሬን መግለፅ አለመቻሉ
- የትውልድን ቀጣይነት መግለፅ አለመቻሉ
- ሽግግራዊ ቅሪቶች ወይንም ፍጥረታት አለመኖር (missing link)
- የፅንሰ ሃሳቡና የሰው ልጅ ተፈጥሮ ተቃራኒ መሆን

ችግሮችን እንመለከትበታለን፣ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፣

## 1. <u>ፅንሰ ሀሳቡ ከመጀመሪያው ያልተነሳ መሆኑ</u>

ፅንሰ ሀሳቡ ቀለል አድርጎ "እንደ አጋጣሚ ማዕድናት ተሰበሰቡ ከዚያ አሚኖ አሲድ ሰሩ፣ አሚኖ አሲዱም ባክቴሪያን አስገኘ" ይበል እንጂ፣ ዛሬ ላይ ሲንግል ሴል ባክቴሪያን ቻርለስ ዳርዊን ከተመለከተበት ማይክሮስኮፕ በረቀቁ ማይክሮስኮፖች ስናጠና የሲንግል ሴል ባክቴሪያ አካል የአሚኖ አሲድ(ፕሮቲን) ስብስብ ብቻ አለመሆኑና በሰውነቷ ውስጥም ከተለያዩ ነገሮች የተሰሩ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች መኖራቸው ነው፣ በዚህም ባክቴሪያን በአሚኖ አሲድ ብቻ የገደበው ፅንሰ ሃሳብ ከመነሻው ስህተት ነው።

በመቀጠል ደግሞ አንድ ሴል ውስጥ ያሉት የተለያዩ የሴል ክፍሎች ዝም ብለው አይሰባሰቡም፣ አሰባሰበቸው የሚመራበት ስርአት ቀድሞ መኖር አለበት። ህይወታዊ ፍጡራን ከመፈጠር አንስቶ እስከማደግ ድረስ ያለው የሰውነታቸው ይዘት(content) እና እድገት የሚመራው በእያንዳንዱ ሴል ውስጥ በሚገኝ ዘረመል (DNA/RNA) በሚባል ማዘዣ ጣብያ ነው። በዚህም የህይወት መጀመሪያ ናት የተባለችው "ሲምፕል ባክቴሪያ" <u>ከመፈጠሯ በፊት "ሲምፕል DNA/RNA" ቀድሞ ሊኖር ይገባል</u>፣ በዚህም መሰረት ይህ ዘረመል የባክቴሪያዋ አካላቶች የሚገነቡበትን ግብአትና ምጣኔ ይመራል።

በዚህም ባክቴሪያን የሚያክል ነገር ሳይፈጠር በፊት የባክቴሪያዋን የሰውነት አፈጣጠር የሚመራ የተፃፈ የDNA/RNA(ዘረመል) የመረጃ ስርአት/ፕሮግራም መኖር አለበት፣ የመረጃ ስርአት ደግሞ ተጨባጭ ቁስ አካል አይደለም ስለዚህ የህይወታዊውም ስነፍጥረት መነሻ ከቁስ አካላዊነት ክልል ውጪ ነው።

በዚህም ስለ የባክቴሪያዋ ህይወት አጀማመር ጥናት መጀመር ያለበት ባክቴሪያዋ እንድትፈጠር ምክንያት ከሆነው የማዘዣ ጣብያ ፕሮግራም እውነታ እንጂ በማዘዣ ጣብያው ሰበብ በተሰባሰበው ቁስ አካል መሆን የለበትም። "ፕሮግራም" ደግሞ የዝግመተ ለውጥ ህግ አይመራም ስለዚህ ይህንን የመረጃ ስርአት የፃፈ ፕሮግራመር በመጀመሪያው መኖር የግድ ይላል።

## 2. የህይወት ጅማሬን መግለፅ አለመቻሉ

ዝግመተ ለውጥ ስለቁሳዊ ነገሮች አመጣጥ በተለያዩ ፅንሰ ሃሳቦችና መላምቶች ያስረዳል ነገር ግን ቁሳዊ ስላልሆነችውና “ህይወት” ስለምትባለዋ ነገር አጀማመር ምንም መናገር አልቻለም፣ ባክቴሪያዋን የሰሩት ቁሶች ዝም ብለው ተሰባሰቡ ብንል እንኳን፣ “ቁስ ያልሆነችው ህይወት በአሚኖ አሲዱ ክምችት ውስጥ እንዴት በቀለች?” ለሚለው ጥያቄ መልስ የለውም፡፡

ዛሬ ባለው ዘመናዊው ላብራቶሪ አሚኖ አሲድንን ማምረት ይቻላል ነገር ግን አሚኖ አሲዱ በተፈለገው መንገድ፣ የተፈለገውን ያህል ይመረት እንጂ መስራት የሚቻለው የአሚኖ አሲድ ክምር እንጂ ከውስጡ ህይወት ብቅ ማድረግ አይቻልም፡፡ ዛሬ ላይ ሳይንስና ቴክኖሎጂው በተራቀቀበት እስከ ሌላ አለማት ድረስ ከፍ ተብሎና እስከ አተምና ፎቶንስ ደረጃ ተወርዶ ምርምር በሚደረግበት ዘመን፣ በናኖ ቴክኖሎጂ በአተምና ሞሌኪውል ላይ ለውጥ በማድረግ በአእምሮ የማይታሰቡ ነገሮች እየተሰሩ ባሉበት ዘመን፣ በተፈጥሮ ያልነበሩትን ኢለመንቶች እስከመፍጠር በተደረሰበት ዘመን፣ የብዙ ዘመናት የኬሚካል ሂደትን በአጭር ጊዜ የሚቋጩ ካታሊስቶች ተፈብርከው በሚገኙበት ዘመን፣ እጅግ ግዙፍና ስልጡን ላብራቶሪዎች ባሉበት ዘመን፣ በላብራቶሪ አሚኖ አሲድ ማምረት እየተቻለ በውስጡ ግን ህይወትን ማብቀል አልተቻለም፣ ህይወታዊ ሲንግል ሴል ይቅርና እስዋን ልትመስል የፈለገች ነገር፣ ቢያንስ እንኳን ወደ ህይወትነት እየሄደ ያለን ነገር (ከፊል ህይወትን) በሙከራ ሊያሳየን አልቻለም፡፡

በዚህም ፅንሰ ሃሳቡ የህይወትን ጅማሮ ላይ ምንም ማለት አልቻለም፣ ይህንን መሠረታዊ እውነታ የተወ የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብ ደግሞ ምናባዊ ጉዞ ብቻ ነው፡፡

## 3. የትውልድን ቀጣይነት መግለፅ አለመቻሉ

የስነፍጥረት ሳይንሱ የመጀመሪያው ህይወት አበቃቀል ላይ ዝም ቢልም፣ ይህ ብቻውን የነበረ ህይወት(ባክቴሪያ) ከተፈጠረ በኋላ ደግሞ እንዴት ሌሎችን ማምጣት ቻለ? የሚለው ደግሞ ሌላ ቀጣይ ግራ አጋቢ ነገር ነው፣ ይህቺ ሲንግል ሴል ባክቴሪያ ምግብና መጠጥም በተሟላበት፣ መመገብም እንዳለባት በምታውቅበት፣ ለመመገብም አቅም ባላትና ምንም አደጋ

በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ብትኖር እንኳን መሰሎችዋን ካላመጣች ሞታ በዚያው በመቅረት የኢቮሉሽን ፅንሰ ሀሳብን ውድቅ ታደርጋለች፡፡

እዚህ ጋር ሌሎች ባክቴሪያዎች "ቢመጡ" ብላ ብትመኝ እንኳን ሌሎቹ የሚመጡት እስዋ በመጣችበት መንገድ እንደሆነ እንጂ እንደ ዛሬዎቹ ባክቴሪያዎች የማዮሲስ/ማይቶሲስን ሂደት እንደሚመጡ አታውቅም፣ ድንገት እንኳን አንድ ነገር ወድቆባት ለሁለት ቢከፍላት እንደ ማዮሲሰ/ማይቶሲሱ ህጉ ሁለት ባክቴሪያ መሆን አትችልም ምክንያቱም ለሁለት መከፈሉ የሴል ዲቪዥን ስርአት ጠብቆ የመጣ ባለመሆኑ ያላት ዕድል መሞት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የባክቴሪያ ዕድሜ(life span) አጭር መሆኑ የባክቴሪያዋ ህይወት በሚሊዮኖች ከሚያስበው የኢቮሉሽን አቆጣጠር ጋር አትገጣጠምም፣ ለባክቴሪያ "ህይወት መጣችና ሄደች" ቅፅበታዊ ነገር ነው፡፡

በዚህም ፅንሰ ሀሳቡ የአንድ ባክቴሪያ ህይወት ይዞ ድርሰቱን ይጀምር እንጂ ህይወት ከዚህች ባክቴሪያ ወደ ሌሎች ቀጣይ ባክቴሪያዎች መተላለፍ የቻለበትን መንገድ መግለፅ አለመቻሉ የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሃሳብ ውድቅ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 4. <u>ሽግግራዊ ቅሪቶች ወይንም ፍጥረታት አለመኖር (missing link)</u>

የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብ ጀማሪው ዳርዊን ሲናገር "የዝግመተ ለውጥ ህግ ትክክለኛ የሚሆነው የሽግግር ፍጥረታት ሲገኙ ነው" ይላል፣ ይህን በምሳሌ ብንመልከት፣ በዝግመተ ለውጥ ሂደት የውሃ እንስሳት ወደ ምድራዊው እንስሳት የመለወጥ ሂደት ውስጥ በውሃም በምድርም መኖር የሚችል "የሽግግር" እንስሳ/ቅሪት መኖር አለበት ይላል፣ መሬት ላይ በሳንባው እየተነፈሰ ውሃ ውስጥ ሲገባ ደግሞ በጊሉ "gills" የሚተነፍስ ወይ በሰማይ እንደልቡ ሲበር ውሎ ውሃ ውስጥ ገብቶ የሚተኛን ፍጥረት እንደማለት ነው፣ ይህ ደግሞ በውኑም በቅሪትም የለም፡፡

ይባሱኑ ደግሞ ዳርዊን "የሽግግራዊ ፍጥረታት ቅሪተ አካላት ከሌሎቹ ፍጥረታት በብዛት መብለጥ አለበት" ይላል ምክንያቱም የሽግግር ፍጥረታት በሁለቱም ቦታዎች/ሁኔታዎች ላይ መኖር ስለሚችሉ፣ እውነታው ግን በተቃራኒው ነው፣ እነዚህን ሽግግራዊ ቅሪቶች በጥቂትም ማግኘት

አልተቻለም፣ ይህ ደግሞ የዳርዊንን የስነ ፍጥረት ፍልስፍናን ፅንሰ ሃሳብ የሚያፈርስ ነው፡፡

"የሽግግር ፍጥረታት" የተባለው እውነት ቢሆን ኖሮ በቅሪት መጥፋት ይቅርና በውኑም በኖሩ ነበረ ምክንያቱም በሁለት ቢላዋ የሚበሉ፣ ደብል አድቫንቴጅ ያላቸው በመሆኑ ራሳቸው መጥፋትና ወደ ሌላ መለወጥ ይቅርና ከናቹራል ሰሌክሽን(ለተፈጥሮ ምቹ የሆነ የሚኖርበት ህግ) በተቃራኒ ባሁኑ ጊዜ ሌሎቹን ፍጥረታት አሸንፈው በኖሩ ነበረ፡፡

በዚህ የሽግግራዊ ፍጥረታት አለመኖር "missing link" የዳርዊን ቲዎሪ ባዶ ሲሆን እንመለከታለን፡፡

## 5. <u>የፅንሰ ሃሳቡና የሰው ልጅ ተፈጥሮ ተቃራኒ መሆን</u>

የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብ ፍጥረታት ለምን እንደሚለያዩ የሚተነትኑበት ሌሎች ደጋፊ ፅንሰ ሃሳቦች አሏቸው፣ ይህም በ"Natural selection"(ለተፈጥሮ ምቹ የሆነ ብቻ መኖር)፣ "Adaptation"(ራስን ከተፈጥሮ ለውጥ ጋር ማመሳሰል)፣ "Mutation"(ከተፈጥሮ ለውጥ ጋር አብሮ መለወጥ) ሲሆኑ እነዚህ ፅንሰ ሀሳቦችም በህይወታዊ ፍጥረታቱ መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራሉ፡፡

ነገር ግን እነዚህን ፅንሰ ሀሳቦች የሰው ልጅ ያለበትን "የአኒማል ኪንግደም" ጋር አምጥተን ስንመለከት፣ የሰው ልጅ ስነተፈጥሮ በአኒማል ኪንግደም ውስጥ ካሉት እንስሳት የተለየ በመሆኑ የሰው ልጅ ስነ ተፈጥሮ ደጋፊ ፅንሰ ሀሳቦቹን ሲያፈርስ እናገኘዋለን፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- የሰው ልጅ ካለበት የአኒማል ኪንግደም ፍጥረታት በተለየ ሰውነቱ በላባ፣ በፀጉር ወይ በእስኬል(ሽካራ ቅርፊት) የተሸፈነ አይደለም፣ ጅራትም የለውም፣ የሰው ዘር እነዚህን አካላት ያላበቀለው ወይንም አብቅሎ የተወው፣ ለየትኛው የዝግመተ ለውጣዊ ጥቅም እንደሆነ ባይነገርም፣ የሰው ዘር ግን በዱር ሲኖር እንደነበረው እነዚህ የአካል መሸፈኛዎች ከቁር፣ ከትንኞች ንክሻ … የሚከላከሉ በመሆናቸው አብቅሎ መተው ይቅርና ባያበቅል እንኳን ሊያበቅል የሚገባ አካላት ነበሩ፡፡

በዚህ ላይ ደግሞ የሰው ልጅ ከሁሉም እንስሳት በተለየ አንድ ራሱን የሚከላከልበት፣ የሚያጠቃበት፣ የሚያመልጥበት … የተለየ አካል የለውም፣ እንደ እባብ መናደፊያ፣ እንደ አንበሳ አደገኛ ጥርስ፣ እንደ ጅብ ጉልበት፣ እንደ ነብር አደገኛ ጥፍር፣ እንደ ሚዳቋ የሩጫ ክህሎትን፣ እንደ ዝንጀሮ ከዛፍ ዛፍ ዘሎ የሚያመልጥበትን ክህሎት፣ እንደ አሞራ ወደ ሰማይ የሚነሳበትን አካላት የሉትም፡፡

የሰው ልጅ ስነተፈጥሮ እንደሌሎቹ ህይወታዊው ፍጡራን በ"Natural selection" (ለተፈጥሮ ምቹ የሆነ ብቻ ይኖራል) ህግ የሚመራ ቢሆን ኖሮ ከሌሎቹ እንስሳት በተለየ እነዚህን አካላትና ክህሎቶች በማጣቱ ምክንያት በእንስሳቱ መካከል ተወዳዳሪ ሆኖ መኖር የማይችልና ከምድር ገፅ የሚጠፋ ፍጡር በሆነ ነበረ፡፡

ነገር ግን ይህ አለመሆኑ የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ጋር በአንድ የተፈጥሮ ሂደት ውስጥ አለመምጣቱንና አለመኖሩን ያሳያል፡፡

- እንስሳቱ በሙሉ የሚያስቡበት አዕምሮ ቢኖራቸውም የሰው ልጅ አዕምሮ ግን ከእንስሳቱ አዕምሮ የተለየ ነው፣ በአዕምሮ ስነፍጥረት ለሰው ልጅ ትንሽም ቢሆን ተቀራራቢነት ያለው እንስሳ የለም፣ የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ጋር በዝግመተ ለውጡ ሂደት ውስጥ በነበረ ኖሮ በዝግመተ ለውጡ "ለሰው ልጅ የቅርብ ናቸው" የተባሉት ቺምፓንዚዎች አዕምሮ ላይ ከሰው አዕምሮ በጥቂቱ አነስ ያለ አዕምሮ እንኳን በተመለከትን ነበረ፣ በዚህም የሰው ልጅ ዘመናዊ መኖርያ ቤቶችን፣ አውሮፕላንና መንኮራኩሮችን ሲሰራ እነሱ ቢያንስ ዳስ የመሰለ ነገር ወይ በእጅ የሚገፋ ጋሪ ወይ እንደ የጥንቱ የሰው ልጅ የጋርዮሽ አሰራር ሌሎችን እንስሳት ሲያላምዱ መታየት ነበረበት፣ ነገር ግን ይህ አልሆነም፣ እነሱም እንደ እንስሳቱ ከመብላትና መራባት በላይ ማሰብ አይችሉም፡፡

ይህ የሰው ልጅ ፍፁም ልዩነት የሚሳየው የሰው ልጅ ስነፍጥረት በእንስሳቱ የስነፍጥረት መንገድ አለመምጣቱን ነው፡፡

እነዚህ የሰው ልጅ ስነተፈጥሮ ከዝግመተ ለውጥ ህጎች ጋር አለመተዋወቅና መቃረን፣ የሰውን ልጅ እንደ እንስሳቱ በዝግመተ ለውጥ ሂደት አለፈጠሩን ያሳያል፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱና ዝግመተ ለውጥ ስለ ስነተፈጥሮ በሚሰጡት ትንታኔ አንድ የሚሆኑባቸው ቦታዎች አሉ፣ ለምሳሌ ዝግመተ ለውጡ እንደሚለው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይም፣ በውሀ ውስጥ የሚኖሩት፣ በአየር ላይ የሚበሩትና ምድራዊ እንስሳትን እግዚአብሄር በቀጥታ አልፈጠራቸውም፣ ሌሎች ፍጡራን እንዲፈጥሩአቸው አዘዘ፣

- ዘፍ.1፡20-ውሃ በውሃ ውስጥና በአየር ላይ የሚበሩትን እንድታስገኝ አዘዘ
- ዘፍ.1፡24 - ምድርም የምድር እንስሳትን እንድታወጣ አዘዘ

በዚህም ከሰው ውጪ ባሉት ህይወታዊ ፍጥረታት አፈጣጠር ላይ የዝግመተ ለውጥና የመፅሀፍ ቅዱሱ ትንታኔ በተወሰነ መጠን ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡

ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ጋር በአካላዊ ማንነቱና በአስተሳሰቡ ፍፁም ልዩ መሆኑና በዚህም ከእንስሳቱ ጋር አብሮ የሚኖር ሳይሆን ራሱን ከእንስሳቱ ለየት አድርጎ እንስሳቱ ላይ ገዢ ሆኖ መገኘቱ፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ደግሞ ሰዎች የተፈጠሩት እንስሳት በተፈጠሩበት መንገድ ሳይሆን በሌላ መንገድ መሆኑና የሰው ልጅም የተፈጠረው ሌሎቹን ፍጥረታት እንዲገዛ እንደሆነ መናገሩ፣ የሰው ልጅ ስነፍጥረትን በአግባቡ የተገፀው በዝግመተ ለውጡ ሳይሆን በመፅሀፍ ቅዱሱ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም የሰው ልጅ ተፈጥሮን በዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና መተንተን የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብን ባዶነት የሚያሳይና የመፅሀፍ ቅዱሱን ቃል የሚያጠናክር እውነታ ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሀሳብ ከመጀመሪያ ያልተነሳ መሆኑ፣ የህይወት ጅማሬን መግለፅ የማይችል መሆኑ፣ የትውልድን ቀጣይነት መግለፅ የማይችል መሆኑ፣ "በብዛት መገኘት አለባቸው" የተባሉት ሽግግራዊ ቅሪቶች ፈፅሞውኑ አለመኖርና ፅንሰ ሃሳቡና የሰው ልጅ ተፈጥሮ ተቃራኒ መሆኑን ስንመለከት ፅንሰ ሀሳቡ ህይወታዊውን ስነፍጥረት መግለፅ የማይችል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 1.2.3. የኢአምላካውያን የስነ ፍጥረት ፅንሰ ሀሳቦች ቀኝ እጅ - (Age Dating)

የስነ ፍጥረት ሳይንሱ ከላይ የተመለከትነውን የዝግመተ ለውጥንና የታላቁን ፍንዳታ የስነፍጥረት ፅንሰ ሀሳቦችን በጊዜ ቀመር አስደግፎ ይናገራል፣ ይህንንም የሚሰራው ኤጅ ዴቲንግ(Age Dating) በሚባለው ቴክኒክ ነው፣ ቴክኒኩም የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎችን የሚጠቀም ሲሆን ታዋቂዎቹ ዩራኒም - ሊድ፣ ዩራኒየም - ቶሪየም፣ ፖታሲየም - አርጎን፣ ሳማሪየም - ኒዮዲየም፣ ሩቡዲየም - ስትሮንቲየም፣ ፖታሲየም - ካልሲየም፣ ራዲዮ ካረበን [6](C-14 Dating) ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉት ዩራኒም - ሊድና ፖታሲየም - አርጎን ቴክኒኮች ሲሆኑ እድሜያቸው በጥቂት ሺዎች ለሚገመቱት ኦርጋኒክ ማቴሪያሎች ደግሞ C-14 ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

የኤጅ ዴቲንግ የአሰራር ቴክኒክ በመሠረተ ሀሳብ ደረጃ ግልፅና ትክክለኛ አሰራር ነው ነገር ግን ቴክኒኩን ባዶ የሚያደርገው በተፈጥሮ ውስጥ ያለው እውነታ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉም ነገር የተገነባው በንጥረ ነገሮች(elements) ነው፣ ከርጉዕነት አንፃር ኢለመንቶች ደግሞ በሁለት ይከፈላሉ የረጉ-ኢለመንቶች(stable elements) እና ያልረጉ-ኢለመንቶች(Radio active elements) ይባላሉ፣ የረጉ ኢለመንቶች በውስጣቸው ባለው ቻርጅ ባላንስ ምክንያት ባሉበት ሁኔታ ረግተው መቀመጥ የሚችሉ ኢለመንቶች ናቸው፣ ያልረጉ(ራዲአ አክቲቭ ኢለመንቶች) ደግሞ በውስጣቸው ያለው ቻርጅ ባላንስ ባለመሆኑ በጊዜ ሂደት እየተሰባበሩ ራሳቸውን ወደ ረጉ ልጅ ኢለመንቶች ይቀይራሉ፡፡

የኤጅ ዴቲንግ ቴክኒክ የሚጠቀመው ይኸው ያልረጉ ኢለመንቶች ወደ ረጉ ኢለመንቶች የመሰባበር ሂደትን ነው፡፡ ለምሳሌ ለአቶሚክ ቦንብ ስራ የሚውለው ዩራኒየም ያልረጋ ኢለመንት በመሆኑ በጊዜ ሂደት ርጉ ወደ ሆኑት ወደ ሊድና ቶሪየም ይሰባበራል፣ በዚህም ዩራኒየሙ ያልረጋ/ወላጅ

[6] ካርበን በተፈጥሮ በC-12 መልክ የሚገኝ ሲሆን C-14 የሚባለው በጨረር ምክንያት በጥቂት መጠን በአየር ውስጥ የሚፈጠር ርጉ ያልሆነው(Radio active) ኢለመንት ነው፡፡

ኢለመንት(ራዲኦ አክቲቭ ኢለመንት) ሲባል ሊድና ቶሪየም ደግሞ የረጋ(ልጅ) ኢለመንት ይባላል፡፡

ወላጅ ኢለመንት ወደ ልጅ ኢለመንቶች የሚሰባበረው በጊዜ ሂደት ነው፣ አንድ በተወሰነ ክምችት የሚገኝ ራዲኦ አክቲቭ ኢለመንት ግማሹ የሚሰባበርበት ጊዜ "half life" ይባላል፣ ለኤጅ ዴቲንግ ዋና መሳሪያ የሆነውም ይኸው የራዲኦ አክቲቭ ኢለመንቶች "ሃፍ ላየፍ" ነው፣ ለምሳሌ አንድ ቅሪተ አካል ወስደን፣ ለምሳሌ በዩራኒም ሊድ ዘዴ ብንመረምረው በውስጡ ከፍርሰት የቀረው ዩራኒየምና በዩራኒየም ፍርሰት የተገኘው የሊድ መጠን ይሰላና ከዩራኒየም ሃፍ ላየፍ ጋር ተነፃፅሮ "ዕድሜው ይህን ያህል ነው" ይባላል፡፡

ይህ በቲዎሪ ደረጃ ቀላል ነገር ቢሆንም ወደ አተገባበር ስንሄድ ግን ቴክኒኩ ብዙ እውነታዎችን ይጥሳል፡፡

ከመነሻው ስንመለከት አሁን እየተፈጠሩ ካሉት C-14 በስተቀረ ሁሉም ራዲኦ አክቲቭ ኢለመንቶች የተፈጠሩት በፍጥረት ቀን ነው፣ በዚህም እነዚህን ኢለመንቶች የሚጠቀሙት ቴክኒኮች በሙሉ ማሳየት ያለባቸው የዕድሜ ልኬት የፍጥረትን ቀንን ብቻ መሆን አለበት፣ በዚህም C-14 ከሚጠቀመው ቴክኒክ ውጪ ያሉት ቴክኒኮች በሙሉ እየሰጡት ያለው የተለያየ ልኬት ስህተት ነው፡፡

በመቀጠል ያለው ሁለተኛ መሠረታዊ ስህተት ቴክኒኩ የሚጠቀመው ተፈጥሮአዊ ያልሆኑ ቅድመ ግምቶች ነው፣ እነዚህን ቅድመ ግምቶች ብንመለከት፡-

1. ቴክኒኩ የተመሰረተው የወላጅና የልጅ ኢለመንቶችን ብዛት በማነፃፀር ነው ነገር ግን በቅሪተ አካሉ/ድንጋዩ ውስጥ ከመነሻው በተፈጥሮ የነበረው የልጅ ኢለመንት መጠን አይታወቅም በዚህም ቴክኒኩ "ልጅ ኢለመንትን ዜሮ ነበረ" ብሎ ቅድመ ግምት ይወስዳል፣ ይህ ደግሞ ትልቅ ስህተት ነው፡፡

   ለምሳሌ ከላይ ባየነው የራኒየም-ሊድ ቴክኒክ ውስጥ የሊድ ኢለመንት በተፈጥሮ በመጀመሪያ በተወሰነ መጠነ ቁስ በቅሪተ አካሉ/ድንጋዩ ውስጥ ይገኛል ነገር ግን ይህ መጠን ተለይቶ የሚታወቅበት መንገድ

ባለመኖሩ ምክንያት በመጀመሪያ የነበረው የሊድ ኢለመንት ብዛት “ዜሮ ነበረ” ብሎ መነሳት በንፅፅሩ ላይ ራሱን የቻለ መዛባትን ይፈጥራል፡፡

2. ናሙናው “እድሜ ልኩን ከምንም ንክኪ ነፃ ነበረ፣ ምንም ወላጅ ሆነ ልጅ ኢለመንት ከውጪ ወደ ውስጥ አልገባምም ከውስጥ ወደ ውጭ አልወጣም” ማለቱ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ስህተትን ይፈጥራል፣ እንደዚህ አይነት ዝግ ስርአት ላብራቶሪ ውስጥ እንጂ በተፈጥሮ አናገኘውም፣ ምድር በሂደት ውስጥ ናት እሳተ ገሞራ፣ የመሬት የቀለጠው ክፍል መጠጠር በተቃራኒው ጠጣሩ ክፍል መቅለጥ፣ የከርሰ ምድር ውስጥ የውሃ እንቅስቃሴ … ብዙ ተፈጥሯዊ ሂደቶች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ “አልተነካካም” ማለቱ ስህተት ነው፡፡

   ስህተቱ ደግሞ የሚጎላው ወደ ፈሳሽነትና ጋዝነት የሚለወጡት ልጅ ኢለመንቶች “ከምንም እንቅስቃሴ ታቅበው ነበሩ” የሚለው ላይ ነው፣ ለምሳሌ ጋዝ የሆነውን አርጎን የሚጠቀመው የፖታሲየም-አርጎን ዘዴን መመልከት ይቻላል፡፡

3. ቴክኒኩ ለጥናቱ የሚፈልጋቸው ቅሪተ አካላት፣ ድንጋይ … የሚያገኘው በብዙ ቁፋሮና ፍለጋ ነው፣ በዚህም ያልተገኙ፣ ያልተደረሰበትና ሊደረስበት የማይቻልና የጠፉ እውነታዎች በሙሉ እንደሌሉ ይታሰባሉ፣ ይህ ደግሞ ስህተት ነው፡፡

   ለምሳሌ አርዲ ሳትገኝ በፊት “ሉሲ የመጀመሪያዋ የሰው ልጅ” ስትባል ነበረ፣ ሉሲ ስትገኝ አርዲ እንደሌለች ይታሰብ ነበረ፣ አሁንም ቢሆን መቼም አርዲ ደግሞ ብቻዋን ዱብ አላለችም ከስዋ በፊት የነበሩት ሰዎች ቅሪተ አፅም ሲገኝ ደግሞ አባባሉ ይቀየራል፡፡

በዚህም የኤጅ ዴቲንግ ቴክኒክ እነዚህን በተፈጥሮ ሊሟሉ የማይችሉ ቅድመ ግምቶች ይዞ በመነሳት የሚሰጣቸው ድምዳሜዎች ትክክለኛ እንዳልሆኑ እንመለከታለን፣ በዚህም በቴክኒኩ ብዙ ሊታገሱት የማይቻል የውጤት ስህተቶች መመልከቱ የተለመደ ነገር ነው፡፡ አብዛኞቹ ዛሬ ከብዙ ቅንብሮች በኋላ የሚነገሩት ውጤቶች ብዙ የኤዲቲንግ ስራዎች ከተሰሩባቸው በኋላ ነው ነገር ግን ለኤዲቲንግ ያልተመቹትን የዚህን ቴክኒክ ውርደቶች ብንመልከት፡-

- <u>በአንድ አለት ውስጥ ያሉ የተለያዩ ማዕድናት የተለያየ ዕድሜ ማሳየታቸው</u>

[7] "በአሜሪካ ውስጥ፣ ሴንት ሄለንስ በሚባል የላቫ ተራራ ላይ የተወሰዱ የተለያዩ ናሙናዎች በፖታሲየም - አርጎን ዘዴ እድሜያቸው ተሰርቶ ነበር፣ በዚህም ከአለቱ የተወሰደው ናሙና 350,000 አመታት አሳየ፣ አለቱ ውስጥ ባሉ ሆርንብሌንድ ማዕድኖች ላይ የተወሰደው ናሙና 900,000 አመታት አሳየ፣ አሁንም ከፓይሮክሲን ማዕድኖች የተወሰደው ናሙና 2,800,000 አመታት አሳየ፣ የሚያሳዝነው ደግሞ አንዳቸውም ትክክለኛ አልነበሩም ምክንያቱም ናሙናሙ የተወሰደበት ላቫ የፈሰሰው በ1980 ሲሆን በወቅቱ ዕድሜው ገና 10 አመታት ብቻ ነበር፡፡"

- <u>አንድን ናሙና በተለያዩ የኤጅ ዴቲንግ ዘዴዎች ሲመረመሩ የተለያዩ ውጤቶች ማሳየታቸው</u>

[8]"በ1954 ዓ.ም ከናጉዋሩ ተራራ ላቫ ፍሰት የቀዘቀዘ ዓለት በRb-Sr isochron ዘዴ ዕድሜው ተሰርቶ 133 ሚሊየን አመታት አሳየ፣ በ Sm-Nd isochron ዘዴ 197 ሚሊየን አመታት አሳየ፣ በPb-Pb ዘዴ 3.908 ቢሊየን አመታት አሳየ፣ በዚህም ለዚህ ላቭ የተለያዩ እድሜዎች ተለካለት፣ የሚያሳዝነው ግን አንዳቸውም ትክክለኛ አልነበሩም ዓለቱ ከፈነዳ ገና 50 ዓመቱ ብቻ ነበረ፡፡"

- <u>ታላቅ ነው የተባለው ታናሽ ሆኖ መገኘቱ</u>

በሀገራችን በአፋር ክልል ሀዳር በተባለው ቦታ የተገኘችው ሉሲ(ድንቅነሽ) ዕድሜዋ 3.5 ሚሊየን አመታት አሳየ፣ በዚሁ ክልል አራሚስ በተባለው ስፍራ የተገኘችው አርዲ ዕድሜ 4.4 ሚሊየን አመታት አሳየ፣ በዚህም አርዲ ሉሲን በ1ሚሊየን አመታት ገደማ ትበልጣታለች፣ በዚህም መሠረት የታናሸየዋ የሉሲ የሰውነት አቋም ከአርዲ በላይ ለሰው ልጆች መቅረብ ነበረበት ነገር ግን የሆነው የዚህ ተቃራኒ ነው፣ የሉሲ "ታላቅ" የተባለችው አርዲ ከሉሲ በበለጠ ለሰው ልጆች የቀረበ የአካል ገፅታ አላት፣ በዚህም እነዚህ ቅሪቶች የሰው ዘሮች ቢሆኑ እንኳን የእድሜ ስሌቱ የተሳሳተ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

---

[7]https://creation.com/learning the lessons of mount st. Helens

[8] ዘለቀ በሃይሉ (2008)፣ **ሳይንስና ኢቮሉሽን**፣ ክፍል አንድ፣ ገፅ 154

- <u>በህይወት ያለን ፍጡር ኤጅ ዴቲንግ ከሺ አመታት በፊት ሞተ ማለቱ</u>

[9]"በህይወት ያለ የቀንድ አውጣ ሼል በ C14 እድሜው ተለክቶ ውጤቱ ከ27,000 ዓመታት በፊት ይኖር እንደነበረ አሳየ፣ (Science, Vol.224 1984 pg. 58-61)"

በዚህም የስነፍጥረታዊ ፅንሰ ሃሳቦች የጀርባ አጥንት የሆነው ኤጅ ዴቲንግ ምን ያህል በስህተት ተነስቶ፣ በስህተት አስልቶ የስህተት ድምዳሜ እየሰጠ እንዳለ ነው፡፡ በዚህም የስነፍጥረት ሳይንሱ በኤጅ ዴቲንግ የሚሊየንና የቢሊየን አመታት ልኬት ላይ ተመርኩዞ እሰጠ ያለው የስነ ፍጥረት ትንታኔዎች በሙሉ ስህተት መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ኢአምላካውያን/ኢአማንያን "ፍጥረታት የተፈጠሩት በተፈጥሮ ሂደት ነው" በማለት ያስቀመጡት የዝግመተ ለውጥና የታላቁ ፍንዳታ የስነ ተፈጥሮ ፅንሰ ሀሳቦች እንዲሁም ቀኝ እጃቸው ሆኖ ፅንሰ ሀሳቦቹን በመደገፍ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን በእድሜ የሚያሰላላቸው "ኤጅ ዴቲንግ" የፍጥረትን አጀማመር መግለፅ የማይችሉ ፅንሰ ሀሳቦች መሆናቸውንና ፍጥረታትም የመጡት እነሱ በሚሉት "በተፈጥሮ ሂደት" አለሆኑን እንመለከታለን፡፡

## 1.3. <u>የስነፍጥረት ሳይንሱ የፈጣሪን ሀለዎት የማጥናት አቅም</u>

ከላይ እንደቀረበው "ፍጥረታት በተፈጥሮ ሂደት ተፈጠሩ" የሚባለው ነገር ስህተት መሆኑን ተመልክተናል፣ ፍጥረታት በተፈጥሮ ሂደት ካልተፈጠሩ ደግሞ ፍጥረታቱ የተፈጠሩት በሌላ መንገድ እንደሆነ ግልፅ ነው፣ አምላካውያን ፍጥረታት የተፈጠሩት "በፈጣሪ አምላክ" እንደሆነ ሲናገሩ ኢአምላካውያን ደግሞ "ፈጣሪ አምላክ" የሚባል አካል እንደሌለ ይናገራሉ፡፡

ይህንን ልዩነት ለማስታረቅ ገለልተኛ በሆነ መንገድ ከመሄዳችን በፊት የስነፍጥረት ሳይንሱ የፈጣሪን ሀለዎት የማጥናት አቅም በቅድሚያ እንመለከታለን፡፡

የስነ ፍጥረት ሳይንሱ ፈጣሪን የማጥናት አቅም ስንመለከት ከመነሻው ሁለት መሠረታዊ ክፍተቶችን እንመለከትበታለን፣ ይህም፡-

[9] ibid ገፅ 206

- የማንነት ልዩነትን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑ፣
- ሁሉም ነገር ባልተጠናበት ሁኔታ ውስጥ የተሰጠ የቸኮለ ድምዳሜ መሆኑን፣

ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 1.3.1. የማንነት ልዩነትን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑ

ፈጣሪ ካለ ፍጡራንን ሊፈጥር የቻለው ከፍጡራኑ በላይ ባለው ማንነት ነው፣ በዚህም ከመነሻው ፍጡር የሆነው ሰው ባለበት የማንነት ልዩነት ምክንያት የፈጣሪውን ህለዎት መመርመር አይችልም፣ “ልመርምር” ቢል እንኳን ምርምሩ ፈጣሪው ጋር ሊደርስ አይችልም፡፡

መንፈሳዊውን አለም ትተን ተፈጣሪ የሆነውን ዩኒቨርስ ስንመለከት ዋንኛ ይዘቶቹ ቁስ፣ ኢነርጂ፣ ሞገድ፣ ህይወት ... የመሳሰሉ ናቸው፣ እነዚህን የፈጠረ ፈጣሪ ካለ የዚህ ፈጣሪ ማንነት ከነዚህ ነገሮች ማንነት ውጪ ነው፣ ለምሳሌ ጀበና ጀበናን አይሰራውም፣ ጀበናን መስራት የሚችለው ከጀበና በላይ የሆነ ማንነት ያለው አካል መሆን አለበት፣ ስለዚህ ፈጣሪ ካለ ይህን ፈጣሪ በምርምር ማጥናት የሚቻለው ምርምሩ ከነዚህ ተፈጣሪ ነገሮች ውጪ ባሉት ነገሮች ላይ ማድረግ ሲቻል ነው፣ የሰው ልጅ ደግሞ እዚህ ድረስ ብቃት ስለሌለው በፈጣሪ ላይ የሚደረገው ጥናትም ሆነ ፍልስፍና በሙሉ ፈጣሪ ጋር መድረስ ስለማይችሉ ውጤቱ “ፈጣሪ የለም” ይሆናል፡፡

ይባሱኑ ደግሞ አማልክታውያን የአምላክን ማንነት የሚገልፁበትን መንገድ ስንመለከት ሰው ፈጣሪን ፈፅሞውኑ ማጥናት አይችልም፣ ፈጣሪን ይቅርና <u>መንፈሳዊ ፍጡራን</u> የሆኑቱ መላዕክቱ እንኳን ሰው ሊያጠናቸው አይችልም፣ ይህም በዋናነት የእነሱ ማንነት የተሰራው ከቁሳዊ ማንነት ባለመሆኑ ነው፣ ለምሳሌ አንድ መልአክ ብቻውን 180,000 ሰዎችን በአንድ ጊዜ የመግደል አቅሙን(2ነገ.19፡35)፣ በሰው ልጅ የማይታሰበውን ከ6-27 ሚሊየን $^{0}$C የሚያቃጥል የፀሀይ አካል ውስጥ መቆምን(ራዕ.19፡17-18)፣ ከመሬት ስበት ነፃ ሆኖ መንቀሳቀስን(መሳ.13፡20) ... ስንመለከት ዋናው ፈጣሪ ይቅርና ሁለቱ ቁሳዊና መንፈሳዊ ተፈጣሪዎች መካከል ያለው ልዩነት በራሱ ተነፃፃሪ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም ፈጣሪ ካለ ተፈጣሪው ያውም ቁሳዊው ፍጥረት ሊገልጠው አቅም የለውም፤ እነዚህ ሁሉ ክፍተቶች እያሉ ደግሞ ተፈጣሪው "ፈጣሪን እመረምራለሁ" ካለ ውጤቱ አሁን የምንመለከተው "ፈጣሪ የለም" ይሆናል፡፡

### 1.3.2. ሁሉም ነገር ባልተጠናበት ሁኔታ ውስጥ የተሰጠ የቸኮለ ድምዳሜ መሆኑ

ከላይ የተመለከትናቸው የማንነት ልዩነት እንዳለ ሆኖ በነዚህ ውሱንነቶች ውስጥ የተሰሩት ጥናቶች ስንመለከት፤ የሰው ልጅ ያጠናው ካላጠናው ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ነው፤ ይህች ምድር አለች፤ ቀጥሎ ምድር ያለችበት ሶላር ሲስተም አለ፤ ሶላር ሲስተማችን የሚገኝበት ሚልክዌይ ጋላክሲ አለ፤ ጋለክሲው ደግሞ በዩኒቨርስ ውስጥ ይገኛል፡፡

"ፈጣሪ የለም" የሚለውን ድምዳሜ የሰጡት አካላት "ምድርን ሙሉ በሙሉ ያውቋታል" ብንል እንኳን፤ የሶላር ሲስተማችን ጥናት ያለው ገና በልጅነት ላይ ነው፤ ሚልክዌይና ዩኒቨርሱ ደግሞ "አልተነኩም" ማለት ይቻላል፤ ምድር በሶላር ሲስተሙ ውስጥ ያላት ድርሻ ከ1% በታች ነው፤ ይህንን በሶላር ሲስተሙ ከፍ ብሎም በሚልክ ዌይ፤ ከዚያም በዩኒቨርስ ውስጥ ያለው ድርሻ ስንመለከት ኢምንት ነው፤ በዚህም ሳይንሱ ያጠናውና ያላጠናው ሊወዳደር የማይቻል ነገር ነው፤ በዚህ ኢምንት ጥናት ውስጥ "ፈጣሪ የለም" የሚለው ድምዳሜ የቸኮለ ድምዳሜ ነው፡፡

ለምሳሌ አንድን ሰው ቤት ውስጥ ፈልገነው "ቤት ውስጥ የለም" ማለት የምንችለው በቤቱ ውስጥ አንድም ክፍል ሳይቀረን ፈትሸን አለመኖሩን ስናረጋግጥ ብቻ ነው ነገር ግን ያልተመለከትንበት ክፍል እያለ "ቤት ውስጥ የለም" ካልን ስህተት ላይ እንወድቃለን፡፡

የሚገርመው ደግሞ ፈጣሪ ይህንን ዩኒቨርስ ከፈጠረ ይህ ፈጣሪ ዩኒቨርስን ሳይፈጥር በፊት ነበረ፤ በዚህም ፈጣሪ በዚህ ዩኒቨርስም አይገደብም፤ በዚህም የሰው ልጅ የፈጣሪ መኖር አለመኖር መናገር የሚችለው በተለይ ከዩኒቨርሱ ውጪም በሚኖረው እውቀቱ ነው፤ ይህ ደግሞ የማይታሰብ ነገር ነው፡፡

ይህ ሁሉ ክፍተት ባለበት “ፈጣሪ የለም” የሚለው ችኮላ ከምን መጣ? ብለን ስንመለከት የሰው ልጅ በተፈጥሮው ያላየውን “የለም” የማለት ባህሪው ነው፣ ለምሳሌ አንድ በሰሀራ በረሀ ውስጥ የሚኖርን ተራ ሰው “ውሃ በተፈጥሮው እንደ ድንጋይ (ግግር በረዶ) ሆኖ ሊቀመጥ ይችላል” ብለን ብንጠይቀው፣ ይህ ሰው በአከባቢው እንደዚህ አይነት ነገር አይቶ ስለማያውቅ “አላውቅም” አይለንም ወይ “ምኑ ሞኞች ናቸው” ብሎ ስቆብን ይሄዳል ጨዋ ከሆነ ደግሞ “ውሃ በተአምር እንደ ድንጋይ አይቀመጥም” ብሎ ይመለስልናል፣ ይህ ሰውኛ ባህሪ ነው፡፡

በዚህ ላይ ደግሞ አምላካውያን “ሰዎች ፈጣሪ የለም ብለው እንዲያስቡ የሚያደርግ ተቃራኒ መንፈሳዊ ሀይል አለ ማለታቸው፣ “ፈጣሪ የለም” የሚለው የሩጫ ድምዳሜ በሰላም አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም ፈጣሪ ካለ፣ በተፈጣሪው ሊጠና በማይቻልበት የማንነት ልዩነት፣ የሰው ልጅ ያጠናው ካላጠናው ሲወዳደር ኢምንት በሆነበት እውነታ ውስጥ፣ የሰው ልጅ ያላየውን “የለም” በሚልበት ባህሪውና አምላካውያን “የሰው ልጆች የፈጣሪን መኖር እንዳያውቁ የሚፈልግ ሰይጣን የሚባል ተቃራኒ ሀይል አለ” በሚሉት እውነታ ውስጥ በመሆኑ ሳይንሱ እነኚህን ክፍተቶች አልፎ የፈጣሪን ህልውና የሚያጠናበት የጥናት ውጤት “ፈጣሪ የለም” የሚል እንደሚሆን ግልፅ ነው፣ በዚህም የስነፍጥረት ሳይንሱ የፈጣሪን ህልውና የማጥናት አቅም እንደሌለው እንመለከታለን፡፡

## 1.4. ከኢአምላካውያንና ከአምላካውያን በተለየ መንገድ የፈጣሪ ህለዎት ምርመራ

ከላይ እንደቀረበው የስነፍጥረት ሳይንሱ “ፈጣሪ የለም” ያለበት መንገድ ስህተት መሆኑን ተመልክተናል፣ ይሁን እንጂ የስነ ፍጥረት ሳይንሱ የጥናት መንገድ ስህተት በመሆኑ ብቻ “ፈጣሪ አለ” ወደሚለው ድምዳሜ በጭፍን መዝለል አመክንዮአዊ አይደለም፣ በዚህም ፈጣሪ አለ? ወይስ የለም? ከሚለው ከሁለቱ ቡድኖች ክርክር ወጣ ብለን ነገሮችን መመልከት አስፈላጊ ነው፣ ይህንንም ጥናት ለማድረግ እንደ ማንኛውም ተመራማሪ በቅድሚያ መመለስ የሚገባቸውን “research question” እናዘጋጅ፣

1. የፍጡራን ውበትና ስነስርአት ኢአምላካውያን ባሉት በዘፈቀደ የተፈጥሮ ሂደት የመጣ ነው ወይስ አምላካውያኑ የሚሉትን ፈጣሪ ያሳያል?
2. አምላካውያን “የፈጣሪ መንገድ ነው” የሚሉት መፅሀፍ ቅዱስ ኢአማኒዎች እንደሚሉት የሰዎች የፈጠራ ስራ ነው? ወይስ የፈጣሪ እጅ ይታይበታል?
3. ቅዱሳት መፅሀፍቱ “እስራኤል ከሌላው አለም ትለያለች” ማለታቸው ልበወለድ ነው? ወይስ በተግባር የሚታይ እውነታ ነው?
4. በቅዱሳት መፅሀፍት ውስጥ የተገለፁት ታሪኮች በዘመናዊው የታሪክና የአርኪዎሎጂ ጥናቶች ማረጋገጥ ይቻላል? ወይስ ልበወለዶች ናቸው?

የሚሉትን ጥያቄዎች በመፈተሽ፣ የፈጣሪን መኖርና አለመኖር በገለልተኛ መንገድ እንፈትሻለን፡፡

### 1.4.1. የፍጡራን ውበትና ስነስርአት ኢአምላካውያን እንደሚሉት በዘፈቀደ በተፈጥሮ ሂደት የመጣ ነው ወይስ አምላካውያን የሚሉትን ፈጣሪ ያሳያል?

የፍጡራንን ውበትና ስነስርአት በመመልከት የፈጣሪ መኖርና አለመኖር ጥያቄን ለመመለስ ለምሳሌ ያህል የሚልክዌይ ጋላክሲ፣ የሶላር ሲስተም፣ የመሬት፣ የውሀና የህይወትን ውበትና ስርአት እንመልከት፣

#### 1. ሚልክ ዌይ ጋላክሲ

[10] "በዩኒቨርስ(ፅንፈ አለም) ውስጥ ብዙ ጋላክሲዎች (የከዋክብት ስብስቦች) ይገኛሉ፣ ከነዚህ ስብስቦች ውስጥ እኛ የምንገኘው "ሚልክ ዌይ" ተብሎ በሚጠራው የወተት መልክ ባለው ጋላክሲ ውስጥ ነው፣ ይህ ጋላክሲ ፀሀይንና ምድርን ጨምሮ እስከ 400 ቢሊየን የሚደርሱ የኮከቦች ስብስብን ይዞ በአማካይ በ$2.3\times10^{41}$ ኪሎግራም ክብደት ከአውሮፕላን ፍጥነት በላይ በ600 ኪሎሜትር በሰከንድ በዩኒቨርስ ውስጥ ይሽከረከራል፡፡"

ይህ ከአእምሮ በላይ የሆነ ክብደት፣ ፍጥነትና ውስብስብ እንቅስቃሴ ለዘመናት ሳይዛነፍ እየተከወነ ይገኛል፣ ይህ ደግሞ በዘፈቀደ የፍንዳታ ሂደት የመጣ አይመስልም፡፡

#### 2. ሶላር ሲስተም

ሶላር ሲስተም ማለት በሚልክ ዌይ ጋላክሲ ውስጥ ፀሀይን ማዕከል አድርገው የሚገኙ አካላት ስብስብ ነው፣ [11] "ሶላር ሲስተማችንም አንድ ፀሀይ፣ ስምንት ዋና ፕላኔቶች፣ አምስት ድንክዬ ፕላኔቶች፣ ብዙ ጨረቃዎችና ብዙ አነስተኛ የሶላር ሲስተም አካላትን ይዞ በ$2.0028\times10^{30}$ ኪሎግራም ክብደት፣ በ220 ኪሎሜትር በሰከንድ ፍጥነት" በሚልክዌይ ጋላክሲ ውስጥ ይሽከረከራል፡፡" ይህ ፍጥነት ከአውሮፕላን ፍጥነት በእጅጉ የበለጠ ነው፡፡

---

[10] http://en.m.wikipidia.org>wiki>milkway galaxy
[11] https://en.wikipidia.org>wiki>solar System

ተመልሶ ደግሞ እያንዳንዱን የሶላር ሲስተሙ አካላት(ፕላኔቶች፣ ጨረቃ...) በሙሉ በተሳፈሩት ሶላር ሲስተም እንቅስቃሴ ውስጥ ሆነው በየግላቸው በራሳቸው አቅጣጫ፣ ፍጥነትና ሀይል በሌላ የእንቅስቃሴ ስርአት ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፡፡

በቀላል ምሳሌ የጨረቃን እንቅስቃሴ ብንመለከት፣ [12] "በአንድ ጊዜ በርካታ ውስብስብ እንቅስቃሴዎችን ታደርጋለች

(1) በራስዋ ዛቢያ ላይ ትሽከረከራለች

(2) በምድር ዙሪያ ትዞራለች

(3) ከመሬት ጋር አብራ በፀሀይ ዙሪያ ትዞራለች

(4) ከፀሃይ ጋር የጋላክሲያችንን ሚልክዌይ ማዕከላዊ ስፍራ ትዞራለች

(5) ከጋላክሲያች ጋር ዩኒቨርስ ውስጥ ትዞራለች"

ሌሎቹ የሶላር ሲስተም አካላትም እንደዚሁ ውስብስብ እንቅስቃሴ ውስጥ ይኖራሉ፣ በነዚህን ስርአቶች ለዘመናት ራሳቸውን ችለው፣ አንዴ ተፅፎ በተሰጣቸው ቀመር (Program) ሳይዛነፉ ይንቀሳቀሳሉ፡፡

እነዚህ ሰማያዊ አካላት በዚህ ክብደትና ፍጥነት ሳይዛነፉና ሳይንገጫገጩ ስርአት ይዘው ለዘመናት መጓዛቸውን ስንመለከት፣ ስርአቱ የመጣው በዘፈቀደነት በፍንዳታነት ይልቅ የመፅሀፍ ቅዱሱ መዝ.19፡1-3 "ሰማያት የእግዚአብሄርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ስራ ያወራል ... <u>ነገር የለም መናገርም የለም፣ ድምፃቸው አይሰማም</u> ..." የሚለው የበለጠ አሳማኝ ሆኖ እንመለከታለን፡፡

## 3. <u>ምድር(Earth)</u>

[13] "ምድር 5.9×$10^{24}$ ኪሎግራም ክብደት፣ በ1,670 ኪሎሜትር በሰአት የሮቴሽን ፍጥነትና በ107,000 ኪሎሜትር በሰአት ሪቮሉሽን ፍጥነት ትሽከረከራለች፣ በዚህ ላይ ደግሞ ከሶላር ሲስተሙ ጋር በ220 ኪሎሜትር በሰከንድ ፍጥነት በሚልክዌይ ጋላክሲ ውስጥ ትሽከረከራለች፣ ከሚልክዌይ

[12] ዘለቀ በሃይሉ(2008)፣ **ሳይንስና ኢቮሉሽን**፣ ክፍል አንድ፣ ገፅ 33-34

[13] https፡//en.wikipidia.org>wiki>earth

ጋላክሲም ጋር በ600 ኪሎሜትር በሰከንድ በዩኒቨርስ ውስጥ ትሽከረከራለች፣"

እነዚህ አራቱም ፍጥነቶች ከአውሮፕላን ፍጥነት በላይ ናቸው፣ ምድር ይህን ያህል ክብደትና ውስብስብ የእንቅስቃሴ አቅጣጫና ፍጥነት ይዛ በነዚህ የተለየዩ እንቅስቃሴዎች ስርአት ውስጥ ሳትዛነፍ መጓዝዋ ለአእምሮ የሚከብድ ነገር ነው፣ ይህ ሁሉ እንቅስቃሴ ደግሞ እየሆነ ያለው ያለ ምንም መንገጫገጭ፣ መዘግየት፣ መፍጠን ... በሌለበትና የትኛውም ህይወታዊ ፍጥረት በማይረበሽበት ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡

እነዚህ ውስብስብ እንቅስቃሴዎች በሙሉ ደግሞ ለዘመናት ሳይዛነፉ በተቀመጠው ቀመር መጓዛቸው የሚያሳየው ፕሮግራም ያደረጋቸው አካል መኖሩን እንጂ በታላቁ ፍንዳታ "በዘፈቀደ" ነው ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

## 4. <u>ውሃ</u>

የውሃን ምንነትና ጥቅም ዘርዝሮ መግለፅ አይቻልም በደፈናው፣ እንደ ውሃ ልማት "ውሀ ህይወት ነው" ወይ እንደ ኬሚስተሪው "Universal solvent" ከማለት በቀር፤ ውሀ ከዚህ ፍፁማዊ ባህሪው በተቃራኒው ደግሞ፡-

- ሌሎቹ ፕላኔቶች ጠብታ ውሀ ሳያገኙ ምድር ግን ከሁሉም ፕላኔቶች ተለይታ ከየትም ቦታ ሆኖ ለሚመለከታት መለያዋ ሆኖ 71% አካሏ በውሀ ተሸፍኗል፣ የሚገርመው ደግሞ የስነተፈጥሮ ሳይንሱ "በሜትዮራይት ግጭት ከመሬት ተቆርጣ ተወረወረች" የተባለችው ጨረቃን ጨምሮ በየትኞቹም ሰማያዊ አካላት ላይ ውሀ እስካሁን አልተገኘም፣ ከውሀ በስተቀረ በአንድ ፕላኔት ላይ ብቻ የተገደበ ንጥረ ነገር የለም፣ እንደ ሳይንሱ ህግ ቢሆን ኖሮ "ህይወት ነው" የተባለው ውሃ ምድርን በ71% ሲሸፍን ሌሎቹ ጎረቤት ፕላኔቶች ላይ ደግሞ ከዚህ አነስ ወይ በዛ ባለ መልኩ መገኘት ነበረበት ነገር ግን ይህ አልሆነም፣
- ከውሱንነቱ በተጨማሪ ደግሞ ይህ የህይወታዊ ፍጥረታቱ የመኖር ዋስትና የሆነውን ውሀ ሁሉም በያሉበት ቦታ ሆነው እንዲያገኙት ውሃው "በውሃ ኡደት/water cycle/ ፍጥረታቱን እየዞረ ያጠጣል፡፡

ይህም እውነታ ፍጥረታት በዘፈቀደው የቢግ ባንግ የፍንዳታ ሂደት መጡ ከሚለው ይልቅ አስቦበት እንደዚህ ያደረገ አካል መኖሩን ያሳያል፡፡

## 5. ህይወት

ህይወት የምትባለው ነገር ቁስ አካል፣ ኢነርጂ፣ ፎቶን ወይንም ዌቭ ባለመሆንዋ የስነፍጥረት ሳይንሱ ምንም ሊላት አልቻለም ነገር ግን የመኖር ያለመኖርዋን እውነታ ይታወቃል፣ አንድ ሰው ሲሞት፣ ሳይሞት በፊት ምን ነበረው? ሲሞትስ ምን ጎደለው? የሚለውን ሳይንሱ መልስ ሊሰጥበት ይገባል፣ አንዳንዶች ህይወትን የሰው ልጅ የሰውነት ስርአት መቆምና አለመቆም አድርገው ይመለከቱታል፣ ይህ ስህተት ነው ለምሳሌ ወዲያው የሞተን ሰው የሰውነት ስርአት በቴክኖሎጂው ድጋፍ መመለስ ይቻላል ነገር ግን በዚህ ሂደት ህይወትን መመለስ አይቻልም፣ ህይወት ማለት ራሱን የቻለ ነገር እንጂ የሰውነት ስርአት ማለት አይደለም፣ የሰውነት ስርአት ህይወት ሳይሆን የህይወት ውጤት ነው፡፡

ለህይወት መኖር ዋነኛ ግብአት በአከባቢው ያለ የተፈጥሮ ፀጋና ጥበቃ ነው፣ ህይወታዊ ሀብት ደግፋ የያዘችም ምድር ብቻ በመሆኗም ምድር ከሌሎቹ ፕላኔቶች ተለይታ ለህይወት መኖር አስፈላጊ የሆኑ ፀጋዎችና ጥበቃዎች በጥንቃቄ ተሟልተውላትና ህይወታዊ ፍጥረታቱም እርስ በርስ ተሳስረው ይገኛሉ፡-

- <u>ለህይወት መኖር ለምድር ከሌሎች ፕላኔቶች ተለይቶ የተቸራት ፀጋ</u>

  ምድር ከሁሉም ፕላኔቶች በተለየና በማይወዳደር መልኩ ከዘፈቀደነት ይልቅ በበላይ አካል በተቀመረ ቀመር ፍጥረታትን ማኖር እንድትችል ፍፁም፣ ሙሉና ውብ ተደርጋለች፣ በርግጥ እነዚህ ፀጋዎች የማይስተዋሉ “በእጅ ያለ ወርቅ” መሆናቸውና እጅግ ብዙ መሆናቸውም ያለውን እውነታ በአንድ ርእስ ወይ በአንድ ምዕራፍ ወይ በአንድ መፅሃፍ ማስቀመጥ አይቻልም፣ ሳይንሱም እያንዳንዳቸውን በተናጠል ዲፓርትመንትና ፋካልቲ እድሜ ልኩን እያጠናቸው ያሉ ነገሮች ናቸው፡፡

  ለም መሬት፣ የህይወት ዋና ግብአት ውሃ በሶስቱም በጋዝ፣ በፈሳሽና በበረዶነት መገኘትና በኡደቱም ለፍጥረታቱ እየዞረ አገልግሎት መስጠቱ፣ የተመጣጠነ የአየር ይዘት፣ የተመጣጠነ የመሬት ስበት፣ የማይነጥፍ

የሃይል ምንጭ የምታቀርብ ፀሃይ፣ የተመጣጠነ የሙቀት-ቅዝቃዜ መጠን፣ የተመጣጠነ የቀንና የለሊት ርዝማኔ፣ የተመጣጠነ የወቅቶችና መፈራረቅ ... ወዘተ ተዘርዝረው በማያልቁ ፀጋዎችና ፀጋዎቹ ተደግፋለች፣ በዚህ ላይ ደግሞ እነዚህ ስርአቶች በሌሎቹ ፕላኔቶች ላይ አንመለከትም፡፡

- <u>ለህይወት መኖር ምድር ከሌሎቹ ፕላኔቶች ተለይታ የተጠበቀችባቸው አደጋዎች</u>

እዚህ ጋር ምድር የተጠበቀችው ከምን አይነት ነገሮች እንደሆነ ሁሉንም ማወቅ አይቻልም ምክንያቱም ከላይ እንደተመለከትነው የሰው ልጅ ጥናት ከዩኒቨርሱ ጋር ሲተያይ ኢምንት ነውና ነገር ግን ባለችው ጥቂቷ ጥናትም ቢሆን ይህች ምድር ህይወታዊ ፍጥረታትን ስለያዘች ከሌሎች ፕላኔቶች ተለይታ ከአደጋዎች ከለላ ሊደረግላት እንደሚገባው ሁሉ እንደዚሁ ተደርጎላት እንመለከታለን፡፡

በዚህም በሌሎች ፕላኔቶች ላይ የምናያቸው ተለዋዋጭ የሆኑ እጅግ ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ያልተመጣጠነ የቀንና የለሊት እርዝማኔ፣ ከፍተኛ የፀሃይ ብርሃን፣ ይህቺ ምድር የማታውቀው "Solar wind" የሚባለው የፀሀይ ተፅዕኖ፣ ከተለያዩ የብርሃን አካላት የሚለቀቁ አደገኛ ጨረሮች፣ የሜትርዮራይት(ተወርዋሪ ኮከብ) ድብደባ፣ ከፍተኛ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታና ተያያዥ ችግሮች፣ መርዛማ ከባቢ አየር፣ ከብናኝ የማይጠራ አየር፣ የአሲድ ዝናብ ... ተጠብቃ እንመለከታለን፡፡

ይህ የሆነው ደግሞ ምድራችን የምትገኝበት ሶላር ሲስተም በሚልክዌይ ጋላክሲ ውስጥ ከወደ ዳር በተረጋጋ ሰፈር በመሆኑ ለከፍተኛ የስበትና የጨረራ ሀይል እንዳትጋለጥ አድርጓታል፤ በሶላር ሲስተሙ ውስጥም የያዘችው የሶስተኛነት ቦታም የተመጣጠነ የሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የተመጣጠነ የፀሀይ ሀይል እንዲሁም የተመጣጠነ የቀንና የለሊት ርዝማኔ እንዲኖራት አድርጓታል፤ ከባቢ አየርዋም በኦዞን ንጣፍ በመሸፈኑ ከፀሃይና ከሌሎች የብርሀን ምንጮች የሚመጡ አደገኛ ጨረሮች ፍጥረታቱን እንዳይጎዱ ያደርጋል፤ ምድር በማግኔቲክ ፊልድ በመሸፈኗ ምክንያት ከፀሀይ ከሚለቀቀው "Solar wind" አያገኛትም፤ ምድር በሁለቱ ግዙፍ የስበት ሀይል ባላቸው በፀሀይና በጁፒተር መካከል

የምትገኝ በመሆኗ ከአብዛኛው የሜቲዎራይት(ተወርዋሪ ኮከቦች) ግጭት ተጠብቃለች፣ የሚገርመው ደግሞ በነዚህ አካላት ሳይሳብ አልፎ የሚመጣው ተወርዋሪ ኮከብ በምድር ከባቢ አየር ውፍረት(thickness) ምክንያት በሚፈጠርበት ሰበቃና በአየሯ ውስጥ በብዛት በሚገኘው አክሲጅን ምክንያት መሬት ሳይደርስ ከባቢ አየር ውስጥ ተቃጥሎ ያልቃል፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ ቅንብሮችን ስንመለከት፣ የምድር ስነፍጥረት ከዘፈቀደ የፍንዳታ ሂደት ይልቅ የፈጣሪን ቀመር ያሳያል፡፡

- <u>ህይወታዊ ፍጥረት እርስ በርስ ትስስር</u>

ህይወታዊ ፍጥረታቱም መካከል ያለው ትስስር እጅግ የሚደነቅ ነው፡፡

ዕፅዋቱ ያለ ፓምፕ(ወይንም ልብ) እንዴት ውሀ ከመሬት ውስጥ ስበው ከግራቪቲ ሀይል በተቃራኒ እስከ ሰባትና ስምንት ሜትር የሚደርስ ቁመታቸው አድርሰው ምግባቸውን በፀሀይ አማካኝነት እንደሚያዘጋጁ፣ እንስሳቱም እፅዋትን በመመገብ ሰውነታቸው እንዴት ምግቡን ሰባብሮ ሀይል ከውስጡ አውጥቶ እንደሚጠምበት፣ ሌሎች እንስሳት ደግሞ እነዚህን ቅጠል ተመጋቢ እንስሳት አድነው እንደሚበሉ በአጠቃላይ በተፈጥሮ የተቀመጠላቸው የምግብ ሰንሰለት ስርአት(food chain)፣ በእንስሳትና እፅዋት መካከል ያለው የካርቦን ዳይኦክሳይድና አክስጂን ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ የሚያደርጉት የማጣራት ስነስርአት፣ እፅዋቱና እንስሳቱ የሚራቡበት ስርአት … ስንመለከት ይህ እየሆነው ያለው ከበዘፈቀደው የዝግመተ ለውጥ ህግ ይልቅ ስርአት ባበጀላቸው ፈጣሪ መኖሩን ያሳያል፡፡

እንስሳቱ ለሰው ልጆች ለማጓጓዣ፣ ለእርሻ፣ ለመብል፣ ለጥበቃ … በተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ ተገርተው መፈጠራቸው፣ ለምሳሌ በሬ "እኔ ከውሻ በላይ ጉልበታም ነኝ" ብሎ እንግዳ ሰው ወይንም አውሬ ሲመጣ ተነስቶ አያባርርም ምክንያቱም የጥበቃ አእምሮ የተሰጠው ለውሻ ስለሆነ፣ እንደዚሁ ድመትም በቤት አካባቢ አይጥ፣ እንቁራሪት፣ እባብ …

የመሳሰሉ ነገሮችን ካየች የማስወገድ የስራ ድርሻዋ በመሆኑ ሌሎቹ እንስሳት እየተመለከቷት ስራዋን ትሰራለች፡፡

ዕፅዋቱም እንደዚሁ ለመድህኒትነት፣ ለማገዶነት፣ ለግንባታ ... አገልግሎቶች ተብለው ተለይተው ተፈጥረዋል፣ ዛሬ ላይ ለህክምና የሚደረገው ምርምር በአብዛኛው የሚያተኩረው "የየትኛው በሽታ መድህኒት በየትኛው አፅዋት ውስጥ ነው የተቀመጠው?" የሚለው ነው፣ አንዳንድ እንስሳትም ይህንን የእፅዋትን መድህኒትነት ያውቃሉ፣ ውሻ ሆዱን ሲያመው እንደ በግ ሳር በልቶ ይድናል፣ ፍየል እባብ ከነደፋት ከሞት ለመዳን የምትበላው የቅጠል ዘር አለ ...

እነዚህ በአካባቢያችን የምናስተውላቸውን፣ በሳይንሱ የምንማራቸውንና በተለያዩ የእንስሳት ዶክመንተሪ ፊልሞች ላይ የምንመለከታቸውን የተፈጥሮ ውበትና ስነስርአት እውነታዎችን በንፁህ ልቦና ስንመዝን ህይወታዊ ፍጥረታቱ የተፈጠሩት ሆነ እየኖሩ ያሉት ከዘፈቀደ ህግ በላይ በፈጣሪ ቀመር መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም "ፈጣሪ አምላክ የለም" የሚለው መሠረት የሌለው ይባሱኑም አምላካውያኑ እንደሚሉት አደጋ ያለው አስተምህሮ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከመነሻው "ፈጣሪ የለም" የሚለው የስነፍጥረት ሳይንሱን ሆነ የሶሻሊዝም ፍልስፍናን ስንመለከት "double standard" የሆነ አስተምህሮ ነው፣ ለምሳሌ ያህል በፈጣሪ የተፈጠረና በሰው የተፈጠረን በተመሳሳይ ቴክኒክ የሚሰሩትን ለምሳሌ የሰው ልጅ ዓይንና የሰው ልጅ የፈጠረውን ካሜራ እንመልከት፣ አይንና ካሜራ የተሰሩትም ሆነ የሚሰሩት በተመሳሳይ መርህ ነው ነገር ግን የሰው አይን ክፍሎች ከካሜራው ክፍሎች በመጠን አንሰው፣ በቋሚ የሀይል አቅርቦት፣ በዕንባና በሽፋሽፍት የፅዳት ስነስርአት ተጠብቀው፣ የተሰበሰበውንም መረጃ ለውሳኔ ሰጪው አእምሮ የሚያስተላልፍበትን ረቂቅ ቅንብርን እየተመለከትን "ካሜራን የሰራ ኢንጅነር አለ ነገር ግን ዓይንን የሰራ ኢንጅነር የለም" የሚባለው አባባል ከስህተት ያለፈና አምላካውያን የሚሉት "የተቃራኒ ሃይል ሴራ" መሆኑን በግልፅ እንመለከታለን ፡፡

የሰው ልጅ በካሜራ ቴክኖሎጂ የፈለገውን ያህል ይራቀቅ እንጂ ጉዳት የደረሰባትን በተመሳሳይ ቴክኖሎጂ የምትሰራዋን አይን የሚተካ ሰው ሰራሽ አይን ግን ለሰው መግጠም አይችልም፣ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ኩላሊት የሚተካ ዲያልሲስ የሚባል መሳርያ አለ፣ የባቄላ ፍሬ የምታክለዋን ኩላሊት ለመተካት የተሰራውን ግዙፍ መሳሪያና ተያያዥ ስርአቶችን እየተመለከትን "የዲያልሲስ ማሽን ሰሪ አለው ረቂቋ ኩላሊት ግን በዘፈቀደ መጣች" የሚባለው አነጋገር ምን ያህል ችግር ያለበት አባባል መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡

ታዋቂው ጀርመናው ፈላስፋ "ኒቼ" ስለዚህ የስነ ተፈጥሮ ውበትና ስነስርአት ሲጠየቅ "በርግጥ የፈጠራቸውና ስርአት ያስያዛቸው ፈጣሪ ነበረ ነገር ግን አሁን ይህ ፈጣሪ የለም" በማለት በ"አልሸነፍም" ባይነት በግማሽ እውነታ ሲከራከር እንመለከተዋለን፡፡

ስዕል ዝም ብሎ አይገኝም ሰዓሊ አለው፤ ቅርፃ ቅርፅ፣ ቤት፣ ሀውልት ... ያለ ሰሪ ዝም ብሎ አይገኝም፤ አንድ ጠጠር ስትወድቅ ዝም ብላ አትወድቅም፣ አንድ የአቧራ ብናኝ ዝም ብላ ከመሬት ላይ አትነሳም ... ሁሉም ነገር በ"cause and effect" በምክንያትና ውጤት ነው የሚመራው፣ በዚህም ይህንን የሚያክል እጅግ የገዘፈ፣ የተወሳሰበ፣ የተዋበና በስርአት የሚመራ ስነፍጥረትን "ዝም ብሎ ነው የመጣው" ማለቱ ከውሸትነት ያለፈ ችግር ያለበት አነጋገር ነው፡፡

በዚህም ከግዙፉ ሚልክ ዌይ፣ ሶላር ሲስተም፣ ህይወታዊ ፍጥረቱ አንስቶ እስከ አተምና ፎቶንስ ድረስ በተመለከተው ስነ ውበትና ስነስርአት፣ አንድ ውብ አድርጎና ስርአት አስይዞ መፍጠር የሚችል፣ አንዳንድ ሳይንቲስቶች "Inteligent Designer" የሚሉት ፈጣሪ አምላክ መኖሩን ያሳያል፡፡

### 1.4.2. አምላካውያን "የፈጣሪ መንገድ ነው" የሚሉት መፅሀፍ ቅዱስ ኢአምላካውያን እንደሚሉት የሰዎች የፈጠራ ስራ ነው? ወይስ የፈጣሪ እጅ ይታይበታል?

ፈጣሪ ካለ የፈጣሪ ቃል ከየትኛውም ትውልድ ዕውቀት በላይ መሆን አለበት፣ በዚህም አምላካውያኑ "የፈጣሪ ቃል ነው" የሚሉት መፅሀፍ ቅዱሱ የፈጣሪ ቃል ለመሆን የመፅሀፉ ዕውቀት መፅሀፉ በተፃፈበት ወቅት ከነበረው ማህበረሰብ አስተሳሰብ በላይ መሆን አለበት፣ በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ "ልዕለ ስብዕናነት" እንዳለውና እንደሌለው በመመልከት የፈጣሪን መኖር አለመኖር እንመለከታለን፣ በዚህም፡-

- መፅሀፍ ቅዱሱ ከሰውኛ መፅሀፍት የሚለይ መሆን አለመሆኑ፣
- መፅሀፍ ቅዱሱ ምንም እንኳን የሳይንስና ቴክኖሎጂ መፅሀፍ ባይሆንም፣ በተወሰነ መልክም ቢሆን ዛሬ "አዳዲስ ናቸው" የምንላቸውን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶችን ቀድሞውኑ የሚያውቃቸው መሆን አለመሆኑ፣
- የትንቢቱ ተጨባጭነት ባለፈው፣ በአሁኑና በሚመጣው ዘመን መረጋገጥ አለመረጋገጡን፣

በመመልከት መፅሀፍ ቅዱሱ የሰዎች ድረሰት ነው? ወይስ ልዕለ ስብዕና እጅ አለበት? የሚለውን እንመለከታለን፡፡

#### 1.4.2.1. መፅሀፍ ቅዱሱ ከሰውኛ መፅሀፍት የሚለይ መሆን አለመሆኑ፣

መፅሀፍ ቅዱሱ ከፈጣሪ ዘንድ የወረደ ከሆነ ከሌሎች መፅሀፍት የሚለይባቸው ባህሪያት ሊኖሩት ይገባል፣ በዚህ አንፃር መፅሀፍ ቅዱሱን ስንመለከት መፅሀፉ ከሌሎች ሰውኛ መፅፍት በብዙ መንገድ እንደሚለይ እንመለከታለን፣ ይህም፣

- በ1,500 ዓመታት ርዝመት ውስጥ ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎች በአንድ ሀሳብ ወጥ በሆነ መልኩ የተፃፈ መፅሀፍ መሆኑ፣
- በ1,900 ዕድሜው አለማርጀቱ፣
- ለማንም አለማዳላቱ፣
- እንዲጠፋ እየተሰራበት በተቃራኒው እየተስፋፋ መገኘቱ፣

ስንመለከት መፅሀፉ ሰውኛ ድርሰት አለመሆኑን ያሳያል፡-

## 1. <u>በ1,500 አመታት ውስጥ ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎች በአንድ ሀሳብ የተፃፈ ወጥ መፅሀፍ መሆኑ</u>

መፅሀፍ ቅዱስ እንደ አብዛኞቹ መፅሀፍት የተፃፈው በአንድ ሰው አይደለም ነገር ግን በአንድ ሰው የተፃፈ እስኪመስል፣ በተለያያ ዘመን፣ ቦታ፣ ባህል፣ ንቃተ ህሊና፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ ማህበራዊ ሁኔታ ... ወዘተ ውስጥ በነበሩ ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎች ነው፣ እነዚህም ሰዎች ሊተዋወቁ በማችሉበት በ1,500 አመታት (ከ1,400 ዓ.ዓ - 100 ዓ.ም) ርዝማኔ ውስጥ ፍፁም በሆነ ተግባቦት አንድ ሰው የፃፈው በሚመስል መልኩ መፅሀፉን አዘጋጅተዋል፡፡

ይህ መፅሀፍ በ1,500 አመታት እርዝማኔ ሲፃፍ ፀሀፊዎቹ ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ ይለያል፣ ከዚያ በላይ ደግሞ ሰዎቹም በግል ያላቸው ችሎታና ሙያ የተለያየ ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

| ተቁ | የመፅሃፉ ስም | ፀሃፊው | የፀሃፊው ሙያ |
|---|---|---|---|
| 1 | ኦሪትዘፍጥረት፣ ዘፀአት.. | ሙሴ | እረኛ(ዘፀ.3፡1) |
| 2 | መፅሀፈ ዕዝራ | ዕዝራ | የስነፅሁፍ ሰው(ዕዝ.7፡6) |
| 3 | መፅሀፈ ነህምያ | ነህምያ | ጠጅ አሳላፊ (ነህ.1፡11) |
| 4 | መዝሙረ ዳዊት | ዳዊት | እረኛ ከዚያ ንጉስ (1ዜና. 29፡26) |
| 5 | መሃልየ መሃልይ፣መክብብ | ሰለሞን | ንጉስ(1ዜና 29፡28) |
| 6 | ትንቢተ ኤርምያስ | ኤርምያስ | ካህን(ኤር.1፡1) |
| 7 | ትንቢተ አሞፅ | አሞፅ | ገበሬ(አሞ.1፡7,አሞ.7፡14) |
| 8 | የማቴዎስ ወንጌል | ማቴዎስ | ቀራጭ (ማቴ.9፡9) |
| 9 | የሉቃስ ወንጌል | ሉቃስ | ሀኪም(ቆላ.4፡14) |
| 10 | የጳውሎስ መልእክቶች (ወደ ሮሜ፣ ቆሮንቶስ ... ) | ጳውሎስ | የህግ ባለሙያ(ሐዋ.22፡3) |
| 11 | የጴጥሮስ መልእክቶች | ጴጥሮስ | አሳ አጥማጅ(ማቴ.4፡18-22) |

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ እነዚህ በአካል እርስ በርስ የማይተዋወቁት ፀሃፊዎች የየራሳቸውን ጥቅልል መፅሀፍ ያዘጋጁ እንጂ እነዚህ ጥቅልል መፅሃፍት በመፅሀፍ ቴክኖሎጂው በአንድ ላይ ተጠርዘው በአንድ መፅሀፍ ሲታተሙ መፅሀፍቱ መካከል የተመለከተው ፍፁም የሆነ አንድነት ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- አንዱ መፅሀፍ "ለወደፊት ይሆናል" ብሎ የተነበየውን ሌላው መፅሀፍ ላይ የትንቢቱን ፍፃሜ እንመለከታለን፣

- ሙሴ(ሙሳ) ከቁሳዊው ስነፍጥረት አጀማመር በመነሳት "በመጀመርያ" ብሎ የጀመረው መፅሀፍ ከ1,500 አመታት በኋላ የመጣው ዮሐንስ(የሕያ) የቁሳዊው ስነፍጥረትን መጨረሻ ምን እንደሚሆን በማሳየት "በዚህ መፅሀፍ ላይ ማንም እንዳይጨምር" ብሎ መፅሀፉን ዘጋው፣

- ኢየሱስና ሐዋርያቱ በአስተምህሮታቸው ውስጥ የቀደሙትን መፅሀፍት እያጣቀሱ በማስተማር ተለያይው በጥቅልል የተቀመጡት መፅሀፍት የአንድ መፅሀፍ አካል መሆናቸውን አሳይተዋል፣ ይባሱኑ ደግሞ "ብሉይ ኪዳን" የሚባሉት መፅሀፍት እንደ ዛሬ በአንድ መፅሀፍ በዚህ መልክ ባልታተሙበት ሁኔታ ውስጥ "የህግ፣ የነብያትና የመዝሙራት መፅሀፍት" ተብለው እንደሚከፈሉ (ሉቃ.24፡44) በወቅቱ መፅሀፍቱ እንደዚህ በአንድ መፅሀፍ ሳይጠረዙ በፊት ሲነገር ነበረ፣

- ከብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢያት የብዙ ዘመናትን ርቀት እንደውም እስከ አዲስ ኪዳኑ የመጨረሻው ዘመን ድረስ መጥቶ ትንቢት የተናገረው በመካከለኛው ዘመን በነብዩ ዳንኤል የተፃፈው "የዳንኤል መፅሀፍ" የአጠቃላይ መፅሀፍ ቅዱሱ ማስተሳሰርያ ሆኖ እንመለከተዋለን፣ ከዳንኤል ትንቢት ከ164 አመታት በኋላ የመጣው ኢየሱስ ከዳንኤል መፅሀፍ ጠቅሶ ሲያስተምር ነበረ(ማቴ.24፡15, ማር.13፡14 ...)፣ በምሳሌዎች በመነገሩ ምክንያት ለመረዳት የሚከብደው የመፅሀፍ ቅዱሱ የመጨረሻ ምዕራፍ "ዮሐንስ ራዕይ" መረዳት የሚቻለው ከዳንኤል መፅሀፍ ጋር አጣምሮ ማንበብ ሲቻል ነው፣ በዚህም የዳንኤል መፅሀፍ የመፅሀፍቱ እርስ በርስ ማሰርያ ገመድ ሆኖ እንመለከታለን፡፡

- ከአንዱ አሰራር ስርአት ወደ ሌላኛው የሚደረጉ ዋነኛ ሽግግሮች ከመከሰታቸው በፊት በቀደምቱ መፅሀፍት ቀድሞ ተደጋግሞ ተተንብዮ ነው፣ ለምሳሌ፣ ከብሉይ ኪዳን አሰራር ወደ አዲስ ኪዳን አሰራር ሲገባ ዝም ተብሎ አልተገባም በቀደምት ነብያቱ በኩል ተደጋጋሚ ትንቢቶች ከተነገሩ በኋላ ነው፣ እንደዚሁ ዛሬ ላይ ባለበት ቦታ ሆኖ እንኳን ሊመጣ ስለሚለው ነገር ይባሱኑም ከዚህ ቁሳዊ ዓለም ፍፃሜ በኋላ ምን እንደሚከሰት ይናገራል፣

- በመፅሀፍ ቅዱሱ መፅሀፍት መካከል ያለው አጠቃላይ አንድነትም ከገነት ታሪክ ተነስቶ ዞሮ መጥቶ የገነት ታሪክ ላይ የሚዘጋ ሙሉ ክበብ የሚሄድ ሙሉ መፅሀፍ ነው፣ አዳም ከገነት ተባረረ፣ ኋለኛው አዳም በተባለው ኢየሱስ(ኢሳ) ደግሞ የተዘጋውን የገነት መንገድ ተከፈተ፤ ይህም የመፅሀፍ ቅዱሱን ሙሉዕነት ያሳያል፡፡

ይህ በመፅሀፉ ጥቅልሎች መካከል የተመለከተው አንድነት ደግሞ በ1,500 አመታት ውስጥ በተለያየ ሙያ፣ ቦታ፣ ባህል፣ ንቃተ ህሊና፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ ማህበራዊ ሁኔታ ... ወዘተ በኖሩ ሰዎች የተፃፈ መሆኑ፣ መፅሀፉ የተፃፈው በሰው እጅ ቢሆንም በበላይነት ሲያፅፍ የነበረን ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

## 2. <u>በ1,900 ዕድሜው አለማርጀቱ</u>

መፅሀፍ ቅዱስ ከ1,400 ዓ.ዓ እስከ 100 ዓ.ም ለ1,500 አመታት የተፃፈ ሲሆን የመጨረሻው መፅሀፍ ከ1,900 አመታት በፊት ተፃፈ፣ በነኚህን ዘመናት የነበሩት ማህበረሰቦች በጋርዮሽ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ቢሆኑም፣ መፅሃፉ ግን እንደ እኩዮቹ አርጅቶ ሙዚየም አልገባም፣ ዛሬም ከሁለት ቢሊየን በላይ ወዳጆች አሉት፣ በብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል፣ በአለም ላይ ከየትኛውም መፅሀፍ በላይ በብዙ ኮፒ እያታተመ ይገኛል፡፡

በዓለማችን ላይ ታላላቅ ፈላስፎች፣ ደራሲዎች፣ ባለቅኔዎች ... በየትውልዱ ተነስተ ለየትውልዱ እጅግ ድንቅ የተባሉ ፅሁፎችን ሲያቀርቡ ቆይተዋል ነገር ግን የስራዎቻቸው ተወዳጅነት ከሁለትና ከሶስት ትውልድ በላይ ሲዘልቅ አልነበረም ነገር ግን መፅሃፍ ቅዱስ ከዚህ በተቃራኒ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተስፋፊነቱ እየጨመረ ይገኛል፡፡

ይህንን እውነታ ስንመለከት መፅሀፍ ቅዱስ ምንም እንኳን በጋርዮሽ ዘመን በነበሩ ሰዎች እጅ ቢፃፍም በውስጡ ያለው እውነታ የአንድ ትውልድ እውነታ ብቻ ባለመሆኑ በየትውልዱ ተቀባይነቱን እንደጠበቀ መሄዱና ይህም ደግሞ ምንም እንኳን መፅሀፉ በሰው እጅ ቢፃፍም መፅሀፉን ያፃፈው ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 3. እንዲጠፋ እየተሰራበት በተቃራኒው እየተስፋፋ መገኘቱ

ከፅሁፎች ሁሉ እንደ መፅሃፍ ቅዱስ ጠላቶች የበዙበት መፅሃፍ የለም፣ መፅሃፍ ቅዱሱ ከአለም ላይ እንዲጠፋ ብዙ ሴራዎች ሲሰሩበትና እየተሰሩበት ይገኛሉ፣ ይህ ደግሞ የአንድ ዘመን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የዕድሜ ልክ ታሪኩ ነው፣ አንዳንዶቹ ከሴራቸው ከባድነት የተነሳ "አሁንስ አለቀለት" ያሉበት ጊዜ ሁሉ ነበረ፡፡

እነዚህም ጥቃቶች መፅሃፍ ቅዱሱ እንዳይታተም ከመከልከል አንስቶ በሰው እጅ ያሉትን ሰብስቦ ማቃጠልና ለወደፊትም እንዳይታተም "አስተምህሮቱ ስህተት ነው" የሚል ተቃራኒ አስተምህሮቶች እስከ ማስፋፋት የሚደርሱ ስራዎችን ያጠቃልላል፡፡

እነዚህም ሙከራዎች ሲደረጉ የነበሩት ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱ በአንድ መፅሀፍ ተጠቃሎ ሳይታተም መፅሀፍቱ በጥቅልል ለየብቻ ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ ነው፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፡-

- የይሁዳ ንጉስ ኢዮአቄም፣ እግዚአብሄር ኤርምያስን ያፃፈውን በወቅቱ ብቸኛ የነበረውን የትንቢት ጥቅልል መፅሀፍ በካራ በመቆራረጥ በእሳት አቃጠለው(ኤር.36፡1-23)፣

- አንትዮከስ ኤጲፋንስ(175-164 ዓ.ም) የተባለው ንጉስ ኢየሩሳሌምን ድል አድርጎ ሲይዝ መፅሃፍ ቅዱስ በእጁ የተገኘ ሰው በሞት እንዲቀጣ በማወጅ "መፅሀፍ ቅዱሱን ሙሉ በሙሉ አጥፍቻለሁ" እስኪል ደርሶ ነበረ፡፡

- ኔሮ(37-68 ዓ.ም) የተባለው የሮማ ቄሳር መጠነ ሰፊ የመፅሀፍ ቅዱስና ክርስቲያኖችን የማጥፋት ስራዎች ሲሰራ ነበረ፡፡

- ዲዮቅልጥያኖስ/Diocletian(284-316 ዓ.ም) የሚባለው የሮማ ቄሳር ሰፊ መፅሃፍ ቅዱስን የማጥፋት ስራዎች በመስራት “ፈፅሜ አጥፍቸዋለሁ” እስከማለት ደርሶ ነበረ፡፡
- የሮማ ቤተክርስቲያን “መፅሀፍ ቅዱስ ከቤተክርስቲያን ውጪ በግለሰቦች እጅ መግባት የለበትም” በማለት በተለያየ ጊዜ የተባዙ ኮፒዎችን ሰብስባ በማቃጠል ፀሀፊዎቹ ላይ ግድያ ፈፅማለች፣ ጄሮም(405 ዓ.ም)፣ ጆን ዋይክሊፍ(1320 ዓ.ም)ና ዊሊያም ትያንዳል(1500 ዓ.ም) የሚባሉ በወቅቱ ታዋቂ የነበሩ ሰዎች የተገደሉት በዚህ ምክንያት ነው፡፡
- ቮልቴር(1,700 ዓ.ም) የተባለው ፈረንሳያዊ የመፅሃፍ ቅዱስ አስተምህሮትን ለማፋለስ ማተሚያ ቤት አቁሞ “መፅሀፍ ቅዱስን የማራከስ” ስራ ሲሰራ ነበረ “በመቶ አመታት ውስጥም መፅሀፍ ቅዱስ ከአለም ላይ ይጠፋል” ብሎ ቢተነብይም ከመቶ አመታት በኋላ ግን መፅሀፍ ቅዱስ እሱ ባቋቋመው ማተሚያ ውስጥ ሲታተም ነበረ፡፡
- በአሁኑ ጊዜም ማርክሲዝምና ኮምኒዝም፣ ኤቲዝም፣ ሂውማኒዝም፣ የኢቮሉሽን ሳይንስ ... የመፅሃፍ ቅዱሱን አስተምህሮት ተረት ተረት ለማድረግ ከመሞከር አንስቶ አሰባስቦ እስከማቃጠል ዘመቻዎች ከፍተውበታል፡፡

ለወደፊቱም በቴክኖሎጂ እገዛ ተመሳሳይ ጥቃቶች ታስቦበት እንደሚገኝ ይነገራል፣ ይህም መፅሀፍ ቅዱሱን እጅግ አመቺ በሆኑ ሶፍት ኮፒዎች በመልቀቅና ከሶፍት ኮፒ አመቺነት የተነሳ ሰዎች ከሃርድ ኮፒ ወደ ሶፍት ኮፒው ስለሚያዘነብሉ፣ ሃርድ ኮፒው በተለያየ መንገድ በመሰብሰብ በሰዎች እጅ የሚቀረውን ሶፍት ኮፒ ደግሞ በቫይረስ፣ ሶፍትዌር አፕዴት ... በተለያዩ ሰበቦች ሙሉ በሙሉ በማጥፋት፣ መፅሃፍ ቅዱሱን ሙሉ በሙሉ የማጥፋት ሴራዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ በታሪኩ ውስጥ እነዚህንና የመሳሰሉት የማጥፋት ሙከራዎች ቢደረጉበትም በተአምራዊ መንገድ ተነስቶ ሲያንሰራራና እንደ ሰደድ እሳት መልሶ አለምን ሲያጥለቀልቅ ይታያል ይባሱኑ ደግሞ መፅሀፉ በብዛት እንዲጠፋ በተሰራበት መጠን ከዚህ ሴራ በተቃራኒ “በመጨረሻ ዘመን ወንጌል ለአለም ይዳረሳል” በተባለው ትንቢት እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

ዛሬ እነዚያ እሱን ሊያጠፉ ሲሰሩ የነበሩቱ ነገስታት ሞተው አስከሬናቸው በየሙዚየሙ እየተጎበኘ ይገኛል፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ግን ሙዚየም ከመግባት ይልቅ ዛሬ ከሚታተሙት አዳዲስ መፅሀፍቶች እኩል ይባሱኑም ከነሱ በበለጠ በብዙ ሚሊዮኖች ኮፒ ያውም በተለያዩ ቋንቋዎች እየተተረጎመና እየታተመ ይገኛል፡፡

በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ በብዙ የማጥፋት ሴራዎችና በማታይታዩ እጆች ጥበቃ መካከል እንደሚገኝ እንመለከታለን፣ ይህ እውነታም መፅሀፉ በልዕለ ሰብአዊ አካል ጥበቃ እየተደረገለት እንደሚገኝ ያሳያል፡፡

## 4. ለማንም አለማዳላቱ

መፅሀፍ ቅዱሱ የተፃፈው ለማንም አድልዎና ፍራቻ የሌለው የፈጣሪ ቃል በሆነ መልኩ በሚዛናዊነትና በገለልተኛነት መንፈስ ነው፡፡

ሁሉም ነገር መነሻ ቦታ እንዳለው ሁሉ፣ የአብርሃም ሀይማኖቶች መነሻ እስራኤል ናት፣ በዚህም አብዛኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ታሪኮች የእስራኤላውያን ታሪኮች ቢሆኑም፣ መፅሀፉ ለእስራኤልም መልካም ነገሮችን እንደፃፈው ሁሉ መጥፎ ጎናቸውንም ሳያዳላላቸው ፅፏል፣ የእስራኤል ህዝብ አልታዘዝ ባለበት ወቅት በፈጣሪ በወረዱበት ቅጣቶች የደረሰበትን ክብረ ነክ ታሪካቸውን ምንም ሳይደብቅላቸው ሲዘግብ ነበረ፣ ለምሳሌ ብንመለከት፣

- እስራኤላውያኑ በደረሰባቸው ቅጣት ከረሀብ የተነሳ የአህያ ስጋ፣ የሰውን ስጋ እና የእርግብ ኩስ መብላታቸውን(2ነገ6፡25-30)፣
- አጭበርባሪ (ዘፍ.27፡19)፣ አስቸጋሪ (ዘኍ.14፡11) እና ጨካኝነት (መዝ.137፡9) መሆናቸውን፣
- ያለመረዳት(ማቴ.11፡21) እና ያለማመን(ማር.9፡19) ችግር ያለባቸው መሆኑን ...

በግልፅ አስቀምጧል፣ እግዚአብሄርም የዚህን ህዝብን አስቸጋሪነት ተመልክቶ ይህን ህዝብ ከምድረ ገፅ ለመጥፋት የወሰነበት ጊዜ ሁላ እንደነበረ(ዘኅ.14፡11-20) ነገር ግን በነሙሴ(ሙሳ) ልመና ይህንን ከማድረግ እንደ ተመለሰ መፅሀፉ ላይ እንመለከታለን፡፡

በመፅሀፉ ላይ እጅግ የተከበሩት ፃድቃን እንኳን በተሳሳቱበት ጊዜ ክብራቸውን ሳይጠብቅ የተባሉትን ነገር ቃል በቃል ፅፏል፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ “ሂድ አንተ ሰይጣን” ተብሎአል፣ ኤፍሬም “ያልተገለበጠ ቂጣ፣ አእምሮ እንደሌላት እንደ ሰነፍ እርግብ” ተብሏል፣ እስራኤላውያን በጀግንነቱ የሚኮሩበት ሳምሶን በፍልስጤማውያን ተማርኮ አይኑን አጥፍተውት ወፍጮ ሲያስፈጩት እንደነበረ፣ ቅዱስ የተባለው ዳዊት በዝሙት መርከሱንና ይህንንም ጥፋቱን ለመደበቅ የንፁህ ሰው ህይወት ማጥፋቱን፣ የብሉይ ኪዳን ዋና መሪዎቹ ሙሴና አሮን በሰሩት ሃጢያት ለአርባ አመታት ተስፋ ሲሰጣቸው የነበረውን የከነአን ምድር እንዳይደርሱ መደረጋቸውን በግልፅ ዘግቧል፡፡

“ጠላት” የሚለውን ሰይጣንን እንኳን ሲገልፀው በተራ የጥላቻ ቃል አይደለም “ሰይጣንን አደገኛ ነው ተጠንቀቁት፣ ሴረኛ ነው፣ እውቀቱ የመጠቀ ነው፣ ከሰው አእምሮ በላይ የሆነ ድንቅ የሚያደርግ፣ ሙታንን ማናገር የሚችል፣ ከሰማይ እሳት ማውረድ የሚችል …” በሚል ከሱ ጋር ያለው ነገር በጥንቃቄ እንዲመራ በማሳሰብ እንጂ በተራ ልበወለዳዊ የጠላትነት ስሜት አይደለም፡፡

እነዚህ ለምሳሌ የቀረቡት የመፅሀፍ ቅዱሱ ገለልተኛ አካሄዶች ስንመለከት፣ መፅሀፉን በባለቤትነት ሲያፅፍ የነበረው ገለልተኛ ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

### 1.4.2.2. ዛሬ አዳዲስ የሆኑብን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶችን ቀድሞውኑ የሚያውቃቸው መሆኑ

መፅሃፍ ቅዱሱ ከ1,400 ዓ.ዓ እስከ 0100 ዓ.ም ድረስ፣ የዛሬ 1,900 አመት ገደማ ተፅፎ ቢያልቅም ነገር ግን ዛሬም ራሱን ከሚያሳድገው ሳይንስና ቴክኖሎጂ እኩል መናገር የቻለ መፅሀፍ ነው፣ እነዚህንም እውነታዎች መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የምናስተውለው ግን የሚከተሉትን ተያያዥ ሰውኛ ውሱንነቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው:-

- መፅሀፉ የሳይንስና የቴክኖሎጂ መማርያ መፅሀፍ ባለመሆኑ መፅሀፉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀቶችን በሰፊው የሚያስተምር አለመሆኑን፣
- ቅዱሳኑ በወቅቱ የተገለጠላቸውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ራዕዮች በነበረው የቋንቋ የቃላት ውሱንነት ምክንያት በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቋንቋ መግለፅ አለመቻላቸውን፣ ለምሳሌ በወቅቱ “አውሮፕላን” የሚባል ሰውኛ ቃል ባለመኖሩ ቅዱሳኑ አውሮፕላንን በራዕይ ሲመለከቱ “አውሮፕላን” የሚለውን በገባቸው መንገድ መግለፃቸውን፣
- በወቅቱ የነበረው ሰውኛ ንቃተ ህሊና ውሱንነት ምክንያት ነገሮችን በደፈናው ተናግሮ የማለፍ ችግር፣ ለምሳሌ በወቅቱ የግራቪቲ ዕውቀት ባይኖርም ነገር ግን መሬት በተፈጠረችበት ቦታ የታሰረችው በዚህ ሀይል መሆኑን በገባቸው መንገድ መግለፃቸውን፣
- መፅሀፉ የተፃፈበት ቋንቋም ሆነ የተተረጎመበት አማርኛ ለአሁኑ ትውልድ “ያረጀ/Old” የመሆኑ እውነታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፣

በዚህም የመፅሀፍ ቅዱሱን የሳይንስና የቴክኖሎጂ እውቀቶች መረዳት የሚቻለው እነዚህን አራት በሰዎች ምክንያት የተፈጠሩበትን ውሱንነቶችን በማስተዋል ነው፣ መፅሀፉ እነዚህ ሰውኛ ውሱንነቶች በሰዎች ምክንያት ይፈጠሩበት እንጂ መፅሀፉን አስተውሎ ላነበበው ሰው ከዘመናዊው ሳይንስና ቴክኖሎጂ እኩል የሚናገር መፅሀፍ ነው፡፡

እዚህ ጋር ሁሉንም መፅሀፍ ቅዱሱ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር አንድ የሚሆንበትን መዘርዘር ባይቻልም ነገር ግን በዚህ ዘመን አዲስ የሆኑና መፅሀፍ ቅዱሱ በተፃፈበት ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ሊያውቁት የማይችሉትና

ልዕለ ስብዕና ያለው አካል ብቻ ሊገለጥላቸው የሚችሉትን ብቻ ወስደን ለምሳሌ ያህል እንመለከታለን፡፡ በዚህም መፅሀፉ ውስጥ ያሉትን

- የቴክኖሎጂ፣
- የተፈጥሮ ሳይንስ፣
- የጤና ሳይንስ፣
- የአካባቢ ጥበቃ ሳይንስን
- የማህበራዊ ሳይንስ

ዘመናዊ አስተምህሮቶቹን እየቀነጨብን እንመለከታለን፡፡

## 1. ቴክኖሎጂ

ከቴክኖሎጂ ትንቢቶች ውስጥ የአውሮፕላንና የኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂን መምጣት የሚናገሩትን ትንቢቶችን ለምሳሌ ያህል እንመልከት፡፡

- **የአውሮፕላን ቴክኖሎጂ**

እስራኤሎች ከአለም ዙሪያ ተሰብስበው ወደ ሃገራቸው የሚመለሱት በአውሮፕላን እንደሆነ ነቢያቱ በራዕይ ተመለከቱ ነገር ግን ይህንን ራእይ ያዩት ነቢያት በዘመኑ የአውሮፕላን ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ "አውሮፕላን" ማለት ስለማይችሉ በገባቸው መንገድ ገለፁት፡-

ኢሳያስ በተለያየ አባባል ገለፀው፣ ኢሳ.18፡1 ላይ "ክንፍ ያላቸው መርከቦች" አለ፣ ክንፍ የሚያገለግለው ለመብረር ነው፣ ለመርከብ ክንፍ ብንሰራለት አውሮፕላን ይመስላል፣ ጥሩ አገላለፅ ነው፣ ይኸው ራዕይ ሲደገምበትም ራዕዩን በተሻለ ገላጭ ቃል ኢሳ.60፡8 "ልጆችሽ ከሩቅ ይመጣሉ … ርግቦች ወደ ቤታቸው እንደሚበርሩ፣ እነዚህ እንደ ደመና የሚበርሩ …" አለ፡፡

ሕዝቅኤልም ይህንን ራዕይ ተመልክቶ የገለፀው በሌላ መንገድ ነው፣ ሕዝ.38፡9 "እንደ አውሎ ነፋስ" አለ፣ ሕዝቅኤል ትኩረቱን ያደረገው ከምስሉ በላይ በአካሄዱና በድምፁ ላይ ነበረ፡፡

እነዚህ ነቢያት "ይህንን ልገልፀው አልችልም"፣ "ማህበረሰቡ የማያውቀውን ስዕፍ ይሳቅብኛል" … ብለው አልተውትም፣ በወቅቱ የነበረው

ማህበረሰብ ቢገባውም ባይገባውም፣ ያዩትን ራዕይ በገባቸው መንገድ ገልፀውታል፣ ዛሬ ግን የአውሮፕላን ቴክኖሎጂን የተመለከተው ይህ ትውልድ መልዕክቱ "እስራኤላውያኑ ወደ ሀገራቸው የሚመለሱት በአውሮፕላን እንደሆነ" መናገሩን በቀላሉ ይረዳል፡፡

- **<u>የዘመናዊ ግብይት ቴክኖሎጂ</u>**

ግብይት ድሮ በአሞሌ ጨው ይፈፀም ነበረ፣ ከዚያ የገንዘብ ኖቶች የግብይት ስርአቱን ተቆጣጠሩት፣ አሁን ደግሞ ከገንዘብ ኖት ጎን ለጎን በግብይት ካርድና በሞባይል ባንኪንግ ግብይት እየተፈፀመ ይገኛል፣ ቀጣዩ ግብይት እንዴት እንደሚከናወን መፅሀፍ ቅዱሱ ይናገራል፡፡

በቀጣዩ ዘመን ግብይት በቀላል ዘዴ ሰውነት ውስጥ በሚቀበር ረቂቅ የሚሞሪ ሲስተም እንዲከናን እንደሚደረግ እየተነገረ ይገኛል፣ ይህንንም የግይት ዘዴ ነቢያቱ በራዕይ ቢመለከቱትም፣ ያዩትን ራዕይ በወቅቱ በነበረው የቋንቋ ውሱንነት ቃል በቃል መግለፅ ባይችሉም በሚገባን ቋንቋ ፅፈውታል፡-

> ራዕ.13፡16-18 "ታናናሾችና ታላላቆችም ባለጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ ... ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይ ሊሸጥ እንዳይችል ..."

ይህ ትንቢት ስለምን እንደሚናገር የሚገባን ዛሬ ቴክኖሎጂውን የተረዳነው ብቻ ነን፣ ቴክኖሎጂውም ዛሬ በሙከራ ላይ የሚገኘውና በኦባማ የጤና ፖሊሲ ላይ የቀረበው፣ በረቀቀ መንገድ በቀኝ እጅ ወይንም በግምባር ውስጥ የሚቀበር ቺፕስ(RFID Chips/Bio chips/micro chips) ቴክኖሎጂ ነው፡፡ በቴክኖሎጂውም ሰዎች የገንዘብ ኖት፣ የመገበያያ ካርድና የሚባይል መገበያያ ስርአትን ሳይጠቀሙ በሰውነታቸው ላይ በሚቀበር ቺፕስ ግብይትን በቀላሉ ይፈፅማሉ፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ እነዚህን ሁለቱን ቴክኖጂዎች እንደሚመጡ መናገሩ ልዕለ ስብዕና ባለው አካል ምሪት መፃፉን ያሳያል፡፡

## 2. የተፈጥሮ ሳይንስ

መፅሀፍ ቅዱሱ በተፃፈበት ወቅት ሰዎች ሊረዱት የማይችሉትን ይባሱኑ በተቃራኒው የሚያስቡትን የዘመናዊ የሳይንስ ዕውቀቶችን አስቀምጦ ነበረ፣ በዚህም የመሬትን ክብነትና የፅንፈ ዓለም (ዩኒቨርስ) ጠፍጣፋነት፣ መሬት በእስፔስ ውስጥ ያላትን አቀማመጥ፣ የሌሎች አለማት(ፕላኔቶች) መኖር፣ የፀሀይ ብርሀን የሚጠፋበት ጊዜ መኖሩን፣ ቁሳዊው ተፈጥሮ የሚጠፋበት ጊዜ መኖሩን(Big Crunch)፣ ፀሀይን ጠጣር አካል አለመሆኗንና የውሀ ዑደት እውቀቶችን ቀጥለን እንመለከታለን፣

- **የመሬት ክብነት (Spherical Earth) እና የዩኒቨርስ ጠፍጣፋነት**

መፅሃፍ ቅዱሱ ውስጥ በድሮ ሰዎች አገላለፅ "ሰማይና ምድር" የሚል ቃል እንመለከታለን፣ "ምድር" የሚለው መሬትን ሲሆን "ሰማይ" የሚለው ደግሞ ከመሬት ውጪ ያሉትን የተለያዩ ቀጠናዎችን ነው፣ እነኚህም ቀጠናዎች፣

- ከባቢ አየር (ዘፍ.1፡20, ሐስ.11፡6 …)
- ከዋክብት ያሉበትን ክልል (ኢሳ.13፡10)
- ከቁሳዊው አለም ውጪ ያለው የመላዕክት መኖሪያ(1ነገ.8፡30,ማቴ.18፡10)
- ከዚያ በላይ ያለው መንበረ ፀባዖት (ማቴ.6፡9, ሮሜ.9፡29)

በዚህም የሰማይን መንፈሳዊ ትርጉም ትተን ቁሳዊውን እውነታ ብቻ ብንመለከት፣ መፅሀፍ ቅዱሱ በጥንታዊው ቋንቋ "ሰማይ" የሚለው ከመሬት ውጪ ያለውን ዩኒቨርስ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ሳይንሱ ምድር ሉል(Sphere) እንደሆነችና ዩኒቨርሱ ደግሞ ጠፍጣፋ እንደሆነ ይነግረናል፣ እንደዚሁ መፅሀፍ ቅዱሱም የመሬትን ሉልነት "የመሬት ክበብ" በማለት (ኢሳ.40፡22), የሰማይን(ዩኒቨርስን) ጠፍጣፋነት ደግሞ "የተዘረጋች(ኢሳ.40፡22, ምሳ.8፡27 …)፣ የምትጠቀለል(ኢሳ.34፡4, ዕብ.1፡10-12)…" በማለት ለያይቶ እንደየ ተፈጥሯቸው ይገልፃቸዋል፡፡

- <u>መሬት በእስፔስ ውስጥ ያላት አቀማመጥ (Earth in Space)</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ ሲፃፍ የነበረው ማህበረሰብ “መሬት ጠፍጣፋ ናት እንዳትወድቅም በድጋፍ ቆማለች” በሚልበት ጊዜ ውስጥ፣ መፅሃፍ ቅዱሱ ደግሞ መሬት ያለድጋፍ በስፔስ ውስጥ ተንጠልጥላ እንዳለች ይናገራል፡-

ኢዮ.26፡7 “… ምድሪቱንም <u>በበታችዋ</u> አንዳች አልባ <u>ያንጠለጥላል</u>፡፡”

መፅሀፉ ምድር ላይ በአይን የሚታይ ማንጠልጠያ በሌለበት ሁኔታ “ያንጠለጠለ” ይላል፣ ይህም የማይታየው ማንጠልጠያ ፕኔቶች እርስ በርስ የተሳሰሩበት “የመሬት ስበት” መሆኑን መረዳት የሚችለው የዛሬው ትውልድ ብቻ ነው፡፡

- <u>የሌሎች ፕላኔቶች(አለማት) መኖር</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ በተፃፈበት ዘመን ሰዎች በአይን ከሚታየው ሰማይና ምድር በላይ መናገር በማይችሉበት ጊዜ ቅዱሳን በተገለጠላቸው እውቀት፣ ሌሎች አለማት(በአሁኑ አነጋገር ፕላኔቶች) እንደነበሩ ተረድተዋል፣ ይህንንም እውነታ አለምን በብዙ ቁጥር በመግለፅ አስረድተዋል፣

- ዕብ.1፡2 “<u>አለማትን</u> በፈጠረበት…”
- ዕብ.11፡3 “<u>ዓለሞች</u> በእግዚአብሄር ቃል እንደተዘጋጁ …”

ይህ በወቅቱ የነበሩት ህብረተሰቦች ሊረዱት የማይችሉት እውቀት ቢሆንም የዛሬው ትውልድ ግን ነብያቱ የተረዱትን እውነታ በደንብ ይረዳል፡፡

- <u>“ሱፐር ኖቫ”</u>

በመጨረሻው ዘመን የፀሀይ ብርሀን እንደሚጠፋ ሳይንሱም መፅሀፍ ቅዱሱም በአንድ አፍ እየተነበዩ ይገኛሉ፣

ማቴ.24፡29 “… ከነዚያ የመከራ ቀናት በኋላ ፀሃይ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ብርሃንዋን ትከለክላለች …”

በማለት፣ የሚገርመው ደግሞ ይህ ሱፐር ኖቫ ከመከሰቱ በፊት ፀሀይ ከፍተኛ ግለት እንደሚፈጠርባት ሳይንሱ ይናገራል፣ መፅሀፍ ቅዱሱም ይህንኑ እውነታ ያመለክታል፣

ኢሳ30፡26 “… የፀሀይም ብርሀን <u>እንደ ሰባት ቀን ብርሀን</u> <u>ሰባት እጥፍ</u> ይሆናል፡፡”

- **<u>ቁሳዊው ተፈጥሮ የሚጠፋበት ጊዜ መኖሩን (Big Crunch)</u>**

ሳይንሱም መፅሀፍ ቅዱሱም አለም ተመልሳ የምትጠፋበት ጊዜ እንዳለ እየተነበዩ ይገኛሉ፡፡

ሳይንሱ አለም በ"ቢግ ባንግ" እንደተፈጠረችው ሁሉ ተመልሳ "ቢግ ክረንች" በሚባለው ሂደት እንደምትጠፋ ይናገራል፣ መፅሀፍ ቅዱሱም ቁሳዊው አለም ሙሉ በሙሉ የምትጠፋበት ጊዜ እንዳለ ይናገራል፣

ራዕ.20፡11"… ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም፡፡"

- **<u>ፀሀይ ጠጣር አካል አለመሆንዋን</u>**

ጥንታዊው ማህበረሰብ ፀሀይን ከምድር በሚመለከትበት ምስልና መጠን፣ ጠጣር ሰማይ ላይ የተለጠፈች አነስተኛ አካል አድርጎ በሚመለከትበት ሁኔታ ውስጥ መፅሀፍ ቅዱሱ ግን በወቅቱ የነበረው ማህበረሰብ ባይቀበለውም ፀሀይ ከመሬት ሆነን በአይን በምንመለከተው መጠን አለመሆኗንና ጠጣር እንዳልሆነች ስለሌላ ነገር በሚያስተምርበት ክፍሉ ላይ ያመለክተናል፣

ራዕ.19፡17-18 "… አንድም መልአክ በፀሀይ ውስጥ ቆሞ …"

- **<u>የውሀ ኡደት</u>**

ጥንታዊው ማህበረሰብ ዝናብ ከሰማይ ውስጥ እንደሚመጣ በሚያስብበት ወቅት መፅሀፍ ቅዱሱ ግን የሚናገረው በሳይንሱ የተማርነውን የውሃ ኡደት ነው፣

መክ.1፡7 "ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባህር ይሄዳሉ፣ ባህሩ ግን አይሞላም፣ ፈሳሾች ወደ ሚሄዱበት ስፍራ <u>እንደገና ወደዚያው ይመለሳሉ</u>፡፡"

- **<u>ከጂሞሎጂስት በቀር ሌላው ሰው የማይረዳው የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል</u>**

መፅሀፍ ቅዱሱን ስናጠና ከጂሞሎጂስት(የቅንጦት ማዕድናት ባለሙያ) በስተቀር ሌላው ሰው ስለ ምን እንደተነገረ የማያውቃቸው ክፍሎች አሉ፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- ዘፀ.28፡17-34 "… በፊተኛው ተራ ሰርድዮን፣ ቶፓዝዮን፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፤ በሁለተኛው ተራ በሉር፣ ሰንፔር፣ አልማዝ፤

በሶስተኛው ተራ ያክንት፣ ኬቴዶን፣ አሜቴስጢኖስ፤ በአራተኛው ተራ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ በወርቅ ፈርጥ ይደረጋሉ … በፍርዱ በደረት ኪስም ውስጥ ኡሪምንና ቱሪምን ታደርጋለህ … በታችኛው ዘርፍ ዙሪያ ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይም ግምጃ ሮማኖች አድርግ፤ በዚያም መካከል በዙሪያው የወርቅ ሻኩራዎች አድርግ፣ የወርቅ ሻኩራ ሮማንም፣ ሌላም የወርቅ ሻኩራ ሮማንም በቀሚሱ ዘርፍ ዙሪያውን ይሆናሉ፡፡"

- ሕዝ28፡13 "በእግዚአብሄር ገነት በኤድን ነበርህ፤ የከበረ ዕንቁስ ሁሉ፣ ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፣ ወርቅ ልብስህ ነበረ …"

- ራዕ.21፡18-21 "ቅጥርዋም ከኢያሰጲድ የተሰራ ነበረ፣ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች፡፡ የከተማይቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጊጦ ነበረ፤ ፊተኛው መሠረት ኢያሰጲድ፣ ሁለተኛው ሰንፔር፣ ሶስተኛው ኬልቄዶን፣ አራተኛው መረግድ፣ አምስተኛው ሰርዶንክስ፣ ስድስተኛው ሰርድዮን፣ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፣ ስምንተኛው ቢረሌ፣ ዘጠነኛው ወራውሬ፣ አሥረኛው ክርስጵራስስ፣ አስራ አንደኛው ያክንት፣ አስራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ፡፡ አስራ ሁለቱም ደጆች አስራ ሁለት እነቁዎች ነበሩ፤ እያንዳንዱም ደጅ ከአንድ እንቁ የተሰራ ነበረ …"

እዚህ ጋር የቀረቡትን ውድ የቅንጦት ማዕድናት ምንነት መረዳት የሚችለው ጂኦሎጂስት ያውም በጄሞሎጂ እስፔሻላይዝ ያደረገ ሰው ብቻ ነው፣ ሌላው በዚህ ትውልድ ያለሰው ቃላቱን ከእንግሊዘኛ መፅሀፍ ቅዱስ ለቅሞ ኢንተርኔት ላይ ካልተመለከተ በቀር ይህንን የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል መረዳት አይችልም፡፡

እነዚህን እውነታዎች ስንመለከት መፅሀፍ ቅዱሱ ምንም እንኳን የሳይንስ መማሪያ መፅሀፍ ባለመሆኑ ሳይንሱን በዝርዝር ባያስተምረንም፣ በአጋጣሚ የነካቸው እውቀቶች ዛሬ በዘመናዊው ሳይንስ ተረጋግጦ ስንመለከት፣ መፅሀፉ ምንም እንኳን በጋርዮሹ ዘመን በሰዎች እጅ ቢፃፍም የዕውቀቱ መነሻ ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

## 3. የጤና ሳይንስ

እዚህ ጋር ሁሉንም መመለከት ባይቻልም ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱሱ በወቅቱ ህብረተሰቡ ከሚያስብበት በተቃራኒ ከዛሬው ሳይንስ በተመሳሳይነት ያስተማራቸውን የጤና መርሆችን እንመልከት፡-

- **የሴቶች ግርዛት አለመፍቀዱ**

የወንዶችን ግርዛት ዛሬ ዘመናዊው ሳይንሱ እንደሚያዘው መፅሃፍ ቅዱሱም "ወንዶች ይገረዙ" ብሎ ያዛል(ዘፍ.17፡10) ነገር መፅሃፍ ቅዱሱ እንደ ሳይንሱ የሴት ልጅ ግርዛትን አያዝም፣ ይህ ደግሞ ጥንታዊ ማህበረሰብ ይቅርና የኛም ማህበረሰብ እንኳን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሴት ልጅ ግርዛትን ሲከውን ከነበረበት እውነታ ጋር ስንመለከተው የሚያስገርም እውነታ ነው፡፡

- **ዘመናዊ የአመጋገብ ስርአት ማስተማሩ**

በዘመናዊው የስነ ምግብ ሳይንስ ሰዎች ቪጂቴሪያን እንዲሆኑና ለስጋ ምግቦች ያላቸውን ፍቅር እንዲቀንሱ ያስተምራል፣ መፅሀፍ ቅዱሱም እንደዚሁ ይመክራል፣

ምሳ.23፡20 "የወይን ጠጅ ከሚጠጡት ጋር አትቀመጥ ለስጋም ከሚሳሱት ጋር፡፡"

በተጨማሪም እንደ ሳይንሱ መፅሀፍ ቅዱሱም ሰዎች ስብና ደም እንዳይመገቡ ያዛል፣

- ዘሌ.3፡17 "ስብና ደም እንዳትበሉ ..."
- ዘሌ.7፡23 "... የበሬ ወይንም የበግ ወይንም የፍየል ስብ ከቶ እንዳትበሉ፡፡"
- ዘሌ.7፡26-27 "በማደሪያዎቻችሁም ሁሉ የወፍ ወይ የእንስሳ ደም ቢሆን አትብሉ፡፡ ደም የሚበላ ሰው ከህዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ፡፡"

መፅሀፉ በወቅቱ የከለከላቸው የአልኮል መጠጥና የስጋ፣ የስብባ የደም ምግብ ጤና ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳት ዛሬ በትምህርት በዝርዝር የተማርናቸው ቢሆንም መፅሀፉ ግን የከለከለው ቀድሞውኑ ነበረ፡፡

ሌላው የመፅሀፍ ቅዱሱ ዘመናዊ አመጋገብ አስትህሮትን የምንመለከተው ለምግብነት የሚውሉትንና ለምግብነት የማይውሉትን ምግቦች በዘረዘረበት በአምስቱ የኦሪት መፅሀፍት ውስጥ ነው፣ ዛሬ የመፅሀፍ ቅዱስ ዕውቀት የሌላቸው ህዝቦች እነዚህን የመፅሀፉን ትዕዛዛት በመተላለፍ የተለያዩ እንስሳትን በመብላት በተለያዩ ጊዜ በዓለም ላይ ለሚነሱ ወረርሽኞች ምንጭ ሆነው እንመለከታለን፡፡

እነዚህም ህዝቦች መፅሀፉ ለምግብነት እንዳይውሉ የከለከላቸውን እባብ፣ ጦጣ፣ ቺምፓንዚ፣ አሳማ፣ ወፍ፣ የለሊት ወፍ … በመመገብ ከእንስሳት ወደ ሰዎች በሚተላለፉ የኮሮና፣ ኢቦላ፣ ሳርስ፣ በርድ ፈሉ፣ ስዋይን ፍሉ … በሽታዎች ሲሰቃዩና ሌሎችንም ህዝቦች አደጋ ውስጥ ሲከቱ እየተመለከትን እንገኛለን፡፡

በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ ጥንታዊ መፅሀፍ ሆኖ ከዘመናዊው ሳይንስ እኩል መናገሩ መፅሀፉ ላይ የልዕለ ስብዕና አካልን እጅ እንመለከትበታለን፡፡

## 4. <u>የአከባቢ ጥበቃ ሳይንስ</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ፣ እንደ ሳይንሱ፣ ሰዎች ለሚኖሩበትና ለሚጠቀሙበት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንዲያደርጉ ያስተምራል፣ ይህም አስተምህሮ ከፍጥረት ታሪክ የሚነሳና አዳም ሲፈጠር የተሰጠው ዋናው ስራ ነበረ፣ "ኤደን ገነትን ይጠብቃትና ያበጃት ዘንድ"(ዘፍ.2፡15)፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ዛሬ በአካባቢ ጥበቃ ሳይንሱ ላይ እንደ አዲስ የምንማረው መሬትን እያሳረፉ ማረስ (Fallow farming) ስርአትን መፅሀፍ ቅዱሱ ቀድሞ ሲያስተምር ነበረ(ዘሌ.25.3-8)፡፡

የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይም ሲሪየስ በመሆኑ ዛሬ አለማቀፋዊ ችግር ሆኖ እንመለከተዋለን፣ እንደዚሁ መፅሀፍ ቅዱሱም ጉዳዩን አጠንክሮ ነው የሚመለከተው፣ ይህም ሰው ወደ ምድር ሲመጣ የተሰጠ የመጀመሪያ ትዕዛዝ ከመሆን አልፎ በምድርም ላይ ጉዳት የሚያደርሱ በመጨረሻው ዘመን እንደሚጠፉ እስከ መናገር ይደርሳል(ራዕ.11፡18)፡፡

## 5. ማህበራዊ ሳይንስ

መፅሀፍ ቅዱሱ ጥንታዊ መፅሀፍ ሆኖ ሳለ በውስጡ የዘመናዊውን ማህበራዊ ሳይንስ አስተምህሮቶችን ይዞ እንመለከታለን፣ ለምሳሌ ያህል ብንመለከት፣

- የህግ የበላይነት መሠረታዊ መርሆች፣
- ሳይኮሎጂው፣ የፖለቲካ ሳይንሱ፣ ሂውማኒቲና መሰሎቹ የዕምነት ተቋማት አዲስ አድርገው የሚያስተምሩት "የአሽናፊ ስነልቦና" እና የመልካም ማህበራዊ ህይወት መርሆች፣
- የዘመናዊው አመራር ሳይንስ መሠረታዊ መርሆችን

ቀድሞ ሲያስተምር እንመለከታለን፣ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### ➢ የህግ የበላይነት

አንድ ማህበረሰብ(ሀገር) ሰላም የሚያገኘው የህግ የበላይነት ሲሰፍን ብቻ ነው፣ መፅሀፍ ቅዱስ የህግ የበላይነትን ሲያስተምር የነበረው ከብዙ ሺ ዘመናት በፊት ነበረ፣ በዚህም በመጀመሪያ ዋነኞቹ ህጎች አትግደል፣ አታመንዝር … የሚሉት አስርቱ ትዕዛዛት ሲወርዱ በተከታይነትም ብዙ ህጎች በማውረድ ሰዎችም በህግ የበላይነት እንዲኖሩ ሲያስተምርና ህግን የሚተላለፉ እንዲቀጡ ሲያደርግ ነበረ፡፡ ዘመናዊው ህግ የሚመራበት መዋቅራዊ አደረጃጀት ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ጠበቃ እና ዳኛ የተባለው አሰራርም ቀድሞ በመፅሃፍ ቅዱሱ ላይ የተመለከቱ የፍትህ ስርአት አደረጃጀቶች ናቸው፡፡

ዘመነኛው ህግ አንድን ወንጀል "ወንጀል" ለመሆን "ዕቅዱ በመጀመሪያ በአዕምሮ ይሰራል፣ ከዚያ በኋላ ነው ወንጀሉ በድርጊት የሚፈፀመው" በማለት ሰዎች በአመለካከት እንዲለወጡ ያስተምራል፣ መፅሀፍ ቅዱስም በዚህ መንፈስ ይባሱኑ ከዚህ በተሻለ መንገድ ሰዎች ከህጉ በላይ አእምሮአቸውን "በፍቅር መርህ" ካነፁ ወንጀል የሚባል እንደማይኖር ያስተምራል፡፡

- ገላ.5፡14 “ህግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈፀማልና፣ እርሱም “ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ”
- ማር.12፡31 “… ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ … ከነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትዕዛዝ የለችም፡፡”
- ሮሜ.13፡10 “ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፣ ስለዚህ ፍቅር የህግ ፍፃሜ ነው፡፡”
- ማቴ.7፡12 “እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ህግም ነቢያትም ይህ ነውና፡፡”

በዚህም የመፅሀፍ ቅዱሱ የህግ ፍልስፍና በጥንታዊያኑ ሰዎች የተፃፈ ቢመስልም፣ በውስጡ ግን ጊዜ የማይሽረው የህግ ፍልስፍና መያዙ፣ ከፀሀፊዎቹ በስተጀርባ ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መኖሩን ያሳያል፡፡

➢ <u>የዘመናዊው አመራር ሳይንስ መሠረታዊ መርሆችን ቀድሞ ማስተማሩ</u>

አሁን ያለው ዘመናዊው የአመራር ሳይንስ በዋናነት የሚያስተምረው መዋቅራዊ አሰራር፣ ያልተማከለ አስተዳደርና የመልካም አስተዳደር ዕሴቶችን ነው፣ ይህ ዘመናዊ ዕውቀት ከ3,500 አመታት በፊት በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ በጥንታዊው ቋንቋ ተቀምሮ እንመለከታለን፣ ይህንም ቀመር በቅዱሳኑ፣ በሙሴና በአማቱ ካህኑ ዮቶር(ዘፀ.18፡1) እንዲሁም በኢየሱስና በደቀ መዛሙርቱ መካከል በነበረው ንግግር ውስጥ እንመለከታለን፣

ዘፀ.18፡14-24 “… የሙሴ አማት ሙሴን … ህዝቡ ሁሉ ከጠዋት ጀምሮ እስከማታ ድረስ በዙሪያህ ቆመው ሳሉ አንተ ብቻ ስለ ምን ተቀምጠሃል? አለው፣ ሙሴም አማቱን … በዚህና በዚያ ሰው መካከል እፈርዳለሁ፣ የእግዚአብሄርንም ስርአትንና ህግ አስታውቃቸዋለሁ አለው፡፡ የሙሴም አማት አለው፡፡ አንተ የምታደርገው ይህ መልካም ነገር አይደለም፡፡

… ከህዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን፣ እግዚአብሄርን የሚፈሩትን፣ የታመኑ የግፍንም ረብ የሚጠሉትን ሰዎች <u>ምረጥ</u>፤ ከእነርሱም የሺ አለቆችን፣ የመቶ አለቆችን፣ የሀምሳ አለቆችን የአስር አለቆችን <u>ሹምላቸው</u>፡፡ በህዝቡ ላይ ሁል ጊዜ <u>ይፍረዱ</u>፤ <u>አውራውንም</u> ነገር ሁሉ ወዳንተ ያምጡ፣

ታናሹንም ነገር ሁሉ እነሱ ይፍረዱ፣ እነርሱም ከአንተ ጋር ሸክሙን ይሸከማሉ፣ ለአንተም ይቀልልሀል፡፡ ሙሴም ... ያለውን ሁሉ አደረገ፡፡”

እዚህ ጋር ምንም እንኳን አገላለፁ ጥንታዊ ቢሆንም፣ በውስጡ ግን ዋነኛውን የዘመናዊውን የአመራር መርህ እንመለከታለን፣ ይህም የአመራርነት ስራ በአግባቡ የሚሰራው በመጀመሪያ ህዝቡን በተለያየ መዋቅራዊ አደረጃጀት መከፋፈል፣ ከዚያ በአደረጃጀቶቹ ላይ ብቃት ያላቸውን አለቆችን መሾም፣ ከዚያ አለቆቹ እስከየት ድረስ ያለውን ውሳኔ መወሰን እንደሚችሉ የስራ ድርሻቸውን ገድቦ መስጠት፣ የትኞቹን ጉዳዮች ደግሞ ለበላይ አካል እንደሚያቀርቡ ማሳየት ... ይህ በጋርዮሽ ዘመን የተነገረ መርህ በዛሬው የዘመናዊው የሊደርሺፕ ሳይንስ መሠረት ነው፡፡

በኢየሱስ የመሪነት ህይወት ውስጥም ሌላ ዘመናዊ የመሪነትን ሳይንስ መሠረታዊ ሀሳብ እንመለከታለን፣ ይህም፣ መሪ ከንጉስነት ይልቅ በአገልጋይነት መንፈስ መስራት እንዳለበት፣

ዮሐ.13፡13-17 “(ኢየሱስም) እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ፡፡ እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡ እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና ... ይህን ብታውቁ ብታደርጉትም ብፁአን ናችሁ፡፡”

ኢየሱስ መሪ እንደመሆኑ መጠን ለተከታዮቹ ያስተማረው በያዙት ስልጣን ራሳቸውን እንዲኮፍሱ ሳይሆን በነሱ አገልግሎት ለሚገለገለው ማህበረሰብ ወርደው ማገልገል እንዳለባቸው ነው፣ ዛሬ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ እያደገ የመጣው የመሪነት ሳይንስም ይህንን “የደንበኛ ንጉስነት” እውነታ አዲስ አድርጎ እያስተማረ ይገኛል፡፡

መፅሀፉ ከነዚህ መሠረታዊ የአመራር መርሆች በተጨማሪም እያንዳንዱ ሰራተኛ ምን አይነት ባህሪዎችን መላበስ እንዳለበት ዘመናዊውን የመልካም አስተዳደር ዕሴቶችንም ያስተምራል፣

- <u>የመልካም አስተዳደር ዕሴቶች</u>
  ቅንነት(ምሳ.28፡18)፣ ታማኝነት(ቲቶ.2፡9-10)፣ አለማዳላት (ዘዳ.24፡17፤ ዘዳ.27፡19)፣ ታታሪነት(ቆላ.3፡23-2) …
- <u>ሰራተኞች በታማኝነት፣ ያለምንም ስህተትና በደል፣ ሰአት ባለማርፈድ እንዲሰሩ በቅዱሳኑ የህይወት ምሳሌ ማስተማሩና ሰራተኞች "አለቃ አየኝ አላየኝ" ሳይሉ የሚሰሩት ለፈጣሪ እንደሆነ አድርገው እንዲሰሩ ማስተማሩ</u>
  - ዳን.6፡4 "… ነገር ግን (ዳንኤል) የታመነ ነበረና ስህተትና በደል አልተገኘበትም …"
  - ኤር.46፡17 "… ሰአቱን የሚያሳልፍ ጉረኛ ብለው ጠሩት፡፡"
  - ቆላ.3፡23-2 "ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፣ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፣ ከጌታ የርስት ብድራትን እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና፡፡ የሚበድልም የበደለውን በብድራት ይቀበላል፣ ለሰው ፊትም አድልዎ የለም፡፡"
- <u>ሙስናን መከልከሉ</u>
  - ሉቃ.3፡14 "… <u>ደመወዛችሁም ይብቃችሁ</u> …"
  - መዝ.50፡17-21 "አንተስ ተግሳፄን ጠላህ፣ ቃሎቼን ወደኋላ ጣልህ፣ <u>ሌባውን ባየህ ጊዜ ከእርሱ ጋር ትሮጥ ነበር</u> …"

ይህ የዘመናዊው የአመራር ሳይንስ በጋርዮሹ ዘመን በተፃፈ መፅሀፍ መቅረቡ መፅሀፉ ልዕለ ስብዕናነት ያሳያል፡፡

- **ሳይኮሎጂው፣ የፖለቲካ ሳይንሱ፣ ሂውማኒቲና መሰሎቹ የዕምነት ተቋማት አዲስ አድርገው የሚያስተምሩት “የአሸናፊነት ስነልቦና” እና የመልካም ማህበራዊ ህይወት መርሆች**

መፅሀፍ ቅዱሱ ቀድሞ ያስተማረው ዕውቀት ዛሬ ሳይኮሎጂው፣ ፖለቲካው፣ የሂውማኒቲና መሰሎቹ የዕምነት ተቋማት በዘመናዊው ቃላት ከሽነው “ሰዎች መልካም አስተሳሰብን (positive mind/positive energy ...) ቢያዳብሩ በህይወታቸው ስኬታማ ይሆናሉ፣ እድሜያቸው ይረዝማል፣ ከጭንቀት፣ ዲፕሬሽን፣ ከኢንዲቪጁዋሊዝም፣ ዕንቅልፍ ከማጣት ... ችግሮች ነፃ ይሆናሉ፣ ማህበረሰቡም ሰላማዊ፣ ልማታዊ ... ይሆናል” ይላሉ፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ሰዎች የ“positive mind” ጥግ የሆነውን የፈጣሪ ማንነት እንዲለማመዱ ያስተምራል፣ የሰው ልጅ በሃጢያት ወድቆ ለሰይጣን ትምህርቶች ከመጋለጡ በፊት፣ በውስጡ የነበረው ይህ ዛሬ “የአሸናፊነት ስነልቦና” የምንለው ስነልቦና ነበረ፤ ለዚህም ነው ፈጣሪ ሰዎችን ወደ ገነት ለመመለስ እቅድ ሲያወጣ ኢየሱስን በመላክ ሰዎች ይህንን ስነልቦና ወደ ቦታ እንዲመልሱ የሚያስተምረው፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ሁለት “አዳሞች” አሉ “ፊተኛው አዳም” እና “ኋለኛው አዳም”፣ የፊተኛው አዳም በኃጢያት በመውደቁ ዘሩን በሙሉ ሀጢያተኛ ማንነትን አወረሰ፣ ሀጢያተኛ ደግሞ ገነት ስለማይገባ የሰው ልጅ ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል መግባቱ ግዴታ ሆነ(ማቴ.25፡41)፣ ከዚያም ፈጣሪ ሰዎችን ወደ ገነት እንዲመለሱ እቅድ ሲያወጣ ኋለኛው አዳም(ኢየሱስ) ላከ፣ ኢየሱስም ልክ ኮራፕት የሆነ ኮምፒውተር በአንቲ ቫይረስ እንደሚታደሰው በፊተኛው አዳም ምክንያት ኮራፕት የሆነውን የሰውን ማንነት በራሱ የፍቅር አስተምህሮ ሊያድስ መጣ፣ በዚህም ሰዎች ኋለኛውን አዳም(ኢየሱስ) ሲቀበሉ በመሠረታዊው የፍቅር አስተምህሮ የአስተሳሰብ ለውጥ(paradaim shift) ይታደሳሉ፡፡

ይህ የአስተሳሰብ ለውጥም ከመሠረታዊው የፍቅር መርህ እስከ “አብዛኞቹ ክርስቲያኖች” የማይቀበሉት “አጋፔ” የሚባለው፣ ደግነት ያለ ምንም መስፈርት መደረግ እንዳለበትና ሰዎች ጠላቶቻቸውን በፍቅር እንዲያሸንፉ የሚያስተምረውን የፍቅር መርህ ድረስ ነው፣ አጋፔ ማለት የሚወዷቸውን መውደድ ሳይሆን በጠላትነት የተነሱባቸውን (ማቴ.5፡44-

45)፣ በጥላቻ ስሜት የሚመለከቷቸውን (ሉቃ.6፡27)፣ የሚረግሙአቸውን (ማቴ.5፡44-45)፣ የማያውቁትን (ሉቃ.10፡30-35) ... መውደድ ማለት ነው፡፡

እነዚህን የኢየሱስ የአጋፔ አስተምህሮቶችን ለምሳሌ ያህል ብንመለከት፣

- ማቴ.5፡39-48 "... ክፉውን አትቃወሙ ዳሩ ግን ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፣ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናፀፊያህን ደግሞ ተውለት፣ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ፡፡ ለሚለምንህ ስጥ፣ ከአንተም ይበደር ዘንድ ለሚወድ ፊቀቅ አትበል ... የሚረግሙአችሁንም መርቁ ለሚጠሏችሁ መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዷችሁ ፀልዩ ... እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ እናንተ ፍፁማን ሁኑ፡፡"
- ሮሜ.12፡14-20 "... የሚያሳድዷችሁን መርቁ፣ መርቁ እንጂ አትርገሙ ... ጠላትህ ቢራብ አብላው፣ ቢጠማ አጠጣው ..."

ሌሎች የመፅሀፍ ቅዱሱን የ"positive mind" ጥግ አስተምህሮቶችን አጠር አጠር አድርገን ብንለከት፣

➢ <u>ሰዎች በፍቅር መርህ እንዲኖሩ ማስተማሩ</u>
  - ገላ.5፡14 "... ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ..."
  - ሮሜ.13፡10 "ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ..."
  - 1ቆሮ.10፡24 "እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ፡፡"
  - ማቴ.7፡12 "እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ህግም ነቢያትም ይህ ነውና፡፡"
  - ኤፌ.5፡33 "... እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፡፡"

➢ <u>ሰዎች የበደሉዋቸውን "ይቅር እንዲሉ" ማስተማሩና ቂም በቀልን መከልከሉ</u>
  - ማቴ.6፡12 "እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፡፡"

- ማቴ.6፡15 “ለሰዎች ግን ሀጢያታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ሀጢያታችሁን ይቅር አይላችሁም፡፡”
- ሮሜ.12፡17-19 “ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ … ራሳችሁ አትበቀሉ፣ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፣ በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ …”
- 1ተሰ.5፡15 “ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ …”

➢ <u>ሰዎች መልካም ባህሪ እንዲላበሱ ማስተማሩ</u>
- ሮሜ.12፡21 “ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ፡፡”
- ማቴ.5፡5-9 - የዋህነት፣ መሀሪነት፣ ልበ ንፁህነት፣ ማስታረቅ …
- ገላ.5፡22 - ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ ራስን መግዛት …
- ያዕ.3፡17 - ታራቂ፣ ገር፣ እሺ ባይ፣ በጎ ፍሬ የሞላባት ጥርጥርና ግብዝነት የሌለበት …
- ቲቶ.1፡7 - የማይኮራ፣ የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ
- ኤር.17፡11, ዕብ.13፡5 - ሰዎች ስግብግብ እንዳይሆኑ
- ማር.10፡24 - ሰዎች በገንዘብ እንዳይታበዩ

➢ <u>ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን እንዲደግፉና ያላቸውን ተካፍለው እንዲኖሩ ማስተማሩ</u>
- ማቴ.25፡35 - የተራቡትን ማብላት፣ የተጠማን ማጠጣት፣ እንግዳን መቀበል፣ የታረዘን ማልበስ፣ የታመመን መጠየቅ፣ የታሰረን መጠየቅ…
- ያዕ.1፡27 “… ወላጆች የሌላቸውን ልጆች፣ ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ …”
- ምሳ.19፡17 “ለድሀ ቸርነት የሚያደርግ ለእግዚአብሄር ያበድራል፡፡”

➢ <u>ሰዎች እንዲሰሩ ማበረታታቱና ስንፍናን መቃወሙ</u>
- ሮሜ.12፡11 “ለስራ ከመትጋት አትለግሙ …”
- 2ተሰ.3፡10 “… ሊሰራ የማይወድ አይብላ …”
- ምሳ.12፡27 “… ለሰው የከበረ ሀብት ትጋት ነው፡፡”
- ምሳ.19፡3 “የሰው ስንፍና መንገዱን ታጣምምበታለች …”
- ምሳ.20፡4 “ታካች ሰው በብርድ ምክንያት አያርስም፤ ስለዚህ በመከር ይለምናል …”

- መክ.4፡5 “ሰነፍ እጆቹን ኮርትሞ ይቀመጣል፤ የገዛ ስጋውንም ይበላል፡፡”

- <u>ሰዎች በያዙት ነገር የአላማ ፅናት እንዲኖራቸውና ወላዋይ እንዳይሆኑ ማስተማሩ</u>

  - ሀጌ.1፡7 “... ልባችሁን በመንገዳችሁ ላይ አድርጉ፡፡”

  ተመሳሳይ ሃሳቦችም በዘዳ.31፡7, ዘዳ.31፡23, ኢያ.1፡6 ... ላይ እንመለከታለን፡፡

- <u>ከጠንካራ ሰራተኛነትና ከአላማ ፅናት ባለፈ መጨነቅ እንደማያስፈልግ ማስተማሩ</u>

  ማቴ.6፡27 “ከናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማነው?

- <u>አማኞች “ኦፕቲሚስት” እንዲሆኑና ነገሮችን ከበጎ እንዲመለከቱ ማስተማሩ</u>

  ሮሜ.8፡28 “እግዚአብሄርን ለሚወዱት እንደ ሀሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፡፡”

በዚህም ዛሬ አዲስ የሚመስሉን የሳይኮሎጂ፣ የፖለቲካው፣ የሂውማኒቲ የፍቅር መርህ፣ የእርስ በርስ እንዋደድ፣ እንረዳዳ፣ ጠንክረን እንስራ፣ በጎ አመለካከት ይኑረን፣ ጭንቀትን እናስወግድ ... ትምህርቶች በሙሉ በዘመናዊው ቋንቋ ተከሽነውና ተብራርተው ይምጡ እንጂ የመፅሀፍ ቅዱሱ የስኬታማ ኑሮ መሠረታዊ መርሆች ናቸው፡፡

በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ በጋርዮሽ ዘመን በሰዎች እጅ ቢፃፍም ነገር ግን ዛሬ ላይ አዲስ መስለው ከሚመጡት አስተምህሮዎች እኩል መናገር መቻሉ መፅሀፉን ያፃፈው ልዕለ ስብዕናነት ያለው አካል መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት መፅሀፍ ቅዱሱ ጥንታዊ መፅሀፍ ሆኖ ነገር ግን ከዘመናዊው የተፈጥሮ ሳይንስ፣ ከቴክኖሎጂው፣ ከጤና ሳይንሱ፣ ከአከባቢ ጥበቃና ከማህበራዊው ሳይንስ እኩል መናገሩ ምን እንኳን መፅሀፉ መጋርዮሽ ዘመን ቢፃፍም ፀሀፊዎቹ ሲፅፉት የነበረው እውቀት ልዕለ ስብዕና ባለው አካል መሪነት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 1.4.2.3. የትንቢቱ ተጨባጭነት ባለፈው፣ በአሁኑና በሚመጣው ዘመን መረጋገጡ

መፅሃፍ ቅዱስ ከሌሎች መፅሀፍት የሚለየው ተራማጅነቱ ነው፣ መፅሀፉ ከያዘው አጠቃላይ እውነታ በተጨማሪ ለየትውልዱ ለይቶ የሚናገረው መልዕክት አለው፣ ይህም በትንቢቶቹ ሲሆን ትንቢቶቹም ባለፈውና በዚህ ትውልድ የተረጋገጡ፣ ለመጪው ትውልድም ተጨባጭ መሆናቸውን ስንመለከት መፅሀፉ በሰዎች እጅ ይፃፍ እንጂ ያፃፈው ልዕለ አእምሮአዊ አምላክ መሆኑን ያሳያል፡፡

### 1. በቀደመው ትውልድ የተረጋገጡ

ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም ለምሳሌ ያህል ክርስቲያኖች የሚናገሩትን የኢየሱስ ታሪክ ብንመለከት፣

| ተቁ | የተነገረው ትንቢት | የተነገረበት ቦታ | የተነገረበት ጊዜ approx.) | የተፈፀመበት ዘመን ቦታ | የተፈፀመበት ዘመን ጊዜ | የዘመን ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከድንግል እንደሚወለድ | ኢሳ.7፡14 | 710ዓ.ዓ | ማቴ.1፡23 | 33ዓ.ዓ | 677 |
| 2 | አሳልፎ የሚሰጠው ነው የሚከፈለው 30 ብር መሆኑ | ዘካ.11፡12 | 470 ዓ.ዓ | ማቴ.26፡15 | 000 | 470 |
| 3 | ልብሱን ሰዎች እንደሚከፋፈሉት | መዝ.22፡18 | 1000ዓ.ዓ | ዮሐ.19፡23 | 000 | 1000 |
| 4 | እጅና እግሩ እንደሚቸነከር | መዝ.22፡16 | 1000ዓ.ዓ | ዮሐ.20፡25 | 000 | 1000 |
| 5 | ጎኑ እንደሚወጋ | ዘካ.12፡10 | 470ዓ.ዓ | ዮሐ19፡34 | 000 | 470 |
| 6 | በሀብታሞች መቃብር እንደሚቀበር | ኢሳ.53፡9 | 710 ዓ.ዓ | ማቴ27፡57-60 | 000 | 710 |
| 7 | ከሞት እንደሚነሳ | መዝ.16፡10 | 1000ዓ.ዓ | ሐስ.2፡31 | 000 | 1000 |

በዚህም የጥንቱ ነብያት ስለመሲሁ እንደተነበዩት ከብዙ አታት በኋላ ትንቢቱ ተፈፅሟል፣ የሚገርመው ደግሞ ከነዚህ ትንቢቶች ዋነኛው ትንቢት፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ "ተፈፀመ" ያለበትንና አዲስ ዘመን የተጀመረበትን ጊዜ፣ ሳይንሱም ሳያውቀው ያውቀዋል፣ ሳይንሱ ዘመንን የሚቆጥርበት ካሌንደር መነሻ ይህንኑ በመስቀሉ ላይ የተፈፀመውን ድርጊት መነሻ በማድረግ ነው፡፡

**2. <u>በዚህ ትውልድ የተረጋገጡ</u>**

በአሁኑ ዘመን እየተፈፀሙ ያሉ ብዙ ትንቢቶች አሉ፣ ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም አንኳር የሆኑትን በሀገራት ደረጃ ያሉትን ክስተቶች ለይተን እንመለከታለን፣ በዚህም ከሶርያ፣ ቱርክ፣ ኢትዮጵያንና የተባበሩት መንግስታት ጋር በተያያዘ የተነገሩትን ትንቢቶችና እየተከናወኑ ያሉትን ድርጊቶች እንመለከታለን፡፡

- **<u>ሶርያ</u>**

ማርች 15, 2011 በሰላማዊ ሰልፍ የተጀመረው የሶርያ አብዮት በሂደት ከቁጥጥር ውጪ እየወጣ ብዙ ሀይላትን በተቃራኒ ቡድን እያሳለፈ በተለይ ከ2013 ጀምሮ በሀገሪቱና በህዝቦቿ ላይ ብዙ ውድመትን ይዞ መጣ፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ይህንን ውድመት ከነጊዜው ጭምር አስቀድሞ ተናግሯል፣

ኢሳ.7፡8 "የሶርያ ራስ ደማስቆ ነው፣ የደማስቆም ራስ ረአሶን ነው፣ በስድሳ አምስት ዓመት ውስጥ ኤፍሬም ይሰባበራልና ሕዝብ አይሆንም፤"

ኢሳ.17፡1-2 "ስለ ደማስቆ የተነገረ ሸክም፡፡ እነሆ ደማስቆ ከተማ ከመሆን ተቋርጣለች፤ ባድማና የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች፡፡ ከተሞቿ ለዘላለም የተፈቱ ይሆናሉ ..."

እነዚህ ነብዩ ኢሳያስ ከ2,000 አመታት በፊት ስለ የሶርያ(ደማስቆ) ውድመት የተናገረው ትንቢቶች ናቸው፣ ኢሳያስ ትንቢቱን "ስድሳ አምስት አመት ውስጥ" ያለው የእስራኤል ምስረታን 1948ን መነሻ በማድረግ ነው፣ ከእስራኤል ምስረታ ቦሀላ 65 አመታትን ስንቆጥር የሶርያ ነገር ከሶርያውያን እጅ ወጥቶ በውጪ ሀይላት እጅ የወደቀበትና ፍፁም ውድመት፣ እልቂት፣ ስደት ... መከናወን የጀመረበት ጊዜ ነው፡፡

- <u>ቱርክ</u>

ቱርክ ለእስራኤል ካላት ጂኦግራፊያዊ ቀረቤታ አንፃር ሐዋርያቱ ብዙ ጊዜ ጎብኝተዋታል፣ ቤተክርስቲያንም መስርተውላታል ነገር ግን በወቅቱ ሐዋርያቱ በተለያዩ አካባቢዎች ከመሰረቷቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተሳሳተ አሰራር በመከተላቸው ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ሰባቱ የኢሲያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ የቱርኳ የኤፌሶን ቤተክርስትያን ነበረች፣ የተሰጣትም ማስጠንቀቂያ፣

ራዕ.2፡1-5 "በኤፌሶን ወዳለው ቤተክርስቲያን … ንስሀም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ፡፡"

እንደ መፅሀፍ ቅዱሱ "መቅረዝ" ማለት "ወንጌል" ማለት ነው፣ በዚህም <u>እንደ ክርስትናው አገላለፅ</u> ቤተክርስቲያንዋ በተነገራትን ማስጠንቀቂያ ባለመመለሷ መቅረዝዋ ከስፍራው ተወስዶባት የአውሮፓ ብቸኛዋ የሰለመች ሀገር ሆናለች፡፡

- <u>ኢትዮጵያ</u>

ኢትዮጵያ ሀያልና ትዕቢተኛ ሀገር ነበረች፣ በዚህም በድሮው ዘመን ግዙፍ የጦር ሰራዊት ነበራት፣

2ዜና.14፡9-13 "ኢትዮጵያዊውም ዝሪ አንድ ሚሊዮን ሰዎችና ሶስት መቶ ሰረገሎች ይዞ ወጣባቸው፣ ወደ መሪሳም መጣ፣ አሳም ሊጋጠመው ወጣ፣ በመሪሳ አጠገብ ባለው በፅፋታ ሸለቆ ውስጥ ተሰለፉ፡፡ አሳም አቤቱ በብዙም ሆነ በጥቂቱ ማዳን አይሳንህም፣ አቤቱ አምላካችን ሆይ ባንተ ታምነናልና በስምህም <u>በዚህ ታላቅ ወገን ላይ</u> መጥተናልና እርዳን፣ አቤቱ አምላካችን አንተ ነህ፣ ሰውም አያሸንፍህ ብሎ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሄር ጮኸ፡፡ <u>እግዚአብሄርም በአሳና በይሁዳ ፊት ኢትዮጵያውያንን መታ፣ ኢትዮጵያውያንም ሸሹ፡፡</u> አሳም ከእነሱ ጋር ያለው ህዝብ እስከ ጌራራ ድረስ አሳደዱዋቸው፡፡"

ይህ የኢትዮጵያ የትዕቢተኝነት ታሪክ የጥንት ዘመን ታሪክ ብቻ አይደለም፣ መፅሀፍ ቅዱሱ በደርግ ጊዜ የነበረውን ትዕቢትም ቀድሞ

ተናገሯል፣ ይህ ቃል የተነገረው ከቤተእስራኤላውያኑ ወደ ሀገራቸው የመመለስ ታሪክ ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ይህንን እውነታ በደንብ ለመረዳት በመጀመርያ ቅድመ ታሪኩን እንመልከት፣ ለእስራኤል ቤተ እስራኤላውያንን ከአለም የማሰባሰቡ ስራ ያን ያህል ከባድ ስራ አልነበረም ነገር ግን ምንም ጠላትነት ካልነበራት ኢትዮጵያ ማስወጣቱ  ያልተጠበቀ ከባድ ስራ ነበረ፣ ደርግ ያለምንም ምክንያት ቤተእስራኤላውያኑ ከኢትዮጵያ "አይወጡም" የሚል አቋም ያዘ፡፡

በዚህም በወቅቱ በተለይ በ"ኦፕሬሽን ሞሰስ" ብዙዎቹ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የተደረጉት በድብቅ በሱዳን በኩል በእግር ስለነበረና በሱዳን ከነበረው ማከማቻ ካምፕም ችግር የተነሳ ብዙ ሰዎች አለቁ፣ "ኦፕሬሽን ሰለሞን" ደግሞ የተደረገው በአደጋ ጥላ ስር ነበረ፣ ይህም ህወሀት አዲስ አበባን ከቦ በነበረበት፣ የደርግ ሰራዊት በቦሌ አውሮፕላን ጣብያ ላይ እገዳ በጣለበትና የወያኔ አየር መቃወሚያዎች የአዲስ አበባን ሰማይ ወጥረው በያዙበት ሁኔታ ውስጥ ነበረ፡፡

በዚህም ሞሳድም(የስለላ ድድርጅቱ) ዜጎቻቸውን ከኢትዮጵያ ያስወጡበት ኦፕሬሽኖችን እንደ ተአምር ነው የሚመለከተው፡፡

ነገር ግን እስራኤላውያኑን ወደ ሀገራቸው የማሰባሰብ ስራ ውስጥ ከኢትዮጵያ የማስወጣቱ ስራ ከባድ እንደሚሆን ቀድሞ መፅሀፍ ቅዱሱ በኢሳ.43፡5 ላይ ጠቆም አድርጎ ነበረ፣ ይህንን ለመረዳት በመጀመሪያ እስራኤላውያን ተሰደው የነበሩበት ሀገራት ከእስራኤል ጋር ያላቸውን አቀማመጥ ስንመለከት ደቡብ የተባለችው ኢትዮጵያ ናት፡፡

> ኢሳ.43፡5-6 "እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፣ ዘርህንም ከምስራቅ አመጣዋለሁ፣ ከምዕራብም አሰበስበዋለሁ፣ ሰሜንን መልሰህ አምጣ(እላለሁ)፣ ደቡብንም <u>አትከልክል</u>፡፡"

እዚህ ጋር ደቡብን ለይቶ "አትከልክል" ማለቱና የደርግ <u>ያለ ምክንያት መከልከል</u> ቀድሞ በትንቢት የተጠቆመ እውነታ ነበረ፡፡

ሌላ ኢትዮጵያን በአለም በሀገር ውስጥ ተፈናቃይ ብዛት አንደኛ ያደረገውን የዘረኝነት ችግር ምንጭ ቀድሞ በትንቢት የተነገረ እውነታ እንመልከት፣

መክ.8፡9 "… ሰው ሰውን ለመጉዳት ገዢ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡"

ዛሬ ኢትዮጵያ ላይ ሰዎች የሚሾሙት በውስጣቸው ባለው የጥላቻና የበቀል መንፈስ ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ግን ይህ አሰራር አለም ላይ እንደሚመጣ አስቀድሞ የተናገረ ቢሆንም በዚህ ቃል በአንደኛነት የተጎዳችው ኢትዮጵያ መሆኗን ስንመለከት ደግሞ ያሳዝናል፡፡

- <u>**የተባበሩት መንግስታት ድርጅት**</u>

ከኢየሱስ መወለድ ከ160 አመታት በፊት የተፃፈው መፅሀፈ ዳንኤል ምዕራፍ 2 ላይ ስለ አለማቀፋዊ መንግስታት ታሪክ እንመለከታለን፣ ከነገስታቱ ውስጥ የመጨረሻው በምድር ሁሉ ላይ ስለሚገዛው መንግስት ሲናገር፣ ይህ መንግስት ከሌሎቹ ነገስታት በተለየ ጠንካራ እንደሚሆን ነገር ግን መንግስቱ "የሸክላና ብረት" ድብልቅ እንደሆነ ይናገራል፣ ይህ "ሸክላና ብረት" ጠንካራና ደካማ መንግስታት አደባልቆ እየመራ ያለው የተባበሩት መንግስታት ታሪክ ነው፡፡

የሚገርመው ደግሞ ይህ መንግስት የሚወድቀው በእስራኤል ላይ ጦር በማዝመቱ ምክንያት መሆኑ፣ በዚህም አደገኛ ጦርነት ምክንያትም የአለም መንግስት ፍፃሜ እንደሚመጣና የኢየሱስ መንግስት ምስረታ እንደሚጀመር ከታች(ዓለምና እስራኤል) በሚለው ርዕስ ስር በዝርዝር ቀርቧል፡፡

## 3. <u>ለወደፊቱም ተጨባጭ ትንቢቶች ማስቀመጡ</u>

ለወደፊቱ አለምና የሰው ልጅ ምን ይሆናሉ? የሚሉትን ትንቢቶች በሙሉ መዘርዘር ባይቻልም፣ ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ ያህል ሊከሰቱ የተዘጋጁና ዛሬ ምልክታቸውን እየተመለከትን ያለውን የአዲሱ የግብይት ቴክኖሎጂ፣ ወንጌል ለአለም ሁሉ መሰበክ፣ የሰዎች ፍቅር መቀዝቀዝና በአለምና እስራኤል መካከል እየተፈጠረ ያለውን ክፍተት እንመለከታለን፡-

- **<u>መጪው ዘመናዊ የግብይት ቴክኖሎጂ</u>**

መፅሀፍ ቅዱሱ በመጨረሻው ዘመን ግብይት በዚህ በኢኮሜርስ እንደሚሆን ቀድሞ ተንብዮዋል፣ በ1.4.2.2/1 እና በ7.3 ክፍሎች ላይም አሰራሩ ምን ያህል ተግባራዊ ሊሆን እንደተዘጋጀ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

- **<u>ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል</u>**

ክርስትና ከ2,000 አመት በፊት በአንዱ ኢየሱስ ተጀመረ፣ በመቀጠል 12ቱ ሐዋርያት እያለ ዛሬ ላይ ከ2 ቢሊየን በላይ ደርሷል፣ የዚህን እጥፍ የሚሆኑቱ ደግሞ በተለያየ መንገድ ወንጌሉን ሰምተዋል፡፡

ይህ ሁሉ ደግሞ እየሆነ ያለው መፅሀፍ ቅዱሱ "ከጊዜ በኋላ ይተዋል" እየተባለ ባለበትና እንዲተውም እየተሰራ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱሱ የጠላቶቹን ሃሳብ ሳይሰማ ተከታዮቹ አስር ሺ በማይሞሉበት ጊዜ በተነገረ "በመጨረሻ ዘመን ወንጌል ለአለም ሁሉ ይሰበካል" ትንቢት መሠረት እየተስፋፉ ይገኛል፣

ማቴ.24፡14 "ለአህዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግስት ወንጌል በአለም ሁሉ ይሰበካ፣ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል፡፡"

ለዚህም ትንቢት ፍፃሜ መፅሀፍ ቅዱሱ ዛሬ ከየትኛውም ጊዜ በላይ በብዛትና በብዙ ሺዎች ቋንቋዎች እየተተረጎመ፣ እየታተመና እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

- **<u>የሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል</u>**

መፅሀፍ ቅዱሱ በመጨረሻው ዘመን የሰዎች ፍቅር እየቀዘቀዘ እንደሚሄድ ይናገራል፡፡

ማቴ.24፡12 "ከአመፃም ብዛት የተነሳ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፡፡"

ይህ የመፅሀፍ ቅዱሱ ትንቢት በተግባር እየተረጋገጠ ያለ እውነታ ነው፡፡

- <u>ዓለምና እስራኤል</u>

የእስራኤል ጉዳይ ሲነሳ የአለም ህዝብ ሁለት ፅንፎችን ይይዛል፣ ይህ በግለሰቦችም በመንግስታትም ደረጃ ያለ እውነታ ነው፣ መነሻ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ የጥላቻው ጎራ ግን እየገዘፈ እንደሚሄድ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ እንረዳለን፣ በዚህም ዛሬ ላይ አብዛኞቹ ሀገራት የእስራኤል ደጋፊዎች አይደሉም፣ አሜሪካ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቷን እየተጠቀመች እንጂ የተባበሩት መንግስታት ብዙ ቦንብ የሆኑ ውሳኔዎችን በእስራኤል ላይ አስተላልፎባት ነበረ፣ በአሁኑ ጊዜም አሜሪካ ውስጥ ከጥቂት ሪፐብሊካን በስተቀረ አብዛኛው ዲሞክራት ፀረ እስራኤል መንፈስ ውስጥ ይገኛል፡፡

ይህ ዓለም ከጊዜ ወደ ጊዜ በእስራኤል ላይ ያለው ጥላቻ እየጨመረ መሄድ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው ነገር ግን በነዚህ ጥላቻዎች ውስጥ መፅሀፉ እስራኤልን "ከባድ ድንጋይ አደርጋታለሁ" እንዳለው የሁሉም ጥላቻ ውሀ ሲያነሳ አይታይም፣

> ዘካ.12፥2-3 "እነሆ ኢየሩሳሌምን የመንገድገድ ዋንጫ አደርጋታለሁ ... ለአህዛብ ሁሉ ከባድ ድንጋይ አደርጋታለሁ የሚሸከሙአት ሁሉ እጅግ ይቆስላሉ፡፡"

እስራኤል ዛሬ ከስደት በመመለስና በምዕራፍ ሰባት ከምንመለከተው ቀጣዩ የመከራ ዘመኗ መካከል ትገኛለች፣ በዚህም ይህ ዘመን በአንፃራዊነት የእስራኤል የእረፍት ዘመኗ ነው፣ በዚህ በእረፍት ዘመኗ ላይ ደግሞ የሚነሱባት ሁሉ ይህ ነው የሚባል ጉዳት ሳያደርሱባት ራሳቸውን የጭንቅ ህይወት ውስጥ ሲከቱ ብቻ ነው የምንመለከተው፣ ተራ ግለሰቦችን ትተን መሪዎችን እንኳን ብንመለከት፣ የሀገር መሪዎች በእስራኤል ላይ ከተነሱበት ቀን ጀምሮ የሚመሩት ህይወት የጭንቅ ህይወት ነው፣ እነዚህ መሪዎችም የፈሩት ነገር ሳይቀርላቸው ከሌሎች መሪዎች ተለይተው እድሜያቸው ሲያጥር ነው የምንመለከተው፣ ከዕድሜ ማጠር በላይ ደግሞ የሚገርመው አያያዛቸውና አገዳደላቸው እንኳን በውርደት ነው ለምሳሌ ጋዳፊ፣ ሳዳም ሁሴን፣ መሀመድ ሙርሲን መመልከት ይቻላል፡፡

እውነታው በእንዲህ እያለ ዘመኑ ወደ መጨረሻው ሲጠጋ አለም ለእስራኤል የሚኖረው ጥላቻና ቁጣ ከላይ በተመለከትነው መንገድ

እየጨመረ እየሄደ በመጨረሻም አለም በአንድ ላይ በመሆን “ማን እርሱን ሊዋጋ ይችላል” የሚባል ጦር(ራዕ.13፡4) በአንድነት በእስራኤል ላይ የሚያዘምትበት ደረጃ ይደርሳል፣

- ዘካ.2፡3 “የምድር አህዛብ ሁሉ በላይዋ ላይ ይከማቻሉ …”

- ሉቃ.21፡20 “ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባ ስታዩ …”

እንደዚሁ ደግሞ በዚህ ጊዜ፣

- ራዕ.11፡18 “አህዛብም ተቆጡ ቁጣህም መጣ …”

እንደተባለው አህዛብ እስራኤልን ለሶስት አመት ከግማሽ አሸንፈው ከገዙ በኋላ (ራዕ.11፡2, ራዕ.13፡5) እግዚአብሄርም ለእስራኤል ይነሳል፣ የእስራኤልን ጠላቶች ይመታል(ራዕ.19፡15-21)፣ የአህዛብ ቁጣም በእግዚአብሄር ቁጣ ይደመደማል፡፡

በዚህም አለም ለእስራኤል ያለውን ጥላቻ እየጨመረ መሄድ ውስጥ የመፅሀፉን ትንቢት ተጨባጭነት እንመለከታለን፡፡

እነዚህን በቀድመው ትውልድ (በኢየሱስ ህይወት የተረጋገጠ)፣ በአሁኑ ትውልድ(በሶርያ፣ ቱርክ፣ ኢትዮያና የተባበሩት መንግስታት የተረጋገጠ) እና በቀጣዩ ትውልድ የሚሆኑ ነገር ግን አሁንም ምልክታቸው እየታዩ ባሉት የመፅሀፍ ቅዱሱ ትንቢቶች እውነተኛነት ስንመለከት፣ ምንም እንኳን መፅሀፍ ቅዱሱ በሰዎች እጅ ቢፃፍም የመፅሀፉ ሃሳብ ግን ልዕለ ስብዕና ካለው አካል መሆኑን እንረዳለን፡፡

### 1.4.3. <u>ቅዱሳት መፅሀፍቱ “እስራኤል ከሌላው ዓለም ትለያለች” ማለታቸው ልበ ወለድ ነው? ወይስ በተግባር የሚታይ እውነታ ነው?</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ እስራኤልን ከሌሎች ሀገራት በተለየ ይመለከታታል፣ በዚህም “እውን እስራኤል ከአለም ህዝቦች የተለየች ናት? ወይስ አይደለችም?” የሚለውን በመመልከት የመፅሀፍ ቅዱሱን ትክክለኛ የፈጣሪ ቃልነትን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት በመጀመሪያ ፈጣሪ ለእስራኤላውያን ህግን አወረደላቸው፣ ህጉንም እንዲጠብቁ አዘዛቸው፣

> ዘሌ.26፡1-8 “እኔ እግዚአብሄር አምላካችሁ ነኝና ለእናንተ ጣዖት አታድርጉ … ሰንበታቴን ጠብቁ … በስርአቴ ብትሄዱ፣ ትዕዛዜን ብትጠብቁ … ዝናባችሁን በወቅቱ አዘንባለሁ፣ ምድሪቱም እህልዋን ትሰጣለች … በምድራችሁ ላይ በፀጥታ ትኖራላችሁ … ሰይፍ በምድራችሁ አያልፍም፣ ጠላቶቻችሁንም ታሳድዳላችሁ … ከእናንተም <u>አምስቱ መቶውን ያሳድዳሉ፣ መቶውም አስሩን ሺ ያሳድዳሉ</u> …”

እንደዚሁ ደግሞ ህጉን ካልጠበቁ ችግር ውስጥ እንደሚገቡ ተናገራቸው፣

> ዘሌ.26፡27-33 “… ባትሰሙኝ በትዕቢተኝነት ብትሄዱብኝ … እናንተንም <u>በአህዛብ መካከል እበትናችኋለሁ</u> … በልባቸው ድንጋጤን እሰድዳለሁ፣ በነፋስም የምትንቀሳቀስ የቅጠል ድምፅ ታሸብራቸዋለች … የልጆቻችሁን ስጋ ትበላላችሁ … <u>በአህዛብም መካከል ታልቃላችሁ</u> … ነገር ግን … ልባቸው ቢዋረድ … እኔ ለያዕቆብ የማልኩትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ፡፡”

በዚህም ቃል መሰረት የእስራኤል ህዝብ ባጠፋ ቁጥር እግዚአብሄር አህዛብን ተጠቅሞ በግልፅ ሲቀጣቸው ነበረ፣ በእስራኤል ሀጢያት ምክንያት እግዚአብሄር ሊያመጣ ያሰበውን ቅጣት ለነብዩ አሞፅ በራዕይ ሲያሳየው(አሞ.7)፣ አሞፅ በተመለከተው ራዕይ ተጨንቆ “ያዕቆብ ታናሽ ነውና እንዴት በዚህ ፊት ይቆማል?” በማለት የሰቀቀን ፀሎት ሲያደርግ ነበረ፡፡

ይሁን እንጂ እስራኤል ሲያጠፉ እግዚአብሄር ለቅጣት አሳልፎ ሲሰጣቸው ነበረ፣ ቅጣቱም ከእግዚአብሄር መሆኑን የሚያሳየው ደግሞ እስራኤላውያኑ የሚቀጡበት ቅጣት የሰው ዘር አይቶት በማያውቀው ቅጣት ነው፣ እነዚህን ቅጣቶች በዘመናዊው ታሪክም ሆነ በመፅሀፍ ቅዱሱ ታሪክ ላይ ተዘግበዋል፣

- ፈርኦን ለ400 አመታት በባርነት ሲገዛቸው(ሐስ.7፡6)፣ ለስራ በማሰብ ሳይሆን "ሆን" ብሎ በብዙ ስራ ሲያስጨንቃቸው(ዘፀ.1፡11) እና የእስራኤል ዘር እንደይበዛ ወንድ ልጅ ሲወለድ እንዲገደል ሲያደርግ ነበረ(ዘፀ.1፡22)፣

- እስራኤላውያን እግዚአብሄር ባልፈቀደበት ጦርነት ገብተውበት "ንብ እንዳሳደደችው" እስኪባል ድረስ የእስራኤል ጦር በጠላቶቹ ተመቶ ሸሽቶአል(ዘዳ.1፡44)፣

- እርኩስ ነገር በማድረጋቸው "ልባቸው ቀለጠ" እስኪባል በጦርነት ውስጥ ተመተዋል(ኢያ.7፡1-5)፣

- በቤተመቅደስ ውስጥ በተሰራ እርኩሰት ምክንያት በአንድ ቀን ውጊያ 30,000 የእስራኤል ወታደሮች በፍልጤማውያን ተገድለዋል (1ሳሙ.4፡1-10)፣

- በተለያየ ጊዜ ከደረሰባቸው ረሃብ የተነሳ የእርግብ ኩስ(2ነገ.6፡25)፣ የአህያ ስጋ(2ነገ.6፡25)፣ የሰው ስጋ(በዘሌ.26፡29, 2ነገ6፡25-30) ... በልተዋል፣

- በእስራኤላዊነታቸው ብቻ ከሌላው ህዝብ ተለይተው እንዲሸበሩ ሲደረጉ ነበረ፣
    - አሞናዊው ናዖስ በተነሳባቸው ጊዜ የእስራኤል ህዝብ በፍራቻ "እንገዛልሃለን" ብለው እንኳን ሽምግልና ሲልኩበት "ለመገዛት ከወሰናችሁ እንኳን ቀኝ አይናችሁን ከውስጣችሁ አውጥቼ ነው የምገዛችሁ" ሲላቸው ነበረ (1ሳሙ.11፡2)፣

- አስ.3፡12-13 "… ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ወዳሉ 127 ሀገሮች … በአስራ ሁለተኛው ወር በአዳር በአስራ ሶስተኛው ቀን አይሁድን ሁሉ፣ ልጆችንና ሽማግሌዎችን፣ ህፃናቶችንና ሴቶችን፣ በአንድ ቀን ይገድሉ ዘንድ፣ ምርኮአቸውንም ይዘርፉ ዘንድ ደብዳቤዎች በመልዕክተኞች እጅ ወደ ንጉሱ አገሮች ሁሉ ተላኩ፡፡"፣
- ዛሬ በምዕራባውያኑ ሀገራት የሚኖሩ ብዙ እስራኤላውያን "በፀረ ሴማዊ" እንቅስቃሴዎች እየተሸበሩ ይገኛሉ፡፡

- ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ኢየሱስን ሲገድሉት፣ ማቴ.27፡25 "… ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን" እንዳሉት፣ የተናገሩት ቃል በባዕድ ምድር ጠበቃቸው፣ በሰላም በሚኖሩበት አውሮፓ ከ1933-1945 የነገሰው ሂትለር እስራኤላውያኑ ላይ ተነስቶ ከ6 ሚለየን በላይ የሚቆጠሩትን እስራኤላውያ በአሰቃቂ ሁኔታ ፈጀ፣ ከፍጅቱ በተጨማሪም አንዳንዶችን እንደ አይጥ የሳይንቲስቶች መመራመሪያ አደረገ፣ ሌሎችን የሰውነታቸው ሞራ እየተገፈፈ ለሳሙና ጥሬ እቃነት አዋለ … በዓለም ላይ በየትኛውም ህዝብ ላይ ተደርጎ የማይታወቅ ጭፍጨፋ ፈፀመባቸው፣ "የቅጠል ኮሽታ ታስደነግጣችኋለች" እንደተባሉት ከዚህ ጭፍጨፋ የተረፉት እንኳን ከደረሰባቸው ሽብር የተነሳ ድንጉጦች የነበሩ፡፡

እግዚአብሄር እስራኤላውያኑን "ካመፃችሁ እቀጣችኋለሁ" እንዳለው፣ እስራኤላውያን የአለም ህዝብ ያላየውን ፍዳ አይተዋል፣ "እበትናችኋለሁ" እንዳለው በተበተኑበትም ሀገር ለውርደት ተዳርገው፣ "እረፍት አታገኙም"(ዘዳ.28፡65) እንደ ተባለ መዘርዘር እስኪያቅት ድረስ መከራቸው በልተዋል፡፡

በነዚህ ቅጣቶች ውስጥ ግን አንድ የሚገርም ቋሚ ታሪክ አለ፣ በታሪክ እንደሚታወቀው ብዙ ህዝቦች ሀገራቸውን ለቀው ተበትነዋል ነገር ግን ተመልሰው ተሰብስበው ሀገራቸውን መመስረት የቻሉ የሉም፣ ሁሉም በተበተኑበት ባህል፣ ቋንቋና ብሄር መካከል ተውጠው ቀርተዋል፤ ፈጣሪ እስራኤልን "ባትመለሱ እበትናችኋለሁ" እንዳለው እስራኤልን ለብዙ ጊዜ ለመበተን አደጋ አሳልፎ ሰጥቷቸው የቅጣት ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ተአምራዊ በሆነ መንገድ መሰበሰባቸው ነው፣ ከመሰባሰባቸው በተጨማሪ የሚገርመው

ደግሞ ይህ “የመበተንና የመሰብሰብ” ሂደት ከተፈጥሮአዊው አሰራር ውጪ የህዝቡ ቋንቋ፣ ባህልና ሀይማኖት ሳይበረዝ፣ ከ12ቱ ጎሳ አንዱም ጎሳ ሳይጎድል መሰብሰባቸው ነው፡፡

ከነዚህ “የመበተንና የመሰብሰብ” ታሪኮች መካከል በቅርብ የነበረውንና ሁላችንም የምናውቀው የ1948 መመለስና እንደ ሀገር መደራጀት ብንመለከት በውስጡ ብዙ ተአምራዊ ነገሮችን እንመለከትበታለን፡፡

እስራኤል ኢየሱስን ሲገድሉት “ደሙ በልጆቻችን” እንዳሉት እግዚአብሄር ልጆቻቸውን ለሂትለር አሳልፎ ሰጠ፣ ከሂትለር እለቂት በኋላ “ወደ ሀገራችሁ ትሰባሰባላችሁ” የተባለው የእግዚአብሄር ጊዜ ሲደርስ “ወደ ሀገራችን” እንመለስ ጥያቄዎች ከህዝቡ መካከል እየተጠናከረ መውጣት ጀመረ፣ ነገር ግን በወቅቱ ይህን ጥያቄ መመለስ የማይታሰብ ነገር ነበረ ምክንያቱም ሀገራቸው ላይ ሙሉ በሙሉ አረቦች ሰፍረውበት ነበረ፣ በዚህም ሀያላኑ ሀገራት አንድ መፍትሄ አቀረቡ ወደ ነበሩበት ሀገር ከመመለስ ይልቅ “አፍሪካ ውስጥ ሰው ከማይኖርባቸው ሰፋፊ ለም መሬቶች ውስጥ አንዱን ቦታ በማካለል እስራኤል የምትባል ሀገር በመመስረት ወደዚህ ቦታ በመሄድ የራሳቸውን ሀገር እንዲመሰርቱ፡፡”

ነገር ግን የፈጣሪ ቃል “ወደ ሀገራችሁ ትሰበሰባላችሁ” ስለነበረ እስራኤላውያኑ ይህንን አማራጭ ሀሳብ አልተቀበሉትም፣ በዚህም በአረቦች የተያዘውን መሬታቸውን በጦርነት በማስለቀቅ መልሰው መያዙ አማራጭ የሌለው ምርጫ አደረጉት ነገር ግን በወቅቱ ይህን ማከናወኑ የማይታሰብ እቅድ ነበረ፣ ምክንያቱም በእስራኤል መሬት ላይ አረቦች ሰፍረዋል፣ አካባቢውን የምትገዛው እንግሊዝም ሀሳቡን አልተቀበለችም፣ የእስራኤል መሬት የሚጎራበተው በአረቦች በመሆኑ ወታደራዊ ቤዝ ማግኘት አይቻልም፣ ከሂትር ጭፍጨፋ የተረፈውን ጥቂት ወጣት መልሶ ወደ ጦርነት መማገድ ሞራላዊ አልነበረም፣ ጦርነቱ የሚካሄደውም በግለሰብ ደረጃ በተሰበሰቡ ቡድኖች እንጂ ከጀርባቸው የተደራጀ ሀገራዊ ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡

በነዚህ ችግሮች መካከል ግን “የማይሳካ” የሚያስብል የጦርነት እቅዶች ተሰሩ፣ ጦርነቱም ተጀመረ ነገር ግን ከእስራኤላውያኑን እቅድ ጀርባ ልዕለ ስብዕና ያለው አካል እንዳለ ባስመሰከረ መልኩ እስራኤላውያኑ ማሸነፍ የማይችሉትን ጦርነት በድል ተወጡት፣ ከዚያም እስራኤል የምትባለውን ሀገር

በመመስረት ከሂትለር የተረፉት ዜጎቻቸውን ወደ ሀገር በመመለስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቦታውን እስራኤል አስመሰሉት፣ ከዚህ በኋላም በተለያዩ ጊዜያት ከአረቦች በተነሱባቸው የመልሶ ማጥቃት ጦርነቶች አስከፊ ጦርነቶች ውስጥ ቢያልፉም ጦርነቶች ግን ለእስራኤል ተጨማሪ መሬቶችን አስገኙ፡፡

ዛሬ እስራኤል በጠላቶቿ መካከል እዮረች ያለችው በ"ከስደት ተመላሽ" መንፈስ ሳይሆን በሀያልነትና በክብር ነው፣ የእስራኤል ሀያልነት የሚመነጨው በዘመናዊ መንገድ ከተደራጀው መከላከያ ሠራዊቷና የደህንነት ተቋሟ ነው፣ እስራኤል ምንም የተፈጥሮ ሀብት የሌላት፣ በነዳጅ ዘይት በከበሩና ጂሀድን መጠቀም በሚችሉ ጠላቶች የተከበበች ሚጢጢ ሀገር ሆና ግዙፍ የመከላከያና የደህንነት ተቋም አደራጅታ በክብር መኖሯ በራሱ ተአምራዊ እጅን ያሳያል፣

- የእስራኤል የመከላከያ ተቋም ከትኛውም ሀያል ሀገር መከላከያ ሰራዊት እኩል የሚታይና "አሉ" የሚባሉ እስከ አቶሚክና ሃይድሮጂን ቦንቦች የታጠቀ፣ የምድር ክብነት ዞረው መምታት የሚችሉ የረዥም ርቀት ሚሳኤሎች የታጠቀ፣ ምድራዊዋ እስራኤል ሙሉ በሙሉ ብትጠፋ እንኳን በጠፋችበት ሁኔታ ውስጥ በከርሰ ምድርና በሳተላይቶች ላይ በተጠመዱ የኒውክለር አረሮች ጠላቶቻቸውን መልሰው አመድ ማድረግ የሚችልበት አቅም አለው፣ በዚህም ማንም አእምሮ ያለው ይህንን ሰራዊት በመደበኛ ጦርነት መግጠም አይችልም፡፡
- የእስራኤል የደህንነት ተቋም በአለም ላይ "አሉ" ከሚባሉ የደህንነት ተቋማት የሚመደብ ነው፣ ከአወቃቀሩና ከአሰራሩ ምስጢራዊነት የተነሳ እጁ እስከየት እንደሚረዝም እንኳን አይታወቅም፣ በዚህም የእስራኤልን ጥቅም ከማስከበር አልፎ ሀገራት እንኳን ችግር ሲገጥማቸው አልፎ ሲረዳቸው ይታያል፣ ብዙ ሀገራትም የደህንነት ስራቸውን ለማዘመን የዚህችን አዲስና ሚጢጢ ሀገር ድጋፍ ሲጠይቁ ይታያል፡፡

ይህ የደህንነት ተቋም "ሞሳድ" ተብሎ በአዲስ መልክ ይደራጅ እንጂ የእስራኤል ህዝብ የደህንነት ተቋማት ጥቅም የገባው ከጥንት ከነኢያሱ ዘመን (ዘኁ.13) ጀምሮ ነው፡፡

በዚህም እስራኤል ከተመሰረተች በአጭር እድሜዋ፣ በትንሽ ጂኦግራፊ ክልል፣ በባዶ የተፈጥሮ ሀብትና በጥቂት የህዝብ ብዛት በአለም ላይ “አለ” የተባለ ጠንካራ የመከላከያና ደህንት ተቋም ይዛ በቱጃር ጠላቶቿ መካከል ሉአላዊነቷን እሰጠብቃ መኖርዋ “እስራኤል ከሌላው የተለየች” እንደሆነች የሚናገረው መፅሀፍ ቅዱሱን እውነተኛነት ብሎም የልዕለ ስብዕና አካል መኖርን ያረጋግጣል፡፡

ይህ የእስራኤል ልዩነት በቁርአኑም ላይ ተገልጿል፣

> 45፡16 “ለእስራኤል ልጆች መፅሃፍንና ህግን፤ ነቢይነትንም በርግጥ ሰጠናቸው፡፡ ከመልካም ሲሳዮችም በርግጥ ለገስናቸው፡፡ <u>በአለማት ላይም አበለጥናቸው</u>፡፡”

የሚገርመው ደግሞ ሀገሪቱ ይህንን ሁሉ ጥንካሬና ሉአላዊነት ይዛ ያለችው በሃይማኖት፣ በዘር፣ በቋንቋና በባህል አንድ በሆኑ፣ ጂሀድን መጠቀም በሚችሉ፣ በነዳጅ ዘይት ሃብት በተንበሸበሹ ከበርቴ ጠላቶቿ መካከል እንደ ሴንጢ ተሰንቅራ ባለችበትና እነዚህ ጎረቤቶቿም ይህቺን በመካከላቸው የተሰነቀረ ጩቤ መስላ የተቀመጠችውን ሀገር ከመሃላቸው ነቅለው ለማጥፋት የቻሉትን ሁሉ ጥረት በሚያደርጉበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ደግሞ ተአምራዊነቱን ያጎላል፣ በዚህ ላይ ደግሞ ሀገሪቱ በነዚህ ጎረቤቶቿን መሸበር ይቅርና እያስፈራራችና በተለያዩ ሴራዎች እያተራመሰቻቸው ትገኛለች፣ ለምሳሌ እንኳን ብንመለከት፣

- <u>ከ1980-1988 የቆየው ኢራንና ኢራቅ ጦርነት</u>፡- ሁለቱም ሀገራት ለእስራኤል ጠላቶች በመሆናቸው እስራኤል ለሁለቱም ተፋላሚ ሀገራት የተቃራኒያቸውን ትክክለኛ የስለላ መረጃዎችን ስትሸጥ ነበረ፣ በዚህም ሁለቱን ጠላቶችዋን ማጫረስ፣ መረጃዎችን በከፍተኛ ገንዘብ መሸጥ፣ በሀገራቱ ላይ ያላትን የደህንነት የበላይነት ማሳየት … የመሳሰሉ ጥቅሞችን ከጦርነቱ ስታገኝ ነበረ፡፡
- <u>IS(Isalamic State)</u> የሚባለው ድርጅት ካቋቋሙት ሀገራት ውስጥ አንዷ እስራኤል ናት፣ ሀገሪቱ ይህንን ድርጅት በማቋቋሟም ብዙ ጥቅሞችን አግኝታበታለች ይህም፡- ጠላቶቼ ናቸው የምትላቸውን የእስልምና ሀገራት በዚህ ቡድን መተራመሳቸው፣ ጠላቶችዋ የሆኑትን

ሁለቱን የእስልምና ቡድኖች፣ ሺአና ሱኒ በዚህ እልህ አስጨራሽ ውጊያ ውስጥ በተለያየ ጎራ ተሰልፈው መዋጋታቸው፣ በወቅቱ በጋዛ ላይ ፈፅማ የነበረችውን የአንድ ለሙቶ እልቂት እንዲረሳ ማድረጓ፣ ከጠላቶችዋ መካከል በሊባኖስ ህዝብ መካከል ተደብቆ ለምት አልሙች ያላት "ሂዝቦላህ" አይ ኤስን ለመዋጋት በወጣበት በሶሪያ ሜዳ ላይ ማግኘትዋና የምትፈልጋቸውን አባሎቹን እየመረጠች ለመግደል ሁኔታዎች መመቻቸታቸው … የመሳሰሉ ብዙ ጥቅሞችን አስገኝተውላት ነበረ፡፡

በዚህም እስራኤል ከገፀ ምድር እንድትጠፋ በሚመኙ ብዙ ጠላቶቿ መካከል በሉአላዊነት ከዚያም አልፎ "የመንገድገድ ዋንጫ" ሆና፣ በአስፈራሪነትና በሴረኛነት ተፈርታ እየኖረች ትገኛለች፣ ይህም መፅሀፍ ቅዱሱ "እስራኤል የተለየች ናት" አባባል እውነታ ያረጋገጠ፣ በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱን እውነተኛነት ብሎም መፅሀፉ ልዕለ ስብዕ ባለው አካል መሪነት መፃፉን አመላካች ነው፡፡

እነዚህ ታሪኮች ያላረጁና ከእስራኤል ምስረታ 1948 ዓ.ም ወዲህ የተፈፀሙ ናቸው፣ ዛሬ ኢአማኒዎች መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የተነገሩትን የእስራኤልን ታሪኮች እንደ ልበወለድ እንደሚያዩት ሁሉ እነዚህን ከላይ የዘረዘሩት ታሪኮች በቀጣዩ ኢአማኒ ትውልድም እንዲሁ "ልበወለድ ናቸው" እንደሚል እሙን ነው ነገር ግን ይህ "ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሎቹ በመስመር ይጓዛሉ" እንደሚባለው ተረት ሳይስተዋል የሚፈስ የታሪክ እውነታ ነው፡፡

### 1.4.4. <u>በቅዱሳት መፅሀፍት ውስጥ የተገለፁት ታሪኮች በዘመናዊው የታሪክና የአርኪዎሎጂ ጥናቶች ማረጋገጥ ይቻላል? ወይስ ልበ ወለዶች ናቸው?</u>

ታሪክና አርኪዎሎጂ የፈጣሪን መኖር ከማይቀበሉት የትምህርት ክፍሎች መካከል ናቸው ነገር ግን እነዚህ የጥናትና ምርምር ዘርፎች የመፅሀፍ ቅዱሱ ታሪኮች ያሉበት መካከለኛው ምስራቅ ጋር ሲደርሱ ምርምራቸው ከመፅሃፍ ቅዱሱ ዘገባ ጋር አንድ ሆኖባቸዋል፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ልበወለድ ባለመሆኑ ክስተቶችን በተከሰቱበት መቼት(ቦታና ጊዜ) በእርግጠኝነት ስለሚያስቀምጥ የመፅሃፍ ቅዱሱ አፃፃፍ ዘዴ ለተመራማሪዎቹ አመቺ ሆኗል፣ የዘመን አቆጣጠር ባልነበረበት ከኢየሱስ በፊት በነበሩትን ዘመናት እንኳን ሲተርኩ የነበሩት ታሪኮች ሲተረኩ ዝም ብለው አልነበረም ከሌሎች ታሪኮች ጋር በማገናኘት ነበረ፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- 1ነገ.6፡1 "የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ አራት መቶ ሰማንያ አመት በሆነ ጊዜ፣ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው አመት፣ ዚፍ በሚባለው በሁለተኛው ወር የእግዚአብሄርን ቤት መስራት ተጀመረ፡፡"
- 2ነገ.25፡27 "እንዲህም ሆነ፤ የይሁዳ ንጉስ ዮአኪን በተማረከ በሠላሳ ሰባተኛው አመት በአስራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያ ሰባተኛው ቀን የባቢሎን ንጉስ ዮርማሮዴቅ በነገሰ በአንደኛው አመት የይሁዳ ንጉስ ዮአኪንን ከወህኒ አወጣው፡፡"
- አሞ.1፡1 "በቴቁሔ ከላም ጠባቂዎች መካከል የነበረ አሞፅ፣ በይሁዳ ንጉስ በዖዝያን ዘመን፣ በእስራኤልም ንጉስ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን፣ የምድር መናወጥ ከሆነበቱ ከሁለት አመት በፊት ..."

ይህ የመፅሀፍ ቅዱሱ ታሪክን ከጊዜ ጋር የማስቀመጥ ባህል ደግሞ ለዘመኑ የታሪክና የአርኪዎሎጂ ተመራማሪዎች ትልቅ እገዛ አድርጎላቸዋል፡፡

በአብዛኛው በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ የተገኙ የታሪክና የአርኪዎሎጂ ግኝቶችም ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጋር አንድ በመሆናቸው፣ የቱ ታሪክ

ነው? የቱስ መፅሃፍ ቅዱስ ነው? እስኪያስብል ደርሰዋል፣ ይህ በመካከለኛው ምስራቅ የተደረጉት የታሪክ ዘገባዎች ከመፅሃፍ ቅዱሱ ጋር አንድ የመሆናቸው እውነታ ደግሞ የመፅሀፍ ቅዱሱ ትክክለኛነት አረጋጋጭ ነው፡፡

ይባሱኑ ደግሞ የአርኪዎሎጂ ግኝቶቹ የመፅሀፍ ቅዱሱን ታሪኮች በተግባር የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል፣ የተወሰኑትን ብንመለከት የኖህ መርከብ፣ የሰዶምና ገሞራ ቃጠሎ ታሪክ፣ ኔፊሊም ስለሚባሉ ቁመታቸው 3ሜትር ስለሆኑ ሰዎች፣ የፈርኦን ወታደሮች የቀይ ባህር ታሪክና የከተሞች ቅጥር ግንቦች ታሪኮች በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ የተገኙ የመፅሀፍ ቅዱሱን ታሪክ በተግባር ያረጋገጡ እውነታዎች ናቸው፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡-

- **<u>የኖህ መርከብ</u>**

የኖህ መርከብ ታሪክ በዘፍጥረት ምዕራፍ 6-8 ላይ ተገልጿል፣ በታሪኩ መሠረትም ከኖህ በስተቀረ ትውልዱ በሙሉ በሀጢያት በመጨማለቁ እግዚአብሄር ትውልዱን በሙሉ ለማጥፋት ኖህን መርከብ እንዲሰራ አዘዘ፣ ኖህም መርከቡን ሰርቶ ሲጨርስ ታላቅ የውሃ መጥለቅለቅ ሆኖ ኖህ ከቤተሰቡና ከያዛቸው እንስሳት ጋር ተረፈ፣ በታሪኩ ውስጥ የጥፋት ውሃው ሲደርቅ መርከቢቱ በአራራት ተራሮች ላይ እንዳረፈችና በውስጥዋ የነበሩትን እንዳራገፈች መፅሀፉ ይናገራል፡፡

ይህ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ታሪክ በእንዲህ እያለ በ1960 ዓ.ም የቱርክ አየር ሀይል ባለሙያዎች የሀገሪቱን የአየር ፎቶዎች በሚያጠኑበት ጊዜ የአራራት ተራሮች ከሚባሉት ውስጥ ጁዲ በሚባለው ተራራ ላይ የመርከብ ቅርፅ የሚመስል አገኙ፣ ከዚያም ወደ አከባቢው በመሄድ ይህንን የመርከብ ቅርፅ የሰራው ከአፈር የተሰራ ግድግዳ የሚመስል ነገር መሆኑንና በተደረገው ተጨማሪ የአርኪዎሎጂ ዝርዝር ጥናትም፣

- የአፈር ግድግዳ የመሰለው ነገር ወደ አፈርነት የተቀየር መርከብ ቅሪት መሆኑ፣
- የመርከቡ ስፋትም ከኖህ መርከብ ስፋት ጋር እኩል መሆኑ፣

ተረጋገጠ፣ ይህም የኖህ መርከብ አረፈች በተባለበት ቦታና በተነገረው መጠን መገኘቱ የኖህ መርከብ ቅሪት መሆኑን ያረጋገጠ ትልቅ የአርኪዎሎጂ ግኝት ነው፡፡

➢ <u>የሰዶምና ገሞራ ቃጠሎ ታሪክ</u>

መፅሃፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ምዕራፍ 18-19 ላይ የ"ሰዶምና ገሞራ" የሚባሉ ከተሞች ስለ ሀጢያታቸው ብዛት እግዚአብሔር ከሰማይ እሳትና ዲን አዝንቦባቸው እንዳቃጠላቸው የሚገልፅ ታሪክ እንመለከታለን፡፡

አርኪዎሎጂስቶች በነዚህ በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ ባደረጉት ቁፋሮ መፅሃፍ ቅዱሱ እንደሚናገረው በእሳት ተቃጥሎ የተቀበረ ከተማ አግኝዋል፡፡

➢ <u>ቁመታቸው 3 ሜትር የሆኑ ሰዎች</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ "ኔፊሊም" የሚባሉ ቁመታቸው ስድስት ክንድ የሚደርስ ማህበረሰቦች በምድር ላይ እንደነበሩ ይነግረናል(ዘፍ.6፡4, ዘኍ.13፡32-33, ዘዳ.3፡11 ...)

በአርኪዎሎጂ ጥናቶችም መፅሀፍ ቅዱሱ እንደተሚናገረው ቁመታቸው 3 ሜትር የሆኑ የሰዎች አጥንቶች ተገኝተዋል፡፡

➢ <u>የፈርኦን ወታደሮች የቀይ ባህር ታሪክ</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ(ዘፀ.14) ላይ እግዚአብሄር እስራኤሎችን ከግብፅ ሀገር ባርነት ሲያወጣ እንዲሄዱ የፈለገው መንገድ ባልነበረበት በባህር ነበረ፣ በዚህም ባህሩን በተአምር ካሻገራቸው በኋላ የፈርኦን ወታደሮች በዚያ መንገድ ሲሄዱ ባህሩን እንደመለሰባቸውና በባህሩ ውስጥ እንደሰጠሙ እንመለከታለን፡፡

በዚሁ የባህር ክፍል ወለል ላይ በተደረገ የአርኪዎሎጂ ጥናት እስራላውያን "ተሻገሩበት" በተባለው የቀይ ባህር ወለል ላይ በባህር ውስጥ ሊገኙ የማይችሉ ሰረገላዎች፣ የጦር መሳርያዎች፣ የሰውና የፈረሶች አፅሞችና የእግር ኮቴ ዱካዎች ተገኝተዋል፣ እነዚህ ግኝቶችም በወቅቱ በአካባቢው ከነበረው ታሪክ ጋር ሲመሳከር የፈርኦን ወታደሮች የጦር መሳርያዎችና ሰረገላዎች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

## ➢ የከተሞች ቅጥር ግንቦች

በድሮ ጊዜ ነገስታት ራሳቸውንና ህዝባቸውን ከጠላት ለመከላከል ግንቦችን ይሰሩ ነበረ፣ ዛሬም እነዚህን ግንቦች ቅሪት በኢየሩሳሌም፣ ሀረርና በቻይና እንመለከታለን፣ እንደዚህ አይነት መፅሃፍ ቅዱሱ ታሪካቸውን የመዘገበላቸው ታዋቂ ግንቦች ነበሩ፣ እነዚህ ግንቦች በነበሩባቸው ቦታዎችም በተደረጉ የአርኪሎጂ ጥናቶች ግንቦቹ በቁፋሮ ተገኝተዋል፣ በዚህም የኢያሪኮ ግንብ ቅሪትና የነህምያ ግንብ ቅሪቶች ተገኝተዋል፡፡

ሌሎች ብዙ የመፅሀፍ ቅዱሱን ታሪክ በተግባር የሚያሳዩ ቅርሶች በእስራኤል ሙዚየሞች ውስጥ ተደርድረው ይገኛሉ፣ ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ምንም እንኳን እስራኤል "ኢየሱስ አልተወለደም ገና ይወለዳል" በማለት አዲሱን ኪዳኑን ባትቀበለውም በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የተጠቀሱት የአዲሱ ኪዳን ቁሳቁሶችና ታሪካዊ ቦታዎች ለምሳሌ፣ የኢየሱስ መቃብር፣ የቃና ዘገሊላ ወይን መጥመቂያ ጋኖች ... እያስጎበኘች ትገኛለች፡፡

እነዚህ ግኝቶች የመፅሀፍ ቅዱሱን ታሪክ እውነታ የሚያረጋግጡ ቢሆንም "ታሪክ የሚያስተምረን የሰው ልጅ ከታረክ አለመማሩ ነው" እንደሚባለው ሆኖ እንጂ ለሚያስተውለው ሁሉም ነገር በግልፅ ተቀምጦ ይገኛል፡፡

ከነዚህ የታሪክና የአርኪዎሎጂ ግኝቶች የምንረዳው የመፅሀፍ ቅዱሱን ትክክለኛ የፈጣሪ ቃልነትን ነው፡፡

## ማጠቃለያ(ኢአማኒነት/ኢአምላኪነት)

በዚህ ምዕራፍ በዝርዝር እንደተመለከትነው ኢአምላካውያን “ፈጣሪ አምላክ የለም ፍጥረታት የተፈጠሩት በተፈጥሮአዊ የቢግ ባንግና ዝግመተ ለውጥ ሂደት ነው” ቢሉም ይህ አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና የፍጥረታት የተፈጠሩት በፈጣሪ አምላክ መሆኑን የፍጥረታትን ውበትና ስነስርአት፣ አምላካውያን “የፈጣሪ ቃል” ነው የሚሉት መፅሀፍ ቅዱሱ ልዕለ ስብዕና ባለው አካል መሪነት የተፃፈ መሆኑ፣ መፅሀፍ ቅዱሱም ለየት አድርጎ የሚመለከታት እስራኤል ከሌሎች ሀገራት የተለየች መሆኗና በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የተፃፉት ታሪኮች በዘመናዊው ታሪክና አርኪዎሎጂ ጥናቶች መረጋገጣቸውን ስንመለከት፣ እነዚህ እውነታዎች የፈጣሪ አምላክን ህለዎት የሚያረጋግጡ ጊዜ ያልሻራቸው እውነታዎች መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡

ይህ አጠቃላይ እውነታ ይሁን እንጂ ሰዎች ምንም መሰረት የሌለውን የኢአምላካዊውን አስተምህሮ የሚከተሉት በድንገት ሳይሆን እራሳቸው በፈጠሩት ክፍተት ምክንያት ፈጣሪ ለሌላ ነገር አሳልፎ ስለሰጣቸው መሆኑን መፅሀፉ ይናገራል፣

> ሮሜ.1፡20-28 “… እግዚአብሄርን እያወቁ እንደ እግዚአብሄርነቱ መጠን ስላላከከበሩትና ስላላመሰገኑት … እግዚአብሄር ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው…”

ሁሉም ኢአምላኪዎች ሲጀምር ሀይማኖት የነበራቸው የመሆኑን እውነታ ከዚህ ቃል ጋር ስንመለከት፣ እነዚህ ሰዎች ለፈጣሪ ክብር ባለመስጠታቸው ምክንያት ፈጣሪ የተረት ተረት መናፍስት አሳልፎ እንደሰጣቸው እንመለከታለን፡፡

በዚህም ብዙዎች የኢአምላካዊነትን(ኤቲዝም፣ ሂውማኒዝም …) ፍልስፍናን የዕውቀት ጥግ አድርጎ ያድንቃቸው እንጂ ፍልስፍናውን ረጋ ብሎ ለሚመለከት ግን ከላይ እንደተመለከተው ውስጡ ባዶ ነው፣ መፅሀፉም እንደዚህ አይነት በፈጣሪ ላይ የሚደረጉ ፍልስፍናዎችን ባዶ እንደሚያደርጋቸው መናገሩ ደግሞ የኢአምላኪነት - መፅሀፍ ቅዱስ ሌላው የትስስር መስመር ነው፣

፲ቆሮ.1፥19-20 “የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ ጥበበኛ የት አለ፣ ጻፊስ የት አለ፣ የዚች አለም መርማሪስ የት አለ፣ እግዚአብሄር የዚችን አለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን፣”

በዚህም በዚህ ምዕራፍ እንደተመለከትነው ፈጣሪ የሳይንሱን የፈጣሪና የስነፍጥረት ፍልስፍና የሞኝነት መንገድ አድርጎታል፣ በዚህም ዝግመተ ለውጥ ዝግመተ አዕምሮ የሆነበትን፣ ሀይማኖቱ ኤቲዝምም ኦቲዝም የሆነበትን እውነታ ተመልክተናል፡፡

የሚገርመው ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱ ሰይጣንን “አውሬ” ማለቱና በዚህ ፍልስፍና የተያዙት ሰዎች “የሰው ዘር ከዝንጀሮ መሰል አውሬ መጣ” ማለታቸው፣ አማኞች ደግሞ “አባታችን እግዚአብሄር ነው” ማለታቸውን ስንመለከት ሁለቱም ቡድኖች በተለያየ አባት ስር መሰለፋቸውንና ሁለቱም ከአባታቸው የሰሙት እንደሚናገሩ እንመለከታለን፡፡

ስለዚህ ይህንን አሳሳች ፍልስፍና ተከትሎ ለአሳሳቹ ወደ ተዘጋጀው መቀጣጫ ቦታ ከመውረድ ከላይ እንደተመለከትነው የፈጣሪን መኖር በመመልከት ይህንን ፈጣሪ በየትኛው የአምላካውያን መንገድ እንደሚገኝ ማጥናቱ ተገቢ ነው፣ በሚቀጥሉት ምዕራፎችም ይህንን ፈጣሪ የምናገኘው በየትኛው ሀይማኖት በኩል ነው? የሚለውን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. እስልምና

እስልምና “የአብርሃም ሀይማኖቶች” ከሚባሉት ሀይማኖቶች የሚመደብ ቀደምት ሀይማኖት ነው፣ ሀይማኖቱ በ6ኛው ክፍለ ዘመን በነብዩ መሀመድ የተመሠረተ ሲሆን የሚመራውም በቁርአንንና በሀዲሳት ነው፣ በእስልምና ቁርአን በቀጥታ ከፈጣሪ የተላከ መፅሀፍ እንደሆነ የሚታመን ሲሆን “ሀዲስ” የሚባሉት መፅሀፍት ደግሞ የነቢዩን ውሎ፣ አስተምህሮና ልምምዶች የተዘገቡባቸው መፅሀፍት ናቸው፡፡

ቁርአን 114 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የቁርአኑ የምዕራፎችና አንቀፆቹ ቅደም ተከተልም ቋሚ በመሆኑ ከቁርአኑ ሲጠቀስ አንዳንድ ጊዜ ሱራ፣ ሱረቱ ወይን ቁርአን እየተባለ በምዕራፉ ቁጥርና አንቀፅ ቁጥር ሲሆን ብዙውን ጊዜ ግን በምዕራፉና በአንቀፁ ቁጥር ብቻ ይቀርባል፣ በዚህ መፅሃፍ ውስጥም ከቁርአኑ የተወሰዱ በሙሉ ይህንኑ አብዛኛው ሰው የሚጠቀምበትን የምዕራፍ ቁጥርና የአንቀፅ ቁጥር ብቻ በመጥቀስ ቀርቧል፣ በዚህም የመፅሀፍ ስም ሳይጠራ በምዕራፍ ቁጥርና አንቀፅ ቁጥር ብቻ የቀረቡት ጥቅሶች በሙሉ ከቁርአን የተወሰዱ ናቸው(ጥቅሶቹንም ከቁርአን ለማየት እንዲያመች የቁርአኑ ምዕራፎች ዝርዝር በመፅሀፉ አባሪ(Annex- II) ገፅ ላይ ቀርቧል፡፡)

ሀዲስን በተመለከተ፣ [14] “የሀዲስ መፅሃፍት ብዛት ብዙ ሺ በመሆኑና በተለያዩ ምክንያቶችም በሙስሊሙ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው `ሲሃቱ ሲታ` የሚባሉት ስድስት መፅሀፍት ናቸው፣ እነሱም ሰሂህ ቡኻሪ፣ ሰሂህ ሙስሊም፣ ጃሚያ አት ቲርሚዲ፣ የአቡ ዳውድ ሱና፣ አቡ አብድር ረህማን እና አቡ አብደላ መሀመድ ናቸው፡፡”

እነዚህ ስድስቱ የሃዲስ መፅሃፍትም ለየብቻቸውም ራሳቸውን የቻሉ መፅሀፍት በመሆናቸው፣ ከነዚህ የሀዲስ መፅሃፍት የተወሰዱት ምንባቦች(ጥቅሶች) በዝርዝር ከነመፅሃፍቱ ስም የቀረቡ ሲሆን አቀማመጣቸውም በእስልምና በተለመደው መንገድ ነው፡-

[14] ዳግማዊ ኃይለ ስላሴ (2008)፣ **ኢስላም ምንድነው? ክርስትናስ?**፣ ገፅ 69

- ሰሂህ ቡኻሪ በጣም ሰፊ መፅሀፍ በመሆኑ ከዚህ መፅሀፍ ላይ የተወሰዱት ጥቅሶች በሙሉ የቀረቡት አብዛኛው ሰው በሚጠቀምበትና ገላጭ በሆነው አራት ደረጃ አጠቃቀስ ነው፣ ይህም "ሰሂህ ቡኻሪ፡ll፡ll፡ll" መልክ ሲሆን፣ በዚህም "ሰሂህ ቡኻሪ" የሚለው የመፅሀፉ ስም ሲሆን፣ ሶስቱ ተከታታይ ቁጥሮች ደግሞ የመፅሃፉ ቅፅ፡ መፅሃፉ ምዕራፍና የአንቀፅ ቁጥሮች ናቸው፣
- ከሰሂህ ሙስሊም መፅሀፍት የተጠቀሰው፣ ሁሉም ሰው በሚጠቀምበት የሶስት ደረጃ አጠቃቀስ ነው፣ ይህም "ሰሂህ ሙስሊም፡ll፡ll" መልክ ሲሆን፣ በዚህም "ሰሂህ ሙስሊም የሚለው የመፅሀፉ ስም ሲሆን፣ ሁለቱ ቁጥሮች ደግሞ የመፅሀፉ ምዕራፍና አንቀፅ ቁጥርን ያመለክታሉ፣
- ከሌሎቹ ቀሪዎቹ አራቱ ሀዲሳት የተወሰዱት ጥቅሶች በሙሉ የቀረቡት "የመፅሀፉ ስም፡ll" መልክ ነው፣ ቁጥሩም የአንቀፅ ቁጥርን ያመለክታል፡፡

በዚህም ያለ መፅሃፍ ስም ዝም ብለው በቁጥሮች ብቻ የተቀመጡት ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከቁርአን ሲሆን ከመፅሀፍ ስም ጋር የተቀመጡት በሙሉ ከሀዲስ የተወሰዱ ናቸው፣ በዚህም መሠረት እያንዳንዱን ትንታኔ ከጥቅሶቹ ጋር እያመሳከሩ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በዚህ ምዕራፍም፣

- የእስልምናና የአይሁድ/ክርስትና አንድነትና ልዩነት
- እስልምና ለማን ተላከ? ማንንስ አይመለከትም?
- ነብዩ መሀመድና የክርስትናው ዒሳ(ኢየሱስ) ተቃራኒ መሆናቸው፣
- የእስልምና ቅዱሳት መፅሀፍት እና መፅሀፍ ቅዱሱ ተቃራኒ መሆናቸው፣
- አላህ እና የአይሁድ/ክርስቲያን አምላክ ተቃራኒ ሀይላት መሆናቸውን፣

ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## 2.1. የእስልምናና የአይሁድ/ክርስትና አንድነትና ልዩነት

ክርስትናና እስልምና የአብርሃም ሀይማኖቶች እንደመሆናቸው መጠን የሁለቱም መሠረት የአይሁድ ሀይማኖት ነው፣ ክርስትና በ0000 በኢሳ(ኢየሱስ) ሲመሠረት እስልምና ደግሞ በ6ኛው ክፍለ ዘመን(በእስልምና ካሌንደር በ0000) በነብዩ መሀመድ ተመሠረተ፡፡

እስልምና የአይሁድ/ክርስትና መፅሀፍትን፣ ነብያትን፣ መላዕክትን ... የሚቀበል ሲሆን (2፡136, 2፡285፣ 29፡46) ክርስትናው ግን የነብዩ መሀመድን ነብይነትና የቁርአንን ቅዱስ መፅሀፍነት በአጠቃላይ በነብዩ መሀመድ የተሰራውን የእስልምናን መንገድ አይቀበልም፡፡

አይሁድ/ክርስቲያኑ የእስልምናን መንገድ የማይቀበለው "ኢሳ ተመልሶ ይመጣል ስለዚህ ዘመኑ(ኪዳኑ) የነብዩ ኢሳና የኢንጅል(የወንጌል) ዘመን ነው፣ የነብዩ መሀመድ መንገድ ከኢሳ መንገድ ተቃራኒ ነው፣ ቁርአኑም ከመፅሀፍ ቅዱስ ተቃራኒ ነው፣ የእስልምናው አምላክና የክርስትናው አምላክ ተቃራኒ ናቸው" በሚል ምክንያት ነው፡፡

የትኛው ትክክለኛ እንደሆነ በዝርዝር የምንመለከት ሲሆን ከዚያ በፊት ግን እስልምና ለማን እንደተላከ አስቀድመን እንመለከታለን፡፡

## 2.2. እስልምና ለማንስ ተላከ? ማንንስ አይመለከትም?

እስልምና የአብርሃም ሀይማኖቶች ከሚባሉት ሀይማኖቶች ውስጥ እንደመሆኑ መጠን ሀይማኖቱም ከሱ በፊት ለነበሩት የአብርሃም ሀይማኖቶች ለአይሁድና ለክርስትና እውቅና ይሰጣል፣ በዚህም አይሁድ/ክርስቶያኖችን "የመፅሃፍቱ ባለቤቶች" (29፡46)፣ "መፅሃፉን የሰጠናቸው" (13፡36) "መፅሃፉን የሚያነቡ" (2፡113)፣ "ቀድሞ እውቀት የተሰጣቸው"(17፡107)፣ ቀድሞ ያመኑት(16፡102) ... ሲላቸው፣ አይሁድ/ክርስቲያኑም ከቁርአን በፊት የተሰጣቸውን መፅሀፍት አጥብቀው እንዲይዙና በያዙት ሀይማኖት እንዲጠነክሩ ይመክራል (5፡66-69, 7፡145, 2፡121 ...)፡፡

ቁርአኑ የወረደበትን ምክንያት ስለ ራሱ ሲናገር "ለአረጋጋጭነት" መሆኑን ይናገራል (6፡92, 2፡41, 2፡91, 2፡97, 3፡3 ...)፣ አረጋጋጭነት የሚያስፈልገው ቀደምት ቅዱሳን መፅሀፍት ከፈጣሪ መውረዱን ላላረጋገጡት

ማህበረሰቦች ነው ነገር ግን አይሁድ/ክርስቲያኖች የተሰጣቸውን መፅሀፍት፣ ከቁርአኑ መምጣት በፊት፣ አረጋግጠው ሀይማኖታቸውን አቁመውበት የነበሩ በመሆኑ የቁርአኑ "አረጋጋጭነት" ብሎም እስልምና ለነዚህ አይሁድ/ክርስቲያን ህዝቦች አለመሆኑን ያሳያል ይባሱኑ ደግሞ ቁርአኑ እንደሚናገረው ቀደምት ለአይሁድ/ክርስቲያኖች የወረዱት መፅሃፍት በጣም የተብራሩ(2፡99, 37፡117)፣ የተዘረዘሩ(6፡98) እንዲሁም ግልፆች(45፡17) መሆናቸውንና ሙስሊሞች እንኳን ከቁርአኑ ያልገባቸውን ነገር ቢኖር ቀድሞ መፅሀፍ የወረደላቸውን አይሁድ/ክርስቲያኖችን እንዲጠይቁ ማዘዙ(21፡7) "አረጋጋጭ" የተባለው ቁርአን ለአይሁድ/ክርስቲያን ማህበረሰብ አለመላኩን በድጋሚ ያረጋግጥልናል፡፡

ቁርአኑ በአይሁድ/ክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ስላለው ሚና ሲናገር፣

> 16፡102 "እነዚያ ያመኑትን(አይሁድ/ክርስቲያኖች) ለማረጋጋት፣ ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር(ቁርአንን) ቅዱሱ መንፈስ(ጅብሪል) እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው፡፡"

በማለት አይሁድ/ክርስቲያኑ ከላይ እንደተነገረው በራሱ ሀይማኖት እንዲረጋጋ ሙስሊሙ ደግሞ በቁርአኑ እንዲመራ እንደወረደ ይነግረናል፡፡

ታድያ ቁርአን የተላከለት የትኛው የህብረተሰብ ክፍል ነው? ብለን ስንጠየቅ ቁርአኑ "<u>እንደ አይሁድ/ክርስቲያን ነብይም መፅሀፍም ላልተላከላቸው ማህበረሰቦች" መሆኑን ለይቶ ይናገራል</u>፣

- 32፡3 "… በእርሱ(በቁርአኑ) ከአንተ በፊት ከአስፈራሪ(ነቢይ) ያልመጣላቸውን ህዝቦች ልታስፈራራበት (ያወረድንልህ) ነው፡፡ እነርሱ ሊመሩ ይከጅላልና(ይፈለጋልና)፡፡"
- 34፡44 "የሚያጠኑዋቸው የኾኑ መፅሀፍቶችን ምንም አልሰጠናቸውም፡፡ ከአንተ በፊትም አስፈራሪ ነብይን ወደ እነርሱ አልላክንም፡፡"
- 43፡23 "…ከበፊትህ በማንኛይቱም ከተማ ውስጥ እሰፈራሪ አልላክንም…"

እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ ከዓለም ህዝብ ውስጥ የትኞቹ ህዝቦች እንደሆኑ ቁርአኑ ለይቶ ይናገራል፣ ይህንን ከመመልከታችን በፊት

እንደ ቁርአኑ አንድ የፈጣሪ የአሰራር እንመልከት፣ ይህም መልዕክተኛ የሚላከው ለወገኖቹና በወገኖቹ ቋንቋ ብቻ መሆኑ፣

- 14፡4 "ከመልክተኛ ማንኛውንም ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ <u>በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አላክንም፤</u>"

- 30፡47 "ከአንተ በፊት መልዕክተኞችን <u>ወደየህዝቦቻቸው</u> በእርግጥ ላክን፡፡"

በዚህም መሠረት ቁርአን/እስልምና የተላከላቸው ህዝቦች፣

9፡128 "<u>ከጎሳችሁ የሆነ</u> ችግራችሁ በእርሱ ላይ ፅኑ የሆነ፣ በእናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምዕመናን ላይ ሩኅሩኅ አዛኝ የሆነ መልዕክተኛ መጣላችሁ፡፡"

በተባለው መሠረት ቁርአኑ የተላከው ለመሀመድ ጎሳ ለአረብ ህዝቦች ነው፣

44፡58 "(ቁርአኑን) በቋንቋህም ያገራነው (ህዝቦችህ) ይገነዘቡ ዘንድ **<u>ብቻ</u>** ነው፡፡"

ቁርአንም በአረብኛ የወረደው ለዚህ መሆኑን በብዙ ክፍሎች ላይ ተመልክቷል (26፡196, 20፡113, 13፡37, 12፡2, 43፡3, 42፡7, 41፡3, 39፡28...)፡፡

በዚህም ቁርአን/እስልምና የተላከው ለአይሁድ/ክርስቲያን አለመሆኑና የተላከውም ለአረቡ ማህበረሰብ **<u>ብቻ</u>** መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም ከአረብ ውጪ ያለ ሰው ቢሰልም እስልምናው ቁርአናዊ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

ይህ እውነታም ቁርአኑ በደነገጋቸው ሀይማኖታዊ ስርአቶች ውስጥም ማስተዋል ይቻላል፣ በቁርአን ውስጥ የተደነገጉት ሀይማኖታዊ ስርአቶች የታዘዙት ለአረቡ ዓለም እንጂ አጠቃላይ ዓለምን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አይደለም፣ በዚህም እስልምናን ለአጠቃላይ ዓለም ካደረግን ሌላው ዓለም ከነዚህ ስርአቶች ጋር ይፋለሳል፣ ለምሳሌ፣

- የስግደት አቅጣጫ ወደ መካ መሆኑ ነገር ግን ይህ አባባል ትክክለኛ የሚሆነው ለአረቡ አካባቢ እንጂ ክብ በሆነችው አለም ላይ ለሚኖሩ ህዝቦች አለመሆኑ፣ ምክንያቱም ከአረብ እየራቅን በሄድን ቁጥር የመካ አቅጣጫ በአንግል እየተገለበጠ የሚሄድ በመሆኑ፣ ከአረብ ሀገራት እየራቅን ስንሄድ በመካ አቅጣጫ መስገድ አይቻልም፣
- የጨረቃ ለጋነት ለሀጅና ዑምራህ፣ ለፆም ... ምልክት እንደሆነ መነገሩ ነገር ግን ይህ በምልክትነት የሚያገለግለው በአንድ በተወሰነ ክልል ለሚኖሩ ማህበረሰቦች እንጂ ለአለም ህዝቦች አለመሆኑ፣ ላንዱ ለጋ ጨረቃ፣ ለሌላው ደምቃ የምትታይ ወይንም ስታበራ ከርማ እየገባች ያለች ... መሆኗ፣ እነዚህን በአንድ ላይ በአንድ ጊዜ መፈፀም ያለባቸውን ፕሮግራሞች የሚያፋልስ መሆኑ፣
- የሶላት ሰአቶች በፀሃይ እንቅስቃሴ የሚወሰን መሆኑ ነገር ግን ከአረቡ አካባቢ እየራቅን በሄድን ቁጥር ይህ በፀሀይ ላይ ተመርኩዞ የሚከናወነው የስግደት ሰአት እየተዛባ የሚሄድ መሆኑና በተጨማሪም በተለያዩ ሀገራትም የጭለማና የብርሃን ምጣኔ የሚለያይ መሆኑ ሶላት በፀሀይ ምልክትነት ተጠቅሞ በአንድ ላይ በአንድ ጊዜ እንዳይፈፀም የሚያደርግ መሆኑ፣
- ሀጅና ዑምራህ ሀይማኖታዊ ግዴታዎች ቢሆኑም ነገር ግን ቴክኖሎጂ ባልሰተስፋፋበት ዘመን ሰዎች ከአሜሪካ፣ ከአውስትራሊያ .. ከመሳሰሉ ሩቅ ቦታዎች መገኘት የማይችሉ መሆኑን በተጨማሪም የዓለም ህዝብ ቢሰልም እንኳን ቦታው ማስተናገድ የማይችል መሆኑና በአሁኑ ጊዜ እንኳን ለዚህ ጉዞ ሀገራት የሚስተናገዱት በተሰጣቸው ኮታ መሆኑ፣
- የሚዲያ ቴክኖሎጂ ባልነበረበት ጊዜ የታወጀው ፆም የሚከናወነው ቀን መሆኑና ከአረቡ አለም እየራቅን ስንሄድ የቀንና የማታው መቀያየሪያ ሰአት እየተለያየ የሚሄድ መሆኑ፣ በዚህ ለአንዱ ቀን ሲሆን ለሌላው ማታ መሆኑ፣ አንዱ ፆም ሲይዝ ለምሳሌ ለሌላው ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት መሆኑ፣ ወይ "ፆም ተፈታ" ሲባል ለሌላው ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት መሆኑ ...

ቁርአኑ ይህንን የጂኦግራፊ አለመናበብ እንዳይከሰት ከላይ እንደተመለከትነው ቁርአኑ ለአረብ መላኩን ከመናገር አልፎ ላልገባው በጂኦግራፊ ቋንቋ ጭምር ይናገራል፣

42፡7 “እንደዚሁም የከተሞች እናት የሆነችውን (የመካን ሰዎች) እና በአካባቢዋ ያሉትንም ልታስፈራራ ... ልታስጠነቅቅ ዐረብኛ የኾነን ቁርአን ወዳንተ አወረድን፡፡”

እነዚህን ከላይ ከቀረቡትን እውነታዎች በአንድ ላይ ስንመለከት ቁርአኑ/እስልምና የተላከው ለአይሁድ/ክርስትና ተከታዮች አለመሆኑና ተለይቶ የተላከው አረብኛ ተናጋሪ ለሆኑ፣ በመካና በአካባቢዋ ለሚኖሩ የአረብ ህዝቦች ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ሰዎች አልገባቸውም እንጂ ይህ ሀይማኖትን በየማህበረሰቡ የመከፋፈል አሰራር ታስቦበት የተደረገው መሆኑን ቁርአን ይናገራል፣

5፡48 “ከእናንተ ለሁሉም ህግንና መንገድን አደረግን፡፡ አላህም በሻ ኖሮ አንድ ህዝብ ባደረጋችሁ ነበር፡፡ ግን በሰጣችሁ ህግጋት ሊሞክራች (ሊያያችሁ)፡፡ በጎ ስራዎችን ለመስራት ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው፡፡”

በዚህም እንደ ቁርአኑ በሶስቱም የአብርሃም ሀይማኖቶች(እስልምና፣ አይሁድ፣ ክርስትና) መካከል ያለው ክፍፍል በአላህ ዘንድ እውቅና ያለው መሆኑን፣ ሁሉም በአንድ መንገድ ላይ መሆናቸውን፣ ገነት የሚገቡትም ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ አይሁዳውያንና ክርቲያኖችም ጭምር መሆኑን(2፡62, 5፡69 ...)፣ አይሁድ/ክርስቲያኖችም “እኛ ብቻ ነን ገነት የምነገባው” እንዳይሉ ማዘዙን(2፡111-112)፣ ሶስቱም ሀይማኖት ተከታዮች ገነት የሚገቡትም በተሰጣቸው መሪ(13፡7) መሪነት(17፡71) መሆኑና የየሀይማኖቶቹ መሪ፣

- የአይሁድ መሪ ሙሳ (32፡23, 17፡2 ...) የተሰጠውም መፅሀፍ ተውራት (5፡44, 5፡66-68, 61፡5 ...)
- የክርስቲያን መሪ ኢሳ/ኢየሱስ (57፡27)፣ የተሰጠውም መፅሀፍ ኢንጅል(5፡46-47, 57፡27 ...)
- የእስልምና መሪ መሀመድ (6፡163, 39፡12, 33፡21 ...) የተሰጠውም መፅሀፍ ቁርአን(5፡48)፣

በዚህም ሁሉም ህዝብ በየግል በተሰጠው መሪና መፅሀፍ እንዲተዳደር ቁርአኑ ያስተምራል፣

5፡44-48 “እኛ ተውራትን(ኦሪትን) በውስጧ መምርያና ብርሀን ያለባት ስትሆን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚህ አይሁዳውያን በሆኑት ላይ በእርሷ ይፈርዳሉ … ኢንጅልንም(ወንጌልንም) … (ለኢሳ) ሰጠነው፡፡ የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ህግ ይፍረዱ፡፡ ወደ አንተም መፅሀፉን(ቁርአንን) … አወረድን … በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ህግ ፍረድ …”

በዚህም ሙሴ የአይሁድ፣ ኢየሱስ የክርስቲያን፣ መሀመድ የአረብ መሪዎች መሆናቸውንና አማኞችም ገነት የሚገቡት በነዚህ መሪዎቻቸው መሪነት መሆኑን ቁርአኑ ይናገራል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ እንደ ቁርአን አስተምህሮ፣ የአይሁድና/የክርስትና ሀይማኖቶች በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የእስልምና እህት የሀይማኖት ድርጅቶች መሆናቸውንና ቁርአን/እስልምና የተላከው ለአረቡ ማህበረሰብ ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም ከአረብ ውጪ ያሉት ህዝቦች ቁርአን/እስልምና የማይመለከታቸው መሆኑንና ቢሰልሙ እንኳን እስልምናቸው ቁራናዊ አለመሆኑን ቁርአን ያመላክተናል፡፡

ስለዚህ ከአረብ ዘር ውጪ የሆኑ ሙስሊሞች የቁርአኑ/የእስልምና መንገድ የገነት መሄጃ መንገዳቸው አይደለም፣ በዚህም እንደ ቁርአኑ ከአረብና ከአይሁድ ዘር ውጪ ላለ ማንኛውም ሰው ለገነት መግቢያነት የተቀመጠለት መንገድ በዘር ያልተወሰነውና በደፈናው “ተከታዮቹ፣ የኢንጅል ባለቤቶች …” በተባለው የኢሳን(ኢየሱስን) መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- 57፡27 “… የመርየም ልጅ ኢሳን … ኢንጅልንም ሰጠነው፡፡ በዚያም በተከተሉት (ሰዎች) ልቦች ውስጥ መለዘብንና እዝነትን … አደረግን፡፡”
- 5፡47 “የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ህግ ይፍረዱ”

ከዘር ጉዳዮች በተጨማሪ እስልምና ከፆታ አንፃርም የተለየ አሰራርን ይከተላል ይህም በእስልምና መንገድ ሴቶች ጀነተ/ገነት እንደማይገቡ ይናገራል፣ ይህንንም የሚናገረው ምክንያታዊ በመሆነ ሴቶች ያለባቸውን እስልምናዊ ችግር በቅድሚያ በመግለፅ ነው፣ ይህም ሴቶች፣

- <u>“እርኩስ ናቸው”</u>

  4፡43 “… ከእናንተ አንዱ ከአይነ ምድር ቢመጣ ወይንም ሴቶች ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ፣ ንፁህ የሆነ የምድር ገፅ አስቡ፡፡ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በራሱ) አብሱ፡፡ አላህ ይቅር ባይና መሃሪ ነውና፡፡”

  በዚህም ወንዱ ሳያውቅ ቢረክስ በመታጠቡ ይነፃል ነገር ግን ሴትዋ ሴትነትዋ ማንነቷ ነው፣ በዚህም ሴት በሴትነቷ ብቻ ቁርአናዊውን “የቅድስናውን ህግ” ማለፍ አትችልም፣ “ያልተቀደሰ(እርኩስ)” ደግሞ ገነት አይገባም፡፡

  ሰሂህ ሙስሊም 4፡1038 “ስትሰግዱ ውሻ፣ ሴትና ፈስ ቢያቋርጡ ስግደት ከንቱ ትሆናለች፡፡” ተመሳሳይ ሀሳብም ሰሂህ ሙስሊም 4፡1032፣ ሰሂህ ቡኻሪ 1፡9፡490 ላይ ቀርቧል፡፡

  እንደ ቁርአኑ እነዚህ ሶስቱ ነገሮች የፀሎት አርካሽ እርኩስ ነገሮች ናቸው፣ ይህም ከላይ ያየነውን “ሴት እርኩስ ናት” የሚለውን የቁርአኑን አስተምህሮ መልሶ ያረጋግጣል፣ “እርኩስ” ደግሞ ገነት አይገባም፡፡

- <u>“በተፈጥሮ ጠማማ ናቸው”</u>

  ሰሂህ ቡኻሪ 4፡55፡548 “ሴቶች ከጎድን አጥንት የተፈጠሩ ናቸው፣ የጎድን አጥንት የተጣመመ ነው፣ ላቃናው ብትሉ ይሰበራል፣ ነገር ግን እንደ ጠማማነቱ ብትተዉት እንደተጣመመ ይቀመጣል፡፡”

  ጠማምነት ያለበት ደግሞ ገነት አይገባም፡፡

- <u>“ከምንም ነገር በላይ ጎጂ ናቸው”</u>

  ሰሂህ ሙስሊም 36፡6603 “ከሴት ይበልጥ ጎጂ ስቃይ ለወንድ አልተውኩም፡፡”

  የዚህ ተመሳሳይ ሀሳብም ሰሂህ ሙስሊም 36፡6604 ላይ ቀርቧል፣

- “የወንዶች ግማሽ ናቸው”
  - 4፡11 “አላህ በልጆቻችሁ (ውርስ በሚከተለው) ያዛችኋል፡፡ ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ብጤ አለው፡፡”
    የዚህ ተመሳሳይ ሀሳብ በሳሂህ ሙስሊም 11፡3933 ላይም ቀርቧል፡፡
  - 2፡282 “የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ እኩል ነው፡፡” የዚህ የዚህ ተመሳሳይ ሀሳብ ሳሂህ ቡኻሪ 3፡48፡826 ላይም ቀርቧል፡፡
- “አእምሮ ጎዶሎ ናቸው”

  ሰሂህ ቡኻሪ 3፡48፡826 “… ነቢዩም፣ የሴት ምስክርነት የወንድ ምስክርነት ግማሽ አይደል፣” አሉ፣ ሴትየዋም “አዎን” አለች፣ ይህ የሆነው የሴቶች አእምሮ ጎዶሎ(deficiency in intelligence) በመሆኑ ነው፣ አለ፡፡”

  የዚህ ተመሳሳይ ሃሳብ በሳሂህ ቡኻሪ 1፡6፡301 ላይም ቀርቧል፡፡

በርግጥ ገነት ቅድስና ያላት ቦታ በመሆኗ እርኩስ፣ ጠማማ፣ መጥፎና ሙሉ ያልሆነ ሰው ሊገባባት አይችልም፣ በዚህም ሴቶች በእስልምና መንገድ ገነት መግባት አይችሉም፡፡ ነብዩ ይህንን ትምህርት ያስተማሩት የምራቸውን መሆኑን የምንረዳው ደግሞ ሁሉም ልጆቻቸው ሴቶች በሆኑበት (33፡40) እና ለነሱ እንኳን ማዳላት በሚገባቸው ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡

በተቃራኒው ደግሞ ወንዶች በሴቶች ላይ በሚሰሩት ሀጢያት እንኳን ከገነት እንዳይጎድሉ “ሴቶችን ከመጉዳት ከሚመጣ ሀጢያት ተጠያቂነት” ነፃ ተደርገዋል፣ በዚህም ወንዱ በህጋዊው እስከ አራት(4፡3) በምርኮ የያዛቸውን እስከ ፈለገው(4፡24) ማግባት፣ ያገባትንም ሲፈልግ መፍታት(2፡227, 33፡51)፣ የፈታትን መልሶ ማግባት(2፡228, 33፡51)፣ በሚስት ስፍራ ሚስት መለወጥ(4፡20)፣ ሚስቱን መደብደብ(4፡34, 38፡44, 70፡30-31)፣ ጊዜያዊ ጋብቻ/temporary marriage(ሰሂህ ሙስሊም 8፡3253፣ ሰሂህ ቡኻሪ 7፡62፡12) ማድረግ እንደሚችል፤ ለሴት ገንዘብ ሰጥቶ(4፡24)፣ ሰአት ሰጥቶ(ሰሂህ ሙስሊም 8፡3252)፣ ልብስ ሰጥቶ (ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡139) ዝሙት መፈፀም እንደሚችል፤ ለሴት የገባውን መሃላ ማፍረስ እንደሚችል(2፡226) ይናገራል፡፡ ነብዩ መሀመድ ደግሞ ከነዚህ በተጨማሪ ዘጠኝ ህጋዊ ጋብቻዎች(ሰሂህ ቡኻሪ 7፡62፡6)፣ ውሽሜዎች መያዝ፣ የውሽሜዎቹን ልጆች ማግባት፣ የአጎት/የአክስት ሴቶች ልጆች

ማግባት(33፡50-51)፣ ከባሮች ጋር መተኛት(33፡52)፣ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች የ9 አመት ልጅ ማግባት(ሰሂህ ቡኻሪ 5፡58፡236) ተፈቅዶለታል፡፡

ወንዱ በገነት ከሚጠብቀው ሽልማቶች አንዱ "በገነት ውስጥ አይናቸው ጎላ ጎላ ያሉ ሴቶች ናቸው"(52፡20-25, 44፡54 ...) ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው በእስልምናው ሴቶች ገነት ስለማይገቡ ቁርአኑ ለሴቶቹ "አይናቸው ጎላ ጎላ ያሉ ወንዶች/ወንድ እንደሚጠብቃቸው" አይናገርምም ወይ እነሱ ከባሎቻቸው ቀድመው ሞተው ገነት ገብተው አይናቸው ጎላ ጎላ ተደርገው ለባሎቻቸው እንደ ሽልማት እንደሚዘጋጁ አይናገርም፣ እንደውም አሁን ሞተው ያሉ ሙስሊም ወንዶች 83፡22 "እውነተኞቹ ምዕመናን በእርግጥ በድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው፡፡" ማለቱ የዚህ አለም ሴቶች ተስፋ እንደሌላቸው እንመለከታለን፡፡

ይባሱኑ ደግሞ ጃሚያ አት ትርሚዲ 2562 "... በገነት ዝቅተኛ ቦታ ያለ ሰው 72 ሚስቶች ይኖሩታል፡፡" ማለቱና ለአንድ ወንድ የሚሸለሙት ሚስቶች ብዛት ምጣኔን ስንመለከት የገነት ሴቶች ከዚህ አለም አለመሆናቸውን እናስተውላለን፣ ታዲያ እነዚህ ሴቶች እነማን ናቸው? ብለን ስንመለከት፣

- ለወንዶቹ የሚዘጋጁት ሚስቶች ከመላዕክት መሆኑ፣
  17፡40 "ጌታችሁ በወንዶች ልጆች መረጣችሁና ከመላዕክት ሴቶች (ልጆች) ያዝን ..."
- ስማቸውም ሁሪ(Houri) እንደሚባሉ፣
  ሰሂህ ቡኻሪ 4፡55፡544 "... ገነት የሚገቡት ሰዎች ሚስቶቻቸው ሁሪ ናቸው፡፡"

ስለነዚህ ሴት መላዕክት ውበትም ሲናገር

- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡52፡53 "አንድ ሁሪ ወደ ምድር መጥታ ለሰዎች ብትታይ በሰማይና በምድር መካከል ያለውን ቦታ በመልካም መዓዛ ትሞላዋለች፡፡"

- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡476 "... ሁሪዎች አጥንትና ስጋቸው ብርሀን የሚያሳልፍ (እንደ መስታወት /transparent) በመሆኑ መቅኔያቸው ይታያል፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡469 "... ገነት የሚገቡት ሰዎች ሚስቶች ቆንጆዎች ናቸው፣ በስጋቸው ውስጥ የአጥንታቸው መቅኔ የሚታይ (transparent flesh) ናቸው፡፡"

በዚህም ሴቶች "እርኩስ ናቸው" ብሎ የጀመረው፣ በገነት ለሴቶች የሚሰጠውን ሽልማት ያልተናገረው፣ ለወንዶቹ የሚሸለሙት ሴቶች ከሰው ዘር ያልሆኑ "ሁሪ" መሆናቸውን ይናገራል፡፡

በዚህም ሴቶች በእስልምናው መንገድ የገነት መግቢያ እድል እንደሌላቸው እንመለከታለን፣ ስለዚህ በእስልምና ውስጥ ያሉ ሴቶች የገነት መግቢያ መንገድ ማግኘት የሚችሉት በፆታ ያልተገደበውና ቁርአኑ በደፈናው "ተከታዮቹ"(57፡27)፣ የኢንጅልም ባለቤቶች(5፡47) ... ባለው በኢሳ(ኢየሱስ) መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

የኢሳን መንገድ የሚሰብከው የክርስትናውን መንገድ የተላከው ለአለም እንጂ ለአንድ ዘር አለመሆኑ(ዮሐ.6፡33, ዮሐ.8፡26፣ ዮሐ.18፡20፣ ሮሜ.11፡15, ገላ.6፡14 ...)፣ ከዚህ በተጨማሪም ኢንጅል(ወንጌሉ) ላይ በፆታ የተከፈለ አሰራር እንደሌለ መናገሩ(ገላ.3፡28)፣ ወንድና ሴት የሚባለው ክፍፍል የመጣው ለ"ብዙ ተባዙ" ህግ እንጂ ለዘላለማዊ ማንነት አለመሆኑና ወደ ገነት ሲገባም የ"ብዙ ተባዙ" አሰራር ስለሌለ ሁሉም የሚሰጠው እንደ መላዕክት ፆታ የሌለው ሰማያዊ አካል መሆኑን(ማቴ.22፡30)፣ በአጠቃላይ ፈጣሪ ሁሉንም ዘርና ፆታ እራሱ የፈጠራቸው በመሆኑ አንዱን እርኩስ አንዱን ቅዱስ የሚደረግበት አሰራር የሌለው መሆኑ፣ ለሁሉም ዘር ሆነ ለሴቶች ገነት ለመግባት የተዘጋጀላቸው መንገድ የኢሳ የክርስትና መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ መፅሀፍ ቅዱሱ ራዕ.2፡5 "እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ..." እንደሚለው በእስልምናው መንገድ ያልተጠቃለሉት አረብ ያልሆኑት ዘሮችና ሴቶች እስልምና እንዳማይመለከታቸውና የሰለሙት እንኳን እስልምናቸው ቁርአናዊ ባለመሆኑ እነዚህ ሙስሊሞች በዘርና በፆታ ወዳልተገደበው ወደ ኢየሱስ(ኢሳ) መመለስ እንዳለባቸው እንመለከታለን፡፡

## 2.3. ነብዩ መሀመድና የክርስትናው ዒሳ(ኢየሱስ) ተቃራኒ መሆናቸው

[15] ነቢዩ መሀመድ ከ570 እስከ ሰኔ 8, 632 ድረስ በአረቡ አለም የኖሩ የእስልምና ሀይማኖት መስራችና መሪ ናቸው፣ ነብዩ የአይሁድ/ክርስትና ነቢያትን ነብይነት የሚቀበሉ ሲሆኑ፣ የሁሉንም ነብያት ታሪክ በበጎ ጎን አንስተዋል ኢድሪስ/ሄኖክ(19፡56)፣ ኢብራሂም፣ ኢስማኢልና ኢስሐቅ(2፡127)፣ ያዕቁብ(2፡132) አሮን/ሀሩን(2፡248)፣ ሳሙኤል(2፡246)፣ ሳኦል/ጧሉት(2፡247)፣ ዳዊት/ዳውድ(2፡251)፣ ኢየሱስ/ዒሳ(2፡253)፣ የህያ/ዮሐንስ(19፡7) … የብዙ የእስራኤል ነቢያት ስም ዝርዝር በ6፡83-86 ውስጥ በሰፊው ተመልክቷል፡፡

ነብዩም በዚህ የእስራኤል ነብያት መንገድ በነብይነት መሾማቸውን ይናገራሉ፣

- 33፡7 "ከነቢዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን ከአንተም፣ ከኑህም፣ ከኢብራሂምም፣ ከሙሳም ከመሪየም ልጅ ዒሳም በያዝን ጊዜ አስታውስ…"
- 6፡90 "እነዚህ(ነቢያት)፤ እነዚያ አላህ የመራቸው ናቸው፡፡ በመንገዳቸው ተከተል፡፡"
- 40፡78 "ካንተ በፊት መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡"

በማለት ነብዩ መሀመድ በቀደመው የነብያት መንገድ በነብይነት እንደተላኩ ይናገራሉ፡፡

ነገር ግን የነብዩ መሀመድና ከላይ የተጠቀሱት የመፅሀፍ ቅዱስ ነብያት መንገድ ስናነፃፅር መንገዳቸው ለየቅል፣ እንደውም እርስ በርስ ይጋጫል፣ ለምሳሌ እንዲሆነንም ከመፅሀፍ ቅዱሱ ነብያ የዋናውን የኢሳን(ኢየሱስን) መንገድ ከመሀመድ መንገድ ጋር እናነፃፅራለን፣ በዚህም፣

- ከነብይነት ሹመት አንፃር፣
- ከቀደምቱ ነብያት መንገድ የአቅጣጫ ለውጥ ከማድረግ አንፃር
- ከሀይማኖት መሪ ስብዕና አንፃር

ሁለቱንም እያነፃፀርን እንመለከታለን፡፡

[15] https://en.m.Wikipedia>wiki>Muhammed in Islam

### 2.3.1. የነብዩ ኢሳ(ኢየሱስ) እና የነብዩ መሀመድ የነብይነት ሹመት

ኢሳ(ኢየሱስ) በነብይነት መሾሙን ቁርአኑ ብዙ ቦታዎች ላይ ተመልክቷል ነገር ግን የነብዩ መሀመድ ነብይነት ላይ ብዙ አጠያያቂ ነገሮችን ያሉበት ሲሆን የነብያትን አነሳስ በሚያውቀው በምስራቁ አለም ማህበረሰብም በመሀመድ ነብይነት ላይ ብዙ ጥያቄዎች ሲነሳ ነበረ፡፡

ነብዩ መሀመድ በነብይነት የተነሱት ቁርአንን በሂራ ዋሻ ውስጥ ከጅብሪል(ገብርኤል) ከተቀበሉ በኋላ ነው(ሰሂህ ቡኻሪ 1፡1፡3)፣ ከዚያም በኋላ ግን ነብይነታቸው "በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበረ" አሉ፡-

- 61፡6 "የመርየም ልጅ ኢሳም፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ … ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ <u>አሕመድ</u> በሆነው የማበስር ስኾን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልእክተኛ ነኝ …"
- 7፡157 "ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራት(ኦሪት)ና በኢንጅል(ወንጌል) ተፅፎ የሚያገኙትን <u>የማይፅፍና የማያነብ ነቢይ</u> የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉት ለኾኑት (በእርግጥ እፅፍለታለሁ)፡፡"

ነብዩ መሃመድ "ስለኔ ነብይነት በመፅሃፍ ቅዱሱ ላይ ተተንብዮ ነበር" ቢሉም ይህ አባባል መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ባለመኖሩ ነብይነታቸው በወቅቱ መፅሃፍ ቅዱሱን በያዘው ማህበረሰብ ተቀባይነት ማግኘት አልቻለም ይባሱኑ የክርስትና ነብያት አነሳስ ታሪክ ለሚያውቀው የአረቡ ማህበረሰብ፣ ለነብይነቱ እውቅና ለመስጠት "እንደ ቀድሞዎቹ ነብያት ተአምራት ያሳየን" አሉ፣

- 21፡5 "የቀድሞዎቹም እንደተላኩ (መልእክተኛ ከሆነ) በተአምር ይምጣብን አሉ፡፡"
- 13፡7 "እነዚያ የካዱት በእርሱ ላይ ከጌታው ተአምር ለምን አልተወረደለትም ይላሉ …"

ነብዩም "ነቢይ ነኝ ነገር ግን ተአምራት አልተሰጠኝም" የሚል መልስ ሲሰጡ ከቆዩ ቦሃላ፣ ይህ መልስ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ተአምራት መሞከር እንዳለባቸው ተገነዘቡ፣ በዚህም 21፡37 "ሰው ቸኳይ ሆኖ ተፈጠረ፡፡ ተአምራቶቼን በርግጥ አሳያችሃለሁና አታቻኩሉኝ፡፡" ሲሉ ቆይተው በመቀጠልም "ተአምራት ሰሩ" የሚሉ መረጃዎች ተለቀቁ፣ እነዚህ ተአምራቶችም፣

- ውሃን ጠርተው ሰዎችን ማስታጠባቸውን(ሰሂህ ሙስሊም 30፡5656)
- ጨረቃን ሰንጥቀው መክፈላቸውን (ሰሂህ ሙስሊም 39፡6728)

የሚገልፁ ዘገባዎች ሲሆኑ ነገር ግን እነዚህ ዘገባዎች ከቁርአኑ "ተአምራት ያልያዘ ነብይ" ከሚለው ሀሳብ ጋር የሚጋጭ መሆኑ፣ መረጃውም የሰዎች ዘገባዎች በሚፃፍበት በሀዲሱ እንጂ በዋናው ቁርአን ላይ አለመመልከቱና ማህበረሰቡም ተአምራቱን በዘገባ እንጂ በአይኑ ያልተመለከተው በመሆኑ አሁንም ነብይነታቸው ተቀባይነት ማግኘት አልቻለም፡፡

በዚህም ነብዩ መሀመድ "በእስራኤላውያኑ ነቢያት መንገድ ነኝ" የሚለው አካሄድ እንደማያዋጣቸው አስተዋሉ፣ የእስራኤላውያኑ ነብያት መንገድ የሚያዋጣው ተአምራት ለያዘና ተአምራቶቹን ለህዝቡ እያሳየ ህዝቡን መምራት ለሚችል ነብይ ብቻ ነው፣ እሳቸው ደግሞ ተአምራት ባለመያዛቸው በዚህ መንገድ መሄድ አልቻሉም፣ በዚህም ከተጀመረው መንገድ የአቅጣጫ ለውጥ ተደረገ፡፡

### 2.3.2. <u>የነብዩ መሀመድ የአቅጣጫ ለውጥ</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ነብዩ መሀመድ በነባሩ የነብያት መንገድ ተቀባይነት በማጣታቸው በመጀመርያ ካስተማሩት መንገድ በመውጣት የአይሁድ/ክርስትናን መንገድ በመተው በራሳቸው መንገድ ሀይማኖት አቋቋሙ፣ በዚህም በመጀመርያ ከአይሁድ/እስራኤላውያኑ ጋር ያሳዩትን አንድነት በመተው የሀይማኖት ባለቤት ፈጣሪ መሆኑን ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባ መልኩ በመጀመርያ የጀመሩትን መንገድ በመተው የጀመሩትን ሀይማኖት በሌላ መንገድ አስኬዱት፣ በዚህም ነብዩ መሀመድ፣

- የእስራኤል ነብያትን በመተው ብቸኛ ነብይነታቸውን አወጁ፣
- የእስራኤል ቅዱሳን መፅሀፍትን በመተው ቁርአኑን ብቻ ተከተሉ፣
- ስለ አይሁድ/ክርስትናን ያስተማሩትን የአንድነት ትምህርት በመተው "ትክክለኛ ሀይማኖት እስልምና ብቻ ነው" አሉ፣
- ከአይሁድ/ክርስትናው የተቃረነ ሀይማኖት ማስፋፍያ እስትራቴጂን ተከተሉ፣

ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 2.3.2.1. <u>የእስራኤል ነብያትን በመተው ብቸኛ ነብይነታቸውን ማወጅ</u>

ነብዩ መሀመድ በሰላሙ ጊዜ የአይሁድ/እስራኤል ነብያትን ነብይነት ተቀብለው ነበረ፣

- 33፡7 "ከነቢዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን <u>ከአንተም</u>፣ ከኑህም፣ ከኢብራሂምም፣ ከሙሳም ከመሪየም ልጅ ዒሳም በያዝን ጊዜ አስታውስ፡፡ ከእነርሱም የከበደ ቃል ኪዳን ያዝን፡፡"
- 6፡90 "እነዚህ(ነቢያት)፤ እነዚያ አላህ የመራቸው ናቸው፡፡ <u>በመንገዳቸው ተከተል</u>፡፡"
- 40፡78 "<u>ካንተ በፊት</u> መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡162 "... ከሌሎች ነብያት በላይ አድርጋችሁ አትመልከቱኝ ..."

ይሁን እንጂ ነብዩ መሀመድ ነብይነታቸው ላይ በተፈጠረው ጥያቄ ምክንያት ይህንን አስተምህሮታቸውን በመተው "ነብይ እኔ ብቻ ነኝ" የሚል መንገድን ተከተሉ፣

- 22፡52 "ከመልክተኛና ከነቢይም <u>ከአንተ በፊት አንድም አላክንም</u> ..."
- 6፡14 "... እኔ መጀመሪያ ትዕዛዝን ከተቀበለ ሰው ልሆን ታዘዝኩ ..."
- 39፡12 "የሙስሊሞች መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ፡፡"
- 6፡163 "... እኔ የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ፡፡"

አሉ፣ በዚህም፣

- "በአላህና በነቢያቱ ያመነ" የነበረውን "በአላህና በነቢዩ ያመነ" በሚለው ተገደበ (4፡13, 24፡51, 33፡12, 33፡36, 49፡14 ...)
- አምስተኛው የእስልምና ምሰሶ (ካሊማ) - "አላህ ... አልራህማኒ ... <u>መሃመድ ነቢያችን</u> ነው" አማኝ በየፀሎቱ የሚደጋግመው የእምነት ቃል ተደረገ፡፡

በዚህም <u>ነቢዩ የእስልምና መጀመሪያውና መጨረሻው ብቸኛ ነብይ ሆነው ተቀመጡ</u>፣ ይህ የነብዩ የአቋም ለውጥ እስልምና የመጣው ከፈጣሪ ነው ወይስ ...? የሚል ጥያቄን ያጭራል፡፡

### 2.3.2.2. የእስራኤል ቅዱሳን መፅሀፍትን በመተው ቁርአኑን ብቻ መከተል

ነብዩ በሰላሙ ጊዜ የአይሁድ/ክርስትና መፅሀፍትን ሙስሊሙ እንዲጠቀምባቸው ሲያስተምር ነበረ፣

- 3፡3 "አላህ ተውራትን(ኦሪትን)ና ኢንጅልንም(ወንጌልን) አውርዷል፣"
- 2፡136 "በአላህና ወደ እኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስሃቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳም በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን፡፡"
- 4፡136 "በዚያም ከበፊቱ ባወረድነው መፅሃፍ እመኑ፡፡"
- 29፡46 " ... (የመፅሀፉን ባለቤቶች) በዚህ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፡፡"

ብሎ ነበረ ነገር ግን መሀመድ ነብይነቱ ላይ በተፈጠረው ጥያቄ ምክንያት ይህንን አስተምህሮቱን በመተው፣

21፡45 "የማስፈራችሁ በተወረደልኝ **ብቻ** ነው፡፡"

በማለት የእስራኤል መፅሀፍት ጉዳይን ቆርጦ ጣለ፣ በዚህም እስልምናው በመሀመድ ላይ **ብቻ** የተወረደውን ቁርአኑን በመለየት በመፅሀፍ መልክ አሳትሞ ይጠቀምበታል፣ ተውራት፣ ኢንጅል ... የሚባሉት በሙሉ አሁን ቀርተዋል፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ጋር "መፈንቅለ ቀደምት መፅሀፍት" አሰራር ባለመኖሩ ሁሉም ቀደምት መፅሀፍት የፈጣሪ ቃል በመሆናቸው በአንድ መፅሀፍ አሰባስቦ ይዟል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የነብዩ የአቋም ለውጥ እስልምና የመጣው ከፈጣሪ ነው ወይስ ...? የሚል ጥያቄን ያጭራል፡፡

ቁርአኑ ከመነሻው በአይሁድ/ክርስትና መፅሀፍት ላይ ተደግፎ መነሳቱና መልሶ ደግሞ እነሱን ጥሎ በመሄዱ በራሱ ላይ ብዙ ክፍተቶችን ይፈጥርበታል፣ ቁርአኑ ብዙ ታሪኮችን የወሰደው ከመፅሀፍ ቅዱሱ ቀነጫጭቦ ነው፣ ሌሎቹን ታሪኮች ደግሞ በቀጥታ ከአይሁድ/ክርስቲያን መፅሀፍት

እንዲነበብ “አውሳ” (38፡48)፣ “አስታውስ” (7፡171, 8፡32, 15፡28 …) እያለ ማዘዙና ለመሀመድም፣

40፡78 “ካንተ በፊት መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡ ከእነሱም ባንተ ላይ የተረከንልህ አልለ፡፡ ከእነርሱም ባንተ ላይ **ያልተረከነው አልለ**፡፡”

ማለቱና መሀመድም ሙስሊሞች ከቁርአኑ ያልገባቸውን ነገር ቢኖር ቀድሞ መፅሀፍ የወረደላቸውን አይሁድ/ክርስቲያኖችን ጠይቁ ማለቱ(21፡7) ቁርአን መፅሀፍ ቅዱሱን ጥሎ እንዳይሄድ የሚያስገድዱት እውነታዎች ናቸው፣ በዚህም ነብዩ “በቁርአን ብቻ ነው የማስፈራራችሁ” በማለት ቁርአን ለብቻው እንዲወጣ ያደረጉበት አሰራር ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 2.3.2.3. <u>ስለ አይሁድ/ክርስትናን ያስተማረውን የአንድነት አስተምህሮ በመተው “ትክክለኛ ሀይማኖት እስልምና ብቻ ነው” ማለቱ</u>

ነብዩ በሰላሙ ጊዜ አይሁድ/ክርስትና ከእስልምና ጋር አንድ መሆናቸውን ሲያስተምር ነበረ፣

- <u>አምላካችን አንድ ነው</u>
  29፡46 “የመፅሀፉን ባለቤቶች … አምላካችን አምላካችሁ አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡”
- <u>የአይሁድ/ክርስትናን መሠረታዊ ዕሴቶች እንቀበላለን</u>
  2፡285 “… ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመፅሃፍቱም፣ በመልዕክተኞቹም፣ ከመልዕክተኞቹም “በአንድም መካከል አንለይም” … ሰማን ታዘዝንም …”
- <u>ክርስቲያኖች ጥሩዎች ናቸው</u>
  5፡82 “… እነዚያን “እኛ ክርስቲያኖች ነን” ያሉትን ለእነዚያ ለአመኑት(ሙስሊሞች) በወዳጅነት በርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ኾነው ታገኛለህ፡፡ ይህ ከእነሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነርሱም <u>የማይኮሩ</u> በመሆናቸው ነው፡፡”
- <u>አይሁድ/ክርስቲያን ያረደውን ልንበላ፣ ሴቶቻቸውን ልናገባ የተፈቀደ ነው</u>

> 5፡5 “… የእነዚያም መፅሃፍ የተሰጡት ሰዎች ምግብ(ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው … ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መፅሃፍን ከተሰጡት ሴቶች … (ሊታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)፡፡”

ነገር ግን የነብዩ ነብይነት ላይ በተፈጠረው ጥያቄ ምክንያት ነብዩ እነዚህን አስተምህሮቶቹን በመተው፣

> 3፡19 “አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሀይማኖት ኢስላም **ብቻ** ነው …”

በማለት የአይሁድ/ክርስትናን “አፍንጫችሁን ላሱ” ብሎ ጥሏቸው ሄደ፣ በዚህም ቀድሞ የአይሁድ/ክርስትና ስርአቶችን በአረባዊ መንገድ ቀየረ፣

- ወደ እየሩሳሌም የነበረው የስግደት አቅጣጫ(ቂብላ) ወደ መካ (መካ) አዞረ
  - ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡13 “ነቢዩ ወደ ባይት ኡል መቅዲስ(ኢየሩሳሌም) ዞረው ለመጀመሪያዎቹ 16 ወይ 17 ወራት ሲሰግዱ ነበረ፣ ነገር ግን ይህ የስግደት አቅጣጫ ወደ መካ ቢሆን ይመኙ ነበረ፡፡ ከዚያ በኋላ ቂብላቸውን(የስግደት አቅጣጫ) ወደ ከአባ አደረጉት፡፡”
  - 2፡144-145 “የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በርግጥ እናያለን፡፡ ወደ ምትወዳት ቂብላ እናዞርሀለን፡፡ ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር … እነዚያ መፅሃፍን የተሰጡትን በአስረጂ ሁሉ ብትመጣቸው ቂብላህን አይከተሉም፡፡ አንተም ቂብላቸውን ተከታይ አይደለህም፡፡”
- የእረፍት ቀን ከእሁድ ወደ አርብ ቀየረ

  62፡9 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ኺዱ፡፡ መሸጥንም ተው፡፡”
- ካሌንደር ቀየረ

  በኢየሱስ ላይ ተመስርቶ የነበረውን የዘመን አቆጣጠር በሂጅራ አቆጣጠር ተካ፡፡
- ከአይሁድ/ክርስቲያን ጋር ያዘዘውን መልካም ግንኙነት መልሶ ከለከለ
  - 5፡51 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ፡፡”
  - 3፡118 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ ከእናንተ ሌላ ምስጢረኛ አትያዙ…”

- 4፥144 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ ከምዕምናን ሌላ ከሃዲዎችን ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ፡፡”

- ከአይሁድ/ክርስቲያን ጋር መጋባትን መልሶ ከለከለ
  2፥221 “አጋሪዎች(አይሁድ/ክርስቲያኖች) የሆኑ ሴቶች እስኪያምኑ (እስኪሰልሙ) ድረስ አታግቡአቸው፡፡”
- አይሁድ/ክርስቲያን ያረደውን መብላት መልሶ ከለከለ
  - 9፥28 “... አጋሪዎች(አይሁድ/ክርስቲያኖች) እርኩሶች ብቻ ናቸው...”
  - 16፥115 “በእናንተም ላይ እርም ያደረገው ... ያንንም(በመታረድ ጊዜ) በእርሱ ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ብቻ ነው፡፡”
- በአይሁድ/ክርስትና “እርኩስ” የተባለውን ግመል የሀይማኖቱ ምልክት በማድረግ የግመል ስጋ እንዲበላ አዘዘ፣
  22፥36 “ግመሎችን ለእናንተ ከአላህ ሃይማኖት ምልክቶች አደረግናቸው፡፡ ከርሷ ብሉ”

በዚህም ነብዩ እስልምናን ከአይሁድ/ክርስትናው መንገድ ለየ፣ ይህም እስልምና የመጣው ከፈጣሪ ነው ወይስ ...? የሚለውን ጥያቄ ያጭራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሙስሊሞች በተፈጠረው የአቋም መዋዠቅ ምክንያት ወደ ክርስትና እንዳይሳቡ በክርስትና ላይ ጠንካራ ሂሶችን ሰነዘሩ፣ ለዚህ ደግሞ ያመቻቸው ለተራው ሰው ከባድ የሆኑት ጥልቅ መንፈሳዊ ዕውቀት የሚፈልጉት የክርስትና አስተምህሮቶች ናቸው፣ በዚህም ነብዩ አምስቱን የክርስትና ከባድ አስተምሮችን “የክርስትና ስህተት” እንደሆኑ አስተማሩ ነገር ግን ነብዩ ቀድሞ የክርስትና አስተምህሮቶች ሲደግፉ ስለነበረ አሁን የቀረበው ሂሳቸው ከመጀመርያው አስተህሮታቸው ጋር መልሶ ሲቃረን እንመለከታለን፣ እነዚህን ሂሶችና ተቃርኖዎችን ብንመለከት፡-

- “ኢሳ(ኢየሱስ) ሰው እንጂ አምላክነት የለውም፣
- አንድ አምላክ እንጂ የስላሴ አስተምህሮ ስህተት ነው፣
- ፈጣሪ አይወልድም አይወለድም፣
- ኢሳ አልተገደለም፣
- የዓለም አምላክ እንጂ `የእስራኤል አምላክ` አባባል ስህተት ነው”

የሚሉትን ሲሆኑ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 2.3.2.3.1. "ኢሳ(ኢየሱስ) ሰው እንጂ አምላክነት የለውም"

ክርስትናው አልመሲህ ኢሳ(ኢየሱስ ክርስቶስ) የሰውና የአምላክ "ተዋህዶ" መሆኑን ይናገራል ነገር ግን ነብዩ ኢሳ ሰው ብቻ እንደሆነና አምላክነት እንደሌለበት አስተማሩ፣

> 3፡59 "አላህ ዘንድ የኢሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው፣ ከአፈር ፈጠረው፣ ከዚያም ለርሱ(ሰው) ሁን አለው ሆነም፡፡"

ይሁን እንጂ ይህን "ከአፈር ፈጠርነው" የሚለው ታሪክ የአዳም አፈጣጠር ታሪክ እንጂ ከመሬማ ስለተወለደው የኢሳ አፈጣጠር ታሪክ አይደለም፡፡

በመቀጠል ደግሞ፣ ኢሳ የሰው አምላክ ተዋህዶ መሆኑና በዚህም ኢሳ ሰው ብቻ ሳይሆን ከሰው ማንነቱ በተጨማሪ ኢሳ እራሱ

- የአላህ መንፈስ መሆኑ
- የአላህ ቃል መሆኑ፣
- እንደ ፈጣሪ መፍጠሩን፣
- ሲወለድም አራስ ልጅ ብቻ አለመሆኑ
- በመጨረሻው ቀን ፈራጅ መሆኑን

በሌሎቹ የነብዩ አስተምህሮዎች ውስጥ እንመለከታለን፣

- **<u>የአላህ መንፈስ መሆኑ</u>**

ቁርአን ኢሳ ከሰው ማንነቱ በተጨማሪ "የአላህ መንፈስ" እንዳለበት ይናገራል፣

> 4፡171 "የመርየም ልጅ አልመሲህ ኢሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የጣላት <u>"የኹን" ቃሉም ከእርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው</u>፡፡"

ይህ ቃል በግልፅ ቋንቋ ኢሳ እንደ ሌላው ሰው ተራ ሰው ሳይሆን መንፈስ የሆነው አላህ ማንነት በውስጡ ያለበት ሰው መሆኑን ያሳያል፣ "ብቻ" የሚለው ቃል ደግሞ የኢሳን ጊዜያዊውን ሰውኛ ማንነት እንኳን ቀለል አድርጎ የተመለከተ አገላለፅ ነው፡፡

ማንም ሰው ሆነ መልአክ “የፈጣሪ መንፈስ” አልተባለም፣ “ጂብሪል(የፈጣሪ መንፈስ)” የሚል ቃል በቁርአን አንዳንድ ቦታዎች ላይ በቅንፍ ተቀምጦ እንመለከታለን፣ መቼም በቅንፍ የሚቀመጠው አሰራር የሰዎች ቅጥያ እንጂ መቸም አላህ በቅንፍ ብሎ አይናገርም፣ ይሁን እንጂ ቁርአኑ ያለቅንፍ በቀጥታ “የአላህ መንፈስ” ያለው ኢሳን ብቻ ነው፣ ቁርአኑ ጅብሪልን ለምን በቀጥታ ያለቅንፍ “የአላህ መንፈስ” አላለውም? ኢሳስ “እንደኛ ስጋ ነው” ተብሎ በምኑ ነው “የፈጣሪ መንፈስ” የሚባለው የሚለውን ስንመለከት፣ የኢሳን ትክክለኛ ማንነት እናገኛል፡፡

በቅንፍ ያለቅንፍ የሚለው እንዳለ ሆኖ፣ የአላህ መንፈስ የተባሉትን ሁለቱ ጂብሪልና ኢሳ ብቻ መሆናቸውን ስንመለከት ኢሳ ከሰው በላይ ከጅብሪል እኩል የሚያደርገው ማንነት በውስጡ እንዳለ እንመለከታለን፣ ሌሎች ኢሳ ከጅብሪል በላይ የሚያደርጉ ተጨማሪ መገለጫዎቹን ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

- <u>የአላህ ቃል ነው</u>

ኢሳ ከሰውኛ ማንነቱና የአላህ መንፈስነቱ በተጨማሪ “እውነተኛ ቃል” ሲባል እንመለከታለን፣

> 19፡34 “ይህ የመሪየም ልጅ ኢሳ ነው፡፡ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት <u>እውነተኛ ቃል</u> ነው፡፡”

እዚህ ጋር ደግሞ ኢሳ “ቃል” የሚባል ማንነት እንዳለው እንመለከታለን፣ የትኛውም ሰው ይሁን መልአክ “ቃል ነው” አልተባለም መፅሀፍ ቅዱሱም ኢሳን “የፈጣሪ ቃል” ይለዋል(ዮሐ.1፡1)፡፡

የፈጣሪ ቃልና የሰው ቃል ይለያያል፣ በሰውኛ “ቃል” ማለት “ድምፅ” ማለት ነው፣ የፈጣሪ ቃል ግን ከዚህ የተለየ ትርጉም አለው፣ ፈጣሪ ፍጥረታትን የፈጠረው “በቃሉ” ነው(2፡117)፣ ስለዚህ የፈጣሪ ቃል እንደ ሰው ቃል ድምፅ ማለት ሳይሆን ከፈጣሪ የሚወጣ የፈጣሪ “የመፍጠር ማንነት” ማለት ነው፣ ኢሳ ደግሞ የፈጣሪ ቃል መሆኑ ኢሳ ከሰው ማንነቱ በተጨማሪ ሰሪ የሆነው የአምላክ ማንነት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ይህ እውነታም ሌላ ቦታ ላይ ቀርቧል፣

4፡171 “የመርየም ልጅ አልመሲህ ኢሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የጣላት “የኹን” ቃሉም ከእርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው፡፡”

ፈጣሪ ፍጥረታትን የሚፈጥረው “ኹን” ብሎ ነው፣ በዚህም ኢሳ “የኹን ቃል ነው” ሲባል ኢሳ የፈጣሪ የመፍጠር ማንነት ማለት ነው፡፡

ይህንን እውነታ ኢሳ በምድራዊ ህይወቱ ወቅት አረጋግጧል፣ 3፡49 እና 5፡110 ላይ እንደምንመለከተው ኢሳ በምድር በነበረበት ወቅት ከጭቃ የወፍ ቅርፅ እየሰራ በትንፋሹን ሲተነፍስበት ህይወትን ያለው ሆኖ ይበርር ነበረ፣ ልክ ፈጣሪ አዳምን ሲፈጥር ጭቃ በሰው ቅርፅ ሰርቶ እፍ ብሎ ህይወትን እንዳስገባበትና ሰውን እንደፈጠረው(ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡570)፡፡

ከፈጣሪ በቀር ማንም ሰውም ሆነ መልአክ ፍጥረት ሲፈጥር አላየነውም፣ ሁሉም ተፈጣሪ ናቸውና፣ ኢሳ ግን “ቃል” የሚባለው “የፈጣሪ የመፍጠር” ማንነት በመሆኑ ይህንን ማንነቱን በተግባር ሲያሳይ ነበረ፡፡

- **ሲወለድ አራስ ብቻ አለመሆኑ**

ቁርአን “የሰው ልጅ ሲወለድ ምንም እንደማያውቅ” ይናገራል፣

16፡78 “አላህ ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ፡፡”

ሰዎች በመሆናችን የዚህን ቃል ትክክለኛነት እናውቃለን ነገር ግን ኢሳ ከሰው ማንነት በተጨማሪ ከላይ የተመለከትናቸውን የፈጣሪን ማንነቶች ስላለው ሲወለድ እንደ ማንኛውም ሰው ያለ እውቀት አይደለም፣

19፡27-30 “በእርሱም የተሸከመቺው ሆና ወደ ዘመዶቿ መጣች፡፡ “መርየም ሆይ! ከባድ ነገር በርግጥ ሰራሽ” አሏት፡፡ “የሀሩን እህት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም፡፡ እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም” አሏት፡፡ ወደርሱም ጠቀሰች፡፡ “በአንቀልባ ያለን ህፃን እንዴት እናናግራለን!” አሉ፡፡ (ህፃኑም) አለ “እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡ መፅሀፍን ሰጥቶኛል ነብይም አድርጎኛል፡፡ በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል፡፡ በህይወትም እስካለሁ ሶላት በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል፡፡ ለናቴም ታዛዥ አድርጎኛል፡፡ ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም፡፡”

ከ19፡21 ጀምሮ ስንመለከት መሬማ ገና ወልዳ ነው ልጇን ይዛ የመጣችው ነገር ግን መሬማ ኢሳ ሲወለድ ከሰው የተለየና "ምንም የማታውቁ ስትሆኑ" እንደሚባሉት ሰዎች ሳይሆን አዋቂ እንደሆነ ተረድታለች፣ በዚህም ነው፣ ምንም እንኳን አነጋገሯ ሰዎቹን ቢያበሳጭም "አናግሩት" ያለችው፣ እዚህ ጋር ሰዎች የሚያስገርማቸው ኢሳ እንደተወለደ መናገሩ ነው ነገር ግን ከዚያ በላይ የሚያስገርመው የተናገረው ንግግር እንደ ህፃን ሳይሆን ሁሉን አዋቂ ከሆነ ከጥልቅ እውቀት የተነሳው ንግግር መሆኑና እኛ እንኳን በዚህ ዕድሜያችን የማናውቀውን ነገር መናገሩ ነው፣ ይህም እንዴት እንደተረገዘን፣ ነብይ እንሁን አንሁን፣ መፅሀፍ ይሰጠን አይሰጠን ... አናውቀውም፣ ስለዚህ ኢሳ ሲወለድ ሌላ ሁሉን አዋቂ ማንነት ያለው ይህም መለኮትነት ማንነት እንደነበረው እንመለከታለን፡፡

በዚሁ መለኮታዊ ማንነቱ ምክንያትም እንደ እስልምና "ኢሳ ከየትኛውም ሰው በተለየ ሲወለድ በሰይጣን አልተነካም"፣

> ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡506 "ማንኛውም ሰው ሲወለድ ሰውነቱን በሁለቱም በኩል ሰይጣን በሁለት ጣቱ ይነካዋል፣ <u>ከኢየሱስ በስተቀር ሁሉም ሰው</u> ሲወለድ እንደዚሁ ነው፣ ሰይጣን ኢየሱስን <u>እንደሌላው ሰው</u> ለመንካት ሞክሮ አልተሳካለትም፡፡"

በዚህ ኢሳ(ኢየሱስ) ሲወለድ ሰው ብቻ እንዳልነበረና ከሰው ማንነት በተጨማሪ መለኮታዊነትን መያዙን እንመለከታለን፡፡

- **<u>በመጨረሻው ቀን ፈራጅ መሆኑ</u>**

ፈጣሪ ፈራጅ ነው፣ የሚፈርደውም ሁሉን አዋቂ በሆነው እውቀቱ ነው፣ ይህ ሁሉን አዋቂነት ደግሞ ለወደፊት የሚሆነውን ማወቅ ጨምሮ ነው፣ በዚህም ፈጣሪ ዛሬ ላይ ሆኖ በእያንዳንዱ ሰው ላይ የሚፈረደውን ያውቃል፡፡

ፈጣሪ እያንዳንዱ ሰው በጊዜ ሂደት ውስጥ በህይወቱ ውስጥ ምን እንደሚሆን፣ ምን እንደሚወስን፣ ምን እንደሚያደርግ ... በዚህም ምን እንደሚፈረድበት ያውቃል፣ ልክ እኛ ከቦታ ቦታ ተጉዘን ነገሮችን ማየት እንደምንችለው እሱ ደግሞ በጊዜ ላይ ተጉዞ ሁሉንም ነገር መመልከት ይችላል፣ በተጨማሪ ደግሞ በእስልምናው "አንድ ሰው ገነት ይግባ ሲኦል ቀድሞ የተወሰነ" በመሆኑ(ሰሂህ ሙስሊም 33፡6393, ሰሂህ ቡኻሪ

4፡55፡549, 4፡54፡430, 8፡77፡593, 9፡93፡540, …)፣ ማን ገነት ይግባ? ማን ሲኦል ይግባ? በአላህ ዘንድ ቀድሞ የተወሰነ ነገር ነው፣ በዚህም ፈጣሪ ዛሬ ላይ ሆኖ ማን ላይ ምን እንደሚፈረድ ያውቃል፡፡

ነገር ግን፣18፡26 "… አላህ በፍርዱ አንድንም አያጋራም፡፡" ማለቱ ይህንን የፈጣሪ ዕውቀት ከፍርድ ቀን በፊት ማንም ሊያውቅ አይችልም፣ ኢሳ ግን የአምላክ ማንነት በውስጡ ስለያዘ ዛሬ ላይ ሆኖ ማን ገነት እንደሚገባ ይባሱኑም ከዚያ አልፎ በገነት ውስጥ ሰዎች ስለሚኖራቸው ደረጃ እንኳን ያውቃል፣

> ሰሂህ ሙስሊም 41፡7015 "… (ደጃል የተባለው ሰይጣን በሚገለጥበት ዘመን) የመሬማ ልጅ ኢሳም ይመጣና (ያለቀሱትን ሰዎች) እንባ ያብስና በገነት ውስጥ የሚኖራቸውን ደረጃ ይነግራቸዋል …"

ይህም ኢሳ ፈራጁ አምላክ ማንነት በውስጡ እንዳለ ያሳየናል፣ ይህንን እውነታ በመመልከት ነው ነብዩ መሀመድ "ህይወቴ በእጁ በሆነች በኢሳ" ያለው (ሰሂህ ሙስሊም 1፡0287)፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ኢሳ የትኛውም ሰውና መልአክ ያልሆነውን የአላህ መንፈስና እውነተኛ(የአላህ) ቃል መሆኑ፣ ሲወለድም አራስ ልጅ ብቻ አለመሆኑና በመጨረሻው ቀንም ፈራጅ መሆኑን ስንመለከት፣ ኢሳ እንደኛ አይነት ሰው ብቻ ሳይሆን ከሰውኛ ማንነቱ በተጨማሪ የፈጣሪ ማንነት የተዋሀደው መሆኑን እንመለከታለን፡፡

#### 2.3.2.3.2. <u>"አንድ አምላክ እንጂ ኢጋሪነት "የስላሴ ትምህርት" ስህተት ነው"</u>

ነብዩ መሀመድ ያወገዙት ሁለተኛው የክርስትና አስተምህሮ የ"ስላሴ" አስተምህሮ ነው፣

- 5፡73 "እነዚያ አላህ የሶስት ሶስተኛ ነው ያሉ በርግጥ ካዱ፡፡ ከአምላክም አንድ አምለክ እንጂ ሌላ የለም፡፡"
- 4፡171 " … (አማልክት) ሶስት ናቸው አትበሉ … አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡"

- 5፡116 “አላህም፡- የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ - እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን፣ በሚለው ጊዜ አስታውስ፡፡”

ነብዩ የስላሴ አስተምህሮ ያወገዘው ከተሳሳተ መረጃ ተነስቶ ነው፣ በ5፡116 ላይ የቀረበውን ስንመለከት ነብዩ “ስላሴ” ብሎ የወሰደው ፈጣሪ፣ ኢሳና መሪየምን ነው፣ ነገር ግን በክርስትናው ስላሴ የሚባለው “አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ” የሚባለው የፈጣሪ ማንነቶች ናቸው፣ በዚህም ነብዩ ስላሴን አስመልክቶ የሰጠው ወቀሳ ከመነሻው የተሳሳተ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በመቀጠል የክርስትናው የስላሴ አስተምህሮ የተለያየ ሶስትነት ሳይሆን ፀሀይ ላይ የተመለከተው ሶስትነት ነው፣ ፀሀይ የምንላት ሰማዩ ላይ የምትታይ ክብ አካል፣ ከእርሷ ወጥተው ስራ የሚሰሩት ብርሀንና ሙቀት የተመለከቱበት የአንድም ሶስትም አሰራር ስርአት ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ወልድን(ኢሳን) ብርሀን ሲለው መንፈስ ቅዱስን ደግሞ በዋናነት በእግዚአብሄር ሀይል ይገልፀዋል፣ የዚህ ተመሳሳይ ምሳሌም በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ እናገኛለን፣ በክርስትናው አስተምህሮ ሰው ስጋ፣ ነፍስና መንፈስ አለው፣ በዚህም በአንድ ሰውና ሶስት ማንነቶችን አሉት፡፡ እነዚህን ምሳሌዎች “ስላሴ” የሚለው ቃል ምን እንደሚመስል ለማሳየት የሚቀርቡ ምሳሌዎች እንጂ የፈጣሪ ማንነት በፀሀይና በሰው ማንነት አይወሰንም፣ እሱ በሁሉም ቦታ የሚገኝ፣ ልዕለ ስብዕና ስላለው አሰራሩና ማንነቱም ልዕለ ስብዕና ነው(ዝርዝሩ በ5.1.2.3 ክፍል ቀርቧል)፡፡

ነብዩ ይህንን ለሰው የማይገባ የፈጣሪ ማንነት በመጠቀም ለአላማቸው ይጠቀሙት እንጂ ይህንን የፈጣሪ የስላሴነት አስተምህሮ እራሳቸውም በሰላሙ ጊዜ በተወሰነ መጠን አስተምረውት ነበረ፣ በዚህም ቁርአኑ ውስጥ አላህ በብዙ ቦታዎች ላይ በብዙ ቁጥር ሲጠራ ነበረ፡-

- 3፡47 “አላህ የሚሻለውን ይፈጥራል “**<u>እንዳችን</u>**” ባሻ ጊዜ ሁን ይለዋል፣ ወዲያውም ይሆናል፣”

  “እንዳችን” የሚለው የሚያሳየው ሰሜቲካዊውን የአክብሮት አጠራር ሳይሆን “ከኛ ውስጥ” “አንዱ” ማለትን ነው፡፡

- 20፡41 “(አላህ ለሙሳ) ለነፍሴም (በመልእክቴ) መረጥኩህ፡፡”

መራጩ አላህ “ነፍሴ” የሚላት የራሱን ክፍል መሆኑን እንመለከታለን፣

- 19፡17 “መንፈሳችንንም ወደ እርስዋ (መርየም) ላክን፡፡ ለእርስዋም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰላት፡፡”

እዚህ ጋር “አንዳችን”፣ “ነፍሴ” “መንፈሳችንን” የሚሉ የአላህን ማንነቶች እንመለከታለን፣ አንዳንዶች የአላህ መንፈስ የሚለውን የክርስቲያኖቹ “ስላሴ” አስተምህሮት ጋር ሊሄድብን ስለሚችል በማለት “የአላህ መንፈስ” የሚለው ላይ በቅንፍ “ጅብሪል” የሚለውን ቃል በመጨመር “የአላህ መንፈስ ጅብሪል ነው” ይላሉ ነገር ግን መልአኩ ጅብሪልና የአላህ መንፈስ የተለያዩ መሆናቸውን ቁርአኑ ላይ ማስተዋል ይቻላል፣

- ጅብሪል የአላህ መልዕክተኛ መሆኑ

  - 19፡19 “(ጅብሪልም) እኔ ንፁህን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልእክተኛ ነኝ አላት፡፡”

  - 19፡64 “(ጂብሪል አለ) በጌታህ ትዕዛዝ እንጂ አንወርድም፡፡ በፊታችን ያለው በኋላችንም ያለው በዚህም መካከል ያለው ሁሉ የእርሱ ነው፡፡ ጌታህም ረሺ አይደለም፡፡”

- መልአክና የአላህ መንፈስ የተለያዩ መሆኑን

  - 70፡4 “ ... መላዕክቱና መንፈሱ ...”

  - 97፡3-4 “መወሰኛይቱ ለሊት ከሺ ወር በላጭ ናት፣ በርሷ ውስጥ መላዕክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ላይ ይወርዳሉ፡፡”

  - 38፡71-74 “ጌታህ ለመላእክት “እኔ ሰውን ከጭቃ ፈጣሪ ነኝ” ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ “ፍጥረቱን ባስተከከልኩና ከመንፈሴ በነፋሁበት ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ሆናችሁ ውደቁ” (አልኩ)፡፡ መላእክትም መላው ባንድነት ሰገዱ፡፡ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር ...”

በዚህም ጅብሪል የአላህ መልአክ መሆኑን፣ የአላህ መልአክና የአላህ መንፈስ ደግሞ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

አላህ ብቸኛ ፈጣሪ በመሆኑ ፍጥረታትን የሚፈጥረው ያለ ብጤ(2፡117)፣ ራሱን ችሎ (6፡101) ነው፣ በዚህም ፈጣሪ ለመፍጠር የጅብሪልን እገዛ አይፈልግም፣ አዳምን ሲፈጥረው ከመንፈሱ ነፍቶበት ነው(15፡28-29) እንደዚሁ መሬማም ስታረግዝም እንደዚሁ ነበረ(66፡12)፣ እዚህ ጋር "ከመንፈሴ በነፋሁበት" የሚለው ቃል ውስጥ አድራጊውና ድርጊቱን ስንመለከት፣ ከውስጥ መውጣትን እንጂ ከአላህ ውጪ ያለ ሌላ አካልን አይደለም፡፡

በዚህም የአላህ መንፈስና ጅብሪል የተለያዩ መሆናቸውንና የአላህ መንፈስ የሚባለው ከአላህ ውስጥ እየወጣ የሚሰራ የአላህ ማንነት መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም አላህና የአላህ መንፈስ የሚባሉ ሁለት የአላህን ማንነቶች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ከላይ እንዳየነው በተአምር የመጣው ኢሳ ውስጥ የአምላክ ማንነት ተመልክተናል፣ የሚገርመው ደግሞ ነፍስን እፍ ብሎ የማስገባት ስራ የሰሩት ልክ እንደ ፀሀይ አንድም ሶስትም የሆኑት አላህ፣ የአላህ መንፈስ(19፡21) እና ኢሳ(3፡49, 5፡110 ...) ብቻ መሆናቸውን ስንመለከት አምላክ ሶስት ማንነት እንዲሁም የስላሴን አስተምህሮ ትክክለኛነት እናረጋግጣለን፡፡

ለዚህም ነው አላህ አንዴ "እኔ"(32፡7, 15፡28, 39፡7 ... ) ሌላ ጊዜ ደግሞ "እኛ"(19፡20, 51፡47-48 ...) እያለ በተለያየ አነጋገር የሚናገረው፡፡

በርግጥ ይህ ከባድ ዕውቀት ነው ምክንያቱም ፈጣሪ ከሰው ልጅ አእምሮ በላይ በመሆኑ ነገር ግን ለመረዳት የሚከብድን እውነታ "ስህተት ነው" ብሎ ማለፉ ስህተት ነው፡፡

### 2.3.2.3.3. <u>"ፈጣሪ አይወልድም አይወለድም፣ ለሱ ብጤም የለውም"</u>

ይህንን አስመልክቶ ነብዩ ሲያስተምሩ፣

- 9፡30 "... ክርስቲያኖችም አልመሲህ ኢሳ የአላህ ልጅ ነው አሉ ... አላህ ያጥፋቸው ከእውነታ እንዴት ይመለሳሉ!"
- 6፡101 "... ለእርሱ(ለአላህ) ሚስት የሌለችው ሲኾን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል ነገርን ሁሉ ፈጠረ፡፡"

ይላል፣ እዚህ ጋር የተፈጠረው ስህተት “ልጅ” የሚለውን ቃል በስነተዋልዶ አይን ብቻ በመመልከት የመጣ ስህተት ነው ነገር ግን “ልጅ” የሚለው ቃል የግድ በስነተዋልዶ መወለድን ብቻ አያመለክትም ለምሳሌ ቁርአኑ ላይ፣

- 111፡1 ላይ አቡ ለሀብ(የእሳት ልጅ) - ሲል “የዚህ ሰው አባት እሳት ነው” ማለት አይደለም፣
- 42፡7 ላይ “መካ የከተሞች እናት” ሲል መካ “ከተሞችን የወለደች ሴት ከተማ” ማለት አይደለም፡፡

ይህ ምሳሌአዊ አነጋገር ነው፣ እንደዚሁ በተለምዶ የዘመኑ ልጅ፣ የአዲስ አበባ ልጅ፣ የስለት ልጅ … በማለት ሲገለፅ ዘመን ወይ አዲስ አበባ ወይ ስለት… የሚባል እናት ወይ አባት ኖሮ አለመሆኑ ግልፅ ነው፣ ሁሉም የተነገረበት አውድ አለው፣ እንደዚሁም የኢሳም የአላህ ልጅነት የተነገረበትን የራሱ አውድ አለው፡፡

እንደ እስልምና የሰው ልጅ ሁለት ማንነቶች አሉት ስጋና ነፍስ(74፡38)፣ በዚህ መሠረትም ኢየሱስ ውስጥ ካሉት ሁለቱ ማንነቶች ውስጥ አንዱ ከማርያም ይዞ የተወለደው ስጋዊ ማንነቱ ሲሆን ሌላው ደግሞ በ2.3.2.3.1 ክፍል የተመለከትነው አምላካዊ ማንነቱ ነው፣ በዚህም ኢሳ በስጋ የሰው ልጅነት አለው በመንፈስ ደግሞ አምላክነት አለው፣ ይህ የአላህ ማንነት ደግሞ ራሱን ዝቅ አድርጎ ስጋ ለብሶ መወለዱና ብዙ ስቃዮችን እስኪመለከት ድረስ መታዘዙ “የአላህ ልጅ” አስባለው፣ በዚህም “የአላህ ልጅ”ነቱ በአውዱ የሚፈታ እንጂ የስነተዋልዶ ልጅነት አይደለም፣ ልክ የእሳት፣ አዲስ አበባ … ልጅ እንደሚባለው ነው፡፡

እዚህ ጋር ለአብዛኛው ሙስሊም ጥያቄ የሚፈጥረው “አምላክ እንዴት እንደ ሰው ሆኖ ሊወለድ ይችላል” የሚለው ነው፣ ይህ አምላክ ሁሉን ነገር ማድረግና ሁሉን ነገር መሆን መቻሉን ካለማወቅ የመጣ ስህተት ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት እንኳን 19፡17 “መንፈሳችንንም ወደ እርስዋ (መርየም) ላክን፡፡ <u>ለእርስዋም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰላት</u>፡፡” የሚለውን መመልከት ይቻላል፣ የአላህ መንፈስ እንዴት ሰው ሊመሰል እና እንደ ሰው አይን አፍንጫው … ሊታይ ይችላል? አይባልም፣ እሱ ሁሉን መሆን ስለሚችል እንዳለ እንቀበለዋለን፣ በዚህም “ፈጣሪ እንደዚህ መሆን አይችልም” የሚለው አነጋገር ስህተት ነው፡፡

### 2.3.2.3.4. “<u>ኢሳ አልተገደለም</u>”

ይህንን አስመልክቶ፣

> 4፡157-158 “እኛ የአላህ መልዕክተኛ የመሪየምን ልጅ አልመሲህ ኢሳን ገደልን፣ በማለታቸው (ረገምናቸው)፣ አልገደሉትም አልሰቀሉትምም … ይልቁንስ አላህ ወደ እሱ አስነሳው፡፡”

እዚህ ጋር ኢሳ አልተገደለም ከሆነ ከፈጣሪ አሰራር አንፃር በእስልምናው ላይ አንድ ክፍተት ይፈጠራል፣ በቁርአኑ ላይ የተገለፀ አንድ ቋሚ የፈጣሪ አሰራር አለ፣ ይህም ሀጢያት የሚሰረየው በመስዋዕት ነው፣ ይህም አላህ በማይሻረው ህጉ የደነገገው ድንጋጌ ነው፣

> 22፡34 “<u>ለአህዛብ ሁሉ</u> (ወደ አላህ) መስዋዕት ማቅረብን <u>ደነገግን</u>፡፡”

የአብርሀም ልጅ ኢስሀቅም የዳነው በዚህ አሰራር መሆኑን ቁርአን ይናገራል፣

> 37፡107 “(የኢብራሂምን ልጅ) በታላቅ ዕርድም (መስዋዕት) ተቤዠነው፡፡”

ይህ የሆነው “ሀጢያት ያለ መስዋዕት ስለማይነፃ ነው” ለእስልምናና ለክርስትና አባት በሆነው በአይሁድ ሀይማኖት ሀጢያት የሚነፃው ስለ ሀጢያት የእንስሳትን መስዋዕት በማቅረብ ነው፣ በዚሁ መርህም በክርስትናው ሀጢያት የሚነፃው በኢየሱስ መስዋዕትነት ነው ነገር ግን እስልምናው ከላይ ከተመለከትነው የቁርአን ቃል አንፃር ወይ እንደ አይሁዱ የእንስሳት መስዋዕት አያቀርብም ወይ እንደ ክርስቲያኑ በኢየሱስ መስዋዕትነት አልተጠቀመም በዚህም የእስልምናው አስተምህሮ በመሀል ሜዳ ላይ ሲቀር እንመለከታለን፣ ኢብራሂምን መስዋዕት አስመልክቶ የአረፋ በአል ይህንን ያህል ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት በታላቅ ስነስርአት እየተከበረ ነገር ግን በዚህ በኢብራሂም መንገድ መሄድ አለመቻል ሊታሰብበት ይገባል፡፡

በክርስትናው ይህ የማንፃት ስራ የሰራው ኢየሱስ ከማርያም ይዞ በተወለደበት የስጋ ማንነቱ ነው ስለዚህ የኢየሱስ መሞት ቁርአናዊ መነሻም ትርጉምም ያለው ሲሆን “አልሞተም” የሚለው አስተምህሮ ደግሞ ክፍተትን የሚፈጥር አስተምህሮ ነው፡፡

ሌላው ከኢሳ መሞት ጋር በተያያዘ ኢሳ አምላክ ከሆነ አምላክ እንዴት ይገደላል? የሚለውን ጥያቄ ሲነሳ ይታያል፣ ይህ አንድ መሠረታዊ እውነታን ያላስተዋለ አባባል ነው፣ አንድ ሰው ተደብድቦ ሲገደል የሚደበደበውም ሆነ የሚሞተው ስጋዊ ማንነቱ እንጂ ነፍሳዊ/መንፈሳዊ ማንነቱ አይደለም፣ ስጋውያን የሚጎዱት ስጋዊ ማንነትን ነው፣ ኢሳም ለስጋውያን ሰዎች ሀጢያት ስርየት መስዋዕትነትን የከፈለው በስጋዊ ማንነቱ ነው፡፡

### 2.3.2.3.5. <u>“የአለም አምላክ እንጂ “የእስራኤል አምላክ” አስተምህሮ ስህተት ነው”</u>

ብዙውን ጊዜ ይህ ሃሳብ የሚነሳው መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ማቴ.15፡24 “ኢየሱስም … ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም፡፡” ያለው አባባልና በመፅሀፍ ቅዱሱ ብዙ ቦታዎች ላይ ያለው “የእስራኤል አምላክ” ከሚለው የእግዚአብሄር መጠሪያ መነሻነት ነው፡፡

በርግጥ ቁርአኑም ለእስራኤል ከሌለኛው አለም ነጥሎ ትልቅ ቦታ ይሰጣታል፣

> 45፡16 “ለእስራኤል ልጆች መፅሃፍንና ህግን፤ ነቢይነትንም በርግጥ ሰጠናቸው፡፡ ከመልካም ሲሳዮችም በርግጥ ለገስናቸው፡፡ <u>በአለማት ላይም አበለጥናቸው</u>፡፡”

በዚህም እስራኤል ለፈጣሪ የተለየች ሀገር መሆንዋን የማይታበይ ሀቅ ነው፡፡

ነገር ግን “የእስራኤል አምላክ” የሚለውን አጥርተን ለማለፍ፣ መፅሀፉ ላይ በመጀመርያ “እስራኤል” የተባለው ያዕቁብ(ያዕቆብ) ሲሆን ከዚያም ይህንን ስም አስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ዘሮች፣ ከዚያ ቀጥሎ እነኚህ ዘሮች የሚኖሩበት ሀገር መጠርያ ሆነ ነገር ግን “እስራኤል” የሚለው ቃል በመጀመርያ የቀረበው “አማኝ” በሚል ትርጉሙ ነው፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ይህ የእስራኤል “አማኝ” ትርጉምና የእስራኤል “ሀገር” ትርጉም የተለያየ መሆኑን ያስረዳል (ሮሜ.9፡6-8, ገላ.4፡22-31 …)፣ እነዚህ ቃላትም በአዲሱ ኪዳን “እስራኤላዊነት” በስጋ ከእስራኤል ዘር በመወለድ ሳይሆን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይነት መሆኑን ያሳያል፣ ይህም በተግባር

የተረጋገጠ እውነታ ነው፣ በስጋ ያሉት እስራኤሎች ኢየሱስ የገደሉበትና ላለፉት 2,000 አመታት በኢየሱስ በኩል የመጣውን ክርስትና አለማግኘታቸውን ስንመለከት ኢየሱስ “እስራኤል” ብሎ ሲጠራው የነበረው ተከታዮቹን እንጂ በስጋ ከእስራኤል የተወለዱት አለመሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህም ኢሳ “ለእስራኤል እነጂ አልተላከሁም፣ ከእስራኤል ቤት ለጠፉ በጎች፣ የእስራኤል አምላክ ...” ብሎ ያስተማራቸው እውነታዎች በሙሉ የተናገራቸው ቁርአኑ “ተከታዮቹ”(57፡27) ለሚላቸው ለክርስቶስ ተከታዮች እንጂ ለእስራኤል ሀገር አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት እነዚህ ከላይ “የክርስትና ስህተቶች” ተብለው የቀረቡት አምስቱ ነጥቦች እንደ ነብዩ ቀደምት አስተምህሮ ስህተት አለመሆናቸውን፣ በዚህም ነብዩ “በነብያቱ መንገድ ነኝ” ብለው “ነብይ እኔ ብቻ ነኝ” ማለታቸው፣ “ቀደምት መፅሀፍትን እንቀበላለን” ብለው “ቁርአን ብቻ” ማለታቸው፣ “አንድ ነን” ሲሉ ከርመው “ትክክለኛው እስልምና ብቻ ነው” በማለት የቀየሩትን እውነታ ስንመለከት ነብዩ ሀይማኖቱን የፈጠሩት ከፈጣሪ በተቀበሉት መልዕክት አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 2.3.2.4. <u>ከአይሁድ/ክርስትናው የተቃረነ ሀይማኖት ማስፋፍያ እስትራቴጂን መከተል</u>

ነብዩ በእስራኤሎቹ ነብያት መንገድ ለህዝቡ ተአምራትን እያሳየ ህዝቡን የሚመራበት መንገድ ባለመኖሩ ነብዩ ለሀይማኖት ማስፋፍያነት የተጠቀመው በሸብርና በጂሀድ በጉልበት የማስለም ስራዎች ናቸው፣

- <u>**ሽብር**</u>

ነብዩ እስልምናን ለማስፋፋት በአሸባሪነት ስራ ተሰማርተው ነበረ፣ ስለራሳቸውም አሸባሪነት ሲናገሩ ሰሂህ ቡኻሪ 4፡52፡220 “... እኔ በሽብር አሸናፊ ተደርጌያለሁ፡፡” ይላሉ፣ ተመሳሳይ ቃልም ሰሂህ ሙስሊም 4፡1066, ሰሂህ ሙስሊም 4፡1067 ... ላይም ቀርቧል፣ ነብዩ ከራሳቸው የሽብር ስራ ባለፈ ተከታዮቻቸውም ለሀይማኖት ማስፋፍያነት የሽብርን መንገድ እዲከተሉ አስተምረዋል(8፡60)፡፡

ነብዩ በዘመናቸው ጭካኔ የተሞላበትን የሽብር እርምጃዎችን በመውሰድና በማስወሰድ አካባቢውን ሲያስሸብሩ ነበረ፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- ሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡590 "... ሰዎቹም ተይዘው ሲቀርቡ ነብዩ የሰዎቹን እጆችና እግሮች ቆራረጠ፣ አይናቸውንም በጋለ ብረት ተኮሳቸው፡፡"
- ለጦርነት በተሰማሩበትም በውጊያ ወንዶቹን ካሸነፉ በኋላ እናቶችንና ህፃናትን ሲገድሉ እንደ ነበረ ሰሂህ ሙስሊም 19፡4321 - 4323 ላይ እንመለከታለን፣
- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡52፡264፣ የአላህ ነቢይ አቡ ራፊን እንዲገድሉ የአንሳሪ ሰዎችን ላከ፣ ከገዳዮቹም አንዱ ሲናገር ... (ጨልሞ ነበረ) በጎረኖ ውስጥ አገኘሁት ... ከዚያ ጎራዴዬን መዝገዬ በሆዱ ውስጥ ሰገሰኩኝ፣ አጥንቱን እስኪነካ ... ከዚያ ጥዋት ሞቱን ጥሩንባ ለፋፊው እስኪያበስረኝ ጠብቄ ከዚያ መጥቼ ለነቢዩ አበሰርኩት፡፡"

ተመሳሳይ የግድያ ትዕዛዝ ነብዩ በከአብ ቢን አል አሽራፍ ላይ ሲሰጥና ተከታዮቹም ሄደው ሲፈፅሙ ሰሂህ ቡኻሪ 5፡59፡369 ላይ እንመለከታለን፡፡

የነብዩ አሸባሪነት በወቅቱ በአካባቢው የናኘ ሲሆን የሚገርመው እሱ ሳይደርስባቸው ቀድሞ "ጎመን በጤና" በማለት ለሱ ግብር ሲገብሩ የነበሩ ነገስታት እንኳን ነበሩ፣ በዚህም የባህሬኑ መንግስት(ሰሂህ ቡኻሪ 5፡59፡351) እና በወቅቱ አጠራር አይላ(Aila) የምትባል ሀገር(ሰሂህ ቡኻሪ 2፡24፡559) ነገስታትን መመልከት ይቻላል፡፡

## ➢ <u>ጂሀድ</u>

ጂሀድ(ቅዱስ ጦርነት) ማለት ሰዎች እስልምናን በሀይል እንዲቀበሉ የሚደረግበት አሰራር ሲሆን የመጨረሻ ግቡም የአለምን ህዝብ ማስለም ነው(8፡39, 48፡16, 13፡15 ...)፡፡

ነብዩ ለሀይማኖት ማስፋፍያ የጂሀድ ጦርነት ወሳኝ እንደሆነ በመረዳቱ ተከታዮቹን ለጂሀድ ውጊያ ሲያደፋፍር ነበረ(2፡65, 8፡65, 4፡84, 22፡78...)፣ ሰፊ ትምህርቶችንም ሲሰጥ ነበረ፣ በዚህም፣ በጂሀድ መሳተፍ በአላህ ዘንድ መወደድ መሆኑን(61፡4)፣ አንድ ሰው በጂሀድ ቢሞት ገነት የሚገባ መሆኑን (ሰሂህ ቡኻሪ 4፡52፡48, 4፡74, 29፡6...)፣ በህይወት ከተረፈም በጦርነቱ

ከዘረፋ የሚገኘውን ሀብትና ምርኮኛ የራሱን ድርሻ የሚከፋፈል መሆኑን(ሰሂህ ቡኻሪ 4፡53፡366, 4፡53፡352, 4፡53፡358, 4፡53፡359 …)፣ በጂሀድ ባይሳተፍ ደግሞ ገሀነም የሚገባ መሆኑን(8፡16)፣ በጂሀድ መለገም ሀጢያት መሆኑን(9፡38-39)፣ ከጂሀድ መመለስ ሀጢያት መሆኑን(9፡84)፣ ከጂሀድ መሸሽ ሀጢያት መሆኑን(33፡16, 8፡15-16)፣ ፈጣሪም ያን ሰው በምድር እንደሚቀጣው(9፡39, 48፡17) አስተማረ፡፡ በዚህም አንድ ሙስሊም በጂሀድ ተዋጊነት መሳተፉ ጥቅም እንጂ ጉዳት የማያመጣበትና አለመሳተፉ ግን በሰማይም በምድርም ተጎጂ እንደሚያደርገው አስተማረ፡፡

በዚህም ነብዩ የትኛውም ጂሀዲስት ከየትኛው ወታደር በላይ በወኔና በድፍረት እንዲዋጋ አደረገ፣ እስልምናንም ለመስፋፋት ይህንን እስትራቴጂ አጠንክሮ ገፋበት፣ በዚህም ነብዩ አብዛኛውን እድሜውን በዚህ የጂሀድ ጦረኝነት አሳለፈ፣ በዚህም እራሱ ብዙ ጦርነቶችን መራ የመካ ወረራ(ሰሂህ ቡኻሪ 5፡58፡122፣ ሰሂህ ሙስሊም 8፡3253 …)፣ የአል ካነዳቅ ጦርነት(the battle of the trench)(ሰሂህ ቡኻሪ 1፡8፡452)፣ የባድር ጦርነት (ሰሂህ ቡኻሪ 5፡59፡358)፣ የአል-ሃራ ጦርነት(ሰሂህ ቡኻሪ 5፡59፡358) … በጦርነቶቹም እራሱም ከባድ ጉዳት እንኳን እስኪደርስበት ሲዋጋ ነበረ፣ ሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡618 “በኡሁዱ ጦርነት … ሄልሜቱ በነቢዩ እራስ ላይ ተሰበረ፣ የነቢዩ ፊትም በደም ተሸፈነ፣ ጥርሱም ተሰበረ፡፡”

በዚህ የጂሀድ ስልትም ሀይማኖቱ ባልተጠበቀ ፍጥነት በአጭር ጊዜ ከአረብ ተነስቶ ሰሜን አፍሪካንና አብዛኛውን ኢሲያን አዳርሶ ወደ አውሮፓ ገሰገሰ፣ በዚህ ግስጋሴው የተደናገጠችው የሮማዋ ካቶሊክ የመስቀል ጦርነት እስከታውጅበት ድረስ በፊቱ መቆም የቻለ ሀይል አልነበረም፡፡ እንደዚሁ አፍሪካ ላይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ያደረገችው ተጋድሎ የእስልምናን አፍሪካን የማስለም ግስጋሴ አስቆመች፣ በዚህም ከኢትዮጵያ ምስራቅና ምዕራብ ላይ እስልምና በተወሰነ መጠን ቢገባም ከኢትዮጵያ አልፎ በደቡብ አቅጣጫ ወደ ሌላው አፍሪካ መስፋፋት አልቻለም፣ ከዚህ የኦርቶዶክስ መራሹ መንግስት መዳከም በኋላ እስልምና በተለይ በምስራቁ ኢትዮጵያ በሀይል የመስፋፋት ሁኔታ የታየበት ሲሆን በዚህም ብዙዎችን በጉልበት አስልሟል፣ ይህንን የእስልምና የሀይል መስፋፋት ታሪክ፣ በግልፅ በመናገራቸው የሚታወቁት ሀረሮች በወቅቱ ለነበረው ሁኔታ አንድ መታሰብያ ስነ ግጥም ቋጥረውለት ነበረ፣

[16]“Salaata Orfoo
Sodaa qottoo
Allaahuu Akibar``

ሲተረጎምም፣

“የኦርፎ ስግደት
መጥረብያ ፍራቻ
አላሁ አክበር”

“ኦርፎ” የሚባለው በወቅቱ የአካባቢውን ህብረተሰብ በግድ እንዲያሰልም በስፍራው የተሾመ ሰው ነበረ፣ ይህ ሰው የስግደት ሰአትን ጠብቀው የማይሰግዱትን ሰዎች አንገታቸውን በመጥረብያ ሲቆርጥ ስለነበረ ህዝቡ “ጎመን በጤና” በማለት በየስግደት ሰአቱ መዝጊድ እየተገኘ ይሰግድ ነበረ፣ ህዝቡም ምንም እንኳን ባላመነበት ነገር በግድ እየሰገደ የነበረ ቢሆንም ለሁኔታው ግን ይህንን መታሰብያ ግጥም ትተውለታል፡፡

ዛሬ ላይ እያንዳንዱ ሙስሊም እስልምና እንዴት ወደ ዘሩ እንደገባ ማወቅ ቢችል ብዙ ተመሳሳይ ታሪኮች እንደሚያገኙ እሙን ነው ይሁን እንጂ ዛሬ ላይ የትኛውም ሙስሊም ነብዩ ስለ ሲኦል ያስተማሩዋቸውን አስፈራሪ ትምህርቶችን ሰምቶ እውነተኛውንና የተሳሳተውን መንገድ የመመርመር ወኔ የለውም፡፡

ከላይ ከቀረቡት ቁርአናዊ ቃሎችና ሀገራዊ ገጠመኞች ጂሀድ ለእስልምና መስፋፋት የጀርባ አጥንት እንደነበረ የሚያሳዩ እውነታዎች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ነብዩ መሀመድ “በአይሁድ/ክርስትና መንገድ ላይ ነኝ” በማለት ተነስተው በወቅቱ በነበረው ማህበረሰብ በነብይነት ተቀባይነት ባያገኙም የራሳቸውን ነብይነት የአቅጣጫ ለውጥ በማድረግበጉልበት በማሸበርና በጂሃድ ተቀባይነት እንዲያገኙና እስልምና እንዲስፋፋ አድርገዋል፡፡

---

[16] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 32

### 2.3.3. <u>ነቢዩ መሀመድ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ከሀይማኖት መሪ ስብዕና አንፃር</u>

ኢየሱስና መሀመድ በአለማችን ወደር የሌላቸው መሪዎች ናቸው ሌላውን ትውልድ ትተን በዛሬው ትውልድ እንኳን ብንመዝናቸው እያንዳንዳቸው ከየትኛውም ታዋቂ መሪ በላይ ከ1.5 ቢሊየን በላይ ተከታይ አሏቸው፡፡

እነዚህ ሁለቱ መሪዎች የሁለቱ አለማቀፍ ሀይማኖቶች፣ የእስልምናና ክርስትና መስራችና መሪዎች ሲሆኑ ሁለቱም መሪዎች እነሱን መከተልና አለመከተል የሲኦልና የገነት ልዩነት አድርገው ይገልፃሉ፣ ስለዚህ የትኛውም ሰው የየትኛውን መሪ መንገድ መከተል እንዳለበት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት፡፡

በዚህም ሁለቱንም መሪዎች፡-

- የፈጣሪን ባህሪ ከመምሰል አንፃር፣
- ፈጣሪ ሰዎች እንዲኖሩ ከሚፈልገው አኗኗር አንፃር፣
- ካላቸው ዕውቀት አንፃር፣
- ገነት ለመግባት እርግጠኛ ከመሆናቸው አንፃር፣

እያነፃፀርን የትኛው መሪ ትክክለኛ መሪ እንደሆነና ሰዉ ማንን መከተል እንዳለበት እንመለከታለን፡፡

#### 2.3.3.1. <u>የፈጣሪ ባህሪን ከመምሰል አንፃር</u>

ሁለቱን መሪዎች ከፈጣሪ መንገድ አንፃር ለማነፃፀር ሁለቱንም በተመሳሳይ መንገድ ከገለፁት ከፈጣሪ ባህሪ አንፃር እንመለከታቸዋለን፣ ሁለቱም መሪዎች ፈጣሪን ከሞላ ጎደል በአንድ መልክ ገልፀውታል፣ አብዛኞቹ የቁርአን ምዕራፎች የሚጀምሩት “በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው” በሚል ቃል ነው፣ ኢየሱስም ፈጣሪን በዚሁ መልክ ይገልፀዋል፡፡

በዚህም ይህን በሁለቱም ሀይማኖቶች ወጥ የሆነው የፈጣሪ ማንነት ይዘን ኢየሱስና መሀመድ ጋር በመሄድ የትኛው በፈጣሪ መንፈስ ውስጥ ሲሰራ እንደ ነበረ፣ የትኛው ደግሞ በተቃራኒ መንፈስ ሲሰራ እንደነበረ እንመለከታለን፣

- **<u>የኢየሱስ መንገድ</u>**

እንደ መፅሀፍ ቅዱስ ኢየሱስ ሰዎችን በፍቅር ጠራ፣ ተከታዮችን ያፈራው ገድሎ ሳይሆን ሞቶላቸው ነው፣ ጠላቶች በተነሱበት ሰአት አልተዋጋቸውም ምክንያቱም "ሩህሩህ፣ አዛኝ ..." መንፈስ ውስጥ የሚኖር በመሆኑ፣ ይህ እውነታም ቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበረ፣

> ማቴ.12፡18-20 "እነሆ የመረጥሁት ብላቴናዬ፣ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ወዳጄ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ ... አይከራከርም አይጮህም፣ ድምፁ በአደባባይ የሚሰማ የለም ... የተቀጠቀጠን ሸንበቆ አይሰብርም የሚጤስን የጥዋፍ ክር አያጠፋም፡፡"

ተከታዮቹ ክርስቲያኖችንም በዚህ የፍቅር መንገድ እንዲጓዙ አስተማረ "ሰዎችን ይቅር ባትሉ ፈጣሪ ይቅር አይላችሁም አለ"፣ ጥላቻን፣ ስድብን፣ በቀልን ከለከለ፣ ይባሱኑ "ባልንጀራውን እንደራሱ የማይወድ ሊከተለኝ አይገባም" አለ(ማቴ.19፡19)፣ ይህ ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም መደረግ እንዳለበት አስተማረ፣ በዚህም ክርስቲያኖች አጋፔ(ጠላትን መውደድ) እስከሚባለው ከባድ የፍቅር ደረጃ እንዲጓዙ አዘዘ፣ በዚህም ለአእምሮ የሚከብዱ የፍቅር ትዕዛዞችን ሰጠ፡-

- ማቴ.5፡44-45 "ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሙአችሁን መርቁ ..."
- ማቴ.5፡39-41 "... ክፉውን አትቃወሙ፣ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፣ እንዲከስህም እጀ ጠባብህን እንዲወስድ ለሚወድ መጎናፀፊያህን ደግሞ ተውለት፣ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ፣ ለሚለምንህ ስጥ፣ ከአንተም ይበደር ዘንድ ለሚወደው ፊቀቅ አትበል፡፡"

አንድ የክርስቶስ ተከታይ ሰዎች ክፉ ቢሰሩበት እንኳን የመጨረሻ እርምጃ "ሲያሳድዳችሁ ፀልዩ" ብቻ ሆነ ይህም በአማኙ ላይ ለሚደርስ ለማንኛውም ነገር መልስ የሚሰጠው ፈጣሪ መሆኑና በዚህም አማኙ በፈጣሪ ሀይል ላይ ብቻ ራሱን እንዲጥልና ከሰው ጋር ሰላም እንዲያወርድ አዘዘ፡፡

በዚህም "ሩህሩህ፣ አዛኝ ..." የተባለውን እውነታ በኢየሱስ ህይወትና አስተምህሮ ውስጥ እንመለከታለን፡፡

- ***<u>የመሃመድ መንገድ</u>***

መሀመድ ከላይ እንደተመለከትነው "ሩህሩህ፣ አዛኝ ..." መንገድ ትቶ የሽብርና የጂሀድን መንገድ መረጠ፣ በዚህም ብዙ ሰዎች ተሸበሩ ተገደሉም፣ ይህንን መርህም የእስልምና መርህ አድርጎ ተከታዮቹ በዚህ መንገድ እንዲሄዱ አስተማረ፡፡

በዚህም በኢየሱስና በመሀመድ መሪነት መካከል ግልፅ የተቃርኖ አካሄድ እንመለከታለን፣ **<u>ለፅድቅ የሚሞትና ለፅድቅ የሚገድል፣ ለፅድቅ የሚያጭበረብርና ለፅድቅ ለአጭበርባሪዎች ጨምሮ የሚሰጥ ...</u>** የሚገርመው ደግሞ ሁለቱም መንገዶች ተመጋጋቢ መሆናቸው ነው፣ በዚህም በፈጣሪ መንገድ ላይ ያለው የትኛው ነው? የሚለውን መለየት አያዳግተንም፡፡

**2.3.3.2.** ***<u>ፈጣሪ ሰዎች እንዲኖሩት ከሚፈልገው ምድራዊ አኗኗር አንፃር</u>***

የቅዱሳን አኗኗር ምን መምሰል እንዳለበት በሁለቱም የእስልምናና የክርስትና ቅዱሳት መፅሀፍት ላይ በተመሳሳይ ቃል ተገልጿል፣ የእስልምናውን ብንወስድ፡-

- ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡456 "... አብዛኞቹ የገነት ነዋሪዎች እዚህ ደሀ የነበሩት ናቸው፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡555 "የገነት መግቢያ ላይ ሆኜ ስመለከት ሀብታሞች እንዳይገቡ ሲከለከሉ አብዛኞቹ ድሆች እንዲገቡ ሲፈቀድላቸው አየሁ፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡435 "እነሱ በዚህኛው አለም ይደሰታሉ፣ እኛ ደግሞ በሚቀጥለው፡፡"

ከዚህ ሀሳብ አንፃር የሁለቱን መሪዎች ኑሮ ስንመለከት፣

- ***<u>የኢየሱስ መንገድ</u>***

ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረባቸው ዘመኖቹ ምድራዊ ሀብት የማከማቸትና ምድራዊ ደስታን የመከተል ሃሳብ አልነበረውም፣ በዘመኑም "ይህ ነው" የሚባል ምድራዊ ንብረት አልነበረውም፣ በወቅቱ የሀብት መነሻ የሆነውን የራሴ የሚለው ቤት እንኳን አልነበረው(ማቴ፡8፡19-20)፣ ይባሱኑም

ሀብታሞቹን "ሰማያዊ መዝገብ እንድታገኙ ምድራዊው ሀብታችሁን ሽጣችሁ ለደሀ ስጡ" ሲል ነበረ(ሉቃ.12፡33)፡፡

ኢየሱስ የሚታወቀውም ምንም ምድራዊ ሀብት የሌለው ነገር ግን በመምህርነቱ፣ በሚሰራው ተአምራት፣ በፈዋሽነቱ … በአጠቃላይ በመንፈሳዊ አገልግሎቱ ብቻ ነው፡፡

- <u>***የመሀመድ መንገድ***</u>

ነብዩ መሀመድ ከላይ ካየነው ቁርአናዊ አስተምህሮ በተቃራኒ ለምድራዊ ሀብትና ደስታ ትልቅ አትኩሮት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስ ነበረ፣ በዚህም ነብዩ ብዙ ሀብትን የማጋበስና ብዙ ሚስቶችን የማግባት ጉዳይ ትልቁ ፈተና ሆኖበት ነበረ፣ ለዚህም ሲል የግል ጥቅሙን ዘላለማዊ በሆነው የፈጣሪ ቃል ውስጥ እንኳን እስከማስገባት ደርሶ ነበረ፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፣

- 58፡12 "እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ መልክተኛውን በተወያያችሁ ጊዜ ከመወያየታችሁ በፊት ምፅዋትን አስቀድሙ፡፡"
- 8፡1 "… የዘረፋ ገንዘቦች የአላህና የመልክተኛው ናቸው፣ ስለዚህ አላህን ፍሩ፡፡"
- 8፡41 "ከማንኛውም ነገር በጦር (ከከሃዲዎች) የዘረፋችሁትም አንድ አምስተኛ ለአላህና ለመልክተኛው …"

በዚህም የመሀመድን የሀብት ብዛት መገመት ይቻላል፣ የሚገርመው በመጀመሪያ ለሱ እንዲሰጠው በቁርአኑ በኩል ያዘዘው ሙሉውን የዘረፋ ገንዘብ ነበረ ነገር ግን በዚህ መንገድ የሚፈጠረው ሀብት እየበዛ በመሄዱና የተዋጊዎቹንም ሞራል ለመጠበቅ ሲል በመጀመርያ ያዘዘውን በመተው የቁርአኑን ቃል "አንድ አምስተኛ" በሚለው አስተካከለው፡፡

በተመሳሳይ መንገድም ቁርአኑ 6፡51 "… ከአላህ <u>**ሌላ**</u> አማላጅ የለም …" እያለ፣ ለገንዘብ በመሳሳት 9፡103 "ከገንዘቦቻቸው ስትሆን በርስዋ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የሆነችን ምፅዋት ያዝ <u>ለነሱም ፀልይላቸው፤</u> ፀሎትህ ለነሱ እርካት ነውና አላህም ሰሚ አዋቂ ነው፡፡" በማለት ቁርአኑን ለራሱ ጥቅም አስተካከለው፡፡

በሚስቶች በኩልም እንደዚሁ ብዙ ሚስቶች ሲያሰባስብ ነበረ፣ በመጀመሪያ እስከ አራት(4፡3) ቢልም ከጊዜ በኋላ በዚህ የቁርአን ህግ መገዛት አቅቶት እስከ አስራ አንድ ሚስቶች ያገባ ሲሆን(ሰሂህ ቡኻሪ 1፡5፡268)፣ ከነዚህ በተጨማሪ ቁጥራቸው የማይታወቅ ውሽማዎች(33፡50-51) እና ባሮች(33፡52) ጋር ሲተኛ ነበረ፡፡

በዚህም መሀመድ በብዙ ምድራዊ ደስታና ምድራዊ ሀብታምነት ሲኖር እንደነበረ፣ ኢየሱስ ደግሞ በተቃራኒው እንደኖረ እንመለከታለን፣ በዚህም የእነዚህን የሁለቱ ሀይማኖት መሪዎች ኑሮ ከላይ ካየነው ቃል ጋር ስናስተያይ፣ የኢየሱስ ህይወት በፈጣሪ መንገድ የተመራ ሲሆን፣ መሀመድ ግን በሀብታምነትና በደስታ ያሳለፈ በቅርቢቱ ህይወት “ቀረኝ” የሚለው ነገር የሌለውና የአላህ ቃል ተቃራኒ ሆኖ ያለፈ ሰው መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 2.3.3.3. <u>ከዕውቀት አንፃር</u>

አንድ መሪ ያውም የዘላለማዊው ህይወት መንገድ መሪ፣ ተመሪውን ወዴት ይዞ እንደሚሄድ ሙሉ እውቀት ሊኖረው ይገባል፣ በዚህም መስፈርት እነዚህን ሁለቱን መሪዎች ስናነፃፅር፡፡

ቁርአን “አላህ ኢሳን(ኢየሱስን) ጥበብን፣ መፅሀፍን፣ ስነፅሁፍን … አስተማረው” ይላል(3፡48, 5፡110)፣ በዚህም ኢየሱስ በቀጥታ የአላህ ተማሪ በመሆኑ ዕውቀቱ እስከ ጥግ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ነገር ግን መሀመድ ይህ እድል አላገኘም፣ በራሱም አልተማረም(62፡2, 7፡157-158 …)፣ እስራኤላዊም ባለመሆኑ ከቀደሙት ቅዱሳን መፅሀፍት አልተማረም፣ በዚህ ላይ ደግሞ ቁርአኑ 40፡78 “ካንተ በፊት መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡ ከእነሱም ባንተ ላይ የተረከንልህ አልለ፡፡ ከእነርሱም ባንተ ላይ **ያልተረከነው አልለ**፡፡” ማለቱ መሀመድ የዕውቀት ዕጥረት እንደሚኖርበት ግልፅ ነው፡፡

ይህንን የነብዩን የዕውቀት ችግር በምሳሌ ብንመለከት፡-

- <u>በአለም ላይ ስላሉት ሀይማኖቶች በቂ እውቀት አልነበረውም</u>

ነብዩ ከክርስትናና አይሁድ እምነት ዉጪ ያሉትን ሃይማኖቶች ፈፅሞ አያውቃቸውም፣ ስለሀይማኖቶች ትምህርት ካስተማረ የሚያስተምረው ስለ

እስልምና፣ አይሁድና ክርስትና ሀይማኖቶች ብቻ ነው፣ ከነዚህ ሀይማኖቶች ውጪ ሌላ ሀይማኖት እንዳለ አያውቅም ነበረ፣

> ሰሂህ ቡኻሪ 8፡77፡597፣ "... ማንኛውም ህፃን ሲወለድ እስላም ሆኖ ነው፣ ነገር ግን ወላጆቹ ወደ ይሁዲነት ወይ ወደ ክርስትና ይቀይሩታል፡፡"

በዚህም ነብዩ ያለበትን የአለማቀፋዊ ሀይማኖቶች የዕውቀት ክፍተት መመልከት ይቻላል፣ ነብዩ በወቅቱ ግዙፍ የነበሩትን የሂንዱይዝም፣ ሺንቶይዝምን ... ሀይማኖቶችን አለማወቁ የነብዩ "ከአላህ ቁርአንን ተቀበልኩ" ቢልም ዕውቀቱ ግን ከግለሰባዊ ዕውቀት ያለፈ እውቀት አልነበረም፡፡

- <u>የክርስትና እውቀቱም የተምታታ ነበረ</u>

ነብዩ ክርስትናን የሚነቅፈው "አጋሪነት" በሚለው የስላሴ አስተምህሮቷ ነው ነገር ግን ነብዩ አጋሪነትን(የስላሴን ትምህርት) የተመለከተው የማርያም፣ የኢሳ(ኢየሱስ)ና የእግዚአብሄር ጥምረት አድርጎ ነው፣

> 5፡116 "አላህም፡- "የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን" በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፡፡"

ይህም ክርስቲያኖች ስላሴ የሚሉት "አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን ካለመረዳት የመጣ ስህተት ነው፡፡

- <u>ስለ ይሁዲ እምነት የነበረው እውቀት የተምታታ ነበረ</u>

ቁርአን እንደ ክርስቲያኖችም ባይሆን ይሁዲዎችንም አንዳንዴ በአጋሪነት ይከሳቸዋል፣

> 9፡30 "አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አለች ..."

ነብዩ "ዑዘይር" የሚለው አይሁዶቹ "ዕዝራ" የሚሉትን ሰው ነው ነገር ግን በየትኛውም የአይሁድ መፅሀፍ ላይ "ዕዝራ የእግዚአብሄር ልጅ ነው" የሚል ቃል አልተፃፈም፣ የአይሁድ መፅሀፍት "ዕዝራ" የሰው ልጅ ያውም "የአሮን ዘርና የሠራያ ልጅ"(ዕዝ.7፡1-5) መሆኑን ይናገራል፡፡

በዚህም “አይሁድ ዕዝራ የአላህ ልጅ ነው” አሉ የሚለው ስህተት ነው፡፡

- <u>የሁለቱን መሬማ(ማርያም) ታሪኮችን መቀላቀል</u>

ነብዩ ኢየሱስን በድንግልና የወለድችው የማርያም ታሪክ ከሞክሼዋ ከነሀሩን(አሮን) እህት ታሪክ ጋር ተቀላቅሎበታል፣

> 19፡27 “... “መሪየም ሆይ! ከባድ ነገርን በእርግጥ ሰራሽ” አሏት፡፡ “የሃሩን እህት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም፡፡ እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም” አሏት፡፡”

ነገር ግን የሃሩን(አሮን) እህት የሆነችው ማሪያም እና ኢየሱስን የወለደችው ማርያም ታሪኮች የተለያዩ ናቸው፣ በሁለቱ ማርያሞች መሃከል ከአንድ ሺ አመት በላይ ልዩነት አለ ነገር ግን የሁለቱ ሴቶች ስም ስለተመሳሰለበት የሁለቱን ታሪክ ቀላቅሏል፡፡

- <u>የሎጥና የኖህ ዘመን ቅጣቶችን ማቀላቀል</u>

> 11፡40 “ትዕዛዝ በመጣና እቶኑ በገነፈለ ጊዜ ... ልጁም ከውሃው ወደ ሚጠብቀኝ ተራራ እጠጋለሁ አለ ... ማዕበሉም ከመካከላቸው ጋረደ፣ ከሰጣሚዎች ሆነ፡፡”

የእቶን እሳት ጥፋት የሆነው በሎጥ ዘመን ነው፣ የጥፋት ውሃ የሆነው በኖህ ዘመን ነው፣ ነብዩ እነዚህ ሁለቱ ታሪኮች ተቀላቅለውበታል፣ በዚህ የታሪክ መቀላቀልም እርስ በርስ የሚጠፋፉት እሳትና ውሃ በመቀላቀሉ፣ ተቀጪዎቹ ምንም ቅጣት ያልወረደባቸው መሆኑ በራሱ ማስተዋል ነበረበት፡፡

እነዚህን እውነታዎች ስንመለከት ነብዩ ትልቅ የእውቀት ክፍተት እንደነበረባቸው እንመለከታለን፣ ነብዩ ይህንን የዕውቀት ክፍተታቸውን በመረዳት የምዕመናቱን አእምሮ ለመጠበቅ የተከተሉት አስተምህሮ ግልፅ የማጭበርበርና የማስፈራራትን አስተምህሮ ነበረ፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

## ➢ ማጭበርበር

ነብዩ ግልፅ የማጭበርበር አስተምህሮቶችን ሲያስተምር ነበረ፣ ይህም አጭበርባሪነት በተለይ ምዕመናኑ ወደ ክርስትና ሀይማኖት እንዳይሳቡና እስልምና ከክርስትና ሀይማኖት የሚበልጥ እንደሆነ ለምዕመናኑ ለማሳየት ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- <u>አይሁዶች/ክርስቲያኖች ቁርአን ሲነበብላቸው ያለቅሳሉ</u>
  5፡83 "(አይሁዶችና ክርስቲያኖች) ወደ መልክተኛውም የተወረደውን (ቁርአን) በሰሙ ጊዜ እውነቱን ከማወቃቸው የተነሳ ዓይኖቻቸው እንባን ሲያፈሱ ታያለህ፡፡ "ጌታችን ሆይ አመንን ከመስካሪዎቹም ጋር ፃፈን" ይላሉ፡፡"
- <u>አይሁዶች/ክርስቲያኖች በቁርአን ደስ ይላቸዋል</u>
  13፡36 "እነዚያ መፅሃፉን የሰጠናቸው ወዳንተ በተወረደው ይደሰታሉ፡፡"
- <u>አይሁዶች/ክርስቲያኖች ቁርአን ሲሰሙ ይሰግዳሉ</u>
  17፡107 "(ቁርአን) በእርሱ እመኑ ወይ አትመኑ በላቸው፣ እነዚያ ከእርሱ በፊት ዕውቀትን የተሰጡት በእነርሱ ላይ በተነበበ ጊዜ ሰጋጆች ኾነው በሸንጎበቶቻቸው ላይ ይወድቃሉ፤"
- <u>አይሁዶች/ክርስቲያኖች መሃመድን እንደ ወንድ ልጃቸው ያውቁታል</u>
  2፡146 "እነዚያ መፅሃፍ የሰጠናቸው ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል፡፡ ከነሱም የተለዩ ክፍሎች እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑ እውነቱን በርግጥ ይደብቃሉ፡፡ ይህ ከጌታህ የሆነ እውነት ነው ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን፡፡"
- <u>ነብዩ መሀመድ እንደሚመጡ በመፅሀፍ ቅዱሱ ተነግሮ ነበረ</u>
  61፡6 "የመርየም ልጅ ኢሳም፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ እኔ ከተውራቱ በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስኾን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልእክተኛ ነኝ ..."
- <u>ቁርአን እንደሚወርድ በመፅሀፍ ቅዱሱ ተተንብዮ ነበረ</u>
  26፡196 "እርሱም (ቁርአን) በቀድሞዎቹ መፃፍት ውስጥ የተወሳ ነው፡፡"

- <u>አይሁዶች/ክርስቲያኖች ቀድሞውኑ ሙስሊሞች ነበሩ</u>
  28፡52-53 "እነዚያ ከእርሱ በፊት መፅሃፍን የሰጠናቸው እነርሱ በእርሱ ያምናሉ፡፡ በእነሱም ላይ በሚነበብላቸው ጊዜ፣ በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የሆነ እውነት ነው፡፡ እኛ ከርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን፣ ይላሉ፡፡"
- <u>"ከኔ በፊት የነበሩት ነብያት አይሁድ/ክርስቲያን ሳይሆኑ ሙስሊሞች ነበሩ"</u>
  - 2፡139-140 " … በአላህ (ሀይማኖት) ትከራከሩናላችሁን … ወይም ኢብራሂም ኢስማኢል ኢስሃቅም ያዕቁብም ነገዶቹም አይሁዶች ወይም ክርስቲያኖች ነበሩ ትላላችሁን፣ "እናንተ ታውቃላችሁ ወይንስ አላህ …"
  - 3፡67 "ኢብራሂም ይሁዳዊም ክርስቲያንም አልነበረም ግን ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ተዘነበለ ሙስሊም ነበረ …"
  - 61፡7 "ኢየሱስ ወደ ኢስላም የሚጠራ ሲኾን …"
  - 22፡78 "… የአባታችሁን የኢብራሂምን ሃይማኖት ተከተሉ፡፡ እርሱ ከዚህ በፊት ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል፡፡"
  - 2፡135 "አይሁድን ወይም ክርስቲያኖችን ኹኑ፤ (ቅኑን መንገድ) ትመራላችሁና፣ አሉም፡፡ "አይደለም የኢብራሂምን ሀይማኖት ቀጥተኛ ሲኾን እንከተላለን፣ [17]ከአጋሪዎች አልነበረም በላቸው፡፡"

ሰዎችም ነብዩን እንዳይጠራጠሩ ነብዩ በየመልዕክቶቹ ውስጥ መሃላን ሲያበዛ ነበረ፣ ለምሳሌ፣

> 52፡1-6 "በጡር (ጋራ) እምላለሁ፡፡ በተፃፈው መፅሃፍም፡፡ በተዘረጋ ብራና ላይ፤ (በተፃፈው)፡፡ በደመቀው ቤትም፡፡ ከፍ በተደረገው ጣራም፡፡ በተመላው ባህርም እምላለሁ፡፡"

ተመሳሳይ መሃላዎቹንም በብዙ ቦታዎች ላይ እንመለከታለን 75፡1, 77፡1-6, 81፡1-15, 85፡1-3, 86፡1-11 …

---

[17] በእስልምና "አጋሪ" ማለት ከአምላክ በተጨማሪ አምልኮን ለሌላ አካል የሚያጋራ ማለት ነው፣ ቁርአን ሁለቱንም አይሁድና ክርስትናን በአጋሪነት ይወቅሳቸዋል (9፡30, 5፡73 …)

እንደዚሁ ጓደኞቹም በመህላዎች ሲያግዙለት ነበረ 53፥1-11 “በኮከብ እምላለሁ በወደቀ (በገባ) ጊዜ፡፡ ነቢያችሁ መሃመድ አልተሳሳተም፤ አልጠመመምም፡፡ ከልብ ወለድ አይናገርም … ሀይሎቹ ብርቱ (መልአክ) አስተማረው፡፡ ዕውቀት ባለቤት የሆነው (አስተማረው በተፈጥሮ ቅርፁ ሆኖ በአየር ላይ) ተደላደለም፡፡ እርሱ በላይኛው አድማስ ሆኖ፡፡ ከዚያ ቀረበ፤ ወረደም … ወደ ባሪያውም (አላህ) ያወረደውን አወረደ፡፡ (ነቢዩም በአይኑ) ያየውን በልቡ አልዋሸም፡፡”

ነገር ግን በወቅቱ የነበሩት ሰዎችም ይህንን የነብዩን አጭበርባሪነት በመመልከት 16፥101 “… አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም፡፡” ሲሉት ነበረ፡፡

- <u>ማስፈራራት</u>

ከማጭበርበሩ ጎን ለጎን ነብዩ የሚነሱበትን ጥያቄዎች ማለፍ የሞከረበት አንዱ መንገድ አስፈራሪ ትምህርቶች በመስጠት ነው፣ አስፈራሪ ትምህርቶች ሰዎችን በፍራቻ መንፈስ ውስጥ በማስገባት የጥያቄና የፍልስፍና መንፈስን ይይዛሉ፡፡

ቁርአኑም ነብዩ መሀመድ አስፈራሪ ነብይ እንደሆነ ይናገራል(21፥45, 13፥7)፣ ከአስፈሪ ትምህርቶቹ ለምሳሌ ያህል አንዱን ብንመልከት፣

> ሰሂህ ሙስሊም 41፥7005 - 41፥7019 “… ደጃል ወጣት ሰው ነው፣ ፀጉሩ ወፍራም፣ የተጠቀለለ፣ ቂጢጫ፤ አንድ አይኑ የማያይ፣ አይኑም የሚንሳፈፍ ወይን ይመስላል፣ በአይኖቹ መከከል “ካፊረ” የሚል ፅሁፍ ተፅፏል … የሚሄድበት ፍጥነት በንፋስ እንደ ሚነዳ ዳመና ነው፤ እሳትና ውሃ ይዞ ይሄዳል፣ እሳቱ እንደ ቀዝቃዛ ውሃ ነው፣ ውሃው እንደ እሳት ነው፤ እሳትና ጫካ አለው እሳቱ ጫካ ነው፣ ጫካው እሳት ነው … ደጃልም ሰውየውን ለሁለተኛ ጊዜ ሊገድለው ሲፈልግ የሰውየው አንገት ወደ መዳብነት ተቀየረ፣ በዚህም የሚገድልበትን መንገድ ስላጣ፣ ሰውየውን ወደ ላይ ወረወረው፣ ሰዎችም ወደ ሲኦል እሳት የወረወረው ይመስላቸዋል፣ ነገር ግን ወደ ገነት ነው የወረወረው፡፡”

ነብዩ ይህን ታሪክ የተናገሩት ለማስፈራራት እንጂ እንደዚህ አይነት ሰው ኖሮ አይደለም የሚገርመው ደግሞ የተረት ነገር ተመልሶ በትክክል ደግሞ መናገር እንደማይቻለው ሁሉ፣ ተረቱ በሌላ ጊዜ ተደግሞ ሲነገር

ከመጀመሪያው ተዛንፎ ነው፣ ይህም ስለ የደጃል የጠፋው አይን በተለየዩ ቦታዎች ላይ የተለያዩ ሃሳቦችን እናያለን፣ ሰሂህ ሙስሊም 41፡7010 "... ደጃል ግራ አይኑ የጠፋ ነው ..." ሲል በሰሂህ ሙስሊም 41፡7005 "ደጃል ቀኝ አይኑ የጠፋ ነው ..." ይላል፡፡

አስፈራሪ ትምህርቶች ሰዎችን በፍራቻ መንፈስ ውስጥ በማስገባት የጥያቄና ፍልስፍና መንፈሳቸውን ይይዛል፣ በዚህም ዘዴ ነብዩ የነበረበትን የዕውቀት ችግር ማዳፈን ችሏል፡፡

ይህ የነብዩ የዕውቀት ችግር ነብዩ ቁርአኑን ሲያስተምሩ የነበሩት ከፈጣሪ ተቀብለው ነው? ወይስ ከራሳቸው? የሚለውን ጥያቄ የሚያጭር ሲሆን በዚህ የመሀመድ የዕውቀት እጥረት መሀመድ እምነት የሚጣልበት መንፈሳዊ መሪ አለመሆኑና የሱን አስተምህሮ ተከትሎ መሄድ የማይቻል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

#### 2.3.3.4. ገነት ለመግባት ካላቸው እርግጠኝነት አንፃር

የሃይማኖት መሪ ከተመሪው ህዝብ ይልቅ የተከተለው መንገድ ገነት እንደሚያደርሰው እርግጠኛ መሆን አለበት፣ መሪው ያልደረሰበት ቦታ ተመሪው መድረስ አይችልምና፣ በዚህም መሪ ግንባር ቀደምትነት አለው፣ ቁርአኑም፣ 17፡71 "ሰዎችን ሁሉ በመሪያቸው የምንጠራበትን ቀን (አስታውስ)" በማለት መሪ ወሳኝ እንደሆነ ይናገራል፡፡

ቁርአን ኢየሱስ ምንም ሀጢያት አለመስራቱን(19፡19) በዚህም ገነት እንደሚገባ ይመሰክራል፣

> 3፡45 "... መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በሆነ ቃል ስሙ አልመሲህ ኢሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም በተከበረ ከባለሟሎችም በሆነ (ልጅ) ያበስርሻል፡፡"

ይላል፣ በዚህም በመጨረሻ ቀን ኢየሱስ ፍርድ የሚጠብቅ ሳይሆን፣ 4፡159 "... (ኢሳ) በትንሳኤ ቀን በነሱ(በመፅሃፉ ሰዎች) መስካሪ ይሆናል፡፡" እንደሚለው በትንሳኤ ቀን የኢየሱስ ስራ የመስካሪነት ስራ ነው፡፡

ነገር ግን ነብዩ መሀመድ ከመነሻው ተአምራት ሳይዝ የጀመረውና ወደ ሰማይ ያልተወሰደበትን ሁኔታ ስንለከት እስልምና ችግር ያለበት መሆኑ፣

- 40፡49-50 “እነዚያም በእሳት ውስጥ ያሉት ለገሃነም ዘበኞች “ጌታችሁን ለምኑልን፤ ከእኛ ከቅጣቱ አንድን ቃል ያቃልልን” ይላሉ፡፡ (ዘበኞቹም) መልእክተኞቻችሁ በተአምራቶች ይመጡላችሁ አልነበሩምን” ይላሉ፡፡”
- 19፡56 “በመፅሃፉ ኢድሪስንም(ሄኖክን) አውሳ፡፡ እርሱ እውነተኛ ነቢይ ነበርና፡፡ ወደ ከፍተኛ ስፍራ አነሳነው፡፡” ማለቱና በዚሁ መርህም ኢሳም(4፡158) ወደ ከፍተኛ ስፍራ መነሳቱ ነገር ግን መሀመድ እንደ እድሪስና ሙሳ ወደ ሰማይ አለመነሳቱና አሁንም ሞቶ ተቀብሮ ያለ መሆኑን ስንመለከት መሀመድ ትክክለኛ ነብይ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

ነብዩም ገነት ለመግባቱ እርግጠኛ አልነበረም፣

- ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡470 “... ሰውን ስራው ከሲኦል አያድነውም ... እኔም እራሴ የአላህ ምህረት በኔ ላይ ካልሆነ መዳን አልችልም ...”
- 46፡9 “... በእኔም በእናንተም ምን እንደሚሰራ አላውቅም፡፡”
- ሰሂህ ቡኻሪ 3፡43፡638፡ ኡም ሰላማ እንደተረከው (ስለ ሁለት የተጣሉ ሰዎች መሀመድ እንዲፈርድ ወደሱ ሲያመጡ) “አስተካክዬ ባለመፍረዴ ሲኦል ልገባ እችላለሁ” በማለት አልፈርድም ሲል እንለከተዋለን፡፡

በዚህም መሀመድ በተከተለው መንገድ ገነት ይግባ አይግባ እርግጠኛ አይደለም ይባሱኑ ደግሞ ነብዩ እንደ ማንኛውም ሰው፡-

- ሀጢያት ሲሰራ ነበረ
  - ቁርአን እስከ አራት ሚስት አግቡ(4፡3) የሚለውን ተላልፎ 11 ሚስቶች ማግባቱ (ሰሂህ ቡኻሪ 1፡5፡268)
  - ሚስቶቻችሁን አታበላልጡ (4፡3) እያለ ነብዩ ግን አይሻን ከሁሉም ሚስቶቹ አስበልጦ የሚወዳት መሆኑ(ሰሂህ ቡኻሪ 7፡65፡330)
  - ከላይ የተመለከትነው የነብዩ የአቅጣጫ ለውጥ፣ የማጭበርበር፣ የሽብርና የግድያ ሀጢያቶች፣

- ከታች በ2.4.4 ክፍል የተመለከተው ቁርአኑን በራሱ መንገድ ማስተካከሉና ቁርአኑ እርስ በርሱ እንዲሁም ከእውነታ ጋር እንዲጋጭ ማድረጉ፣

- <u>አላህም መሳሳቱን ሲነገረው ነበረ</u>
  - 47፡19 "... ስለ <u>ስህተትህም</u> ... ምህረትን ለምን፡፡"
  - 4፡105-106 "እኛ በሰዎች መካከል አላህ ባሳወቀህ ልትፈርድ ወደ አንተ በርግጥ መፅሀፉን አወረድን፡፡ <u>አላህን ምህረትን ለምን</u>፡፡ አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና፡፡"
- <u>ለስህተቱም ምህረትን ሲለምን ነበረ</u>
  ሰሂህ ቡኻሪ 8፡75፡319 "... እኔ በአንድ ቀን ውስጥ <u>70 ጊዜ አላህን ይቅርታ እጠይቃለሁ ንሰሀም እገባለሁ</u>፡፡"

ነብዩ ከአላህ ምህረትን ይለምን እንጂ

- ሰሂህ ቡኻሪ 9፡93፡473 "ሰዎችን የማይምሩትን አላህ አይምራቸውም፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 8፡73፡26 "ሌሎችን የማይምር ምህረትን አያገኝም፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 3፡34፡335 "በክፉ ፋንታ ክፉ አትመልሱ ..."

የሚሉትን ትዕዛዛትን ተላልፎ በሸብርና በጂሀድ ብዙ ሰዎችን ማስገደሉን ስንመለከት ነብዩ ምህረት ማግኘት እንደማይችል እንመለከታለን፡፡ መሪው መግባት ካልቻለ ደግሞ ተመሪው ህዝብም የሚገባበት መንገድ እንደሌለ ቁርአኑ ይናገራል(17፡71)፣ በዚህም የሙስሊም ማህበረሰብ ገነት መግባት እንደማይችል እንመለከታለን፡፡

## ማጠቃለያ (የነቢዩ መሀመድ እና የኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ንፅፅር)

ከላይ እንደተመለከትነው ሁለቱ የአለማችን ወደር የለሽ መሪዎች ፍፁም ተቃራኒ ሆነው አግኝተናቸዋል፣ ይህም ተቃርኖ የመጣው ሁለቱም የሚመሩት በተቃራኒ መንፈስ በመሆኑ ነው፣ በርግጥ ይህ ግልፅ ተቃርኖዋቸው ትክክለኛውን መሪ እንድንመርጥ ምርጫችንን ግልፅ ያደርግልናል፡፡

ነብዩ መሀመድ ከኢየሱስ ጋር ፍፁም ተቃራኒ እንደሆነው ሁሉ ከፈጣሪ ቃል ሆነ ከመሪነት ስነምግባር ጋር ተቃራኒ ሆኖ አግኝተነዋል፣ በዚህም ማንም ሰው እውነታውን ከሌላ ሰውኛ ተፅዕኖዎች ነፃ ሆኖ ከተመለከተ ከመሀመድና ከኢየሱስ መንገድ የኢየሱስን መንገድ እንደሚመርጥ ግልፅ ነው፡፡

ይህ እውነታ በመንፈሳዊው ብቻ ሳይሆን በስጋዊው ህይወትም የተመለከተ እውነታ ነው፣ አንድ "ኢየሱስን እከተለዋለሁ" የሚል ሰው እንደ ኢየሱስ በመልካም ባህሪ ቢኖር በሰውም በመንግስትም ተወዳጅ ይሆናል ነገር ግን አንድ "የመሃመድን መንገድ ጠብቄ እሄዳለሁ" የሚል ሰው ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል፣ እንደ መሀመድ ሰዎችን እንዲሰልሙ ቢያስገድድ፣ አልሰልም ያሉትን ቢያሸብር፣ ቢገድል፣ ቢያስገድል፣ የጂሀድ ጦርነት ቢያውጅ፣ የአይሻ አይነት የ9 አመት ልጅ ቢያገባ፣ 11 ሚስቶች ቢያገባ ... ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል፣ በዚህም ዛሬ ላይ ያሉት ሙስሊሞች የመሀመድን መንገድ ሙሉ በሙሉ አይከተሉም፣ ከነዚህ ተግባራት አንዱን ልፈፅም ቢሉ የሚጠብቃቸው እስር ቤት ነው፣ ነብዩም በዚህ ዘመን ኖረው ቢሆን ኖሮ ...

በዚህም ከመሀመድ መንገድ ይልቅ የኢሳ መንገድ ለስጋዊውም ሆነ ለመንፈሳዊው ህይወት ትክክለኛ መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

## 2.4. የእስልምና ቅዱሳት መፅሀፍት እና መፅሀፍ ቅዱሱ ተቃራኒ መሆናቸው

እስልምና የአብርሃም ሀይማኖቶች መካከል እንደመሆኑ መጠን ከርሱ ቀደምት የሆኑትን የአብርሃም ሀይማኖቶች መፅሀፍት ከፈጣሪ መውረዳቸውን እራሱ(ቁርአኑም) በዚሁ መንገድ ከፈጣሪ እንደወረደ ስለራሱ ይናገራል፣

> 2፡136 "በአላህና ወደ እኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስሃቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳም በተሰጡት ከነርሱ <u>በአንድም መካከል የማንለይ</u> ስንሆን አመንን፡፡"

በዚህም ቁርአኑ ከሱ በፊት የወረዱት መፅሀፍት(መፅሀፍ ቅዱስ) የፈጣሪ ቃል መሆኑን ይመሰክራል፣ በ1.4 ክፍልም እንደቀረበው በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ የተመለከተው ልዕለ ስብዕናነት የመፅሀፉ ትክክለኛ የፈጣሪ ቃልነት ያረጋግጥልናል፣ በዚህም የክርስትው መፅሀፍ ቅዱስ ትክክለኛ የፈጣሪ ቃል መሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለውም፡፡

እንደ እስልምና አስተምህሮ ቁርአን ከፈጣሪ በቀጥታ የወረደና በፈጣሪ ጥበቃ የሚደረግለት መፅሀፍ በመሆኑ(15፡9, 6፡19 ...)፣ ያለምንም እንከን፣ መዛነፍ፣ መጉደልና መጨመር እንደወረደ የተቀመጠ መፅሀፍ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ቁርአኑን በዝርዝር ስንመለከት መፅሀፉ እንደ መሀመድ ነብይነት ብዙ ችግሮች ያሉበት መፅሀፍ፣ ይህም፣

- "ወረደ" የተባለበት መንገድ የተምታታ መሆኑን፣
- የተሰባሰበው በተወዛገበ መንገድ መሆኑን፣
- ውስጡም የተለያዩ ነገሮች ጥርቅም መሆኑን፣
- አምላካዊ ቃልነቱን በሚያፈርስ መልኩ መስተካከሉ፣ ከእውነታና እርስ በራሱ የመጋጨት

ችግሮችን እንመለከትበታለን፣ ቀጥሎ ቀርቧል፣

### 2.4.1. ቁርአን “ወረደ” የተባለበት መንገድ የተምታታ መሆኑ

ቁርአን ከፈጣሪ(ከአላህ) ዘንድ በቀጥታ በመሃመድ ላይ እንደተወረደ ቁርአኑ ይናገራል፣

- 26፡194 “ከአስፈራዎቹ (ነቢያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)፡፡”
- 32፡2 “የመፅሃፉ መወረድ ጥርጥር የለበትም፡፡ ከአለማት ጌታ ነው፡፡”
- 25፡6 “ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለን ምስጢር የሚያውቀው አወረደው፡፡”

የዚህ ተመሳሳይ ሃሳብ በብዙ ቦታዎች ላይ ቀርቧል 21፡2,39፡1-2,39፡41

ነገር ግን መሀመድ ቁርአኑን “ተቀበለ” የተባለበትን መንገድ ስንመለከት ብዙ የተምታታ ነገር እንመከታለን፣

- አላህ መሀመድን አስተማረው(53፡6-18)፣
- አላህ በመሀመድ ልቦና ላይ አወረደው(26፡194)፣
- መሀመድ በህልም ተቀበለ(ሳሂህ ቡኻሪ 9፡87፡111)፣
- በደወል ድምፅ ከሰማይ ይገለጥለታል(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡2)
- ገብርኤል ተገልጦ መሀመድን አስተማረው(ሰሂህ ቡኻሪ 1፡1፡2)

ይህም ቁርአኑ “ወረደ” የተባለበት መንገድም የተምታታ መሆኑና ያወረደውም አካል አላህ ይሁን ገብርኤል የተምታታ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 2.4.2. ቁርአን የተሰባሰበው በተወዛገበ መንገድ መሆኑ

ነብዩ መሃመድ ባለመማሩ(7፡158) ምክንያት ቁርአኑንን አልፃፈውም፣ በዚህም የተወሰኑ የቁርአን ክፍሎችን በተማሩት ሰዎች(25፡5) በፓፒረስ ቅጠልና በቀጫጭን ነጭ ድንጋዮች(ሰሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509) ላይ ያፃፉ ሲሆን ሌሎቹን ክፍሎች ደግሞ በሽምደዳ እንዲያዙ አደረጉ(ሰሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509)፡፡

ቁርአኑ በእንዲህ ሁኔታ እያለ ነብዩ በህይወት ተለዩ፣ ከዚያም ተከታዮቻቸው ሀይማኖቱን በጂሀድ ማስፋፋት ቀጠሉ፣ ይሁን እንጂ በያማማ ጦርነት ብዙ ቁርአንን በቃላቸው የያዙት ሰዎች በማለቃቸው ምክንያት በቃል

የተያዘው የቁርአን ክፍል ፈፅሞውኑ እንዳይጠፋ፣ በአእምሮ የተያዘው የቁርአኑ ክፍል ቶሎ በፅሁፍ እንዲቀመጥ የሀይማኖቱ መሪዎች መከሩ፣ በዚህም አቡ በከር አስ-ሲዲቅ ለዛይድ ቢን ታቢት ቁርአኑን በአንድ መፅሀፍ እንዲያሰባስቡ አዘዙዋቸው(ሰሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509)፡፡

ዛይድ ቢን ታቢት ግን ይህንን ተልዕኮ ማስፈፀም እንደማይቻል በመናገር ሀሳቡን በመቃወም "የአላህ ነቢይ ያልሰሩትን እንዴት ችለህ ትሰራለህ … ቁርአን በአንድ መፅሀፍ አሰባስብ ከምትለኝ አንድን ተራራ ነቅለህ ቦታውን ቀይረው ብትለኝ ይቀለኛል" በማለት የተሰጣቸውን ግዳጅ ቢቃወሙም ስራው የግዴታ ስለነበረ ስራውን ጀመሩ(ሰሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509)፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተጀመረው ስራ በብዙ ጉድለቶች ውስጥ ቀጠለ፣ ጉድለቶቹም፡-

- ነብዩ ግልፅ ሳያደርጉ የሞቱት የቁርአን ክፍል መኖሩ፣

  አቡ ዳውድ ሱና፡787 "… የአላህ መልዕክተኛ ከኛ ጋር ተወሰዱ፣ ይሄ ክፍል የዚያ አካል መሆኑን ግልፅ አላደረጉልንም፡፡"

- ነብዩ ቁርአኑን በሙሉ በቃል መያዝ መቸገራቸውን፣

  ቁርአንን ነብዩ ቢቀበሉትም ነብዩ ቁርአኑን ሙሉ በሙሉ በቃል መያዝ ተቸግረው ነበር፣ ይህ እውነታ ሀዲስ ላይ በሰፊው ተዘግቧል፣ ሰሂህ ቡኻሪ 1፡8፡394, ሰሂህ ሙስሊም 4፡1179, አቡ ዳዉድ 3970, ሰሂህ ቡኻሪ 3፡48፡823, ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡449-450…፣ ነብዩ ስላልተማሩ የተቀበሉትን ቁርአን መፃፍ ባይችሉም ቁርአኑን የያዙት በቃላቸው ነበረ፣ ይሁን እንጂ ቁርአኑን እንደዚህ መርሳታቸው የወረደላቸውን ቁርአን ሙሉ በሙሉ ማስተላለፍ እንዳልቻሉ እንመከታለን፡፡

- የጠፋ የቁርአን ክፍል መኖሩ

  ሰሂህ ቡኻሪ 6፡61፡510፣ ኡትማንም ለሃፍሳ(የነቢዩ ሚስት) "ቁርአኑን በመፅሀፍ እየሰራን ስለሆነ፣ አንቺ ጋር ያሉትን የቁርአን ፁሁፎች ላኪልን" ሲላትና እሰዋም ያገኘችውን ስትልክለት ነገር ግን ጉዳት የደረሰባቸው

የፓፒረስ ቅጠሎች መኖራቸውን [18]የተወሰነ በፓፒረስ ላይ የተፃፈን የቁርአን ክፍል፣ በነብዩ ሞት ሀዘን ወቅት ፍየል ቤት ገብታ የፓፒረሱን ቅጠል በመብላትዋ የተወሰኑ የቁርአን ክፍሎች አብሮ መጥፋቱን ስትናገር እንመለከታለን (የኢብን ማጃህ ሱናን 3፡1944)፡፡

- ሰብሳቢዎቹ ያልተግባቡባቸው የቁርአን ክፍሎች መኖሩ፣

  - አቡ ዳውድ ሱና 786፡ ያዚድ አል ፋሪሲ እንደዘገበው፣ ኢብን አባስ ሲናገር እንደሰማሁት "ኡትማን ቢን አፉንን ጠየኩት "ለምንድነው የአል-ተውባህና የአል-አንፋልን ክፍሎች ወደ "ረዣዥሞቹ ሰባቱ ምዕራፎች" በመካከላቸው "ቢስሚላሂ ራህማኒ ረሂም" ሳትፅፍ የቀላቀልከው፣" አሉት፣ ኡትማንም "… ይዘቱን ሳየው … የዚህ አካል ነው ብዬ ስለገመትኩኝ ነው…" ሲል እንመለከታለን፣ ይህንን ሀሳብ በጃሚ አት ቲረሚዝ 5፡3086 ላይም እንመለከታለን፡፡
  - ሰሂህ ቡኻሪ 6፡61፡510፣ ውስጥ እንደተመለከተው ቁርአኑ በአንድ ሲሰባሰብ፣ "ኡስማንም ለሶስቱ ቁረይሻዊ ሰዎች "ምናልባትም ከዛይድ ቢን ታቢት ጋር በአንዳች ባትስማሙ ቁርአን በቁረይሽ ዘዬ ስለወረደ ዝም ብላችሁ በቁረይሽ አነጋገር ፃፉት፡፡" ሲል እንመለከታለን፡፡

በነዚህ ችግሮች ውስጥም ቁርአኑ ተፅፎ ካለቀ ቦሃላ በወቅቱ የነበረው ከሊፋ ኡስማን፣ አንድ አይነት ቁርአን ብቻ እንዲኖር በማሰብ ቁርአኑ በመጀመርያ የተፃፉበትን የፓፒረስ ቅጠሎች፣ ድንጋዮች … እና ሌሎቹ አይነት ቁርአኖች በሙሉ ሰብስቦ አቃጠለ፣ የሚገርመው ደግሞ ከሊፋው እንዳሰበው ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የቁርአን ኮፒዎች ይገኛሉ፣ [19]"ከከሊፋ ኡስማን ሞት በኋላ ቁርአን የተለያዩ ቅጂዎች እንዳሉት በታሪክ መዛግብት ተመልክቷል፣ በዚህ ዘመን አራት ቅጆዎች እንዳሉት ይነገራል፣ እኔ ሶስቱን ማግኘት ችያለሁ … አራቱ ቅጂዎችም፣ የዋርሽ ቁርአን፣ የቃሉን ቁርአን፣ የአል ዱሪ ቁርአን፣ የሃፍስ ቁርአን፣ ሲሆኑ በመካከልቸውም ብዙ ልዩነት አላቸው፡፡"

---

[18] ሳሂህ ኢማን(2007)፣ **ድብቁ እውነት ሲገለጥ**፣ ሶስተኛ እትም፣ ገፅ 30
[19] ሳሂህ ኢማን(2007)፣ **ድብቁ እውነት ሲገለጥ**፣ ሶስተኛ እትም፣ ገፅ 19-22

ከላይ በተመለከቱት ቁርአንን የማሰባሰብ ችግሮች ምክንያት ዛሬ አብዛኛው ሙስሊም የሚጠቀመዉ ቁርአን ላይ ብዙ ችግሮች ተፈጥረውበት እንመለከታለን፣ ይህም፣

ቁርአኑን ነብዩ መሀመድ በሚያውቁበት መንገድ ማስቀመጥ አልተቻለም፣ የቁርአኑ ምዕራፎቹ የተቀመጡት በአወራረዳቸው ቅደም ተከተል ሳይሆን በርዝመታቸው እጥረታቸው ቅደም ተከተል ነው፣ ከመግቢያው ምዕራፍ "አል ፋቲሃ" በስተቀር ሌሎቹ ከሞላ ጎደል የቀረቡት በምዕራፎቻቸው እርዝማኔ እንጂ በተወረዱበት ቅደም ተከተል አይደለም ለምሳሌ አል ተውባህ የወረደው በመጨረሻው ላይ ነው(አቡ ዳውድ ሱና 785) ነገር ግን ቁርአኑ ላይ የምናየው በዘጠነኛው ምዕራፍ ላይ ነው፡፡

በመቀጠል ችግሩ ቁርአኑን የስነፅሁፍ ስነምባር የጎደለው መፅሀፍ እንዲሆን አድርጎታል፣ እነዚህም ችግሮች የክሮኖሎጂ፣ አሰልቺ ድግግሞሽ፣ ግራ መጋባት፣ ታሪኮች መቀላቀል፣ ያልተዘገቡ ታሪኮችና የተቆረጡ ታሪኮችን እንመለከትበታለን፣

- <u>የክሮኖሎጂ ችግር</u>
  በየምዕራፎቹ የምንመለከተው ታሪክ የጊዜ ፍሰት ጠብቀው አልተፃፉም፣ ይህንን ለመረዳት ክሮነሎጂውን ጠብቆ የተፃፈ መፅሀፍ ለምሳሌ መፅሀፍ ቅዱሱን ብንለከት ሲጀምር "በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" በማለት ከመጀመሪያው ሲጀምር፣ በመካከሉም የቀረቡት ታሪኮች የክስተታቸውን ጊዜ ጠብቀው የተፃፉ ሲሆን፣ ሲጨርስም "በመጨረሻ" በማለት የቁሳዊው አለም መጨረሻ እንዴት እንደሚሆን በመተረክ ይቋጫል፣ ቁርአኑን ግን ስንመለከት እንደዚህ ከመጀመሪያው ታሪክ አይነሳም፣ አጨራረሱም መጨረሻ ባልሆነ መልኩ ነው የሚጠናቀቀው፡፡
- <u>አሰልቺ ድግግሞሽ</u>
  በምሳሌ ብንመለከት ፈርኦንና ሙሴ ስለ <u>እስራኤል ህዝብ መለቀቅ</u> የተነጋገሩት ንግግር ብቻ በተመሳሳይ ቃላት ከ23 በላይ ቦታዎች ላይ ተደጋግሟል፣ 2፡5-51, 7፡127, 8፡54, 10፡75, 11፡96, 14፡6, 17፡101, 20፡49, 20፡77-78, 23፡45-48, 26፡16-53, 27፡12, 28፡3, 29፡39, 40፡23-24, 40፡37, 43፡46, 44፡17, 51፡38, 69፡9, 73፡16, 79፡15-17,

85፡18 … የሚገርመው ደግሞ እንደዚህ በመደጋገሙ ውስጥ ተጨማሪ አዲስ ነገር አናገኝበትም፣ ሁሉም አጠር አጠር ተደርገው በተመሳሳይ ቃላት የተደጋገሙ ተመሳሳይ ታሪኮች ናቸው፣ ይህ ችግርም የቁርአንን ንባብ አሰልቺ አድርጎታል፡፡

• ግራ መጋባት

እነዚህ ግራ የተጋቡትን አንቀፆች ብንመለከት፡-

- 49፡14 "የአረብ ዘላኖች "አምነናል" አሉ፡፡ "አላመናችሁም፤ ግን ሰልመናል በሉ፡፡ "እምነቱ በልቦቻችሁ ውስጥ ገና (ጠልቆ) አልገባም፡፡"
  "የሰለመ" ማለት "ያላመነ" ማለት ነው እንዴ?
- 57፡27 " … (ኢየሱስን) በተከተሉት (ሰዎች) ልቦች ውስጥ መለዘብንና እዝነትን፣ አዲስ የፈጠሩትን ምንኩስና **አደረግን**፡፡ በእነርሱ ላይ ምንኩስና አልፃፍናትም፡፡ ግን የአላህን ውዴታ ለመፈፀም ፈጠሩዋት፡፡"
  የፈጠሩትን "አደረግን" ይላል ተመልሶ ደግሞ "አልፃፍናትም" ይላል
- የአላህ አሸናፊነትና ጥበበኝነት እንዴት ይገለፃሉ?
  5፡38 "ሰራቂውንና ሰራቂቱንም በሰሩት ነገር ለቅጣት ከአላህ የሆነ መቀጣጫ እጆቻቸውን ቁረጡ፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡"
- 29፡61 "ሰማያትን ምድርን የፈጠረ ፀሀይና ጨረቃን የገራ ማን እንደሆነ በርግጥ ብትጠይቃቸው በርግጥ አላህ ነው ይሉሃል፡፡ ታዲያ እንዴት ይመለሳሉ፡፡"
- 23፡84-90 "… የሰባቱ ሰማያት ጌታና የአርሹ ባለቤት ማን ነው በላቸው፣ በርግጥ የአላህ ነው ይሉሃል … ይልቁንም እውነት አመጣንላቸው፡፡ እነርሱም (በመካዳቸው) ውሸታሞች ናቸው፡፡"
- ምስክርነት ማን በማን ላይ?
  41፡22 "ጆሮዎቻችሁ ዓይኖቻችሁና ቆዳዎቻችሁም በእናንተ ላይ ከመመስከራቸው የምትደበቁ አልነበራችሁም፡፡"
  ሰው ማለት የአካላት ህብረት ነው፣ ሁሉም አካላቱ ማሰብያ አእምሮ ኖሯቸው በራሳቸው ሀሳብና ፍቃድ የሚኖሩ ሳይሆኑ ሁሉም ባንድነት የአንድ ሰው ማንነት ናቸው፣ በዚህም አንዱ አካል

"አልተስማማሁም ነበር" ብሎ ምስክር የሚሆንበት አሰራር የለም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሞቶ አፈር የሆነ ይባሱኑ በአውሬ የተበላ፣ በቃጠሎ የጠፋ ... ምንም ቀሪ የሌለውስ ምን ይደረጋል?

- ተራራውን ነቅሎ ከበላያቸው ያስኬድ ነበረ

  2፡93 "የጡርን ጋራ ከበላያችሁ ያነሳን ስንኾን(በኦሪት ህግ እንድትሰሩ) ኪዳናችሁን በያዝን ጊዜ (አስታውሱ)፡፡ "የሰጠናችሁን በሃይል ያዙ ስሙም" (አልን)፡፡ ሰማንም አመፅንም አሉ፡፡"

  ነገር ግን እኚህ ሰዎች አምፀዋል፣ ተራራውን ያነሳው ለወከባ ነበር እንዴ?

- አብረው የማይሄዱ ሀሳቦች

  44፡25-30 "(እስራኤሎች ከግብፅ ሲወጡ) ከአተክልቶችና ከምንጮች ብዙ ነገሮችን ተው፡፡ ከአዝመራዎችም ከመልካም መቀመጫዎችም፡፡ <u>በርስዋ ተደሳቾች ከነበሩባት ድሎት (ብዙ ነገር ተው)</u> ... የእስራኤልንም ልጆች <u>አዋራጅ ከሆነ ስቃይ</u> በእርግጥ አዳንናቸው፡፡"

- ከሰው ልጅ መሳሳትና ከምድር መፈጠር የቱ ይቀድማል? በአላህ ስም ለማስፈራራት ካልሆነ በቀር?

  50፡7 "ምድርን ዘረጋናት፡፡ በርስዋም ውስጥ ጋራዎችን ጣልንባት፡፡ በውስጥዋም ከሚያስደስት ዓይነት ሁሉ አበቀልን፡፡ (ይህንን ያደረግነው) <u>ተመላሽ</u> ለኾነ ባሪያ ሁሉ ለማሳየትና ለማስገንዘብ ነው፡፡"

- 5፡64 "አይሁዶች የአላህ እጅ የታሰረች ናት አሉ፡፡ እጆቻቸው ይታሰሩ..."

  አይሁዶች ዓለምን እንደዚህ ማሽከርከራቸው እጆቻቸውን በደንብ ሳይታሰር ቀርቶ ነው?

- <u>ያልተዘገቡ ታሪኮች</u>

ነብዩ ያልተናገሩት ክፍል መኖር፣ የጠፉ ክፍሎች መኖርና ነብዩ ቁርአኑን በቃል መያዝ አለመቻላቸው ምክንያት መሠረታዊ ነገሮች በቁርአን ላይ ሳይዘገቡ ቀርተዋል፡፡

ለምሳሌ ሀዲስ ላይ የምንመለከተው ደጃል የተባለው ሰው ታሪክ ቁርአኑ ላይ አልተዘገበም፣ ኢብራሂም ሊሰዋው የነበረው የትኛውን ልጅ እንደሆነ አልተዘገበም ኢስማኤልና ኢስሀቅ መካከል ሰፊ መንፈሳዊ ትርጉም አለና፣ ሙስለሊሞች ከቁርአኑ እኩል ስልጣን ያለው ሀዲስ የተባለ የሙስሊም መመርያ መፅሀፍ ይኑር አይኑር አልተናገሩም … የመሳሰሉ መሰረታዊ ነገሮች ቁርአኑ ላይ ሳይዘገቡ ቀርተዋል፡፡

- <u>የታሪኮች መቆረጥ፣</u>

ለምሳሌ፣ አንድ "አቡ ለሀብ" የሚባል ሰው ታሪክ ምዕራፍ 111 ላይ እናገኛለን፣ የዚህ ሰው ታሪክ የተፃፈው በዚህ ምዕራፍ ላይ ብቻ ሲሆን፣ ምዕራፉ አጭር በመሆኑ ሙሉ ምዕራፉን እንመልከት፣

111፡1-5 "የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ(ጠፉ እርሱ) ከሰረም፡፡ ከእርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም፡፡ የመንቀልቀል ባለቤት የሆነች እሳት በእርግጥ ይገባል፡፡ ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትሆን፡፡ በአንገትዋ ላይ ከጭረት የኾነ ገመድ ያለባት ስትኾን፡፡"

እዚህ ጋር የምንመለከተው የተቆረጠ ታሪክ ነው፣ ይህ አቡ ለሀብ የተባለው ሰው እዚህ ጋር የተጠቀሰው ጥፋት በማጥፋቱ እንደሆነ ይገባናል ነገር ግን እዚህ ጋር ሰዎች እንዲማሩ የተፈለገው ዋናው ነጥብ የዚህ ሰው ጥፋት ምን እንደሆነ አልተጠቀሰም፣ በዚህ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋናው ሀሳብ ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡

- <u>የታሪኮች መቀላቀል፣</u>

ቁርአን መፅሀፍ ቅዱሱን ቢቀበልም አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከመፅሀፍ ቅዱሱ የተወሰዱ ታሪኮች ከሌሎች ታሪኮች ጋር ተቀላቅለዋል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- 38፡48 "ኢስማዒልን፣ <u>አልየሰዕንም፣ ዙልኪፍንም</u> አውሳ፡፡"
- 40፡23-24 "ሙሳን … ወደ ፈርኦን <u>ወደ ሃማን፣ ወደ ቃሩንም</u> ላክነው፡፡"

- 50፡12-14 “ከእነርሱ በፊት የኑህ(ኖህ) ህዝቦችና የረሰስ ሰዎች፤ ሰሙድም አስተባበሉ፡፡ ዓድም ፈርዖንም፤ የሉጥ(ሎጥ) ወንድሞችም፤ የአይከት ሰዎችም የቱብበዕ ህዝቦችም ሁሉ መልክተኞቹን ሁሉ አስተባበሉ፡፡ ዛቻዬም ተረጋገጠባቸው፡፡”

እነዚህ ከታወቂ የመፅሀፍ ቅዱሱ ፃድቃን ስሞች ጋር የገቡት አልየሰዕ፣ ዙልኪፍ፣ ሃማን፣ ቃሩን፣ ሰሙድ፣ ዓድ፣ የረሰስ ሰዎች፣ የአይከት ሰዎች፣ የቱብበዕ ህዝቦች የሚባሉት ታሪኮች በአይሁድ/እስራኤል መፅሀፍት ላይ የሉም፣ እነዚህ ታሪኮች የተቀላቀሉት ከሌላ በታ ነው፣ በዚህም ቁርአኑ ላይ የታሪክ መቀላቀል ተፈጥሮበታል፡፡

እነዚህ ከላይ የተመለከቱት፣ ነብዩ ግልፅ ያላደረጉት የቁርአን ክፍል መኖሩ፣ የጠፉ የቁርአን ክፍል መኖሩ፣ ቁርአንን ነብዩ ባስተማሩት መንገድ ማስቀመጥ አለመቻል፣ ክሮኖሎጂውን ጠብቆ ማስቀመጥ አለመቻል፣ የክሮኖሎጂ ችግር፣ የአሰልቺ ድግግሞሽ መፈጠር፣ ግራ መጋባት፣ ታሪኮችን አለመዘገብ፣ የመቆራረጥና የታሪክ መቀላቀል ችግሮቹን በአንድ ላይ ስንመለከት ቁርአን “ከፈጣሪ በቀጥታ የወረደና በፈጣሪ ጥበቃ የሚደረግለት ቅዱስ መፅሀፍ ነው” ማለት እንደማይቻል ያሳያል፡፡

### 2.4.3. <u>የቁርአን ይዘት የተለያዩ ነገሮች ጥርቅም መሆኑ</u>

የቁርአኑን ይዘት በዝርዝር ስንመለከት፣ ቁርአን ከፈጣሪ ወይ ከገብርኤል ለመሀመድ የመጣ መገለጥ ሳይሆን የተወሰኑ ከ60-70% መፅሀፍ ቅዱሳዊ አሰተምህሮቶችን ከሌሎች ነገሮች ጋር በማቀናበር ነው፣ የተቀናበሩትም ነገሮች ነብዩ በሀሰት “ጅብሪል ተናገረኝ” የሚሉት የግል ፍልስፍና፣ ሰዎች መሀመድን የመከረው ምክር፣ መሀመድ ሰዎች ለጠየቁት ጥያቄ የሰጠው መልስ፣ መሀመድ ሰዎችን የመከረው ምክር፣ የግለሰቦች አስተያየት፣ የመሀመድ የግል ጉዳይ፣ ተረቶችና የመሳሰሉትን ነገሮች በአንድ ላይ በማጠራቀም ነው፣ ሁሉንም በዝርዝር እንመለከታለን፡-

## 1. <u>በሀሰት “ጅብሪል ተናገረኝ” የሚሉት ዘዴ</u>

ሰሂህ ቡኻሪ 4፡55፡546፣ አናስ እንደዘገበው፣ ነብዩ መዲና መምጣታቸውን አብዱላ ቢን ሰላማ እንደሰሙ ወደ ነብዩ መጡና፣ ከአንተ በቀር ማንም ሊመልሰው የማይችል ሶስት ጥያቄ እጠይቅሀለሁ አንደኛ …፣ ሁለተኛ …፣ ሶስተኛ “ለምንድነው ልጅ አባቱን እና የናቱን ወንድም የሚመስለው፣ ነብዩም “መልሱን ጅብሪል/ገብርኤል አሁን ነገረኝ … በግንኙነት ወቅት አባት ቀድሞ ስሜቱን ከጨረሰ የሚወለደው እሱን ይመስላል፣ እናት ቀድማ ከጨረሰች እስዋን ይመስላል …”

ይህ ውሸት መሆኑንና የልጅ መልክ የሚወሰነው በስሜት ሳይሆን የወንዱና የሴቷ ዘረመሎች የሚጣመሩበት መንገድ መሆኑን ስንመለከት ነብዩ የራሳቸውን ሀሳብ “ገብርኤል ተናገረኝ” ብለው ሲናገሩ እንደነበረ እንመለከታለን፡፡

በርግጥ በ2.3.3.3 ክፍል እንደተመለከትነው የነብዩ መሀመድ አስተምህሮ ሁሉን ከሚያውቀው ፈጣሪ አለመሆኑ፣ በ2.3.2 ክፍል እንደተመለከትነው ነብዩ ከአይሁድ/ክርስትና ሀይማኖት የአቅጣጫ ለውጥ ማድረጋቸው እንዲሁም ከታች በ2.4.4 ስር የተመለከተው ቁርአኑ ለመሀመድ ድክመት ተብሎ መከለሱ፣ ከእውነታ ጋር እንዲሁም እርስ በርስ መጋጨቱ ውስጥ ይህንኑ እውነታ ያረጋግጣሉ፡፡

## 2. <u>ሰዎች መሀመድን የመከሩት ምክር</u>

ለምሳሌ ብንመለከት፣

> ሰሂህ ቡኻሪ 1፡8፡395፡ ኡመር ቢን አል ካታብ እንደተረከው፡ ጌታዬ በሶስት ነገር ከኔ ጋር ተስማማ … አንደኛው …፣ ሁለተኛው የሴቶችን መሸፋፈን የሚመለከተውን አንቀፅ አስመልክቶ፣ ለአላህ ነቢይ “ሚስቶችህ ሰውነታቸውን ቢሸፍኑ መልካም ነው ምክንያቱም ጥሩም መጥፎም ሰው ይናገራቸዋልና” አልኳት፣ <u>በዚህም ስለሴቶች መሸፋፈን የሚያዘው አንቀፅ ተገለጠ</u>፡፡ ሶስተኛ የነቢዩ ሚስቶች በነቢዩ ላይ አንድ ሆነው በተነሱበት ጊዜ እኔም፣ “ነቢዩ ሁላችሁንም ቢፈታ አላህ ከናንተ የበለጠ ሚስቶች ይሰጠዋል” አልኳቸው፣ <u>በዚህ እኔ የተናገርኩት አንቀፅ ወረደ</u>፡፡”

ተመሳሳይ ሀሳብ ሰሂህ ቡኻሪ 6:60:10 ላይም ቀርቧል፡፡

እነዚህ የሰው ምክሮች የአላህ ቃል ተደርገው ቁርአኑ 33:59 እና 66:5 ላይ መቅረባቸው፣ ቁርአን ፈጣሪ ቃል አለመሆኑን ያሳያል፡፡

## 3. መሀመድ ሰዎችን የመከረው ምክር

ሰዎች ነብዩ መሀመድን ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ፣ ነብዩ ለሰዎች የሚመልሱት መልስ እንደ አላህ ቃል እንዲያዝ ሲያዙ ነበረ፣ በዚህም መልሶቻቸው በቁርአኑ ላይ የአላህ ቃል ተደርገው እንመለከታለን፣ ለምሳሌ

> ሰሂህ ሙስሊም 26:5395 "አይሻ እንተረከችው፣ ሰአዳ ልትፀዳዳ ሜዳ ወጣች፣ ከሴቶች ሁሉ ረዥምና ጠብደል በመሆኗ ከሚያውቃት ሰው መደበቅ አትችልም፣ ዑመር ከታብ ተመለከታት "ሰአዳ፣ ኧረ በአላህ ልትደበቂ አትችይም፣ ስትወጪ ጠንቀቅ አለ"፣ ወደ ቤትም ተመለሰች፣ በወቅቱ የአላህ መልዕክተኛ እኔ ቤት እየተመገበ ነበረ፣ አጥንት በእጁ ይዞ ነበረ፣ ሰአዳም "ዑመር እንዲህ እንዲህ አለኝ" ብላ ተናገረች፣ <u>በዚህ ጊዜ መገለጥ መጣ</u>፣ አጥንቱን በእጁ እንደያዘ "ስትፈልጊ መውጣት ተፈቀደ" አለ፡፡"

እንደዚህ አይነት ብዙ ተመሳሳይ የቁርአን ቃል አወራረዶችን ብዙ ቦታዎች ላይ ተመልክቷል፣

- ሰሂህ ቡኻሪ6:60:44 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 2:198
- ሰሂህ ቡኻሪ 6:60:51 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 2:223
- ሰሂህ ቡኻሪ 6:60:52 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 2:232
- ሰሂህ ቡኻሪ 6:60:209 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 11:114
- ሰሂህ ቡኻሪ 6:60:203 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 11:5

እነዚህ የመሀመድ ምክሮች የፈጣሪ ቃል ተደርገው በቁርአኑ ላይ ተፅፈዋል፣ እንደዚህ "መገለጥ መጣ" ሳይባል በቀጥታ የተቀመጡ የመሀመድ አስተያየቶችም ቁርአን ላይ ይታያሉ፣ ለምሳሌ፣

- 11:34 "ለናንተ ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደሆነ ምክሬ አይጠቅማችሁ፡፡"

- 10፡3-5 “ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው ... ከእርሱ ፈቃድ በኋላ ... እነሆ አላህ ጌታችሁ ነውና ተገዙት፣ አትገሰፁም ... መመለሻችሁ ወደ እርሱ ነው ... እርሱ ያ ...”
- 6፡2-3 “እርሱ ያ ከጭቃ የፈጠራችሁ ከዚያም (የሞት) ጊዜን የወሰነ ጊዜ አለ ... እርሱም ያ በሰማያትና በምድር (ሊግገዙት የሚገባው) አላህ ነው... የምትሰሩትንም ሁሉ ያውቃል፡፡”

እነዚህን ቀጥተኛ የመሀመድን ምክሮች በቁርአን ውስጥ መመልከቱ “ቁርአን ከፈጣሪ የወረደ ነው” የሚለውን ሀሳብ ያፈርሳል፡፡

## 4. <u>የሰዎች አስተያየት</u>

እነዚህ አስተያየቶች በድጋፍና በተቃውሞ የተሰጡ ሲሆኑ ከሁለቱም በአንዳንድ ምሳሌ እንመልከት፣

- በድጋፍ የተሰጠ አስተያየት

  53፡1-11 “በኮከብ እምላለሁ በወደቀ (በገባ) ጊዜ፡፡ ነቢያችሁ መሃመድ አልተሳሳተም፤ አልጠመመምም፡፡ ከልብ ወለድ አይናገርም ... ሀይሎቹ ብርቱ (መልአክ) አስተማረው፡፡ ዕውቀት ባለቤት የሆነው (አስተማረው በተፈጥሮ ቅርፁ ሆኖ በአየር ላይ) ተደላደለም፡፡ እርሱ በላይኛው አድማስ ሆኖ፡፡ ከዚያ ቀረበ፤ ወረደም፡፡ ... ወደ ባሪያውም (አላህ) ያወረደውን አወረደ፡፡ (ነቢዩም በአይኑ) ያየውን በልቡ አልዋሸም፡፡”

- በተቃውሞ የተሰጠ አስተያየት

  21፡5 “በእውነቱ (ቁርአኑ) የሕልሞች ቅዠቶች ነው፡፡ ይልቁንም ቀጠፈው እንዲያውም እርሱ ቅኔን ገጣሚ ነው፡፡ ቀድሞዎቹም እንደተላኩ (መልእክተኛ ከሆነ) በተአምር ይምጣብን አሉ፡፡”

እነዚህ የፈጣሪ ቃላት አይደሉም፡፡

## 5. <u>መሀመድ የግል ጉዳዩን የፈጣሪ ቃል አድርጎ የፃፈበት</u>

ነብዩ የራሳቸውን የግል ጉዳዮች የፈጣሪ ቃል አስመሰለው ቁርአን ላይ አስገብተዋል፣ ለምሳሌ፣

- 33፡30-33 “የነብዩ ሴቶች ሆይ … <u>ያ በልቡ ውስጥ በሽታ ያለበት እንዳይከጅል</u> በንግግር አትለስልሱ …”
- 33፡53 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ … ወደ ምግብ ካልተፈቀደላችሁ በስተቀር የነቢዩን ቤቶች (በምንም ጊዜ) አትግቡ … <u>በተመገባችሁ ጊዜ ወዲያውኑ ተበተኑ</u>፡፡ ለወግ የምትጫወቱ ኾናችሁ (አትቆዩ) … <u>ዕቃን (ለመዋስ) በጠየቃችኋቸው ጊዜ ከመጋረጃ ኋላ ሆናችሁ ጠይቋቸው</u> …”
- 49፡1-2 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ … ድመፆቻችሁን ከነብዩ ድምፅ በላይ ከፍ አታድርጉ…”

መቼም ሰማይና ምድርን የሰራው ፈጣሪ ስለመሀመድ ሴቶች፣ ስለመሀመድ ጓዳ፣ መሀመድ ጋር ስለሚመጡ ወሬኞች ለትውልድ በሚተላለፍ ቅዱስ መፅሀፉ አያወራም ነብዩ ፈጣሪን ተመስሎ በቁርአኑ በኩል ካልተናገረ በቀር፡፡

## 6. <u>ተረቶች</u>

ቁርአን “የፈጣሪ ቃል” ቢባልም በውስጡ ግን ብዙ በግልፅ የተቀመጡ ተረቶች ይዟል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- <u>በነሃስ ግድብ የተገደቡ የእጁጅ መጁጅ ህዝቦች</u>

  18፡93-97 “ከዚያ (ወደ ሰሜን አቅጣጫ) መንገድን ቀጠለ፡፡ በሁለቱ ጋራዎች መካከል በደረሰ ጊዜ በአቅራቢያቸው ንግግርን ለማወቅ የማይቃረቡ ህዝቦች አገኘ፡፡ “ዙርቀርነይን ሆይ! የእጁጅና መጁጅ በምድር ላይ አበላሺዎች ናቸውና በእኛና በእነሱ መካከል ግድብን ታደርግ ዘንድ ግብርን እናደርግልህን” አሉ … (እሱም)በጉልበት እገዙኝ፡፡ በእናንተና በእነርሱ መካከል ብርቱ ግድብ አደርጋለሁና፡፡ “የብረት ታላላቅ ቁራጮች ስጡኝ (አላቸው) … (ብረቱን) እሳት ባደረገው ጊዜ “የቀለጠውን ነሀስ ስጡኝ፤ በእርሱ ላይ አፈስበታለሁና” አላቸው፡፡ (የእጁጅና መእጁጅ) ሊወጡት አልቻሉም፡፡ ለእርሱ መሸንቆርንም አልቻሉም፡፡ “ይህ (ግድብ) የጌታዬ ችሮታ ነው፡፡”

እነዚህ የእጁጅና መዕጁጅ ህዝቦችና በሁለት ተራሮች መሃከል የተሰራው የነሃስ ግንብ፣ በየትኛው የምድር ክፍል ላይ ይገኛል? ከተባለ፣ መልስ የለም፣ እነሱ የሚገኙት በመሬት ላይ ሳይሆን በተረቶች ውስጥ ብቻ ነው፡፡

ይህ በፈረንጆቹም ዘንድ የታወቀ ተረት ነው፣ አሌክሳንደር ዘግሬት የተባለው ሰው በተረት ውስጥ እንደዚህ እንዳደረገ ይነገራል፡፡ የዚህን የአሌክሳንደር ዘግሬት የተባለው ሰው ተረት ነብዩ ሌላ ቦታም ላይ አቀናብሮ ተጠቅሞታል፣ አሌክሳንደር ዘግሬት ንስር አሞራና ፈረስ አዳቅሎ የሚበር ፈረስ ሰርቶ በዚህ አውሬ በርሮ ገነት እንደገባ ይነገራል፣ መሃመድም በዚህ የተረት ፈረስ(ቡራቅ) ወደ ገነት (ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡429) እና ሩቁ መዝጊድ(17፡1) መሄዱን ተናግሯል፡፡

- <u>ከሰው የተለዩ ከፀሀይ መከለያ የሌላቸው ህዝቦች</u>

18፡89-90 "ከዚያም መንገድ ወደ ምስራቅ ቀጠለ፣ <u>ወደ ፀሃይ መውጫ በደረሰ ጊዜ</u> ለእነሱ ከበታችዋ መከለያን ባላደረግንላቸው ሕዝቦች ላይ ስትወጣ አገኛናት፡፡"

እነዚህ ፀሀይ የምትወጣበት ጉድጓድ አጠገብ ያሉ መከለያ የሌላቸው ህዝቦች የትኞቹ ህዝቦች/ሀገር እንደሆኑ ብናውቅ ጥሩ ነበረ፡፡

- <u>ነሀስ የሚፈልቅበት ምንጭ</u>

34፡12 "... (ለሱሌይማን) የነሀስንም ምንጭ ለእርሱ አፈሰስንለት፡፡"

ምንጩ የሱሌይማን ሀገር በሆነችው እስራኤል የት እንደሚገኝ ቢጠቁሙን መልካም ነበረ፣ ምንጩ ደርቆ ቢሆን እንኳን ቢያንስ ዛሬ ቅሪቱ ይገኝ ነበረ፡፡

- <u>ሰንበትን ስላላከበሩ ዝንጀሮ የተደረጉ ሰዎች፡-</u>

7፡163-166 "ከእርሱም ከተከለከሉት ነገር(ሰንበትን እንዳይሰሩ) በኮሩ ጊዜ ለእነሱ "ወረዶች ዝንጀሮች ሁኑ አልን፤" (ኾኑም)፡፡"

ሰንበትን የማያከብሩትን እንደዚህ ይሆናሉ ከሆነ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ጨምሮ ሰንበትን የማያከብር ህዝብ ጉድ በሆነ ነበረ፡፡

- <u>ጉንዳኖች ሰዎችን በስም ያውቃሉ ወቅታዊውን ፖለቲካም ይከታተላሉ</u>

27፡18 "(እነ ሱለይማን) በጉንዳንም ሸለቆ በመጡ ጊዜ አንዲት ጉንዳን፡- እናንተ ጉንዳኖች ሆይ! ወደ መኖሪያችሁ ግቡ፤ ሱለይማንና ሰራዊቱ እነርሱ የማያውቁ ሲሆኑ አይሰባብሩአችሁም አለች፡፡"

እዚህ ጋር ሰለሞን በተሰጠው ጥበብ የበራሪን ቋንቋ ያውቃል ተብሏል(27፡16)፣ ታዲያ ጉንዳንዋስ ሱሌይማንን የሚባል ሰው መኖሩን፣ ሱሌይማንን ከሰው መለየትን፣ ሱለይማን ወታደሮች እንዳሉት፣ የሱለይማን ወታደሮች በዚያ እንደሚያልፉ የዘመቻቸውን ፕሮግራም ... እውቀቶችን ከየት አገኘች? ይህ ስህተት የመጣው "የሱለይማን ጥበብ ወሰን የለውም" ብሎ አስፍቶ ከማሰብ የሰፋቱ ብዛት ጉንዳንዋም ስላጠቃለለ እንጂ የጉንዳን ሰለሞን ወይ የጉንዳን ነቢይ ኖሮ አይደለም፡፡

በወቅቱ የነበሩት ህዝቦችም ይህንን የመሀመድን ተረት ተረት ተገንዝበው፣ ቁርአኑ 25፡5 "አሉም "የመጀመሪያ ሰዎች ተረቶች ናት፣ አስፃፋትም፣ እርሷም በእርሱ ላይ ጧትና ማታ ትነበብለታለች፡፡" ብለው ነበረ፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ቁርአኑ ከፈጣሪ ቃልነት ይልቅ በሰሚ ሰሚ ከመፅሀፍ ቅዱሱ የተገኙ እውቀቶች፣ ነብዩ "ገብሬል ተናገረኝ" በሚሉት ውሸት፣ የሰዎችና የመሀመድ ምክሮች፣ የሰዎች አስተያየቶች፣ የመሀመድ የግል ጉዳዮች፣ ተረቶች ... ጥርቅም መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም ቁርአንና ፈጣሪን የሚያገናኛቸው ነገር የለም፣ ቁርአኑ የሰዎች የአእምሮ ስራ ነው፣ ይህንንም እውነታ ቀጥሎ በምንመለከተው የቁርአኑን አምላካዊ ቃልነት በሚያፈርስ መልኩ በመሀመድ መስተካከሉ፣ ከእውነታ ጋርና እርስ በራሱ በመጋጨት ውጤቶች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

### 2.4.4. <u>አምላካዊ ቃልነቱን በሚያፈርስ መልኩ መስተካከሉ፣ ከእውነታና እርስ በራሱ መጋጨቱ</u>

ፈጣሪ ሁሉን አዋቂ በመሆኑ በሌላ ጊዜ ሌላ እውቀት ተገልጦለት የተናገረውን አይቀይርም፣ ቃሉም አይምታታበትምም አይዋሽምም ነገር ግን ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን በሚያሳይ መልኩ ለመሀመድ ስንፍና ሲከለስ፣ እርስ በርስ እንዲሁም ከእውነታ ጋር ሲጋጭ  እንመለከታለን፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፣

#### 2.4.4.1. <u>ለመሀመድ ስንፍናና ጥቅም ተብሎ በየጊዜው መከለሱ</u>

ነብዩ ከራሱ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በመጀመርያ “ቁርአን የአላህ ቃል ነው” ብሎ አስተምሮ አንዳንዶቹ ትዕዛዛት በተለይ ከሴት ጋር በተያያዘ ያወረደው ቃል ለራሱም ለመፈፀም ከብዶት ነበረ፣ ይህም ነብዩ ከነበረበት ሀብት፣ ዝና፣ ስልጣን ... ከፍ እያለ ሲመጣ በብዙ አማራጮች በመከበቡ ነው ነገር ግን ምን ችግር አለው በምትኩ ሌላ ቃል አወረደ፣

በመጀመሪያ 4፡3 “... ከሴቶች ለናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት ሶስት ሶስት አራት አራትም አግቡ፣ <u>አለማስተከከልን ብትፈሩ</u> አንዲትን ብቻ ወይንም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን ያዙ፡፡” አለ

ነብዩ ይህንን “አለማስተካከል ብትፈሩ” የሚለውን ህግ በመተላለፍ አይሻን ከሚስቶቹ ሁሉ አስበልጦ ስለሚወዳት(ሰሂህ ቡኻሪ 7፡65፡330) ቁርአኑን ተመልሶ አስተካካለው፣

> 33፡51 “ከእነርሱ የምትሻትን ታቆያለህ፡፡ የምትሻትን ወዳንተ ታስጠጋለህ፡፡ (በመፍታት) ካራቅሃትም የፈለግሃትን (በመመለስ ብታስጠጋ) <u>በአንተ ላይ ሀጢያት የለብህም</u>፡፡”

በመቀጠል ይህንን እስከ አራት የሚፈቅደውን ተላልፎ ሚስቶቹን ወደ ዘጠኝ(ሰሂህ ቡኻሪ 7፡62፡69) ከዚያም ወደ አሳደገ(ሰሂህ ቡኻሪ 1፡5፡268) ነገር ግን ይህ ድርጊቱ “ሀጢያት” እንዳይሆንበት ይህን ስንፍናውን ሽፋን የሚሰጠውና ከዚህ በላይ ገደብ ማለፍ እንደሌለበት የሚገልፅለትን ሌላ ቃል አወረደ፣

33፥52 "ከእነዚህ በኋላ እጅህ ከጨበጠቻቸው(ባሮች) <u>በስተቀር</u> ሴቶች ላንተ አይፈቀዱልህም፡፡ ከሚስቶችም መልካቸው ቢደንቅህም እንኳ እነርሱ ልታላውጥ (አይፈቀድልህም)፡፡"

የሚመጣው ስለማይታወቅም ነብዩ በሚስት ብዛት በቁጥር እንዳይገደብ ሌላም መከራከርያ ቃል አውርዷል፣

33፥50 "… የአመነች ሴት ነፍሷን(ራሷን) ለነብዩ ብትሰጥ ነብዩ ሊያገባት የፈለገ እንደሆነ <u>ከምዕመናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትሆን (ፈቀድንልህ)</u>፡፡

የሚገርመው ደግሞ "ማንም የጣለውን ሲያነሱበት አይወድም" እንደሚባለው አባባል ነብዩ ይህንን ሁሉ ሚስት ይዞ፣

33፥53 "… ሚስቶቹንም ከእርሱ በኋላ <u>ምን ጊዜም</u> ልታገቡ ለእናንተ አይገባችሁም፡፡ ይህ አላህ ዘንድ ከባድ ሀጢያት ነው፡፡"

ሲል እንመለከተዋለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ የሚወገዙትን ነገሮች ለሁሉም መፍቀድ ሲያቅተው ለራሱ ብቻ ለይቶ ቃል ሲያወርድ እንመለከተዋለን፣

33፥50 "አንተ ነቢዩ ሆይ እኛ እነዚያን … የአጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችንም ሴቶች ልጆች፣ የየውሽማህን ሴቶች ልጆች፣ የየሹሜህንም ሴቶች ልጆች (ማግባት) <u>ላንተ ፈቅደንልሀል</u>፡፡ የአመነች ሴት ነፍሷን(ራሷን) ለነብዩ ብትሰጥ ነብዩ ሊያገባት የፈለገ እንደሆነ <u>ከምዕመናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትሆን (ፈቀድንልህ)</u>፡፡

ነብዩ ቁርአኑን በየጊዜው እንደዚህ ማስተካከሉ ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል ሳይሆን የመሀመድ የአእምሮ ውጤት መሆኑን እንመለከታለን፣ በወቅቱ የነበሩት ሰዎችም መሀመድን "አንተ … በርግጥ እብድ ነህ" (37፥36, 44፥14, 15፥6) ሲሉት ነበረ፡፡

### 2.4.4.2. <u>ከእውነታ ጋር መጋጨቱ</u>

ፈጣሪ ሁሉን አዋቂና ቅዱስ በመሆኑ አይዋሽም ሁሉን አዋቂ ዘመን ተሻጋሪ እውነታን ይናገራል ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ "የፈጣሪ ቃል ነው" በተባለው ቁርአን ውስጥ ውሸቶችን እንመለከታለን፣ ለምሳሌ፣

1. <u>"የፀሃይ መግቢያና መውጫ ጉድጓድ መኖሩ"</u>

ቁርአን ስለ ፀሀይ መግቢያና መውጫ ሰፊ ትንታኔ ይሰጣል፣

18፡85-93 "መንገድን (ወደ ምዕራብ) ተከተለ፡፡ ወደ ፀሃይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት፡፡"

ይህንን ሳይንሱ ያልደረሰበትን ጉድጓድ ሀዲስ በዝርዝር ይገልፀዋል፣

ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡421 አቡ ዳር እንደተረከው፡ ነብዩ በፀሃይ መጥለቂያ ጊዜ "ፀሀይ ስትጠልቅ የት እንደምትሄድ ታውቃለህ" አለኝ እኔም "ይህን በደንብ የሚያውቁት አላህና ነቢዩ ናቸው" አልኩት፣ እሱም "የአላህ ዙፋን ስር ገብታ <u>እስከትተኛ</u> ትሄዳለች፣ ከዚያም እንደገና ለመውጣት ፍቃድ ትቀበላለች፣ ነገር ግን ተመልሳ መተኛት ትፈልጋለች ግን ትከለከላለች፣ በመጣችበት መንገድ መመለስም ትፈልጋለች ነገር ግን ትከለከላለች፣ በዚህም በተወሰነላት መንገድ ብቻ እንድትሄድ የአላህ ትዕዛዝ ነው፤" አለኝ፡፡

ይህንን ትርክት በድጋሚ ሌላም ቦታ ላይ እናገኛለን፣

ሳሂህ ሙስሊም 1፡297 አቡ ዳር እንደተረከው፡ ... የአላህ ዙፋን ስር ገብታ እስከትተኛ ትሄዳለች፣ ከዚያ ተነሺና ወደ መጣሺበት ቦታ ተመልሰሽና ውጪ ትባላለች ...

በሳይንስ ዕውቀቱ ከነብዩ መሀመድ ለሚበልጠው የዛሬው ሙስሊም ይህ ቃል ማፈሪያ ቃል ነው፡፡

2. <u>"ምድር "ሉል"(Sphere) ሳትሆን ጠፍጣፋ መሆኗ"</u>

<u>"ምድር የተዘረጋች ናት"</u>

- 13፡3 "እርሱ ያ ምድርን የዘረጋ..."
- 51፡48 "ምድርን ዘረጋናት፡፡"

ተመሳሳይ ሀሳቦችን 15፡19, 50፡7 ... ቦታዎች ላይ ቀርቧል፡፡

<u>"ተራራ ስለሚከልለን እንጂ ምድር ጠፍጣፋ ሜዳ ሆና ትታየን ነበረ"</u>

- 18፡47 "ተራራዎችን የምናስኬድበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ምድር ግልፅ ሆና ታያታለህ፡፡"

- 20፡105-107 “ከጋራዎችም ይጠይቁሃል፤ በላቸው “ጌታዬ መበተንን ይበትናቸዋል፡፡ (ምድርንም) ትክክል ሜዳ ሆና ይተዋታል፡፡”

“ምድር የተነጠፈ ምንጣፍ ትመስላለች”

- 71፡19 “አላህም ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ አደረጋት፡፡”
- 78፡6 “ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣"
- 20፡53 “(እርሱ) ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ ...”

በዚህም ቁርአኑ የምድርን ጠፍጣፋነት እርግጠኛ ሆኖ በተለያየ ቃላት ደጋግሞ ይነግረናል፣ ይህ ደግሞ ፈፅሞ ስህተት ነው፣ 51፡48 “ምድርን ዘረጋናት፡፡ ምን ያማርን ዘርጊዎች (ነን)” የሚለው የአላህ መመፃደቂያ ዛሬ መሬት ሉል(Sphere) መሆንዋን ለተገነዘበው ሙስሊም ማፈሪያ ነው፡፡ የሚገርመው ደግሞ ይህ የተሳሳተው የ“ምድር የጠፍጣፋነት” አስተምህሮ፣ ሌሎች እውነታዎችንም አዛብቶበታል፣ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 3. “መሬት እንዳትነቃነቅ በተራሮች መቸከልዋ”

ከላይ እንደተመለከትነው መሬት “ጠፍጣፋ” በመሆኗ እንዳታረገርግ አላህ በተራሮች ችካል እንዳዋቀራት ቁርአን ይናገራል፣

- 78፡6-7 “ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣ ጋራዎችን ችካሎች አላደረግንምን፣”
- 16፡15 “በምድር ውስጥ በናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለባት፤”
- 31፡10“... በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለ፡፡”

ይህንን ሀሳብ፣ ሀዲስ በዝርዝር ያስረዳናል፣

> ጃሚያ አት ቲርሚዲ 6፡44፡3369 “... አላህ መሬትን ሲፈጥር መንቀጠቀጥ ጀመረች፣ ስለዚህ ተራሮችን ፈጠረና “በላይዋ ላይ ሁኑ” አላቸው፣ ከዚያ መሬት ከመናወጥ ተረጋጋች፡፡”

“መሬት ከመናወጥ ተረጋጋች” ተብሎ የመሬት መንቀጥቀጥ ከየት እንደሚመጣ ቢነግሩን መልካም ነበረ ወይስ ችካሉን በደንብ አልቸከለም?

## 4. “ከሰማይ የወረደው ችካል”

ቁርአን ተራሮች በምድር ላይ ከላይ እንደተጣሉ ይናገራል(15፡19, 41፡9-10, 18፡47, 20፡105 ...) እንደዚህ ማድረግም ያስፈለገው ምድር እንዳታረገርግ በሚል እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡

ነገር ግን የተራሮች የድንጋይ ተፈጥሮን ስንመለከት ከሌላ ቦታ የተጣሉ፣ ለአከባቢው ልዩ በሆኑ ድንጋዮች የተዋቀሩ ሳይሆን አብዛኞቻቸው

በየአካባቢያቸው ካለው የመሬት ንጣፍ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በተፈጥሮአዊ ሂደት ከመሬት ውስጥ የወጡ ናቸው፣ ይህም "ከሰማይ የወረደ ችካል" አስተምህሮ ያፈርሳል፡፡

የሚገርመው ደግሞ ተራሮች ለዘላለም እንደቆሙ የነበሩና የሚኖሩ ሳይሆን በመሬት ውስጣዊና ዉጫዊ ሂደት አንዳንዶች በሂደት እየጠፉ ሌሎች ደግሞ በሂደት እየተፈጠሩ የሚሄዱ ናቸው፣ ለምሳሌ የሂማልያ ተራራ በአመት በአንድ ኢንች ያድጋል፡፡

5. ***"ምድር ጠፍጣፋ በመሆኗ ወርድና ስፋት አላት"***

57፡21 "ከጌታችሁ ወደ ኾነች ምሕረት፣ ወርዷ እንደ ሰማይና ምድር ወርድ ወደ ሆነች ገነት ተሽቀዳደሙ፡፡"

ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ ሰዎች ጠርዝዋን ለማየት በተሽቀዳደሙ ነበረ፣ መንግስታትም ሰዎችና እንስሳቱ ከጠርዝዋ እንዳይወድቁ በመሬት ጠርዝ ዙሪያ ትልቅ አጥር በሰሩ ነበረ፡፡

6. ***"ምድር ጠፍጣፋ በመሆኗ ምዕራብና ምስራቅ የሚባሉ ቋሚ ቦታዎች አሏት"***

55፡17 "የሁለቱ ምስራቆች ጌታ፤ የሁለቱ ምዕራቦችም ጌታ ነው፡፡"

መሬት ጠፍጣፋ ከሆች ይህ አባባል ትክክል ነው ነገር ግን መሬት ክብ በመሆንዋ ምዕራብ ወይ ምስራቅ የሚባል ቦታን ማግኘት አንችልም፣ እንፈልግ ብንልም መሬት ክብ በመሆኗ ስንዞር እንቀራለን እንጂ ይህንን ቦታ ፈፅሞ አናገኘውም፡፡

7. ***"መንገዶች የተሰሩት በአላህ ነው"***

43፡10 "(እርሱ) ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ በርስዋም ውስጥ ትመሩ ዘንድ ለእናንተ መንገዶችን ያደረገላችሁ ነው፡፡"

ፈጣሪ ሁሉን ነገር መስራት ይችላል ነገር ግን ፈጣሪ ሰዎች እንዲሰሩት የሰጣቸው ስራዎች አሉ፣ ከነዚህ ውስጥ አንዱ የመንገድ ስራ ነው፣ በዚህም መንገድ ሲሰራ ምናየው በሰው እንጂ በአላህ አይደለም፣ ፈጣሪ ቀድሞውኑ መንገዶች የሚሰራ ቢሆን ኖሮ ሰው የሌለበት ጫካዎችና በረሀዎች መንገድ በኖራቸውና የመንገዶች ባለስልጣን መስሪያ ቤት ባላስፈለገ ነበረ፡፡

8. ***"ሰማይ በጠንካራ ግንባታ የተሰራ መሆኑና ሽንቁር የሌለበት መሆኑ"***

መፅሃፍ ቅዱሱ ላይ ሰማይ የሚል ቃል አለ፣ ይህ ቃል ከመሬት ውጪ ያሉትን የተለያዩ ቀጠናዎችን ለማመልከት የሚጠቀመው ሀሳባዊ ቃል ነው፣ እነዚህም

- ወፎች የሚበሩበት ከባቢ አየር (ዘፍ.1፡20, ሐስ.11፡6)
- ከዋክብት ያሉበት ህዋ (ኢሳ.13፡10)
- ከቁሳዊው አለም ውጪ ያለው የመላዕክት መኖሪያ (1ነገ.8፡30, ማቴ.18፡10)
- ከዚያ በላይ ያለው መንበረ ፀባዖት (ማቴ.6፡9, ሮሜ.9፡29)

ነገር ግን ቁርአኑ "የመፅሃፍ ቅዱሱ አረጋጋጭ ነኝ" በማለት ይህንን ሰማይ በዝርዝር አስረዳለሁ ብሎ ብዙ ስህተት ሲያተራምስ እንመለከተዋለን፣ ስህተቱም የመጣው የቀደመው የጋርዮሽ ትውልድ ሰማይን በሚመለከትበት እይታ በመመልከት ነው፡፡

ቁርአን ሰማይ የቱ ጋር እንዳለ ሲናገር

- 71፡15-16 "አላህ ሰባት ሰማያት አንዱን ካንዱ በላይ ሲኾን እንዴት እንደ ፈጠረ አታዩምን፣ <u>በውስጣቸው ጨረቃን አብሪ አደረገ</u>፡፡"
- 37፡6 "እኛ ቅርቢቱን ሰማይ በከዋክብት ጌጥ አጌጥናት፡፡"

ከዚህም የምንረዳው የመጀመርያው ሰማይ በከዋክብቱ ተጊጦ ከጨረቃ በታች እንደሚገኝ ነው፣ ስለዚህ ሰማይ የተፃፉትን ነገሮች ስንመለከት፣

<u>"ሰማይ ሊታለፍ በማይቻል ግንባታ የተሰራ ነው"</u>

- 50፡6 "ወደ ሰማይ ከበላያቸው ስትሆን ለእርስዋ ምንም ቀዳዳዎች የሌሉአት ኾና እንዴት እንደገነባናትና (በከዋክብት)እንዳጌጥናት አልተመለከቱምን፡፡"
- 51፡47 "ሰማይንም በሃይል ገነባናት፡፡"
- 67፡3-5 "ያ ሰባት ሰማያትን የተነባበሩ ሆነው የፈጠረ ነው ... ከስንጥቆቹ አንዳች ታያለህን፣ ከዚያም ብዙ ጊዜ አይንህን መላልስ፡፡ አይንህ ተዋርዶ እሱም የደከመ ሆኖ ወዳንተ ይመለሳል፡፡"

<u>"የሰማይ ግንባታ ሊሰበር፣ ሊቀደድ፣ሊሰባበርና ሊወድቅ የሚችል ቁስ ነው"</u>

- 34፡9"... በእነርሱ ላይ ከሰማይ ቁራጭን እንጥልባቸዋለን..."
- 81፡11 "ሰማይም በተገሸጠች ጊዜ፤"
- 84፡1 "ሰማይ በተቀደደች ጊዜ፤"
- 42፡5 "(ከአላህ ፍራቻ) ሰማያት ከበላያቸው ሊቀደዱ ይቀርባሉ፡፡"
- 25፡25 "ሰማይም በደመና የምትቀደድበትን ... ቀን (አስታውስ)፡፡"
- 82፡1 "ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ፤"
- 73፡18 "ሰማዩ በርሱ (በዚያ ቀን) ተሰንጣቂ ነው፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጨረቃ የተጓዙት ሳይንቲስቶች ቁርአንን አንብበው ቢሆን ኖሮ ጉድ ሆነን ነበረ፣ ዛሬ ሳይንቲስቶች በቴሌስኮፓቸው ከጨረቃ አልፈው ዩኒቨርሱን መመርመር መጀመራቸውና ከጨረቃም አልፈው ሌሎች ፕላኔቶች ድረስ መንኮራኩር ማምጠቅ መቻላቸውን ስንመለከት የቁርአኑ የግንባታ ታሪክ ውሸት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

9. <u>“ሰው የሚኖረው ዳስ በሚመስል አለም ውስጥ ነው”</u>

እንደ ቁርአኑ አሁን ያለው የሰው መኖሪያ ቦታ ከላይ እንደኮርኒስ በተዘረጋ ሰማይ ከታች ተራሮች እንደ ቋሚ እንጨት ጣል ጣል በተደረገባት እንደ ምንጣፍ በተዘረጋች ምድር ላይ ሲሆን ከርቀት ለተመለከታት ምድር የዳስ መልክ ያላት መኖርያ ናት፡፡

<u>“የሰማይ ጣርያነት”</u>

- 40፡64 “… (አላህ) ሰማይን ጣርያ ያደረገላችሁ ነው፡፡”
- 21፡32 “ሰማይንም (ከመውደቅ) የተጠበቀ ጣራ አደረግን፡፡”

<u>“የምድር ምንጣፍነት”</u>

- 71፡19 “አላህም ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ አደረጋት፡፡”
- 78፡6 “ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣"
- 20፡53 “(እርሱ) ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ …”

<u>“ተራሮች እንደ ቋሚ እንጨት በምድር ላይ መቸከላቸው”</u>

- 78፡6-7 “ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣ ጋራዎችን ችካሎች አላደረግንምን፣”
- 16፡15 “በምድርውስጥ በናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለባት፤”
- 31፡10 “… በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለ፡፡”
- 88፡17-19 “(ከሃዲዎች) አይመለከቱምን … ወደ ተራራዎች እንዴት እንደ ተቸከሉ፡፡”

<u>የዳሱ ምስል</u>

- 2፡22 “(እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ሰማይን ጣሪያ ያደረገው …”
- 55፡33 “የጋኔንና የሰው ጭፍሮች ሆይ! <u>ከሰማያትና ከምድር ቀበሌዎች</u> መውጣት ብትችሉ ውጡ፡፡ በስልጣን እንጂ አትወጡም፡፡ (ግን ስልጣን የላችሁም)፡፡”
- 32፡4 “አላህ ሰማያትንና ምድርን <u>በመካከላቸውም ያለውን</u> በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ከዚያም በአርሹ ላይ(ስልጣኑ) የተደላደለ ነው፡፡”

ከነዚህ ቃላት የዳሱን ምስል መመልከት ይቻላል፣ ከላይ የሰማይ ጣርያ፣ ከስር አልፎ አልፎ ተራራ እንደ ቋሚ እንጨት ጣል ጣል የተደረገባት የተነጠፈች ምድር ፣ ይህ ጥንታዊው የጋርዮሽ ዘመን የነበረው ህዝብ ሰማይና ምድርን የሚመለከትበት እይታ እንጂ እውነታ አይደለም፡፡

10. <u>"ዩኒቨርስ የተደራረበ 14 አንባሻ የምትመስል መሆኑ"</u>

ቁርአን መሬትን ጨምሮ ዩኒቨርስ የሚባለውን የአጠቃላይ የሰማያትን ምስል ይነግረናል፣

- 65፡12 "አላህ ያ ሰባት ሰማያት የፈጠረ ነው፡፡ ከምድርም መሰላቸውን (ፈጥሮአል)፡፡"

  ተመሳሳይ ሀሳብ ሳሂህ ቡሃሪ 3፡43፡634, 4፡54፡418 ... ላይም ቀርቧል

- 71፡15-16 "አላህ ሰባት ሰማያት አንዱን ካንዱ በላይ ሲኾን እንዴት እንደ ፈጠረ አታዩምን፣ በውስጣቸው ጨረቃን አብሪ አደረገ፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡418 "ቁራጭ መሬት ያለአግባብ የሚወስድ ሰው፣ በትንሳኤ ቀን ሰባት መሬቶች ድረስ ይሰምጣል፡፡"

በዚህም በቁርአኑ ቴልስኮፕ ዩኒቨርሳችንን ስንመለከት፣ ከላይ ያየነው የዳስ ምስሉ ላይ ወደላይና ወደታች ስድስት ስድስት ሰማያትንና ምድራትን በመጨመር፣ ልክ በመካከላቸው ክፍተት ኖሯቸው የተደረደሩ 14 አምባሻዎች ምስል ነው፡፡

አንዳንድ ሙስሊሞች ይህንን "ሰባት ሰማያት" የሚለውን "ስለ ፕላኔቶች ነው" የተፃፈው በማለት ቁርአኑን እውነተኛነት ለማሳየት ይጥራሉ ነገር ግን "ሰባት መሬት ድረስ ይሰምጣል" ማለት አንዱ ባንዱ ላይ ማለት እንጂ እንደ ፕላኔቶች አጠገብ ለአጠገብ ያለ ሁኔታን አያሳይም፣ ፕላኔቶችም ሰባት ሳይሆኑ በዚህ ሶላር ሲስተማችን ውስጥ ብቻ ስምንት መደበኛ ፕላኔቶችና አራት ድንክ ፕላኔቶች ናቸው ያሉት፣ በሌሎቹ ሶላር ሲስተሞች ያሉት ደግሞ በሺዎች የሚቆጠሩ ፕላኔቶች ናቸው፣ ውሸትን ውሸት ማለት ሲገባቸው ወደ እውነት በማጠጋጋት እውነት ለማስመሰል መልፋቱ ስህተት ነው፡፡

11. <u>የተቀያየረው እውነታ "ጨረቃ አብሪ ፀሃይ አንፀባራቂ"</u>

እንደሚታወቀው ፀሀይ ቋሚ የብርሀን ምንጭ ናት፣ ጨረቃ ደግሞ ከፀሀይ ተቀብላ ታንፀባርቃለች ነገር ግን ቁርአኑ የሁለቱን አሰራር አቀያይሯል፣

- 25፡16 "ያ በሰማይ ቡርጆችን ያደረገና በእርስዋም አንፀባራቂ(ፀሀይ) አብሪ ጨረቃንም ያደረገ ጌታ ክብሩ በጣም ላቀ፡፡"

- 10፡5 “እርሱ ያ ፀሃይን አንፀባራቂ ጨረቃንም አብሪ ያደረገው ነው፡፡”

እውነታው ግን ፀሀይ አብሪ ጨረቃ ደግሞ አንፀባራቂ ናት፡፡

12. <u>“የፀሀይና ጨረቃ የማይዛነፍ ተራ”</u>

ቁርአን ፀሀይና ጨረቃ ተራ እንዳላቸው ይነግረናል፣

- 36፡40 “ፀሀይ ጨረቃን ልትደርስባት አይገባትም፡፡ ሌሊትም ቀንን (ያለጊዜው) ቀዳሚ አይሆንም፡፡ ሁሉም በመዞሪያቸው ውስጥ ይዋኛሉ፡፡”
- 31፡29 “አላህ ለሊትን በቀን ውስጥ የሚያስገባ፣ ቀንንም በለሊት ውስጥ የሚያስገባ፣ ፀሃይንና ጨረቃንም የገራ መሆኑን አታይምን፣”

ጨረቃ መሬትን ስትዞር መሬት ደግሞ ፀሀይን ትዞራለች፣ በዚህም ፀሃይና ጨረቃ የእርስ በርስ አንፃራዊ እንቅስቃሴ የላቸውም፣ ሁለቱም በአንዴ የሚወጡበትና በአንዴው የሚጠፉበት አንዳንዴም ትይዩ ሆነው ለመሬት ግርዶሽ የሚፈጥሩበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በዚህም በመካከላቸው ምንም አንፃራዊ የእንቅስቃሴ ህግ የለም፣ ስለዚህ የቁርአን “የፀሀይና የጨረቃን የማይዛነፍ ተራ” አስተምህሮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

13. <u>“ፀሃይ ድቡልቡል(Sphere) ሳትሆን ሰማዩ ላይ የተለጠፈች ክብ ነገር መሆንዋ”</u>

ይህንን ሀሳብ ቁርአኑ ሲናገር፣

81፡1 “ፀሀይ በተጠቀለለች ጊዜ፣” ይላል፣ ይህንን ሀሳብ ሀዲሱ ሰፋ አድርጎ ይገልፅልናል፣ ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡422 “… በትንሳኤ ቀን ፀሃይና ጨረቃ እጥፍጥፍ(folded) ይደረጋሉ፡፡”፣

ይህ ጋርዮሹ ማህበረሰብ መሬት ላይ ሆኖ በአይኑ የሚመለከታት ፀሀይ ምስል እንጂ እውነታ አይደለም፣ ሳይንሱ ፀሀይ ጠጣር ነገር ሳትሆን በሀይድሮጂንና ሂሊየም ጋዞች የተሰራች እንደ መሬት ሉል (Sphere) እንደሆነች ይናገራል፡፡

14. <u>“ከፀሃይና ጨረቃ ውጪ ያሉትን የብርሀን አካላትን እንደ ጌጥ አሳንሶ መመልከት”</u>

ከመሬት ስንመለከት ከፀሀይና ጨረቃ ውጪ ያሉት የብርሀን አካላት ሰማዩን ያሳመሩ ጌጦች ይመስላሉ፣

- 41፡12 “… ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን፡፡”
- 15፡16 “… (ሰማይን) ለተመልካቾችም (በከዋክብት) አጊጠናታል፡፡”

ነገር ግን እነዚህ ከርቀት የምንመለከታቸ ከዋክብቶች አንዳንዶቹ መሬትን፣ ፀሀይንና ጨረቃን የሚበልጡ ናቸው፣ አንዳንዶቹ መካከል ያለው ርቀት መሬትና ጨረቃ መካከል ካለው ርቀት እጅጉን ይበልጣል፣ በዚህም የቁርአኑ ቃል ከእውነታው ምን ያህል እንደራቀ እንመለከታለን፡፡

**15. <u>“ከዋክብት ሰማይ ውስጥ ይገባሉ”</u>**

56፡75-76 “በከዋክብትም መጥለቂያዎች እምላለሁ፡፡ እርሱ ብታውቁ ታላቅ መሃላ ነው፡፡”

“እርሱን ብታውቁ” ብሏል ነገር ግን ይህንን ያላወቀው¡ ሳይንስ ከዋክብት “መጥለቂያ የላቸውም፣ የፀሃይ ብርሃን ሲደምቅ የእነሱ ድምቀት ስለሚጠፋ የጠለቁ ይመስለናል” ይለናል፡፡

**16. <u>“ከዋክብት ሰማይ ላይ የሚሄዱበት መንገድ አላቸው”</u>**

ቁርአን ሰማይ ጠጣር ግንባታ አድርጎ በመነሳቱ የሚንቀሳቀሱት ከዋክብት የራሳቸው መንገድ እንዳላቸው ይናገራል

51፡7 “የ(ከዋክብት) መንገዶች ባለቤት በኾነችው ሰማይ እምላለሁ፡፡” ይህ እውነት የሚሆነው “የሰማይ ግንባታ ፅንሰ ሀሳብ” ባይፈርስብን ነበረ ነገር ግን እሱ ስለፈረሰ መሄጃ መንገድ ይቅርና ጥርጊያ መንገድ እንኳን የለም፡፡

**17. <u>“ዝናብና በረዶ የሚመጣው ከሰማይ ውስጥ መሆኑ”</u>**

ከላይ እንደተመለከትነው ቁርአኑ “ሰማይ ማለት በከዋክብት የተጌጠ፣ ጠጣርና ሽንቁር የሌለበት አካል” መሆኑን ነግሮን ነበረ ነገር ግን እዚህ ጋር ተመልሶ ደግሞ፣

- 24፡43 “… ከሰማይም በውስጧ ካሉት ጋራዎች በረዶን ያወርዳል፡፡”
- 16፡65 “አላህም ከሰማይ ውሃን አወረደ፡፡”
- 43፡11 “ያም ከሰማይ ውሃን በልክ ያወረደላችሁ ነው፡፡”

ችግር የለውም “ለነዚህ መውረጃ የተዘጋጁ ቀዳዳዎች ሊኖሩ ይችላሉ” ብለን እንለፍ ነገር ግን ይህ “ከሰማይ ውስጥ የሚፈስ ውሃ ፅንሰ ሀሳብ “የውሃ ኡደትን” በማያውቁ የጋርዮሽ ሰዎች አስተሳሰብ እንጂ እውነታ አይደለም፡፡

**18. <u>“ደመና የሚነዳበት እሳት”</u>**

ጃሚያ አት ቲርሚዲ 3117 “ከመላዕክት መሃከል ለደመናት ተጠያቂ የሆነው መልአክ ደመናትን የሚነዳበት ትንሽ እሳት አለው … የነጎድጋድ ድምፁም የሚወጣው መልአኩ ደመናውን ለመንዳት በሚመታው ግዜ ነው …”

የበጋውን ደመና የሚነዳው መልአክ የእሳት መግረፊያ ስለሌለው ይሆን ሲነዳ ድምፁ የማይሰማው?

**19. <u>“በልጅ ውስጥ የእናት የዘር ተዋፅዖ የለም”</u>**

ቁርአን የሰው ልጅ የሚፈጠረው ከወንድ ዘር ብቻ እንደሆነና ሴት፣ ልክ መሬት ውስጥ ዘር ተዘርቶ መሬት ዘሩን እንደምታበቅለው፣ ከወንድ የመጣውን ዘር ማብቀያ ስፍራ እንደሆነች ይነግረናል፣

<u>“ዘር ከወንድ ብቻ መሆኑ”</u>

- 53፡46 “ከፍትወት ጠብታ (በማህፀን ውስጥ) <u>በምትፈስስ ጊዜ</u>፡፡”
- 86፡5-7 “ሰውም ከምን እንደ ተፈጠረ ይመልከት፡፡ ከተስፈንጣሪ ውሃ ተፈጠረ፡፡ ከጀርባና ከእርግብግብቶች መካከል የሚወጣ ከኾነ (ውሃ)፡፡”
- 80፡17-19 “... ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው፤ መጠነውም፡፡”
- 30፡54 “አላህ ያ ከደካማ(ፍትወት ጠብታ) የፈጠራችሁ ነው፡፡ ከዚያ ደካማነት በኋላ ሀይልን አደረገ፡፡”

ተመሳሳይ ሀሳቦችም 16፡4, 36፡77 ... ቦታዎች ላይ እንመለከታለን

<u>“ዘር መሬት ውስጥ እንደሚዘራና እንደሚበቅል የሰውም ዘር ከወንድ ወጥቶ በሴት ውስጥ የሚያድግ መሆኑ”</u>

- 2፡223 “ሴቶቻችሁ ለእናንተ እርሻ ናቸው፡፡ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኹነታ ድረሱ ...”
- 4፡4 “ሴቶችም መህሮ<u>ቻቸውን</u> በደስታ ስጡ፡፡”
- 21፡77 “በተጠበቀ መርጊያ ውስጥም (በማህፀን) አደረግነው፡፡”
- 23፡12-14 “በርግጥ ሰውን ... በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፡፡”

ነገር ግን ሴቶች ዘር የሚበቅልበት “የተጠበቀ መርጊያ” ቦታ ብቻ ሳይሆኑ እነሱም በልጆቻቸው ውስጥ ከወንዱ እኩል የራሳቸው የዘር አስትዋፅዖ አላቸው፣ ሴቶች የዘር አስትዋፅዖ ባይኖር ኖሮ እናቱን/እናቷን የሚመስል/የምትመስል ልጅ ባልኖረ/ች ነበረ፡፡

**20. <u>“የሰው ልጅ በማህፀን ውስጥ የረጋ ደም ከዚያ ቁራጭ ስጋ ነበረ“</u>**

23፡13-14 “... የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፡፡”

ሀዲስ ይህንን ሀሳብ ዘርዘር አድርጎ ያስረዳናል፣

ሰሂህ ቡኻሪ 4፡55፡549 "... ሁላችንም ስንፈጠር በናታችን ሆድ ውስጥ ለመጀመሪያው 40 ቀናት እንሰበሰባለን፣ በቀጣይ አርባ ቀናት ደግሞ የረጋ ደም እንሆናለን፣ ቀጥሎ ባሉት 40 ቀናት ደግሞ ቁራጭ ስጋ ..."

እንደዚህ አይነት የፅንስ የእድገት ደረጃ የለም፣ የሰው ልጅ ከተፀነሰበት ጊዜ አንስቶ ይብዛም ይነስም እንጂ አካል፣ ህይወት፣ ቅርፅ ... ያለው እንጂ የረጋ ደም፣ ቁራጭ ስጋ የሚሆንበት የፅንስ እድገት ደረጃ የለም፡፡

**21. <u>"የሰው ልጅ ህይወት የሚፈጠርበት አጥንት ካበቀለ ከ120 ቀናት በኋላ ነው"</u>**

23፡12-14 "በርግጥ ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፡፡ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፡፡ ቁራጭዋም ስጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፡፡ አጥንቶቹንም ስጋ አለበስናቸው፡፡ <u>ከዚያም</u> (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረት አድርገን አስገኘነው፡፡"

ይህንን ሀሳብ ሀዲስ ሰፋ አድርጎ ያቀርበዋል፣

ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡549፣ "... ሰው በናቱ ማህፀን ውስጥ (ከ120 ቀናት በኋላ) አላህ አራት ነገር እንዲፅፍ መልአክ ይልካል እነሱም፣ የሚሰራውን ስራዎቹን፣ የሚሞትበትን ቀን፣ የሚኖርበትን አኗኗርና በህይማኖቱ የተባረከ ይሁን የተረገመ ይሁን ይፅፋል፣ ከዚያ ነፍስን ወደ ፅንሱ ያስገባል ..."

ነገር ግን ህይወት የሚገኘው በመጀመርያው ቀን እንጂ አጥንት ካወጣ በኋላ አይደለም፣ ፅንስ ይቅርና እያንዳንድዋ የወንድ እስፐርም ሴል እንዲሁም የሴቷ እንቁላል እራሳቸው ህይወት አላቸው፡፡

**22. <u>"የህፃን ፆታ የሚወሰነው አካሉ ከተሰራ በኋላ ነው"</u>**

75፡36-39 "ሰው ስድ ሆኖ መትተውን ይጠረጥራልን፣ የሚፈስስ የኾነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን፣ ከዚያ የረጋ ደም ሆነ (አላህ ሰው አድርጎ) ፈጠረውም፡፡ አስተካከለውም፡፡ <u>ከእርሱም</u> ሁለት አይነቶችን ወንድና ሴት አደረገ፡፡"

ይህንን ሀሳብ ሀዲስ ተንትኖ ያስረዳል፣

ሰሂህ ሙስሊም 33፡6397 እና ሰሂህ ቡኻሪ 8፡77፡594 "... አላህ ለፅንስ ጥበቃ መልአክ ይመድባል፣ እሱም፣ አምላኬ አሁን የዘር ጠብታ ነው፣ አምላኬ አሁን የረጋ ደም ነው፣ አምላኬ አሁን ስጋ ሆኖአል ይላል፣ ከዚያ አላህ የመጨረሻውን ቅርፅ ሊሰጠው ሲወስን፣ መልአኩም ወንድ ነው ሴት ይሁን፣ ጥሩ ወይስ መጥፎ ሰው ይሁን ... ብሎ ይጠይቃል ..."

ፆታ የሚወሰነው በእርግዝና ጊዜ የወንዱና የሴቷ ዘር በሚገናኝበት ጊዜ በሚፈጠረው የዘረመል ጥምርታ እንጂ ከቆይታ በኋላ አይደለም፡፡

**23. <u>"በፅንስ ውስጥ ያለውን ማንም አያውቅም"</u>**

ሰሂህ ቡኻሪ 2፡17፡149 "... በፅንስ ውስጥ ያለውን ማንም ሊያውቅ አይችልም..."

ይህ ቃል የትክክለኛው ፈጣሪ ቃል ባለመሆኑ ዛሬ በአልትራሳዎንድና በመሳሰሉት ቴክኖሎጂ በፅንስ ውስጥ ያለው ነገር ማወቅ ይቻላል፡፡

**24. <u>"አንድ ሙስሊም አስር ያልሰለሙ ሰዎችን ያሸንፋል"</u>**

2፡65 ወይም 8፡65 "አንተ ነቢዩ ሆይ! ምእመናንን በመዋጋት አደፋፍራቸው፡፡ ከእናንተ ውስጥ ሀያ ታጋሾች ቢኖሩ ሁለት መቶን ያሸንፋሉ፡፡ ከእናንተ መቶ ቢኖሩ ከእነዚያ ከካዱት እነሱ የማያውቁ ህዝቦች ስለሆኑ ሺህን ያሸንፋሉ፡፡"

ቴኳንዶ ቤት ሙስሊሞች የሚበዙት ይህ የቁርአኑ ስሌት አልመጣ ብሎአቸው ይሆን እንዴ?

**25. <u>"ሙስሊም በአንድ አንጀቱ ሲመገብ ሙስሊም ያልሆነ ሰው በሰባት አንጀቱ ይመገባል"</u>**

- ሰሂህ ሙስሊም 23፡5113 "ሙስሊም ያልሆነ ሰው በሰባት አንጀት ይበላል ሙስሊሙ ግን የበሚላው በአንድ አንጀቱ ነው፡፡"

  ይህ ሃሳብ በተደጋጋሚ እስከ 23፡5118 ድረስ ተብራርቷል፣
- ሰሂህ ሙስሊም 23፡5120 "... አማኝ በአንድ አንጀቱ ሲጠጣ ያላመኑት በሰባት አንጀት ይጠጣሉ፡፡"

እዚህ ጋር ሙስሊም የህክምና ባለሙያዎች ብታስረዱን መልካም ነው፣ ቁርአኑ እውነት ወይ ውሸት ነው የሚናገረው? ሰው ሲሰልም ስድስቱ አንጀትስ የት ይገባል?

**26. <u>"ሰው የሚያስበው በደረቱ ነው"</u>**

- 6፡125 “አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን ለኢስላም ይከፍታል፡፡ ሊያጠመው የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ችጋራ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል፡፡”
- 3፡29 “በደረቶቻችሁ ውስጥ ያለውን ብትደብቁ ወይም ብትገልፁት አላህ ያውቀዋል፡፡”
- 39፡22 “አላህ ደረቱን ለእስልምና ያስፋለትና ...”

ደረት ማሰቢያ አካል አይደለም፣ ይህንን ስህተት የወለደው፣ “ሰው የሚያስበው በልቡ ነው” የሚለውን ተለምዶአዊ አነጋገርን በስፋት ለማብራራት በመሞከር ነው፣ ሰው የሚያስበው በአእምሮው እንጂ በደረቱ አይደለም፣ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ቀጫጭን ሰዎች ጉድ ሆነው ነበረ፡፡

**27. “<u>የአማኞች መቃብር ይሰፋል የትምክህተኞች በአንድ ላይ ይጨመቃል</u>”**

ጃሚያ አት ቲረሚዲ 1071 “... የአማኝ መቃብር ሰባ በሰባ ድረስ ይለጠጣል ብርሃናማም ይደረጋል ... ትምክህተኛ የነበረ ሰው መቃብር ግን በአንድ ላይ ይጨመቃል፣ የጎድን አጥንቶቹ እስኪጣበቁ ድረስ ይጨፈለቃል ...”

ምንም እንኳዋን ጉዳዩ ስለ ድህረ ሞት ቢሆንም ተመልሶ በአካባቢያችን ስለምንመለከተው መቃብር በመሆኑ እውነታውን በቀላሉ ማወቅ እንችላለን፣ በዚህም ሁሉም መቃብሮች ከተሰሩበት ስፋት ሲያንሱ፣ ሲሰፉ፣ መብራት ሲገባላቸው ... አልተመለከትንም፡፡

**28. “<u>ማፋሸግ ከሰይጣን ነው</u>”**

በእስልምና ማፋሸግ የተከለከለ ነው፣ ምክንያቱም፣

- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡509 “ማፋሸግ ከሰይጣን ነው፡፡”
- ሰሂህ ቡኻሪ 8፡73፡.245 “አላህ ማንጠስ ወደደ፣ ማፋሸግ ግን ጠላ ... ማፋሸግ ከሰይጣን ነው፣ ቶሎ አቋርጡ፣ ሰይጣን ይስቅባችኋል፡፡”
- ሰሂህ ሙስሊም 42፡7130 “... ስታፋሽጉ ሰይጣን እንዳይገባ በእጃችሁ አቃርጡ፡፡”

ሰው የሚያፋሽገው ሰውነቱ እረፍት፣ እንቅልፍና የለመደው ማነቃቂያ በሚፈልግበት ጊዜ እንጂ በሰይጣን አይደለም፣ ሰውየው ሰውነቱ የፈለገውን ነገር ሲያገኝ ማፋሸጉን ያቆማል፡፡

**29. “<u>የውሃ ብክለት የሚባል ነገር የለም</u>”**

ሱናን አቡ ዳውድ 66፣ የሆነ ሰው መጥቶ የአላህን መልዕክተኛን “ቡዳህ ከሚባለውና የሞቱ ውሾች፣ የወር አበባ ጨርቆጭና ቆሻሻ ከሚጣልበት የውሃ

ጉድጓድ ውሃ ቀድተን መታጠብ እንችላለን?" ብሎ ጠየቀ፣ የአላህ መልዕክተኛም "በርግጥ ውሃ ንፁህ ነው፣ ምንም ነገር እሱን አያቆሽሽም አሉ፡፡"

30. **"ተላላፊ በሽታ የሚባል ነገር የለም"**

ሰሂህ ሙስሊም 26፡5508 "... ተላላፊ በሽታ የሚባል ነገር የለም፡፡"
ተመሳሳይ ሀሳብም ጃሚ አል ቲርሚዲ 2143 ላይ እንመለከታለን፡፡

31. **"የሰውነት ማተኮስ ከሲኦል ሙቀት ነው"**

ሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡621 "... ትኩሳት ከሲኦል ሙቀት ስለሆነ ትኩሳቱን በውሃ አጥፉት፡፡"
የዚህን ተመሳሳይ ሃሳብ በተጨማሪ በሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡619 - 7፡71፡622፣ ተብራርቷል፡፡

ትኩሳቱ ከሲኦል ሙቀት ከሆነ ለምን ታማሚ ብቻ ከሌላው ሰው ተለይቶ ያተኩሰዋል?፣ ከሲኦል ትይይዩ ስለተቀመጠ ይሆን? እንደዚያ ከሆነ ከውሀው ይልቅ የሚሻለው ቦታውን መቀየር ነው፡፡

32. **"የቀትር ወበቅ መነሻው የሲኦል ሙቀት ነው"**

ሰሂህ ቡኻሪ 1፡10፡513 "ዙሁር የምትሰግዱት ወበቁ ቀዝቀዝ ሲል ነው፣ ወበቁ የሚመጣው ከሲኦል እሳት ነው፡፡"

ወበቅ የሚመጣው ከፀሀይ እንጂ ከሲኦል እሳት አይደለም፣ ታድያ ፀሀይ ስትጠፋ ወበቅ ለምን አይኖርም?

33. **"የዝንብ ክንፍ መድሃኒት ይዟል"**

ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡537 "አንዳችሁ በምትጠጡት ውስጥ ዝንብ ቢገባባችሁ፣ በመጠጡ ውስጥ ንከሩት፣ አንዱ ክንፉ በሽታ እንደያዘው ሌለኛው ክንፉ ደግሞ ለበሽታው መድሃኒት ይይዛል፡፡"

34. **"ጥቁር አዝሙድ ሁሉንም በሽታ ይፈውሳል"**

ሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡592 "ጥቁር አዝሙድ ከሞት በስተቀር ሁሉንም በሽታ ይፈውሳል፡፡"

መቼም ከዚህ በኋላ ለህክምና ወጪ አናወጣም እንደማትሉ ተስፋ አደርጋለሁ¡

35. **"የግመል ሽንት ከበሽታ ይፈውሳል"**

ሰሂህ ቡኻሪ 8፡82፡796 "... ነቢዩም እንደነገሩዋቸው ... ሄደው የግመሎችን ወተትና ሽንት ለመድሃኒትነት ጠጡ ከዚያ ጤናማና ወፍራም ሆኑ፡፡"

የዚህን ተመሳሳይ ሃሳብ ሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡590 እና ሰሂህ ሙስሊም 16፡4130 ላይ እንመለከታለን፡፡

ሃሳቡ ትክክል ቢሆን ኖሮ ዛሬ የግመል ሽንት እየታሸገ በተሸጠልን ነበረ ነገር ግን አልሆነም ሌላው ማህበረሰብ ይቅርና ሙስሊሙ ማህበረሰብም እንኳ ዛሬ ይህንን የቁርአን ቃል አይሰማም፡፡

እነዚህ ከላይ ከተራ ቁጥር 29 ጀምሮ የምንመለከታቸው የእስልምና የጤና አስተምህሮቶች የተሳሳቱ ይባሱኑ አንዳንዶቹ በሽታን የሚፈጥሩ ናቸው፣ "ቦኮ ሀራም"ን ጨምሮ ብዙ አሸባሪ ቡድኖች ዘመናዊውን ህክምናን የሚቃወሙት ይህ እስላማዊው የህክምና ዘዴ "በቂ ነው" በማለት ነው፡፡

**36. <u>"መብረቅ ከሃዲዎችን ለመቅጣት ነው የሚወርደው"</u>**

13፡13 "ነጎድጓድ ... እነርሱም (ከሃዲዎች) በአላህ የሚከራከሩ ሲሆኑ በእርስዋ የሚሻውን ይመታል፡፡ እርሱም ሀይለ ብርቱ ነው፡፡"

ተመሳሳይ ሀሳብ ጃሚ አል ቲርሚዲ 5፡44፡3117 ላይም እንመለከታለን፣ ነገር ግን ከሃዲዎች በክረምት እንጂ በበጋ የሉም እንዴ?

**37. <u>"የፀሃይ ግርዶሽ የሚከሰተው አላህ አማኞችን ለማስፈራራት ነው"</u>**

ሰሂህ ቡኻሪ 2፡18፡158፣ "ፀሃይና ጨረቃ ግርዶሽ የሚፈጥሩት ... አላህ አማኞችን ሊያስፈራራበት ነው፡፡"

የፀሀይ ግርዶሽ የተፈጥሮ ሂደት በመሆኑ እንዴትና መቼ እንደሚከሰት ይታወቃል፣ በዚህም ለዚህ ትውልድ ይህንን ክስተት "የአላህ ማስፈራሪያ" ነው ማለት አስቂኝ ነው፡፡

**38. <u>"ተወርዋሪ ኮከቦች የሰይጣን መቀጣጫ ናቸው"</u>**

- 37፡6-10 "እኛ ቅርቢቱን ሰማይ በከዋክብት ጌጥ አጌጥናት፡፡ አመፀኛም ከሆነ ሰይጣን ሁሉ መጠበቅን ጠበቅናት፡፡ ወደ ላይኛው ሰማይ አያዳምጡም፡፡ ከየወገኑም ሁሉ ችቦ ይጣልባቸዋል፡፡ የሚባረሩ ሲሆኑ(ይጣልባቸዋል)፡፡ ለእነሱም ዘውታሪ ቅጣት አለባቸው፡፡ ንጥቂያ የነጠቀ ወዲያውም አብሪ ኮከብ የተከተለው ሲቀር፤"
- 72፡8-10 "(ጂኒዎችም) እኛ ሰማያትን (ለመድረስ) ፈለግን፡፡ ብርቱ ጠባቂዎችንና ችቦዎችንም ተሞልታ አገኘናት፡፡ ወደ እርስዋም (ወሬን) ለማዳመጥ በመቀመጫዎች እንቀመጥ ነበር፡፡ አሁን ግን የሚያዳምጥ ሰው ለእርሱ ተጠባባቂ ችቦን ያገኛል፡፡"

- 67፡5 "ቅርቢቱን ሰማይም በእርግጥ በመብራቶች (በከዋክብት) አጌጥናት፡፡ ለሰይጣንም መቀጣጫዎች አደረግናት፡፡ ለእነርሱም (ለሰይጣኖች) የእሳት ቅጣት አዘጋጀን፡፡"

ተመሳሳይ ሃሳብም ሀዲስ ሰሂህ ሙስሊም 26፡5538 ላይ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ የተመለከትነው "የሰማይ ግንብነት ፅንሰ ሀሳብ" ስለፈረሰ ሰይጣናቱ ተጠግተው የሚያዳምጡት ጣርያም የለም፡፡

**39. <u>"ጥቁር ውሻ ሰይጣን ነው"</u>**

ሰሂህ ሙስሊም 4፡1032 - አቡ ዳር እንደዘገቡት፡ የአላህ መልዕክተኛ "... ፀሎት የሚቋረጠው በፈስ፣ በሴትና ጥቁር ውሻ ማለፍ ነው" ... ጥቁር ውሻ ደግሞ ከሌሎቹ አይነት ውሾች በምን ይለያል አልኩት እሱም "ጥቁር ውሻ ሰይጣን ነው" አለኝ፡፡"

ከመላሹ በላይ ተንኮለኛው ጠያቂው ነው፣ የጥቁር ውሻ ፊት እንደሚስፈራ እያወቀ¡¡

**40. <u>"ሰይጣን የወደቀ ምግብ ይበላል"</u>**

ሰሂህ ሙስሊም 23፡5043 እና 23፡5044 "(ከተመገባችሁ በኋላ) ጣታችሁንና ሳህናችሁን ላሱ ምክንያቱም በረከታችሁ የቱ ጋር እንዳለ አታውቁመምና፣ ልትጎርሱት ያላችሁት ከእጃችሁ ቢወድቅ አንስታችሁ ቆሻሻውን ጠርጋችሁ ብሉት፣ ለሰይጣን ልትተውት አይገባምና፡፡"

እስቲ የወደቀውን ምግብ እዚያው ተውትና ሰይጣን መጥቶ ሲበላው ተመልከቱት፣ ከላይ ያየነው ጥቁር ውሻ መጥቶ መብላት ግን ግምት ውስጥ ሊገባ አይገባም፣ ሰይጣንን ነው መጠበቅ ያለባችሁ፡፡

## <u>ማጠቃለያ(ከእውነታ ጋር መጋጨት)</u>

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው በሙሉ የዋነኞቹ የእስልምና ቅዱሳን መፅሀፍት ውሸቶች ናቸው፣ የሚገርመው ደግሞ የውሸት ነገር መጋለጡ ስለማይቀር መሀመድ የተናገራቸው ቃላት ውሸትነት ሲረጋገጥበት በተለያየ ዘዴ ፈተናውን ሲያልፍ ነበረ፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- አንድ ሰው ነብዩ ባሉት መድሃኒት ወንድሙ አለመፈወሱን ሲናገር፣

ሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡614 "አንድ ሰውም ወደ ነቢዩ ቀርቦ 'ወንድሜ (በተቅማጥ ምክንያት) ለመንቀሳቀስ አቅም አጥቷል' አለ፣ ነቢዩም 'ማር አጠጣው' አሉት፣ ሰውየውም ተመልሶ 'ማር አጠጣሁት ነገር ግን

አባሰበት' አለ፣ ነቢዩም 'አላህ ትክክለኛውን ተናግሯል፣ የወንድምህ ሆድ ውሸት ተናገረ' አሉት፡፡"

- "መሬት እንዳትንቀሳቀስ በተራራ ተዋቅራለች" መባሉና በአካባቢያቸው ስለሚበዛው መሬት መንቀጥቀጥ ሲጠይቅ በማይጨበጥ መንገድ ሲያስረዳ ነበረ፡፡

  ሰሂህ ቡኻሪ 9፡88፡214 "... እዛ (ናጂድ በተባለው ቦታ) የመሬት መንቀጥቀጥና የመቅሰፍት ቦታ፣የሰይጣን ራስ ጎን የሚወጣበት ቦታ ነው"

- ነብዩ "ተላላፊ በሽታ የለም" በማለታቸው ጥያቄ የተፈጠረባቸውን በደዊኖች ለማሳመን፣

  ጃሚ አል ቲርሚዲ 2143 "... አንድ ነገር ሌላውን አይበክልም(ተላላፊ በሽታ የለም) ... እንደዚያ ካልሆነ የመጀመሪያው ታማሚ በሽታውን ከየት አመጣው? ... አላህ ሁሉንም ነፍስ ፈጠረ፣ ህይወቱን ፃፈ፣ የሚቀሰፍበትን ጊዜ ፃፈ ..."

  በማለት በደዊኑን ከባድ ጥያቄ በመጠየቅ ፈተናውን ተወጥተውታል፡፡

ይህንን የመሀመድን አካሄድ ያስተዋሉ በወቅቱ የነበሩት ሰዎች፣ የመሀመድን ቁርአን "ውሸት ነው" ሲሉ ነበረ፣

- 25፡4"... (ቁርአን ሙሃመድ) የቀጠፈው... ውሸት እንጂ ሌላ አይደለም..."
- 34፡43 "... ይህም ቁርአን የተቀጣጠፈ ውሸት ነው እንጂ ሌላ አይደለም..."
- 38፡7 "... ይህ ውሸት መፍጠር እንጂ ሌላ አይደለም ..."

ሲሉ ነበረ፣ እነዚህ አስተያየቶች ዛሬ ላይ ትክክለኛ ሆነ ነው የምንመለከተው፣ በዛሬው ትውልድና በመሀመድ መካከል ያለው የእውቀት ልዩነት ደግሞ የባሰ ሰፊ በመሆኑ ቁርአኑ መፅሀፍ ቅዱሱን አልፎ የሄደባቸው ቦታዎች አስቂኝ ውሸቶች ብቻ ሆነው ቀርተዋል፣ ቁርአን ስለራሱ የተናገረው 59፡21 "ይህንን ቁርአን በተራራ ላይ ባወረድነው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ የተነሳ ተዋራጅ ተሰንጣቂ ሆኖ ባየኸው ነበር፤" የሚለው አሁን አስቂኝ ማስፈራርያ ብቻ ነው፡፡

ፈጣሪ ሁሉን ቅዱስና አዋቂ ስለሆነ አይዋሽም በዚህም ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል አይደለም፡፡

### 2.4.4.3. ቁርአን እርስ በርስ እንዲሁም ከሀዲሳት ጋር መጋጨቱ

ፈጣሪ ቅዱስና ሁሉን አዋቂ በመሆኑ ከመነሻው ሲናገር አንዱን እውነት ይናገራል በዚህም ከጊዜ በኋላ ሌላ እውነት ተገልጦለት መጀመርያ ከተናገረው ጋር እርስ በርስ አይጋጭበትም ነገር ግን ቁርአን ስንመለከት የሚናገረው ነገር እርስ በርስ እንዲሁም ከሀዲሳት ጋር ይጋጫል፣ ይህ ደግሞ ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን ያሳያል፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

#### 2.4.4.3.1. እርስ በርስ የሚጋጨው የአላህ የመጨረሻ ዘመን ፍርድ

ቁርአን፣ አላህ በፍርዱ ፃድቅ መሆኑንና ሰውን ሁሉ በአግባቡ እንደሚዳኝ ይናገራል(4፡40, 21፡47 …)፣ ፍርድም የሚሰጠው በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ(58፡22)፣ በመልክተኛው ያመነና ዘካ የሰጠ(2፡43)፣ ሰጋጅ(2፡43)፣ መልካም የሰራ(2፡25)፣ በአላህ መንገድ የተጋደለ (61፡4)፣ ቤቱን (ካዐባን) በሀጅ ወይ በዑምራህ የጎበኘ(2፡158) በሚሉ መስፈርቶች ነው፡፡

በነዚህም መስፈርቶችም የሰዎች ስራ በትክክለኛ ሚዛን ተመዝኖ ዋጋቸው እንደሚሰጣቸው ቁርአኑ ይናገራል፣

> 21፡47 "በትንሳኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን፡፡ ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፡፡ (ስራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርስዋን እናመጣታለን፡፡"

ይሁን እንጂ ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡564, ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡565 … ላይ ስንመለከት የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ያለው ሰው ሲኦል እንደገባ እንመለከታለን፡፡

በሌላ ቦታ ደግሞ "… (አላህ) የፈለገውን ይምራል የፈለገውን ይቀጣል፡፡"(3፡129, 5፡18, 5፡20 …) በማለት ከላይ ተጠቀሱት የፍርድ ሚዛንና መስፈርቶች ትርጉም ሲያጡ እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በባሰ ደግሞ አንድ ሰው ገነት ወይን ሲኦል መግባት አለመግባቱ በራሱ የተወሰነው ሰውየው ሳይወለድ፣ የራሱ ምንም አስትዋፅዖ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ ቁርአኑ ይናገራል፣

- <u>አላህ ቀድሞውኑ ለገሃነም የፈጠራቸው ሰዎች መኖራቸው</u>
  - ሰሂህ ቡኻሪ 4፡55፡549፣ "... ሰው በናቱ ማህፀን ውስጥ (ከ120 ቀናት በኋላ) አላህ አራት ነገር እንዲፅፍ መልአክ ይልካል እነሱም፣ የሚሰራውን ስራዎቹን፣ የሚሞትበትን ቀን፣ የሚኖርበትን አኗኗርና በሀይማኖቱ <u>የተባረከ</u> ይሁን <u>የተረገመ</u> ይሁን ይፅፋል፣ ከዚያ ነፍስን ወደ ፅንሱ ያስገባል ..."

    ተመሳሳይ ሃሳብ ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡430, 8፡77፡593, 9፡93፡540... ላይ እናገኛለን
  - ሰሂህ ሙስሊም 33፡6393 "... ክፉ ማለት በናቱ ሆድ ውስጥ ክፉ እንዲሆን ... የአላህ መልአክ በዚያ ይቀርፀዋል፡፡"
  - 7፡179 "ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን በርግጥ ለገሃነም ፈጠርን፡፡"
  - 32፡13 "በሻን ኖሮ ነፍስን ሁሉ እምነቱዋን በሰጠናት ነበረ፣ ግን ገሃነምን ከአጋንንትና ከሰዎች የተሰበሰቡ ሆነው በእርግጥ እሞላለሁ፡፡"
  - 16፡9 እና 11፡118 "ጌታህም በሻ ኖሮ ሰዎችን ሁሉ አንድ ህዝብ ባደረጋቸው ነበረ ... የጌታህም ቃል ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች ከሁሉም በእርግጥ እሞላታለሁ በማለት ተፈፀመች፡፡"
- <u>አላህ እምነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጋቸው ሰዎች መኖሩ</u>

  32፡13 "በሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት ነበር፡፡"
- <u>አላህ የሚያሳስታቸው መኖራቸው</u>

  4፡88 "... አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን <u>አላህም ያሳሳተውን ሰው</u> ለእርሱ መንገድ ፈፅሞ አታገኙለትም፡፡"
- <u>አላህ የሚያጣምማቸው መኖራቸው</u>
  - 4፡88 "... አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን ..."
  - 35፡8"... አላህ የሚሻውን ሰው ያጠምማል፣ የሚሻውንም ያቀናል፡፡"

  ተመሳሳይ ሀሳቦችም በ7፡186, 39፡36,74፡31...ቦታዎች ላይእናገኛለን፡፡
- <u>አላህ እንዳያስታውሱ የሚያዘናጋቸው መኖራቸው</u>

  18፡28 "ልቡን እኛን ከማስታወስ ያዘነጋነውን ..."

- <u>አላህ ልቦናቸው እንዳያስተውል የሚዘጋባቸው መኖራቸው</u>
  - 18፡57 "… በልቦቻቸው ላይ እንዳያውቁት ሽፋኖችን፣ በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን <u>አደረግን</u>፣ ወደ መምራትም ብትጠራቸው ፈፅመው አይመሩም፡፡"
  - 47፡23-24 "እነዚህ እነዚያ አላህ የረገማቸው፣ ያደነቆራቸውም፣ አይኖቻቸውንም ያወራቸው ናቸው፡፡"
  - 2፡6 "እነዚያ የካዱት (ሰዎች) ብታስፈራራቸውም ባታስፈራራቸውም በነርሱ ላይ እኩል ነው፤ አያምኑትም፡፡ አላህ በልቦቻቸው ላይ በመስሚያቸውም ላይ <u>አትሞባቸዋል</u> …"
  - 17፡46 "(ቁርአንን) እንዳያውቁት በልቦቻቸው ላይ ሽፋንን በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን <u>አደረግን</u>፡፡"
  - 6፡25 "ከእነርሱ ወደአንተ (ወደ መሃመድ) የሚያዳምጥ ሰው አለለ፡፡ በልቦቻቸው ላይ እንዳያውቁት ሺፋኖችን በጆሮዎቻቸውም ላይ ድንቁርናን <u>አደረግን</u>፡፡"

የሚገርመው ደግሞ ሰውየው ለማመንና ገነት ለመግባት ቢፈልግና ቢጣጣር እንኳን ጥረቱ ዋጋ የለውም፡፡

11፡34 "ለናንተ ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደሆነ ምክሬ አይጠቅማችሁ፡፡"

አላህም ይህን ሁሉ አድርጎ ተመልሶ ደግሞ፣

43፡74-76 "አመፀኞች በገሃነም ስቃይ ውስጥ ናቸው … <u>አልበደልናቸውምም፤ ግን በዳዮቹ እነርሱው ነበሩ</u>፡፡" ይላል፡፡

በዚህም ቁርአን ስለ ፈጣሪ ፍርድ አሰጣጥ የሰጠው አስተምህሮ ምን ያህል እርስ በርሱ እንደሚጋጭ እንመለከታለን፡፡

### 2.4.4.3.2. <u>የሰይጣን የገሃነም ፍርድ</u>

የሰው ልጅ ገሀነም ሆነ ጀነት ለመግባት የራሱ አስትዋፅዖ እንደሌለው ሁሉ ጋኔኖችም የተቀመጠላቸው እድል ተመሳሳይ ነው ነገር ግን የእነሱን ከሰው ለየት ለማድረግ የተሞከረው "ኢብሊስ ከመጀመሪያው ስህተቱ የራሱ ነበረ" ለማለት ተሞክሯል፣

2፥34 “ለመላዕክትም፣ ለአዳም ስገዱ ባልን ጊዜ(አስታውስ)፡፡ ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ ኢብሊስ(ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፤ ኮራም ከከሃዲዎቹ ሆነ፡፡”

ኢብሊስ ግን ለሰው አለመስገዱ ቁርአናዊ ነበረ፣ ይህም አምላክ አላህ ብቻ በመሆኑ(3፥2, 47፥19)፣ ስግደትም ለአላህ ብቻ በመሆኑ(6፥162)፣ አላህ በርሱ የማጋራትን ሀጢያት ስለማይምር(4፥116) እና ከአላህ ውጪ ለሌሎች የሚሰግዱትንም “አጋሪ” እያለ ስለሚያወግዝ(6፥11-19)፣ በዚህም ኢብሊስ ከአላህ ውጪ ለማንም አለመስገዱ ትክክል ነበረ፡፡

በተጨማሪም ኢብሊስ እንደተናገረው ስግደት የሚደረገው ለበላይ አካል ነው(7፥12)፣ ኢብሊስ ሳይባረር በፊት አደምን ይበልጠው ነበረ ምክንያቱም አደም የተፈጠረው ከጭቃ ነው(55፥14)፣ ኢብሊስ ደግሞ ከነበልባል(15፥27)፣ በዚህም ኢብሊስ ያነሳው ቁርአናዊ መከራከሪያ 15፥33 “ከሚቅለጨለጭ ሸክላ ከግም ጭቃ ለፈጠርከው ሰው ልሰግድ አይገባኝም፣” ትክክል ነበረ፡፡

በዚህም ኢብሊስ እንዲሳሳት ምክንያት የሆነው አላህ ቃሉን ተላልፎ ኢብሊስን “ለአዳም ስገድ” ማለቱ እንጂ የኢብሊስ የአላህን ቃል መተላለፍ አልነበረም፡፡

ይህ የኢብሊስን ትክክለኛነት ለማሳየት ቀረበ እንጂ፣ ጉዳዩ ያለቀው በኢብሊስ ድርጊት ሳይሆን ከፍጥረት መጀመሪያ ነው፣ 7፥179 “ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን በርግጥ ለገሃነም ፈጠርን፡፡” በሚለው ቃል፣ በዚህም አላህ ኢብሊስ ሲፈጥረው ለሲኦል እንዲሆን አጣሞ ነው፣

15፥39 “(ኢብሊስ) አለ “ጌታዬ ሆይ! እኔን በማጥመምህ …”

ስለዚህ ኢብሊስን ያሳሳተው አላህ መሆኑና ለኢብሊስ መሳሳት ተጠያቂውም አላህ መሆኑን እንመለከታለን፣ ይህም እላይ ካየነው በሰው ልጆች ላይ ከሚፈረደው የተምታታ የፍርድ ሂደት ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

### 2.4.4.3.3. በስጋዊ አይን የተተረከው ገነትና ገሀነም

ቁርአን በገነት ውስጥ ስለሚኖረው ደስታና በገሀነም ስለሚኖረው ቅጣት ሰፊ ትንታኔዎችን ይሰጣል ነገር ግን ትንታኔዎቹ በሙሉ የቀረቡት በስጋዊ አይን እንጂ ለፍርድ ስለምትቀርበው ነፍስ አይደለም፣ በስጋዊ አይን የተሰጡት ትንታኔዎችም ቢሆኑ እንደ ፈጣሪ እይታ ሁሉንም ትውልድ ያገናዘቡ ሳይሆኑ መሀመድ በሚረዳው የኑሮ ዘይቤ መሠረት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

➢ **መብላትና መጠጣት በገነት**

ቁርአኑ በገነት ውስጥ ሰፊ የመብላትና መጠጣት ዘመን እንደተዘጋጀ ይናገራል ነገር ግን ምግብና መጠጦቹ የተሳሉት በስጋዊ እይታ በነመሀመድ ዘመን በነበረው የቅንጦት ምግቦችና አመጋገብ ስነስርአቶች እንጂ ወደ ፈጣሪ ስለምትሄደው ነፍስና የሁሉንም ትውልድ አኗኗር ዘይቤ በተመለከተ መልኩ አይደለም፣

- 56፡18 "ከጠጅ ምንጭም በብርጭቆዎችና በኩስኩስቶች በፅዋም (በእነሱ ላይ ይዞራሉ) ... ከሚመጡትም ዓይነት በእሸቶች፡፡ ከሚሹትም በኾነ በራሪ ስጋ (ይዞሩባቸዋል)፡፡
- 52፡22-23 "ከሚሹት ሁላ እሸትንና ስጋን እንጨምርላቸዋለን፡፡ በውስጥዋ መጠጥን ይጠጣሉ፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡469 "... የገነት ኗሪዎች የሚጠቀሙበት ዕቃ የተሰራው በወርቅና በሲልቨር ነው፣ ማበጠሪያቸውም የተሰራው ከወርቅ ነው፣ ለእሳትነትም የሚጠቀሙት በጣም የሚነደውን የቃጫ መሰል ዛፍ(aleo) እንጨት ነው ..."
- 2፡25 እና 3፡15 "እነዚያ ያመኑትንና መልካሞችንም የሰሩትን ... ከርስዋ ከፍሬ (ዓይነት) ሲሳይን በተመገቡ ቁጥር (ፍሬዎችዋ ስለሚመሳሰሉ) ይህ ያ ከአሁን በፊት የተመገብነው ነው ይላሉ፡፡ እርሱንም ተመሳሳይ ሆኖ ተሰጡ፡፡"
- 83፡23-27 "በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ ኾነው ይመለከታሉ፡፡ በፊቶቻቸው ላይ የድሎትን ውበት ታውቃለህ፡፡ ተጣርቶ ከታተመ ጠጅ

ይጠጣሉ፡፡ ማተሚያውም ምስክ ከሆነ፤ በዚህም ተሽቀዳዳሚዎች ይሽቀዳደሙ፡፡ መበረዣውም ከተስኒም ነው፡፡”

- 76፡17 “በእርስዋም መበረዣዋ ዘንጀቢል የሆነች ጠጅ ይጠጣሉ፡፡”
- 43፡71-73 “ከወርቅ የኾኑ ሰፋፊ ዝርግ ሳሕኖችና ኩባያዎች በነርሱ ላይ ይዝዞራሉ፡፡ በእርስዋም ውስጥ ነፍሶች የሚከጅሉት፣ ዓይኖችም የሚደሰቱበት ሁሉ አልለ ... ለእናንተም በውስጥዋ ብዙ ፍሬዎች በርግጥ ዘውታሪዎች ናችሁ፡፡”

ይሁን እንጂ መብላትና መጠጣት ካለ መፀዳዳትም ሊኖር ነው፣ ገነት ደግሞ ሽንት ቤት አይኖርም፣ ይህን ክፍተት አስመልክቶ መሃመድ ሲናገር “ሰዎች የሚበሉትና የሚጠጡት ሁሉ የሚወጣው በላብና በግሳ ነው” ብሎአል (ሰሂህ ሙስሊም 4፡6798, ሰሂህ ቡኻሪ 4፡55፡544)፣ ይህም አያስኬድም እንደዛ ከሆነ መሀመድ የተመለከተው በላብና በግሳት የተሞላ ግማታም ገሀነም እንጂ ገነት አይደለም፣ ይህ ገነትን በስጋዊ አይን ከመመልከት የመጣ ስህተት ነው፡፡

መሀመድ ገነትን የሳላት በስጋዊ ሁኔታና በዘመኑ በነበረ የቅንጦት ኑሮ ምስል እንጂ ወደ ፈጣሪ በምትሄደው የነፍስ ማንነትና ፍላጎት አይደለም፣ ስጋዊ እይታውም ቢሆን የሁሉም ትውልድ እውነታ አይደለም፣ ያንን ትውልድ የሚያጓጓ እነኚህ ጠግቦ መብላት፣ መጠጣት፣ መስባት፣ በደንብ የሚነዱ እንጨቶችን መሞቅ፣ በወርቅ ማበጠሪያ፣ በወርቅና የሲልቨር እቃዎች መጠቀም ነበረ፣ ለዚህ ትውልድ ደግሞ እነዚህ ትርጉም የላቸውም ይባሱኑም የዚህ ትውልድ ፍላጎት አለመስባት፣ “ቬፐ/ቅርፅ” እንዳይበላሽበት ምግብ በመቀነስና ጤናማው የቪጂቴሪያን አመጋገብ ስልት ነው፡፡

ወደ ፈጣሪ ሄዳ ገነት ትግባ ሲኦል ትግባ ፍርድ የምትቀበለውም ነፍስ ናት(ከታች በዝርዝር ቀርቧል)፣ በዚህም በስጋ እይታ የቀረበው የቁርአኑ የገነት አስተምህሮ እውነታውን በመሳቱ ምን ያህል እርስ በራሱ እንደተምታታ እንመለከታለን፡፡

## ➢ ሴክስ በገነት

ቁርአን በገነት ውስጥ ሴክስ እንዳለ ይናገራል፡-

52፡20-25 "በተደረደሩ አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ኾነው (በገነት ይኖራሉ)፡፡ ዓይናማዎች በኾኑ ነጫጭ ሴቶች እናጠናዳቸዋለን ... ለነርሱም የኾኑ ወጣቶች ልክ የተሸፈነ ሉል መስለው በእነርሱ ላይ (ለማሳለፍ) ይዘዋወራሉ፡፡ ሚጠያየቁ ኾነው ከፊላቸው በከፊሉ ላይ ይዞራል፡፡"

ተመሳሳይ ሃሳብ 44፡54, 56፡22 ... ቦታዎች ላይ እናገኛለን፡፡

በርግጥ ይህ በ2.2 ክፍል ስር እንደተመለከትነው ምድራዊዎቹ ሴቶች የእስልምና ገነት ስለማይገቡ ይህ ጉዳይ የሚመለከተው ወንዶችን ብቻ ነው፣ ለወንዶቹ የሚዘጋጁት ሴቶች ምድራዊ ሳይሆኑ "ሁሪ" የሚባሉ መላዕክት መሆናቸውን በዚሁ ክፍል ተመልክተናል፡፡

በገነት "አለ" የተባለው የሴክስ ጉዳይም እንግዳ ነው፣

- ጃሚያ አት ትርሚዲ 2562 "... በገነት ዝቅተኛ ቦታ ያለ ሰው 72 ሚስቶች ኖሩታል፡፡"
- ጃሚ አት ቲርሚዲ 2536 "በገነት ውስጥ ወንዶች የአንድ መቶ ሰዎች የሴክስ ችሎታ ይሰጣቸዋል፡፡"
- ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡402 "በገነት ውስጥ አንድ ትልቅ 60 ማይል ስፋት ያለው አዳራሽ አለ፣ በየኮርነሩ ሌሎቹን ሚስቶችን የማያዩ ሚስቶች ተቀምጠዋል፣ እና አማኞችም እየሄዱ እየጎበኙዋቸው ይደሰቱባቸዋል፡፡"

ነገር ግን ይህ በገነት የተነገረው የሴክስ ጉዳይ ስጋዊ እንጂ ነፍሳዊ/መንፈሳዊ ካለመሆንም አልፎ ከቁርአኑም ጋር የሚጋጭ ነው፡-

1. በመጀመሪያ ቁርአኑ እንደሚለው አደምና ሀዋ ሴክስ የጀመሩት በሰይጣን ከተታለሉ በኋላ ነው 7፡20 "ሰይጣንም ከሀፍረተ ገላቸው የተሸሸገውን ለእነርሱ ሊገልፅባቸው በድብቅ ንግግር ጎተጎታቸው ... ከዛፊቱም በቀመሱ ጊዜ ሀፍረተ ገላቸው ለሁለቱም ተገለፀላቸው፡፡"

በዚህም በቁርአኑ መሠረት የሴክስ ነገር የተገለፀው በሰይጣን ምክንያት መሆኑንና የመባረራቸው ምክንያትም እሱ ሆኖ እያለ አሁንም ወደ ገነት ሲመለሱ ወደዚህ ሰይጣን ወደ ገለጠውና ለመባረራቸው ምክንያት ወደሆነው ነገር ይመለሳሉ ማለቱ ስህተት ነው፡፡

2. አደም በገነት በነበረበት ጊዜ አንዲት ሀዋ እንጂ 72 ሀዋዎች አልነበሩትም፣ ይህ የአደምና ሃዋ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ቋሚ የፈጣሪ አሰራር በመሆኑም በሁሉም ትውልድ ውስጥ ያለው የወንድና ሴት አንድ ለአንድ ምጣኔ ነው፣ በዚህም "ሚስቶች" የሚለውም ሀሳብ ከፈጣሪ አሰራር መርህ አንፃር ስህተት ነው፡፡

ይህም ደግሞ ሌላ እርስ በርስ መጋጨት ይፈጥራል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ የቁርአን "የገነት ሴክስ" አስተምህሮ ወደ ፈጣሪ ሄዳ ፍርድን ስለምትቀበለው ነፍስ (ከታች በዝርዝር ቀርቧል) ፍላጎት ሳይሆን በስጋዊው የሴክስ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ትንታኔ ነው፣ "ሚስቶች" የሚለው አገላለፅም ከፈጣሪ አሰራር ጋር የሚጋጭ አስተምህሮ ነው፡፡

- **<u>ገሀነም በእስልምና</u>**

እንደ ገነት ሁሉ መሀመድ ገሀነምን የተመለከተው በስጋዊ አይን ነው፣ ነገር ግን ሲኦልን የሳለው ከገነት በተቃራኒ ምስሉን በማበላሸት ነው፣ በዚህም ስለ ገሀነም አመጋገብ ከላይ ካየናቸው ጥራቶች በተቃራኒው በሚያስጠላ ምስል ቀርበዋል፣

- 56፡51-55 "… እናንተ ጠማሞች አስተባባዮች ሆይ! ከዘቁም ዛፍ በርግጥ በይዎች ናቸሁ፡፡ ከርስዋም ሆዶቻችሁን ሞይዎች ናችሁ፡፡ በርሱ ላይም ከፈላ ውሃ ጠጪዎች ናችሁ፡፡ የተጠሙንም ግመሎች አጠጣጥ ብጤ ጠጪዎች ናችሁ፡፡"
- 88፡4-7 "ተኳሳን እሳት ይገባሉ፡፡ በጣም ከፈላች ምንጭ ይጋታሉ፡፡ ለእነርሱ ዶሪዕ ከሚባል (እሾሃም) ዛፍ እንጂ ሌላ ምግብ የላቸውም፡፡ <u>የማያሰባ</u> ከረሃብም የማያብቃቃ ከኾነው፡፡"

- 37፡64-66 “(የዘቁም ዛፍ) እርስዋ በገሀነም አዘቅት ውስጥ የምትወጣ ዛፍ ናት፣ እንቡጧ ልክ የሰይጣን ራሶች ይመስላል፣ እነርሱ ከርሷ በይዎች ናቸው፣ ሆዶችን ከእርሷ ሞይዎች ናቸው፡፡”
- 47፡15 “… ሞቃትን ውሀ እንደተጋቱ፣ አንጀቶቻቸውንም ወዲያውኑ እንደቆራረጠው …”
- 56፡41-44 “የግራ ጓደኞችም ምንኛ(የተዋረዱ) የግራ ጓዶች ናቸው፣ በመርዛ ንፋስ በጣም በፈላ ውሀ ውስጥ ናቸው፣ ከጥቁርም ጭስ በሆነ ጥላ ውስጥ፣ ቀዝቃዛ መልካምም ያልሆነ …”
- 69፡36 “ምግብም ከእሳት ሰዎች እጣቢ (እዥ) በስተቀር የለውም፡፡”

እነኚህ ሁሉ ትንታኔዎች የነፍስ ጉዳይ ሳይሆኑ የስጋዊ ጉዳዮች ናቸው፣ በተጨማሪም እነዚህ ስጋዊ ጉዳዮች የተቃኙትም በነመሀመድ ዘመን ባለው የችግር ምስሎች እንጂ አጠቃላይ እውነታ አይደለም፣ ከሁሉ “የሰይጣን ራሶች የመሰለ ምግብ” የሚለው ደግሞ አስቂኝ ነው፡፡

የሚገርመው ደግሞ ከገሀነም ጋር በተያያዘ ስለሚኖረው ሴክስ ቁርአኑ ምንም አይናገርም፣ ትክክለኛ ያልሆኑት ፆታዊ ግንኙነቶችን ገነት ውስጥ ስላስገባ በገሀነም ውስጥ ፆታዊ ግንኙነት ጥላሸት የሚቀባበትን ምንም መንገድ አላገኘም፣ በገሀነም ሴክስ መኖሩን አለመናገሩ አንዳንድ ሰዎች ገሀነምን መልካም ቦታ አድርገው እንዳይመለከቱ ያደረገው ጥንቃቄ ሊሆን ይችላል¡¡

በአጠቃላይ ስንመለከት እነዚህ በቁርአኑ የተሰጡት የገነት-ገሀነም ትንታኔዎች የቀረቡት በስጋዊ እይታ እንጂ ከነፍስ ማንነት አንፃር አይደለም፣ ነገር ግን ወደ ፈጣሪ ሄዳ ፍርድዋን የምትቀበለው ነፍሳዊ ማንነት እንጂ ስጋዊ ማንነት እንዳልሆነች ቁርአኑ በሌላ ስፍራ ላይ ደግሞ ይናገራል፣

- 9፡27-30 “(ለአመነች ነፍስም) “አንቺ የረካሺው ነፍስ ሆይ! “ወዳጅ ተወዳጅ ሆነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ፡፡ በባሮቼ ውስጥ ግቢ፡፡ ገነቴንም ግቢ፤” (ትባላለች)፡፡”
- 74፡38 “ነፍስ ሁሉ በሰራችው ስራ ተያዥ ናት፡፡”
- 50፡21 “ነፍስም ሁሉ ከእርስዋ ጋር ነጂና መስካሪ ያለባት ኾና ትመጣለች፡፡”

- 75፡14 “በርግጥ ሰው በነብሱ ላይ አስረጅ ነው (አካሎቹ ይመሰክሩበታል)፡፡”
- 73፡20 “… ከመልካም ስራም ለነፍሶቻችሁ የምታስቀድሙትን ሁሉ እርሱ የተሻለና በምንዳ ታላቅ ሆኖ አላህ ዘንድ ታገኙታላችሁ፡፡”

ዛሬም እንደምንመለከተው ሰው ሲሞት ስጋው እዚህ ቀርቶ ነው ነፍሱ ወደ ፈጣሪ የምትሄደው፣ ይህንንም በሞቱት ሰዎች ላይ መመልከት እንችላለን፣ ቁርአኑም ስለሞቱትና ስጋቸው ተቀብሮ ነፍሳቸው ወደ ፈጣሪ ስለሄዱት ሰዎች ይናገራል፣

- 3፡169 “እነዚያ በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡፡ በእርግጥ እነሱ እጌታቸው ዘንድ ህያዋን ናቸው፤”
- 43፡74-76 “አመፀኞች በገሃነም ስቃይ ውስጥ ናቸው … አልበደልናቸውምም፤ ግን በዳዮቹ እነርሱው ነበሩ፡፡”

በዚህም ምንም እንኳን ሰዎች ሲሞቱ ስጋቸው እዚህ ቢቀርም በነፍሳቸው(በመንፈሳዊው ማንነታቸው) ገነት ወይንም ገሀነም ውስጥ እንዳሉ ይናገራል፡፡

በዚህም ሰው ሲሞት ወደ ገነት/ገሀነም የምትሄደው ነፍስ መሆኗ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ፣ ስለገነት ተድላና ስለ ገሀነም ጭንቅ በስጋ አእምሮ ገምቶ ሰፊ ትምህርት መስጠቱ ስህተት መሆኑና ቁርአኑም ላይ እርስ በርስ ግጭቶች እንደሚፈጥር ይባሱኑ ቁርአኑ ነፍሳዊና መንፈሳዊ ሽልማቶችና ቅጣቶችን አለማወቁ በራሱ ቁርአኑ ሰውኛ ፈጠራ መሆኑን በራሱ ላይ ያሳበቀበት እውነታ ነው፡፡

ከላይ በሰፊ ትንታኔ የቀረበው፣ ቁርአን ምን ያህል እርስ በርሱ እንደሚጋጭ ለማሳየት ነው ነገር ግን በዚህ መልክ እየተነተኑ መሄዱ በጣም ስለሚሰፋ ሌሎቹን እርስ በርስ ግጭቶቹን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን፡፡

## 1. አላህ ፍርድ የሚሰጠው ምን ላይ ተመርኩዞ ነው?

“አላህ ሁሉን አዋቂ” በመሆኑ በራሱ እውቀት

10፡18 “... አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን ...”

የሰውን ስራ በሚዛን ሰፍሮ

21፡47 “በትንሳኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን፡፡ ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፡፡ (ስራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርስዋን እናመጣታለን፡፡ ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ፡፡”

ተመሳሳይ ሀሳቦችንም በ7፡8-9, 7፡13, 18፡49, 21፡47, 17፡71, 23፡101-103, 99፡7 ... ቦታዎች ላይ ተመልክቷል፡፡

በመላዕክት ምስክርነት

50፡17-21 “ሁለቱ ቃል ተቀባዮች(መላዕክት) ከቀኝና ከግራ ተቀማጮች ሆነው በሚቀበሉ ጊዜ (አስታውስ) ... ነፍስ ሁሉ ከርስዋ ጋር ነጂና መስካሪ ያለባት ኾና ትመጣለች፡፡”

በኢሳ ምስክርነት

4፡159 “... (ኢሳ) በትንሳኤ ቀን በነሱ(በመፅሃፉ ሰዎች) መስካሪ ይሆናል፡፡”

በሰውየው የአካል ክፍሎች ምስክርነት

41፡22 “ጆሮዎቻችሁ ዓይኖቻችሁና ቆዳዎቻችሁም በእናንተ ላይ ከመመስከራቸው የምትደበቁ አልነበራችሁም፡፡”

ታድያ ምስክር የሚሆነው የትኛው ነው? ሁሉም እንዳንል ተጨማሪ ምስክር የሚጠራው የአንዱ ምስክርነት ብቻውን አስተማማኝነት ከሌለው ነው ይባሱኑ ደግሞ “ሁሉን አዋቂ”ው ጋር የምስክር አስፈላጊነት ደግሞ የበለጠ ግራ አጋቢ ነገር ነው፡፡

## 2. አማላጅ ማነው?

አላህ ብቻ ነው ሌላ አያስፈልግም

- 6፡51 “... ከአላህ **ሌላ** አማላጅ የለም ...”
  ተመሳሳይ ሀሳቦችም 6፡70, 32፡4, 39፡44 ላይ ቀርቧል
- 10፡18 “... እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ፤ አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን በላቸው ...”

- 39፡43 “ይልቁንም (ቁረይሾች) ከአላህ ሌላ አማላጆችን ያዙ ... ምልጃ መላውም የአላህ ብቻ ነው፡፡”
- 39፡7 “... ማንኛይቱም ኃጢያት ተሸካሚ ነፍስ የሌላይቱን ኃጢያት አትሸከምም፡፡”

  ተመሳሳይ ሃሳብ 53፡38, 17፡15, 6፡164 ላይ እንመለከታለን፡፡

ሰዎች

- 9፡103 “ከገንዘቦቻቸው ስትሆን በርስዋ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የሆነችን ምፅዋት ያዝ ለነሱም ፀልይላቸው፤ ፀሎትህ ለነሱ እርካት ነውና አላህም ሰሚ አዋቂ ነው፡፡”
- 60፡4 “(ኢብራሂም ለአባቱ) ደህና ሁን፡፡ ወደፊት ከጌታዬ ምሕረትን እለምንልሃለሁ፡፡ እርሱም ለኔ በጣም ሩህሩህ ነውና፣ አለ፡፡”

  ተመሳሳይ ሀሳብም በ9፡114 እና 19፡47 ... ላይ ቀርቧል፡፡
- 7፡155-156 ላይ ሙሳ ስለ ህዝቡ የምልጃ ፀሎት ሲያቀርብና አላህም ይቅርታ ሲያደርግ እንመለከታለን፡፡

በነፍስ አፀድ ያሉ ቅዱሳን

40፡7 “እነዚያ አርሹን የሚሸከሙት ... ለተፀፀቱት መንገድህንም ለተከተሉት ምህረት አድርግላቸው ... እያሉ ለእነዚያ ላመኑት ምህረትን ይለምናሉ፡፡”

መላዕክት

53፡26 “በሰማያት ውስጥ ካለ መልአክም ብዙዎች (ሊማለዱለት) ለሚሻውና ለሚወደው ሰው ከፈቀደ በኋላ ቢኾን እንጂ ምልጃቸው ምንም አትጠቅምም፡፡”

### 3. ሰዎች ገሀነም እንዲገቡ ምክንያት የሆነው ማነው?

አላህ

35፡8 “... አላህ የሚሻውን ሰው ያጠማል ...”

ሰይጣን

15፡39 “(ኢብሊስም) ... ለነርሱ በምድር ላይ (ሀጢያትን) እሸልምላቸዋለሁ፣ ሁሉንም አጠማቸዋለሁ፡፡

ሰዎች እራሳቸው

30፡9 “... መልዕክተኞቻቸውም በተአምራት መጡባቸው (አስተባበሉምና ጠፉ)፣ አላህም የሚበድላቸው አልነበረም፣ ግን ነፍሶቻቸውን ይበድሉ ነበረ፡፡”

**4. <u>በፍርድ ቀን ሰዎች ሀጢያተኞች መዝገባቸው ምኑ ጋር ይደረግላቸዋል?</u>**

<u>በጀርባቸው</u>

84፡10 “መፅሃፉን በጀርባው ኋላ የተሰጠውማ፤ (ዋ ጥፋቴ በማለት) ጥፋትን በርግጥ ይጠራል፡፡”

<u>በግራ እጃቸው</u>

69፡25 “መፅሃፉን በግራ የተሰጠውማ (ዋ ጥፋቴ) ምነው መፅሃፌን ባልተሰጠሁ ይላል፡፡”

**5. <u>የገሀነም ሰዎች ምግብ ምንድነው?</u>**

<u>ዶሪዕ ብቻ</u>

88፡6 “… ለእነርሱ ዶሪዕ ከሚባል (እሾሃም) ዛፍ <u>እንጂ ሌላ ምግብ የላቸውም</u>፡፡”

<u>የቁስል እጣቢ ብቻ</u>

69፡36 “ምግብም ከእሳት ሰዎች እጣቢ (እዥ) <u>በስተቀር የለውም</u>፡፡”

<u>ዘቁም ነው</u>

37፡64-66 “እርስዋ በገሀነም አዘቅት ውስጥ የምትወጣ ዛፍ ናት፡፡ እንቡጣ ልክ የሰይጣናት ራሶች ይመስላል፡፡ እነርሱም ከርስዋ በይዎች ናቸው፤ ሆዶችንም ከእርስዋ ሞይዎች ናቸው፡፡”

**6. <u>ተራሮች በቂያማ ቀን(በመጨረሻው ቀን) ምን ይሆናሉ?</u>**

<u>እንደ ተነከረ ሱፍ ይሆናሉ</u>

70፡9 “ጋራዎችም በተለያዩ ቀለማት እንደ ተነከረ ሱፍ (ነፋስ እንደ ሚያበረው) በሚኾኑበት ቀን፡፡”

<u>ነደው ይጠፋሉ</u>

78፡20 “ጋራዎች በሚነዱበት(እንደ) ሲራብዱም በሚኾኑበት (ቀን) …”

**7. <u>ስንት ገነቶች አሉ?</u>**

<u>አንድ</u>

57፡21 “ከጌታችሁ ወደ ኾነች ምሕረት፣ ወርዷ እንደ ሰማይና ምድር ወርድ ወደ ሆነች ገነት ተሽቀዳደሙ፡፡”

<u>ሁለት</u>

55፡46 “በጌታው ፊት መቆምን ለፈራ ሰው ሁለት ገነቶች አሉት፡፡”

<u>አራት</u>

55፡62 “ከሁለቱ ገነቶችም ሌላ ሁለት ገነቶችም አሉ፡፡”

8. **<u>አላህ የት ይኖራል?</u>**

<u>በዙፋኑ/አርሹ ላይ</u>

- 57፡4 “እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀን ውስጥ የፈጠረ፣ ከዚያም በዙፋኑ ላይ(ስልጣኑ) የተደላደለ ነው፡፡”
- 11፡7 “እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ነው፡፡ አርሹም በውሀ ላይ ነበረ ...”

<u>በሁሉም ቦታ</u>

2፡115 “... (ፊቶቻችሁን) ወደ የትም ብታዞሩ የአላህ ፊት እዚያው ነው፡፡”

<u>በቤቱ(በካዕባ)</u>

2፡158 “... ቤቱን(ካዕባን) በሐጅ ወይም በዑምራህ ስራ ለጎበኘ ሰው...”

9. **<u>አላህ ሊታይ ይችላል?</u>**

<u>ሊታይ ይችላል</u>

53፡11-13 “(ነቢዩ በዓይኑ) ያየውን ልቡ አልዋሸም፡፡ ታዲያ በሚያየው ላይ ትከራከሩታላችሁን፣ በሌላይቱ መውረድ ጊዜ በእርግጥ አይቶታል፡፡”

<u>ሊታይ አይቻልም</u>

6፡103 “(አላህን) ዓይኖች አያገኙትም፤ (አያዩትም)፡፡”

10. **<u>አላህ ለሰዎች በቀጥታ ይናገራል?</u>**

<u>አዎን ይናገራል</u>

- 4፡164 “... አላህም ሙሳን ማነጋገር አነጋገረው፡፡”
- 2፡253 “እነዚህን መልዕክተኞች ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ አበለጥን፣ ከነርሱ ውስጥ አላህ ያነጋገረው አለ፡፡”

<u>አይናገርም</u>

42፡51 “ለሰውም አላህ በራዕይ ወይም ከግርዶ ወዲያ፣ ወይም መልዕክተኛ (መልአክን) የሚልክና በፈቃዱ የሚሻውን ነገር የሚያወርድለት ቢኾን እንጂ (በገሃድ) ሊናግረው ተገቢ አይደለም፡፡”

11. **<u>አላህ ቃሉን ይለውጣል ወይስ አይለውጥም?</u>**

<u>አይለውጥም</u>

10፡64 “... የአላህ ቃላት መለወጥ የላትም፤”

<u>ይለውጣል</u>

2፡106 “ከአንቀፅ <u>ብንለውጥ</u> ወይም እርሷን ብናስረሳህ <u>ከርሷ የሚበልጥ ወይም ብጤዋን እናመጣልሀለን</u>፡፡”

12. <u>አላህ የሽርክ (የማጋራት) ሀጢያትን ይቅር ይላል?</u>

<u>ይቅር አይልም</u>

4:116 “አላህ በርሱ የማጋት ወንጀልን አይምርም፡፡”

<u>ይቅር ይላል</u>

4:153 “(የመፅሃፉ ሰዎች) ... ከዚያም ተአምራቶች ከመጡላቸው በኋላ ወይፈኑን (አምላክ አድርገው) ያዙ፡፡ ከዚያም ይቅር አልን፡፡”

13. <u>ፍጥረታት በምን ያህል ጊዜ ተፈጠሩ?</u>

<u>በስድስት ቀን</u>

25:59, 50:38, 57:4 ... “ያ ሰማያትን ምድርን በመካከላቸው ያለውን ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ፣”

<u>ከስድት ቀን በላይ</u>

41:9-12 “በላቸው፣ እናንተ በዚያ ምድርን በሁለት ቀኖች ውስጥ በፈጠረው አምላክ በርግጥ ትክዳላችሁን ... በውስጥዋም ምግቦችዋን(ካለፉት ሁለት ቀኖች ጋር) በአራት ቀናት ውስጥ ለጠያቂዎች ትክክል ሲሆኑ ወሰነ፡፡ ከዚያም ወደ ሰማይ <u>ጭስ ሆና ሳለች</u> አሰበ፡፡ ለእርስዋም ለምድርም “ወዳችሁም ሆነ ጠልታችሁ <u>ኑ” አላቸው፡፡ “ታዛዦች ሆነን መጣን” አሉ</u>፡፡ በሁለት ቀኖች ውስጥ ሰባት ሰማያት አደረጋቸው፡፡”

እዚህ ጋር ስድስት የፍጥረታት ቀኖችን በግልፅ እንመለከታለን፣ ነገር ግን በ5ኛውና በ6ኛው ቀን ሰማይን ሲዘረዝር በመጀመሪያ ጭስ መስላ ተፈጥራ የነበረችውና ሲጠሩም “ታዛዦች ሆነን መጣን”፣ “አሉ” የተባሉትና ቀድሞውኑ ተፈጥረው የነበሩትን የተፈጠሩበትን ጊዜ ስንደምርበት የፍጥረት ቀናት ከ6ቀናት በላይ መሆኑን እንረዳለን፡፡

14. <u>ልጅ በእናቱ ሆድ ውስጥ እውቀት አለው ወይስ የለውም?</u>

<u>የለውም</u>

16:78 “አላህ ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ፡፡”

<u>አለው</u>

ሰሂህ ቡኻሪ 8:77:597 “... የአላህ መልእክተኛ እንዳለው “ማንኛውም ህፃን ሲወለድ እስላም ሆኖ ነው፣ ነገር ግን ወላጆቹ ወደ ይሁዲነት ወይ ወደ ክርስትና ይቀይሩታል፡፡”

15. <u>ነቢያት እኩል ናቸው ወይስ ይበላለጣሉ?</u>

<u>እኩል ናቸው</u>

2፡285"... በመልዕክተኞቹም ከመልዕክተኞቹ በአንድም መካከል አንለይም፡፡"
ይበላለጣሉ
2፡253 "እነዚህን መልዕክተኞች ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ አበለጥን፣ ከነርሱ ውስጥ አላህ ያነጋገረው አለ፡፡"

**16. ቁርአን በመሀመድ ላይ ተወረደ? ወይስ መሀመድ ላይ አልተወረደም?**

መሀመድ ላይ የተወረደ ነው
26፡194 "ከአስፈራዎቹ (ነቢያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)፡፡"
የዚህን ተመሳሳይ ሃሳብ 21፡2, 39፡1-2, 39፡41 ... ቦታዎች ላይ ቀርቧል፡፡
አልተወረደም
16፡64 "ባንተ ላይ መፅሀፉን አላወረድንም ..."

**17. ቁርአን በምን ያህል የጊዜ ርዝማኔ ወረደ?**

በአንድ ለሊት
- 44፡3 "እኛ (ቁርአኑን) በተባረከች ለሊት ውስጥ አወረድነው፡፡"
- 97፡1 "እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ለሊት አወረድነው፡፡"

በረዥም የጊዜ ሂደት ተከፋፍሎ
- ቁርአን የተገለጠው በረዥም የጊዜ ሂደት መሀመድ መካና መዲና በኖረባቸው ጊዜያት ነው፣ ሰሂህ ቡኻሪ 7፡72፡787 "ነብዩ መካ 10 አመት ሲቆዩ ከዚያም 10 አመት መዲና ኖሩ፡፡"
- 25፡32 "እነዚያ የካዱት "ቁርአን በእርሱ ላይ ለምን በጠቅላላ አንድ ጊዜ አልተወረደም" አሉ፡፡ እንደዚሁ በእርሱ ልብህን ልናረጋ (ከፋፍለን አወረድነው)፡፡ ቀስ በቀስ መለያየትንም ለየነው፡፡"
- 17፡106 "ቁርአንንም በሰዎች ላይ በዝግታ ላይ ሆነህ ታነበው ዘንድ ከፋፈልነው፡፡ ቀስ በቀስ ማውረድም አወረድነው፡፡"
- 3፡3 "ከዕርሱ በፊት ያሉትን መፅሀፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን መፅሃፉን(ቁርአንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ ..."

**18. መሃመድ መካ የቆየው ለምን ያል ጊዜ ነው?**

ለ10 ዓመት - ሰሂህ ቡኻሪ 7፡72፡787 "... መካ ለ10 አመት ሲቆዩ ..."
ለ13 ዓመት - ሰሂህ ቡኻሪ 5፡58፡242 "... ከዚያ መካ ለ13 አመታታ ቆየ ..."
ለ15 ዓመት - ሰሂህ ሙስሊም 30፡5809 "መሀመድ እንደ ነብይ ከተገለጠ ቦሃለ በመካ 15 አመታት ቆየ"

19. <u>መሀመድ ቁርአንን ሙሉ በሙሉ በቃሉ ያውቃል?</u>

<u>አዎን ያውቃል</u>

87፡6 "(ቁርአንን)በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ አትረሳምም፡፡"

<u>ሙሉ በሙሉ አያውቅም፣ አንዳንዶቹን ሲረሳ ነበረ</u>

- ሰሂህ ቡኻሪ 1፡8፡394 "... እኔ እንደናንተው የሰው ልጅ ነኝና ልረሳ እችላለሁ፣ ስለዚህ እኔ ከረሳሁኝ አስታውሱኝ ..."
- ሰሂህ ሙስሊም 4፡1179፡ "... የአላህ መልዕክተኛም ... እኔኮ የሰው ልጅ ነኝ፣ እናንተ እንደምትረሱት እኔም እረሳለሁ ..."
- አቡ ዳዉድ 3970 አይሻ እንደተረከችው፣ አንድ ሰው ቂያማ እየሰገደና ድምፁንም ከፍ አድርጎ ቁርአን በቃሉ ይቀራ ነበረ፡፡ በነጋታው የአላህ መልዕክተኛ "አላህ ምህረቱን ያብዛልኝ ... ትላንት ማታ ስንትና ስንት አንቀፆችን አስታወሰኝ፣ ረስቻቸው ነበረ" አሉ፡፡
- ሰሂህ ቡኻሪ 3፡48፡823 "አይሻ እንደተረከችው፡ ነብዩ መዝጊድ ውስጥ ሆነው ቁርአን በቃሉ ይቀራ የነበረን ሰው ሰሙ፣ ከዚያ "አላህ ምህረቱ በኔ ላይ ይሁን ... የረሳሁትን የቁርአን ብዙ ክፍሎች አስታወሰኝ" አሉ፡፡
- ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡449-450፣ እዚህ ቦታ ላይ የምንመለከተው ለመሀመድ ቁርአን ሲገለጥለት አላህ "እንዳትረሳ የምነግርህን ብቻ አዳምጥ፣ ስነግርህ ምላስህን አታንቀሳቅስ፣ ምላስህን ካንቀሳቀስክ የምትረሳው ክፍል ይኖራል" ማለቱና መሀመድ ግን ቁርአኑን ሲቀበል ሳያውቅ ምላሱን ማንቀሳቀሱን እንመለከታለን፣ በዚህም የተረሱ የቁርአን ክፍሎች እንዳሉ ሀዲስ ምስክር ነው፡፡

20. <u>መሀመድ ከቁርአኑ መርሳቱ ቁርአናዊ ነው?</u>

<u>አይደለም</u>

87፡6 "(ቁርአንን)በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ <u>አትረሳምም</u>፡፡"

<u>አዎን</u>

2፡106 "ከአንቀፅ ብንለውጥ ወይም እርሷን <u>ብናስረሳህ</u> ከርሷ የሚበልጥ ወይም ብጤዋን እናመጣልሀለን፡፡"

21. <u>ከመሀመድ በኋላ የሚመጣ ነብይ አለ? ወይስ የለም?</u>

<u>የለም</u>

33፡40 "ሙሃመድ ... የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፡፡"

<u>አለ</u>

"መኽዲ" የሚባለው ነብይ(የአቡ ዳውድ ሱና 4285) እና ወደ ፈጣሪ የተወሰደው ነቢዩ ኢሳ (ሰሂህ ሙስሊም 41፡6924, ሰሂህ ሙስሊም 1፡0289) ከመሀመድ በሀላ ይመጣሉ፡፡

**22. <u>ሳያበላልጡ በመያዝ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ይቻላል?</u>**

<u>ይቻላል</u>

4፡3 "... ከሴቶች ለእናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት ሶስት ሶስትም አራት አራትም አግቡ፡፡ <u>አለማስተካከልንም ብትፈሩ</u> አንዲትን ብቻ ወይም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን (ባሮችና ምርኮኞች) ያዙ ..."

<u>አይቻልም</u>

4፡129 "... በሴቶችም መካከል ምንም እንኳዋ ብትጓጉ (በፍቅር) ለማስተካከል አትችሉም፡፡"

**23. <u>ዝሙት የተፈቀደ ነው?</u>**

<u>የተፈቀደ ነው</u>

4፡24 "ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው ... ከዚያችሁም (ከተከለከሉት) ወዲያ ጥብቆች ሆናችሁ ዝሙተኛ ሳታሆኑ <u>በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለናንተ ተፈቀደ</u>፡፡ ከእነሱም በርሱ(በመገናኘት) <u>የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች</u> ..."

ሀዲስ ላይም ሰአት ሰጥቶ(ሰሂህ ሙስሊም 8፡3252)፣ ልብስ ሰጥቶ (ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡139) ዝሙት መፈፀም እንደሚቻል ያሳያል፡፡

<u>የተከለከለ ነው</u>

17፡32 "ዝሙትን አትቅረቡ፡፡ እሱ በርግጥ መጥፎ ስራ ነውና፡፡ መንገድነቱም ከፋ፡፡"

**24. <u>ያልሰለሙትን ሴቶች ማግባት ይቻላል?</u>**

<u>አዎን</u>

5፡5 "... ከምእመናት ጥብቆቹም ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መፅሃፍን ከተሰጡ("ክርስቲያኖች") ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማዊዎችና (ዝሙተኞች) የምስጢር ወዳጅ ያዢዎች ሳትሆኑ ጥብቆች ኾናችሁ መኅሮቻቸን በሰጣችኋቸው ጊዜ (ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)፡፡"

<u>አይቻልም</u>

2፡221 "ኢጋሪዎች("ክርስቲያኖች") የሆኑ ሴቶች እስኪያምኑ ድረስ አታግቡአቸው፡፡"

**25. <u>ሙስሊም ክርስቲያን/አይሁድ ያረደውን መብላት ይፈቀድለታል?</u>**

<u>ይፈቀዳል</u>

5፡5 "... እነዚያም መፅሃፍን የተሰጡ ሰዎች(አይሁድ/ክርስቲያን) ምግብ(ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው፡፡"

<u>አይፈቀድም - ክርስቲያን የሚያርደው "በስመ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ብሎ ስለሆነ</u>

2፡173 "በእናንተ ላይ እርም ያደረገው ... በእርሱም (ማረድ) ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ነገር ብቻ ነው፡፡"

6፡121 "በእርሱም ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ፡፡"

**26. <u>ከአይሁድ/ከክርስቲያን ከሲኦል የሚድኑ አሉ?</u>**

<u>አዎን</u>

2፡111-112 "ገነትንም አይሁድን ወይም ክርስቲያኖችን የሆነ እንጂ ሌላ አይገበባትም አሉ፣ ይህቺ (ከንቱ) ምኞታቸው ናት ... አይደለም ሌላውም ይገባባታል ..."

<u>አያመልጡም</u>

3፡85 "ከኢስላም ሌላ ሀይማትን የሚፈልግ ሰው ፈፅሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡"

**27. <u>ፍርድ ተላልፎበት ሲኦል የገባ ሰው የሚወጣበት መንገድ አለው</u>**

<u>የለውም</u>

ሲኦል የገባ አይወጣም 2፡167, 5፡36-37, 32፡14, 35፡36-37, 41፡28...

<u>አለው</u>

የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ያለው ከሲኦል እንዲወጣ ይደረጋል፣ ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡564, ሰሂህ ቡኻሪ 8፡76፡565 ...

**28. <u>በሃይኖማት ማስገደድ ይቻላል?</u>**

<u>አይቻልም</u>

2፡256 "በሀይማኖት ማስገደድ የለም፡፡"

<u>ይቻላል</u>

- 13፡15 "በሰማያትና በምድር ያሉት ሁሉ በውድም ሆነ <u>በግድ</u> ለአላህ ይሰግዳሉ፡፡"
- 48፡16 "... <u>ትጋደሉዋላችሁ ወይም ይሰልማሉ</u>፡፡"

**29. <u>ቅዱሳን መላዕክት በየትኛው ፆታ ይጠራሉ?</u>**

<u>በሴት</u>

3፡39 “(ዘከሪያ) በፀሎት ማድረሻ ክፍል ሆኖ ሲፀልይ መላዕክት <u>ጠራችው</u> “አላህ በየሕያ(በዮሐንስ) ከአላህ በሆነ ቃል የሚያረጋግጥ ጌታም ድንግልም ከደጋጎቹ ነቢይ ሲኾን ያበስርሀል” በማለት …”

<u>በወንድ</u>

53፡27 “እነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም <u>የማያምኑት</u> መላዕክትን በሴት አጠራር ይጠራሉ፡፡”

**30. <u>መላዕክት ለቅጣት ብቻ ነው የሚወርዱት?</u>**

<u>አዎን</u>

15፡7-8 “ከእውነተኞች እንደሆንክ ለምን በመላዕክት(መስካሪ) ለምን አትመጣም(አሉ)፡፡ መላእክትን በእውነት በቅጣት እንጂ አናወርድም፡፡”

<u>አይደለም ለሌላ ስራም ይወርዳሉ</u>

- 16፡2 “ከባሮቹ በሚሻውሰው ላይ መላዕክትን ከራዕይ ጋር ያወርዳል …”
- 53፡5 “(መሃመድን) ኃይሎቹ ብርቱው (መልአክ) አስተማረው፡፡”

**31. <u>ደመና የሚነዳው አላህ፣ መልአክ ወይስ ንፋስ?</u>**

- 24፡43 “አላህ ደመናን የሚነዳ መኾኑን አላየህምን…”
- ጃሚያ አት ቲርሚዲ 3117 “ከመላዕክት መሃከል ለደመናት ተጠያቂ የሆነው መልአክ ደመናትን የሚነዳበት ትንሽ እሳት አለው … የነጎድጋድ ድምፁም የሚወጣው መልአኩ ደመናውን ለመንዳት በሚመታው ግዜ ነው …”

**32. <u>ጂሃድ በተቀደሱ ወራት ይደረጋል?</u>**

<u>አዎን</u>

9፡36 “የወሮች ቁጥር አላህ ዘንድ … አስራ ሁለት ወር ነው፣ ከእነሱም አራቱ የተከበሩ ናቸው … በነሱ ውስጥም … አጋሪዎች በአንድ ላይ ሆነው እንደሚዋጉዋችሁ በአንድ ላይ ሆናችሁ ተዋጉዋቸው …”

<u>አይፈቀድም</u>

9፡5 “የተከበሩት ወሮችም ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን(የስላሴ አማኞችን) ባገኛችሁ ቦታ ግደሉዋቸው፡፡”

**33. <u>ሰይጣን ከሰው ልጅ ሲነፃፀር በመጠን ምን ያክላል?</u>**

<u>ረቂቅ</u>

ሰሂህ ሙስሊም 26፡5404 “ደም ሰውነታችን ውስጥ እንደሚዘዋወረው፣ ሰይጣንም በሰውነታችን ውስጥ ይዘዋወራል፡፡”

<u>በጣም ትንሽ</u>

- ሰሂህ ሙስሊም 4፡7132 “... ስታፋሽጉ ሰይጣን እንዳይገባ በእጃችሁ አቃርጡ፡፡”
- ሰሂህ ሙስሊም 2፡462 “... ሰይጣን የለሊቱን ጊዜ አፍንጫችን ውስጥ ያሳልፋል፡፡”
- ሰሂህ ቡኻሪ 2፡21፡245 - አብዱላህ እንደተረኩት የሆነ ሰው ነቢዩ ጋር ቀረበና እስከሚነጋ ድረስ እንደሚተኛና ለፀሎት እንኳን መነሳት እንደሚያቅተው ነገራቸው፣ ነቢዩም “ሰይጣን በጆሮው ውስጥ ሸንቶበት ነው” አሉ፡፡

<u>ትንሽ</u>

37፡64-66 “እርስዋ በገሀነም አዘቅት ውስጥ የምትወጣ ዛፍ ናት፡፡ እንቡጧ ልክ የሰይጣናት ራሶች ይመስላል፡፡ እነርሱም ከርስዋ በይዎች ናቸው፤ ሆዶችንም ከእርስዋ ሞይዎች ናቸው፡፡”

<u>መካከለኛ (እንደ ሰው)</u>

- ሰሂህ ቡኻሪ 3፡38፡505 “... አቡ ሁራይራ ሰይጣንን ሲሰርቅ ያዙት...”
- 55፡56 “በውስጣቸው ከበፊታቸው (ከባሎቻቸው በፊት) ሰውም ጃንም ያልገሰሳቸው (ሴቶች) ...”

<u>በጣም ግዙፍ</u>

ሰሂህ ቡኻሪ 9፡214 “... እዛ (ናጂድ በተባለው ቦታ) የመሬት መንቀጥቀጥና የመቅሰፍት ቦታ የሰይጣን ራስ ጎን የሚወጣበት ቦታ ነው፡፡”

**34. <u>ሰይጣን ለገነት የተመረጡ ሰዎችን ማሳሳት ይችላል?</u>**

<u>አይችልም</u>

38፡82-83 “(ኢብሊስም) አለ “በአሸናፊነትህ ይሁንብኝ፤ በመላ አሳስታቸዋለሁ፡፡ ከእነርሱ ምርጥ ባሮችህ ሲቀሩ፡፡”

<u>ይችላል</u> (አማኞችን ማሳሳት ስለሚችሉ ለገሀነም ከታሰበው በላይ ሰዎችን ማስገባታቸው፡፡)

6፡128 “አጋንንት ጭፍሮች ሆይ! ከሰዎች(ጭፍራን በማጥመም) በርግጥ አበዛችሁ (ይባላሉ)፡፡”

35. <u>የኑሕ(የኖህ) ልጅ ከጥፋት ውሃ(ጎርፍ) አምልጧል?</u>

<u>አዎን</u>

- 37፡76-77 "እርሱንም (ኑሕን) ቤተሰቦቹንም ከከባድ ጭንቅ አዳንን፡፡ ዘሮቹንም እነርሱን ብቻ ቀሪዎች አደረግን፡፡
- 21፡76 "ኑሕንም ከዚያ በፊት (ጌታውን) በጠራ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ለእርሱም (ጥሪውን ተቀበልነው፡፡ እርሱንም ቤተሰቦቹንም ከከባድ ጭንቅ አዳን፡፡"

<u>አላመለጠም</u>

11፡42-43 "... ኑሕም ልጁን ከመርከቢቱ የራቀ ሆኖ ሳለ "ልጄ ሆይ ከኛ ጋር ተሳፈር ከከሃዲዎች አትሁን" ሲል ጠራው፡፡ (ልጁም) "ከውሃው ወደ ሚጠብቀኝ ተራራ እጠጋለሁ አለ" ... ማዕበሉም በመካከላቸው ወረደ፡፡ ከሰጣሚዎቹም ሆነ፡፡"

36. <u>ፈርኦን ህፃናቱ እንዲገደሉ ያዘዘው መች ነው?</u>

<u>ሙሳ ነብይ በነበረበት ጊዜ</u>

40፡25 "(ሙሳ) ከእኛ ዘንድ እውነትን ይዞ በመጣላቸው ጊዜ "የእነዚያ ከእርሱ ጋር ያመኑትን ሰዎች ወንዶች ልጆች ግደሉ ... አሉ፡፡"

<u>ሙሳ ህፃን በነበረበት ጊዜ፣ በዚህም እናቱ በሳጥን በባህር ላይ በሳጥን ጣለችው</u>

20፡39-40 "(ህፃኑን) በሳጥን ውስጥ ጣይው፣ እርሱንም (ሳጥኑን) በባህር ላይ ጣይው፡፡ ለእኔ ጠላት ለእርሱ ጠላት የሆነ ሰው ይይዘዋልና ... ከጭንቅም አዳንንህ ..."

37. <u>በጉባኤ የሚደረገው ፀሎት በግል ከሚደረገው ፀሎት በስንት እጥፍ ይበልጣል?</u>

<u>ሀያ አምስት ጊዜ</u>

ሰሂህ ቡኻሪ 1፡11፡619 "በጉባኤ የሚደረግ ፀሎት በግል ከሚደረገው ፀሎት 25 እጥፍ ይበልጣል፡፡

<u>ሀያ ሰባት ጊዜ</u>

ሰሂህ ቡኻሪ 1፡11፡618 "በጉባኤ የሚደረግ ፀሎት በግል ከሚደረግ ፀሎት 27 እጥፍ ይበልጣል፡፡

38. <u>ዉዱ(ለፀሎት የሚደረግ እጥበት) ስንት ጊዜ ይደረጋል?</u>

<u>አንድ ጊዜ</u> - ሰሂህ ቡኻሪ 1፡4፡159

<u>ሁለት ጊዜ</u> - ሰሂህ ቡኻሪ 1፡4፡160
<u>ሶስት ጊዜ</u> - ሰሂህ ቡኻሪ 1፡4፡161

**39. <u>አልኮል መጠጣት ይፈቀዳል?</u>**

<u>አዎን፣ እንኳን በምድር በገነትም ይገኛል</u>

- 16፡67 "ከዘንባባዎችና ከወይኖችም ፍሬዎች (እንመግባችኋለን)፡፡ ከእርሱ ጠጅና መልካም ምግብን ትሰራላችሁ፡፡"
- 83፡25-27 "(ገነት ውስጥ) ተጣርቶ ከታተመ ጠጅ ይጠጣሉ፣ ማተሚያው ምስክ ከኾነ ... መበረዣውም ከተስኒም ነው፡፡"
- 76፡17 "በእርስዋም መበረዣዋ ዘንጀቢል የሆነች ጠጅ ይጠጣሉ፡፡"
- 47፡15 "(በገነት) ... ለጪዎች ሁሉ ጣፋጭ የሆነች የወይን ጠጅ ወንዞች ከተነጠረ ማርም ወንዞች አሉባት፡፡"

<u>አይፈቀድም</u>

5፡90 "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣኦታትም አዘላምም ከሰይጣን ስራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡"

**40. <u>ቆሞ መጠጣት ይፈቀዳል?</u>**

<u>አይፈቀድም</u>

ሰሂህ ሙስሊም 23፡5017 "ነብዩ ሰዎች ቆመው መጠጣት እንደሌለባቸው አዘዋል፡፡"

<u>ይፈቀዳል</u>

ሰሂህ ሙስሊም 23፡5023 "ለነብዩ ውሀ ስሰጣቸው እንደ ቆሙ ጠጥተዋል፡፡"

ቁርአን ስለራሱ ሲናገር 4፡82 "ቁርአንን በጥንቃቄ አይመረምሩም፣ ከአላህ ሳይሆን ከሌላ ቢሆን ብዙ ልዩነት ባኙበት ነበር፡፡" ይላል፣ ይህን የቁርአን ቃል ከዚህ በላይ ካየነው እውነታ ጋር ስናነፃፅር ቁርአኑ እራሱ ከፈጣሪ አለመሆኑን በራሱ ላይ የሚመሰክርበት እውነታ ነው፡፡

እነዚህን እርስ በርስ ግጭቶች ቁርአን ላይ መመልከታችን፣ ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል መሆኑን ይቅርና በጠንቃቃ ሰው እንኳን አለመፃፉን ያሳያል፣ በርግጥ ለዚህ ችግር ዋናውን ድርሻ የሚይዘው የመሀመድ አለመማርና ቁርአኑን እየረሳ መቸገሩ ነው፣ መጀመርያ ያዘዘውን በፅሁፍ ቢያስቀምጥና ስጋዊ ፍላጎቶቹን ቢገድብ ኖሮ አድሮ ሌላ ቃል ባላወረደ ነበረ ይሁን እንጂ ግን ቁርአን የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

## 2.5. አላህ እና የአይሁድ/ክርስትና አምላክ ተቃራኒ ሀይላት መሆናቸው

በእስልምና "አላህ" ማለት ሁሉን የፈጠረ፣ ሁሉን የሚያውቅ፣ ሁሉን የሚችል፣ በሁሉም ቦታ የሚገኝ(2፡115)፣ ለሰውም ከደም ጋኑ ጅማት ይልቅ የቀረበ(50፡16) አምላክ ነው፣ ቁርአን አላህና የክርስትናው እግዚአብሄር አንድ እንደሆኑ ይናገራል፣

29፡46 "... (የመፅሀፉን ባለቤቶች) አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፡፡"

እንደዚሁ ብዙ ክርስቲያኖችም የቁርአኑ አላህና የመፅሃፍ ቅዱሱ እግዚአብሄር አንድ መሆናቸውንና የስም ልዩነቱም በቋንቋ ልዩነት የመጣ እንደሆነ ያምናሉ፣ ይህቺ መፅሀፍም እስከዚህ ክፍል ድረስ በዚሁ መልክ ስትመለከት ነበረ፡፡

ነገር ግን የሁለቱን ማንነት በዝርዝር ስንመለከት አላህና እግዚአብሄር የተለያዩ እንደውም ተቃራኒ ሀይላት ናቸው፣ ይህንንም ዕውነታ ከአላህ ባህሪ፣ ከሰይጣናት ጋር ባለው ትስስር፣ ለመሀመድ ቁርአን ሲገለጡላቸው በነበሩት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታዎች ውስጥ በምንመለከተው እውነታ፣ ከአላህ ቅድመ እስልምና ማንነትና ከካዕባ ታሪክ አንፃር ስንመለከት አላህና እግዚአብሄር ተቃራኒ ሀይላት ሆነው እናገኛቸዋለን፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 2.5.1. ከባህሪ አንፃር

ትክክለኛው ፈጣሪ የመልካም ነገሮች አፅናፍ ላይ ይገኛል፣ ሰይጣን ደግሞ የክፉ ነገሮች፣ ሰዎች በዚህ መካከል ባለው ቦታ(ልኬት) ላይ ተበትነው ይገኛሉ፣ በዚህ የማንነት ልኬት ላይ የአላህን ማንነት በመመልከት አላህ የሚመደበው ወደ እግዚአብሄር ነው ወይስ ወደ ሌላው የሚለውን ብንመልከት፡-

#### 1. አሳሳችነት

አሳሳችነት የሰይጣን ባህሪ ነው፣ ይህንንም ባህሪውን በቁርአን 38፡82, 7፡20, 20፡120 ... ቦታዎች ላይ እንመለከታለን፣ እንደዚሁ አላህም "አሳሳች" ሲባል እንመለከታለን፡፡

4፡88 “… አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን አላህም ያሳሳተውን ሰው ለእርሱ መንገድ ፈፅሞ አታገኝለትም፡፡”

በዚህም ሁለቱም አሳሳች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

## 2. አጥማሚነት

አጥማሚነት የሰይጣን ባህሪ ነው 15፡39 “(ኢብሊስ አለ) … ሁሉንም አጠማቸዋለሁ፡፡” እንደዚሁ አላህም ይህንን ስራ ሲሰራ እንመለከታለን፡፡

- 11፡34 “ለናንተ ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደሆነ ምክሬ አይጠቅማችሁ፡፡”
- 4፡88 “… አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን አላህም ያሳሳተውን ሰው ለእርሱ መንገድ ፈፅሞ አታገኝለትም፡፡”
- 35፡8 “… አላህ የሚሻውን ሰው ያጠምማል፡፡”

ተመሳሳይ ሀሳቦችን በ7፡186, 39፡36, 74፡31 … ቦታዎች ላይ እናገኛለን፡፡

በዚህም ሁለቱም አጥማሚ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

## 3. አታላይነት

አታላይነት የሰይጣን ባህሪ ነው፣ እንደዚሁ አላህም አታላይነት ስራ እንደሚሰራ እንመለከታለን፣

4፡142 “መናፍቃን አላህን ያታልላሉ፡፡ እርሱም አታላያቸው ነው፡፡”

በዚህም ሁለቱም አታላይ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

## 4. ፈታኝነት

ሰይጣን በሰዎች ላይ ፈተና(ችግር) እንደሚያመጣ የታወቀ ነው፣ አላህም እንደዚሁ ፈታኝ መሆኑ፣

- 21፡35 “ … ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን፡፡”
- 2፡155 “ከፍርሃትና ከረሀብም በጥቂት ነገር፣ ከገንዘቦችና ከነፍሶችም፣ ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን፡፡”

- 18፡7 “እኛ … ልንፈትናቸው …”

በዚህም ሁለቱም ፈታኝ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

5. <u>ከማስተዋል ማዘናጋት</u>

ሰይጣን ልቦናን ያዘናጋል 18፡63 “… ማስታወሱን ሰይጣን እንጂ ሌላ አላስረሳኝም፡፡”፣ እንደዚሁ አላህም ልቡናን የሚዘጋ መሆኑን፣

- 18፡28 “ልቡን እኛን ከማስተዋል ያዘነጋነውን …”
- 17፡46 “(ቁርአንን) እንዳያውቁት በልቦቻቸው ላይ ሽፋንን በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን አደረግን፡፡”

ተመሳሳይ ሀሳቦችም በ18፡57, 47፡23-24, 2፡6, 6፡25 ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህም ሁለቱም አዘናጊ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

6. <u>ማስረሳት</u>

ሰይጣን ሰው እንዲረሳ ያደርጋል(18፡63, 58፡19 …)፣ አላህም እንደዚሁ እንደሚያስረሳ ቁርአን ላይ እነመለከታለን፣

- 2፡106 “ከአንቀፅ ብንለውጥ ወይም እርስዋን <u>ብናስረሳህ</u> …”
- 18፡28 “ልቡን እኛን <u>ከማስታወስ</u> ያዘነጋነውን …”

በዚህም ሁለቱም የሚያስረሱ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት አላህና ሰይጣን በአሳሳችነት፣ በአጥማሚነት፣ አታላይነት፣ በፈታኝነት፣ ልቦናን በመዝጋትና በማስረሳት አንድ መሆናቸውን፣ በዚህም አላህ በየትኛው ወገን ያለ መንፈሳዊ ሀይል እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

### 2.5.2. <u>ከሰይጣን ጋር ባለው ትስስር</u>

ቁርአን ሰይጣናትን በቀጥታ ቢያወግዝም ውስጥ ለውስጥ ግን ሰይጣናቱ የአላህ መልዕክተኛ እንደሆኑ ያሳየናል፣ አንድ ቃል ለምሳሌ ብንመለከት፣

> 2፡102 “… ሰይጣናት ሰዎችን ድግምት የሚያስተምሩ ሲሆኑ ካዱ፡፡ ያንን በባቢል <u>በሁለቱ መላዕክት</u> በሃሩትና በማሩት ላይ የተወረደውን ነገር(ያስተምሯቸዋል)፡፡”

በማለት ሰይጣናትም መላዕክትም ስራቸው አንድ እንደሆነ ቢናገርም የፈጣሪ መላዕክት ግን ድግምት የማይሰሩ በመሆናቸው እዚህ ጋር "መላዕክት" ተብለው የቀረቡት ሰይጣናት መሆናቸውን መላዕክትነታቸውም ለአላህ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ጂኒ፣ የሞት መናፍስትና ጋኔን በስልጣንና በስራ ድርሻ የሚለያዩ የሰይጣን(ኢብሊስ) አይነቶች ናቸው፣ ቁርአኑ ላይ አላህና የእስልምና ቅዱሳን ከነዚህ አካላት ጋር አብረው እንደሚሰሩ ደግሞ በግልፅ ተመልክቷል፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

1. **ጂኒዎች**፡-

ቁርአኑ ጂኒዎችን ላይ በበጎ ጎን እንድንመለከታቸው ለጂኒዎች የስም ማደስ ስራ ሲሰራ እንመለከታለን፣

- ሰሂህ ቡኻሪ 2፡19፡177 "… ነብዩ እንዳሉት፣ አነጂም ሳነብላቸው ተኛሁኝ፣ ከሱም ጋር የተኙት ሙስሊሞች፣ እምነት የለሾች(pagans)፣ ጂኒዎችና የሰው ልጆች በሙሉ ናቸው፡፡"
- 72፡1-2 "… እነሆ ከጂን የሆኑ ጭፍሮች (ቁርአንን) አዳመጡ፡፡ እኛ አስደናቂ … ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን (ቁርአን ሰማን)፡፡ በእርሱ አመንን፣ አሉ፡፡"

ተመሳሳይ ሀሳብም ሰሂህ ቡኻሪ 5፡58፡199 ላይ እንመለከታለን፡፡

መሀመድ ከጅኒዎች ጋር በነበረው መልካም ግንኙነትም ሰዎች ጂኒዎችን የሚጎዳ ስራ እንዲያቆሙ ሲያዝ ነበረ፣

- አቡ ዳውድ 39 "… የጅኒ ተወካዮች ወደ ነቢዩ መጡና ነቢዩን፣ መሀመድ ሆይ ተከታዮችህን በኩበት፣ ከሰልና አጥንት ራሳቸውን እንዳያፀዱ ንገርልን፣ እነዚህ ለኛ የተሰጡ ናቸው፣ አሉት፡፡"
- ጃሚያ አት ትርሚዚ 18 "… የአላህ መልዕክተኛ እንደተናገሩት፣ በኩበትም ሆነ በአጥንት እስቲንጃ አታድርጉ የወንድሞቻችሁ የጅኖች ምግብ ነውና፡፡"

እዚህ ጋር "ከሰል፣ ኩበትና አጥንት" የሚሉት ቃላት የቀረቡት በመንፈሳዊ ትርጉም ነው ምክንያቱም ጅኒዎቸ በአይን የማይታዩ መንፈሳዊ ፍጡራን ስለሆኑ፣ መንፈሳዊ ፍጥረት ቁሳዊ ምግብ አይበላም ነገር ግን እዚህ ጋር መመልከት የተፈለገው ጅኒዎች በእስልምና ያለቸውን ቦታ ነው፡፡

በአጠቃላይ በእስልምና ጂኒዎች በመልካም ስም የሚነሱና ሙስሊሞች እነሱን መጉዳት እንደሌለባቸው እንመለከታለን፡፡

2. <u>የሞት መናፍስት፡-</u>

ዋናው ፈጣሪ ሰው በተሰጠው እድሜው በህይወት እንዲኖር ፈጠረው ነገር ግን የዚህ ፈጣሪ ተቃራኒ የሆነው ሰይጣን የሰው ልጆች በተሰጣቸው እድሜ እንዳይኖሩ ቀድሞ ይቀጥፋቸዋል፣ አላህም ከነዚህ ቀጣፊዎች ጋር አብሮ እንደሚሰራ ቁርአኑ ይናገራል፣

- <u>ከሞት መላዕክት ጋር አብሮ እንደሚሰራ</u>
  6፡100 "<u>ለአላህ አጋንንትን የፈጠራቸው</u> ሲሆን ... ወንዶች ልጆችንና ሴቶች ልጆችንም ... <u>ለዕርሱ ቀጠፉ</u>፡፡"
- <u>ከነፍሰ ገዳይ ሰዎች ጋር አብሮ እንደሚሰራ</u>
  በ2.3.2.4 ክፍል እንደተመለከተው የአላህ ቃል የሆነው ቁርአን ሰዎች በጂሀድ እንዲጋደሉ ያዛል፣ ከማዘዝም አልፎ ደግሞ በዚህ መጋደል ውስጥ ስለሚገደሉት ሰዎች ሀላፊነቱ የአላህ መሆኑን ይናገራል፣
  8፡17 "አልገደላችሃቸውም ግን አላህ ገደላቸው፡፡ (ጭብጥ አፈር) በወረወርክ ጊዜ አንተ አልወረወርክም፡፡ ግን አላህ ወረወረ (ወደ አይኖቻቸውም አደረሰው)፡፡"

  ብዙ ጊዜ ጂሀዲስቶች ጂሀዳዊ እርምጃቸውን ሲወስዱ "በአላህ ስም" ይላሉ፣ ብዙዎችም እንዲህ ተብለው ነው የተገደሉት፣ የአይኤስ ግድያዎች፣ በቱርክ የሩሲው አምባሳደር፣ በሊቢያ የተገደሉት ኢትዮጵያውያንና ግብፃውያን፣ ሀማስ ወደ እስራኤል ሮኬት ሲያስወነጭፍ ... "አላህ ከበር" ብለው ነው፡፡

- አላህም የሞት መናፍስቱን ስራም እንደሚሰራ
  - 17፡16-17 "ከተማን ለማጥፋት **በፈለግን** ጊዜ ባለፀጋዎች እናበዛለን፡፡ በውስጧም ያምፃሉ፡፡ በእርስዋ ላይ ቃሉ(ቅጣቱ) ይፈፀምባታል፡፡ ማጥፋትንም እናጠፋታለን … ከክፍለ ዘመናት ሰዎች ያጠፋናቸው ብዎች ናቸው፡፡"
  - 32፡26 "(አላህም) ከክፍለ ዘመናት ሰዎች ብዙዎችን ያጠፋን መሆናችንን … "
  - 38፡3 "ከእነርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦችን ብዙን አጥፍተናል፡፡"

በአጠቃላይ ስንመለከት አላህ ከሞት መናፍስትና ከነፍሰ ገዳይ ሰዎች ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑና እራሱም ይህንን የሰው ነፍስ ማጥፋት ስራ እንደሚሰራ እንመለከታለን፡፡

## 3. አጠቃላይ ሰይጣናት/ጋኔኖች፡-

አላህ ከጂኒዎችና ከሞት መናፍስቱ በተጨማሪ ከአጠቃላይ የሰይጣን ዘሮች(ጋኔን፣ አጋንንት …) ጋር አብሮ እንደሚሰራ ቁርአኑ ይናገራል፡-

- የአላህ መልዕክተኞች መሆናቸው
  19፡83 "እኛ ሰይጣናትን በከሀዲዎች ላይ (በመጥፎ ስራ) ማወባራትን(ለክፉ ማነሳሳት) የሚያወባሩዋቸው ሲኾኑ የላክን መሆናችንን አላየህምን፡፡"
- ከነብዩ ጋር ቅርበት ያላቸው መሆኑን
  72፡19 "እነሆም የአላህ ባሪያ (ሙሀመድ አላህን) የሚጠራ ሆኖ በተነሳ ጊዜ (ጋኔኖች) በእርሱ ላይ ድርብርቦች ሊኾኑ ቀረቡ፡፡"
- [20] "የእስልምና ቅዱሳኑን" ሲረዱ የነበረ መሆኑ
  - 34፡12 "… (ለሱሌይማንም) … ከጋኔኖችም በጌታው ፍቃድ በፊቱ የሚሰሩትን (አደረግንለት)፡፡"

---

[20] እዚህ ጋር "የእስልምና ቅዱሳን" የተባለበት ምክንያት፣ ምንም እንኳን ሱሌይማን የመፅሀፍ ቅዱሱ ሰሎሞን እንደሆነ፣ ዳውድ ደግሞ ዳዊት እንደሆነ ቢነገርም መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ሰለሞንና ዳዊት ከጋኔናችና ከሰይጣናት ጋር አብሮ መስራታቸውን የሚናገር ቃል ስለሌለ ነው፡፡

- 21፡82 "ከሰይጣናትም ለርሱ(ለሱለይማን) (ሉልን ለማውጣት) የሚጠልሙንና ከዚያም ሌላ ያለን ስራ የሚሰሩትን (ገራንለት)፣ ለእነሱም ተጠባባቂዎች ነበርን፡፡"
- 27፡15-17 "ለዳውድና ለሱለይማን ዕውቀትን በርግጥ ሰጠናቸው… ሱለይማንም ሰራዊቶቹ ከጋኔን፣ ከሰውም፣ ከበራሪ የሆኑትም ተሰበሰቡ፡፡ እነሱም የከመከማሉ፡፡"

በአጠቃላይ ጂኒዎች ቁርአንን መውደዳቸው፣ ማዳመጣቸው፣ ነብዩም ጂኒዎችን "ወንድሞቻችሁ ናቸው" ማለቱና የጅኒዎችን ጥቅም እንዳይነካ መከልከሉ፣ አላህና የእስልምና ቅዱሳንም ከጅኒዎች በተጨማሪም ከአጠቃላይ ጋኔኖች፣ አጋንንት፣ የሞት መናፍስትና ሰይጣናት ጋር አብረው የሚሰሩ መሆናቸውን ስንመለከት ጂኒ፣ የሞት መናፍስት፣ ጋኔን፣ አጋንንት፣ ሰይጣንና አላህ አንድ ወገን መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

### 2.5.3. ለመሀመድ ቁርአን ሲገለጡላቸው በነበሩት መንገዶች፣ ጊዜና ቦታዎች ውስጥ የምንመለከተው እውነታ

ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ የአንድን ነገር ማንነት ለማጥናትና ለማወቅ የሚረዱን ዋነኛ መስፈርቶች ናቸው፣ በዚህም አላህ ሲገለጥበት የነበረበትን ጊዜ ቦታና ሁኔታ በመመልከት የአላህን ማንነት ስንመለከት፣

- ቁርአን የተገለጠበት ጊዜ

97፡1 "እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው፡፡ መወሰኛይቱም ሌሊት ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ፣ መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺ ወር በላጭ ናት፡፡ በርስዋ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ፡፡ እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት፡፡"

እዚህ ጋር "ሌሊት" የሚለው ቃል የተተረጎመው በቀጥተኛ ትርጉም ሳይሆን በመንፈሳዊ ትርጉሙ ነው ምክንያቱም ቁርአኑ የወረደው በአንድ ሌሊት ሳይሆን በረዥም የጊዜ ሂደት ስለሆነ(25፡32, 17፡106, 3፡3)፡፡

በመንፈሳዊው አተረጓጎም ሌሊትና ቀን የተለያየ ትርጉም አላቸው፣ በቀን የሚሰራው "ማንንም የማይፈራው" ማለት ነው፣ በሌሊት የሚሰራው

“ተደብቆ የሚሰራ” ማለት ነው፣ በዚህም ቁርአኑ የወረደው በመንፈሳዊ ሌሊት መሆኑ ቁርአኑ ከዋናው አምላክ ሳይሆን በድብቅ ከሚሰራው የዋናው አምላክ ተቃራኒ መንፈሳዊ ሀይል መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በእስልምና ውስጥ ዋና ዋናዎች ክስተቶችና ስነስርአቶች ከሌሊት ጋር የተያያዙ ናቸው፣ እስልምናው ለጊዜ መቁጠርያ፣ ለፆም መያዣና መፍቻ እንዲሁም ለሀይማኖቱ አርማነት የሚጠቀሙት ሌሊት የምትነግሰው ጨረቃን ነው፣ ይባሱኑ እውነታውን በመቃረንም ጨረቃ አብሪ፣ ፀሀይ አንፀባራቂ(10፡5) ይላል፣ ነብዩ መሀመድም “ቡራቅ” የተባለውን አውሬ የሚጋልቡት በለሊት ነው(ሰሂህ ቡኻሪ 5፡57፡22, ሰሂህ ሙስሊም 1፡309...)፡፡

በዚህ የእስልምናና የሌሊት ጥብቅ ግንኙነት ውስጥ የአላህን ማንነት እንመለከታለን፡፡

- <u>ቁርአን የተገለጠበት ቦታ</u>

ፈጣሪ ለሙሳ ተውራት(ኦሪትን) የሰጠው በተራራ ላይ ነበረ(ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡162)፣ መሀመድ ቁርአንን የተቀበለው “ሂራ” በሚባል ዋሻ ውስጥ ነው(ሰሂህ ቡኻሪ 1፡1፡3)፣ ይህ የመንፈስ አሰራር ተቃርኖን ያሳያል፡፡

አላህ የት እንደሚኖር ስንመለከትም ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡421 “... ፀሀይ ስትጠልቅ የአላህ ዙፋን ስር ገብታ <u>እስከትተኛ</u> ትሄዳለች ...” ማለቱና 18፡85-93 “... ወደ ፀሃይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት፡፡” በሚለው አነጋገር ውስጥ የፀሀይን ነገር ትተን (ምክንያቱም ፀሀይ ዓለምን ትዞራለች እንጂ የምትገባበት ጉድጓድ የላትምና) ሁለቱን ቃላት በአንድ ላይ ስንመለከት አላህ የሚገኘው መንፈሳዊ ስሙ “የጥቁር ጭቃ ምንጭ” በተባለው ቦታ ነው፣ ይህ ደግሞ አላህ ዋናው ፈጣሪ ሳይሆን አንድ አካባቢን የሚገዛ መንፈስ መሆኑን ያሳያል፡፡

- <u>ቁርአን ሲገለጥ የነበረበት ሁኔታ</u>

ነብዩ መሀመድ የቁርአን እንዴት ሲገለጥላቸው እንደነበረ ሲናገሩ

ሰሂህ ቡኻሪ 1፡1፡2 “... <u>ዋናዎቹ</u> መልዕክቶች የሚመጡልኝ በደወል ድምፅ ነው ...”

ሀዲሳቱ የደወልን ድምፅ የሚገናኘው ከሰይጣን ጋር እንደሆነ ይናገራሉ

> ሰሂህ ሙስሊም 24፡5277-5279 "... ደወል የሰይጣን የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡"

በዚህም በደወል ድምፅ የሚናገረው ማን እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

እነዚህን ቁርአን የወረደበት ጊዜና ቦታና ሁኔታ በአንድ ላይ ስንመለከት አላህ ማለት ዋናው ፈጣሪ አለመሆኑን ይባሱኑም የዚህ የዋናው ፈጣሪ ተቃራኒ መንፈስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 2.5.4. ከአላህ ቅድመ እስልምና ማንነት

[21] "አላህ" የሚለው ስም የመጣው "አል-ኢላህ" የሚለውን የጣዖት ስም በማሳጠር ነው፣ በአረቡ አካባቢ "ኢላህ" የሚባል ጣኦት ሲመለክ እንደነበረ የአቡ ዳውድ ሱና 4272 እና 4273 ላይ እንመለከታለን፡፡ ዛሬም በእስልምና "ኢላህ" የሚለው አሪጂናሉ የጣዖት ስም "እርኩስ" ተብሎ አለመተውና ይባሱኑ "ቅዱስ" ተደርጎ ትርጉሙ "አምላክ ማለት ነው" በማለት፣ "ላ ኢላህ ኢል አላህ" እያለ ሙስሊሙ ለአላህ ያለውን እምነት በየጊዜው እየደጋገመ የሚናገርበት ቃል መሆኑን ስንመለከት አላህና ኢላህ አንድ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

[22] "በአካባቢው የተጠኑትን የአርኪዎሎጂ ግኝቶችንና መሃመድ በመካ የተመለከታቸው ሶስቱን ሴት አማልክት "አል-ለት፣ ዑዛ እና መናት"(53፡19-20)፣ የ"አል-ኢላህ" (በአሁኑ አጠራር "አላህ") የሚባለው አምላክ ልጆች ነበሩ፡፡"

በዚህም አላህ ማለት ኢላህ የተባለው አረብ አካባቢ ሲመለክ የነበረ ጣዖት ነው፡፡

---

[21] https://en.m.wikipedia>wiki>Allah

[22] ዳግማዊ ኃይለ ስላሴ(2008)፣ **ኢስላም ምንድነው? ክርስትናስ?**፣ ገፅ 74

### 2.5.5. ከ“ካዕባ” ግንባታና አምልኮ ታሪክ

እንደ እስልምና አስተምህሮ ካዕባ የመጀመሪያው መዝጊድ(3፡96) መሆኑና ያሰራውም ኢብራሂም(2፡127, ሰሂህ ቡኻሪ 4፡55፡583) መሆኑ ይነገራል፣ እውነታውን ስንመለከት ግን ከአባ ከኢብራሂም ታሪክ ጋር አይገናኝም፡-

1. መዝጊድ የእስልምና ማምለኪያ ቦታ ነው፣ መሀመድ ደግሞ የሙስሊሞች መጀመሪያ ነው(22፡52, 6፡163, 39፡12, 6፡14)፣ በዚህም ከመሀመድ ከብዙ ዘመናት በፊት የነበረው ኢብራሂም ከእስልምና ጋርም አይገናኝም የካዕባን መዝጊድም አላሰራም፣
2. ከአባ የሚገኘው በሳውዲ ውስጥ ነው፣ መሃመድም የተላከው ቀድሞ ፈፅሞውኑ መልዕክተኛ ላልተላከላቸው (28፡46, 32፡3, 34፡44, 36፡ 2-6) እና በስህተት ውስጥ ለነበሩ ለዓረብ ህዝቦች(62፡2) እንጂ እንደ ኢብራሂም ያሉ ነቢያት ለተላኩለት ምድር አይደለም፣

በዚህም የመፅሀፍ ቅዱሱ አብርሀም ከከአባ ታሪክ ጋር እንደማይገናኝ እንመለከታለን፡፡

ስለ ካዕባ ግንባታ ታሪክ ቁርአኑን በደንብ ስንመለከተው ካዕባ የተሰራው በኢብራሂም ሳይሆን በቁረይሽ ሰው መሆኑን እናስተውላለን፣

> 106፡1-4 “ቁረይሽን ለማለመድ(ባለዝሆኖቹ አጠፉ)፡፡ የብርድና የበጋን ወራት ጉዞ ሊያላምዳቸው ይህንን ሰራ፡፡ ስለዚህ የዚህን ቤት (የከዕባን) ጌታ ይገዙ፡፡ ያንን ከረሃብ ያበላቸውን ከፍርሀትም ያረካቸውን (ጌታ ያምልኩ)፡፡”

በዚህም ካዕባ ከመፅሀፍ ቅዱሱ አብርሃም እንዲሁም ከነባሩ የአይሁዳውያን እምነት ጋር አይገናኝም ነገር ግን ካዕባን ከአብርሀም ጋር ማገናኘቱ ያስፈለገው ሰዎች ጣዖትን እግዚአብሄር አድርገው እንዲያመልኩ ለማድረግ ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

1. ካዕባ ከእስልምና በፊት የቁረይሽ ህዝቦች ለአምልኮ ሲጠቀሙበት የነበረ ስፍራ ነው(ሰሂህ ሙስሊም 43፡7179, 106፡1-4)፣

2. መሀመድም ለነዚህ ጣኦት አምላኪ ህዝቦች ቁርአንን ይዞ ሲመጣ

- ነባሩን የቁረይሾችን የጣዖት አምልኮ ስፍራ "ካዕባ"ን አለማፍረሱና ይባሱኑ "የአላህ ቤት"(2፡158,106፡1-4) ማለቱ፣
- ወደ ኢየሩሳሌም የነበረውን ስግደት(ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡13) ወደዚህ ካዕባ አቅጣጫ መቀየሩ(2፡144-145)፣
- ነባሩን በካዕባ "ሶፋና መርዋ" መካከል የነበረውን የጣዖት አምልኮ ስነስርአት በእስልምና መምጣት እንዳይተው ማዘዙ(ሰሂህ ቡኻሪ 6፡60፡22 – 6፡60፡23,2፡158 ...)
- በካዕባ ውስጥ የሚመለከውን ዋናውን ጣዖት "ጥቁር ድንጋይ" መሳለሙና ሌሎችም እንዲሳለሙት ማድረጉ(ሰሂህ ቡኻሪ 2፡26፡667)
- "ኢላህ" የሚባለውን የጣዖት ስም መልሶ ቅዱስ ቃል ማድረጉን

ስንመለከት ነብዩ መሀመድ በአይሁድ/ክርስርትና ሀይማኖት ስም ትልቅ ሽወዳ መስራቱን እንመለከታለን፣ በሽወዳውም በካዕባ የሚኖረውን(2፡158) እና በጂኦግራፊ(በአካባቢ) የተወሰነው "የዚህች ሀገር ጌታ" የተባለው(27፡91) የቁረየሽ አምላክ "አላህ" ዋናው ፈጣሪ አምላክ ተደርጎ እንዲመለክ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ከላይ የተመለከትናቸው የአላህ ባህሪ ከሰይጣን ባህሪ ጋር መመሳሰል፤ አላህ ከጂኒ፣ አጋንንት፣ ሰይጣን፣ ጋኔን፣ የሞት መናፍስት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑ፤ ቁርአኑ ለመሀመድ የተገለጠበት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ሰይጣናዊ መሆኑ፤ ከአላህ ቅድመ እስልምና ታሪክና ከካዕባ የግንባታ ታሪክ "አላህ" በአካባቢው ቁረይሾች ድሮም የሚያመልኩት ጣዖት መሆኑን እንረዳለን፡፡

## <u>ማጠቃለያ(እስልምና)</u>

ቆም ብሎ ላስተዋለ ሰው <u>አንድ እውነታ ከመጀመርያው ጀምሮ በቋሚነት እየተደጋገመ ይገኛል</u>፣ ነብዩ መሀመድ በእስራኤል ነብያት መንገድ ነኝ ብሎ በተቃራኒ መንገድ መሄዱ፣ ቁርአን “የፈጣሪ ቃል” ተብሎ ውስጡ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑ እንዲሁም “አላህ እግዚአብሄር ነው” ተብሎ የእግዚአብሄር ተቃራኒ ሀይል መሆኑን፤ መቸም ዋናው ፈጣሪ እንደዚህ አይነት ድብብቆሽ እንደማይሰራ እሙን ነው፣ እንደዚህ አይነት ድብብቆሽ የሚሰራው እንደ ፈጣሪ መመለክ የሚፈልገው መንፈስ ነው፣ እሱም ከላይ ከነፀባዩና ማንነቱ የተመለከትነው የቁረይሾች ጣዖት ነው፡፡

በዚህም ሙስሊሙ ማህረሰብ፣ መሀመድ የሰራውን ህገወጥ በቁረጥ ወደ ቀደመው መንገድ መመለስ ይገባዋል፣ ይህም መንገድ ነብዩ፣ ቁርአኑና አላህ ተመሳስለው የተነሱበት የክርስትናው መንገድ ነው፣ በክርስትና ስር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም ትክክኛዋ ቤተክርስቲያን የትኛዋ ናት? የሚለውን በቀጣይ ምዕራፎች ውስጥ በሰፊው እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. ከክርስትና በመውጣት ሌላ ሀይማኖት የተከተሉ

በዚህ ምዕራፍ ስር የምንመለከተው በክርስትና እምነት ተቋማት ስር የነበሩ ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ከክርስትና በመውጣት ሌላ ሀይማኖትን መስርተው የወጡትን ቡድኖች ነው፣ በዚህም

- ሀይማኖትን ከማህበረሰብ ጋር በማያያዝ፣
  - ነባሩን ባህላዊ ሀይማኖት በዘመናዊ ፍልስፍና በማደራጀት በዘመናዊ መልክ የተቋቋመው "ዘመናዊ ዋቄፈና"
  - ክርስትናን በራሳቸው ማህበረሰብ እሴት የቀረፁት "ራስተፈሪያን"፣
- እንደ ቁርአን ከመፅሀፍ ቅዱሱ በኋላ "በተላከላቸው ቅዱስ መፅሀፍ" ከክርስትና የወጡ (ባኢ፣ ሞርሞኒዝም፣ ሺንቼአንጂ፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒስት፣ የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴና የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን)

ሲሆኑ ሁሉንም በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 3.1. ከክርስትና ወደ ማህበረሰባዊ ሀይማኖት የተመለሱ

ነብዩ መሀመድ ሀይማኖትን ከማህበረሰብ ጋር በማያያዝ ለአረቡ ማህበረሰብ የተላከው እስልምና እንደሆነ አሰተምረዋል፣ በተመሳሳይ መንፈስም አንዳንዶች ክርስትናንም ከዘር ጋር በማገናኘት ከክርስትና ወደ ራሳቸው ማህበረሰባዊ ሀይማኖት ተመልሰዋል፣ ከነዚህ ማህበረሰባዊ ሀይማኖቶች መካከል ለምሳሌ ያህል ዘመናዊውን ዋቄፈናንና የራስ ተፈሪያንን ሀይማኖት እንመለከታለን፡፡

### 3.1.1. ዘመናዊ ዋቄፈና

እንደ ዋቄፈና አስተምህሮ "ዋቄፈና ቀደምት የኦሮሞ ብሄረሰብ ባህላዊ ሃይማኖት ነው፣ ይሁን እንጂ በአፄ ሚኒሊክ መንግስት ጫናና በኦርቶዶክስና እስልምና ሀይማኖቶች መስፋፋት ምክንያት ሀይማኖቱ ሙሉ በሙሉ በነዚህ ሁለቱ ሀይማኖቶች ተወረሰ፡፡"

ከረዥም ዘመናት በኋላ የኦሮሞ ህዝብ ብሄራዊ ማንነቱ ሲከበርለት፣ ብሄሩ ለዘመናት በነበረበት ጭቆና ለመጥፋት ተቃርበው የነበሩትን ማንነቶቹን ይህም ቋንቋው፣ ባህሉ፣ አስተዳደርዊ ስርአቱ … መልሶ እየገነባ ይገኛል፣ ነገር ግን በዚህ የብሄርን ማንነት መልሶ የመገንባት ሂደት ውስጥ ዋቄፈታዎች ሀይማኖትን የብሄር ማንነት በማድረግ የዋቄፈና ሀይማኖትንም ከብሄሩ ማንነት ጋር መልሶ በመገንባትና በዘመናዊ መንገድ በማደራጀት ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህም [23]በ1996 ዓ.ም በነ አቶ ድርቢ ደምሴ ጥረት ዋቄፈና በፍትህ ሚኒስቴር እንደ አንድ ሀይማኖት "የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች ማህበር" በሚል እውቅናና የምስክር ወረቀት አግኝቷል፣ ከዚህ ጊዜም ጀምሮ ዋቄፈና እንደ ሀይማኖት በዘመናዊ መልክ ተደራጅቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ምንም እንኳን ባህላዊው ዋቄፈና እንደ የትኛውም ባህላዊ ሀይማኖት ዓለማቀፋዊውን ዕይታ ያለመያዝ ውሱንነቶች የነበሩበት ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በዘመናዊ መልክ የተደራጀው ዘመናዊው ዋቄፈና ግን ከባህላዊዎቹ በተለየ እንደሌሎቹ ዓለማቀፍ ሀይማኖቶች ራሱን በዓለማቀፋዊ ፍልስፍና አደራጅቷል፡፡

በዚህም ዘመናዊው ዋቄፈና "ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ ነው፣ አይሁድ፣ አረብ … ይህንን አምላክ በራሳቸው ዕሴት እንደሚያመልኩት ኦሮሞም ይህን አምላክ በራሱ እሴት ያመልካል" ይላሉ፣ በዚህም ዘመናዊው ዋቄፈና ከባህላዊ ሀይማኖቶች ተለይቶ ከአብርሃም ሀይማኖቶች የተመሳሰለበትን ፍልስፍና እንመለከትበታለን፡፡ ዘመናዊው ዋቄፈና በዚህም አስተምህሮቱም ብዙ ክርስቲያኖችን ወደ ራሱ መመለስ የቻለ ሲሆን

---

[23] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 50-54

ብዙዎችን ደግሞ ግራ በማጋባት በክርስትናና በዋቄፈናነት መካከል እንዲዋልሉ አድርጓቸዋል፡፡

በዚህ ምዕራፍም፣

- የዘመናዊው ዋቄፈና ሀይማኖታዊ ቁመና፣
- ሀይማኖቱ ለመስፋፍያነት የተጠቀመው ዘዴዎች፣
- ሀይማኖቱ ከክርስትና ጋር ያለውን ሽኩቻ፣

በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 3.1.1.1. <u>የዘመናዊው ዋቄፈና ሀይማኖታዊ ቁመና</u>

ማንኛውም የሀይማኖት ተቋም እንደ ሀይማኖት ተቋምነቱ ሀይማኖታዊ ቁመና ሊኖረው ይገባዋል፣ በዚህ መሠረት ዘመናዊውን ዋቄፈናን በሀይማኖታዊ መስፈርቶች እንመለከታለን፣ በዚህም ሀይማኖቱ የሚመራበት መዋቅር፣ መዋቅሩንም የሚመሩ የሀይማኖት መሪዎችን፣ የሀይማኖቱ የማምለኪያ ስፍራ፣ የአምልኮ ፕሮግራም እና ሀይማኖቱ የሚመራበት ቅዱስ መፅሀፍ ሁኔታን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

ዋቄፈና እንደ አንድ ሀይማኖታዊ ድርጅት ሀይማኖታዊ ፍቃድ ያውጣ እንጂ ሀይማኖቱ እንደ አንድ ሀይማኖታዊ ድርጅት የሚመራበት ሀይማኖታዊ መዋቅር የለውም፣ የዋቄፈና ሀይማኖት ፕሬዚዳንት ማን ነው? አይታወቅም፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌ ደረጃ ያለው የሀይማኖቱ መዋቅርም አይታወቅም፣ የሚከተለው የአመራር አይነት አይታወቅም፣ ማንም ስለ ዋቄፈና ሀይማኖት የሚያስበው በኢሬቻ በአል ቀን ብቻ ነው፣ በዚህም ሀይማኖቱ “ሀይማኖታዊ ድርጅት” ይባል እንጂ ውስጡ ሀይማኖታዊ ቁመና የለውም፡፡

ለሀይማኖታዊ ስነስርአት ማስኬጃም አንድ ሀይማኖት ራሱን የቻሉ የሀይማኖት መሪዎችና የመሪዎች ማፍለቂያ ማዕከላት ሊኖሩት ይገባል፣ ዛሬ ላይ የዋናው ዋቄፈና ሀይማኖት መሪ ማን እንደሆነ አይታወቅም፣ ምን አይነት አገልጋዮች እንደሚጠቀም አይታወቅም፣ ለምሳሌ ቄስ፣ ዲያቆን፣ ፓስተር፣ መሪጌታ … ራሳቸውን ለሀይማኖታዊ አገልግሎት የለዩ ሰዎች የሉትም፡፡ ዋቄፈና ይህንን ችግሩን ለመፍታት አባ ገዳዎችን እንደ ሀይማኖት መሪ

እየተጠቀመ ይገኛል፣ ይሁን እንጂ ገዳ አስተዳደራዊ ስርአት እንጂ የሀይማኖት ተቋም አይደለም፡፡

ዋቄፈና እንደ አንድ የሀይማኖት ተቋም የኢሬቻ በአል ከሚከናወንበት ቦታ ውጪ ቋሚ ማምለኪያ ቦታም ሆነ ፕሮግራም የለውም፣ በዚህም በተለይ ታች ላለው ለብዙሀኑ ህብረተሰብ ተደራሽ አይደለም፣ የሀይማኖቱ ተከታዮቹ በሞት፣ በውልደት … የሚፈልጉትን ሀይማኖታዊ አገልግሎት እየሰጣቸው አይደለም፡፡ በዋቄፈና ወጥ ሳምንታዊ ወይ በየቀኑ የሚከናወኑ የአምልኮ ፕሮግራሞች የሉትም፣ ሀይማኖቱ በኢሬቻ ክብረ በአላቶቹ ጊዜያት ካለው ፕሮግራም ውጪ እንደ ሀይማኖት ምዕመኑን የሚያገለግልበት አምላኩንም የሚያመልክበት ቋሚ ፕሮግራም የለውም፣ በዚህም ዋቄፈና = ኢሬቻ ሆኖ እንመለከተዋን፡፡

ከመንፈሳዊ መፅሀፍም ጋር በተያያዘ ዋቄፈና እንደ ክርስትና፣ እስልምና፣ ሂንዱ … ሀይማኖቶች ወጥ በሆነ መንገድ የሚመራበት የራሱ ቅዱስ መፅሀፍ የለውም ይባሱኑም የሀይማኖቱ ምሁራን እንደዚህ አይነት መፅሀፍ ሊኖር እንደማይገባ ይናገራሉ [24] "ፈጣሪና ሰው አይነጋገሩም … እንደዚህ ማለትም ነውር ነው … ፈጣሪ ሰዎች የሚያስቡበትን አእምሮና "አያንቱማ"(መንፈሳዊ ሀይል) ይሰጣል እንጂ … ከፈጣሪ በቃልም በመፅሀፍም መቀበል የሚባል አሰራር የለም፡፡" ይላሉ፡፡

ነገር ግን ሌሎቹ ሀይማኖቶች ጋር የምንመለከተው መፅሀፍም በፈጣሪ ተፅፈው የወረዱ ሳይሆን በዋናነት ፈጣሪ መንፈሳዊ ሀይል በሰጣቸው ሰዎች የተፃፉ ናቸው፣ በዚህም ዋቄፈና "መፅሀፍ አያስፈልግም" ከሚል "አያንቱ" የሚላቸው ሰዎች ጋር ያለውን መንፈሳዊ ዕውቀት በመፅሀፍ አለማዘጋጀቱን በድክመት መቀበል አለበት፡፡

ሀይማኖቱ ቅዱስ መፅሀፍ ማጣቱና በሰዎች አሉታ ላይ ተመስርቶ መመራቱ የመጀመሪያ ሀይማኖቱ አዋቂዎች ዘንድ የነበረው ዕውቀት በአእምሮ እየተያዘ ለሁሉም ትውልዶች መተላለፍ አይችልም፣ ምክንያቱም የሰው ልጅ ባለበት ደካማነት ሁሉንም እውቀት እንደ ኮምፒውተር ሙሉ በሙሉ ገልብጦ

---

[24] Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa**, fuula 25

“Copy Paste” አድርጎ መያዝ አይችልም፣ ይባሱኑ ሃይማኖቱ በክርስትናና በእስልምና አስተምህሮቶች ተፅዕኖ ስር ወድቆ በነበረበት ሁኔታና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ሃይሎች ግራኝ አህመድ፣ ዮዲት ጉዲት … በተፈራረቁበት ተፅእኖዎች ጠፍቶ አሁን ባለው በፖለቲካው ይሁኝታ ነፍስ በዘራበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ እምነቱና አስተምህሮቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲዋረድ መጥቷል አያስብልም፡፡

በዚህም በሀይማኖቱ ላይ ብዙ የዕውቀት ክፍተቶችን እንመለከታለን፣ በቀላል ምሳሌ እንኳዋን ብንመለከት ዛሬ ላይ በሀይማኖቱ ላይ ብዙ ጥናትና ምርምር ያደረጉ፣ ሀይማኖቱን በመንግስት ደረጃ ሰርተፊኬት ያስገኙትን የሀይማኖቱ መሪዎችን ስለ ሀይማኖቱ ፍልስፍና ያላቸው ዕውቀት ውሱን ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- [25] “ሰይጣን የሚባል መኖሩን አናውቅም”
- [26] “ፈጣሪ ሰውን ይምሰል አይምሰል አናውቅም”
- [27] “ከሞት በኋላ ህይወት ይኑር አይኑር አናውቅም”

ሲሉ እንመለከታለን፣ የሀይማኖት መሪ ሆኖ “አናውቅም” ያመጣው ደግሞ ይኸው የመንፈሳዊ መፅሀፍ አለመኖር ነው፡፡

ሀይማኖቱ ቅዱስ መፅሀፍ በማጣቱ ምክንያት በሀይማኖቱ ዙርያ አንድ አከራካሪ ነገር ሲነሳ መዳኘት እስከማይቻልበት ደረጃ ይደርሳል፣ ለምሳሌ በኢሬቻ በአል አከባበር ዙሪያ እርድ፣ ደም/አራቄ ሃይቅ/ወንዝ ውስጥ ማፍሰስ፣ ዛፍ ቅቤ መቀባት፣ የወንድ ብልት ቅርፅ በጭንቅላት ላይ ማሰር … አከራካሪ ጉዳዮችን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም የሽማግሌዎቹ ጎራ ለትክክኘነቱ ሲሟገቱ ዘመነኞቹ ደግሞ ከክርስትና እውቀታቸው በመነሳት “ተው ይሄ ሰይጣናዊ አሰራር ነው” በማለት የሚያወግዙበትና ፖሊስ መሃላቸው እስኪገባ ድረስ ሽኩቻ በመካከላቸው ሲፈጠር እንመለከታለን፣ የትኛው ነው

[25] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 31, 68
[26] Ibid, fuula, 172
[27] ibid, fuula 35,40,68, 172

ትክክለኛው? መፍረድ አይቻልም ምክንያቱም ሀይማኖቱ ቅዱስ መፅሀፍ ስለሌለው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ሀይማኖቱ እንደ ሀይማኖት ተቋም ሀይማኖታዊ መዋቅር ማጣቱ፣ ሀይማኖታዊ መሪዎች ማጣቱ፣ ተደራሽ ማምለኪያ ቦታዎችና ሀይማኖታዊ ፕሮግራሞች ማጣቱ እንደዚሁም ሀይማኖቱ የሚመራበት ቅዱስ መፅሀፍ ማጣቱ ዋቄፈናን “ሀይማኖት” ለማለት አያስችልም ነገር ግን ሀይማኖቱ በነዚህ ጉድለቶቹ ውስጥ ብዙ ምዕመናንን ሊሰበስብ የቻለው ከሀይማኖታዊ ጉዳዮች ይልቅ በሌሎች ምክንያቶች ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 3.1.1.2. <u>ዘመናዊው ዋቄፈና ለመስፋፍያነት የተጠቀመው ዘዴዎች</u>

ዋቄፈና ምንም እንኳን ሀይማኖታዊ አቋም ባይኖረውም ነገር ግን በአንድ ጊዜ ብዙ ተከታዮችን ከክርስትናው መውሰድ ያስቻለውንና ሌሎችም በሱ ላይ ትችት መሰንዘር እንዳይችሉ ያደረገው ወሳኝ እስትራቴጂዎችን በመከተሉ ነው፣ እነዚህ እስትራቴጂዎቹም፡-

- የሀይማኖቱ መሪዎች የተከተሉት “ዋቄፈታነት ኦሮሞነት፣ ኦሮሞነት ዋቄፈናነት” አስተምህሮ፣
- የዋቄፈና ሀይማኖትን በገዳ አስተዳደራዊ ስርአት ስር በማስገባት፣
- የኢሬቻ በአልን የኦሮሞ የነፃነትና የባህል ቀን ክብረ በአል በማስመሰል፣
- የብሄሩን ማንነት መልሶ በማቆም ውስጥ ዋቄፈና የብሄሩ ማንነትና ባህል ተደርጎ እንዲወሰድ በማደረግ፣

ሲሆን የነዚህን እስትራቴጂዎች ጥቅምና ጉዳት በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## ➢ የሀይማኖቱ መሪዎች የተከተሉት "ዋቄፈታነት ኦሮሞነት፣ ኦሮሞነት ዋቄፈናነት" አስተምህሮ

እዚህ ጋር ያለው አስተምህሮ [28] "የአይሁድና የአረብ ህዝቦች የራሳቸው ሀይማኖት አላቸው፣ እንደዚሁ ኦሮሞም የራሱ ሀይማኖት ዋቄፈናን አለው፣ ስለዚህ ኦሮሞ ሆኖ የራሱን ትቶ እነዚህን የባዕድ ሀይማኖቶች መከተል ራስን አለማወቅ ነው፡፡" የሚል አስተምህሮ ነው፣ በዚህም በኦሮሞነትና በዋቄፈታነት መሃከል ምንም ልዩነት እንደሌለና ወደ ዋቄፈና ያልመጣ ኦሮሞ "የኦሮሞ ብሄርተኝነት (sabbonummaa) በውስጡ የሌለ የአስተሳሰብ ባሪያ ነው" የሚል አስተምህሮትን ይከተላሉ፡፡

በርግጥ በ2.2 ክፍል እንደተመለከትነው በመሀመድ በኩል የተላከው እስልምና የተላከው ለአረብ ህዝብ ነው እንደዚሁ በሙሴ በኩል የወረደው የአይሁድ ሀይማኖት የተላከው በስጋ እስራኤላውያን ለሆኑት ብቻ ነው፣ ነገር ግን ከክርስትና ጋር በተያያዘ "ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች፣ የእስራኤል አምላክ ..." የሚሉትን ቃላት በመውሰድ ብቻ "ክርስትናም ለእስራኤል ብቻ ነው የተላከው" ማለቱ ስህተት ነው፡፡

ይህም ስህተት የመጣው "እስራኤል" የሚለውን ቃል ከስር መሠረቱ ባለመረዳት ነው፣ በመጀመሪያ "እስራኤል" የተባለው ያዕቆብ ነው፣ ከዚያም በሂደት ይህ ስም የአስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ዘሮች ስም ሆነ፣ ከዚያ በሂደት እነኚህ ዘሮች የሚኖሩባት ሀገር መጠርያ ሆነ ነገር ግን ከመጀመሪያው "እስራኤል" የሚለው ስም የወጣው "አማኝ" በሚለው ትርጉሙ ነው፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ በአዲስ ኪዳን ክፍሉ ይህን የእስራኤላዊነት "አማኝ" ትርጉምና "እስራኤል ሀገር" ትርጉም የተለያየ መሆኑን ያስተምራል(ሮሜ.9፡6-8, ገላ.4፡22-31 ...) ይህንኑ እውነታም በተግባር ማረጋገጥ ይቻላል፣ በሀገር እስራኤላዊ የሆኑት እስራኤላውያን የአይሁድ እምነት ተከታዮች እንጂ በኢየሱስ በኩል የወረደውን የክርስትና እምነት ተከታዮች አይደሉም፡፡

---

[28] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 18-19

በዚህም ሀይማኖቶችን በብሄር የመከፋፈል እስትራቴጂ የሚሰራው ለክርስትና ሳይሆን ለአይሁድ ሀይማኖትና ለእስልምና ሀይማኖቶች ነው፣ በዚህም አንድ ኦሮሞ በብሄር-ሀይማኖት ስሌት ብቻ ከእስልምና ወይ ከአይሁድ ሀይማኖት ወደ ዋቄፈታነት ቢመለስ ምክንያታዊ ቢሆንም በሀይማኖት-ብሄር ስሌት ካልተሰራው ከክርስትና ወደ ዋቄፈታነት መመለሱ ግን ስህተት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኦሮሞነትንና ዋቄፈታነትን በዚህ መልክ በማያያዝ ዋቄፈታ ያልሆነውን ኦሮሞ ለኦሮሞነቱ እውቅና ማሳጣቱም መሠረታዊውን የግለሰቦችን የሀይማኖት ነፃነት የሚጎዳ አካሄድ ነው፣ አንድ ኦሮሞ ኢአምላኪ፣ ክርስቲያን፣ ሙስሊም … መሆኑ "ኦሮሞነቱን አጣ" ተብሎ ሊተረጎም አይገባም፣ "ሀይማኖት የግል ነው፣ ብሄር የጋራ ነው"፣ እንደዚህ አይነት ጥምረት መፍጠሩም ለጊዜው ጠቃሚ ይምሰል እንጂ የብሄሩን ማንነት በራሱ የሚጎዳ አካሄድ ነው፣ ምክንያቱም፣

- በዋቄፈታ እምነት ላይ የሚታዩት ድክመቶች(ቅዱስ መፅሀፍ ማጣት፣ ሀይማታዊ መዋቅር ማጣት …) የኦሮሞ ድክመት ተደርጎ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
- ሀይማኖትን በብሄር ከከፋፈልን ኦሮሞ ከሙቶ አመታት በላይ ተሸንፎ የነበረው "አምላኩ ተሸንፎበት ነበር" የሚል እንድምታ አለው፣ እንደዚያ ከሆነ የኦሮሞ አምላክ የሚባለው ዋናው ፈጣሪ አምላክ ሳይሆን ሊሸነፍ የሚችል አከባቢያዊ ጣዖት ሊሆን ነው፡፡

በዚህም "የሀይማኖት ብሄር ጥምርታ" በመስራት ዋቄፈና የተከተለው እስትራቴጂ ለጊዜው ይምሰል እንጂ አካሄዱ የተሳሳተ ይባሱኑም በግለሰቦች መብትና በብሄሩ ማንነት ላይ ጉዳት የሚያመጣ እስትራቴጂ ነው፡፡

- <u>የዋቄፈና ሀይማኖትን በገዳ አስተዳደራዊ ስርአት ስር በማስገባት</u>

ለዋቄፈና ሀይማኖት መስፋፋት ሌላው ትልቁን አስትዋፅዖ ያበረከተው የዋቄፈና ሀይማኖትና ራሱን በገዳ አስተዳደራዊ ስርአት ስር ማስገባቱ ነው፣ ይህም ብዙዎች የገዳ ስርአትን ለመደገፍ ሲሉ ዋቄፈታነትን እንዲደግፉና እንዲቀበሉ ሲያደርግ፣ ሌሎች ደግሞ ከገዳ ስርአት ጋር ላለመጋጨት ዋቄፈናን

በዝምታ እንዲመለከቱ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ የገዳ አባቶችም የዋቄፈና ሀይማኖትን በባለቤትነት እንዲይዙ አድርጓል፡፡

ነገር ግን የገዳ ስርአትና የዋቄፈና ጥምረት ትክክለኛ የሚሆነው ሁሉም ኦሮሞ ዋቄፈታ በነበረበት ወቅት ነው ነገር ግን አሁን ኦሮሞ በሙሉ ዋቄፈታ አይደለም፣ ዛሬ አብዛኛው ኦሮሞ የሌላ እምነት ተከታይ ነው፣ በዚህም የገዳ ስርአት - ዋቄፈና ጥምረት ሊያበቃ፣ አስተዳደራዊ ስርአትና ሀይማኖት ሊለያዩ፣ የገዳ አስተዳደረዊ ስርአት በሀይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ መግባት ሊያቆምና ዋቄፈናም ሀይማኖታዊ ፍቃድ እንደተሰጠው ሁሉ ራሱንም ከገዳ ስርአት ተለይቶ ራሱን ችሎ ሊቆም ይገባል፡፡

በርግጥ ዋቄፈና ከገዳ ጋር ያለው ጥምረት ውስጥ ተጠቃሚ በመሆኑ ጥምረቱ እንዲለያይ አይፈልግም ነገር ግን ጥምረቱ የገዳ ስርአትን ይጎዳል፣ ምክንያቱም ጥምረቱ የገዳ ስርአት የብሄሩን የሌላው እምነት ተከታዮችን የማይወክልና በዚህም እነዚህ ሰዎች ከገዳ ስርአት ደጋፊነት ወደ ኋላ እንዲሉ የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጥምረቱ ዋቄፈና እንደ ሀይማኖት ያሉበት ጉድለቶች(ቅዱስ መፅሀፍ፣ የሀይማኖት መዋቅር … ማጣቱ) የገዳ ስርአት ጉድለት ያደርጋል፡፡

ስለዚህ የገዳ የአስተዳደር ስርአት በሁሉም ኦሮሞ ዘንድ ተቀባይነትና ድጋፍ ለማግኘት እንዲሁም በዋቄፈና ምክንያት ደካማ ስርአት ከመሆን ለመዳን ራሱን ከሀይማኖታዊ ጉዳዮች ነፃ ማድረግ አለበት፡፡

- <u>**የኢሬቻ በአልን የኦሮሞ የነፃነትና የባህል ቀን ክብረ በአል በማስመሰል**</u>

ዋቄፈና በዋናነት የሚታወቀው በኢሬቻ ክብረ በአሉ ነው፣ ኢሬቻ ሀይማኖታዊ በአል ቢሆንም አብዛኛው ሰው በአሉን የሚያከብረው ከሀይማኖታዊ በአልነቱ ይልቅ በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር እጦት የታፈነ ህዝብ የሚተነፍስበት ቀን በመሆኑና የኦሮሞ የባህል ቀን በመደረጉ ነው፣ በነዚህ ሁለቱ ሰበቦችም ነው ዋቄፈና አብዛኛውን የብሄሩን አባላት በቀላሉ ማግኘት የቻለው፡፡

በርግጥ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ከፖለቲካ ነፃነት ጋር ተያይዞ የነበረው ችግር በብዙ ቄሮዎች መስዋዕትነት በተወሰነ መጠን መልክ እየያዘ በመምጣቱ የኢሬቻን በአል ከፖለቲካዊ ፍላጎት አንፃር የመሳተፍ ፍላጎቱ

አሁን እምብዛም አይታይም፣ አሁን ያለው ትልቁ የመሳብያ መንገድ የኢሬቻ ቀን ልክ እንደ ጨምበላላ፣ ጊፋታ፣ ሶሎል፣ አሸንዳ … የብሄር በአላት፣ የኦሮሞ የባህል ቀን እንዲመስል በማደረግ ነው፡፡

ነገር ግን በኢሬቻና በነዚህ የብሄሮች በአላት መካከል መሠረታዊ ልዩነት እንመለከታለን፣ የነዚህ ብሄሮች በአላት ባህላዊ በአላት ናቸው፣ ኢሬቻ ግን የዋቄፈና ሀይማኖት ሀይማኖታዊ በአል ነው፣ ኢሬቻ ሀይማኖታዊ በአል ሆኖ በባህላዊ በአልነት እንዲከበር የሚደረገው ብሄሩ የራሱ የዘመን መለወጫ ባህላዊ በአል አጥቶ አይደለም፣ ኦሮሞ "Dhaha" የሚባል የራሱ ካሌንደርና የራሱ ዘመን መለወጫ በአል አለው ነገር ግን ይህ የዘመን መለወጫ ቀን እንዲታወቅም እንዲከበርም አይፈለግም ምክንያቱም ይህ ቀን ከተከበረ ቀኑ የኦሮሞ ባህላዊ የበአል ቀን ስለሚሆንና ዋናው የዋቄፈና ሀይማኖት ማስፋፍያ፣ የኢሬቻ በአልን፣ ዞሮ የሚመለከተው ሰው አይኖርም፣ በዚህም ኦሮሞ እንደሌሎቹ ብሄሮች የራሱን ዘመን መለወጫ እንዳያከብር የተደረገው በዋቄፈና ሀይማኖት አክራሪዎች ነው፡፡

የኦሮሞ ህዝብ ጠቢብነት የሚያሳየውና በተለይ በቦረናና ሰሜን ኬንያ አካባቢ ባሉ ኦሮሞዎች የሚታወቀውን የኦሮሞ ኦሪጂናል ካሌንደርና የዘመን መለወጫ በአል ሊመለስ ይገባል፣ በዚህም ማንኛውም የተለያየ ሀይማኖት ተከታይ ኦሮሞ በእኩልነት የሚያሳትፍ ባህላዊ በአል ሊቋቋም ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዋቄፈና ሀይማኖት ተብሎ እንደ ሀይማኖት ቢደራጅም እንድ አንድ ሀይማኖት በሀይማኖትነት ወጣ ብሎ መሄድ አይፈልግም፣ ከላይ እንደተመለከትነው ሀይማኖቱ ኦሮሞነትንና የገዳ ስርአትን በከለላ እየተጠቀመ እየተስፋፋ እንዳለው ሁሉ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ዋቄፈና ባህል እንደሆነ የሚነገርበትና ሀይማኖቱ በዚህ ስም የሚንቀሳቀስበትንም ሁኔታ እንመለከታለን፣ ይህም ደግሞ ለሀይማኖቱ ራሱን የቻሉ ጥቅሞችን አስገኝቶለታል፣ ባህል ማሳደግ ሁሉንም የብሄሩን አባላትና መንግስትን የሚመለከት እንዲሁም አይነኬ የማንነት ጉዳይ በመሆኑ ዋቄፈናም በዚሁ ሽፋን ተከልሎ እንዲያድግና ራሱንም ከሌሎች ሀይማኖቶች ነቀራ ከለላ ማግኘት እንዲችል አድርጎታል፣ ይህም ሌላው የሀይማኖቱ የድብብቆሽ ጫወታ ነው፡፡

ነገር ግን ባህልና ሀይማኖት የማይዳበሉ የተለያዩ እሴቶች እንደመሆናቸው እንዲሁም ዋቄፈና በፌዴራል መንግስቱ በሀይማኖትነት እንደመመዝገቡ መጠን እንደ ሀይማኖት ራሱን ችሎ መስራት አለበት፡፡

- <u>**የብሄሩን ማንነት መልሶ በማቆም ውስጥ ዋቄፈና የብሄሩ ማንነትና ባህል ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ**</u>

የአንድ ብሄር መገለጫው ቋንቋው፣ ባህሉ፣ አኗኗሩ፣ እሴቶቹ፣ የአስተዳደር ስርአቶቹ ... ናቸው ነገር ግን አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናትና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፣ መረዳጃ ማህበሮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ... የዋቄፈታ ሃይማኖትን የብሄር ማንነትና ባህል በማድረግ የኦሮሞን ባህልና ማንነት መልሶ በማቆም ሂደት ውስጥ ዋቄፈናንም በዚህ ውስጥ በማጠቃለል ለሀይማኖቱ ሰፊ እገዛ እያደረጉለት ይገኛል፡፡

በዚህም እነዚህ ድርጅቶች ህዝቡን ለዋቄፈናነት ሲቀሰቅሱ፣ በፖለቲካ ሲደግፉ፣ ሃይማኖቱን ሲያደራጁ፣ በበጀት ሲደጉሙ፣ የማምለኪያ ቦታና ፕሮግራም ሲያዘጋጁ፣ የኢሬቻን በአል ዝግጅትና ድምቀት ሲንቀሳቀሱ ... እንመለከታለን፣ አንዳንዶቹ ከዚህ ባለፈ [29]“ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ መለያ ነው” በማለት የብሄሩን ሌላ እምነት ተከታዮች እውቅና እስከመንሳት ሲደርሱ እንመለከታለን፣ ይህም የራስን ሀይማኖት በኦሮሙማ ሽፋን አስገድዶ በሌላው ኦሮሞ ላይ የመጫን አሰራር ነው፣ ይህ ደግሞ ወንጀልም ነው፣ ኢ-ህገ መንግስታዊም ነው፣ ህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 “የማንኛውም ሰው የአምልኮ ነፃነት በምንም ሰበብ ጫና ሊደረግበት አይገባም” ይላል፣ እንደዚሁ አንቀፅ 11/3 “መንግስት በሀይማኖት ጣልቃ አይገባም” ይላል፣ በዚህም የነዚህ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለዋቄፈና የሚያደርጉት ድጋፍ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ለምሳሌ ጨምበላላ፣ ጊፋታ፣ አሸንዳን ... በአላት በመንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ድጋፍ ቢያደርጉላቸው ስህተት የለውም ምክንያቱም እነዚህ በአላት ባህላዊ በአላት ናቸውና ነገር ግን በሀይማኖትነቱ ለሚታወቀውና በሀይማኖትነት ለተመዘገበው ለዋቄፈና ብሎም ለዋቄፈና ሀይማኖታዊ በአል “ኢሬቻ”የሚያደረገው ድጋፍ ስህተት ነው፡፡

---

[29]www.oromiatourism.gov.et, accessed on September, 2017GC

በዚህም እነዚህ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ህገ መንግስቱን ቢያከብሩ፣ ሀይማኖቶችን በእኩል አይን ቢመለከቱ፣ ሰው የእነሱን ሀይማኖት እንዲከተል በኦሮሙማ ሰበብ ጫና ባያደርጉና ከተደራጁለት አላማ ውጪ በመውጣት በሀይማኖቶች መካከል ልዩነት ባይፈጥሩ መልካም ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ዋቄፈና የሀይማኖት አቋም ሳይኖረው በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በአጭር ጊዜ እንደዚህ ሊስፋፋ የቻለው በሰቦኑማ(ኦሮሙማ)፣ በገዳ ስርአት፣ በባህልና በማንነት ፖለቲካ ሽፋን እንጂ በሀይማኖታዊ አቋሙ አይደለም፡፡

### 3.1.1.3. የዋቄፈናና የክርስትና ሽኩቻ

ባህላዊውን ዋቄፈና ክርስትናውና እስልምናው እኩል ለእኩል በሚባል መልኩ ቢካፈሏቸውም፣ ዘመናዊው ዋቄፈና አሁን ተመልሶ በሚደራጅበት ጊዜ ግን አማኞቹን ማስመለስ የቻለው ከክርስትናው ሀይማኖት ብቻ ነው፣ የዋቄፈና ዋናው አትኩሮት የክርስትና ሀይማኖት ሲሆን ራሱንም የክርስትና መሠረት አድርጎ ይመለከታል፣ እንደዚሁ ደግሞ ክርስትናውም ዋቄፈናንን "ቅድስና የጎደለው የሰይጣን አምልኮ" አድርጎ ይመለከተዋል፣ እነዚህን ሁለቱን ሽኩቻዎች ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

#### 3.1.1.3.1. የዋቄፈና አስተምህሮ - "የክርስትና መሠረት ዋቄፈና ነው"

እንደ የዘመናዊው ዋቄፈና ምሁራን [30] "ዋቄፈና ከጥንት የሰው ልጅ መፈጠር ጀምሮ የነበረ ሀይማኖት ነው"፣ [31] "የክርስትና መሠረትም ዋቄፈና ነው" ይላሉ፣ ይንንም ሲያስረዱ፣

- [32] "በኑቢያ ዘመን ዋቄፈና "ኦሲሪስ" በመባል ይታወቃል፣ ኦሲሪስ ከ6,500 አመታት በፊት ኑቢያኖች ሲከተሉት የነበረ ሀይማኖት ነው፣ የኩሽ ህዝቦችም ለብቻ ወጥተው የሞርሞር ሀይቅ፣ በጥቁር አባይ፣ አካባቢ ሰፍረው በአንድ አምላክ በዋቄፈና ሲኖሩ ነበረ፣ ስለዚህ

---

[30] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 19-20

[31] Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa**, fuula 16

[32] ibid, fuula 20

የሁሉም ሀይማኖቶች መሠረት ዋቄፈና ነው፡፡(Maatii Sabaa, Daaniyaa, 2009, fuula 56-57)" ይላል፡፡

- [33] "ሙሴና ኢየሱስ ዋቄፈታ ነበሩ፣ የዋቄፈናን እምነት ከግብፅ ይዘው ወደ ሀገራቸው በመመለስ ክርስትናን ፈጠሩ፡፡"

እነዚህ የዘመናዊው ዋቄፈና ምሁራን የሚናገሩት ነገር ለዋቄፈና የሀይማኖት አባቶችም ሆነ ለሌላውም ሰው እንግዳ ታሪኮች ናቸው፣ እነዚህ ታሪኮች ከየት እንደመጡም አወዛጋቢ ነው፣

- ዋቄፈታ የራሱ ቅዱስ መፅሀፍ የለውም በዚህም "ይህን ታሪክ ከዚያ አገኘን" አይባልም፣
- ይህ ታሪክ በጥንታዊ መፅሀፍት በመፅሀፍ ቅዱሱም ሆነ በቁርአኑ ላይ አልተዘገበም፣
- እነዚህ ታሪኮች የትኛውም ባህላዊ የእምነቱ አበው ጋር አይገኝም ምክንያቱም የቀረበው የዘመናዊው ታሪክ አስተምህሮ ናቸው፣
- በዘመናዊው ታሪክም ይህንን አባባል አናገኝም ይባሱኑም አባባሉ ብዙ የዘመናዊው ታሪክ ጥናቶችን ያተራመሰ አባባል ነው፣ በመጀመሪያ የሰው ልጆች ዘር መገኛ ኑቢያ አይደለም፣ የሰው ዘር መነሻን ከ6,500 አመታት የሚሰላው በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ስሌት እንጂ በሳይንሱ የሰው ልጅ ዘር የጀመረው ከሚሊዮን አመታት በፊት ነው፣ በዚህም የ6,500 አመታትን ስሌት ከዘመናዊው ታሪክ ጋር አብሮ አይሄድም፣ በተጨማሪም አባባሉ ሱዳን ውስጥ ያለውን የኑብያ ህዝብ፣ የኩሽ ህዝብና የኦሮሞን ህዝብ አንድ አድርጎ ነው የተመለከተው፡፡

ይህ በሀይማኖት ሽኩቻ ምክንያት የማይገናኙ ታሪኮች የተገናኙበት ልበወለድ ብቻ ነው፡፡

---

[33] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 59, 91 fi
Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa**, fuula 17

እንደዚህ የማይገናኙ ድርሰቶችን ከማገናኘት ይልቅ ግን እውነተኞቹን ነገር ግን ዛሬ የኦሮሞ ባለቤትነት ደብዛቸው የጠፉና በመገንጠል ፖለቲከኞች ምክንያት ሳይፈለጉ የቀሩ የኦሮሞ የኢትዮጵያ ክርስትና መሠረት መሆኑን የሚያሳዩ ታሪኮችን በመግለጡ ላይ በሰሩ በተሻለ ነበረ፡፡

እዚህ ጋር ስለኩሽ/ኦሮሞ ህዝቦች ታሪክ ስንመለከት የሌሎች የሰሜቲክ የናይሎቲክ፣ የኦሞቲክ … ህዝቦችንም ታሪክ ሳንነዘንጋ ነው፣ ሁሉም ኢትዮጵያንና ክርስትናን መሠረት እንዲይዝ ብዙ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ ነበረ፣ እያደረጉም ይገኛል ነገር ግን <u>እዚህ ጋር የኩሽ/ኦሮሞን አስተዋፅዖ ለይቶ መመልከት የተፈለገው በዘመናዊው ዋቄፋና የተሰራውን የተሳሳተ አስተምህሮን ለማስተካከል ብቻ ነው</u>፣ በዚህም በዚህ ክፍል የኩሽቲክ/ኦሮሞ ህዝቦች ከሰሜን አፍሪካና ከኢትዮጵያ ክርስትና ጋር በተያያዘ የነበራቸውን ሚና በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

ከመነሻው ስንመለከት የኩሽ ህዝቦች በአረቦች ወደ ደቡብ ከመገፋታቸው በፊት በሰሜን አፍሪካ ይኖሩ ነበረ፣ ዓለም የሚደነቅበት "the nile civilization" የሚባለው ስልጣኔ የኩሽቲክ ህዝቦች ስልጣኔ ነበረ፣ ከኩሽ ውስጥ ደግሞ አሮሞ ዋነኛው ነው፣

> [34] "ፕሮፌሰር ቭላድሜር 'ጥንት ጋላ(ኦሮሞ) መሆን የተከበረና የተወደደ ቁም ነገር ነበረ፣ የዝናና የትምክህት ምንጭ ነበረ፡፡' በማለት ገልፆታል፣ በኩሽ ስም ይታወቅ የነበረው የአባይ ቀበሌና ሌሎችም ተበታትነው የነበሩት የግብፅ ግዛቶች ኑቢያ ተሰኝተው በ3ሺ ዓ.ዓ ሲዋሃዱ የመንግስቱ መስራቾችና የጦር አበጋዞች ጋሎች(ኦሮሞዎች) ነበሩ፣ ከዓለም ድንቅ ነገር የመጀመሪያዎቹ የሆኑት ፒራሚዶች በዚሁ ዘመን ገደማ ያሰሩት መሀንዲሶችና ጠበብቶች ጋሎች(ኦሮሞዎች) ነበሩ፡፡"

---

[34] መቶ አለቃ በቀለ ሡጉ(1967)፣ **ቀንበርን ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ**፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ገፅ 23-25፡፡
እዚህ መፅሀፍ ላይ ኦሮሞ የሚለውን "ጋላ" ተብሎ በተሳሳተ መንገድ በመግለፁ ምክንያት "ጋላ" ከሚለው አጠገብ በቅንፍ "ኦሮሞ" ተብሎ ተገልጿል፡፡

በናይል ስልጣኔ ዘመናዊው የሂሳብ፣ ጂኦግራፊ፣ ስነፈለግ፣ ዲሞክራሲ ... ፍልስፍናና አስተምህሮቶች መሠረት የተጣለበት ዘመን ነው፣ ከሳይንስ ደግሞ ስነፅሁፍ ስለሚቀድም ይህ የኩሽ/የኦሮሞ ህዝብ ቀድሞውኑም የራሱ ስነፅሁፍ ነበረው፣ ዛሬ በአፍሪካ ውስጥ ካሉት ጥቂት ሀገር በቀል ስነፅሁፎች ውስጥ አንዱ የሳባ ስነፅሁፍ ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ሳባ የኩሽ ልጅ እንደሆነ ይናገራል(ዘፍ.10፡6-8, 1ዜና.1፡8-10)፡፡

ዛሬ የኩሽቲክ ህዝቦች ታሪክ የማይመስሉት የክርስትና ቅርሶች ላይ የምንመለከተው የሳቢያኖችን ፅሁፍ፣ የሳባ ንግስት ታሪክ፣ "ህንደኬ" ስለተባለችው የኢትዮጵያ ንግስትና የገንዘብ ሚኒስትሯ ጃንደረባ ታሪክ(ሐስ.8፡27)፣ ነብዩ ኤርምያስን ከሞት ስለ ታደገው ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ታሪክ(ኤር.38) ... የኩሽቲክ ህዝቦች ገናና በነበሩበትና የሰሜቲክ ህዝቦች ወደ ኢትየጵያ ሳይስፋፉና የኩሽን መንግሥት ሳይገረስሱ [35] ከ4ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበሩ ታሪኮች ናቸው፡፡ አንዳንድ የውጪ ሀገራት መፅሀፍ ቅዱሳትም "ኢትዮጵያ" በሚለው ቦታ "ኩሽ" ሲሉ እንመለከታለን፡፡

እነዚህንና ተመሳሳይ ታሪኮች በዋናው የኦርቶዶክስ ኢንሳይክሎፒዲያና በዋናው ዊኪፒዲያ ላይ ተዘግቧል፡፡

- [36] "... Biblically speaking, then, Ethiopia was the land of Kush ... Ancient Kushite elements are still exhibited in the unique architecture of the earliest Orthodox churches ..."

- [37] "In Greco-Roman epigraphs, Aethiopia was a specific toponym for ancient nubia ... the name Aethiopia also occurs in many translations of the Old Testament in

---

[35] https://en.m.wikipedia.org/Axumite Kingdome
https://en.m.wikipedia.org/Kush Kingdome

[36] **The Encyclopedia of Eastern Orthodox Christianity,** Edited by John Anthony McGuckin, Volume I, 2011, Blackwell Publishing Ltd. ISBN: 978-1-405-18539-4, Page 6.

[37] https://en.m.wikipedia.org/Ethiopia/Etymology

allusion to Nubia. The ancient Hebrew texts identify Nubia instead as Kush. How ever in the New Testament the Greek term Aitiops occurs, referring to the servant of the kandake(ህንደኬ), the queen of kush. ”

እነዚህና መሰል የኩሽ(የኦሮሞ) የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ክርስትና መሰረትነት ዛሬ ተሸፍኖ ኦሮሞ ከኢትዮጵያና ክርስትና ጋር የተዋወቁት በሚኒሊክ ተደርጎ በመገንጠል ፖለቲከኞች መነገሩ ስህተት ነው፡፡

አብዛኛው የኦሮሞ ምሁር የኩሽ ህዝቦች(በተለይ ኦሮሞ) ኢትዮጵያ የተባለችው ሀገርና የኢትዮጵያ የክርስትና መሠረት እንዲሁም የብዙ ታሪካዊ እሴቶች ባለቤት መሆኑን ያውቃል ነገር ግን የመገንጠል ፖለቲከኞችን ፍራቻ ባለቤትነቱን እያወቀ ባላወቀ ይባሱኑ እኚህ ፖለቲከኞች ለፖለቲካቸው እንዲያመች ኦሮሞ ከሌላው ኢትዮጵያ በሀይማኖት፣ በስነፅሁፍ፣ በካሌንደር … እንዲለይና በዚህም በሂደት የመገንጠል መንፈስ እንዲያሳድግ እየተሰራ ባለው ሴራ ውስጥ ባላየ እየሄደ ይገኛል፡፡ የመገንጠል ፖለቲከኞች ኦሮሞ በስልጣኔ ማማ ላይ እንደነበረ ይናገሩ እንጂ ኦሮሞ ስልጣኔውን ሲያካሂድበት የነበሩትን እሴቶች ማንሳትም አይፈልጉም ሌሎችም ስለዚህ እንዲናገሩ አይፈልጉም፡፡

በዚህም ነው ሀይማኖታዊ መስፈርት የማያሟላውን “ሀይማኖት” ሀይማኖት አድርገው፣ ሀይማኖቱንም በብሄር ማንነት፣ ባህልና የገዳ አስተዳደራዊ ስርአት ሸፍነው፣ የብሄሩን ካሌንደርና ባህላዊ በአል እንዳይከበር አድርገው፣ የብሄሩ ቀደምት ስነፅሁፍ እንዳይፈለግና አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማደግ የሚችልበት መንገድ ላይ እንዳይሰራ ሸፍነው እየሄዱ የሚገኙት፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት የኩሽቲክ/የኦሮሞ ህዝብ የራሱ ፊደል የነበረው፣ የኢትዮጵያ የክርስትና ውስጥ ጉልህ ሚና የነበረው፣ የዘመናዊው ሳይንስ ምንጭ እንዲሁም ዓለም ዲሞክራሲ በማያውቅበት ጊዜ የዲሞክራሲን ፍልስፍና ቀድሞ የፈጠረ ህዝብ ነው፡፡

ነገር ግን ዘመናዊው ዋቄፈና ከዚህ በመነሳት ኩሽ/ኦሮሞ እንደ ፈጣሪ ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ አድርጎ መናገሩ ደግሞ ስህተት ነው፣ ኩሽ/ኦሮሞ

የነዚህ ነገሮች ባለቤት እንደሆነው ሁሉ የክርስትና ምንጭ ደግሞ እስራኤል ናት፡፡

እውነታን መቃወም ደግሞ የትም አያደርስም ከትዝብት በቀር፣ በምሳሌ ብንመለከት፣ ዘመናዊው ዋቄፈና ራሱን "የክርስትና መሠረት ነኝ" ይበል እንጂ እውነታውን ስንመለከት ግን ክርስትናን ተደግፎ የቆመው ዋቄፈና ነው፣ ይህም ከቀላል "የኢሬቻ በአል የሚከበረው የኦርቶዶክሱን መስቀል ሳምንት ነው" ከሚለው አባባል አንስቶ የሰው ልጅ ትልቁ ጥያቄ የሆነውን "ዓለም እንዴት ተፈጠረች፣ የሰው ልጅ እንዴት ተፈጠረ ..." ጥያቄዎችን የሚመልሰው በክርስትናው ላይ ተንተርሶ ቃላቱን ወደ ኦሮምኛና ኦሮሚያ በማስጠጋት ነው፣ ለምሳሌ [38]

- የዓለም ስነፍጥረት
  ክርስትና - በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይና ምድርን ፈጠረ፣
  ዋቄፈና-በመጀመሪያ"ዋቃ" ኦሎ(ከላይ ያሉትን) እና ጀሎ(ምድርን) ፈጠረ
- የሰው ልጅ ስነ ፍጥረት
  ክርስትና - እግዚአብሄር አዳምን ከአፈር አበጀው፣ ከአዳም አጥንት ወስዶ ሄዋንን አበጀ፣
  ዋቄፈና - "ዋቃ" በመጀመሪያ አንድ ሰው ፈጠረ፣ ከዚያም ይህን ሰው ለሁለት በመክፈል ወንድና ሴት አደረጋቸው፣
- በመጀመሪያ የተፈጠሩት ሰዎች ስም
  ክርስትና - አዳምና ሄዋን ይባላሉ፣
  ዋቄፈና - አስዴምና ሀዌ ይባላሉ፣
- የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ሲኖሩ የነበረበት ቦታ
  ክርስትና - ኤደን ገነት፣
  ዋቄፈና - ኤደደ ገናሌ፣

በመጀመሪያ ላይ ያለው "ሰማይና ምድር" የሚለውን በተመሳሳይ የኦሮሚኛ ቃል በመቀየር "ኦሎና ጀሎ"፣ "ኦሎ" ማለት የላይኛው ማለት ሲሆን "ጀሎ" ማለት ደግሞ የታችኛው ማለት ነው፤ በሁለተኛው ላይ ያለው ታሪክ

---

[38] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 21-23

ቀጥታ ኮፒ የተደረገ ታሪክ ነው፤ ሶስተኛ ላይ የተመለከተው "አዳምና ሄዋን" የሚለው ሊተረጎም ስለማይችል፣ ቃሉን ወደ አቅራቢያ ተመሳሳይ የኦሮምኛ ቃል በማስጠጋት አዳምን "አስዴም"(ወደዚህ ና)፣ ሄዋንን "ህዌ"(ስሙኝ) በሚለው ቃል ተለውጧል፤ በአራተኛ ላይም የምንመለከተው እንደ ሶስተኛው ቀረብ ያለ ኦሮሚኛ ቃል ማጠጋጋት ነው፣ በዚህም "ኤደን ገነት" የነበረው "የኦሮሞ መነሻ ነው" ወደሚባለው "መደ ወላቡ"ና ገናሌ ወንዝ በማጠጋጋት "ኤደደ ገናሌ" በሚለው ቃል ተለውጧል፡፡

በዚህም ዋቄፈና የክርስትናውን ታሪክ እንዳለ በመውሰድና ኦሮሚኛ በማድረግ የስነፍጥረት ታሪኩን ጉድለት ለሟሟላት ሞክሯል፣ በነዚህ የታሪክ ሽሚያ ውስጥ የሚያስገርመው ነገር ዋቄፈና በመጀመርያ የተፈጠሩት ሁለቱ ሰዎች የሚናገሩት ቋንቋ ኦሮምኛ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

ዘመናዊው ዋቄፈና ሁሉንም ታሪክ እንዳለ ለመልገበጥ ሀፍረት ስለያዘው ሌሎች ነገሮችን በዝምታ ነው ማለፍ የፈለገው፣ በጀመረው የመፅሀፍ ቅዱሰን ታሪኮች ኦሮምኛ በማድረግ መንገድ መግፋት አልደፈረም፣ የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ ምን ይሆናል? ቁሳዊው አለም የወደፊት እጣ ፈንታ ምንድነው? የፈጣሪ የወደፊት እቅድ ምንድነው? ... ለሚሉት ጥያቄዎች ዋቄፈና ምንም መልስ የለውም፡፡ የስነፍጥረቱ ታሪክ ላይም ከአዳምና ሄዋን ታሪክ በቀጥታ ወደ ኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ነው የሚወርደው፣ በዚህ መካከል ስላለው የሰው ዘር በዝምታ ነው የሚያልፈው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ከአዳም ታሪክ ቀጥታ ወደ እስራኤል ታሪክ አልወረደም፣ በዚያ መካከል ስለ ሌሎች ዘሮች አመጣጥ ይዘረዝራል፣ ኦሮሞ ያለበትን የኩሽቲክ ዘር እንኳዋን እንዴት እንደመጣና የኩሽ ልጆች እነማን እንደሆኑ እንኳን ያስተምራል፣ በዚህም በሁለቱ ሀይማኖቶች መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት እንመለከታለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን ዘመናዊው ዋቄፈና ራሱን "ቀደምት ሃይማኖት" በማድረግ የስነ ፍጥረት ታሪክ ጋር በመሄድ ከክርስትናው ጋር የታሪክ ሽሚያ ውስጥ ይግባ እንጂ ዋቄፈና ከኦሮሞ ውጪ በሌሎች ክርስትናና እስልምናን ባልተቀበሉ ህዝቦች ዘንድ ቢያንስ በሌሎች የኩሽቲክ ብሄሮች እንኳን አለመታወቁ፣ በዋቄፈና ውስጥም ከኦሮሞ ብሄር ማንነት፣ እሴቶች ... ውጪ ስለሌሎች ኩሽቲክ ስለሆኑ እንደ ሱማሌ፣ አፋር፣ ሲዳማ ... ብሄረሰቦች

ምንም አለመነገሩ፣ ዋቄፈናን የፍጥረት መጀመሪያ ይቅርና ኩሽቲክ ጋር እንኳን ማድረስ እንዳንችል ያደርገናል፡፡

ስለዚህ የኩሽቲክ ዘር ሀረግ የሆነው "ኦሮሞ" በኩሽቲክ ዘር ውስጥ መነሻ እንዳለውና የብሄሩ የተወሰነ ክፍልም ይህንን ሀይማኖት የተከተለበት ጊዜ እንዳለ ሁሉ፣ ሀይማኖቱም የራሱ መነሻ ጊዜና ቦታ አለውው፣ በዚህ ከሆነ ቦታና ጊዜ የተጀመረን ሀይማኖት ከፍጥረት የተነሳ አድርጎ ከጥንት ከመጡት ሀይማኖቶች ጋር ማወዳደሩ ስህተት ነው፡፡

በዚህም በዋቄፈታ "የክርስትና መሠረት ዋቄፈና ነው" የሚለው ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 3.1.1.3.2. <u>የክርስትና ትችት በዋቄፈና ላይ</u>

ክርስትናው ጋር ስንመጣ ክርስትና ዋቄፈናን የሚተቸው፣

- "ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ አይደለም"
- "ዋቄፈና የሚያመልከው ብዙ አማልክትን ነው"
- "ዋቄፈና ጣዖታዊ ነው"

በሚሉ ሀሳቦች ሲሆን እነዚህን የክርስትና አስተምህሮዎችን ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡-

- **<u>"ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ አይደለም"</u>**

እንደ ክርስትናው አስተምህሮ፣ ዋቄፈና ራሱን ከዋናው ፈጣሪ ጋር ቢያያይዝም ሀይማኖቱ በአንድ ሀገር ያውም በአንድ ብሄር ያውም በተወሰኑ የብሄሩ ሰዎች ያውም ባለው የፖለቲካ ይሁኝታነት ተወስኖ የሚሄድ መሆኑ ዋቄፈና የዋናውን አምላክ ተከታይ ሳይሆን በብዙ ነገሮች የሚወሰን አነስተኛ አምላክን የሚከተል ሀይማኖት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህንንም አምላክ ደግሞ ዋቄፈና በራሱ "የኦሮሞ አምላክ"፣ "ጥቁር የሆነው የጥቁሮች አምላክ" ... ማለቱ የዋቄፈና አምላክ ዋናው አምላክ ሳይሆን በብሄር ወይ በቀለም የተገደበ አነስተኛ አምላክ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህም ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ ሳይሆን በተለያዩ ነገሮች የተገደበ አነስተኛ አምላክን መሆኑን ያሳያል፡፡

## ➢ “ዋቄፈና የሚያመልከው ብዙ አማልክትን ነው”

ዋቄፈና ራሱን የዋናው አንድ አምላክ ተከታይ ቢያደርግም በውስጡ ግን ብዙ የሚሰገድላቸውና መስዋዕት የሚቀርብላቸው አማልክትን አሉ፣ ለምሳሌ ያህል፡-

1. “አያና”(ውቃቢ) የሚባለው ስግደት የሚደረግለት መንፈስ፣ [39] “እያንዳንዱ ሰው ለራሱ፣ ለአባቱ(ቦረንቲቻ)፣ ለእናቱ(አቴቴ) እና ለሀገሩ አያና መስገድ ይገባዋል፡፡”
2. [40] አቴቴ (ስሟ ከማሪያም ጋር የሚመሳሰል “ማረም” የምትባለው “የወሊድ መንፈስ” የምትመለከበት ስነስርአት፣ ለዚህች አምላክም በሀገር ደረጃ በኢሬቻ ሳምንት በቡራዩ መልካ አቴቴ ታላቅ ክብረ በአል የሚደረግላት ሲሆን በቤተሰብ ደረጃም እናቶች በራሳቸው ፕሮግራም መሰረት “Atetee facaafachu” የሚባል የአምልኮ ስነስርአት ያደርጋሉ፡፡
3. [41] ቃልቻ(Raaga/ትንቢት የሚተነብይ)፣ [42] አያንቱ/አያና ለሚባሉት በገልማ/ጊምቢ ስግደት የሚደረግላቸው አማልክትን ይመለካሉ፣

እነዚህን እውነታዎችም ዋቄፈና ከአንድ አምላክ አምላኪነት ይልቅ የብዙ አማልክት አምላኪነቱን ያሳያል፡፡

## ➢ “ዋቄፈና ጣዖታዊ ነው”

ዋቄፈና ዋናውን አምላክ ባለመከተሉና ብዙ አማልክትን የሚከተል ሀይማኖት በመሆኑ ምክንያት በውስጡ ግልፅ ጣዖታዊ እሴቶችን ይዟል፣ እነዚህን ዕሴቶች በምሳሌ ብንመለከት፣

- ዋቄፈና እንደ ቅዱስ የሚመለከታቸው [43]“የኮከብ ቆጣሪነት፣ የሙት መንፈስ ሳቢነት፣ ማሊማ/ጫምሲቱ(ዝናብ ላይ ስልጣን ያለው መንፈስ)፣

---

[39] Tarruu Unguree(LLB)(2015)፣ **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa,** fuula 43-50

[40] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 121

[41] ibid, fuula, 42-43

[42] ibid, 64, 90

ራግዱ(ተንባይ)፣ ሞራ ገላጭ፣ ጨሌ/ጠጠር የሚቆጥሩ፣ መዳፍ፣ ጀበናና የእጣን ጢስ የሚያነቡ ... የሀይማኖቱ እሴቶች መሆናቸው፣

- [44] መካደም፣ [45] የመስዋዕት ዕርድ፣ [46] የምግብ መስዋዕት "ደደርባ/daddarbaa (ከመብላትና መጠጣት በፊት የተወሰነውን መጣል/ማፍሰስ) እና ዲባዩ/Dhibaayyuu (መስዋዕቱ በተወሰነ ቦታ ብቻ የሚቀርብበት የአምልኮ ስነስርአት)፣

- በኢሬቻ በአል አከባበር ላይ የአካባቢው ሰዎች በዚያን ቀን በስፍራው የሚያካሂዱት እርድ፣ ዛፍ እንጨት መቀባት፣ አረቄ ሀይቁ ውስጥ መጣል...

ስነስርአቶች የሚያሳዩት ሀይማኖቱ የሚያመልከው ዋናውን ፈጣሪ ሳይሆን በዚያ ስፍራ የሚገኘውን አከባቢያዊ ጣዖት መሆኑን ያሳያል፡፡

ከነዚህ አከባቢያዊ ጉዳዮች በተጨማሪም ዋቄፈና ስለሚያመልከው አምላክም ሲናገር [47]"ፈጣሪ ጥቁር ነው" ማለቱና በክርስትናው የሚመለከው ፈጣሪ ደግሞ በነጭና ብርሀናማ አገላለፆች መገለፁ፣ እነዚህ ሁለቱ ሀይማኖቶች በተቃራኒ ሀይላት እንደሚመሩ ያሳያል፣ ሁለቱም ጋር የተጠቀሰው ቀለም ደግሞ የቀለም ጉዳይ ሳይሆን ምሳሌያዊ አገላለፅ ነው ምክንያቱም ክርስትናው "አምላክ መንፈስ በመሆኑ እንደ ሰው ስጋና ደም የለውም" ስለሚል ዋቄፈናም [48] "ፈጣሪ ሰውን ይምሰል አይታወቅም" ስለሚል፡፡

በምሳሌያዊ አነጋገሩም ክርስትናው ፈጣሪን "ነጭና ብርሀናማ" በማለት መግለፅ የፈለገው ቅድስናውን ለማመልከት መሆኑና ነገር ግን ዋቄፈና "ዋቀ ጉራቻ" የሚለው ውስጥ "ጉራቻ"(ጥቁር) የሚለው ቃል ምሳሌነት የሚነሳው

[43] Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa,** fuula 64-65
[44] ibid, 90-91
[45] ibid, 117
[46] ibid, 76
[47] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**,fuula, 124
[48] ibid, fuula, 172

በመጥፎ ጎን መሆኑ፣ ለምሳሌ በኦሮምኛ እንኳን “Baga Gurraacha gannaatii baga booqa birraatti dabarte - እንኳን ከጥቁሩ ክረምት ወደ ብርሀናማው ፀደይ አሸጋገረህ” ይባላል፣ እንደዚሁ የአንድ ሰውን ቀናተኝነት ለመናገር “ለምን ፊትህ ጠቆረ”፣ መቆሸሽን ለማመልከት “እንደ ጥላሸት የጠቆረ” ... መባሉ፣ ዋቄፈና ጣዖታዊ ሀይማኖት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ዘመናዊው ዋቄፈና ራሱን በዘመናዊ ፍልስፍና አደራጅቶ ይቅረብ እንጂ ሀይማኖቱ እንደየትኛውም ኋላቀር ሀይማኖት ጣዖታዊ ሀይማኖት እንጂ ዋናውን አምላክ የሚከተል ሀይማኖት አይደለም፡፡

የተወሰነ የኦሮሞ ህዝብ ከአብርሃም ሀይማኖቶች መምጣት በፊት እንደየትኛውም ህብረተሰብ በራሱ ሀይማኖት በዋቄፈና ይኖር ነበረ፣ በዚህም ዋቄፈና በወቅቱ ከነበሩት የህብረተሰብ ሀይማኖቶች የተለየ ሀይማኖት አልነበረም፣ በዋቄፈና ውስጥ ያሉትን ሀይማኖታዊ እሴቶችንም ስንመለከት ዕሴቶቹ በሁሉም ኋላ ቀር ሀይማኖቶች ያሉ ሰይጣናዊ እሴቶች(Satan Specific) እንጂ ለኦሮሞ የተለዩ የኦሮሞ ማንነቶች(Oromo Specific) አይደሉም፣ በዚህም በሁሉም ኋላ ቀር ሀይማኖቶች የምናገኛቸውን ዕሴቶችን የኦሮሞ ማንነቶች አድርጎ በፖለቲካው አስደግፎ እየተሄደ ያለው አካሄድ መናፍስታዊ ሴራ ብቻ ነው፡፡

በዚህም ማንም ሰው እንደ ልጅነት ጊዜ “አየሆዬ” ስለተባለ ብቻ ማን እንዳለ፣ ለምን እንደተባለ ... ሳያጣራ “ሆ” እያለ መከተሉ አደጋ እንዳለው ሊገነዘብና በብሄር ስም በጭፍን ከመነዳት በየትኛው መናፍስታዊ ጎራ እየተሰለፈ እንዳለ ማስተዋሉ መልካም ነው፡፡

የስህተት አሰራሮችን ቀድሞ የሚያስጠነቅቀው መፅሀፍ ቅዱስ፣ ለዋቄፈናና መሰል ኋላ ቀር ሀይማኖቶች ቀድሞ የራሱ መልዕክት አስቀምጧል፣

> Isa.1:29 “Qilxuu jalatti hirreefattanii itti gammaddan sanaaf yeella`uuf jirtu, iddoo dhaaba isa fo`attan sanaafis salphachuuf jirtu;”

### 3.1.2. ራስ ተፈሪያን

[49] የራስ ተፈሪያን ሀይማኖት በ1930 ተመሠረተ፣ የእምነቱ ተከታዮች አንድ ሚሊየን የሚደርሱ ሲሆኑ በአብዛኛው የሚገኙትም በካሪቢያን አካባባቢ በተለይ በጃማይካ ሀገር ሲሆን በኢትዮጵያ ሻሸመኔ አካባቢ እንዲሁም በአሜሪካና በእንግሊዝም በተወሰነ መጠን ይገኛሉ፡፡

የራስ ተፈሪያን ሀይማኖት ተከታዮች "የምናመልከው አንዱን ሰማይና ምድርን የፈጠረውን አምላክ ነው" ይላሉ፣ ይህንንም አምላክ "ጃህ" ብለው ይጠሩታል፣ ይህም ስም "እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን የተጠራበት "ጂሆቫ" ከሚለው ስም የተወሰደ ነው" ይላሉ፡፡ ሀይማኖቱ ከሌሎች የክርስትና ሀይማኖቶች የሚለየው በዋናነት ንጉስ ኃ/ስላሴን "መሲህ" ማድረጉ፣ የኢትዮጵያ ምድር "የተስፋይቱ ምድር/ፅዮን" ማለቱ፣ የእግዚአብሄር ምርጥ ህዝቦች "ጥቁር ህዝቦች ናቸው" ማለቱና ከነዚህ ጋር በተያያዙ አስተምህሮቶች ነው፡፡

የሀይማኖቱ አመሠራረት ታሪክም ከቅኝ ግዛት ዘመን ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው፣ በቅኝ ግዛት ዘመን የአፍሪካ ጥቁር ህዝቦች በአውሮፓውያኑ ነጭ ወራሪዎች መጠን የለሽ ግፍ ሲፈፀምባቸው ቆይቷል፣ ከነዚህ ውስጥ ዋነኛው ግፍ የተፈፀመባቸው በነጮች የባርያ ንግድ ከአፍሪካ ተሸጠው በአውሮፓ፣ በካሪቢያን፣ በላቲንና በሰሜን አሜሪካ በባርነት በጉልበት ስራ እንዲሰማሩ የተደረጉት ጥቁር አፍሪካውያን ናቸው፡፡

[50] በ1833 አብርሃም ሊንከን የባርያ ንግድ እንዲቆምና በባርነት የተያዙ ሰዎች ነፃ እንዲወጡ ሲያውጅ በአብዛኛው ባርያዎች በነበሩ ነዋሪዎቿ የምትታወቀው ጃማይካ የጥቁሮች ሀገር ሆና ተመሠረተች፣ በወቅቱም የነዚህ ጥቁር ህዝቦች መሪ፣ አክቲቪስትና "ወደ አፍሪካ እንመለስ" እንቅስቃሴ መሪ የነበረው ማርክስ ጋረቬይ በውስጡ ያለውን ራዕይ(በሂደት ትንቢት የተባለ) ንግግር ተናገረ "አፍሪካ ላይ ጥቁር ሰው ሲነግስ ነፃነታችን እንደቀረበ እወቁ" አለ፡፡

---

[49] https፡//en.m.wikipedia.org>wiki>Rastafari

[50] www.bbc.co.uk.guides

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኃ/ስላሴ በ1930 እኤአ ኢትዮጵያ ላይ ንጉስ ሆነው መሾማቸው አለማቀፍ ዜና ሆነ፣ በንግስናቸው ፕሮግራም ላይም ከአለም ዙርያ ብዙ ልዑላንና የመንግስት ተወካዮች የተገኙ ሲሆን በወቅቱ ኒውዮርክ ታየምስ ስለ ንግስናቸው ሰፊ ሽፋን በመስጠት ዘገበ፣ በዚህ ጊዜ የማርክስ ጋርቬይ ተከታዮች የመሪያቸው ትንቢት ፍፃሜ እንደደረሰ አወጁ፡፡

አፄ ኃይለ ስላሴ ደግሞ ራሳቸውን ኢየሱስ በተጠራበት ስም “ሞአ አንበሳ ዘእምነ ነገደ ዘ ይሁዳ”(ራዕ5፡5) ብለው መጥራታቸው እንዲሁም በኢየሱስ ሹመት “የነገስታት ንጉስ”(ራዕ.17፡14, ራዕ.19፡16) ብለው ራሳቸውን መሾማቸው፣ አፄውን ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር አገናኝቶ “የጥቁሮች መሲህ” ለማለት ተጨማሪ አስትዋፅዖ አበረከተ፡፡

[51] እንደነ ሊአናርድ ሆዌል ያሉ የክርስትና ቀሳውስት ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ስለ ኢትዮጵያ የተነገሩትን ቃላት (ዘፍ.2፡13, መዝ.68፡31, አሞ.9፡7, ራዕ.5፡5 ...) በማገናኘት የንጉሱን “መሲህነት”ና የኢትዮጵያ ምድር “ተስፋይቷ ምድር - ፅዮን” መሆን መሰከሩ፡፡

ከዚያም ከጥቂት አመታት በኋላ የኢጣልያን ወረራ ተፈፀመ ኃ/ስላሴም ከሀገር ሸሹ፣ ከዚያም ኢትዮጵያ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ ንጉሱ በ1966 እኤአ ወደ ጃማይካ ተጓዙ፣ በዚህም ጊዜ የአፄውን መሲህነት የተቀበለው የጃማይካ ህዝብ ትልቅ አቀባበል አደረገላቸው፡፡

ሀይማኖቱም በጊዜ ሂደት ውስጥ እየተደራጀ በተለያዩ ፍልስፍናዎች እየጠነከረ መጣ፣ ራሱንም በቀኝ ገዢ ነጮች ከሚመራው “የነጮች ክርስትና” ተፅዕኖ ነፃ በሚያደርግ፣ በጥቁር ህዝቦች ላይ የነበረው የባርነት የስነልቦና ጫና “በሚጠግን”ና የጥቁር ህዝቦችን ማንነት በሚያንፀባርቅ መንገድን ራሱን አደራጀ፡፡ በዚህም ሃይማኖቱ በራሱ ጥቁር የሀይማኖት መሪዎች መመራትና ከዚያም ባለፈ በክርስትና ውስጥ የነበሩትን ነጭ ተኮር አስተምህሮቶችን ወደ ጥቁርነት የመቀየር ሰፊ ስራዎች ተሰሩ፣ ለምሳሌ፣

[51] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Rastafari

- “ፈጣሪ በመጀመሪያ ጥቁር ህዝቦችን ፈጠረ፣ ከዚያም ሰዎች ሀጢያትን ሲሰሩ ሀጢያት የሰሩ ሰዎችን ከለር ከላያቸው ላይ አጠፋ፣ በዚህም ሀጢያተኞቹ ነጭ ሲሆኑ የፈጣሪ ምርጥ ህዝቦች ደግሞ ጥቁሮች ናቸው፣ የቀደምት እስራኤላውያን ጥቁሮች ነበሩ፣ ኢየሱስም ጥቁር ነበረ፣
- መፅሀፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፃፈው በአፍሪካ ቋንቋ በአማርኛ ነው፡፡”

የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡

በዚህም እስትራቴጂ ቤተክርስቲያኗ ከጅማሮው በጥቁሩ ማህበረሰብ ዘንድ መስፋፋት ብታሳይም ይህ የመስፋፋት ታሪኳ ግን የጥቂት ጊዜ ታሪክ ብቻ ነበረ፣ ይህም ለጥቁሮች ስነልቦና ተብለው የገቡት ልበወለዶች በሂደት በገጠማቸው ፈተና ነው፣ ይህም፣

- “የፈጣሪና የሰው ተዋህዶ ናቸው” የተባሉት ኃ/ስላሴ መገደልና እንደ መሲሁ ኢየሱስ ከሞት መነሳት አለመቻል፣
- የተስፋይቱ ምድር(ኢትዮጵያ) ህዝቦች በረሀብና እርስ በርስ ጦርነት መርገፍ፣
- መፅሀፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ አለመፃፉና አማርኛው መፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም መሆኑን ህዝቡ እያወቀ መምጣቱ፣
- ጥቁርና ነጭም የሚለዩት በሀጢያት መስራት አለመስራት ሳይሆን በጂኦግራፊ ክልል ሰዎች ለአየር ፀሀይ ባላቸው ተጋላጭነት የሚወሰን መሆኑ በሂደት መስተዋሉ …

ረጋ ተብሎ ሲታይ ሁሉም ውሸት እየተስተዋለ መጣ፣ በዚህም ሀይማኖቱ በሂደት የመዳከም ሁኔታ ውስጥ ገባ ነገር ግን በዚህ የመዳከም ሂደት ውስጥ የሬጌው ሙዚቀኛ ቦብ ማርሊይ በጃማይካው የሬጌ ሙዚቃ ስልት ባገኘው አለማቀፋዊ ታዋቂነት፣ ሀይማኖቱም የማንሰራራት ዕድል መልሶ አገኘ፡፡

"ቦብ ራስ ተፈሪያን ነው" ይባል እንጂ ዘፈኖቹ ውስጥ ግን የምንመለከተው የሀይማኖት ፍልስፍና ራስ ተፈሪያንነትን አይደለም፣ እስቲ ለምሳሌ "Get up, stand up" ዘፈኑ ውስጥ ጥቂት ስንኞችን እንመለከት፡-

"Most people think Great God will come from the skies
Take away everything and make everybody fill high

.

.

.

Almighty God is a living man ..."

እነዚህን ስንኞች "ከሰማይ የሚመጣ አምላክ የለም፣ ሰው እራሱ አምላክ ነው" የሚል ፍቺ የሚሰጡን ሲሆን ይህም የሚያሳየው "ሰው እግዚአብሄር ነው" የሚለው የሂውማኒቲ አስተምህሮ እንጂ የአንድ አምላክ የራስ ተፈሪያን አስተምህሮ አይደለም፡፡

በርግጥ መፅሀፍ ቅዱሱ የሚያወግዘው የ"ዘፋኝነት" ህይወት ውስጥ ያለ ሰው የሀይማኖት የጀርባ አጥንት መሆን አይችልም እንዲሁም የአብዛኞቹን የሀይማኖቱን ተከታዮች ህይወት የዘፋኝነትና ሱሰኝነት ህይወት መሆኑ ሀይማኖቱ ከትክክለኛው መፅሀፍ ቅዱስ መንገድ አለመሆኑን ያሳየናል፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የሀይማኖቱ መሪዎች ነብዩ መሀመድ ክርስትና ላይ የሰሩትን አይነት ቅጥያን በአፄ ኃ/ስላሴ መሲህነትና በኢትዮጵያ ፅዮንነት ስም ለመስራት ያደረጉት ጥረት ባዶ መሆኑ፣ የራስ ተፈሪያን እምነት የጥቁሮችን ሞራል ለማንሳት ሲባል የተቋቋመ ሀይማኖት እንጂ መንፈሳዊ እውነታን ተከትሎ የተቋቋመ ሀይማኖት አለመሆኑን ያሳያል፡፡

የሚያሳዝነው ነገር የዚህ ማህበረሰብ የሀይማኖት መሪዎች ህዝቡን በውሸት ሞራሉን ለመጠገን ከመልፋት ይልቅ፣ እነዚህ ህዝቦች በስጋዊ ህይወታቸው የተጎዱትን ጉዳት ትክክለኛውን መንፈሳዊ መንገድ በማሳየት እንዲካሱ በረዱ ኖሮ መልካም ነበረ፣ የምድሩ ሞራላዊ ጉዳት ለመጠገን ተብሎ የምድሩም በአግባቡ ሳይጠገን ሰማያዊውን ጉዳትን ማምጣት፣ ጥቁሩን ማህበረሰብ ከባሪያ ነጋዴዎቹ በላይ የሚጎዳ አሰራር ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሌላው አሳዛኝ ነገረ አሁን ያለው የጃማይካውያን ትውልድ እንደ ቀደምቱ ትውልድ በባርነት ህይወት ውስጥ አላለፈም፣ ሁሉም በነፃነት ተወልዶ በነፃነት ያደገ ነው ነገር ግን አሁንም የጃማይካ ህዝብ እንደ ህዝብ ሌላው አለም ያለበት ስነ ልቦና ላይ የለም፣ በዚህም የአንድ ወቅት ክስተት ትውልዱ ላይ ተለጥፎ በህዝቡ ላይ መቆሚያ የሌለው ጉዳት ሲያመጣ ይታያል፣ በዚህም አብዛኞቹ ጃማይካውያን የስነ ልቦና ጉዳተኞች መሸሸጊያ በሆነው ሱሰኝነት፣ ዘፋኝነት፣ ግዴለሽነት፣ ሰካራምነት ... ህይወት ውስጥ ይገኛሉ፣ ይህም የአንድ ወቅት ክስተት የዘር መለያ ሆኖ ይገኛል፣ ይህ ደግሞ መርገምት ነው፡፡

በባርነት ህይወት ውስጥ ማለፍ ከባድ ነገር ነው፣ እንዲህ ላደረጉት እግዚአብሄር የስራቸውን ሰፍሮ የሚሰጣቸው ሲሆን፣ የራስ ተፈሪያን ህይማኖት ተከታዮች ሊያውቁት የሚገባው ነገር ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱሱ አምላክ ለተበደሉ የሚፈርድ(መዝ.103፡6)፣ በዳዮችን የሚቀጣ(ቆላ.3፡25)፣ ከሀብታሞች በላይ ድሆችን የሚወድ(ሉቃ.16፡19-25)፣ ዝቅ ያሉትን ከፍ የሚያደርግ እንዲሁ ከፍ ከፍ ያሉትን የሚያዋርድ(ማቴ.23፡12)፣ በአጠቃላይ የምስኪኑ ወዳጅ የተጎዳ ጥቁር ህዝብ ረዳት መሆኑን ነው፡፡

በዚህም ህዝቡ እውነቱን አስተውሎ በመመልከት፣ ለሞራል ግንባታ ተብሎ በክርስትናው ላይ የተሰራውን ህገወጥ ቅጥያ በመቁረጥ፣ እንደ ሀገር የተፈጠረውን መርገምት በመለወጥ፣ የዘላለም ህይወት የሆነውን የነፍስን ጉዳይ በመመልከት፣ ወደ ተተወው ክርስትና መመለስ ያለበት መሆኑ በገሀድ ያለ እውነታ ነው፡፡

## ማጠቃለያ (ከክርስትና ወደ ማህበረሰባዊ ሀይማኖት የተመለሱ)

በ2.2 ክፍል እንደቀረበው እስልምና ለአረቡ ማህበረሰብ የተላከ ሀይማኖት ነው፣ እንደዚሁ ደግሞ ዋቄፈና በኦሮሞ፣ ራስ ተፈሪያን ደግሞ በጃማይካውያን የተወሰኑ ሀይማኖቶች ናቸው፣ የነዚህ ሀይማኖቶች የጀርባ አጥንት ከሀይማኖታዊ ጉዳይ በላይ ፖለቲካዊው አመክንዮ ነው፣ ይህም ፖለቲካዊ አመክንዮ "የማህበረሰብን ማንነት መገንባት" በሚል ሀይማኖትን የብሄር ማንነት አድርጎ የመውሰድ ችግር ነው፣ ነብዩ መሀመድ ከጠላቶቻቸው እስራኤሎች በሀይማኖት ለመለየት እስልምናን ለአረብ እንዳመጣው፣ ዘመናዊው ዋቄፈናም "ከሰሜቲኮች ክርስትና" እንዲሁም ራስ ተፈሪያንም "ከነጮች ክርስትና" ለመለየት፣ የፖለቲካውን የነፃነት ትግል ሀይማኖቱ ድረስ ያስገቡበት አሰራር ነው፡፡

በዚህም ሳይስተዋል በፖለቲካ ምክንያት ብዙዎች ከሁለቱ ተቃራኒ መናፍስታዊ ሀይሎች ኋላ እየተሰለፉ ይገኛሉ፣ የሚያሳዝነው እነዚህ ሰዎች እየተሰለፉ ያሉት ፖለቲካውን በማየት እንጂ ስለ መናፍስታዊ ሀይሎቹ ማንነት በማጤን አይደለም፣ በዚህም እነዚህ ሰዎች ሳያስተውሉ ባልመረጡት መንፈሳዊ ሀይል ዕዝ ስር እየተሰለፉ ይገኛሉ፡፡

በዚህም እነዚህ ወገኖች መንፈሳዊው እውነታ ከጊዜያዊው ፖለቲካ በላይ መሆኑ በመረዳት፣ በፖለቲካ ምክንያት ከሄዱበት የተሳሳተ መንገድ በመመለስ ወደ ተዉት ክርስትና መመለስ እንዳለባቸው እንመለከታለን፣ በክርስትና ስር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም ትክክኛዋ ቤተክርስቲያን የትኛዋ ናት? የሚለውን በቀጣይ ምዕራፎች ውስጥ በሰፊው እንመለከታለን፡፡

## 3.2. ከመፅሀፍ ቅዱሱ በኋላ በመጣ "ቅዱስ" መፅሀፍ ከክርስትና የወጡ (ባኢ፣ ሞርሞኒዝም፣ ሺንቼአንጂ፣ የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒስትና የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ ናቸው)

እነዚህ ሀይማኖቶች በዋናነት የሚመሩት ከመፅሀፍ ቅዱሱ በኋላ በወረደላቸው "ቅዱስ" መፅሀፍ ነው፣ እነዚህ ቅዱሳን መፅሀፍት ከፊል መፅሀፍ ቅዱሳዊ ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪም እንደ ቁርአን የመስራቹንም አስተምህሮ ጨምረው ይዘዋል፡፡

ከነዚህ ሀይማኖቶች ውስጥ ባኢ፣ ሞርሞኒዝምና ሺንቼአንጂ የሚባሉት በሀገራችን ውስጥ በግልፅ እየሰሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒስትና የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ የሚባሉት ደግሞ በቤተክርስቲያን ደረጃ ባይደራጁም በግል የእነሱን አስተምህሮ የሚከተሉ ሰዎች አሉ ነገር ግን እስካሁን የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን ተከታይ ሀገራችን ውስጥ ይኑር አይኑሩ መረጃ የለኝም፡፡

በዚህ ምዕራፍም የነዚህ ሀይማኖቶች አስተምህሮ በዝርዝር በመመልከት የሁሉንም ማጠቃለያ ሀሳብ በአንድ ላይ እንመለከታለን፡፡

### 3.2.1. ባኢ(ባሀኡላህ) – Baha'I (Baha' Ullah)

[52] ይህ ሀይማኖት የተመሠረተው በ1844 ዓ.ም ራሱን "ባብ"(the gate) ብሎ በሚጠራው ሚርዛ አሊ መሀመድ በሚባል የሺአ እስልምና ተከታይ በነበረ ኢራናዊ ነው፣ ይህም ሰው ራሱን "መሀመድ ከዘሬ ይመጣል ያለው ክርስቶስ - መኽዲ"(የአቡ ዳውድ ሱና 4285) እንደሆነ ይናገራል፡፡

[53] "ሀይማኖቱ ከምስረታው አንስቶ ብዙ ስደቶችን ያስተናገደ ሲሆን፣ መሪውም እስኪገደል ድረስ አቶማን "ሶሪያ" ብሎ በሚጠራው ግዛቱ (የዛሬይቱ እስራኤል) ላይ ለ10 አመት ያህል ታስሯል፡፡ ምንም እንኳን ባብ በብዙ ስቃይ ውስጥ አልፎ ቢገደልም የሱ መገደል ግን ሀይማኖቱን

---

[52] **Mankinds search for God**, Watch Tower Bible and Tract Societyof Pennsylvania(1990), page 304

[53] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Baha'i Faith

ከመስፋፋት አላቆመም፣ በአሁኑ ጊዜም ሀይማኖቱ በአለም ላይ ከ7.3 ሚሊየን በላይ ተከታዮች አሉት፡፡"

"ባብ" ይህን ሀይማኖት ለመመሥረት ምክንያት የሆነውም "ሀይማኖቶች በሙሉ መነሻቸው መለኮታዊ ነው፣ ሀይማኖቶች የሚለያዩት አላስፈላጊ በሆኑ ጥቃቅን ነገሮች ነው" በሚል እምነቱ ነበረ፡፡ በዚህም ሀይማኖቱ የዋና ዋናዎቹን ሀይማኖቶች ነቢያት (አብርሃም፣ ሙሴ፣ ቡድሃ፣ ክሪሺና፣ ኢየሱስ፣ መሀመድ) ነብይነት የሚቀበል ሲሆን መስራቹም ራሱን በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያካትታል፡፡

ሀይማኖቱም የሚመራው ከመፅሀፍ ቅዱስና ከሌሎች ዕምነቶች መፅሀፍት አውጣጥቶ በራሱ መንገድ በፃፈው "አል ኪታብ አል አቅዳስ" (ከሁሉ የበለጠ የተቀደሰ መፅሀፍ) በሚባለው መፅሀፉ ነው፡፡" መፅሀፉም የየሀይማኖቶችን አስተምህሮ በአንድ ላይ በመጨፍለቅ የተዘጋጀ መፅሀፍ ሲሆን በአንድ ላይ መደባለቅ የማይችሉትን አስተምህሮዎችን ደግሞ ትቷቸዋል፣ በዚህም፣

- የክርስትና መሠረት የሆነውን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተከፈለውን ቤዛነትና የስላሴ አስተምህሮ፣
- የሂንዱይዝምን ደጋግሞ መወለድ (reincarnation) አስተምህሮ

በመፅሀፉ ውስጥ አላካተታቸውም፡፡

### 3.2.2. ሞርሞኒዝም (Mormonism/The Church of Jesus Christ Latterday Saints)

[54] "የሞርሞን ቤተክርስቲያን ጆሴፍ እስሚዝ በሚባል ሰው በኒውዮርክ ከተማ በ1820 ተመሠረተች፣ ቤተክርቲያኗ በአሁኑ ጊዜ ከ15 ሚሊየን በላይ አባላት እንዳሏት ይነገራል፡፡"

[55] "እንደ ቤተክርስቲያኗ አባባል ሞሮኒ የተባለው መልአክ በ1820 ዓ.ም ለጆሴፍ ተገልጦለት፣ ጆሴፍ የተሰወረውን የወርቅ ሳህን አግኝቶ በላዩ

---

[54] https://en.m.wikipedia>wiki>mormons

[55] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 49-51

የተፃፈውን መልዕክት እንዲተረጉም ነገረው፣ ጆሴፍም መልአኩ የነገረውን የወርቅ ሳህን "ኩሞራ" በተባለው ተራራ ስር በ1827 ዓ.ም አገኘው፣ መልአኩም ለጆሴፍ በሳህኑ ላይ የተፃፈውን ምልክት ማንበብ የሚችልበት "ዑሪምና ቱሚም" የተባለውን ትልቅ መነፅር ሰጠው፣ ጆሴፍም በዚያ መነፅር ፅሁፉን ተርጉሞ ከጨረሰ በኋላ በ1830 ዓ.ም ህይማኖቱ የሚመራበትን "The book of mormon" መፅሀፍ አሳተመ፡፡

ይህን "አዲስ" ተብሎ የቀረበው "ቅዱስ" መፅሀፍ በአብዛኛው መፅሀፍ ቅዱሱን ቃል በቃል በመገልበጥ እና የራስ ፍልስፍናዎችን በመጨመር የተዘጋጀ መፅሀፍ ነው፣ መፅሃፉ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ቃላትን ይያዝ እንጂ በውስጡ ብዙ መፅሀፍ ቅዱሱን የሚቃረኑ አስተምህሮቶችን ይዟል ለምሳሌ፡-

1. "እግዚአብሄር እንደኛው ሰው ነበረ፣ መፅሀፍ ቅዱሳዊ መርሆችም ቀድሞ በመረዳቱና በነዚህ መርሆች በመመራቱ ወደ እግዚአብሄርነት አደገ፣ በዚህም ማንም ሰው የሞርሞን መፅሀፍ በሚያስተምረው መልክ የመፅሀፍ ቅዱሱን መመርያ በመከተል ወደ እግዚአብሄርነት ማደግ ይችላል፣
2. የአዳም በሀጢያት መውደቅ አስፈላጊና መልካም ነበረ፣
3. ስላሴ ስራቸውን በህብረት የሚሰሩ ሶስት የተለያዩ አማልክት ናቸው፣
4. ኢየሱስ የሉሲፈር የመንፈስ ወንድም ነው፣ ስሙም ሚካኤል ወይንም አዳም ይባላል፣
5. የክርስቶስ ሞት ያለፈውን ሀጢያታችንን እንጂ የአሁኑንና የወደፊቱን አያጠፋም፡፡"

የሚሉ ትምህርቶችን እንመለከትበታለን፡፡

### 3.2.3. ሺንቼአንጂ (Shincheonji Church of Jesus the Temple of the Tabernacle of the Testimony, SCJ)

[56] “የሺንቼአንጂ ሀይማኖት በማርች 14, 1984 ሊ ማን-ሂ(Lee Man-hee) በሚባል ሰው በደቡብ ኮርያ ውስጥ ተመሠረተች፣ እንደ ሀይማኖቷ አስተምህሮ ሊ ዳግም የሚመጣው ክርስቶስ ሲሆን መፅሀፍ ቅዱሱ በዘይቤያዊ አነጋገር የተፃፈ በመሆኑ መፅሀፉን እንዲተረጉም ስልጣን የተሰጠው ሰው ሊ እንደሆነ ታስተምራለች፣ ቤተክርስቲያኗ በአሁኑ ጊዜ ከ120,000 በላይ አባላት አሏት፡፡”

[57] ሀይማኖቱ በክርስትና አስተምህሮ ይምጣ እንጂ በውስጡ የግብረ ሰዶምና የዮጋ አስተምህሮቶችን ይዟል፣ ኢየሱስ 12 ሐዋርትን መርጦ ወደ ዓለም እንደላከው መስራቹም በተመሳሳይ መንገድ 12 ደቀ መዛሙርቶች ያሉት ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ጴጥሮስ የተባለው ክንፍ ቅርንጫፍ ነው፣ ቤተክርስቲያኗ አዲስ አበባ ውስጥም የአምልኮ ቦታዎች ያሏት ሲሆን ሰዎችንም ወደ ሀይማኖቱ የሚጋበዙትም በድርጅቱ ስም ሺንቼአንጂ ሳይሆን “የኮሪያ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ውስጥ መፅሀፍ ቅዱስ እናጥና” በሚል ቀላል ዘዴ ነው፡፡”

### 3.2.4. የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን (Unification church/ Unification movement)

ሀይማኖቷ ራሷን “ቤተክርስቲያን” ትበል እንጂ የቤተክርስቲያን እራስ ከሆነው ክርስቶስ በላይ የምትመለከተው ነብይ ስላላት ሀይማኖቷ “ቤተክርስቲያን” መባል ባትችልም በዚህ ክፍል ብቻ ሀይማኖቷ ራስዋን በምትጠራበት ስም “ቤተክርስቲያን” ብለን እንጠራታለን፡፡

---

[56] https://en.m.wikipedia>wiki>Shincheonji Church of Jesus the Temple of the Tabernacle of the Testimony

[57] https://mbasic.facebook.com.YeChristian Tube (Christian Tube - ክርስቲያን ቲዩብ), posted on sep.21, 2019

[58] "የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን በ1950 ስሙ ሰን ማየንግ ሙን በተባለ በደቡብ ኮሪያ በሚኖር ሰሜን ኮሪያዊ ተመሠረተ፣ ሙን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ደቡብ ኮሪያ ውስጥ የተማረ ሲሆን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ጃፓን ውስጥ ተማረ፡፡" እንደ "ቤተክርስቲያኗ" እምነት [59] ሙን የ16 አመት ልጅ ሳለ በአፕሪል 17, 1935 ዓ.ም፣ በፋሲካ ጠዋት ላይ ኢየሱስ ተገልጦለት "በመሰቀሌ ምክንያት ያልጨረስኳቸውን ስራዎች ትጨርሳለህ" በማለት ተናገረው ይላሉ፡፡

በዚህም ሙን "ሶስተኛው አዳም" ስለሚባል፣ ሙን ራሱን ከአንደኛውና ከሁለተኛው አዳም(ኢየሱስ) አስበልጦ ይናገራል፣ በዚህም "በእግዚአብሄር ከተላኩ ቅዱሳን መካከል በጣም የተሳካልኝ እኔ ነኝ፣ ስለ ህይወትና ስለ ዓለም ኢየሱስን ጨምሮ ከብዙዎች ጋር ተከራክሬ ሁሉንም ካሸነፍኩ በኋላ ራሳቸውን ለኔ አስገዝተዋል" ይላል፡፡

ሙን "ለቤተክርስቲያንዋ" መመሪያነት "መለኮታዊ መመሪያ"(The devine Principle) የሚል ቅዱስ መፅሀፍ ከመፅሀፍ ቅዱሱንና ከራሱን ፍልስፍና በማቀናጀት ያዘጋጀ ሲሆን ይህም መፅሀፍ በቤተክርስቲያንዋ ከመፅሀፍ ቅዱሱ እንኳን ቅድሚያ የሚሰጠው መፅሀፍ ነው፡፡

መፅሃፉ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ቃላትን ይያዝ እንጂ በውስጡ ግን ብዙ መፅሀፍ ቅዱሱን የሚቃረኑ አስተምህሮቶችን እንመለከታለን፣ ለምሳሌ፡-

- "ሰው ስጋ የለበሰ እግዚአብሄር ነው፣
- ኢየሱስ ሰው እንጂ አምላክ አይደለም፣
- ሰው በሀጢያት የወደቀው እንዳይበላው የተከለከለውን ፍሬ በመብላቱ ሳይሆን ሄዋን በስጋዋ አዳምን ስለፈተነችው ነው፣
- ሄዋን ከሉሲፈር ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት አድርጋ ቃየል ተወለደ ይህም <u>የኮምኒዝም ስርአት</u> ነው፣ ሄዋን ከአዳም አርግዛ አቤል ተወለደ ይህም <u>የዲሞክራሲ ስርአት</u> ነው፣

---

[58] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 103

[59] http://en.m.wikipedia.org>wiki>unification church

- ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱ የእግዚአብሄር እቅድ አልነበረም፣ የክርስቶስ ትንሳኤና ምፅአት የሚባሉት አስተምህሮቶች የስህተት ትምህርት ናቸው፡፡”

የሚሉ ትምህርቶችን እንመለከትበታለን፡፡

### 3.2.5. ክርስቲያን ሳይንስ (Christian Science)

[60]“የክርስቲያን ሳይንስ ሀይማኖት በ1879 ዓ.ም ሜሪ ቤከር በተባለች ሴት መሪነት በአሜሪካ ሀገር ተመሠረተ፣ ሜሪ ብዙ ታዋቂነት አግኝታ ሀይማኖት እንድትመሰርት ያበቃት “ሳይንስና ጤንነት” በሚለው መፅሀፏ ታዋቂነት ምክንያት ነው፡፡”

ሜሪ “መፅሀፍ ቅዱስ ስልጣን ያለው መፅሀፍ ቢሆንም ብዙ ስህተቶች ያሉበት መፅሀፍ ነው” በማለት በራስዋ ፍልስፍና “አስተካክላ” ያዘጋጀችው መፅሀፍ ከመፅሀፍ ቅዱሰ በላይ ስልጣን እንዳለው ትናገራለች፣ ተከታዮቿም [61]“ሜሪ ሳይንስና ጤንነት የሚባለውን መፅሀፍ ያዘጋጀችው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመሆኑ መፅሀፉ ከስህተት ሁሉ ነፃ የሆነ ትክክለኛ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም ነው” ብለው ያምናሉ፡፡

መፅሀፉ የመፅሀፍ ቅዱስ ቃላትን ይያዝ እንጂ መሠረታዊ የሆኑትን የመፅሀፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች አይቀበልም፣ ከነዚህ ውስጥ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- “እግዚአብሄር ሰብአዊነት ያለው አካል ሳይሆን፣ አእምሮ፣ ህይወት፣ እውነት፣ ፍቅር፣ ፕሪንሲፕል ... ማለት ነው፣
- ድንግል ማርያም መንፈሳዊ የሆነ ሀሳብ አርግዛ ወለደች፣ ሃሳቧንም “ኢየሱስ” አለችው፣
- ሰው “የፍቅር ሀሳብ” ምስል እንጂ ቁስ አካል አይደለም፣

---

[60]https://en.m.wikipedia>wiki>Christian Science

[61] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 63

- ሀጢያት፣ በሽታና ሞት የተሳሳተ አስተሳሰብ ውጤቶች ብቻ ናቸው፣ ኢየሱስም የመጣው "ሀጢያት አለ" የሚለውን የተሳሳተ እምነት ለማጥፋት ነው፣
- በሽተኞች የሚፈወሱት "በሽታ የለም" ብለው በመካድ ሳይሆን በሽታ አለመኖሩን ሲያውቁ ብቻ ነው፣
- የሀጢያተኛው ሲኦል ሌላ ነገር ሳይሆን ክፉ ማድረጉ ነው፣ ቅዱሱም ትክክል የሆነውን ነገር በማድረግ የራሱን መንግስተ ሰማያት ይፈጥራል፣
- ፀሎት አስፈላጊ ነገር ሲሆን የሚፀለየው ግን ወደ ሰብአዊው አምላክ ሳይሆን "መለኮታዊ ሀሳብ" ወደ ሆነው አምላክ ነው፣
- የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የጌታቸውን ሀይልና ስልጣን አላወቁም ነበረ፣ ከተሰቀለ በኋላ ያልሞተ መሆኑን እስከሚረዱበት ጊዜ ምንም አይነት ተአምርና አስደናቂ ስራዎች አልሰራም ... በመቃብሩ ውስጥ ኢየሱስ የተደበቀ መሆኑን ስላላወቁ ኢየሱስ ሞቷል ብለው አመኑ፡፡"

የዚህን ሀይማኖት መመሪያዎች ከኢአምላካውያኑ ሂውማኒዝም ጋር በብዙ መልኩ የሚመሳሰል ሲሆን ነገር ግን ክርስቲያን ሳይንስ ከሂውማኒዝም በተለየ በአንድ በኩል ወደ መንፈሳዊነት ጠለቅ በማለት ፀሎት፣ የክርስቶስ መስቀል ላይ ዋጋ መክፈል ... የሚባሉ አስተምህሮዎችን ሲከተሉ በሌላ በኩል ደግሞ ከሂውማኒቲ በራቀ "በሽታ የሚባል ነገር የለም" የሚል አስተምህሮ ይከተላሉ፡፡ በዚህ "በሽታ የለም" አስተምህሮ ምክንያትም ብዙ የቤተክርስቲያኗ አባላት የህክምና እርዳታ ሳያገኙ ሊድን በሚችል በሽታ አልቀዋል፡፡

### 3.2.6. <u>አማኝ ኢቮሉሽኒስት (Theistic Evolutionism/God-Guided Evolution)</u>

[62] እነዚህ ቡድኖች ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱንና የኢቮሉሽንን(የዝግመተ ለውጥን) ሳይንስ በማጣመር አዲስ እምነትን የፈጠሩ ሲሆን የዚህ እምነት ተከታዮችም እግዚአብሄር ፍጥረታትን ለመፍጠር የኢቮሉሽንን(የዝግመተ ለውጥ ህግ) እንደተጠቀመ ያምናሉ፡፡

---

[62] ዘለቀ በሃይሉ (2010)፣ **ሉሲ ምን ያህል ዕውነት ነች**፣ ገፅ 99

[63]እምነቱ የሚመራው፣ ፍራነሲስ ኮሊንስ የተባለው ሰው በ2006 ዓ.ም መፅሀፍ ቅዱሱና የኢቮሉሽን ሀሳቦችን በአንድ ላይ በመቀየጥ "The Language of God" ብሎ ባሳተመው መፅሀፍ ነው፣ መፅሀፉም የሳይንስና መፅሀፍ ቅዱስ ቅይጥ ነው፣

- "እግዚአብሄር ከ14 ቢሊየን አመታት በፊት ዩኒቨርስን ፈጠረ፣
- ዩኒቨርስም ህይወትን እንድታወጣ አስተካከለ፣
- ህይወት የምትባለዋ ነገር ከተጀመረች በኋላ ፈጣሪ ሌላ ተጨማሪ ጣልቃ ገብነት አላደረገም፣
- ከዚህችም የህይወት መጀመሪያ ፍጥረታት በዝግመተ ለውጥ ህጉ መጡ..."

አስተምህሮቱ "መፅሀፍ ቅዱሱንና የኢቮሉሽን ፅንሰ ሀሳቦችን በአንድ ላይ አስታርቀናል" ይበል እንጂ መፅሀፍ ቅዱሱና የኢቮሉሽን ሀሳቦች ከተጋጩ ለኢቮሉሽኑ ሃሳቦች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

### 3.2.7. የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ (The new age movement)

[64] ይህ ሀይማኖት በ1970 ዓ.ም በምእራባውያን ሀገራት ተመሠረተ [65] ሀይማኖቱም አንድ ወጥ ሀይማኖት ሳይሆን በውስጡ ብዙ እምነቶችን ክርስትና፣ የዮጋ፣ የተመስጦ፣ የኮከብ ቆጠራ ... ሰብስቦ ይዟል ለዚህም የሚያቀርበው ምክንያትም "አንድ ፍፁማዊ መንፈሳዊ መንገድ የለም" የሚል ነው፡፡ የህይማኖቱ ዋነኛ አስተምህሮም "ሰዎች መንፈሳዊ ማንነታቸውን (እግዚአብሄር የሆነውን ማንነት) በማሳደግ እግዚአብሄርነት ጋር እንዲደርሱ መርዳት ነው፡፡" በዚህም የህይማኖቱ ዋነኛ አትኩሮት የግለሰቦችን መንፈሳዊ ሀይል ማበረታታት ላይ ነው፡፡

ሀይማኖቱ በዋናነት የሀንዳውያን አስተምህሮ የሚያነሳ በመሆኑ ራስን በተመስጦ ውስጥ አስገብቶ አእምሮን ፍፁም ባዶ በማድረግ ከአማልክት

---

[63]https://en.m.wikipedia>wiki>The language of God
[64]https://en.m.wikipedia>wiki>new age
[65] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 109

ምሪትን የመቀበል፣ ዮጋ፣ በተመስጦ ውስጣዊ ስሜቶችን በማዳመጥና በመከተል ወደ ደህንነት ማደግና "ደጋግሞ መወለድ" (reincarnation) አስተምህሮን በዋናነት ይከተላል፡፡

የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ ክርስቲያናዊ ቃላትን በሽፋን እየተጠቀመ ብዙ ክርስቲያኖችን መውሰድ ይቻል እንጂ ውስጡን ስንመለከት ብዙ ኢ-ክርስቲያናዊ አስተምህርቶችን ይዟል፣ ለምሳሌ፡-

- "ሰው እግዚአብሄር ነው፣
- ሰው "እግዚአብሄር" ስለሆነ ደህንነቱ በራሱ እጅ ነው፣ ሌላ አዳኝ አያስፈልገውም፣
- ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን ትልቅ መምህርና ለሰዎች ምሳሌ የሚሆን የህይወት መርህ የነበረው ሰው ነበረ፡፡"

እነዚህ አስተምህሮቶችም መሠረታዊውን የክርስትና አስተምሮ ይጥሳል፡፡

ብዙ ሰዎች፣ ሀይማኖቶችን አንድ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱትን ሶስቱን የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ፣ ኢኩሜኒዝምንና ባኢን አንድ አድርገው ቢመለከቱም በሶስቱ መካከል ግን መሠረታዊ ልዩነቶች አሉ፣ ኢኩሜኒዝም የሚንቀሳቀሰው የክርስትና ሀይማኖቶችን (አርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት...) አንድ ለማድረግ ነው፣ የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴና የባኢ አትኩሮት ግን ሁሉንም ሀይማኖቶች አንድ ለማድረግ ሆኖ ሁለቱም አንድነቱን መስራት የሚፈልጉት ግን በተለያየ መሠረት ላይ ነው፣ ባኢ የሀይማቶች አንድነት ለመፍጠር የሚሰራው በእስልምና መሠረት ላይ ሲሆን የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ ደግሞ በህንዶችን ሀይማኖት መሠረት ላይ ነው፡፡

## ማጠቃለያ(የራሳቸው "ቅዱስ መፅሀፍ" አዘጋጅተው ከክርስትና የወጡ)

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ሀይማኖቶች ከእስልምና ቦሃላ ነገር ግን እንደ እስልምናው መፅሀፍ ቅዱሱን ተተግነው በመነሳት ብዙዎችን ከመፅሀፍ ቅዱሱ መንገድ ያፈለሱ ሀይማኖቶች ናቸው፡፡

ከነዚህ ሀይማኖቶች ውስጥ ባኢ፣ ኢኩሜኒዝምና የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ ሀይማኖቶች፣ ሀይማቶችን አንድ ለማድረግ እንደሚሰሩ ቢናገሩም "ልዩነታችንን ትተን በአንድ ላይ እናምልክ" አካሄዳቸው ግን አደገኛ ሴራ ያለበት አካሄድ ነው፣ ይህም እያንዳንዱ ሀይማኖት ወደ አንድነቱ ለመምጣት ሲል ቢያንስ አንድ ዕሴቱን አጉድሎ ይመጣል፣ በዚህም በትክክለኛ አስተምህሮን የምትከተለው አንዷ(በዚህ ደረጃ ያልለየናት) ቤተክርስቲያን ለአንድነቱ ስትል የራሷን እሴቶች አጉድላ ከትክክለኛ መንገድ ጎድላ ትመጣለች፣ ይህ ደግሞ ትክክለኛዋ ቤተክርስቲያን ከምድረ ገፅ እንድትጠፋ ያደርጋል፣ ከዚህ በተጨማሪ ቅዱሱ ከእርኩሱ ጋር አብሮ መስራት ስለማይፈልግ አካሄዱ በቅዱሱ መንፈስ የሚኖሩትን በእርኩሱ መንፈስ እንዲያዙ የሚያደርግ አካሄድ ነው፡፡

የሰው ልጆችን መንፈሳዊ አንድነትን ለማምጣት መስራት በጎ ነገር ቢሆንም ይህንን አንድነት ማምጣት የሚቻለው ግን እንደዚች መፅሀፍ ትክክለኛውን መንገድ መርምሮ በማሳየት መሆን ሲገባ "አንድ ሲደመር አንድ ሁለትም፣ ሶስትም፣ አራትም … ሊሆን ይችላል" በሚል የማሸማገልና በሚጋጩበት ቦታ ደግሞ የራስን ሀይማኖት በሌላው ላይ በመጫን መሆን የለበትም፡፡

ከላይ የቀረቡት የሰባቱን ሀይማኖቶች አካሄድ በአንድ ላይ አጠቃለን ስንመለከት፣ ሁሉም የእስልምናውን ተሞክሮ በመውሰድ መፅሀፍ ቅዱሱን ለመተዋወቂያነት ተጠቅመው በዚያ ላይ የራሳቸውን ፍልስፍና ከሽነው የራሳቸውን ቅዱሳት መፅሀፍት በማዘጋጀት ብዙዎችን ከክርስትና ገንጥለው የወጡበትን እውነታ እንመለከታለን፡፡

"ነቢዩ" መሀመድ እስልምናን ሲፈጥር ከመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የሚመቹትን ክፍሎች በመውሰድና የራሱን በመጨመር ቁርአንን እንዳዘጋጀው እነዚህ ሀይማኖቶችም ከመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የተቀነጫጨቡ እውነታዎችን ከራስ

ፍልስፍና ጋር በማዋሃድ ባዘጋጁት "ቅዱስ መፅሀፍ" ነው ከክርስትናው ብዙዎችን አስኮብልለው የወጡት፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ግን ማንም መንደርደሪያ እያደረገው የራሱን ፍልስፍና እየጨመረ ሰዎችን በተሳሳተ መንገድ ይዞ እንዳይሄድ ቀድሞውኑ ራሱን የሚከላከልበትና አጭበርባሪዎች የሚጋለጡበትን መንገድ አስቀምጧል፣ ይህም፣

- በመፅሀፍ ቅዱሱ አዳዲስ መሠረታዊ ነገሮች ከመምጣታቸው አስቀድሞ በነቢያት አፍ እየተተነበየ የሚሰራበት መርህ፣ ይህ የአሰራር መርህም በሰበር የሚገባ እንግዳ አስተምህሮ እንዳይኖር ያደርጋል፣ ለምሳሌ አዲስ ኪዳን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ … ሳይመጡ በፊት በነቢያቱ ቀድሞውኑ በትንቢት ሲነገር ነበረ፣ ለወደፊት የሚመጡት እንኳን ለምሳሌ፣ ኢ-ኮሜርስ፣ የአርማጌዶን ጦርነት፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ … ቀድመው ተተንብየው ይገኛሉ፡፡

በዚህም በመፅሀፍ ቅዱሱ የአሰራር መርህ ሰበር ነገር የለም፣ እነዚህ ሀይማኖቶችም ከመፅሀፍ ቅዱሱ ተነስተው ያደረጉት መሠረታዊ ለውጥ በምንም ትንቢት አለመደገፉ በመፅሀፍ ቅዱሱ መንገድ አለመሆናቸውን መፅሀፉ በራሱ ያሳየናል፡፡

የሚገርመው ደግሞ እነዚህ ሀይማኖቶች በመሀመድ ተምሳሌት ቢነሱም ቢያንስ እንኳን እንደ መሀመድ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ "አህመድ የሚባል ነብይ እንደሚመጣ በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ተተንብዮ ነበር" የሚል የሀሰት መንጠልጠያ እንኳን መስራት አልቻሉም፣ በተጨማሪም እስልምናው እንደ ተጠቀመው እንደ ጂሃድ አይነት ፍቱን መስፋፍያ እስትራቴጂ አልተጠቀሙም እንጂ አነሳሳቸው በተመሳሳይ መንፈስ ነበረ፡፡

- መፅሀፍ ቅዱሱ ሲፃፍ የድርጊቶችን ክሮኖሎጂ(የጊዜ ቅደም ተከተል) በጠበቀ መልኩ ነው፣ በዚህም ሲጀምር "በመጀመሪያ" ብሎ በቁሳዊው አለም መጀመሪያ ታሪክ ጀመረ፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ከ1,500 አመታት በኋላ ተፅፎ ሲያልቅ የቁሳዊውን ፍጥረት መጨረሻ ምን እንደሚሆን አሳይቶ "በመጨረሻም" ብሎ "በዚህ ላይ ማንም እንዳይጨምርበት" ብሎ

ዘጋ(ራዕ.22፡18-19)፣ በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ ተጨማሪ አዲስ መፅሀፍ የሚቀበልበት አሰራር የለውም፡፡

- ኢየሱስም የመጣበትን አላማ ጨርሶ ሰውንና እግዚአብሄርን በማስታረቅ ከዚያም “እኔ መንገድ ነኝ በዚህ መንገድ ሂዱ” በማለት በመሄዱ ሐዋርያቱም ይህንኑ አስረግጠው ገላ.1፡8 “ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን፡፡” ማለታቸውን ስንመለከት አዲስ መንገድ የተዘጋ መሆኑን፣ ከዚህ ወንጌል መንገድ ላይ አዲስ አስተምህሮ ማስኬድ የማይቻል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ አስተምህሮዎች መፅሀፍ ቅዱሱ በተፃፈበት መንፈስ ሊፃፉ አለመቻላቸውና ይባሱኑ ከላይ እንደተመለከትነው ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር በሀሳብ መለያየታቸው መፅሀፎቹ በተለየ መንገድ ላይ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ እነዚህን ቅጥያ አስተምህሮቶችን የሚቀበልበት አሰራርም ሆነ ቦታ የለውም፣ በምንም ሊረዳቸው አይችልም፣ አጭበርባሪነታቸውን ከማጉላት በቀር፡፡ በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱን መነሻ አድርጎ ሰውን ከመፅሀፍ ቅዱሱ አንስቶ በሌላ መንገድ መቀየስ ለሚፈልጉ አጭበርባሪዎች መንገዱ ዝግ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ይህ እውነታ በእንዲህ እንዳለ፣ እስልምናም ሆነ እነዚህ ሰባቱ ሀይማኖቶች መፅሀፍ ቅዱሱን መንደርደሪያ አድርገው ተነስተው ተመልሰው መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የመነሳታቸው እውነታ የመፅሀፍ ቅዱሱን እውነተኛ የፈጣሪ ቃልነት የሚያረጋግጥና የሰይጣንን የመፅሀፍ ቅዱሱን የማራከስ ሰፊ ጥረቶችን የሚያረጋግጥ ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

በዚህም በአጭበርባሪዎች ተታለው ክርስትናን የተውት ሀይማኖቶችና ተከታዮቻቸው በሙሉ ወደ ክርስትና መመለስ እንዳለባቸው እንመለከታለን፣ በክርስትና ስር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም ትክክኛዋ ቤተክርስቲያን የትኛዋ ናት? የሚለውን በቀጣይ ምዕራፎች ውስጥ በሰፊው እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. ኦርቶዶክስና ካቶሊክ

የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፣ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ቀድሞ "የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን" ከሚባለው ወጥ አሰራር በኋላ መከፋፈሎች መምጣት ሲጀምሩ እንደተፈጠሩ ይታመናል፡፡ አብያተ ክርስቲያናቱ ምንም እንኳን ከታች የምንመለከታቸው ችግሮች በዘመናት ሂደት ውስጥ የገቡባቸው ቢሆንም መፅሀፍ ቅዱሱ ከእስራኤል ተነስቶ ለአለም እንዲዳረስ ማድረጉ ላይ ሰፊ ስራ ሰርተዋል፡፡

የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ እጅግ የተቀራረበ በመሆኑ መሠረታዊ ልዩነቶቻቸው ከፈጣሪ ውጪ ባሉት ከማርያም፣ ታቦት፣ መላእከት፣ ፃድቃን፣ ሰማዕታት … ጋር በተያያዘ የሚከተሉት የተለያየ የአሰራርና የአከራሪነት ደረጃ ነው፣ የዚህች መፅሀፍ አትኩሮት በመሠረታዊው የዕምነት አስተምህሮ ላይ በመሆኑ ይህንን የሁለቱን ሀይማኖቶች ልዩነት በመተው ሁለቱንም ሀይማኖቶች በአንድ ላይ ተመልከታለች፡፡

ብዙዎች እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ከጥንት የመጡ በመሆናቸው ምንም ችግር እንደሌለባቸው ይናገራሉ ነገር ግን "ጥንትነት" ዋስትና እንደማይሆንና እነሱ ይቅርና ዋናዎቹ የመሠረቱዋቸው አብያተ ክርስቲያናት እንኳን በሰይጣን ሴራ ተጭበርብረው ከነበሩበት ትክክለኛ መንገድ ሲወጡ እንደነበረ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ እንመለከታለን፤ ኢየሱስ ካረገ 100 አመት እንኳን ሳይሞላው ነው አዳዲስ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ከስህተታቸው እንዲመለሱ ሲመክር የነበረው(ራዕ.2፡14, ራዕ.3፡2 …)፣ ጳውሎስም ከመሠረታቸው ጥቂት አመታት እንኳን ያላስቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ከስህተታቸው እንዲመለሱ ሲወቅስ ነበረ(1ቆሮ.1፡12)፣ በብሉይ ኪዳንም እንደዚሁ እግዚአብሄር ቅዱሳኑን ተጠቅሞ በቤተመቅደሱ ውስጥ ብዙ የተሀድሶ ስራዎች ሲሰራ ነበረ(ዘፀ.32፡20, መሳ.6፡25-30, 2ነገ.10፡26-28, 2ነገ.23፡4, 2ዜና.29፡5, 2ዜና.34 …)፡፡

ይህም የሆነው ሰዎች በትክክለኛው መንገድ እንዳይሄዱ የሚፈልገው ሰይጣን በመኖሩ ነው፣ የሰይጣን ሰርጎ ገብነትና እግዚአብሄር ደግሞ ቤቱን የሚያድስበት አሰራር የተመለደ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ነው፣ ስለዚህ ከ"ስህተት ነፃ" አባባል ትክክል የሚሆነው ሰይጣን በህይወት ከሌለ ብቻ ነው፣ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናትም ብዙ ዘመናትን አልፈው እንደመጡት መጠን ለብዙ የሰይጣን ሴራዎች እንደሚጋለጡ ሳይታለም የሚፈታ እውነታ ነው፡፡

በነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የገቡትን መሠረታዊ ስህተቶችን ስንመለከት በአራት ክፍል ይመደባሉ፣ እነዚህም፣

- የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ቦታ ከኢየሱስና ከእግዚአብሄር ወሰን ጋር መቀላቀል፣
- ብሉይ ኪዳን እያለ አዲስ ኪዳን የመጣበትን ሚስጥር አለማግኘት፣
- ቅድስናቸው ሳይፈተሽ ከቅዱሳን መፅሀፍት የተቀላቀሉ ተጨማሪ መፅሀፍት፣
- ከዋናው መፅሀፍ ቅዱስ የሚጋጩ ትውፊቶች

ናቸው፣ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## 4.1. የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ቦታ ከኢየሱስና ከእግዚአብሄር ወሰን ጋር መቀላቀል

ማርያም/ቅዱሳን/መላዕክት በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያናት የገዘፈ ቦታ ይሰጣቸዋል፣ ይህ አሰራርም የእነዚህ አካላት ቦታ ከኢየሱስና ከእግዚአብሄር ወሰን ጋር እንዲቀላቀል አድርጓል፣ በዚህም የአማላጅነት ስራ፣ የሰው ልጅችን ከሲኦል የማዳን ስራ እንዲሁም መመለክ ያለበት ማን መሆን እንዳለበት/እንዳለባቸው በቤተክርስቲያኗ ተደበላልቆ ይገኛል፣ በዚህም፣

- ሰማያዊ አማላጅ ማነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሶስቱ ወይስ ሁለቱ?
- የሰው ልጆች ከሲኦል እንዲድኑ ምክንያት የሆነው ማን ነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሶስቱ ወይስ ሁለቱ?
- መመለክ ያለበት ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ እግዚአብሄር፣ ወይስ አራቱም?

የሚሉትን ጥያቄዎች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1. ሰማያዊ አማላጅ ማነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሶስቱ ወይስ ሁለቱ?

“አማላጅ” የሚለው ቃል በዋናነት ሁለት መፅሀፍ ቅዱሳዊ ትርጉሞች አሉት፣ በመጀመሪያ ደረጃ ያለው “ተጣልተው የተለያዩ አካላትን የሚያስታርቅ” ማለት ሲሆን ሁለተኛው የምልጃ ትርጉም በብዙ ሰዎች ዘንድ የማይታወቀው በሮሜ.8፡26 ላይ የምንመለከተው “ጉድለትን በመሙላት ብቁ ማድረግ” ማለት ነው”፣ በዚህ በሁለተኛው የምልጃ ትርጉም ላይ ሁሉም ጋር ያለው አስተሳሰብ ተመሳሳይ በመሆኑ ልዩነት የተፈጠረበትን የመጀመርያውን አተረጓጎም በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

የማስታረቅ ምልጃ በሁለት ይከፈላል፣ ምድራዊና ሰማያዊ ምልጃ በሚል፣ ምድራዊው ምልጃ ቅዱሳን በአፀደ ስጋ እያሉ ስለሌሎች ሰዎች የሚያደርጉት ፀሎት ነው፣ መፅሃፍ ቅዱሱ ቅዱሳን በምድራዊው ህይወታቸው

ስለ ሌሎች ሰዎች እንዲማልዱ ያዛል(1ጢሞ.2፡1-2)፣ እዚህም ላይ ሁሉም ተመሳሳይ ሀሳብ ስላለው እዚህ ውስጥም አንገባም፡፡

ነገር ግን በብዙዎች መካከል ሰፊ ልዩነት የፈጠረው በሰማይ(በመንፈሳዊው አለም) ስለሚደረገው ቋሚ የምልጃ አይነት ነው፣ በዚህም በሰማያዊው ስፍራ በአማላጅነት ለሰው ልጆች በቋሚነት የሚቆመው ማነው? የሚለውን በሰፊው እንመለከታለን፡፡

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በድሮው ጊዜ ማርያም፣ ቅዱሳንና መላዕክት በሙሉ ሰማያዊ አማላጅ እንደሆኑ ሲነገር ነበረ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በተለይ ከ“ማህበረ ቅዱሳን” እና ዘመናዊ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ጋር በተያያዘ ከማርያም ውጪ ስላሉት አማላጅነት የምንሰማው ድምፅ እያነሰ መጥቷል፣ አሁን ያለው ትልቅ ድምፅ ማርያም - “አማላጅ”፣ መላዕክት - “ተራዳኢ”፣ ፃድቃን/ሰማእታት - “መታሰቢያ የሚደረግላቸው” ወደሚለው ሲያዘነብል ይታያል፡፡

ይህ የስራ ክፍፍል በአሰራር ደረጃ የተሻለ ነው ምክንያቱም ማርያም፣ መላዕክትና ቅዱሳን የተለያየ ተፈጥሮ፣ ማንነት፣ ችሎታ፣ ስልጣን ... ስላላቸው ሁሉንም እኩል አድርጎ አንድ ስራ ላይ መመደብ አሳማኝ አልነበረም ይባሱኑም “ሁሉም አማላጆች ናቸው” ማለቱ ብዙ ጥያቄን ይፈጥራል፣ አንዱ ብቻውን ሙሉ ምልጃ ማድረግ አለመቻል ነው? ወይስ አንዱ ባያማልደኝ ወይ ቢረሳኝ ሌላው አልፎበት ይሰራል ከሚል ነው? ወይስ አማላጆቹ መካከል ተቀናጅቶ የመስራት ችግር ስላለ ነው? ወይስ ፈጣሪ ዘንድ መግባት ላይ ልዩነት ስላለ ነው? የሚሉ ግራ መጋባቶችን ይፈጥር ነበረ፡፡

ስለዚህም ከዚህ ግራ አጋቢ አሰራር ወጥቶ አንድ ቋሚ ለምልጃ ሙሉ ብቃት ያለውና ለዚህ አገልግሎት የተለየ አማላጅ መምረጡ ትክክል ነው፣ በዚህም ይመስላል ባሁኑ ጊዜ “ማርያም” ከሁሉ በላቀ የአማላጅነትን ማዕረግ ይዛ ነጥራ ወጥታለች፣ በዚህም “ያለ ማርያም አማላጅነት ዓለም አይድንም” እስከማለት ተደርሷል፡፡

በርግጥ በነፍስ አፀድ ያሉቱ ቅዱሳንና መላዕክቱ ባሉበት በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሄር አማላጅ አጣሁ(ኢሳ.59፡16, ሕዝ.22፡30-31 ...) ማለቱና በዚህ ላይ ደግሞ መላዕክቱና ቅዱሳኑ እልፍ አእላፍ መሆናቸውና እነሱም

በሀይልና በስልጣን መለያየታቸውን ስንመለከት ሰማያዊውን የምልጃ አገልግሎትን ከቅዱሳኑና ከመላዕክቱ ላይ አንስቶ ለማርያም ብቻ መስጠቱ አግባብነት አለው፡፡

ነገር ግን ይህንን የምልጃ አገልግሎትን ከቅዱሳኑ አንስቶ ለማርያም ብቻ መስጠቱ ደግሞ ሌላ ክፍተት ይፈጥራል፣ ይህም የምልጃቸው ልዕቀታቸውን መፅሀፍ ቅዱሱ የሚመሰክርላቸው ሙሴና ሳሙኤል(ኤር.15፡1) እያሉ ማርያምን ከነሱ በላይ ማስኬዱ አሳማኝ አይደለም እንደዚሁም በስጋው ወራት ስለ እስራኤል ዘር መዳን ያማለደው ሙሴ(ዘኁ.14፡11-20) እያለ ወይን ጠጅ ስለማስሞላት የማለደችውን ማርያምን ማስበለጥ አሳማኝ አይደለም፡፡

በነዚህ ግራ አጋቢ ነገሮች ላይ ደግሞ ማርያም፣ መላዕክትና ቅዱሳን ሰዎች ከምድር የሚፀልዩትን ፀሎት ለመቀበል እንደ እግዚአብሄር "በሁሉም ስፍራ የመገኘት" ችሎታ አላቸው? ብለን ስንመለከት ደግሞ አማላጅነታቸው ላይ ሌላ ጥያቄን ይፈጥራል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን አማላጅነት ሀሳቦች እንደዚህ መምታታቱ የሰማያዊው የአማላጅነት ስራ የእነሱ ስራ ባለመሆኑ ይሆን እንዴ? የሚለውንም ጥያቄ መመልከቱ ተገቢ ነው፣ ስለዚህ የማርያም፣ መላዕክት፣ ቅዱሳንና የኢየሱስን አገልግሎቶችና ማንነቶችን በዝርዝር በመመልከት ትክክለኛው ሰማያዊ አማላጅ ማነው? የሚለውን ጥያቄ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 4.1.1.1. የማርያም አማላጅነት

መፅሀፍ ቅዱሱ ማርያም ብፅዕት እንደሆነችና ኢየሱስን በድንግልና አርግዛው በድንግልና እንደወለደችው ይናገራል፣ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ለማርያም የሚሰጠው ቦታ ግን ከዚህ ባለፈ ማርያም ሰማያዊ አማላጅ እንደሆነች ይነገራል፡፡

ለዚህ ሃሳብ በዋናነት የሚቀርበው መከራከሪያም "የማርያም የቃና ዘገሊላ ምልጃ የሰማያዊው ምልጃዋ ተምሳሌት ነው" የሚልና ከመፅሃፍ ቅዱሱ ውጪ በሌሎች መፅሃፍት ላይ ስለ ማርያም የተገለፁት "ማርያም ስለሰው ልጆች ሃጢያት ሞተች በሶስተኛው ቀን ተነሳች … በአብ ቀኝ ትገኛለች" በሚሉ አስተምህሮዎች መሠረት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

#### 4.1.1.1.1. “የማርያም የቃና ዘገሊላ ምልጃ የሰማያዊው ምልጃዋ ተምሳሌት ነው”

የቃና ዘገሊላን ታሪክ የምናገኘው በዮሐ.2፡1-11 ላይ ነው፣ ይህ ቃል የሚናገረው ማርያምና ኢየሱስ ቃና ዘገሊላ በተባለ ቦታ ሠርግ ላይ ተገኝተው በነበረ ጊዜ የወይን ጠጅ በማለቁ ማርያም ኢየሱስን ለምና ኢየሱስም በተአምራዊው መንገድ ውሀን ወደ ወይን ጠጅ የቀየረበት ታሪክ ነው፡፡ ቤተክርስቲያንዋም ከዚህ ታሪክ በመነሳት “ማርያም በቃና ዘገሊላው ሰርግ ላይ አማልዳለች” ከማለት አልፋ “የቃና ዘገሊላው ምልጃ የማርያምን ሰማያዊ ምልጃ ምሳሌ ነው” ትላለች፡፡

እዚህ ጋር ምድራዊውን የምልጃ ስራ ወደ ሰማዊው ተምሳሌትነት ከመውሰዳችን በፊት፣ የምድራዊው ምልጃዋ ላይ የነበረውን ክፍተት መመልከቱ ጠቃሚ ነው፣ ይህም ማርያም ኢየሱስን ስትለምን፣ ኢየሱስ ልመናዋን በቀጥታ ከመፈፀም፣

- “አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ” ማለቱ የማርያም የአማላጅነት ብቃት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ፣
- “ጊዜዬ ገና አልደረሰም” በሚለው ውስጥ ደግሞ የማርያም የእግዚአብሄርን ጊዜን አለማወቅ ችግርን እንመለከታለን፣

እነዚህን ችግሮች በማርያም ምልጃ ውስጥ መመልከታችን፣ ከማርያም ውጪ ደግሞ የትኛውም አማላጅ እንደዚህ አለመባሉንና ማርያምንም ከቃና ዘገሊላ በኋላም በሌላ የምልጃ ስራ ውስጥ አለመመልከታችን፣ ማርያምን የሰማዩ የምልጃ ስራ ጋር ማድረስ ይቅርና በምድር ላይ የሞከረችው አንዱ ምልጃዋ ላይ እንኳን ጥያቄ ፈጥሮ እንመለከታለን፡፡

እነዚህ በማርያምና በኢየሱስ መካከል የነበሩት አወዛጋቢ ንግግሮች እንዳሉ ሆነው፣ ውሀው ወደ ወይን ጠጅ መቀየሩን ብቻ በመመልከት “ማርያም በቃና ዘገሊላ ላይ አማልዳለች” ቢባል እንኳን ሌላ ችግር ደግሞ ከፊታችን ይጠብቀናል፣

- “ምድራዊ አማላጆች ሰማያዊ አማላጆች ናቸው” የሚል መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለንም፣ መፅሃፍ ቅዱሱም ስለ ማርያም ድህረ ስጋዊ የምልጃ አገልግሎት ምንም አልተናገረም ይባስኑ ሐዋርያቱ ከወንጌላትና ከ“ሐዋርያት ስራ መፅሀፍ” በኋላ በተፃፉት ሌሎቹ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ አንድም ቦታ ላይ “ማርያም” የሚል ቃል አለመጠቀማቸውን ስንመለከት ማርያም በድህረ ስጋዊ ህይወቷ የምትሰራው የምልጃ ስራ አለመኖሩን እንመለከታለን፡፡
- ማርያም አሁን በምድር ላይ የለችም፣ በዚህም ሰማያዊ አማላጅ ለመሆን ፀሎት ከምድር መቀበል መቻል አለባት ነገር ግን ማርያም እንደ እግዚአብሄር “በሁሉም ስፍራ መገኘት” የሚቻልበትን አምላካዊ ማንነት የላትም፣ በዚህም ሰዎች ወደ ማርያም የሚያደርጉት የ“አማልጅኝ” ጩኸትን ማርያም መቀበል አትችልም፣ በዚህም ወደ ማርያም የሚደረገው ፀሎት “እሪ በከንቱ” ብቻ ነው፡፡

በዚህም የማርያምን ምድራዊ ምልጃ በቃና ዘገሊላ ተሞክሮ ብዙ ግራ አጋቢ ጥያቄዎችን የተፈጠረበት፣ እስዋም ከዚህ ውጪ ሌላ ምልጃ ሳትሞክር የተወችበት፣ መፅሀፍ ቅዱሱም ከወንጌሉና ከሐዋርያት ስራ መፅሀፍ በኋላ በተፃፉት መፅሀፍት ውስጥ ስሟን ሳያነሳ ያለፈበትና ማርያምም “በሁሉም ስፍራ በመገኘት ፀሎትን መቀበል” አምላካዊ ማንነት የሌላት መሆኑን ስንመለከት፣ የማርያም የቃና ዘገሊላ ታሪክ ተንተርሶ “በሰማዩም ታማልዳለች” የሚለው ሃሳብ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

#### 4.1.1.1.2. “ማርያም ለሰው ልጆች ሃጢያት ሞተች”

አንድ ሰው አማላጅ ሆኖ ሀጢያት ለማስረይ ስለሚሰረየው ሀጢያት መስዋዕት ማቅረብ አለበት(ዕብ.5፡1)፣ በዚህም በብሉይ ኪዳን የነበሩት ሊቀካህናት እንስሳትን ለመስዋዕትነት ያቀርቡ ነበረ፣ በአዲሱ ኪዳን ኢየሱስ እራሱን መስዋዕት አደረገ፣ ማርያምም አማላጅ ለመሆን ስለ ሀጢያት የሚሰዋ መስዋዕት ልታቀርብ ይገባል፣ ይህንም ክፍተት ለመዝጋት ቤተክርስቲያኗ ማርያም ለሰው ልጆች መስዋዕት መሆኗን ትናገራለች፡-

[66] "ፀሀየ ፅድቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እመቤታችን ማሪያም 64 ዓመት በሆናት ጊዜ ... ሙቺ አላት፡፡ እርስዋም አንተን ወልጄ ያንተ እናት ሆኜ እንዴት ልሙት ብትለው እመቤታችን በፈቃድዋ እንዳልሞተችለት ዐውቆ 9,999 ነፍሳት በአንድ ቀን ተኮንነው ገሀነመ እሳት ሲወርዱ አሳያት፡፡ እነዚህም ነፍሳት እመቤታችንን ማሪያምን ባዩ ጊዜ፣ እመቤታችን ሆይ ለዘመዱ የማያዝን አንጀት ራሱን የማይሸከም አንገት አንጀቱም አንጀት አንገቱም አንገት አይደለምና ከልጅሽ አስታርቂን፣ ከገሃነም እሳት አውጪን፣ መንግስተ ሰማያት አግቢን" ብለው ቢያለቅሱባት እርሷም እመቤታችን ማሪያም ልጄ ሆይ ወዳጄ ሆይ እባክህ ማርልኝ አለችው፡፡ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ደቂቀ አዳምን (የአዳም ልጆችን) ከገሀነመ እሳት አውጥቼ መንግስተ ሰማያት ያገባሁት ተገፍፌ፣ ተገርፌ፣ ተሰቃይቼ፣ ተቸንክሬ፣ ሞቼ፣ ተነስቼ አይደለም? <u>አንቺም ስለነዚህ ነፍሳት ኃጢያታቸው ካልሞትሽላቸው ዘለዓለም በገሀነም እሳት ወርደው ይቀራሉ አላት፡፡ እርሷም እመቤታችን እንኳን አንድ ጊዜ ሰባት ጊዜ ልሙት ብላ ሞታለች</u>፡፡ (መፅሃፈ ፀሎት ወመዝገበ ፀሎት በአማርኛ፣ ነገረ ማርያም ገፅ 638-640፡ ተስፋ ገብረ ስላሴ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ፡ 1989 ዓ.ም፡፡)"

በዚህም መሠረት ማርያም ስለሰው ልጆች ሀጢያት መስዋዕት መሆኗን ስለዚህም ማርያም አማላጅ መሆንዋን ቤተክርስቲያኗ ትናገራለች፡፡

ነገር ግን ይህንን ታሪክ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አናገኝም ይባሱኑም መፅሀፍ ቅዱሱ፣ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ አንድ ጊዜ የከፈለው ዋጋ ለአዳም ልጆች ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘር በሙሉ መሆኑን፣ ሌላም አጋዥ ሳያፈልገው ሰዎችን ከሀጢያት ሁሉ ማንፃት የሚችል ጉድለት የሌለበት መስዋዕት መሆኑን ነው (1ዮሐ.1፡7, ዕብ.10፡12, ዕብ.7፡26-27, ቆላ.1፡21-22, ዕብ.10፡11-14, ዕብ.7፡22-27, ዕብ.9፡25-28 ...)፡፡

---

[66] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን ዘሃገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም** ፣ ሁለተኛ እትም፣ ገፅ.154

በዚህም ክርስቶስ አንዴ የሰራው ስራ ብቻውን ሰውን መቀደስ የሚችል ሙሉ ያለቀለት ስራ እንጂ እሱ ሳይጨርሰው ማሪያምም መስዋዕት ሆና የምታሟላው ቀሪ ስራዎች እንደሌሉት እንመለከታለን፣ ይህም የ"ማርያም ለሰው ልጆች ሀጢያት ስርየት መሞት" ሃሳብ ስህተት መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

### 4.1.1.1.3. "ማርያም በአብ ቀኝ ትገኛለች"

ሰማያዊ አማላጅ ለመሆን ሌላው መስፈርት ሀጢያትን ይቅር የሚለው አብ ዘንድ መገኘት መቻል ነው፣ ለዚህም ቤተክርስቲያኗ፣ ማርያም በአብ ዘንድ እንደምትገኝ ታስተምራለች፣ [67]"(ማርያምም ስትሞት) ሐዋርያትም ወስደው ቀበሩዋት፣ በሶስተኛውም ቀን ከሞት ተነሳች ... ወደ ሰማይም አረገች በቀኝም ተቀመጠች፡፡ (የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ፤ ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጋሜው፡ ገፅ.207-209፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፤ 1983 ዓ.ም)"

ነገር ግን ይህ "በአብ ቀኝ" የመገኘት ታሪክ የኢየሱስ ታሪክ ነው፣ ይህም በትንቢት የተተነበየ(መዝ.110፡1) በወንጌላቱም የተገለፀ(ማር.16፡19) በራዕይ የተረጋገጠ(ሐስ.7፡55) እውነታ ነው፣ ስለማሪያም በአብ ቀኝ መገኘት መፅሃፍ ቅዱሱ ላይ የትም ቦታ ላይ አናገኝም፣ ደግነቱ "ቀበሩዋት" የተባሉት "ሐዋርያት ናቸው" መባሉና ሐዋርያቱ ደግሞ በመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ አንድም ቦታ ላይ አለመናገራቸው፣ የማርያም በአብ ቀኝ መገኘት ታሪክ ውሸት መሆኑና ማርያምን እግዚአብሄር ቀኝ የማድረስ ሙከራው ስህተት መሆኑና ይህንንም ተተግኖ ማርያምን ሰማያዊ አማላጅ ያደረገው አስተምህሮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት "ማርያም በሰማያዊው(መንፈሳዊ) ስፍራ ታማልዳለች" በማለት የቀረቡት መከራከርያዎች በሙሉ ስህተት መሆናቸውን፣ በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይም አንድም ቦታ ላይ "ማርያም ታማልዳለች" የሚል ቃል ወይ በሌላ ተቀራራቢ አባባል "ማርያም ለሰው ልጆች መንገድ፣ ጠበቃ፣ መካከለኛ ... ናት" ተብሎ አለመጠቀሱ፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የምንመለከታቸውም ቅዱሳን እንድታማልዳቸው ወደሷ ፀሎት

---

[67] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን ዘሃገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም**፣ ሁለተኛ እትም፣ገፅ.154-155

አለማድረጋቸው፣ ማርያምም እንደ እግዚአብሄር በሁሉም ስፍራ ተገኝታ ፀሎት መቀበል አለመቻሏን ስንመለከት ማርያም በሰማያዊ(መንፈሳዊ) ስፍራ በአማላጅነት አገልግሎት አለመሾሟን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1.2. <u>የመላዕክት አማላጅነት</u>

ቤተክርስቲያንዋ የመላዕክትን አማላጅነት ለማስረዳት በዋናነት የምታቀርበው ቃል፡-

> ዘካ.1፡12 "... የእግዚአብሄርም መልአክ መልሶ፣ አቤቱ የሰራዊት ጌታ ሆይ እነዚህን ሰባ አመት የተቆጣሃቸውን የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው? አለ፡፡"

የሚለውን ቃል ነው፣ ይህንን ክፍል ስናጠና <u>ይሄ መልአክ የተንቀሳቀሰው ጥናት እንዲያደርግ እንጂ እንደ አማላጅ የሰዎች የ"አማልደኝ" ልመና ቀርቦለት አይደለም</u>፣ በዚህም ይህ ቃል ለመላዕክት ከሚቀርበው የ"አማልደኝ" ፀሎት ጋር አይያያዝም ነገር ግን ከመላዕክቱ የስራ ድርሻ፣ ባህሪና ተፈጥሮ አንፃር ስንመለከት መላዕክቱ እንደማያማልዱ እንመለከታለን፡-

- <u>ከመላዕክቱ የስራ ድርሻ አንፃር</u>

ቤተክርስቲያኗ "መላዕክት አማላጆቻችን ናቸው" ትበል እንጂ አንድ ግልፅ ያላደረገችውና በደፈናው ያለፈችው ነገር አለ ይህም፣ መላዕክቱ እጅግ ብዙ እልፍ አእላፍ ከመሆናቸውና እነሱም ደግሞ በስራ ድርሻ፣ በስልጣን ... ከመለያየታቸው አንፃር ሁሉም ያማልዳሉ? ወይስ የተወሰኑቱ ብቻ ናቸው? የሚለው ግልፅ አላደረገችም፣ ለምሳሌ እንኳን ብንመለከት የገብርኤልና የሚካኤል የስራ ድርሻ የተለያየ ነው፣ ገብርኤል በእግዚአብሄር ፊት ይቆማል(ሉቃ.1፡19)፣ ሚካኤል የጦር መሪ ነው(ራዕ.12፡7)፣ በሌላ በኩል ደግሞ መፅሃፍ ቅዱሱም የሁሉንም መላዕክት ስምና የስራ ድርሻ አልነገረንም፣ ሊነግረንም አይችልም፣ ምክንያቱም መላዕክቱ እልፍ አእላፍ ናቸውና ዳንኤልም ስለሚካኤል ሲናገርም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ(ዳን.10፡13) ይላል እንጂ ሌሎቹ እንደሱ የ"አለቅነት" ስልጣን ላይ ያሉት ብዛት፣ ስምና የስራ ድርሻ አልነገረንም፡፡

በዚህም የመላዕክት አማላጅነት አስተምህሮ ትልቅ ክፍተት እንዳለበት እንመለከታለን።

በሌላ በኩል ደግሞ መላዕክቱ የተፈጠሩት በእግዚአብሄር በመላክ እግዚአብሄርንም ሰዎችንም እንዲያገለግሉ ነው ነገር ግን መላዕክቱ የሰዎች መልዕክተኞች ስላልሆኑ ከሰዎች ወደ እግዚአብሄር እንዲያደርሱ የተቀመጠ አሰራር የለም፣ በሰው የሚሰጣቸው ተደራቢ የስራ ድርሻ የለም፣ በዚህም መልዓክን "ለምንልኝ ልላክህ" ማለት በራሱ የመላዕክቱንና የእግዚአብሄርን ክብር የሚጋፋ የድፍረት አነጋገር ነው።

➢ <u>ከመላእክቱ ባህሪ አንፃር</u>

መላዕክቱ የህግን ፍፅምና እንደሚያከሩና እንደ እግዚአብሄር "ይቅር" የሚባል ነገር እንደማያውቁ እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡበት ታሪክ ውስጥ መመልከት ይቻላል።

ዘፀ.23፡20-21 "በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአከን በፊትህ እሰድዳለሁ። በፊቱ ተጠንቀቁ፣ ቃሉን አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ <u>ሃጢያት ብትሰሩ ይቅር አይልምና</u> አታስመርሩት።"

እዚህ ጋር እስራኤላውያኑን የእግዚአብሄርን ምህረት ተለማምደው የሚያደርጉትን መጨማለቅ በመልአኩ ፊት እንዳያደርጉ እግዚአብሄር አስቀድሞ ያስጠነቀቀበት ቃል ነው።

በአዲስ ኪዳኑም በገብርኤልና በዘካሪያስ መካከል የነበረው እውነታ ይህንኑ ያረጋግጥልናል፣

ሉቃ.1፡20 "(መልአኩ ገብርኤልም ዘካርያስን) እነሆም በጊዜው የሚፈፀመውን ቃሌን ስላላመንህ፣ ይህ ቀን እስከሚሆን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው።"

ገብርኤል በዘካርያስ አለማመን የዘካርያስን አፍ ዘግቶ ሄደ፣ እግዚአብሄር ሰዎች ቃሉን አለማመን አይደለም "አንፈልግህም"፣ "አንሰማህም" ብለው ሲሄዱ እንኳን ሲራራላቸው ብዙ ቦታዎች ላይ ተመልክተናል፣ መልአክ ጋር ግን ምህረትን አንመለከትም፣ ቅድስና ከጎደለ መቅጣት ብቻ ነው።

በዚህም መልአክ ስለ ሰዎች አግዚአብሄርን መለመን አይደለም፣ ስለተሰራ ጥፋት እዚያው ነው ዋጋን የሚሰጠው፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ በተቃርኖ መንገድ እየሄደች ትገኛለች፡፡

➢ <u>የተቀያየረው የስልጣን ደረጃ</u>

የአዲስ ኪዳን አማኞች የእግዚአብሄር ልጅነት ስልጣን ተሰጥቶአቸዋል(ሮሜ.8፡14-17)፣ መላእክት ደግሞ የእግዚአብሄር አገልጋዮች ናቸው፣ በዚህም በእግዚአብሄር ፊት ከአገልጋይና ከልጅ ማን ይበልጣል? በዚህም ልጅ አገልጋይን የሚለምንበት አሰራር፣ የአካሄድ ስህተት ነው፡፡

➢ <u>ሌላው “እሪ በከንቱ”</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ማርያም እንደ እግዚአብሄር በሁሉም ስፍራ መገኘት አለመቻል ወደ ማርያም የሚደረገውን ፀሎት “እሪ በከንቱ” እንደሆነ ተመልከተናል፣ እንደዚሁም መላዕክቱም ተፈጣሪ በመሆናቸው ይህን የእግዚአብሄርን ችሎታ የላቸውም፣ በዚህም በአጠገብ ላልታዩ መላዕክት የሚደረግ ፀሎት “እሪ በከንቱ” ብቻ ነው፡፡

በዚህም የምልጃ ስራ የመላዕክቱ የስራ ድርሻ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

መላዕክቱ ቢያማልዱ ኖሮ በብሉይ ኪዳን ዘመን መላዕክቱ ባሉበት እግዚአብሄር “ወደኔ የሚማልድ አጣሁ” አይልም ነበረ(ኢሳ.59፡16, ሕዝ.22፡30-31 …)፣ በመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥም መላዕክትን አንድም ቦታ ላይ “አማላጅ” ወይንም አማላጅነታቸውን የሚያሳዩ እንደ “መካከለኛ፣ አስታራቂ ጠበቃ …” በሚሉ ቃላት አለመጠራታቸው፣ እንዲሁም ቅዱሳኑም መላዕክትን “አማልዱኝ” ብለው ወደነሱ ሲፀልዩ አለመመልከታችን፣ መላዕክት የ“አማላጅነት” አገልግሎት እንደማይሰጡ እንመለከታለን፡፡

በዚህም የመላዕክት አማላጅነት አስተምህሮ ክርስቲያናዊ አይደለም ነገር ግን ይህ አስተምህሮ ከየት እንደመጣ ስንመለከተው ቁርአኑ(53፡26) ላይ እናገኘዋለን ስለዚህ የዚህ አሳሳች ትምህርት ምንጭ ከየት እንደመጣ ግልፅ ነው፣ ስለዚህ ይህን አስተምህሮ የምትከተሉ ተቀደሱ፡፡

### 4.1.1.3. <u>የቅዱሳን አማላጅነት</u>

ሰማዕታት፣ ፃድቃንና ቅዱሳን የሚባሉት ቃላት መካከል ተመሳሳይነት እንመለከታለን፣ "ሰማዕታት" ማለት "ሀይማኖታችንን አንለውጥም" ብለው የተሰዉ ሰዎች ሲሆኑ፣ ፃድቃንና ቅዱሳን መካከል ግን የጎላ ልዩነት አንመለከትም ነገር ግን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ምሁራን ዘንድ በአብዛኛው [68] ቅዱሳን የሚለው ሰፋ ያለና ፃድቃኑና ሰማዕታቱንም የሚያጠቃልል ቃል በመሆኑ፣ ሶስቱንም በአንድ ላይ "ቅዱሳን" በሚለው ቃል እንጠራቸዋለን፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱን ስንመለከት ቅዱሳን በምድራዊው ህይወታቸው እንዲሰሩት ከተሰጣቸው ስራዎች ውስጥ አንዱ የማማለድ ስራ ነው (1ጢሞ.2፡1-2, 2ቆሮ.5፡19 ...) በዚህ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረትም ቅዱሳን በስጋዊ ህይወታቸው ሲያማልዱ ነበረ አሁንም የሚያማልዱ አሉ፡፡

ነገር ግን ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህንን የቅዱሳን አፀደ ስጋዊ የማማለድ አገልግሎት በመለጠጥ ቅዱሳኑ ከሞቱ በኋላም በሰማይም የምልጃ አገልግሎታቸው እንደሚቀጥሉ ትናገራለች፣ በዚህም "ለነዚህ ቅዱሳን ሃጢያታችንን ብንናዘዝ በፈጣሪ ፊት ያማልዱናል" ትላለች፣ ለዚህም ድጋፍ ብዙ ጥቅሶች ሲቀርቡ እንመለከታለን [69] "2ነገ.13፡20-21, ራዕ.14፡13, ሉቃ.16፡22, ራዕ.6፡9-11, ማቴ.17፡2 ..." ነገር ግን ከ2ነገ.13፡20-21 ውጪ ያሉት ጥቅሶች በሙሉ የሚናገሩት የቅዱሳን ትንሳኤ መኖሩንና በትንሳኤም ህይወትና እንቅስቃሴ መኖሩን እንጂ አንዱም ጥቅስ በአፀደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን የምልጃ አገልግሎት እንደሚሰሩ አይናገርም፡፡

ከነዚህ ውስጥ ለየት የሚለው 2ነገ.13፡20-21 ነው፣ እዚህ ጋር የቀረበው ታሪክ አስከሬን የኤልሳዕን አጥንት በመንካቱ የተነሳበት ታሪክ ነው ነገር ግን በሰማይ በመገኘት ሀጢያት ማማለድና በጉድጋድ ውስጥ የተመለከተው ተአምራት በጣም የተራራቁ ነገሮች ናቸው፡፡ በጉድጓድ ውስጥ የተመለከተው ታሪክ እግዚአብሄር በቅዱሳኑ የሚሰራው ተአምራዊ አሰራር እንጂ ቅዱሳኑ በእግዚአብሄር ፊት ስለሚሰሩት ስራ አይደለም፣ ተአምራቱ የተሰራው

---

[68] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998)፣ **ነገረ ቅዱሳን - ፩**፣ የከፍ/ትም/ተቋ(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ገፅ መግቢያ ክፍል

[69] ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣ **ነገረ ቅዱሳን - ፩**፣ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ በሰንበት ተ/ቤ/ማ/መ ማ/ቅ/ት/ሐ/አገ/ዋና ክፍል፣ ገፅ.82

በምድር ነው፣ መመልከት የፈለግነው በሰማይ ስላለው ምልጃ ነው፣ በዚህም ሁለቱ ምንም የማይገናኙ ታሪኮች ናቸው፡፡

ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱሱን ስንመለከት ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ የማማለድ ስራ እንደማይሰሩ እንመለከታለን፡-

➢ <u>በአፀደ ነፍስ ያሉት በአፀደ ስጋ ያሉትን መርዳት የማይችሉ መሆኑን</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ በአፀደ ነፍስ ያሉት ሰዎች በአፀደ ስጋ ያሉትን ሰዎች መርዳት እንደማይችሉ ይናገራል፣

- ዕብ.7፡23-25 "እነርሱ <u>እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው</u> ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፣ <u>እርሱ(ኢየሱስ) ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ</u> የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነሱ ሊያማልድ ዘወትር ይኖራልና..."
- መክ.94-6 "... ሙታን ግን አንዳች አያውቁም ... <u>ከፀሃይ በታችም</u> በሚሰራው ነገር ለዘለአለም እድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም፡፡"

እነዚህ እውነታዎችም በተግባር የተረጋገጡባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ፣

- እነ ሄኖክ፣ ኤልያስ፣ አብርሃም ... በነፍስ አፀድ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ኢሳ.59፡15-16 "... እግዚአብሄርም አየ ... ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ..." መባሉ፣ እንደዚሁም ሕዝ.22፡30-31 ላይ ቅዱሳኑ በነፍስ አፀድ እያሉ የሚማልድ በመጥፋቱ ህዝቡ በሀጢያቱ መቀጣቱ፣
- ሉቃ.16፡19-31 ላይም የአብርሃም፣ አልአዛርና ሀብታሙ ሰው በአፀደ ነፍስ የሚያደርጉትን ንግግር እንመለከታለን፣ በዚህም ንግግራቸው ውስጥ ሀብታሙ ሰው በሲኦል እንደተሰቃየና ቤተሰቦቹ ወደ ሲኦል እንዳይወርዱ በጭንቀት አብርሃምን ሲለምነው እንመለከተዋለን፣ ነገር ግን በገነት ያለው አብርሃም በሲኦል ያሉትንም ሆነ በምድር ያሉትን ሰዎች ምንም ሊረዳ እንደማይችል ይነግረዋል ይባሱኑ በአፀደ ስጋ ላሉት መፍትሄ የሚሰጡት እዚያው በአፀደ ስጋ ያሉት ነቢያት እንጂ በአፀደ ነፍስ ካሉት ጋር የማይነካካ መሆኑን ሲነግረው እንመለከታለን፡፡
- ፊሊጵ.1፡23-24 ላይ "ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ... ነገር ግን በስጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው፡፡" በማለት ቅዱሳን የሚጠቃቀሙት በስጋ እያሉ መሆኑን ማሳየቱ በተመሳሳይ

መልኩም 2ጢሞ.4፡7 ላይ ጳውሎስ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫውን ጨርሻለሁ …" በማለት ፈጣሪ ከሱ የሚጠብቀውን ስራ መጨረሱን ሲናገር እንመለከታለን፡፡

እነዚህን እውነታዎች ስንመለከት በአፀደ ነፍስ ያሉት በአፀደ ስጋ ላሉት የምልጃ አገልግሎት መስጠት እንደማይችሉ ነው፡፡

➢ <u>በአፀደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን ያሉበት መንፈስ የፈራጅነት እንጂ የአማላጅነት አለመሆኑ</u>

በአፀደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳን ከፍርድ ቀን በፊት ያላቸው ፍላጎት በሀጢያተኞች ላይ ፍርድ እንዲፈጥን የሚጠይቁ እንጂ ፍርድ እንዳይፈረድ የሚማልዱ አይደሉም፣

ራዕ.6፡9-11 "አምስተኛውንም ማህተም በፈታ ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሄር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሰዊያ በታች አየሁ፡፡ በታላቅ ድምፅ እየጮሁ፣ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፣ <u>እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም? ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከመቼ አትበቀልም?</u> አሉ … እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪፈፀም ድረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው፡፡"

በፍርድ ቀንም ፍርድ በሰዎች ላይ እንዳይፈረድ የሚማልዱ ሳይሆን እራሳቸውም ከክርስቶስ ጋር በፈራጅነት ይገለጣሉ፣

- 1ቆሮ.6፡2 "ቅዱሳን በአለም ላይ <u>እንዲፈርዱ</u> አታውቁምን?"
- ማቴ.19፡28 "እየሱስም እንዲህ አላቸው፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እናንተስ የተከተላችሁኝ፣ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ <u>እናንተ ደግሞ በአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ</u> በአስራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ፡፡"

በዚህም "በአፀደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን አማላጅ ናቸው" የሚለው ከእውነታው የተቃረነ አስተምህሮ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

➢ **ሌላው "እሪ በከንቱ"**

ከላይ በማሪያምና መላዕክት አማላጅነት ርዕስ ስር እንደተመለከትነው፣ ቅዱሳኑም እንደ እግዚአብሄር በሁሉም ስፍራ መገኘት ስለማይችሉ፣ ወደ ቅዱሳኑም "አማልዱኝ" ተብሎ የሚደረገው ፀሎት "እሪ በከንቱ" ብቻ ነው፡፡

በዚህም ቅዱሳኑ በሰማያዊው ስፍራ ላለው የምልጃ ስራ አለመሾማቸውን እንመለከታለን፣ ይህ የቅዱሳን ሰማያዊ አማላጅነት አስተምህሮ ክርስቲያናዊ ሳይሆን እንደ መላዕክት አማላጅነት ቁርአናዊ ነው(40፡7) ስለዚህ ይህንን አስተምህሮ የምትከተሉ ተቀደሱ፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ሰማያዊውን የምልጃ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን ነው፡፡

#### 4.1.1.4. **የኢየሱስ አማላጅነት**

ከላይ እንደተመለከትነው ቤተክርስቲያኒቱ "አማላጅ" ብላ የያዘቻቸው ማርያም፣ መላዕክትና ቅዱሳን ሰማያዊውን የምልጃ አገልግሎት አይሰጡም ስለዚህ ትክክለኛውን ሰማያዊ አማላጅ ማወቁ የግድ ነው፣ ትክክለኛው ሰማያዊ አማላጅ ማነው? የሚለው ጥያቄ መፅሃፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በብዙ ቦታዎች ላይ በተለያየ መንገድ ይናገራል፡፡

ነገር ግን የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅነት አትቀበልም፣ የቤተክርስቲያኗ ምሁራኖች ኢየሱስ እንደማያማልድ የሚያስረዱት በተለያየ መንገድ ነው፣ ሁሉንም በተናጠል እንመለከታለን፡-

1. "ኢየሱስ ፈፅሞ አማላጅ አይደለም፣
2. የኢየሱስ ምልጃ ከውርስ ሃጢያት እንጂ ከድረገት ሀጢያት አይደለም፣
3. ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ወደ አምላካዊ ማንነቱ ተመልሷል፣ ከዕርገቱ በኋላ አይለምንም፣ አሁን እሱ ፈራጅ ነው፡፡"

የሚሉ የተለያዩ አመለካከቶች ቢኖሩም መፅሃፍ ቅዱሱ ግን በሚያስገርም መልኩ ለሁሉም በቂ መልስ አለው፡፡

### 4.1.1.4.1. “ኢየሱስ ፈፅሞ አማላጅ አይደለም”

እነዚህ ወገኖች በደፈናው “ኢየሱስ የማማለድ ስራ አይሰራም፣ እሱ ሙሉ አምላክ ነው፣ ማን ማንን ይለምናል? `ኢየሱስ አማላጅ ነው' ማለት በራሱ የእሱን ክብር መንካት ነው” ይላሉ፡፡

የዚህ ሀሳብ ዋነኛው ስህተት የሚነሳው ኢየሱስ ለሰው ልጆች መዳን ሲል ራሱን ዝቅ አድርጎ “ተዋህዶ” ሆኖ የመጣበትን ማንነት ካለመረዳት ነው፣ አይሁዶችም የሰቀሉት ይህንኑ ራሱን ዝቅ ያደረገበትን አሰራር ባለመረዳት ነው፡፡

ነገር ግን የኢየሱስ አማላጅነት በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ በተለያዩ መንገዶች ተነግሯል፡-

1. **አማላጅነቱ በትንቢት ተነግሯል**

በብሉይ ኪዳን አማላጆች ሊቀካህናቱ ነበሩ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ዘመን አማላጅ ኢየሱስ እንደሚሆን ቀድሞ በትንቢት ተናግሯል፣

> ኢሳ.53፡12 “ስለዚህ እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፣ ከሀያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፣ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ ከአመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና፣ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ሀጢያት ተሸከመ፣ ስለ አመፀኞችም ማለደ፡፡”

በዚህም የኢየሱስ አማላጅነት ቀድሞ በትንቢት ተተነበየ በቀጣዩ ክፍሎች ደግሞ የትንቢቱን ፍፃሜ እንመለከታለን፡፡

2. **በስሙ ትርጓሜ ተመለከተ**

ኢየሱስ ሲወለድ ስሙ “ኢየሱስ” ተብሎ እንዲጠራ ያዘዘው እግዚአብሄር ነው፣ ሲያዝም የስሙን ትርጉም ተናግሮ ነው፣

> ማቴ.1፡21 “... እርሱ ህዝቡን ከኃጢያታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፡፡”

አማላጅ የሚያስፈልገው ለሀጢያት ስርየት ነው፣ ኢየሱስ ማለት “ከሀጢያት የሚያድን” ማለት በመሆኑ የሀጢያት ስርየት ጉዳይ የሚመለከተው ኢየሱስን ብቻ ነው፣ ለዚህም ነው መፅሀፍ ቅዱሱ፣

- 1ዮሐ.2፡2 “እርሱም የሃጢታችን ማስተሰረያ ነው፣”

- 1ዮሐ.3፡5 “እርሱም ሀጢያትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ…”

የሚለው፣ በዚህም የአማላጅነት ቦታ ለሌላ አካል የሚሰጥበት አሰራር ሊኖር አይችልም፣ የሚገርመው ደግሞ ለምድራዊው አማላጅነት እንኳን ቅዱሳን ፀሎታቸውን ማድረግ ያለባቸው “በኢየሱስ ስም” በመሆኑ(ዮሐ.14፡13-14, ዮሐ.15፡16, ዮሐ.16፡24 …)፣ ምድራዊውም ሆነ ሰማያዊው የምልጃ ጉዳይ ላይ ስለ ሀጢያት ስርየት ራሱን መስዋዕት ያደረገው የኢየሱስ መኖር የግዴታ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

3. <u>በሊቀካህንነት ሹመቱና በሹመቱም ስለ ሀጢያት ስርየት የሚያስፈልገውን መስዋዕት በማቅረቡ</u>

አንድ አካል ራሱን ችሎ ሀጢያትን ማሰረይ የሚችለው ለሀጢያት ስርየት፣

- በሊቀ ካህነት ሹመት ሲሾም፣
- ለሀጢያት ስርየት የሚያፈሰው ደምና የሚያቀርበው መስዋዕት ሲኖረው ነው፣

የአዲስ ኪዳኑ ብቸኛ አማላጅ ኢየሱስ በመሆኑ እነዚህ ለሀጢያት ስርየት የሚያስፈልጉትን ሶስቱን ዋና ግብአቶችን አሟልቶ እንመለከተዋለን፣

➢ <u>የሊቀካህንነት ሹመት</u>

"ሊቀካህን” ማለት በሰዎችና በእግዚአብሄር መካከል በመገኘት መስዋዕት በማቅረብ የሰዎችን ሀጢያት የሚያስተሰረይ ማለት ነው(ዕብ.8፡3, ዕብ.5፡1, ዕብ.7፡27 …)፣ በዚህም በብሉይ ኪዳን ዘመን የሀጢያት ስርየት ሲሰራ የነበረው በሊቀካህናቱ በኩል ነበረ፣ በአሁኑ በአዲስ ኪዳን ዘመን መፅሀፍ ቅዱስ ያስቀመጠው ብቸኛ ሊቀካህን ኢየሱስን ብቻ ነው(መዝ.110፡1-4, ዕብ.3፡1, ዕብ.5፡6, ዕብ.6፡20, ዕብ.7፡1-3, ዕብ.7፡23-26)፣ በዚህም የኢየሱስ የአዲስ ኪዳነ ብቸኛው ሊቀካህንነት ብቸኛው የአዲስ ኪዳን አማላጅ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

- <u>ለሃጢያት ስርየት የሚፈስ ደምና የሚቀርብ መስዋዕት</u>

ለሀጢያት ስርየት አማላጁ ከሊቀካህንነተ ሹመት በተጨማሪ ስለሀጢያት ስርየት የሚሆን ደም ማፍሰስ እንዲሁም መስዋዕት ማቅረብ አለበት፣ ይህ የሆነበት ምክንያት ስለሀጢያት ስርየት የማይሻሩ ሁለት መሠታዊ ህጎች በመኖራቸው ነው፣

- “ሃጢያት ያለ ደም አይነፃም” (ዕብ.9፡22)
- “የሃጢያት ደሞዝ ሞት ነው”(ሮሜ.6፡23)

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊቀካህናቱ ይህንን የሀጢያት ማንፃት ስራ ሲከውኑ የነበሩት የእንስሳቱን ደም በማፍሰስና በሀጢያተኛው ሰው ፋንታ እንስሳቱን መስዋዕት በማድረግ ነው ነገር ግን በአዲስ ኪዳኑ ዘመን የሰው ልጆች ሀጢያት በብዛትና በአይነት እየጨመረ በመሄዱ የእንስሳቱ መስዋዕት ሰውን ከሀጢያቱ ሊያነፃው አለመቻል(ዕብ.10፡11, ዕብ.10፡4 ...) እንዲሁም በአፀደ ነፍስ የሚገኙትን የብሉይ ዘመን ቅዱሳን ሀጢያት ማስወገድ ስለሚያስፈልግ(ቆላ.1፡20, ዕብ.9፡23 ...) ከእንስሳቱ መስዋዕት በላይ የሆነና የአለምን ሆነ በነፍስ አፀድ ላሉት ሀጢያት በአንዴው ማስወገድ የሚችል መስዋዕት ስላስፈለገ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሀጢያት ስርየት የራሱን ደም በማፍሰስ(1ጴጥ.1፡18-19, ቆላ.1፡19-20 ...) እና በመስቀል ላይ መስዋዕት በመሆን(ዕብ.9፡26, ዕብ.10፡12 ...) የሰው ልጆችን ሀጢያት አሰረየ፡፡

በዚህም ኢየሱስ በሊቀካህንነቱ ሹመት፣ የራሱን ደም በማፍሰስና ህይወቱን በመስቀል ላይ መስዋዕት በማድረግ፣ የማስታረቅ ስራውን አከናወነ፣ በዚህም በአዲስ ኪዳኑ ዘመን የኢየሱስ አማላጅነት ይባሱኑም ብቸኛ አማላጅነት የታየበት እውነታ ነው፡፡

**4. <u>እንደ አማላጅነቱም አማልዶአል</u>**

ኢየሱስ እንደ አማላጅነቱ በተግባር አማልዶ አሳይቷል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- ሉቃ.22፡31-32 “እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ <u>አማለድሁ</u>...”

- ሉቃ.23፡34 “ኢየሱስም፡፡ አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ፡፡”
- ዮሃ.17፡1-17 “ከክፉ እንድትጠብቃቸው ... በእውነትህ ቀድሳቸው”

እነዚህ ጥቅሶች ከቁጥር አንድ ጀምሮ የተመለከትናቸው ቃላት በተግባር የተረጋገጡባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡

## 5. <u>በአማላጅነቱም የሰው ልጅንና ፈጣሪን አስታርቋል</u>

“አማላጅ” ማለት የተጣሉ አካላት የሚያስታርቅ “አስታራቂ” ማለት ነው፣ ኢየሱስ አማላጅ በመሆኑ በሀጢያት ምክንያት የተለያዩትን ሰውና እግዚአብሄርን የማስታረቅ ስራ በብቃት ተወጥቷል፣

- ቆላ.1፡19-22 “... በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በፊት የተለያቻችሁትን ክፉ ስራችሁንም በማድረግ በሃሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን <u>በስጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ</u>፡፡”
- ኢፌ.2፡16 “ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ... ያስታርቅ ዘንድ ነው”

በዚህም ኢየሱስ የሰውን ልጅና ፈጣሪን በማስታረቅ አማላጅነቱን የተረጋገጠበት እውነታ ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ በአንድነት የኢየሱስን አማላጅነት የሚነግሩን እውነታዎች ናቸው፣ በዚህም “ኢየሱስ አማላጅ አይደለም” የሚለው አባባል ክርስቲያናዊ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1.4.2. <u>“ኢየሱስ ከውርስ ሃጢያት እንጂ ከድረጊት ሀጢያት አያማልድም”</u>

አንዳንዶች ከላይ የተመለከተው ዘዴ አላዋጣ ሲላቸው፣ ሀጢያትን በሁለት በመክፈል የውርስና የድርጊት ሀጢያት በማለት፣ “ኢየሱስ አማላጅ የሆነው ለውርስ ሀጢያት(ከአዳም ለሚወረሰው ሀጢያት) እንጂ ለድርጊት ሀጢያት(አንድ ሰው ለሚፈፀመው ሀጢያቶች) አይደለም፣ የድርጊት ሀጢያት አማላጆች ማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ናቸው” ይላሉ፡፡

ነገር ግን ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ በሀጢያት አይነት ያልተከፋፈለና ለሁሉም አይነት ሀጢያቶች መሆኑ፣ በዚህም ኢየሱስ ሳይሰራ የቀረውና ዛሬ በማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን በኩል የሚሰራ ስራ አለመኖሩን መፅሀፍ ቅዱሱ ይነግረናል፡-

1. **<u>ኢየሱስ ዋጋ የከፈለው ለሁሉም ሀጢያት መሆኑና አማላጅነቱም ከሁሉም ሀጢያት መሆኑ</u>**

የኢየሱስ ምልጃ በሀጢያት አይነት የሚከፈል ሳይሆን ምልጃው ከሁሉም አይነት ሀጢያት መሆኑን ቃል በቃል ተገልጿል፣

1ዮሐ.1፡7 “የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም <u>ከሃጢያት ሁሉ</u> ያነፃናል፣”

እዚህ ጋር “**<u>ከሃጢያት ሁሉ”</u>** የሚለው ቃል “ሀጢያት ሳይከፋፈል” ማለት ነው፣ ይህም የኢየሱስ የደም ጉልበት በተለያየ አይነት ሀጢያት እንደማይገደብና ሀጢያትን ሁሉ ማንፃት የሚችል መሆኑን ያሳያል፡፡

2. **<u>ኢየሱስ አንዴ የከፈለው ክፍያ ሙሉ መሆኑና ሳይጨርስ ለሌላ አካል የተወው ስራ አለመኖሩ</u>**

ኢየሱስ የከፈለው ሙሉ የሀጢያት ዋጋ መሆኑና ይህም አንዴውኑ በመስቀል ላይ የተጨረሰ መሆኑ፣

- ዕብ.10፡11-14 “ሊቀካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢያትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መስዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሟል፤ እርሱ(ኢየሱስ) ግን ስለ ሀጢያት <u>አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ</u> በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀመጠ … <u>አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍፁማን አድርጎአቸዋልና፡፡”</u>

- ዕብ.7፡22-27 "... እርሱም እንደነዚያ ሊቀካህናት አስቀድሞ ስለራሱ ሀጢያት በኋላም ስለ ህዝቡ ሀጢያት ዕለት ዕለት መስዋዕት ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህንን አንድ ጊዜ ፈፅሞ አድርጎአልና፡፡"
- ዕብ.9፡25-28 "ሊቀካህናት በየአመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፣ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፣ እንዲህ ቢሆንስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፣ አሁን ግን በአለም ፍፃሜ ራሱን በመሰዋት ሀጢያትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል፡፡ ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ተመደበባቸው፣ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ሀጢያት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ሀጢያት ይታይላቸዋል፡፡"

ከዚህም የምንረዳው ኢየሱስ አንዴው የከፈለው ዋጋ ሙሉ መሆኑና ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የሚሸፍኑለት ጉድለት አለመኖሩን ነው፡፡

## 3. ኢየሱስ በከፈለው ዋጋ ብቻ አንድ ሰው መፅደቅ የሚችል መሆኑ

በአዲስ ኪዳን ፅድቅ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው፣ በዚህም አንድ ሰው በኢየሱስ ሲያምን የውርስ ሀጢያቱ ተሰርዮለት የድርጊት ሀጢያቱ አይቀርበትም፣ በዚህም አንድ ሰው በኢየሱስ ሲያምን የውርስ፣ የድርጊትና ሌላም አይነት ሀጢያት ካለ ከሁሉም በአንዴው ነፅቶ "ፃድቅ" ይሆናል፣

- ሮሜ.3፡22 "... በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሄር ፅድቅ ነው፡፡"
- ሮሜ.5፡9-11 "ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከፀደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን፡፡ ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሄር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን በኃላ በህይወቱ እንድናለን፤ ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሄር ደግሞ እንመካለን፡፡"
- ሮሜ 5፡17- "በአንዱ በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሰ ይልቁን የፀጋን ብዛትና የፅድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በህይወት ይነግሳሉ፡፡"

"መፅደቅ" ማለት ከሀጢያት መንፃት ማለት ነው፣ "ፅድቅ" ደግሞ ፅድቅ ነው፣ ደረጃ የለውም "በኢየሱስ ማመን ያፀድቃል" ማለት ያፀድቃል ማለት ነው፣ የኢየሱስ ደም የውርስ ሀጢያትን አሰርዮ የድርጊት ሀጢያትን ማንፃት የማይችል አድርጎ የደሙን ጉልበት በአንድ ጊዜ ስራ ብቻ በመገደብ ለድርጊት ሃጢያት ሌላ አማላጅ መፈለጉ ስህተት ነው፡፡

በዚህም ማሪያም/ፃድቃን/መላዕክት በምልጃ ስራ ለማስገባት የምናሽጋሽግላቸው ቦታ የለም፣ <u>የኢየሱስ ደሙ ጉልበት የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን አጋዥነት ሳይፈልግ ብቻውን ማፅደቅ ይችላል</u>፡፡

በዚህም "የኢየሱስ መስዋዕትነት ለውርስ እንጂ ለድርጊት ሀጢያት አይሰራም" የሚለው አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና የኢየሱስን አማላጅነት መሸፈን የማይቻል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1.4.3. <u>"የኢየሱስ አማላጅነት በምድራዊ ህይወቱ ብቻ ነው፣ ኢየሱስ ከዕርገቱ በኋላ አብን አይለምንም፣ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም"</u>

በመጀመሪያ የተመለከትነው "ኢየሱስ ፈፅሞ አማላጅ አይደለም" የሚሉ ግሩፖችን ነው፣ በመቀጠል የተመለከትነው ይህ ሀሳብ አላስኬድ ያላቸው ደግሞ ሀጢያትን በሁለት በመክፈል፣ የውርስና የድርጊት በማለት፣ የድርጊትን ሀጢያት ምልጃ ስራን ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ለመስጠት የሞከሩትን ነው፣ ሌሎች ደግሞ ከላይ የተመለከትነውን እውነታዎች በማስተዋል ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በምልጃ ስራ ለማስገባት ሌላ ሶስተኛ መንገድ ሲቀይሱ ይታያል፡፡

በዚህም የኢየሱስን ህይወት በሁለት ምዕራፍ በመክፈል "ቅድመ ዕርገትና ድህረ ዕርገት" በማለት፣ የተወሰነ የምልጃ ክፍልን ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ለመስጠት ሲሰሩ እንመለከታለን፡፡ በዚህም "ኢየሱስን ከእርገቱ በፊት ሲያማልድ ነበረ አሁን ግን ኢየሱስ አብን አይለምንም፣ አሁን ከዕርገቱ በኋላ ፈራጅ ነው" በማለት ከዕርገቱ በኋላ ያለውን የምልጃ ስርአት ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ይሰጣሉ፣ እነዚህን ሁለቱንም ሃሳቦች ቀጥለን እንመለከታለን፡-

## ➢ "ኢየሱስ ከዕርገቱ በኋላ አብን አይለምንም"

እነዚህ ግሩፖች ለዚህ የሚያቀርቡት መከራከሪያ፣

ዮሐ.16፡26 "በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤"

የሚለውን ቃል ነው፣ ይህ ቃል የሚናገረው ስለ ሁለት የተተካኩ ነገሮች ነው፣ ይህም ኢየሱስ ለሰዎች በቀጥታ ወደ አብ ሲያደረግ የነበረው ቀጥታ ልመና "በስሙ መለመን" በሚለው መተካቱን እንጂ የኢየሱስ የምልጃ አገልግሎት ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን መሰጠቱን አይደለም፡፡ ኢየሱስ ከዕርገቱ በፊት ለሰዎች ሀጢያት ስርየት በቀጥታ አብን ሲለምን ነበረ ነገር ግን ከዕርገቱ በኋላ ሰዎች በኢየሱስ በኩል የሀጢያት ስርየት ማግኘት የሚችሉት በስሙ በመፀለይ ነው፣ ይህ እውነታም ብዙ ቦታዎች ላይ ተገልጿል፣

- ሐስ.10፡43 "በእርሱ የሚያምን ሁሉ <u>በስሙ</u> የሀጢያቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል፡፡"
- ዮሐ.16፡23 "በዚያን ቀን ከእኔ አንዳች አትለምኑም፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ <u>በስሜ</u> የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል፡፡"
- ሉቃ.24፡47 "<u>በስሙም</u> ንሰሀና የሀጢያት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአህዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተፅፎአል፡፡"
- 1ዮሐ.2፡12 "ልጆች ሆይ ሀጢያታችሁ <u>ስለ ስሙ</u> ተሰርዮላችኋል ..."

ይህም የሚያሳየው ዛሬ ሰዎች ኢየሱስን በአካል አግኝተው እንዲያማልዳቸው መጠየቅ ባይችሉም፣ የእሱን ምልጃ ማግኘት የሚችሉት በስሙ በኩል በሚያደርጉት ፀሎት መሆኑን ነው፣ ኢየሱስና ስሙ ደግሞ አንድ መሆናቸውን መፅሀፍ ቅዱሱ ያሳየናል፣ ይህም በኢየሱስ እመኑ እንደተባለው(ዮሐ.20፡31)፣ ሰዎች በኢየሱስ ስም እንዲያምኑ መነገሩ(1ዮሐ.3፡23, ሐስ.3፡16, ዮሐ.2፡23, ዮሐ.1፡12 ... )፣ እንዲሁም ኢየሱስ በቀጥታ ለሰው ልጆች ሲሰጣቸው የነበሩት አገልግሎቶችን ከእርገቱ በኋላ ሰዎች በስሙ በኩል እንዲያገኙ መደረጉ፣ እነሱም፣ የሀጢያት ስርየት(1ዮሐ.2፡12)፣ የዘላለም ህይወት(1ዮሐ.5፡13)፣ የእግዚአብሄር ልጅነት(ዮሐ.1፡12)፣መዳን (ሐስ.4፡12)፣ ተስፋ(ማቴ.12፡21)፣ኢጋንንት

ማውጣት(ማር.16፡17)፣ ተአምራት መስራት(ማር.9፡39)፣ ፈውስ(ሐስ.3፡16)... የመሳሰሉ ኢየሱስና ስሙ አንድ መሆናቸውን የሚገልጡ እውነታዎችን እንመለከታለን፡፡

በዚህም ከእርገት በኋላ የኢየሱስን የምልጃ አገልግሎቱን ማግኘት የሚቻለው በስሙ በመፀለይ መሆኑና ስሙ ደግሞ እራሱ ኢየሱስ በመሆኑ የኢየሱስን ድህረ ዕርገት አማላጅነት አሁንም የሚመለከተው ኢየሱስን እንጂ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

- **<u>“ኢየሱስ ከዕርገቱ በኋላ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም”</u>**

የእነዚህ ግሩፖች ደግሞ “ኢየሱስ በምድር በነበረበት ወቅት ሰውንና ፈጣሪን የማስታረቅ የምልጃ ስራውን ሰርቷል በአሁኑ ጊዜ ግን የሚሰራው የፈራጅነት ስራ ነው” ይላሉ፣ ለዚህም የሚያቀርቡት

> ዮሐ.5፡22-23 “ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድንም ያከብሩት ዘንድ፣ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው እንከዋን አይፈርድም፡፡”

በርግጥ የኢየሱስ ፈራጅነት የሚያከራክር አይደለም ነገር ግን ግልፅ ሊሆን የሚገባው ኢየሱስ በፈራጅነት የሚገለጠው በፍርድ ቀን ነው፣ የፍርድ ቀን ደግሞ ገና ነው፣ በዚህም መታወቅ ያለበት ቁም ነገር የእግዚአብሄር ፕሮግራም ነው፣ ፈራጁ ኢየሱስ ቢሆንም ነገር ግን ኢየሱስ በፈራጅነት የሚገለጠው በፍርድ ቀን ነው፡፡

በትንሳኤውና በፍርድ ቀን መካከል ያሉትን የኢየሱስን አገልግሎቶች ስንመለከት **ቅዱሳንን ከፍርድ የማስመለጥ** የምልጃ ስራ ነው፣ ይህንን ስራውንም ሐዋርያቱ “ከድህረ ዕርገቱ” በኋላ በፃፏቸው መልዕክቶቻቸው ውስጥ በተለያዩ አባባሎች፣ አማላጅ፣ መካከለኛ፣ ጠበቃ ... በማለት ገልፀውታል፡-

## 1. <u>አማላጅ</u>

የኢየሱስን አማላጅነት ኢየሱስ ካረገ በኋላ በተፃፉት የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ቃል በቃል ተነግሯል፣

ሮሜ.8፡34 "የሞተው፣ ይልቁን ከሙታን የተነሳው፣ በእግዚአብሄር ቀኝ ያለው፣ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡"

ይህ ቃል ግልፅ አድርጎ ይናገራል፣ ይህም የኢየሱስ አማላጅነት የድሮ ታሪክ ሳይሆን የአሁን ድርጊት መሆኑን በዚህም "ስለእኛ የማለደው" ሳይሆን ስለእኛ "የሚማልደው በማለት እንዲሁም ይህንን የሚሰራው የት ሆኖ እንደሆነ በማመልከት "በአብ ቀኝ" በማለት ነው፣ በዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ የአሁን(ድህረ ዕርገት) አገልግሎቱ ሰማያዊ የምልጃ አገልግሎት መሆኑን ይነግረናል፡፡

ዕብ.7፡22-27 "እንዲሁ ኢየሱስ <u>ለሚሻል</u> ኪዳን ዋስ ሆኖአል፡፡ <u>እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው</u> ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤ <u>እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር</u> ስለሆነ <u>የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም **ሊያማልድ** ዘወትር በህይወት ይኖራልና</u> ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሄር የሚመጡትን ፈፅሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡"

እዚህ ጋር እያወዳደረ ያለው የቅዱሳኑን ምልጃና የኢየሱስን ምልጃ ልዩነት ነው፣ በዚህም የኢየሱስ ምልጃ ዘላቂ፣ በሞት የማይገደብና ከዕርገቱም በኋላ የማይቆም መሆኑን ነው፡፡

ይህም መፅሀፍ ቅዱሱ ቃሉን ሰምተው <u>ለሚድኑ ብቻ</u> ለይቶ ቃል በቃል የተናገረበት ቦታ ነው፡፡

## 2. <u>መካከለኛ</u>

ኢየሱስ በፈራጅነቱ ከመገለጡ በፊት አሁን የሚገኘው በሰውና በእግዚአብሄር መካከል በሚገኘው የአማላጅነት ቦታ ነው፣ በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ካረገ በኋላም "መካከለኛ" ይለዋል፣

- 1ጢሞ. 2፡5 "አንድ እግዚአብሄር አለና፣ በእግዚአብሄርና በሰውም መካከል ያለው <u>መካከለኛ</u> ደግሞ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡"

- ዕብ.9፡15 "ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲፀና ህግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለሆነ፣ የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፡፡"

- ዕብ. 12፡24 "የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፣ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደ ሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል፡፡"

ይህ የኢየሱስ መካከለኛነት "እኔ ወደ አብ የሚወስደው መንገድ ነኝ"(ዮሐ.14፡6)፣ "እኔ ወደ አብ የሚያስገባው በር ነኝ"(ዮሐ.10፡7)፣ "በእርሱ ወደ እግዚአብሄር የሚመጡትን"(ዕብ.7፡25) ... በመሳሰሉት መፅሀፍ ቅዱሳዊ ቃላት ተመልክቷል፣ በዚህ መካከለኛው ኢየሱስ አሁን በሰውና በእግዚአብሄር መካከል ሆኖ የማስታረቅ ስራውን እየሰራ ይገኛል፡፡

### 3. ጠበቃ

ኢየሱስን ወደ ፈራጅነቱ ከመሄዱ በፊት አሁን እየሰጠ ያለው አገልግሎት ስለ ሰው ልጆች ሀጢያት ስርየት የጠበቃነት አገልግሎት ነው፣ መፅሀፉ ይህንን የተናገረው ኢየሱስ ካረገ በኋላ ነው፡-

1ዮሐ.2፡1 "ልጆቼ ሆይ፣ ሀጢያትን እንዳታደርጉ ይህን እፅፍላችኋለሁ፡፡ ማንም ሀጢያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ፃድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡"

በዚህም ኢየሱስ ቅዱሳን ላይ ፍርድ እንዳይተላለፍ ስለነሱ የቆመ ጠበቃ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት የኢየሱስ አማላጅነት ሊሸፈን የማይችል እውነታ ነው፣ የሚገርመው ደግሞ የአዲስ ኪዳን የሰማያዊው አማላጅነት አገልግሎት ስራ ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ አካላት ሊፈፅሙት አይችሉም፣ ምክንያቱም፡-

1. የሰማያዊው ቤተመቅደስ ሊቀካህን ኢየሱስ በመሆኑ

በብሉይ ኪዳን ዘመን የሀጢያት ስርየት ሲደረግ የነበረው በሰው ሊቀካህን በምድራዊዋ ቤተመቅደስ ነበረ፣ አሁን ኢየሱስ ሰማያዊው አማላጅ በመሆኑ፣ የምልጃ ስራውን የሚሰራው ሰማያዊ ሊቀ ካህን ሆኖ

(ዕብ.8፡1)፣ የቃል ኪዳንዋ ታቦት ባለችበት በሰማያዊቷ ቤተመቅደስ(ራዕ.11፡19) ነው፣

- ዕብ.8፡1-7"… በሰማያት በግርማው ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፣ እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳዋን አገልጋይ ነው፣ እርስዋም በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት …"
- ዕብ.9፡1-12 "ፊተኛይቱም ደግሞ የአገልግሎት ስርአትና የዚህ አለም የሆነው መቅደስ ነበራት … ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው … ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሰራች ማለትም ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈፅሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም…"
- ዕብ.6፡20 "በዚያም ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዲቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው፣ ስለኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ፡፡"

በዚህም ኢየሱስ የሰማያዊዋ ቤተመቅደስ ሰማያዊ ሊቀካህን በመሆኑ የሰማያዩን የምልጃ ስራ የሚሰራው ኢየሱስ ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

2. <u>እንደ ሰማያዊ ሊቀካህንነቱም በሰማያዊው ቤተመቅደስ መስዋዕት ማቅረቡ</u>

ዕብ.9፡11-12 "ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሰራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘላለም ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈፅሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች አይደለም፡፡"

3. በተዋህዶነቱ ውስጥ <u>በፈጣሪ ማንነቱ ስለ ፅድቅ የሚሟገት መሆኑ፣ በሰውኛ ማንነቱ የሰውን ድካምና የሰይጣንን ፈተና ግምት ውስጥ የሚያስገባ(ዕብ.4፡15)</u> በመሆኑ በሰውና በፈጣሪ መሃል ትክክለኛውን

የምልጃ ሚዛን መጠበቅ የሚችል መሆኑ፣ ኢየሱስ ብቸኛው ሰማያዊ አማላጅ መሆኑን ያሳያል፡፡

4. በተዋህዶነቱ ውስጥ ባለው አምላክነት በሁሉም ቦታ በመገኘት የሰዎችን የንስሀ ፀሎት መቀበል መቻሉ ከላይ የተመለከትነው የ"እሪ በከንቱ ችግር" ችግር የሌለበት መሆኑን ያሳያል፡፡

5. ስሙ "ኢየሱስ" በመሆኑና "ኢየሱስ" ማለት ደግሞ "ከሀጢያት የሚያድን"(ማቴ.1፡21) ማለት መሆኑ እንዲሁም እየሱስ የተገለጠው ሀጢያትን ሊያስወግድ መሆኑ(1ዮሐ.3፡5) ስንመለከት የሀጢያት ስርየት ጉዳዮች ከሱ በቀር ማንንም የማይመለከት መሆኑና ማንም አማላጅ ለመሆን ስሙ "ኢየሱስ" ሊሆን እንደሚገባ ይባሱኑ ደግሞ ምድራዊ አማላጆች እንኳን የምልጃ ፀሎታቸውን ማከናወን ያለባቸው "በኢየሱስ ስም" በመሆኑ(ዮሐ.14፡13-14, ዮሐ.15፡16, ዮሐ.16፡24 ...)፣ ምድራዊውም ሆነ ሰማያዊው የምልጃ ጉዳይ ውስጥ ኢየሱስ የግዴታ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

6. ምልጃ ያስፈለገው ለአስታራቂነት መሆኑ፣ የሰው ልጆችንና ፈጣሪን ያስታረቀው ኢየሱስ መሆኑ፣ ኢየሱስን ብቸኛ አማላጅ ያደርገዋል፡፡

<u>በዚህም ኢየሱስ ምትክ የሌለው **አንዱና ብቸኛው ሰማያዊ አማላጅ** መሆኑና በአዲስ ኪዳን</u> የሀጢያት ስርየት ጉዳይ ዞሮ ዞሮ የሚመጣው ኢየሱስ ጋር ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው የኢየሱስ አማላጅነትን ለመሸፈን ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፣ እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ደግሞ አላማቸው ሰዎች በኢየሱስ አማላጅነት የሀጢያት ስርየት አግኝተው ገነት እንዳይገቡ ነው፣ ይህንንም ስራ የሚሰራው ከመነሻውም ሰዎች ከገነት እንዲባረሩ ምክንያት የነበረው ዲያብሎስ ነው፣ አሁንም ደግሞ ሰዎች የኢየሱስን ምልጃ ተጠቅመው ወደ ገነት እንዲገቡ የቀረበውን መንገድ እንዳይታይ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም እያንዳንዱ ሰው በዚህ ሴራ ሊነቃና ከዲያብሎስ ወጥመድ በማምለጥ በኢየሱስ በኩል የመጣውን ፅድቅ በሙላት ሊጠቀም ይገባዋል፡፡

### 4.1.2. የሰው ልጆች ከሲኦል እንዲድኑ ምክንያት የሆነው ማን ነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሶስቱ ወይስ ሁለቱ?

ከላይ እንደተመለከትነው ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ያለአግባብ በኢየሱስ የምልጃ ስራ ላይ እንዲገቡ ተደርገው ሰው የኢየሱስን የምልጃ አገልግሎት እንዳያገኝ ተደርጓል ነገር ግን ይህ ሰዎች በኢየሱስ እንዳይድኑ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የመጋረድ ስራ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ ከምልጃ በተጨማሪም ዋናውን ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣለትን ተልዕኮ፣ የሰው ልጆችን ማዳን እንኳን እስከ መጋረድ ይባሱኑ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ እስከ ማጠልሸት የተሰሩ ድርሰቶችን እንኳን ይዟል፡፡

"አዳኝ" የሚለው ቃል ሰፋ ያለ ትርጉም አለው፣ ይህም ማስታረቅ፣ ማማለድ፣ ቤዛነት፣ መድሀኒትነት ... በአጠቃላይ ከሲኦል አስመልጦ ለመንግስተ ሰማይ ሙሉ ማድረግን ያመለክታል፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ሰዎች የሚድኑት በኢየሱስ ብቻ መሆኑን ይናገራል፣

ሐስ.4፡12 "መዳንም በሌላ በማንም የለም፣ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፡፡"

እዚህ ጋር መፅሀፍ ቅዱሱ "ሌላ የለም" የሚለውን ቃል የጨመረው ከኢየሱስ ሌላ ወደ ማንም እንዳንመለከት በሚል ነው ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ይህ ቃል ሰሚ አጥቶ የሰው ልጆችን የማዳን ስራ የሚሰሩት ማርያም፣ መላዕክትና ቅዱሳን እንደሆኑ ነው የሚነገረው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

#### 4.1.2.1. "ማርያም የሰው ልጆችን ከሲኦል ታድናች"

ከላይ በ4.1.1.1.2 ክፍል "ማርያም ስለ ሰው ልጆች ሀጢያት ሞተች" የሚል ሀሳብ ተመልክተናል፣ ቤተክርስቲያኗ ይህንን ሀሳብ በማስፋት "የሰው ዘር ከሲኦል የዳነው በማርያም አማካኝነት ነው" በማለት ማርያምን "ኪዳነ ምህረት፣ የአለም መድሀኒት፣ ቤዛዊት አለም፣ ምዕራገ ፀሎት ..." በማለት ኢየሱስ ወደ ምድር የመምጣት ዋናውን ተልዕኮው ለማርያም ስትሰጥ እንመለከታለን፣

## ➢ <u>"ኪዳነ ምህረት/ሰአሊተ ምህረት/"</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት በሙሴ በኩል በወረደው ኪዳን ሰዎች መዳን ስላልቻሉ ኪዳኑ ተሽሮ አዲሱ ኪዳን በኢየሱስ በኩል ወረደ፣ ኪዳን የሚፀናው በደም በመሆኑ ሙሴ ብሉይ ኪዳንን በኮርማዎች ደም እንዳፀናው(ዘፀ.24፡7-8) ኢየሱስ ደግሞ አዲሱን ኪዳን በመስቀል ላይ ባፈሰሰው በራሱ ደም አፀና፣

ማቴ.26፡28 "(ኢየሱስም) ስለ ብዙዎች ኃጢያት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡"

በዚህም የአዲስ ኪዳኑ ባለቤት ስለኪዳኑ ደሙን ያፈሰሰው ኢየሱስ ነው፣ ከዚህ በኢየሱስ በኩል ከተደረገው ኪዳን በኋላ በሞተችው ማርያም በኩል የወረደ ሌላ ኪዳን የለም ነገር ግን በኢየሱስ በኩል በወረደው ኪዳን ሰዎች እንዳይድኑ በሚሰራው አካል ምክንያት በማርያም በኩልም ኪዳን የወረደ በማስመሰል ማርያምን "ኪዳነ ምህረት/ሰአሊተ ምህረት" ተብላ የኢየሱስ ኪዳን እንዲሸፈን ሲደረግ እንመለከታለን፡፡

## ➢ <u>"የአለም መድሃኒት"</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ "የዓለም መድሀኒት" የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፣

1ዮሐ.4፡14 "እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድሀኒት ሊሆን እንደላከው እንመሰክራለን፡፡"

መድሀኒቱ ኢየሱስ መሆኑና እሱም ከአብ የተላከ በመሆኑ ጉድለት የሌለበት መድሀኒት መሆኑ እሙን ነው ነገር ግን በማርያም ስም የኢየሱስ መድሀኒትነት እንዳይታይና ሰዎች እንዳይድኑበት በሚሰራው ስራ ምክንያት ቤተክርስቲያኒቷ "የአለም መድሀኒት" የተባለው የኢየሱስ አገልግሎትና ማንነት የምትሰጠው ለማርያም ነው፣

[70] "... እመቤታችንን <u>የዓለም ሁሉ መድሀኒት አድርጎ እንደፈጠራት</u> ልብ አድርገችሁ እወቁ፡፡ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ፣ ተአምረ ማርያም 3ኛ እትም ፣

---

[70] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን/ቀሲስ/ ዘሀገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም**፣ 2ኛ ዕትም፣ ገፅ 83

ምዕ.12፡1-62፣ ገፅ 43-62፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1989 ዓ.ም፡፡”

➢ **“ቤዛዊት አለም”**

መፅሀፍ ቅዱሱ የሰው ልጆች ቤዛ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ይነግረናል፣

ሮሜ 3፡23-24 “ሁሉም ሀጢያትን ሰርተዋል የእግዚአብሄርም ክብር ጎድሎአቸዋል፣ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በፀጋው ይፀድቃሉ፡፡”

የኢየሱስ ቤዛነት ሙሉ በመሆኑ ሰዎችን የማፅደቅ ችሎታ እንዳለው ይህ ቃል ይነግረናል ነገር ግን ሰዎች በዚህ ሙሉ በሆነው በኢየሱስ ቤዛነት እንዳይድኑ በሚፈልገው አካል ምክንያት በቤተክርስቲያኗ ይህ የኢየሱስ ቤዛነትእንዳይታይ የሰው ልጆች ቤዛ ማርያም እንደሆነች ይነገራል፣

[71] “... ማርያም በሲኦል ላሉ ነፍሳትና ለሰው ልጆች ሁሉ ሞታ በሶስተኛ ቀን ከሞት ተነስታ አርጋ በቀኝ በመቀመጧ የከፈለችው ዋጋ እርሷን ቤዛዊት አለም አሰኝቷታል፡፡ (መፅሀፈ ፀሎት ወመዝገበ ፀሎት በአማርኛ፣ ነገረ ማርያም ገፅ 638-640፣ ተስፈ ገብረ ስላሴ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ 1989 ዓ.ም)”

➢ **“ምዕራገ ፀሎት”**

እንደ ቤተክረርስቲያኗ አገላለፅ “ምዕራገ ፀሎት” ማለት የፀሎት ማሳረጊያ ማለት ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ የፀሎት ማሳረጊያ ኢየሱስ እንደሆነና ማንም ሰው ፀሎቱን “በኢየሱስ ስም” ካሳረገ ለፀሎቱ መልስ እንደሚያገኝ ይናገራል (ዮሐ.14፡13፣ ዮሐ.14፡14፣ ዮሐ.16፡24 ...)፡፡ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ባለው ኢየሱስን በማርያም የመጋረድ ስራዎች ምክንያት “ምዕራገ ፀሎት” በማርያም ስም እንደሆነ ይነገራል፣

[71] Ibid, ገፅ 88

[72]"ድንግል ሆይ ... የፀሎት ማሳረጊያ አንቺ ነሽ።" (አባ ፅጌ ድንግል፣ ማኅሌት ፅጌ፣ ገፅ 613)

እነዚህ "ማርያም ለሰው ልጆች ሀጢያት በመሞት ለሰው ልጆች ኪዳነ ምህረት፣ የሀጢያት መድህኒት፣ ቤዛ፣ ምዕራገ ፀሎት ናት" የሚሉት ለማርያም የተሰጡት አገልግሎቶችና ማንነቶች በሙሉ የኢየሱስ አገልግሎቶችና ማንነቶች ነበሩ።

ኢየሱስ የሰራው ስራ ሙሉ በመሆኑም ማርያም በነዚህ መስኮች ኢየሱስን የምታግዝበት አሰራርም የለም፣ ማርያም የሰው ልጆችን ከሲኦል ማዳን የምትችል ቢሆን ኖሮ የኢየሱስ መምጣት ባላስፈለገ ነበረ፣ ኢየሱስ የመጣው ማርያም ይህን ስራ መስራት ስለማትችል ነው።

በርግጥ ትክክለኛዋ ማርያም በልጅዋ ላይ እንደዚህ አይነት ፉክክርና መፈንቅለ ስልጣን እንደማታደርግ ይታወቃል ነገር ግን ይህ የኢየሱስን ታሪክ እየተከታተለ በማርያም የሚሸፍነው አካል እንዲህ እያደረገ ያለው የኢየሱስ አዳኝነት እንዳይታ ነው፣ ይህም ሰዎች ከገነት እንዲባረሩ ምክንያት የሆነውም ዲያብሎስ ነው።

#### 4.1.2.2. "መላዕክት የሰው ልጆችን ከሲኦል ያድናሉ"

መላዕክት "አማላጅ ናቸው" በማለት ሰዎች በክርስቶስ አማላጅነት እንዳይድኑ የተሰራውን ስራ ከላይ ተመልክተናል፣ ይህ ክርስቶስን በመላዕክት የመሸፈን ስራ በዚህ የሚያበቃ አይደለም፣ ዋናው ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበትን ተልዕኮውን እስከመሸፈን የሚደርስ ነው፣ በዚህም በቤተክርስቲያኗ የሰው ልጆችን ከሲኦል የማዳን ስራ የሚሰሩት መላዕክት መሆናቸው ትናገራለች፣

[72] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን/ቀሲስ/ ዘሀገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም**፣ 2ኛ ዕትም፣ ገፅ 90

[73] "ሚካኤል ዘወትር በ12(ወር በገባ በ12ኛው ቀን) እልፍ አእላፍ ነፍሳትን ከሲኦል በክንፎቹ ይዞ ይወጣል፣ (ድርሳነ ሚካኤል ገፅ 32-40)፣ ይህ ድርጊት የሚካኤል ብቻ ሳይሆን ሁሉም መላዕክት በሚዘከሩበት ቀናቸው የሚያደርጉት የዘወትር ተግባር ነው፡፡"

በዚህ ስሌት ከሄድን ሲኦል ባዶ በቀረች ነበረ፣ መላዕክቱ የሰው ልጆችን ከሲኦል የማዳን ስራ መስራት የሚችሉ ቢሆን ኖሮ የኢየሱስ መምጣት ባላስፈለገ ነበረ፣ ይህ ከላይ የተመለከትነው በማርያም ስም ኢየሱስን የመጋረድ ስራ እዚህም ጋር በመላዕክቱም ስም እየተሰራ መሆኑን ያሳያል፣ ይህም በመላዕክቱ ስም ሰዎች በኢየሱስ ስራ አምነው ገነት እንዳይገቡ የሚሰራው ቀድሞም ሰዎች ከገነት እንዲባረሩ ያደረገው ዲያብሎስ ነው፡፡

#### 4.1.2.3. "ቅዱሳን የሰው ልጆችን ከሲኦል ያድናሉ"

ቅዱሳን "አማላጅ ናቸው" በማለት ሰዎች በክርስቶስ አማላጅነት እንዳይድኑ የተሰራውን ስራ ከላይ ተመልክተናል፣ ይህ በቅዱሳን ስም ክርስቶስን የመጋረድ ስራ በዚህ አይቆምም ዋናውን ኢየሱስ ወደ ምድር የወረደበትን ተልዕኮ እንኳን እስከመሸፈን ይሄዳል፣ ከዚህ በባሰ ደግሞ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅዱሳኑን የሰው ልጆችን ለማዳን ከኢየሱስ በላይ መስራታቸውን ይነገራል፣ ይህም የኢየሱስን ስራ በማሳነስ ሰዎች የኢየሱስን አዳኝነት እንዳይመለከቱ ለማድረግ የተሰራ ልበወለድ ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

- "ከኢየሱስ `የላቀ` ስር ነቀል ስራ ሊሰሩ የነበሩ"

[74] "ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ፣ ቅዱስ ሚካኤል ነጥቆ ሄሮድስ ካስፈጃቸው 14 እልፍ ህፃናት ደምሮታል፡፡ እስዋንም በክንፉ ተሸክሞ ከጣና ሀይቅ አድርሷታል፣ በዚያም ከመከራዋ ብዛት ከገድሏ ፅናት ሰውነቷ ተበሳስቶ የአሳ መመላለሻ እስኪሆን ድረስ ከባህሩ ገብታ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ሳትል አስራ ሁለት አመት ፀልያለች፣ በመጨረሻም ጌታ ምን አደርግልሽ

---

[73] መሪጌታ ጽጌ ፅጌ ስጦታውና መሪ ጌታ ሙሴ መንበሩ፣ **ኦርቶዶክስ መልስ ካላት እኛም ጥያቄ አለን** (VCD)

[74] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998)፣ **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ (የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ ገፅ 69

ዘንድ ትሻለሽ አላት እሷም "… ውሉደ አዳም እንዳይስቱ ዲያብሎስን ማርልኝ አለችው፣ ከሆነልሽ ጠርተሽ አምጪው አላት … ከዚያም(ከሲኦል) ስትወጣ ነፍሳትን ማርካ ወጥታለች፡፡"

በመጀመሪያ ክርስቶስ የተባለውን ለኢየሱስ ብቻ የተሰጠውን ስም በመጋራት "ክርስቶስ ሠምራ" ተብሎ ተጀመረ፣ ቀጥሎ በሃሳብ ደረጃ እንደ ክርስቶስ በማስታረቅ አገልግሎት ተስተካከለች፣ ቀጥሎ እንደ ክርስቶስ ነፍሳትን ከሲኦል ወደ ገነት አስመለጠች፣ በመጨረሻም ኢየሱስ የሰራውን የሰው ልጅና እግዚአብሄርን የማስታረቅ ስራ `አልፋ` "የሀጢያት መሠረቱን፣ የሰው ልጆች አሳሳቹ ዲያብሎስ ምህረትን እንዲያገኝ እግዚአብሄርን ለመነች"፡፡

ይህ ያልተሳካ፣ ሊሳካ የማይችል ነገር ነው፣ ነገር ግን ይህ ልበወለድ የራሱ አላማ አለው፣ አላማውም ሰዎች "ኢየሱስ ለሰይጣን መዳን ቢሰራ ኖሮ ስር ነቀል መፍትሄ ይገኛል" ብለው እንዲያስቡ ለማድረግና ኢየሱስ የከፈለውን ዋጋ ለማሳነስ የተሰራ ልበ ወለድ ነው፣ ነገር ግን የሰው ልጅና የዲያብሎስ ተፈጥሮና ስህተት የተለያየ በመሆኑ በፈጣሪ ፊት ምህረት የሚሰጠውና የማይሰጠው አለ፣ ዋናው ነገር ደግሞ ምህረት የፈጣሪ ፀጋ እንጂ እንደ መብትም የሚታይ ነገር አይደለም፣ በሀጢያት ውስጥ ያለ ምህረትን እንደ መብት አድርጎ ማውራት አይችልም፣ ስለጥፋቱ የሚገባው ሲኦል ነበረ፣ የመሃሪው ርህራሄ በዝቶ እንጂ፡፡

ይህ ሰዎች ያለአግባብ እንዲያስቡ በማድረግ የመጣላቸውን የምህረት ዕድል እንዳያገኙ የሚሰራው ከገነት እንዲባረሩ ምክንያት የሆነውና ዛሬም ሰዎች በኢየሱስ የመጣውን ምህረት አግኝተው ወደ ገነት መመለሻ ዕድል እንዳይጠቀሙ የሚፈልገው ዲያብሎስ ነው፡፡

- "ከክርስቶስ በላይ ስለ ሀጢያት ስርየት ዋጋ የከፈሉ"

[75] "አንድ ቀን ጌታችን ለቅዱስ ነአኲቶ ለአብ በአካል በቤተመቅደስ ተገልፆለት፣ ወዳጄ ልጄ ነአኲቶ ለአብ ሆይ … እኔ ለሰው ልጆች ስል

[75] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998)፣ **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ (የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ገፅ 58

ደሜን ያፈሰስኩት መከራውን የተቀበልኩት አንድ ቀን ነው፣ አንተ ግን አርባ አመት ሙሉ ደምህን፣ እንባህን እያፈሰስክ ...”

➢ “አንዴ ይቅርና ሶስቴም ሞቶ የተነሳ”

መፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥ ከሚታዩ ልዕቀት ያላቸው ስራዎች አንዱ የክርስቶስ ለሰው ልጆች ሀጢያት ሞቶ መነሳት ነው ነገር ግን ይህንን እንዳናደንቅ በቤተክርስቲያኗ “ሶስት ጊዜ ሞቶ የመነሳት” ልበወለድ እንመለከታለን፣

[76] “ቅዱስ ጊዮርጊስ ሶስት ጊዜ ሞቶ ሶስት ጊዜ ተነስቷል፡፡”

➢ እንደ ክርስቶስ በስማቸው በኩል ንሰሀና የሀጢያት ስርየት የሚደረግባቸው፣

መፅሀፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ስለ ሰው ልጆች ሀጢያት ስርየት በከፈለው ዋጋ በስሙ የሀጢያት ስርየት እንደሚገኝ ይናገራል(ሉቃ.24፡47) ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ቅዱሳንም ከላይ እንደተመለከትነው “ስለሰው ልጆች ሀጢያት ዋጋ ከፍለዋል” ስለሚባል በስማቸው “የሀጢያት ስርየት” እንደሚደረግ ይባሉኑም ስርየቱ ከኢየሱስ በበለጠ ከአማኙ ግለሰብ ባለፈ እስከ ትውልድ የሚዘረጋ የሀጢያት ስርየት እንደሚያስደርጉ ታስተምራለች፣

- [77] “አምላከ ፍቅርተ <u>ክርስቶስ</u> ብሎ ባንቺ ስም የተማፀነ ... እስከ አስራ አራት ትውልድ ይማርልሻል፡፡”
- [78] “አቡነ እስትንፋስ <u>ክርስቶስ</u> ከፈጣሪያቸው እስከ አስራ ሰባት ትውልድ ድረስ ዓስራተ ምህረት(የምህረት ቃል ኪዳን) ተቀብለው...”
- [79] “... ስሟን(<u>ክርስቶስ</u> ሠምራ) የጠራውን እስከ አስር ትውልድ እንዲምርላት ተስፋዋን ነግሯት ...”

---

[76] አሉላ ጥላሁንና ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ(1997)፣ **ነገረ ቅዱሳን-፫**፣ ገፅ 80
[77] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ ገፅ 80
[78] Ibid, ገፅ 96

ቅዱሳኑ የተቀደሱት በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ነው፣ በዚህም የኢየሱስ ተፎካካሪ አይደሉም፣ ኢየሱስም ቅዱሳኑን "ከኔ በላይ ተአምራትን ታደርጋላችሁ" አለ እንጂ "ከኔ በላይ ትሆናላችሁ" አላለም ነገር ግን ስሙን ከክርስቶስ ጋር አመሳስሎ በኢየሱስ ስራ ፉክክር ውስጥ የሚገባው ሰዎች በክርስቶስ አምነው እንዳይድኑ የሚሰራው ተፎካካሪ መንፈስ እሱም ዲያብሎስ ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክትና ክርስቶስ የተለያየ አፈጣጠር፣ ችሎታ፣ ፀጋ … አላቸው፣ በዚህም በእግዚአብሄር መንግስት አሰራር ውስጥ እንደ ልዩነታቸው እግዚአብሄርን የሚያገለግሉት በተሰጣቸው የስራ ድርሻና ሀላፊነት ነው፡፡

ነገር ግን እነዚህን አራቱንም አካላት <u>እኩል በማድረግ</u>፣ ማርያም፣ መላዕክታትንና ቅዱሳኑን ከአቅማቸው በላይ በክርስቶስ ወንበር ላይ <u>በማስቀመጥ</u> ከዚህም አልፎ ክርስቶስን "<u>በማስበለጥ</u>"፣ ክርስቶስ የሰራው የሰው ልጆች የማዳን ስራ በሰፊው የመጋረድ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ መፅሀፍ ቅዱሱ ግን እነዚህ አራቱም አካላት እኩል መሆን ይቅርና "መዳን በሌላ በማንም የለም" በማለት በኢየሱስ ላይ ሌላ ተደራቢ መያዝ እንደማይቻል ይናገራል፣ ቃሉ ለሚያምኑት ድነት ነው ለሚጠፉት ደግሞ ሞኝነት ነው፡፡

ስለዚህ ማንም ሰው በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተሰራ ባለው ሴራ ላይ ሊነቃና ከጥፋት በፊት በክርስቶስ ላይ የተጋረደውን መጋረጃ አውርዶ፣ በሱ ቦታ የተቀመጡትን ወደየ ቦታቸው መልሶ፣ በነሱ ስም የሚነግደውን ዲያብሎስን ባዶ አስቀርቶ በኢየሱስ በኩል የመጣውን ድነት ቢጠቀም ይሻለዋል፡፡

---

[79] Ibid, ገፅ 69

### 4.1.3. መመለክ ያለበት ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ እግዚአብሄር፣ ወይስ አራቱም?

ከላይ እንደተመለከትነው በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የኢየሱስ አማላጅነት ቀጥሎም ጠቅላላ የኢየሱስ አዳኝነት ተጠቃሎ ተወስደዋል፣ ይህ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ቅዱሱን መንገድ መግፋት በዚህ አያቆምም ወደ እግዚአብሄር የመመለክ ክልልም ይዘልቃል፣ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን በዚህ ክልል ውስጥ እንዲገቡ የተደረገው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም ለማርያም የተሰጡት ምክንያቶች ግን ሰፋ ያሉ በመሆናቸው ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች በቅድሚያ በመመልከት በመቀጠል ደግሞ እንዴት ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን እየተመለኩ እንደሚገኙ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 4.1.3.1. ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆኑ ምክንያቶች

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለማርያም የሚሰጠው ልዕለ ስብዕና አስተምህሮ ማርያምን የእግዚአብሄር ብቻ የሆነው "መመለክ" ግዛት ውስጥ አስገብቷታል፣ እነዚህ ልዕለ ስብዕና አስተምህሮቶችም በዋናነት "ማርያም ለኢየሱስ እናት በመሆኗ ለእኛም እመቤታችን ናት፣ ዘላለማዊ ድንግል ናት፣ "ፅዮን" ተብሎ በትንቢት ስለሷ ተነግሮ ነበረ" የሚሉ ምክንያቶች ሲሆን ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

##### 4.1.3.1.1. "የኢየሱስ እናትነትዋና ለእኛም እመቤታችን በመሆንዋ"

ኢየሱስ የአምላክና የሰው ተዋህዶ በመሆኑ የእግዚአብሄርም የሰውም ልጅ ነው፣ የእግዚአብሄር ልጅ የተባለው እራሱ እግዚአብሄር ሆኖ ራሱን ዝቅ አድርጎ የሰው ስጋ ለብሶ እስከሞት እንኳን በመታዘዙ ሲሆን የሰው ልጅ የተባለው ደግሞ የሰውን ስጋ ለብሶ በማርያም በኩል በመወለዱ ነው፡፡

ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ፣ በኢየሱስ ተዋህዶ ማንነት ውስጥ ያለውን አምላክነትን ማርያም የወለደችው በማድረግ፣ ማርያምን "የአምላክ እናት/እመ አምላክ" በማለት ለማርያም ልዕለ ስብዕናነትን ሲሰጣት ይታያል፣ በዚህም አምላክ "እግዚአብሄር" እንደሚባለው እስዋም በግዕዙ "እግዝእትነ" ስትባል፣ እግዚአብሄርን "አባታችን" እንደሚባለው ማርያምም "እመቤታችን፣ እናታችን ..." ስትባል፣ ኢየሱስ ስለ ፀሎት ካስተማረበት "የአባታችን" ፀሎት አብሮም፣

ለማርያምም "እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ..." የሚል ፀሎት ይደረግላታል፣ በዚህም ማርያም ከእግዚአብሄር አቻ ስትደረግ እንመለከታለን፡፡

ነገር ግን ኢየሱስ ስጋ ሳይለብስም በፊት በአምላክነቱ ነበረ ዕብ.7፡3 "እናትና አባት የለውም፣ ለዘመኑም ቁጥር የሉትም" ስለዚህ ማርያም በኢየሱስ ተዋህዶነት ውስጥ ያለውን አምላክነት አልወለደችውም፣ እናትነትዋ በተዋሃደው ማንነት ውስጥ ላለው ስጋ ሰውነቱ ብቻ ነው፣ በዚህም ማርያምን "የአምላክ እናት/እመ አምላክ" የሚለው ጋር ማድረሱ ስህተት ነው፣ አምላክ አይወለድም፣ አልተወለደምም፡፡

ኢየሱስ ሰዎች ለማርያም የሚሰጡት ቦታ ከስጋዊ እናትነት በላይ እንዳይሄድ ጥንቃቄ አድርጓል፣ በዚህም ከማርያም ጋር በነበሩት ንግግሮቹ፣ ግንኙነቶቹ እንዲሁም ሰዎች ስለ እናቱ የሚሰጡትን ልዕለ ስብዕና አስተያየቶች ላይ በሰጣቸው ትምህርቶች ውስጥ መመልከት ይቻላል፡-

- ዮሐ.2፡4 "ኢየሱስም (ማርያምን) አንቺ ሴት፣ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ... አላት"
- ሉቃ.2፡41-50 ላይ ማርያም ዮሴፍና ኢየሱስ የፋሲካን በአል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በሚመለሱበት ጊዜ፣ የአንድ ቀን መንገድ ሙሉ ሲጓዙ ኢየሱስ ከነሱ መቅረቱን አላስተዋሉትም ነበረ፣ ማርያምም ኢየሱስን ዘንግታዋለች እሱም ስጋዊ ወላጆቹን ትቶ ወደ መንፈሳዊ ነገሩ አዘንብሎ ነበረ፡፡
- ሉቃ.11፡27-28 "... ከህዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፣ የተሸከመችህ ማህፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁአን ናቸው አለችው፣ <u>አዎን ብፁአንስ</u> የእግዚአብሄርንቃል ሰምተው የሚያደርጉት ናቸው አለ"
- ማር.3፡31-35 "እናቱና ወንድሞቹ መጡ በውጪም ቆመው ወደ እርሱ ልከው አስጠሩት፡፡ ብዙ ሰዎችም በዙሪያው ተቀምጠው ነበረና እነሆ እናትህና ወንድሞች በውጪ ቆመው ይጠብቁሃል አሉት፡፡ መልሶም <u>እናቴ ማን ናት</u>? <u>ወንድሞቼስ እነማን ናቸው</u>? <u>አላቸው፣ እነሆ እናትና ወንድሞቼም፡፡ የእግዚአብሄርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ ነው እህቴም እናቴም አለ፡፡</u>"

በዚህም ኢየሱስ እናቴ የሚለው በስጋ የወለደችውን ማርያምን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰሙ እናቶች በሙሉ “እናቶቼ ናቸው” ያለበትና ለሱ ሁሉም እናቶች እኩል መሆናቸውንና ማርያምንም ከሌሎች እናቶች ተለይታ የማትታይ መሆኑን ያሳየበት እውነታ ነው፡፡

ይህም ማርያም ከስጋዊ እናትነትዋና ኢየሱስን ለአገልግሎት ብቁ እስኪሆን ድረስ ከማሳደግዋ በላይ ከሌላው ሰው የተለየ ልዕለ ስብዕና ያለው ማንነት እንደሌላት የምንመለከትበት እውነታ ነው፣ በዚህም ነው “ማርያም” የሚለውን ቃል ከወንጌላቱና ከሐዋርያት ስራ መፅሀፍ በኋላ ከኢየሱስ ዕርገት በኋላ በተፃፉት መፅሀፍት ውስጥ የማንመለከተው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ማርያምን ከሰው ማንነት አሳልፎ ከእግዚአብሄር አስተካክሎ “እናታችን”፣ “እመቤታችን”፣ “እግዝዕትነ” ማለቱ እንደዚሁም ከአባታችን ፀሎት እኩል “እናታችን” የሚለው ፀሎት ማዘጋጀቱ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.3.1.2. በትንቢት “ፅዮን” ተብሎ ስለስዋ መነገሩ

የማርያም ልዕለ ሰብዕና ለማሳየት የሚቀርበው ሌላው ሀሳብ “መፅሀፍ ቅዱሱ ፅዮን እያለ በትንቢት የሚናገረው ስለ ማርያምን ነው” የሚለው ነው፣ ለዚህም ማሳያነት የኢሳያስ ትንቢት ላይ ያለው ቃል በብዛት ሲነሳ እንመለከታለን፡-

> ኢሳ.60፡12-14 “ለአንቺ የማይገዛ ህዝብና መንግስት ይጠፋል … የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ”

ይህ ቃል ከ“ማርያም ስእል” አጠገብ ተፅፎ ብዙ ጊዜ ተመልክተናል ነገር ግን ይህ ኢሳ.60፡12-14 ሙሉው ቃል አይፃፍም እንጂ ሙሉው ቢፃፍ ኖሮ በሰከንድ ውስጥ “አይ ነገሩ ሌላ ነው፣ ለምን ቃሉን በመቁረጥ በስእል በማስደገፍ ያጭበረብሩናል” ያስብላል፣ እስቲ ቃሉን ሰፋ አድርገን እንመልከት፣

> ኢሳ.60፡12-14 “ለአንቺ የማይገዛ ህዝብና መንግስት ይጠፋል፣ እነዚያ አህዛብም ፈፅመው ይጠፋሉ፡፡ የመቅደሴን ስፍራ ያስጌጡ ዘንድ የሊባኖስ ክብር፣ ጥዱና አስታው ባርሰነቱም፣ ወደ አንቺ ይመጣሉ፣

የእግሬንም ስፍራ አከብራለሁ፡፡ አስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ፣ የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ፤ የእግዚአብሄር ከተማ፣ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ፅዮን ይሉሻል፡፡ ከሰውም ማንም እስከ ማያልፍብሽ ድረስ የተተውሽና የተጠላሽ ነበርሽ፤ ነገር ግን የዘላለም ትምክህትና **የልጅ ልጅ** ደስታ አደርግሻለሁ ... ከዚያ በኋላ በምርድሽ ውስጥ ግፍ፣ በዳርቻሽም ውስጥ ጉስቁልናና ቅጥቃጤ አይሰማም፤ ቅጥርሽን መዳን በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያለሽ፡፡"

ይህንን ቃል ስንመለከት "ፅዮን" ተብሎ የተነገረው ስለ ማርያም ሳይሆን "ፅዮን" ስለተባለችው ከተማ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ሌሎቹንም ቤተክርስቲያኒትዋ "ፅዮን ማርያም ናት" ለማለት የምታቀርባቸውን ማስረጃዎችንም ስንመለከት እንደዚሁ "ፅዮን" የምትባለው ከላይ እንደተመለከትነው ህዝቦች የሚኖሩበት የከተማ ስም ሆኖ እናገኘዋለን፡-

- መዝ.86(87)፡1-7 – እዚህ ጋር ቃሉ ግልፅ አድርጎ የሚናገረው ሀገር ስለሆነችው ፅዮን ነው፣ ይህቺ ሀገርም የተመሰረተችው በተራሮች ላይ ስለሆነች "መሰረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው" ይላል፣ ሀገሪቱንም ያነፃፀረው ከረዓብ፣ ባቢሎን፣ ፍልስጥኤም፣ ጢሮስና ኢትዮጵያ ሀገሮችና ህዝቦች ጋር ነው፣ ከተማ በመሆኗም "በውስጥዋ ለተወለዱ አለቆችዋ" ይላል፡፡

- መዝ.131(132)፡13-18 - ሙሉ ምዕራፉን ስናነብ ፅዮን ተብላ የተገለፀችው በቀጥታ ዳዊት የመሠረታት ፅዮን ከተማ ናት፣ ይህም ዳዊት በከተማይቱ ለእግዚአብሄር ቤተመቅደስ፣ ለታቦቱም ማረፊያ እስከሚሰራባት ያለውን ጉጉት የተናገረበት መዝሙር ነው፣ ማርያም ላለመሆንዋም "አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ፣ ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ፣ ካህናቶችዋንም ደህንነት አለብሳቸዋለሁ፣ ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል" ይላል፡፡

- መዝ.44(45)፡9-17 - ሙሉውን ምዕራፍ ስናነበው ምዕራፉ ድንግል ስለሆነች ሴትና ስለ ታጨችለት ንጉስ የሚናገር ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፣ ይህንን በጥበብ የተነገረን ቃል በቀጥታ በመተርጎም "ቃሉ የሚናገረው

ስለማርያምና ስለ እግዚአብሄር ነው" ማለቱ መቅሰፍት ነው፣ "ስለ ማርያምና ኢየሱስ ነው" ማለቱም እንዲሁ ሌላ መቅሰፍት ነው፣ በማያውቁት ገብቶ ከመቀሰፍ "አልገባኝም" ብሎ መተዉ ብልህነት ነው፡፡

ነገር ግን ይህንን የታጨችው ሴትና ንጉሱ ማንን ለማመልከት እንደሆነ ለመረዳት እስቲ በተመሳሳይ መንፈስ የተፃፉ ሌሎች ቃላትን እንመልከት፣

- ኤፌ.5፡25-26 "ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ …"
- ራዕ.21፡2 "ቅድስቲቱም ከተማ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሄር ዘንድ ስትወርድ አየሁ፡፡"
- ራዕ.21፡9 "… ከሰባቱ መላዕክት አንዱ መጥቶ፡- ወደዚህ ና የበጉን ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሀለሁ ብሎ ተናገረኝ፡፡"

በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ በሚስትነት እንዲሁም በሙሽራነት በአጠቃላይ በሴትነት የሚመስላት በክርስቶስ የተወደደችውና ለሷ ብሎም ደሙን ያፈሰሰላት ቤተክርስቲያን/እስራኤል/አዲሲቷን ኢየሩሳሌም ናት፡፡

"ፅዮን የማርያም ናት" ለሚሉ ሰዎች እነዚህን ለምድራዊዋ ፅዮን ከተማ የተነገሩ ቃላትን እንዴት እንደሚፈቱት ቢነግሩን መልካም ነበረ፣

- ኢሳ.52፡1 "ፅዮን ሆይ … ያልተገረዘና ርኩስ ከእንግዲህ ወዲህ አይገባብሽም…"
- ሰቆ.ኤር.4፡22 "… ፅዮን ሆይ የበደልሽ ቅጣት ተፈፀመ፣ ከእንግዲህ ወዲህ አያስማርክሽም…"
- ሰቆ.ኤር.4፡11 "… እግዚአብሄር መአቱን ፈፅሞአል፣ ፅኑ ቁጣውን አፍስሷል፣ እሳትን በፅዮን ውስጥ አቃጠለ፣ መሰረትዋንም በላች፡፡"፣
- ኢሳ.3፡17 "… ስለዚህ ጌታ የፅዮን ቆነጃጅትን አናት በቡሃነት ይመታል፣ እግዚአብሄርም ሀፍረተ ስጋቸውን ይገልጣል …"

በዚህም ፅዮንና ማርያም ፈፅሞ የማይገናኙ ታሪኮች መሆናቸውን እንመለከታለን፣

ትክክለኛውን የፅዮንን ማንነት ስንመለከት፣ ፅዮን የቦታ ስም ነው በስጋዊው(በምድራዊው) ትርጉሙ ዳዊት የመሠረታት ውብ ከተማ ናት (2ሳሙ.5፡7-9, 1ነገ.8፡1, 1ዜና.11፡5, 2ዜና.5፡2, ኤር.26፡18 ...)፣ በመንፈሳዊው(ሰማያዊው) ትርጉሙ ደግሞ በአንድ በኩል በራዕ.2፡2-9 ላይ የተመለከተችው በኢየሱስ ለወደፊት የምትመሰረተዋ አዲሲቷ ከተማ ስትሆን በሁለተኛው ትርጉም ደግሞ ፈጣሪ የሚገኝባት እጅግ ውብ ስፍራ ናት(ዕብ.12፡22, ኤር.31፡6, ኤር.52፡1 መዝ.134፡3, ኢዩ.3፡17, ኢዩ.3፡21, ዮሃ.14፡1 ...)፡፡

በዚህም ፅዮን በሴት ፆታ በመጠራቷ ብቻ "ፅዮን ማርያም ናት ብሎ" ለማርያም ልዕለ ስብዕናነትን መስጠቱ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

#### 4.1.3.1.3. "ዘላለማዊ ድንግልና"

በቤተክርስቲያንዋ ሌላው ለአምልኮተ ማርያም ምክንያት የሆነው [80] "ማርያም ዘላለማዊ ድንግል ናት" የሚለው ለማርያም ልዕለ ሰብዕናነት የሚሰጠው አስተምህሮ ነው፣ ለዚህ የማርያም "ዘላለማዊ ድንግልና" በዋናነት የሚቀርቡት ማስረጃዎች በመኃ.4፡12 እና በሕዝ.44፡1-3 የተነገሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ናቸው ነገር ግን እነዚህ ምሳሌዎች በማስተዋል ከተመለከትናቸው እነዚህ ቃላት የተነገሩት ለሌላ አካላት እንጂ ለማርያም አይደሉም፣

> መኃ.4፡12 "እህቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት፣ የተዘጋ ምንጭ የታተመ ፈሳሽ ናት፡፡"

በመኃልየ መሀልይ መፅሀፍ ላይ በሴት ፆታ የተገለፀችውን ማንነት በዝርዝር ስንመለከት ማርያም መሆን አትችልም ምክንያቱም ማርያም ጥቁር አይደለችም(መኃ.1፡5)፣ እረኛ አልነበረችም (መኃ.1፡8)፣ አልተደበደበችም(መኃ.5፡7)፣ አልቆሰለችም(መኃ.5፡7)፣ አልተዘረፈችምም (መኃ.5፡7) ...

---

[80]**ቅድስት ድንግል ማርያም በኦርቶዶክሳውያን አስተምህሮ**፣ 2ኛ እትም፣ አዘጋጅ ታድሮስ ያዕቆብ ማላቲ፣ ትርጉም በኤራቅሲስ ዘተዋህዶ፣ አሳታሚና አከፋፋይ፣ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ /በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ፣ ማህበረ ቅዱሳን፣ 2008 ዓ.ም፣ ገፅ.15-19

በዚህም በሴት ፆታ ስለተገለፀ ብቻ "የማርያም ታሪክ" ነው ማለቱ ስህተት ነው፡፡

ሕዝ.44፡1-3 "ወደ ምስራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበረ፡፡ እግዚአብሄርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ ገብቶታልና ተዘግቶ ይኖራል(አለ)፡፡"

ይህ ቃል የሚናገረው በቤተመቅደስ ውስጥ ስለነበረው ጉዞ እንጂ በማርያም ሆድ ውስጥ ስለተደረገ ጉዞ አይደለም፣ እንደዚያ ከተባለ ደግሞ ቁጥር 4 ላይ የተገለፀው "የሰሜኑ በር" ምንዋ ሊሆን ነው? የዚሁ ተመሳሳይ ቃል ሕዝ.11፡1 "መንፈስ አነሳኝ ወደ ፀሀይ መውጫ ወደ ሚመለከተው ወደ እግዚአብሄር ቤትም ወደ ምስራቁ በር አመጣኝ፡፡ እነሆም በበሩ መግቢያ ሀያ አምስት ሰዎች ነበሩ፣ በመካከላቸውም የህዝቡን አለቆች የዓዙርን ልጅ ያዕዛንያን የበነያስ ልጅ ፈላጥያን አየሁ፡፡" የሚለውንስ ቃል ምን ልንለው ነው?

በዚህም እነዚህ ቃላት ስለ ማርያምን የተነገሩ ባለመሆናቸው፣ ለማርያም ዘላለማዊ ድንግልና በድጋፍነት መቅረብ አይችሉም፡፡

ስለ ማርያም ድንግልና ስንመለከት፣ ማርያም ኢየሱስን የፀነሰችውና የወለደችው በድንግልናዋ ነው ነገር ግን ይህንን ድንግልናዋን ከዚህ እውነታ አሳልፎ ለዘላለም ማድረጉ ስህተት ነው፡፡

ከመነሻው "ዘላለማዊ ድንግልና" የሚለው ሀሳብ ውስጥ "ዘላለማዊነት" የሚያያዘው ከበሰባሽ ስጋ ጋር ሳይሆን ዘላለማዊነት ካለው መንፈሳዊው አካል ጋር ነው፣ በዚህም የማርያምን ምድራዊውን ስጋ ወስዶ ዘላለማዊ ማድረግ የመጀመሪያው ስህተት ነው፡፡ ከሞት ወይ ከመነጠቅ በኋላ ባለው መንፈሳዊ ህይወት ሰው የሚለብሰው ዘላለማዊውን መንፈሳዊ አካል ነው(1ቆሮ.15፡40-50)፣ ይህ አካል ደግሞ ፆታ የለውም(ማቴ.22፡30) በዚህም ማርያም የነበራትን ስጋዊ ድንግልና ወደ መንፈሳዊው አለም ወስዶ ዘላለማዊ የሚደረግበት አሰራር የለም፡፡

ማርያም ኢየሱስን በድንግልና አርግዛው በድንግልና ብትወልደውም የማርያም ድንግልና እስከመቼ እንደነበረ መፅሀፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣ በመጀመሪያ ማርያም በድንግልናዋ ለዮሴፍ ለሚስትነት የታጨችበት ጊዜ ላይ ኢየሱስ ስጋ ለብሶ የሚወለድበት ጊዜ ስለደረሰና እግዚአብሄርም ማርያምን ለዚህ አገልግሎት ከሴቶች ሁሉ መርጧት ስለነበረ በመንፈሳዊ አሰራር ኢየሱስ በማርያም ማህፀን ውስጥ እንዲረገዝ ተደረገ፡፡

ነገር ግን ማርያም ለዚህ አገልግሎት መታጨቷን ያልተረዳው ዮሴፍ፣ እጮኛው ሆና እሱ ሳይገናኛት ስላረገዘች፣ በእርግዝናዋ ምክንያት ካሰበው ትዳር በስውር ሊተዋት አሰበ ነገር ግን በዚህ መካከል የጌታ መልአክ ዮሴፍ ማርያምን ከእጮኝነት እንዳይተዋት ተናገረው፡-

ማቴ.1፡20-24 “የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፣ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ከመውሰድ አትፍራ፣ አለው ... ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፣ እጮኛውንም ወሰደ፡፡”

አንዳንዶች “የዮሴፍን እጮኝነት በጠባቂነት እንጂ እኛ በምናስበው በትዳር መንገድ አይደለም” ቢሉም የዮሴፍ እጮኝነት ግን በትዳር እንጂ በሌላ መንገድ ባለመሆኑ መፅሀፍ ቅዱሱ የኢየሱስን የዘር ሀረግ የሚቆጥረው በአብርሃም - ዳዊት - ዮሴፍ የዘር ሀረግ በኩል ነው፡-

- ማቴ.1፡1-16 “የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መፅሀፍ፣ አብርሀም ይስሀቅን ወለደ ... ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን ዕጮኛ ዮሴፍን ወለደ፡፡
- ዮሐ.1፡46 “ፊሊጶስ ናትኤልን አግኝቶ፡፡ ሙሴ በህግ ነቢያትም ስለ እርሱ የፃፉትን <u>የዮሴፍ ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስ</u> አግኝተነዋል አለው፡፡”
- ዮሐ.6፡42 “አባቱና እናቱ የምናውቃቸው ይህ <u>የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ</u> አይደለም?

በዚህም ኢየሱስ የተፀነሰው በመንፈሳዊው አሰራር ቢሆንም ዮሴፍ በኢየሱስ አባትነት መጠራቱ የዮሴፍና የማርያም ግንኙነት የትዳር ግንኙነት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

አንዳንዶች ደግሞ "ዮሐንስ ማርያምን ወሰዳት" (ዮሐ.19፡27) የሚለውን መሠረት በማድረግ "ማርያም ኢየሱስን በድንግልናዋ ከወለደችው በኋላ ከሐዋርያቱ ጋር ወደ አገልግሎት ሄደች እንጂ ወደ ዮሴፍ ትዳር አልሄደችም" ቢሉም ዮሐንስ ማርያምን የወሰዳት ከክርስቶስ ሞት በኋላና ማርያምም ከ48 አመት በላይ ከሆናት በኋላ ነው ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ ታሪኮች የማይገናኙ ታሪኮች ናቸው፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ የማርያም ድንግልና እስከመቼ እንደቆየ በግልፅ ይነግረናል፣

ማቴ.1፡25 "(ዮሴፍም)የበኩር ልጅዋን <u>እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም</u>፡፡"

ይህም ቃል ክርስቶስ እስኪወለድ ድረስ ዮሴፍ ከማርምያም ጋር እንዳልተኛ ያሳየናል ነገር ግን ከኢየሱስ መወለድ በኋላ ማርያምና ዮሴፍ በትዳር ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምዖንና ይሁዳ የሚባሉ ወንዶች ልጆችና ስማቸው ያልተነገሩ ሴቶች ልጆች ወልደው አብረው ሲኖሩ እንደነበረ መፅሀፍ ቅዱሱ ይነግረናል፡፡

- ማቴ.13፡55 "ይህ የፀራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ <u>ያእቆብ</u>ና <u>ዮሳስምኦን</u>ና <u>ይሁዳ</u>ም አይደሉምን? <u>እህቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን</u>?"
- ማር.3፡31-35 "እናቱና ወንድሞቹ መጡ በውጪም ቆመው ወደ እርሱ ልከው አስጠሩት፡፡ ብዙ ሰዎችም በዙሪያው ተቀምጠው ነበረና እነሆ እናትህና ወንድሞች በውጪ ቆመው ይጠብቁሃል አሉት፡፡ መልሶም እናቴ ማን ናት፣ ወንድሞቼስ እነማን ናቸው አላቸው፣ እነሆ እናትና ወንድሞቼም፡፡ የእግዚአብሄርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ ነው እህቴም እናቴም አለ፡፡"

እዚህ ጋር ኢየሱስ ያነፃፀረው ስጋዊ ቤተሰቡንና መንፈሳዊ ቤተሰቡን ነው፡፡

በዚህም ከላይ እንደተጠቀሰው ማርያም ከኢየሱስ ውልደት በኋላ ለዮሴፍ ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምኦንና ይሁዳ የሚባሉ ወንዶች ልጆችንና

በእስራኤል ባህል ሴቶች ተፅዕኖ ስለሚደረግባቸው ስማቸው ያልተገለፁ ሴቶች ልጆችን እንደ ወለደችለት እንመለከታለን፡፡ በዚህም ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆነው የ“ዘላለማዊ ደንግልና” ሀሳብ መሰረተ ቢስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ማርያምን “እመቤታችን፣ ፅዮን፣ ዘላለማዊ ድንግልና” በማለት ለማርያም ለመስጠት የታሰበው ልዕለ ስብዕና አስተምህሮ ስህተት መሆኑና በዚህ መነሻም ለማርያም የሚደረገው አምልኮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.3.2. <u>በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ከእግዚአብሄር አምልኮ የተካከለ ሙሉ አምልኮ</u>

“አምልኮ” ማለት “አምላክ” አድርገው በአምላክነቱ ለሚከተሉት አካል የሚደረግ ስግደት፣ ፀሎት፣ ምስጋና፣ ዝማሬ፣ ውዳሴ የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው፣ በቤተክርስቲያንዋ ውስጥ እነዚህ በሙሉ ለእግዚአብሄርም በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስምም እየተደረጉ ይገኛል፣ የሚገርመው ደግሞ አምልኮ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አምልኮው የሚደረገው የእግዚአብሄር መመለኪያ ብቻ የነበሩት ቤተመቅደሱን/ቤተክርስቲያኑን፣ ታቦቱን፣ ሰንበታቱን ... በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም በማካፈል ነው፣ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡-

#### 4.1.3.2.1. <u>በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የሚደረግ ስግደት</u>

በቤተክርስቲያኒቱ ከእግዚአብሄር በተጨማሪ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ስግደት እየተደረገ ይገኛል ነገር ግን ቤተክርስቲያኒቷ “ለአምላክህ ለእግዚአብሄር ብቻ ስገድ” ከሚለው ቃል ጋር ላለመጋጨት ስግደትን በሁለት በመክፈል “ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የሚደርገውን ስግደት “የፀጋ ስግደት” ስትል ለእግዚአብሄር የሚደርገውን ደግሞ “የባህሪ ስግደት” ትላለች፡፡

ነገር ግን በሁለቱ ስግደቶች መካከል የአተገባበር ልዩነት አለመኖሩን ስንመለከት “ስግደት በሁለት ይከፈላል” የሚለው ክፍፍል ትርጉም የሌለው መሆኑና “ስግደት” ስግደት መሆኑን እንረዳለን፡፡

### 4.1.3.2.1.1. <u>በማርያም ስም የሚደረግ ስግደት</u>

በቤተክርስቲያኗ ለመላዕክትና ለቅዱሳን ለሚደረገው ስግደት ድጋፍ የተወሰኑ <u>የብሉይ ኪዳን</u> ጥቅሶች ቢቀርቡም(ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን)፣ ለማርያም ለሚደረገው ስግደት ግን ምንም መነሻ እየቀረበ አይደለም ይባሱኑ ደግሞ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ የሰብአ ሰገል ሰዎች ለኢየሱስ ብቻ ሰግደው ለማርያም ሳይሰግዱ መቅረታቸውን(ማቴ.2፡1-11) ስንመለከት በማርያም ስም ይቅርና ለማርያም እንኳን ስግደት እንደማይደረግ እንመለከታለን፡፡

ቤተክርስቲያኗ ለቅዱሳንና ለመላዕክት ለሚደረገው ስግደት <u>ከብሉይ ኪዳን</u> ጥቅሶችን ታቀርባለች ነገር ግን እነዚህን ጥቅሶች አስተውለን ስንመለከት "ስግደት" የተባለው የቀረበበት አውድ <u>በአምልኮ</u> ሳይሆን ፊት ለፊት ለተመለከቱት ቅዱስ/መልአክ በሚቀርብ <u>በአክብሮት ሰላምታ</u> ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.3.2.1.2. <u>በቅዱሳን ስም የሚደረግ ስግደት</u>

ቤተክርስቲያኗ ለቅዱሳን ስግደት መደረግ እንዳለበት ትናገራለች፣ ለዚህም በማስረጃነት የምታቀርበው ሰዎች በብሉይ ኪዳን ዘመን ለቅዱሳን ያደረጉትን ስግደት ነው (ዘፍ.23፡7, ዘፍ.33፡3, ዘፀ.18፡7, ዳን.2፡46, 1ሳሙ.20፡41, 1ሳሙ.25፡23 ...)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ "ስግደት ለእግዚአብሄር ብቻ"(ዘፀ.20፡4-5) የሚለውን በመመልከት ቤተክርስቲያንዋ ስግደትን [81] "የባህሪ ስግደትና የፀጋ ስግደት" በማለት በሁለት በመክፈል ለእግዚአብሄር የሚሰገደውን "የባህሪ ስግደት" ስትል ለቅዱሳን የሚደረገውን ደግሞ "የፀጋ ስግደት" ትላለች፡፡ ለእግዚአብሄር የሚደረገው ስግደት ሁሉንም ስለሚያግባባ ለቅዱሳን ይደረጋል ስለሚባለው የፀጋ ስግደት በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

---

[81] ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣ **ነገረ ቅዱሳን - ፩**፣ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ በሰንበት ተ/ቤ/ማ/መ ማ/ቅ ት/ሐ/አገ/ዋና ክፍል፣ ገፅ.67

ከመነሻ “የፀጋ ስግደት” የሚለውን ስያሜ ስንመለከት ሰው ለቅዱሳኑ የሚያደርገውን “ፀጋ” ማለት አንችልም “ፀጋ” ማለት እግዚአብሄር ለሰዎች እንዲያው በነፃ የሚሰጠው ስጦታ ማለት እንጂ ሰዎች ለቅዱሳን የሚሰጡት ስጦታ አይደለም፣ በዚህም “የፀጋ ስግደት” የሚለው ስያሜ አግባብ አለመሆኑን እንመለከታለን፣ በመቀጠል ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ለእግዚአብሄርና ለቅዱሳን በሚደረጉት ሁለቱ አይነት ስግደቶች መካከል የተግባርም ሆነ የይዘት ልዩነት ባለመኖሩ ሁለት አይነት ስግደት አለመኖሩና ስግደት አንድ አይነት ብቻ መሆኑን እንረዳለን፡፡

የዚህ ስህተት መነሻ ከላይ የቀረበው በብሉይ ኪዳን ሰዎች ለሰዎች ያደረጉትን ስግደት ነው ነገር ግን እነዚህን ስግደቶች በየአውዱ ብንመለከት ስግደቱ የአክብሮት ሰላምታ እንጂ “ለአምላክህ ለእግዚአብሄር ብቻ ስገድ” ቃልን የሚገዳደር ድርጊት አይደለም፣ ቀጥሎ እንመለከታለን፡-

- አማኝ ለአማኝ ያደረገው ስግደት
    - 1ሳሙ.25፡23 “አቢግያ ዳዊትን ባየችው ጊዜ ከአህያዋ ላይ ፈጥና ወረደች፣ በዳዊት ፊት በግምባርዋ ወደቀች፣ በምድርም ላይ እጅ ነሳች፡፡”
    - ዘፀ.18፡7 “ሙሴም አማቱን ሊገናኝ ወጣ፣ ሰገደም፣ ሳመውም፤ እርስ በርሳቸው ደህንነታቸውን ተጠያየቁ፣ ወደ ድንኳኑም ገቡ፡፡”
    - 1ሳሙ.20፡41 “ብላቴናውም በሄደ ጊዜ ዳዊት ከስፍራው በደቡብ አጠገብ ተነሳ፣ በምድርም ላይ በግምባሩ ተደፋ፣ ሶስት ጊዜም ለሰላምታ ሰገደ ...”
- አማኝ ላላመነው ያደረገው ስግደት
    - ዘፍ.23፡7 “አብርሃም ተነሳ፣ ለምድሩ ህዝብም፣ ለኬጢ ልጆች ሰገደ”
    - ዘፍ.33፡3 “... (ያዕቆብም) ወደ ወንድሙም(ዔሳው) እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ ሰገደ፡፡”

- <u>ያላመነው ለአማኝ ያደረገው ስግደት</u>

  ዳን.2፡46 "የዚያን ጊዜ ንጉሡ ናቡከደነፆር በግምባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል <u>ሰገደለት</u>፣ የእህሉንም ቁርባን ዕጣኑንም ያቀርቡለት ዘንድ አዘዘ፡፡"

እዚህ ጋር "ያላመነው ለአማኝ" እንደዚሁም "አማኝ ላላመነው" ያደረጉትንም ስግደት በመልካም ተምሳሌትነት አንወስደውም፣ በዚህም ዛሬ ላይ "አማኞች ለቅዱሳን" ለሚያደርጉት ስግደት "በተምሳሌትነቱ" መውሰድ የምንችለው "አማኝ ለአማኝ" ያደረገውን ስግደትን ነው፡፡

አማኝ ለአማኝ ያደረገውን ስግደት ስንመለከት በውስጡ የምንመለከተው አምልኮን ሳይሆን <u>በፊታቸው ለተመለከቱት ሰው</u> በባህላዊ አክብሮታዊ የሰላምታ አሰጣጥ ዘዴ ሰላም ማለታቸውን ነው፣ ይህም የድሮ ሰዎች አክብሮታቸውን ለመግለፅ በመጎንበስ ወይንም በግምባር በመውደቅ ለሚያከብሩት ሰው የሚሰጡት የሰላምታ አሰጣጥ አይነት ነው፣ ይህንን ዛሬም በቻይናና በጃፓን ባህላዊ ፊልሞች ላይ መመልከት ይቻላል፣ ለዚህ አይነት ሰላምታ ሌላ ቃል ባለመኖሩ ቅዱሳኑ በወቅቱ "ሰገደ" የሚለውን ቃል ተጠቀሙለት፡፡

በዚህም የብሉይ ኪዳኑ "ሰገደ" የሚለው ቃል አሻሚ አገላለፅ ምክንያት በብሉይ ኪዳን ለቅዱሳን የተደረገውን ስግደት በሁለት እንደሚከፈል እንመለከታለን፣

1. <u>የአክብሮት ሰላምታ ስግደት</u>፣ ይህም <u>በስጋ ላሉትና ፊት ለፊት</u> ለሚታዩ ቅዱሳን የሚደረግ የድሮ ሰዎች ለአክብሮት በማለት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ወይንም በግንባር በመውደቅ ሰላምታ የሚሰጡበት አሰራር ነው፣

2. <u>የአምልኮ ስግደት</u>፣ ይህም "በሁሉም ስፍራ ይገኛል" ተብሎ ለሚታመነው <u>በፊት ለፊት በአካል ሳይመለከቱ በመንፈስ</u> የሚደረግ መንፈሳዊ ስግደት ነው፡፡

ዛሬ በቤተክርስቲያንዋ ለቅዱሳኑ የሚደረጉ ስግደቶችን ስንመለከት ከብሉይ ኪዳኑ ስግደት የሚለይበት መሠረታዊ ልዩነት አለው፣ በብሉይ ኪዳን አማኞች የሰገዱት ስግደት በፊት ለፊታቸው ለተመለከቷቸው ቅዱሳን ነው

ነገር ግን ዛሬ በቤተክርስቲያኗ የሚደረገው ስግደት በህይወት ለሌሉ፣ በአካል ለማይታዩ፣ እንደ እግዚአብሄር "በሁሉም ቦታ ይገኛሉ" በማለት በመንፈስ የሚደረግ ስግደት ነው፣ ይህ ደግሞ የአምልኮ ስግደት ነው፡፡

በብሉይ ኪዳኑ የተመለከተው ይህ አሻሚ የስግደት አተረጓጎም በአዲስ ኪዳኑ ግልፅ ተደርጎ እንመለከታለን፣ በአዲሱ ኪዳን ስግደት የተደረገላቸው ቅዱሳን ኢየሱስና ጴጥሮስ ናቸው፣ ኢየሱስ የአምላክ ተዋህዶ ስለሆነ የተደረጉለትን ስግደቶች አልተቃወመም፣ ነገር ግን ጴጥሮስ ሰው በመሆኑ ስግደት ሲደረግለት ፈፅሞ ተቃወመ(ሐስ.10፡25-26)፣ ምክንያቱም ጴጥሮስ "ለአምላክህ ለእግዚአብሄር ብቻ ስገድ" የሚለውን ቃል ስለሚያውቅ፣ በዚህም ጴጥሮስ ስግደት ለሰዎች መደረግ እንደሌለበት በግልፅ ቋንቋ ለእኛ ለአዲስ ኪዳን አማኞች አሳይቶን አለፈ፡፡

በዚህም በቤተክርስቲያንዋ "የፀጋ ስግደት" በሚል ሽፋን በፊት ለፊት ለሌሉ ቅዱሳን የሚከናወነው ስግደት ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

#### 4.1.3.2.1.3. በመላዕክት ስም የሚደረግ ስግደት

መላዕክት እንደ ሰው ፍጡራን ናቸው፣ ስራቸውም እግዚአብሄርን ማምለክ(ኢሳ.6፡3)፣ እግዚአብሄርን ማገልገልና በእግዚአብሄር ትዕዛዝ ሰዎችን መርዳት ነው፣ በዚህም መላእክቱ በእግዚአብሄር ትዕዛዝ የሰው ልጆችን ከክፉ ያድናሉ(መዝ.34፡7)፣ ይጠብቃሉ(መዝ.91፡10-12)፣ ክፉውን ይዋጋሉ(ኢሳ.37፡36)፣ ቅዱሳንን ያፅናናሉ(ዳን.10፡21)፣ ይመግባሉ(1ነገ.19፡1-8)፣ የፀሎትን መልስ ያመጣሉ(ሐዋ.12፡5)፣ ነፍስን ያሳርጋሉ(ሉቃ.16፡22) ...

ቤተክርስቲያንዋ ለመላዕክትም ስግደት እንዲደረግ ታስተምራለች፣ ለዚህም የምታቀርበው መከራከርያ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ለመላዕክት(ለሰማይ ሰራዊት) ያደረጉትን ስግደት ነው(ዘፍ.19፡1-2, ዘኍ.22፡31, ኢያ.5፡14, 1ዜና.21፡16, ዳን.8፡15-17, መሳ.13፡20 ...)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እዚያው ብሉይ ኪዳን ላይ ለመላዕክት ስግደት ሊደረግ እንደማይገባና ስግደት ለእግዚአብሄር ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፣

- ሶፎ.1፡5-6 "... ለሰማይ ሰራዊት የሚሰግዱትን ... አጠፋለሁ"

- ዘዳ.4፡19 "... የሰማይ ሰራዊትን ባየህ ጊዜ፣ ሰግደህላቸው አምልከሃቸውም እንዳትስት ተጠንቀቅ፡፡"

ተመሳሳይ ቃላትም 2ነገ.21፡5-6,2ዜና.33፡5-6,ኤር.19፡13...ላይ ቀርቧል

በዚህ ቤተክርስቲያኗ ለመላዕክት የሚደረገውን ስግደት ለእግዚአብሄር ከሚደረገው ስግደት ለመለየት ከላይ እንደተመለከትነው፣ ስግደትን በሁለት በመክፈል [82] "የባህሪ ስግደትና የፀጋ ስግደት" በማለት፣ ለእግዚአብሄር የሚደረገውን ስግደት የባህሪ ስግደት ስትል፣ ለመላዕክት የሚደረገውን ደግሞ የፀጋ ስግደት፡፡" በማለት ለእግዚአብሄርም ለመላዕክትም ስግደትን ታከናውናለች፡፡

ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው የፀጋ ስግደት የተባለውና ቤተክርስቲያንዋ ለመላዕክቱ እንዲደረግ ያዘዘችው የስግደት አይነት ከስያሜው ጀምሮ የተሳሳተ መሆኑን፣ ሁለቱ ስግደቶች መካከልም በተግባር ምንም ልዩነት የሌለ መሆኑንና ቤተክርስቲያኒቷ "ለመላዕክት ሊሰገድ ይገባል" በማለት ከብሉይ ኪዳን የምታቀርባቸው ጥቅሶችና ዛሬ የሚደረገው ስግደት መሀከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን፣ ይህም፣ በብሉይ ኪዳን ሰዎች ለመላዕክት የሰገዱት ፊት ለፊታቸው በአካል ቆሞ ላዩት መልአክ በመጎንበስ አክብሮታቸውን በማሳየት መሆኑንና ዛሬ የሚደረገው ስግደት ግን መልአኩን በአካል ባላዩበት እንደ እግዚአብሄር በሁሉም ስፍራ የመገኘት ማንነት በመስጠት፣ በመንፈስ የሚደረግ የአምልኮ ስግደት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከላይ የተመለከትነው ይህ በብሉይ ኪዳኑ የተወሳሰበው አገላለፅ በአዲሱ ኪዳን ግልፅ ተደርጎ እንመለከታለን፣ ይህንንም እውነታ ለመረዳት በዮሐንስና ገብርኤል መካከል የነበረውን ነገር እስቲ እንመልከት፡-

- ራዕ.19፡10 "ልሰግድለት በእግሩ ስር ተደፋሁ፡፡ እርሱም፡፡ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሄር ስገድ ... አለኝ፡፡"

[82]ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣**ነገረ ቅዱሳን-፩**፣በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰንበት ተ/ቤ/ማ/መ ማ/ቅ ት/ሐ/አገ/ዋና ክፍል፣ገፅ.105-106

- ራዕ.22፡8-9 “ይህንን ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ፡፡ በሰማሁትና ባየሁት ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ፡፡ እርሱም፡፡ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህን መፅሃፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሄር ስገድ አለኝ፡፡”

ከዚህ ከዮሐንስና ከገብርኤል ንግግር ሰዎች ለመላዕክት መስገድ እንደሌለባቸው እንመለከታለን፣ ሁለቱም ቦታ ላይ “ተጠንቀቅ” የሚለው ሃይለቃል ደግሞ ለሚያስተውል ሰው የራሱ ትርጉም አለው፡፡

እንደ ስልጣኑና ለእግዚአብሄር ባለው ቀረቤታው(ሉቃ.1፡19) ቢሆን ኖሮ ለመላእክት ለመስገድ አንደኛ ተመራጭ ገብርኤል ነበረ “አትስገዱልኝ” ብሎ ከለከለ እንጂ፣ መልአክ ያዩ ብዙ <u>የአዲስ ኪዳን</u> ፃድቃን አሉ ኢየሱስ፣ ማርያም፣ ዘካሪያስ፣ ቆርኔሌዎስ ... ነገር ግን አንዳቸውም ለመላዕክቱ ሲሰግዱ አልተመለከትንም፣ እንድንሰግድም አላዘዙም፡፡

<u>በዚህም ዛሬ በቤተክርስቲያኗ ምንም ትዕዛዝ በሌለበት እንደ ብሉይ ኪዳኑ ቅዱሳኑ እንኳን መልአክን በአካል ሳያዩ፣ መላዕክት እንደ እግዚአብሄር “በሁሉም ስፍራ ይገኛሉ” በማለት ለመላዕክት በመንፈስ የሚደረገው የአምልኮ ስግደት ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡</u>

መፅሃፍ ቅዱሱን ጠንቅቆ ላነበበ ሰው በመላዕክቱ አለም ሁለት ጎራዎች አሉ፣ ቅዱስና እርኩስ፣ በቅዱሱ ጎራ ያሉት በሙሉ የሚሰግዱለትም ሆነ እንዲሰገድለት የሚፈልጉት ለእግዚአብሄር ብቻ ሲሆን በእርኩሱ መንገድ ያሉት መንፈሳዊ ሀይላት ደግሞ እራሳቸው እንደ እግዚአብሄር ስግደትን ይፈልጋሉ፣ በዚህም በሁለቱም የመላዕክት ጎራ መካከል ሰፊ የአስተሳሰብ ልዩነት እንመለከታለን፣ ይህንንም እውነታ ሁለቱ መላዕክቶችን (ቅዱሳኑና እርኩሳኑ) ሲናገሩ እስቲ እንመልከት፣

ራዕ.19፡10 መልአኩ ገብርኤል “እንዳትሰግድልኝ ተጠንቀቅ” ሲል

በሌላ በኩል ደግሞ፣

ማቴ.4፡9 ላይ ዲያብሎስ “ወድቀህ ብትሰግድልኝ”

ሲል እንመለከተዋለን፣ በዚህም ቅዱሱ መልአክ ስግደትን አልቀበልም ሲል ዲያብሎስ ደግሞ "ለኔ ስገድ አለ"፣ በዚህም እንዲሰገድላቸው የሚፈልጉት እርኩሳኑ መላዕክት ብቻ መሆናቸውንና ዲያብሎስ ራሱን ቅዱሳን መላዕክት አስመስሎ እንደሚያጭበረብር መፅሀፍ ቅዱሱ መናገሩን(2ቆሮ.11፡14) ስንመለከት፣ በቅዱሳኑ ስም እያጭበረበረ ያለው ዲያብሎስ መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም በአጭበርባሪው ተጭበርብረው ከእግዚአብሄር ውጪ በተለያየ ስም ስግደት እየፈፀሙ ያሉ ሰዎች አደጋ ውስጥ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.3.2.2. <u>ከስግደት በተጨማሪ ወደ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የሚደረጉ አምልኮዎች</u>

በመግቢያው ላይ እንደተመለከትነው "አምልኮ" ብዙ ክፍሎች አሉት፣ ስግደት፣ ፀሎት፣ ምስጋና፣ ውዳሴ ... ከነዚህ ውስጥ ስግደትን ከላይ በስፋት የተመለከትን ሲሆን ሁሉንም የአምልኮ ክፍሎች በዚህ መልኩ መዘርዘሩ ሰፊ ስለሆነ ሌሎቹን የአምልኮ ክፍሎች ቀጥለን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን፡-

1. <u>ፀሎት፡-</u> መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ፀሎት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሲደረግ አንመለከትም፣ ፀሎት የሚደረገው ለእግዚአብሄር ብቻ ነው፣ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ፀሎት እየተደረገ ይገኛል፣ ዋናው አምልኮም የሚደረገው በማርያም ስም በመሆኑ በመላዕክትና ቅዱሳን ስም ከሚደረገው መደበኛ ፀሎት በተጨማሪ ከወሊድ ጋር በተያያዘ ፀሎት የሚደረገው በማርያም ስም ብቻ ነው "እመቤቴ በሰላም ትገላግልሽ፣ ማርያም በሽልም ታውጣሽ ..."

   የሚገርመው ደግሞ ከወሊድ አጋዥነት የተገለሉት የመላዕክትና ቅዱሳን ስም ብቻ ሳይሆን እግዚአብሄርም ጭምር ነው፣ ወሊድ ላይ ከማርያም ስም ውጪ ማንም አይጠራም፣ ይህም እንደ ዋቄፈና፣ የግሪካውያኑና የግብፃውያኑ በሙያ የተከፋፈሉ አማልክት "ማሪያም" የወሊድ አምላክ በመደረጓ ነው፡፡

2. <u>ምስጋና</u>፡- በቤተክርስቲያኗ ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ምስጋና ሲደረግ እንመለከታለን፣ ይህ ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ አሰራር ነው፣ መፅሀፍ

ቅዱሱ ላይ ሰዎች ምስጋናቸውን ሲያቀርቡ የነበሩት ለእግዚአብሄር ብቻ ነበረ፣ እንደውም ኢሳ.42፡8 “አምላክህ እግዚአብሄር እኔ ብቻ ነኝ፣ የእኔንም ክብር የሚጋራ ሌላ አምላክ የለም፣ ጣዖታትም ምስጋናዬን እንዲካፈሉ አልፈቅድም፡፡” ይላል፣ በዚህም የእሱን ምስጋና የሚጋራ ጣዖት ብቻ ነው፣ ይህም በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተደረገ ያለውን ነገር ያስረዳል፡፡

3. መዝሙር፡- መፅሃፍ ቅዱስ ላይ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሲዘመር አንመለከትም ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ በሆነ መንገድ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሲዘመር እንመለከታለን፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ሲዘመርለት የምንመለከተው ለእግዚአብሄር ብቻ ነው፣ እንደልቤ የተባለው ዳዊት እውነትም እንደልብ መሆኑን ለእግዚአብሄር ብቻ በመዘመር አሳየ፣ አሁን ግን የምንመለከተው ለእግዚአብሄር “ልብ አድርቅ” የሆነውን አሰራር ነው፡፡

4. ውዳሴ፡- ውዳሴ የሚቀርበው መወደስ ለሚገባው አካል ነው፣ ይህም አካል ራሱን ችሎ ስላደረገው ድንቅ ልዕለ ስብዕና ድርጊቱ ነው፣ በዚህም በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ሲወደስ የምንመለከተው እግዚአብሄር ብቻ ነው ራዕ.4፡9-11, ራዕ.7፡12 … ነገር ግን በቤተክርስቲያንዋ ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ በሆነ መንገድ ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን ስም በተለያየ መንገድ በመፅሀፍት፣ በቅዳሴ፣ በመዝሙሮች … ውዳሴ ሲደረግ እንመለከታለን፡፡

5. ስዕለት፡-“ስዕለት” ማለት ቃልኪዳን ማለት ነው፣ “እንዲህ ካደረክልኝ እንዲህ አደርጋለሁ የሚል ቃል ኪዳን”፣ በዚህም ስዕለት የሚቀርበው ለዚሁ ለጥያቄ ፈፃሚው ብቻ ነው፣ በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ስዕለት ሲቀርብ የነበረው ለእግዚአብሄር ብቻ ነው(በዘፍ.28፡20-22, ዘሌ.27፡2, ዘኁ.21፡2, መሳ.11፡31, መዝ.42፡8 …) ነገር ግን በቤተክርስቲያንዋ ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ በሆነ መንገድ ለማርያም/መላእክት/ቅዱሳን ስም ስዕለት ሲደረግ እንመለከታለን፡፡

6. መስዋዕት፡- መፅሀፍ ቅዱሱ መስዋዕት ለእግዚአብሄር ብቻ መሆኑን ይናገራል፣ መሳ.13፡16, ሐስ.14፡13-15 … ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ በሆነ መንገድ በማርያም/መላእክት/ቅዱሳን

ስም በተዘጋጁት የመታሰቢያ ቀን፣ ሰንበታትና በአላት መስዋዕቶች እርድ፣ ዳቦ፣ ፀበል ... ሲቀርቡ እንመለከታለን፣ በዚህም "የገብሬል ዳቦ፣ የማርያም ፅዋ ... ሲባል እንመለከታለን፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ እነዚህ የአምልኮ ክፍሎች በሙሉ ሲከናወኑ የነበረው ለአምላክ እግዚአብሄር ብቻ ነበረ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እነዚህ ድርጊቶች መፈፀማቸው በቤተክርስቲያኗ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንስም አምልኮ እየተደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡

ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን "አምልኩን" ባለማለታቸውና እግዚአብሄርም "በነሱ በኩል በውክልና አምልኩኝ" ባለማለቱ "አምልኮው በነሱ ስም ለማን እየተደረገ ነው?" የሚለው ግልፅ ነው፣ እሱም ከላይ በስግደት ክፍል የተመለከትነው እንደ እግዚአብሄር መመለክን የሚፈልገው ዲያብሎስ ነው፣ የሚገርመው ደግሞ የፉክክሩ መጠን ምን ያህል እንደሆነ የምንመለከተው ዲያብሎስ በዘዴ ከመመለክ አልፎ አምልኮውን እንኳን የሚቀበለው የእግዚአብሄር የአምልኮ ንብረቶችን ከባለቤቱ ከእግዚአብሄር ባለቤትነት የስም ማዞር ስራ በመስራት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.3.3. <u>አምልኮው የሚደረገው የእግዚአብሄርን ነገሮች በማጋራት መሆኑ</u>

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ እንደተመለከተው እግዚአብሄር እንዲመለክበት የሚፈልግበትን የራሱ የአምልኮ ነገሮችን ለይቶ አስቀምጧል፣ እነሱም ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን፣ ታቦት፣ ሰንበት፣ በአል ... የመሳሰሉት ናቸው ነገር ግን ዛሬ በቤተክርስቲያኗ እንደ እግዚአብሄር መመለክ በሚፈልገው የእግዚአብሄር ተፎካካሪው አካል በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የእግዚአብሄርን መመለኪያ ነገሮች ከእግዚአብሄር ተካፍሎ ይገኛል፡፡

የዚህን ምስጢር ያልተገነዘቡቱ እነዚህ የእግዚአብሄር የአምልኮ ነገሮች ለሌሎች ያካፈሉበትን ሶስት ምክንያቶች ሲነገሩ ይሰማል፣

- በምሳ.10፡7 "... የፃድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው" እና መዝ.112፡6 "... የፃድቅ መታሰቢያ ለዘለአለም ይኖራል" በሚለው መሰረት ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን መታሰቢያ ለማድረግ በሚል፣

- በመዝ.33(34)፥21 “ ... ፃድቃንን የሚጠሉ ይፀፀታሉ” በሚለው መሠረት ለፃድቃን ያላቸውን ፍቅር ለማሳየት እንደሆነ፣
- ማቴ.10፥41 “ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይን ዋጋ ይወስዳል፣ ፃድቅን በፃድቅ ስም የሚቀበል የፃድቁን ዋጋ ወስዳል፡፡”

በሚለው መሠረት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ነገር ግን ለፃድቃን የሚደረገው “መታሰብያ፣ ፍቅርን ማሳየትና ፅድቃቸውን መቀበል” አሰራር መደረግ ያለባቸው በየራሳቸው መንገድ መሆን አለበት፣ አምልኮም በራሱ መንገድ፣ ሶስቱን የተለያዩ ድርጊቶችን አንድ በማድረግ ተመልሶ ደግሞ “እነዚህን ሶስቱንም የምናከናውነው በእግዚአብሄር የአምልኮ ንብረቶች ነው” ማለቱ ከጀርባ ያለውን ሴራ ያሳያል፣ ለቅዱሳኑ “መታሰብያ፣ ፍቅርን ማሳየትና ፅድቃቸውን መቀበል” መከናወን ያለበት በየራሱ መንገድ ነው፣ እነዚህ ነገሮች በየራሳቸው መንገድ ባለመከናወናቸው ራሱ ሌላ ስህተት እየተሰራ ነው፣ በዚህም ይህ አሰራር “ከሁለት ያጣ” አሰራር ነው፡፡

እነዚህን የማይገናኙ ነገሮችን አገናኝቶ፣ ይህንንም መንደርደርያ አድርጎ የእግዚአብሄር የአምልኮ ንብረቶች ላይ መጥቶ የመቀመጡ አሰራር የእግዚአብሄር ተፎካካሪ መንፈስ ሴራ ነው፡፡

እነዚህ የእግዚአብሄር የነበሩ ነገር ግን ዛሬ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ለሚመለኩት የተከፋፈሉትን የእግዚአብሄር መመለኪያዎች ብንመለከት፣

1. ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን፡- መፅሀፍ ቅዱሳችን ላይ ስንመለከት ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን ሲሰየሙ የነበሩት በባለቤቱ በእግዚአብሄር ስም እንጂ በማርያም/መላእክት/ቅዱሳን ስም አልነበረም ምክንያቱም አንድ ንብረት የሚጠራው በባለቤቱ ስም ስለሆነ፣ በዚህም የመፅሀፍ ቅዱሱን ስንመለከት ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያናት የሚሰየሙት በባለቤቱ በእግዚአብሄር ስም ነው፣
   - የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ (ኤር.51፥51, ዳን.5፥3, ማቴ.26፥61...)
   - የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን (ማቴ.16፥18, ሐስ.20፥28, 1ቆሮ.1፥2...)

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አንድም ቦታ ላይ የማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም የተሰየመ ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን አላየንም ነገር ግን አሁን ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ በማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን እየተተከለ ይገኛል፡፡

2. ታቦት፡- ታቦት የእግዚአብሄር ብቻ ነበረ፣ በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ “የእግዚአብሄራ ታቦት” ይላል (ኢያ.4፡5, 1ሳሙ.3፡3, 2ዜና.8፡11 …)፣ “የ” የምትለዋ ቃል ባለቤትነትን ታሳያለች፡፡

   መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አንድም ቦታ ላይ የማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም የተሰየመ ታቦት አላየንም ነገር ግን አሁን ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ በማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም ታቦት እየተሰየመ ይገኛል፡፡

3. ሰንበት፡- ሰንበት የእግዚአብሄር ብቻ ነበረ(ዘሌ.23፡3, ዘፀ.16፡29 …)፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ለማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም እንዲከበር የታዘዘ ሰንበት አንመለከትም፡፡

   ነገር ግን አሁን ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ በማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም በወራት ውስጥ ተራ በማስገባት የተራቸው ቀን ሰንበት(ስራ የማይሰራበትና ለእነሱ ውዳሴ፣ ቅዳሴ፣ ዝማሬ … የሚደረግላቸው ቀን) ተሰጥቶአቸው እንመለከታለን፡፡

4. በአል፡- በአል ሲከበር የነበረው ለእግዚአብሄር ብቻ ነበረ (ዘፀ.10፡9, ዘፀ.13፡6 …) መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ለማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን የታዘዘ በአል አንመለከትም፡፡

   ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ በማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም በአል ታዘጋጃለች፣ ይህንንም የምታደርገው ለነሱ በተሰጠው ቀኖች፣ ቤተክርስያናትና ታቦታት ነው፡፡

እነዚህን እውነታዎች አጠቃለን ስንመለከት በቤተክርስቲያኗ የእግዚአብሄር መመለኪያ ብቻ የነበሩት ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን፣ ታቦት፣ ሰንበትና በአል በማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ስም ተከፋፍሎ ይገኛል፣ ማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ አይደሉም ነገር ግን ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ የሆነው ይህ በነሱ ስም የእግዚአብሄርን መመለኪያ

ነገሮች የማከፋፈሉ ስራ ነው፣ ይህም እንግዳ አሰራር የመጣው በነሱ ስም ጣልቃ ገብቶ እንደ እግዚአብሄር እየተመለከ ባለው መንፈስ ነው፡፡

የሚገርመው ደግሞ ይህ መንፈሳዊው ምስጢር በደፈናው በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ይቅረብ እንጂ በየአካባቢው የሚመለከው ራሱን የቻለ መንፈስ ነው፣ ለምሳሌ ቁልቢ የሚመለከውና አዲስ አበባ የሚመለከው "ገብርኤል" ሁለቱም በደፈናው "ገብርኤል" ይባሉ እንጂ ሁለቱም እኩል ሀይል የላቸውም፣ የቁልቢው "ገብርኤል" ከአዲስ አበባው "ገብርኤል" በስልጣን ከፍ ያለ ነው፣ በተመሳሳይ መልኩ ኩክ የለሽ ማርያም ከሌሎቹ ማርያሞች በስልጣን ትበልጣለች ... ብዙ ተመሳሳይ በአንድ ስም የሚመለኩ ነገር ግን የተለያየ ማንነት ያላቸውን መናፍስትን ማስተዋል ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ፣

- በማርያም/መላእክት/ቅዱሳን ስም ሙሉ አምልኮ(ስግደት፣ ፀሎት፣ ምስጋና፣ ዝማሬ፣ ውዳሴ፣ ስለት፣ መስዋዕት) እየተደረገ መሆኑን፣
- አምልኮውም የሚደረገው እግዚአብሄር ለራሱ እንዲመለክበት በለያቸው(ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን፣ ታቦት፣ ሰንበትና በአል) በመከፋፈል መሆኑን፣
- ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን "አምልኩን" አለማለታቸውን፣
- "እናምልካቸው" ቢባል እንኳን እንደ እግዚአብሄር በሁሉም ቦታ የመገኘት ባህሪ ስለሌላቸው ከሰው አምልኮን መቀበል የማይችሉ መሆኑን፣
- መመለክ የሚፈልጉት እግዚአብሄርና ዲያብሎስ ብቻ መሆናቸውን፣
- እግዚአብሄር በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም በእጃዙር አምልኩኝ አለማለቱን፣

ስንመለከት፣ አምልኮው በስህተት በባዶ ሜዳ ለዘመናት እየተደረገ ያለ ድርጊት ሳይሆን፣ አምልኮውን በማርያም/መላእክት/ቅዱሳን ስም እየተቀበለ ያለ አካል መኖሩን፣ ይህም እንደ እግዚአብሄር መመለክ የሚፈልገው የእግዚአብሄር ተፎካካሪው መንፈስ፣ ዲያብሎስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ይህ አዲስ ነገር አይደለም ምክንያቱም ከመነሻው የዲያብሎስ ውድቀት ምክንያት ይኸው ራሱን ከእግዚአብሄር የማስተካከል ፍላጎቱ ነበረ፣ ሰይጣን ድሮ ሲመለክ የነበረው በቀጥታ ነበረ ነገር ግን አሁን ከክርስትና መስፋፋት ጋር በተያያዘ ይህ ቀደምት አሰራሩ ተደናቅፎበት ይገኛል፣ አሁን በራሱ ስም ቢንቀሳቀስ ማንም እንደማይሰማው ያውቃል፣ በዚህም ይህን አዲስና “ውጤታማ” ዘዴውን አቀናበረ፣ ተመሳስሎ መገኘት (Camouflage)፣

ሰይጣን ራሱን ለውጦ ሌላ ገፀ ባህሪ ለብሶ በቅዱሳኑና በመላዕክቱ ስም እንደሚጫወት መፅሀፍ ቅዱሱ ቀድሞውኑ ተናግሯል(2ቆሮ.11፡14)፣ ሰይጣን ራሱን “ቅዱስ ሚካኤል” ብሎ በሌላ ስፍራ ደግሞ “ቅዱስ ሩፋኤል” ብሎ ሲያጭበረብር እንደነበረ በ4.3.4.7 ክፍል መመልከት ይቻላል፣ እንደዚሁ በ2.5 ክፍል ዲያብሎስ ራሱን “ፈጣሪ ነኝ ብሎ” በአረቡ ማህበረሰብ ዘንድ እንዴት እያጭበረበረ እንዳለ ተመልክተናል፣ “ክርስቲያኖች” ጋር ደግሞ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ያጭበረብራል፣ ለዚህ ነው መፅሀፍ ቅዱሱ ሰይጣንን “ሽንጋይ” የሚለው(ኤፌ.6፡11)፣ የሚያሳስተው በሽንገላ ስለሆነ ሰዎች መሳሳታቸውን እንኳን ማስተዋል አይችሉም፡፡

ስለዚህ በዚህ ነገር ውስጥ ያላችሁ፣ ይህን የሰይጣንን ሽንገላ በማስተዋል፣ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን ወደ ቦታቸው በመመለስ፣ በነሱ ስም የሚሰራውን ከቤተክርስቲያናችሁ ጠርጋችሁ በማስወጣት እግዚአብሄርን ብቻ ልታመልኩት ይገባል፡፡ እንዲህ በማድረግ ቤተክርስቲያናችሁን ስትቀድሱ እግዚአብሄር ደግሞ በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋል(ኢያ.3፡5)፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገናላችሁ(ኤር.6፡16)፡፡

## 4.2. ብሉይ ኪዳን እያለ አዲሱ ኪዳን የመጣበትን ምስጢር አለማግኘት

አንድ ክርስቲያን “መፅሃፍ ቅዱስ” ከሚለው ቃል ቀጥሎ ማወቅ ያለበት የሁለቱን የመፅሃፍ ቅዱስ ክፍሎች ርዕሶች ትርጉም ነው “አዲስ ኪዳን”ና “ብሉይ ኪዳን”፣ ከመነሻው “ኪዳን” ማለት “የሁለት ወገኖች ውል” ማለት ነው፣ ዳዊትና ዮናታን ቃል ኪዳን አደረጉ(1ሳሙ.18፡3-4)፣ ባልና ሚስትም ለትዳር ቃል ኪዳን አደረጉ ይባላል፤ እንደዚሁ እግዚአብሄር ለሰው ልጆች መዳን ከተለያዩ ትውልዶች ጋር በዋናነት አምስት ጊዜ ቃልኪዳን ሲያደርግ እንመለከታለን፣ በአዳም (ዘፍ.2፡16-17)፣ በኖህ (ዘፍ.9፡1-7)፣ በአብርሃም (ዘፍ.17፡1-21)፣ በሙሴ(ዘፀ.24፡7-8) እና በክርስቶስ(1ቆሮ.11፡23-26)

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው በሙሴና በኢየሱስ በኩል የወረዱትን ኪዳኖችን አንድነትና ልዩነትን ነው፣ “ብሉይ ኪዳን” ማለት በሙሴ በኩል የወረደው ኪዳን ሲሆን በኪዳኑም መሠረት ሰዎች ፅድቅን የሚያገኙት የእግዚአብሄርን ህጎችና የአምልኮ ስርአቶች በፍፅምና በመጠበቅ ነው፣ “አዲስ ኪዳን” ማለት ደግሞ በኢየሱስ በኩል የወረደው ኪዳን ሲሆን በኪዳኑም መሠረት ሰዎች ፅድቅን የሚያገኙት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው፡፡

ይህ በመሠረተ ሀሳብ ደረጃ ቀላል ነገር ነው ነገር ግን ወደ ዝርዝሩ ሲገባ ልዩነቱ ሊረዱት የሚከብድ ከባዱ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል ሆኖ እናገኘዋለን፣ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያንንም ግራ ያጋባትና በሁለቱ ኪዳናት መካከል እንድትዋልል ያደረጋትም ይኸው አስተዋዮች ብቻ ሊመለከቱት በሚችለው ልዩነቱ ነው፣

- በአንድ በኩል ኢየሱስ “እኔ ህግን ልሽር አልመጣሁም” እያለ ሐዋርያቱ ደግሞ “የብሉይ ኪዳን ተሽሯል” አሉ፣
- “ብሉይ ኪዳን ተሽሯል” ሲባል የ39ኙ የብሉይ መፅሃፍት ዕጣ ፋንታ ምንድነው?
- “ብሉይ ኪዳን ተሽሯል ሲባል በብሉይ ኪዳን የታዘዙቱ ታቦት/ፅላት፣ ሰንበት ... ዕጣ ፋንታስ ምንድነው?

- በአዲስ ኪዳን ፅድቅ በእምነት ከሆነ ህግን የሚተላለፍ ሰው ዕጣ ፋንታስ ምንድነው?

እነዚህን ግራ አጋቢ ጥቄዎችን ለመመለስ በመጀመርያ "የብሉይ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን ህግ" እንዲሁም "ብሉይ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት" መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

### 4.2.1. "የብሉይ ኪዳን" እና "የብሉይ ኪዳን ህግ" አንድነትና ልዩነት

"ብሉይ ኪዳን" ማለት በዋናነት እግዚአብሄር የእስራኤልን ህዝብ ለማፅደቅ በሙሴ በኩል ያወረደው ኪዳን(ውል) ነው(ዘፀ.24፡7-8, ሮሜ.9፡4...)፣ በዚህም ውል መሠረት እግዚአብሄር ያወረደውን ህግ የጠበቀ ይፀድቃል ህጉን የጣሰ ይኮነናል፡፡

ነገር ግን ሰዎች የወረደውን ህግ በፍፅምና በመጠበቅ መፅደቅ ስላልቻሉ አዲሱ ኪዳን መጣ፣ አዲሱ ኪዳንም ሲመጣ ህጉን ሳይጥል "ሰዎች የሚፀድቁት በክርስቶስ ሲያምኑ ነው" አለ፣ በዚህም "ብሉይ ኪዳን ተሽሯል" ሲባል "የብሉይ ኪዳን ህግ" ተሽሯል ማለት ሳይሆን የተሻረው ህግን በመጠበቅ ፅድቅ የሚገኝበት አሰራር ነው፡፡

በአዲስ ኪዳን ዘመን ፅድቅ የሚገኘው በኢየሱስ በማመን ነው፣ በአዲሱ ኪዳን ህጉ ምን ቦታ ይኖረዋል? የሚለውን በ4.2.3.5 ክፍል በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 4.2.2. "የብሉይ ኪዳን" እና "39ኙ የብሉይ ኪዳን መፅሃፍት" አንድነትና ልዩነት

"ብሉይ ኪዳን" የሚለው ቃል ዋናው ትርጉም ከላይ የተመለከትነው ህግን በመጠበቅ ፅድቅ የሚገኝበት ኪዳን/የውል ስምምነት ነው፣ ቃሉ ከዚህ በተጨማሪም ሌላ ትርጉምም አለው፣ ይህም በህትመት ቴክኖሎጂ መምጣት ምክንያት በተበታተነ መንገድ በጥቅልል የነበሩት ቅዱሳት መፅሀፍት በአንድ ላይ በመፅሀፍ ተጠርዘው ሲሰሩ፣ ከክርስቶስ በፊት ለነበሩት ለ39ኙ መፅሀፍት ስብስብ የተሰጠ ስያሜ ነው፣ የእነዚህ መፅሀፍት ይዘትም የስነፍጥረት ታሪኮች፣ ከፈጣሪ የወረዱ ህጎች፣ የብሉይ ኪዳን ውል፣ የፃድቃን

የህይወት ምሳሌዎች፣ የእስራኤል ህዝብ ታሪኮች፣ ትንቢቶች፣ ዝማሬዎች … የተፃፉበት የመፅሀፍ ቅዱሱ ክፍል ነው፡፡

በዚህም "ብሉይ ኪዳን" በሚለው ቃል ውስጥ እነዚህን ሁለቱን ትርጉሞች፣ ይህም "የብሉይ ኪዳን ውል" እና "የብሉይ ኪዳን 39 መፅሀፍት" ትርጉም ተለይተው ሊታወቁ ይገባል፣ በዚህም "ብሉይ ኪዳን ተሻረ" ማለት የተሻረው የብሉይ ኪዳን ውል(ይህም ህግን በመጠበቅ መፅደቅ) እንጂ 39ኙ መፅሀፍት አይደሉም፣ ምክንያቱም መፅሀፉ ውስጥ ያለው የስነፍጥረት ታሪክ፣ መዝሙር … አይሻርምና፡፡

ከላይ የቀረቡትን ሁለቱን ሀሳቦች አጠቃለን ስንመለከት "ብሉይ ኪዳን ተሽሯል" ሲባል የተሻረው ህግን በመጠበቅ ፅድቅ ይገኝበት የነበረው መንገድ እንጂ የብሉይ ኪዳን ህግና የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት አይደሉም፡፡

አሁን "ብሉይ ኪዳን" ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ ያለው ግራ አጋቢ ነገር ግልፅ በመሆኑ ሁለቱን ኪዳናት ከውልነቱ አንፃር ወደ ማነፃፀሩ እናልፋለን፡፡

### 4.2.3. ቤተክርስቲያኗ በአዲሱ ኪዳንና በብሉይ ኪዳን ሽግግር ውስጥ ያላስተዋለችው እውነታ - "ሁለቱ ኪዳናት ተተካኪ እንጂ ተዳባይ አለመሆናቸው"

በመግቢያው ላይ እንደተመለከትነው "ኪዳን" ማለት የውል ስምምነት ነው፣ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት የተለያዩ ውሎች እንደማይኖሩት ሁሉ፣ እግዚአብሄር ሰዎች እንዲፀድቁበት የሚጠቀመው ውል/ኪዳን አንድ ነው፣ በመጀመርያ የብሉይ ኪዳን ውል ነበረ፣ ይህ ውል መስራት ባለመቻሉም አዲሱ ኪዳን ወረደ፡፡

ብሉይ ኪዳን ላይ አዲሱ ኪዳን ሲመጣ ሁለት ኪዳኖች(ውሎች) አብረው እንደማይሰሩ ሁሉ፣ አዲሱ ኪዳን የቆመው የቀደመው ኪዳን ተሽሮ ነው፣

- ዕብ.10፡9 "… ሁለተኛውን ሊያቆም ፊተኛውን ይሽራል …"
- ዕብ.8፡7-13 "ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ስፍራ ባልተፈለገም ነበር … አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቷል"

- ዕብ.7፡18-19 "ህጉ ምንም ፍፁም አላደረገምና ስለዚህ የምትደክም የማትጠቅም ስለሆነች የቀደመችው ትዕዛዝ ተሽራለች፣ ወደ እግዚአብሄርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል፡፡"

በዚህም የሁለቱ ኪዳኖች ውል ተዳባይ ሳይሆኑ ተተካኪ መሆናቸውን እንመለከታለን፣ በኪዳናቱ ውስጥም የተተካኩትን ዋና ዋናዎቹን ነገሮች ብንመለከት፣

| ተቁ | ፍሬ ሀሳብ | በብሉይ ኪዳን | በአዲስ ኪዳን |
|---|---|---|---|
| 1 | ኪዳኑ የመጣበት | በድንጋይ ፅላት(ኢያ.3፡6-8, 1ሳሙ.4፡5) | በኢየሱስ (ሚል.3፡1, ዕብ.12፡24) |
| 2 | ኪዳኑ የፀናው | በኮርማ ደም(ዘፀ.24፡7-8) | በኢየሱስ ደም (ማቴ.26፡28, 1ቆሮ.11፡23-26) |
| 3 | የሃጢያት ማስተሰረያ | የእንስሳት ደም(ዕብ.10፡11 | የኢየሱስ ደም (1ዮሐ.1፡7) |
| 4 | ፅላት | የድንጋይ ሰሌዳ (ዘፀ.24፡12) | የሰው ልብ (2ቆሮ.3፡3) |
| 5 | ቤተ መቅደስ | በድንጋይ የተገነባ (ማቴ.24፡1-2) | የሰው ልጅ (1ቆሮ.6፡19-20) |
| 6 | ሰንበት | ቀን | ኢየሱስ (ቆላ.2፡16) |
| 7 | ሊቀካህን | ምድራዊ ሰው (ዕብ.7፡28) | ኢየሱስ(ዕብ.4፡14, ዕብ.6፡20) |
| 8 | ፅድቅ የሚገኘው | ህግን በመጠበቅ | በኢየሱስ በማመን (ገላ.2፡16) |

ከነዚህ ውስጥ ቤተክርስቲያኗ ያተካካችው ከ1-3 ያሉትን ሲሆን ከ4-8 ያሉትን ግን አላተካካችም፣ ቤተክርስቲያኗ እነዚህ ተተካኪ ነገሮችን ማተካካት ባለመቻሏ አዲሱን ኪዳን መፈፀም አልቻለችም የኪዳኑንም በረከቶች ማግኘት አልቻለችም፣ ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን፡-

### 4.2.3.1. የብሉይ ኪዳኑ ፅላት/ታቦት በአዲስ ኪዳኑ ፅላት/ታቦት አለመተካት

በብሉይ ኪዳን "ፅላት" ማለት በእግዚአብሄር እጅ አስርቱ ትዕዛዛት የተፃፈበት የድንጋይ ሰሌዳ ነው፣ ፅላቱም የሚቀመጠው በእንጨት በተሰራ ታቦት ውስጥ ነው፣ በዚህም በተለምዶ "ታቦት" የሚለው ቃል ሰፋ ያለና ፅላትንም የሚያካትት በመሆኑ በዚህ ክፍል ሁለቱም በአንድ ላይ ለመጥራት "ታቦት" የሚለውን ቃል እንጠቀማለን፡፡

በብሉይ ኪዳን በቁሳቁስ የሚሰራው ታቦት/ፅላትና ቤተመቅደስ ተሰጥቶ ነበረ፣ በአዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሄር መንፈስ ማደርያ የሰው ልጅ በመሆኑ በቁስ የሚሰራው ታቦት/ፅላትና ቤተመቅደስ አሰራር ተሽሮ ታቦቱ/ፅላቱና ቤተመቅደሱ የሰው ልጅ ሆነ፡፡

ነገር ግን በቤተክርስቲያንዋ አዲሱ ኪዳን ብሉዩን ስላልተካ ከቁስ የሚሰራው ታቦት/ፅላትና ቤተመቅደስ ለአዲስ ኪዳኑ ታቦት/ፅላትና ቤተመቅደስ ቦታውን አለቀቀም፣ የሚገርመው ደግሞ ቤተክርስቲያኗ ለዚህ አሰራሯ የምታቀርበው መከራከርያ በሙሉ የሚያቀርቡት ከብሉይ ኪዳን ብቻ ነው፣ እንደ መከራከርያ የሚያቀርቡትም [83] "ታቦት መፅሀፍ ቅዱሳዊ ነው" የሚል እንጂ ብሉይ ኪዳን በአዲሱ ኪዳን ሲተካ ታቦት ከፍ በተደረገበት ትርጉሙ አይደለም፡፡

ይህንን መተካካት ከመነሻው ብንመለከት፣ በመጀመርያ እስራኤላውያን በሙሴ በኩል በዘፀ.24 ላይ የተናገረውን ቃል ኪዳን (ብሉይ ኪዳን) በመቀበላቸው በዘፀ.25 ላይ ታቦቱ የቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን ተሰጣቸው፣ በዚህም ታቦቱን ከቃል ኪዳኑ ጋር ስለሚያያዝ "የቃል ኪዳኑ ታቦት" ይባላል (ዘኁ.14፡44, ዘዳ.10፡8, ዘዳ.31፡25, ኢያ.3፡3, 1ሳሙ.4፡4, 2ሳሙ.15፡24, 1ነገ.3፡15, 1ዜና.15፡26, 2ዜና.5፡7 ...)፣ ነገር ግን ህዝቡ በቃል ኪዳኑ ፀንቶ መኖር ባለመቻሉ እግዚአብሄር ቃል ኪዳኑን እንደሚሽርና በዚህም ለቃል ኪዳን የተሰጣቸው የታቦት አሰራር አብሮ እንደሚሻር በነቢያቱ አፍ ቀድሞ ተናገረ፣

[83] መምህር ዶ/ር ዘነበ ለማ፣ **የሙሴን ህግ አስቡ**(VCD)፣ ስለ ታቦት ለሚነሳ ጥያቄ የማያዳግም ምላሽ፣ ዘአብ መዝሙር ቤት

ኤር.3፡16-17 "በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ፣ ይላል እግዚአብሄር፣ በዚያ ዘመን፡፡ የእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ታቦት ብለው ከእንግዲ ወዲህ አይጠሩም፤ ልብ ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም፤ ልብ አያደርጉትም፣ አይሹትምም፣ ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም ... **ከእንግዲህ ወዲህ እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሄዱም**፡፡"

በዚህም ለብሉይ ኪዳን ዘመን የታዘዘው የቃል ኪዳኑ ታቦት በአዲሱ ኪዳን ቦታ የሌለውና ይባሱንም እንደማይሰራ ቀድሞ ተናገረ፡፡

ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ(ማሳያ ሞዴል) በመሆኑ(ዕብ.8፡5)፣ የብሉይ ኪዳኑ ታቦት ሲሻር የአዲስ ኪዳኑ ታቦት/ፅላቱ ማን እንደሆነ? የት እንደሚቀመጥ? ... አነፃፅሮ ነው፣ የሁለቱንም ንፅፅር ለማስተዋል፣ መፅሀፍ ቅዱሱ "ፊደል ቀለምና ድንጋይ" የሚለው የብሉይ ኪዳኑ በድንጋይ ፅላት ላይ የተፃፈውን ፅሁፍ ለማመልከት ሲሆን "የስጋ ልብ፣ ስጋ በሆነ የልብ ፅላት፣ በመንፈስ የሚፃፍና ህጌን በልቦናቸው" የሚለው ደግሞ በሰው ልብ የሚሆነው ፅላት/ታቦት ለማመልከት የተጠቀመው ቃል ነው፣ ቀጥለን ንፅፅሩን እንመልከት፣

- ኤር.31፡31-33 "እነሆ ከእስራኤልና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ... ከግብፅ ሀገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም ... ከነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይሄ ነውና፣ ይላል እግዚአብሄር፤ ህጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፣ በልባቸውም እፅፈዋለሁ ..."

- ሮሜ.7፡6 "አሁን ግን ... በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እነጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም፡፡"

- 2ቆሮ.3፡3-7 "እናንተም በህያው እግዚአብሄር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፣ ስጋ በሆነ ልብ ፅላት እንጂ በድንጋይ ፅላት ያልተፃፈ ... እርሱም ደግሞ፣ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን ... ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረፀ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፣ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም፣"

በዚህም በብሉይ ኪዳን በድንጋይና በእንጨት ሲሰራ የነበረው ታቦት/ፅላት በአዲሱ ኪዳን በእግዚአብሄር መንፈስ በሰዎች ልብ ውስጥ በሚሰራበት አሰራር መተካቱን እንመለከታለን፣ ይህም አሰራር በአዲስ ኪዳን "የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ የሰው ልጅ ነው" ከሚለው አሰራር ጋር የተያያዘ ነው፣ በዚህም በአዲስ ኪዳን ያለው አሰራር ከቁሳዊው አሰራር ወደ መንፈሳዊ ትርጉም ከፍ ያለ መሆኑን እንመለከታለን(ዕብ.9፥9-10)፡፡

ለዚህም ነው በአዲሱ ኪዳን ስለ ቁሳዊው ታቦት/ፅላት አጠቃቀም ትዕዛዝ ያልተሰጠው፣ መሪዎቹም ኢየሱስና ሐዋርያቱም ታቦት ሰርተው ሲያገለግሉት፣ ሲገለገሉበትም፣ ሲሰግዱለትም ሆነ ሲሸከሙት ያልታየው፣ ይህም የሆነው ከላይ በተገለፀው የሁለቱ ኪዳናት መተካካት ምክንያት በተተካካው የታቦት ትርጉም ምክንያት ነው፡፡

ሌላው ታቦቱ ጋር በተያያዘ ብዙ ሰውን ግራ ያጋባው "የሙሴ የቃል ኪዳን ታቦት በኢትዮጵያ ውስጥ አክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን ይገኛል" የሚባለው ነው፣ ይህ የተሳሳተ ነው፣ ታቦቱ አሁን በምድር ላይ የለም ምክንያቱም ዘመኑ አዲስ ኪዳን ስለሆነ በክብር ወደ ሰማይ ተወስዷል(ራዕ.11፥19)፣ በኢትዮጵያ ውስጥ አይኖርም ምክንያቱም ቃል ኪዳኑ የእስራኤል እንጂ የኢትዮጵያ አይደለምና፣ ሰለሞን ለልጁ በስጦታ አልሰጠም ታቦት በስጦታ የሚሰጥ እቃ አይደለም በተጨማሪም ከሰለሞን በኋላ በቤተመቅደስ ውስጥ ነበረና(2ዜና.35፥3)፣ ከዘረፋ እንዲድን በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል እንዲደበቅ አልተደረገም ምክንያቱም የኢትዮጵያ ታቦትና የቃል ኪዳኑ ታቦት መካከል ሰፊ ልዩነት አለና(ዝርዝሩን በ4.4.2.2 ክፍል መመልከት ይቻላል)፣ በዚህም የቀረበው ሀሳብ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ ሁለቱ ኪዳናት ተተካኪ በመሆናቸው ቁሳዊው ታቦት/ፅላት በአዲሱ ኪዳን በመንፈሳዊ ትርጉም የተተረጎመ መሆኑን ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ የብሉይ ኪዳኑ ቁሳዊው ታቦት/ፅላት ባለመነሳቱ የአዲስ ኪዳኑ ታቦት/ፅላት ቦታውን መያዝ አለመቻሉንና በዚህም ቤተክርስቲያኗ የአዲስ ኪዳኑን ታቦት/ፅላት በረከት ማግኘት አለመቻሏን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.3.2. የብሉይ ኪዳኑን ቤተመቅደስ በአዲስ ኪዳኑ ቤተ-መቅደስ አለመተካት

ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን ሲተካ ከተተካኩት ውስጥ ሌለኛው ቤተመቅደስ ነው፣ በአዲስ ኪዳን የቤተመቅደስ ትርጉም ከተለመደው በግንባታ ከሚሰራው ቤተመቅደስ ወደ መንፈሳዊ አተረጓጎም ከፍ ተደረገ፣ ኢየሱስም ከአንዳንዶች ጋር መግባባት ያልቻለው በዚህ ከፍ በተደረገው ትርጉም በመናገሩ ነበረ፡-

- ዮሐ.4፡20-24 "አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፣ እናንተም ሰው ሊሰግድ የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው፣ ኢየሱስም እንዲህ አላት፣ አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል ... ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ <u>በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት</u> ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል..."
- ዮሐ.2፡19-21 "ኢየሱስም መልሶ፣ ይህንን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሶስት ቀንም አነሳዋለሁ አላቸው፣ ስለዚህ አይሁድ፣ ይህ ቤተመቅደስ ከአርባ ስድስት አመት ጀምሮ ይሰራ ነበር፣ አንተስ በሶስት ቀን ታስነሳዋለህን? አሉት፡፡ <u>እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል</u> ነበረ፡፡"

ኢየሱስ ይህንን የተናገረው በብሉይ ኪዳኑ ቤተመቅደስ በሚባለው ግንባታ ሳይሆን በአዲስ ኪዳኑ ትርጉም ነበረ፣ ይህንን የአዲስ ኪዳን አተረጓጎም ሐዋርያቱም ሲያስረዱ፣

- 1ቆሮ.3፡17 "... የእግዚአብሄርም ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ፡፡"
- 1ቆሮ.6፡19-20 "... ስጋችሁ ከእግዚአብሄር የተቀበላችሁት በእናንተ ውስጥ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?"
- 2ቆሮ.6፡16 " ... እኛ የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ ነንና ..."

በዚህም በቁሳዊ እቃ በግንባታ የሚሰራው የብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ በአዲሱ ኪዳን በመንፈሳዊው ትርጉም የሰው ልጅ መንፈሳዊ መሰራት ሆኖ እንመለከታለን፣ ይህም በአዲሱ ኪዳን ፅላቱ የሰው ልብ ከሆነበት አሰራር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያኒቱ ምን ያህል ከአዲስ ኪዳኑ ጋር መሄድ እንዳልቻለች እንመለከታለን፡፡

### 4.2.3.3. የብሉይ ኪዳኑ የቀን ሰንበት በአዲስ ኪዳኑ ሰንበት በክርስቶስ አለመተካት

ቤተክርስቲያንዋ ሁለቱን ኪዳናት ስለተቀላቀሉባት የሰንበት ነገር ላይ ወጥ አቋም ለመያዝ የተቸገረችበትና በሁለት ልብ የቆመችበት ቦታ ነው፣ በዚህም ሰንበት ለማክበርና ለመተው ሁለት ልብ ሆኖባታል፣ በዚህም በሰንበት እንደ እርሻ ያሉ ከባባድ ስራዎችን ስትከለክል ነገር ግን እንደ ማብሰል ያሉ አነስተኛ ስራዎችን አትቃወምም፣ በዚህም ወይ ብሉይ ኪዳን እንደሚያዘውና ዛሬ አይሁዳውያን አካባቢ እንደምንመለከተው "ምንም ነገር ባለመስራት" አላረፈችም ወይ እንደ አዲስ ኪዳኑ "ሰንበት(እረፍት) ክርስቶስ ነው" ብላ የቀኑን ሰንበት በክርስቶስ አልተካችም፣ በዚህም ሁለት ልብ ሆና እንመለከታለን፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን "ሰንበት" ማለት ሰባተኛው ቀን ነው፣ ይህም ቀን ፈጣሪ ፍጥረታቱን ፈጥሮ ያረፈበት ቀን ነው(ዘፍ.2፡2)፣ በዚህም መፅሀፉ ይህንን ቀን በሰዎችም ዘንድ የእረፍት ቀን (ዘሌ.23፡3, ዘዳ.5፡14)፣ የሚቀደስ ቀን (ዘፀ.20፡8, ኤር.17፡22)፣ የደስታ ቀን (ኢሳ.58፡13) ... መሆን እንዳለበት ይናገራል፣ ይህንንም ትዕዛዝ የሚተላለፍ እስከ ሞት የሚደርስ ብርቱ ቅጣት እንዲጣልበት ያዛል(ዘፀ.31፡14)፡፡

እነዚህ ሁሉ የብሉይ ኪዳን ትዕዛዞች እያሉ የአዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን መተካት ምክንያት፣ ኢየሱስ የሰንበት ቀን አለማክበሩን(ዮሐ.5፡1-18, ዮሐ.9፡14-16) ከዚያም አልፎ ሌሎችም እንዳያከብሩ ማስተማሩ(ማቴ.12፡1-12, ማር.2፡23-28, ሉቃ.6፡1-9 ...) ከዚያም ሐዋርያቱ "የቀኑ ሰንበት መሰረዙን" መናገራቸው (ዕብ.4፡9) እንመለከታለን፡፡

ሰንበትን ማክበር የተላለፈው ያውም በትልቁ የአስርቱ ትዕዛዛት ላይ ነው(ዘፀ.20፡8)፣ ክርስቶስ ደግሞ "ህግን ልሽር አልመጣሁም" ብሎ ለምን ህግን ይሽራል? የሚሉ ጥያቄዎች በወቅቱም ሆነ ከዚያ በኋላ በነበረው ትውልድ ውስጥ ጥያቄ አስነስቷል፣ የሚገርመው ደግሞ አሁንም ብዙዎችን ግራ አጋብቷል፡፡

ነገር ግን መፅሃፍ ቅዱሱን በማስተዋል ላጠና የሚጋጩ ቃላት አለመኖራቸውንና "ህግ አይሻርም" እንደተባለው አለመሻሩን ነገር ግን

የሰንበት አተረጓጎም እንደ ቤተመቅደሱ ትርጉም ከፍ ባለ አተረጓጎም በመተካቱ ነው፣

ቆላ.2፡16-17 “እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በአል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፣ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፣ አካሉ ግን ክርስቶስ ነው፡፡”

አካሉ ሲገለጥ ጥላ(ማሳያ ሞዴሉን) ማንም አይከተለውም፣ በዚህም በአዲስ ኪዳኑ ማረፊያው በቀን ሳይሆን በክርስቶስ መሆኑና፣ ክርስቶስን ያገኘ ከሁሉ ነገር እንዳረፈና ሰንበት እራሱ ክርስቶስ መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም በሳምንት አንድ ቀን ከማረፍ የዘላለምን እረፍት ክርስቶስን መምረጡ የተሻለ ነው፡፡

### 4.2.3.4. የብሉይ ኪዳኑን የሰው ሊቀካህን በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ሊቀካህን አለመተካት

“ሊቀካህን” ማለት በሰዎችና በእግዚአብሄር መካከል በመገኘት ስለ ሰዎች ሀጢያት መስዋዕት በማቅረብ ሀጢያት የሚያስተሰረይ ማለት ነው(ዕብ.8፡3, ዕብ.5፡1, ዕብ.7፡27 ...)፣ የመጀመሪያው ሊቀካህን አሮን ነበረ፣ ከዚያም እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ብዙ ሰዎች በዚህ ስልጣን ሲሾሙ ነበረ፣ በአዲሱ ኪዳን ግን በሊቀካህንነት የተሾመው ኢየሱስ ብቻ ነው፣ ነገር ግን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስም በኋላ ሰዎችን በሊቀካህንነት ትሾማለች፣ ይህ ደግሞ የአዲስ ኪዳኑን አሰራር ያላገናዘበና የክርስቶስን የሊቀካህንነት ሹመት የሚጋፋ አሰራር ነው፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ግን በአዲስ ኪዳን ሊቀካህኑ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን ይናገራል፣

- ዕብ.7፡28 “ህጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀካህናት አድርጎ ይሾማል፣ ከህግ በኋላ የመጣ የመሃላው ቃል ግን ለዘላለም ፍፁም የሆነውን ልጅ ይሾማል፡፡”
- ዕብ.4፡14-15 “እንግዲህ ... ትልቅ ሊቀካህናት የእግዚአብሄር ልጅ ኢየሱስን ስላለን፣ ፀንተን ሀይማኖታችንን እንጠብቅ፡፡”

- ፲ጢሞ.2፡5 “አንድ እግዚአብሄር አለና በእግዚአብሄርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡”

በዚህም በአዲሱ ኪዳን ሊቀካህን ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ከኢየሱስ ቀጥለው የነበሩት ዋናዎቹ እነ ጳውሎስና ጴጥሮስ እንኳን ሊቀካህን አልተባሉም፡፡

ስለዚህ በአዲሱ ኪዳን በእግዚአብሄርና በሰዎች መካከል የሚቆመው ሊቀካህን ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ሌሎቹ አማኞች በሙሉ “ካህናት” ናቸው(፲ጴጥ.2፡5, ፲ጴጥ.2፡9, ራዕ.፲፡6, ራዕ.5፡9-፲0)፣ ስለዚህ የብሉይ ኪዳኑን አሰራር በመተው የሊቀካህንነት ቦታን ለአዲስ ኪዳኑ ሊቀካህን ለክርስቶስ መተዉ መልካም ነው፡፡

### 4.2.3.5. <u>በብሉይ ኪዳኑ “ህግ በመጠበቅ” ይገኝ የነበረውን ፅድቅ በአዲስ ኪዳኑ “በክርስቶስ ማመን” አለመተካት</u>

ቤተክርስቲያንዋ ሁለቱ ኪዳናት ባለማተካካቷ ምክንያት የሁለቱ ኪዳናት የፅድቅ መንገድ ተቀላቅሎባት ይገኛል፣ በዚህም አንድ ሰው የሚፀድቀው እንደ ብሉይ ኪዳን ህጉን ፈፅሞ በመጠበቅና እንደ አዲሱ ኪዳን በክርስቶስ በማመን እንደሆነ ትናገራለች፡፡ የአዲሱ ኪዳኑ “ሰዎች በክርስቶስ አምነው ብቻ ይፀድቃሉ” የሚለው ብቻውን የማፅደቅ ብቃቱ አላሳመናትም፣ በዚህም ሰው ለመፅደቅ በኢየሱስ ከማመን በተጨማሪ የብሉይ ኪዳንኑ የህግ ፍፅምና መጠበቅ እንዳለበት ታስተምራለች፡፡

ለዚህ ማጠናከሪያም ያዕ.2፡24-26 ላይ “ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በስራ እንዲፀድቅ ታያላችሁና … ከነፍስ የተለየ ስጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁም ከስራ የተለየ እምነት የሞተ ነው፡፡” የሚለውን ቃል ታቀርባለች፡፡

በዚህም ምዕመናኖችዋ ፅድቅን ለማግኘት በክርስቶስ ከማመን በተጨማሪ የህግን ፍፃሜ በመጠበቅ ለመፅደቅ ሲታገሉ ይታያል ነገር ግን ይህ ስህተት መሆኑና ስህተቱም የመጣው የሁለቱን ኪዳናት ልዩነትና የያዕቆብ መልዕክት የተፃፈበትን አውድ ካለማወቅ የተነሳ መሆኑን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

የሐዋርያውን የያዕቆብ መልዕክት ከመጀመሪያው አንስተን ስንመለከት፣ ያዕቆብ እያወዳደረ ያለው ጫፍ ለጫፍ ስለወጡት ሁለት ሰዎች ነው፣ እነሱም በያዕ.2፡18 ላይ የተገለፁት፣ "በህግ ብቻ ነው የምፀድቀው" የሚለውና "በእምነት ብቻ ነው የምፀድቀው ስራ አያስፈልገኝም" ስለሚሉ ሰዎች ነው፣ ያዕቆብም ሊወቅስ የፈለገው "እኔ እምነት አለኝ ስራ አያስፈልገኝም" የሚለውን በእንግሊዘኛው "antinomian" ስለሚባለው አስተምህሮ ነው፣ ከመግቢያው ይሄ ሰውዬ ምን እንደሚመስል ነግሮናል፣ ያዕ.1፡23-26 "ቃሉን የሚሰማ የማያደርገው … አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ የሚያመልክ የሚመስለው …" በማለት የሰውየውን ማንነት አሳይቶናል፡፡

እንደዚህ አይነት ሰዎች፣ "ህግ አታፀድቅም" የሚለውን "ህግ ተሽራለችን" በማለት የሚያነቡ ናቸው ነገር ግን በአዲሱ ኪዳን ህግ አልተሻረችም፣ ምንም እንኳን ህግ ማፅደቅ ባትችልም የማስኮነን አቅም ግን አላት፣ ህግን የጣሰ ዛሬም ሀጢያተኛ ነውና ነገር ግን በአዲሱ ኪዳን አንድ ሰው ህግን የሚጠብቀው ሊፀድቅበት ሳይሆን በመፅደቁ ምክንያት ነው፣ በዚህም ምክንያት ነው በክርስቶስ አምኖ ፀድቆ ሳያስተውል ህግን ለሚጥሰው ሰው የኢየሱስ አማላጅነት ከኩነኔ የሚያድነው፡፡

በዚህም ለተወሰነ አውድ "በእምነት ድኛለሁ መልካም ስራ መስራት አያስፈልገኝም" ለሚል ሰው ተለይቶ የተፃፈውን የያዕቆብን መልዕክት ወስዶ ለሁሉም ሰው እንደተነገረ አድርጎ የአዲስ ኪዳኑን የፅድቅ መንገድ ደካማ አድርጎ ተሞክሮ ያልተቻለውን የብሉይ ኪዳን የፅድቅ መንገድ(የህግን ፍፅምና መጠበቅ) ማዳበሉ ስህተት ነው፣ አደጋም አለው ምክንያቱም ከመነሻው ህጉን በመጠበቅ መፅደቅ ይቻል ቢሆን ኖሮ የክርስቶስ መምጣት አላስፈላጊና የከፈለውም ዋጋ ከንቱ የሚያደርግ ነውና፣ በዚህም፣

- የህግን ፍፅምና በመጠበቅ መፅደቅ የማይቻል መሆኑን፣
- በአዲሱ ኪዳን ሰዎች የሚፀድቁት በክርስቶስን በማመን ብቻ መሆኑን፣
- ህግ በመጠበቅ መፅደቅና በእምነት መፅደቅ የማይዳበሉ መሆኑን፣
- ህግ ማፅደቅ ባይችልም ማስኮነን የሚችል መሆኑን፣
- አማኝ ሳያስተውል ለሚያደርገው የህግ ጥሰት ዋስትና መቀመጡን

ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 4.2.3.5.1. የህግን ፍፅምና በመጠበቅ መፅደቅ የማይቻል መሆኑ

በአዳም መውደቅ ምክንያት የሰው ልጅ ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል(ማቴ.25፡41) እየጎረፈ በመሆኑ እግዚአብሄር የሰው ልጆች ከሲኦል እንዲድኑ አቀደ፣ ለዚህም በየዘመናቱ ከተለያዩ ትውልዶች ጋር ቃል ኪዳን በማሰር ሰዎች ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ ወደ ገነት የሚገቡበትን መንገድ ሲያዘጋጅ ነበረ፣ በዚህም በነሙሴ ዘመን ከእስራኤል ህዝብ ጋር ብሉይ ኪዳንን አደረገ፣ በዚህ ቃል ኪዳን መሠረትም ህዝቡ የወረደለትን ህግ፣ የአምልኮና የመንፃት ስርአቶችን በመጠበቅ ፅድቅ የሚያገኝበት አሰራር ዘረጋ፡፡

ነገር ግን ፈጣሪ በሙሴ በኩል ያወረደውን የመፅደቂያ መንገድ አንድም ሰው ማሟላት አልቻለም፣ ሁሉም ሃጢያተኛ ሆኑ፣

- ሮሜ.9፡31 “እስራኤል ግን የፅድቅን ህግ እየተከተሉ ወደ ህግ አልደረሱም፡፡”
- ሮሜ.3፡20 “የህግ ስራ በመስራት ስጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይፀድቅ ነው…”
- ገላ.2፡16 “ስጋን የለበሰ ሁሉ በህግ ስራ ስለማይፀድቅ”

በዚህም የመጀመሪያው የማፅደቂያ መንገድ አለመስራቱ ተረጋገጠ፣ በዚህም የብሉይ ኪዳኑ ማፅደቂያ መንገድ ተሻረ(ዕብ.10፡9, ዕብ.7፡18-19, ዕብ.8፡7-13)፣ “ህግን በመጠበቅ መፅደቅ” የተባለው የፅድቅ መንገድ ተዘጋ፣ ቀጥለን የምንመለከተው ሌላ ፅድቅ የሚገኝበት መንገድ ተዘጋጀ፡፡

### 4.2.3.5.2. በአዲሱ ኪዳን ሰዎች የሚፀድቁት በክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑ

የብሉይ ኪዳን ሰዎችን ማፅደቅ ባለመቻሉ የሰው ልጅ በሃጢያቱ ምክንያት ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል መጉረፉን ስላልቆመ፣ ፈጣሪ ሰዎች የሚድኑበትን ሌላ ቀለል ያለ መንገድ ቀየሰ፣ ይህም ስለሰዎች ጥፋት ስለሚያስፈልገው መስዋዕት ክርስቶስ ዋጋ እንዲከፍልና ሰዎች ደግሞ “በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን” እንዲፀድቁ፣

- ሮሜ.3፡21-24 “አሁን ግን በህግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሄር ፅድቅ ያለ ህግ ተገልጦአል፣ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ

የሆነ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሄር ፅድቅ ነው፣ ልዩነት የለምና ሁሉም ሀጢያት ሰርተዋልና የእግዚአብሄርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በፀጋው ይፀድቃሉ፡፡"

- ራዕ.21፡6 "አልፋና ያሜጋ የመጀመርያውና መጨረሻው እኔ ነኝ ለተጠማ ከህይወት ውሀ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ፡፡"
- ራዕ.22፡17 "መንፈሱና ሙሽራው "ና" ይላሉ፣ የሚሰማም "ና" ይበል፣ የተጠማም ይምጣ፣ የወደደም የህይወትን ውሃ እንዲያው ይውሰድ፡፡"
- ገላ.2፡16-21 "ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲፀድቅ እንጂ በህግ ስራ እንዳይሆን አውቀን፣ ስጋን የለበሰ ሁሉ በህግ ስራ ስለማይፀድቅ፣ እኛ ራሳችን በህግ ስራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንፀድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል ... የእግዚአብሄርን ፀጋ አልጥልም፣ ፅድቅስ በህግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ፡፡"

በዚህም በአዲሱ ኪዳን ፅድቅ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ተደረገ፡፡

አዲሱ የፅድቅ መንገድ ምንም እንኳን ኢየሱስን ትልቅ ዋጋ ቢያስከፍለውም ለሰዎች ቀለል የተደረገው ግን ሰው ሁሉ ከሲኦል እንዲድንበት በማሰብ ነው፣ ነገር ግን ይህን ቀለል ያለውን መንገድ በማቅለልና ለብቻው ያለውን የማፅደቅ ብቃት ላይ መናገር ለቅጣት ይዳርጋል

ዕብ.10፡28-29 "የሙሴን ህግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሶስት ቢመሰክሩበት ያለርህራሄ ይሞታል፤ የእግዚአብሄርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ እርኩስ ነገር የቆጠረ የፀጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፣ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል፡፡"

በዚህም ክርስቶስን የከፈለውን ዋጋ በማቃለል በሱ ላይ ሌላ ነገር መደረብ የዘላለም ቅጣትን በራስ ላይ መጋበዝ ነው፡፡

### 4.2.3.5.3. ህግ በመጠበቅ መፅደቅና በእምነት መፅደቅ ተተካኪ እንጂ ተዳባይ አለመሆናቸው

ሁለቱ ኪዳናት ተተካኪ እንጂ ተዳባይ ባለመሆናቸው በሁለቱ ኪዳናት የወረዱት ሁለቱ መፅደቂ መንገዶች ተተካኪ እንጂ ተዳባይ አይደሉም፣ ይህንንም መተካካት መፅሀፍ ቅዱሳችን፣ "ህግና እምነት"፣ "ህግና ፀጋ"፣ "ስራና ፀጋ" እያለ በተለያየ አገላለፅ እያነፃፀረ ተተካኪነታቸውን ይነግረናል፡-

- ሮሜ.3፡20-22 "... የህግ ስራን በመስራት ስጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይፀድቅ ነው ... አሁን ግን በህግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሄር ፅድቅ ያለ ህግ ተገልጦአል፣ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሄር ፅድቅ ነው..."
- ገላ.2፡16-21 "ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲፀድቅ እንጂ በህግ ስራ እንዳይሆን አውቀን፣ ስጋን የለበሰ ሁሉ በህግ ስራ ስለማይፀድቅ፣ እኛ ራሳችን በህግ ስራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንፀድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል ... የእግዚአብሄርን ፀጋ አልጥልም፣ ፅድቅስ በህግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ፡፡"
- ገላ.3፡23-26 "እምነት ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከህግ በታች እንጠበቅ ነበረ፡፡ እንደዚህ በእምነት እንፀድቅ ዘንድ ህግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኗል፣ እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚታችን በታች አይደለንም፣ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁና፤"
- ገላ.5፡4 "በህግ ልትፀድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከፀጋው ወድቃችኋል፡፡"
- ፊሊጵ.3፡8-9 "... ስለእርሱ ሁሉን ተጎዳሁ፣ ክርስቶስን አገኝ ዘንድ፣ በክርስቶስም በማመን ያለው ፅድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሄር ዘንድ ያለው ፅድቅ እንጂ ከህግ ለኔ ያለው ፅድቅ ሳይሆንልኝ ..."

- ኤፌ.2፥8-9 "ፀጋው በእምነት አድኖአችሃል፣ ይህም የእግዚአብሄር ስጦታ እንጂ ከእናንተ አይደለም፣ ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም፡፡"

በዚህም ሁለቱም መፅደቂያ መንገዶች ተተካኪ መሆናቸውን እንመለከታለን፣ በዚህም ቤተክርስቲያንዋ የሁለቱ ኪዳናት ተተካኪነት ባለማወቅ ለፅድቅ "የህግ ፍፅምናና በክርስቶስ ማመን" ብላ ያስቀመጠችው ተደራራቢ መፅደቂያ መስፈርቶች ስህተት መሆኑና የአዲስ ኪዳን አማኞች ፅድቅን የሚያገኙት "በክርስቶስ በማመን" ብቻ መሆኑ እንመለከታለን፡፡

#### 4.2.3.5.4. ህግ ማፅደቅ ባይችልም ማስኮነን የሚችል መሆኑ

ሰዎች ህግን በፍፅምና ጠብቀው ሊኖሩበት አይቻሉ እንጂ፣

- በአዲሱ ኪዳን ህጉ አልተሻረም

  ማቴ.5፥18 "እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከህግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈፀም ድረስ፡፡"

- ህጉ አሁንም ቅዱስ ነው

  ሮሜ.7፥12 "...ህጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት፡፡"

- ህጉ ዛሬም ያስፈልጋል

  ሮሜ.3፥20 "... ኃጢያት በህግ ይታወቃልና፡፡"

- ህጉን የተላለፈ ሀጢያተኛ ስለሚሆን ህጉ ዛሬም ሰዎችን ማስኮነን ይችላል

  ሮሜ.6፥23 "የሀጢያት ደመወዝ ሞት ነውና ..."

በዚህም ሰዎች ህግን ጠብቀው በህጉ መፅደቅ ባይችሉም፣ ህግ ግን ሰዎችን ማስኮነን እንደሚችል እንመለከታለን ነገር ግን በክርስቶስ አምኖ የፀደቀ ሰው ህግን ተላልፎ ሀጢያት ቢሰራ ምን ይሆናል የሚለውን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### 4.2.3.5.5. አማኝ ሳያስተውል ለሚያደርገው የህግ ጥሰት ዋስትና መቀመጡ

ብዙዎችን ግራ የሚያጋባውና ሁለቱንም መፅደቂያ መንገድ እንዲይዙ ያደረገው፣ በክርስቶስ አምነው የፀደቁ ሰዎች ሀጢያት ሲሰሩ እጣ ፋንታቸው ምንድነው? የሚለው ነው፣ ይህንን ለመረዳት ከመነሻው ሀጢያት የሌለበት ሰው እንደሌለ ማወቅ ያስፈልጋል፣

1ዮሐ.1፡8 "ማንም ሃጢያት የለብኝም የሚል ይዋሻል"

በዚህም ሁሉም ሰው ሀጢያት አለበት ነገር ግን አማኝ በተቻለው መጠን ራሱን ከሀጢያት ገድቦ እየኖረ ሳያስተውል ወይንም ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ለሚሰራው ሀጢያት የኢየሱስ አማላጅነት(1ዮሐ.2፡1) እና የእግዚአብሄር ምህረት(ዕብ.8፡12) ከኩነኔ ያድኑታል፡፡

1ዮሐ.2፡1 "ልጆቼ ሆይ፣ ሀጢያትን እንዳታደርጉ ይህን እፅፍላችኃለሁ፡፡ ማንም ሀጢያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፣ እርሱም ፃድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡"

ይህ ተፈጥሮአዊውን ሰውኛ ማንነት ያገናዘበ እውነታ ነው፣ አንድ በክርስቶስ አምኖ የፀደቀ ሰው እንዳመነ መልአክ አይሆንም የነበረውን የሀጢያት ህይወት እየተላቀቀ የሚሄደው በሂደት ነው፣ ይህ አባባል ግን "እምነት አለኝ ህግ አያስፈልገኝም" ከሚለው ያዕቆብ ካወገዘው ትዕቢተኛ ሰው ለይተን ማየት ያስፈልገናል ምክንያቱም ሲጀምር "ወንድሞቼ ሆይ ሀጢያትን አታድርጉ" ብሎ ስለሚጀምር፡፡

ስለዚህ የመፅሀፍ ቅዱስን አሰራር በየአውዱ መመልከት ከስህተት ያድናል፣ ስለዚህ ማንም ሰው የክርስቶስ ደም ለማፅደቅ ሙሉ አቅም እንዳለው አውቆ፣ በክርስቶስ በኩል የመጣውን በረከት በሙላት መጠቀም አለበት፡፡

### 4.2.4. ቤተክርስቲያኗ ሁለቱን ኪዳናት ባለመተካካቷ ያጣቻቸው የክርስትና እሴቶች

ከላይ እንደተመለከትነው በቤተክርስቲያኗ ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳኑ ቦታ ባለመልቀቁ ምክንያት ቤተክርስቲያንዋ በክርስቶስ በማመን ወደ ድነት መምጣት አልቻለችም፣ ከመሠረታዊ የክርስትና ዕሴቶችን፣ ይህም መንፈስ ቅዱስን መቀበል፣ የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎችን መቀበልና ዳግም መወለድ ጋር እንግዳ ሆናለች፡፡

#### 4.2.4.1. መንፈስ ቅዱስን መቀበል

ሰዎች በክርስቶስ በማመናቸው ከሚያገኙት ጥቅሞች ዋነኛው መንፈስ ቅዱስ በነሱ ላይ ማረፉ ነው፣ በዚህም ብዙ ቅዱሳን በክርስቶስ ሲያምኑ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ነበረ፤ 1ተሰ.4፡8, ሐስ.8፡15-17, ሐስ.10፡44, ሐስ.19፡6, ሉቃ.11፡13, ዮሐ.20፡22, ሐስ.1፡8, ሐስ.4፡8, ሐስ.4፡31, ሐስ.5፡32, ሐስ.6፡3-5, ሐስ.13፡52, 1ዮሐ.4፡13 …

መንፈስ ቅዱስን መቀበል ክብርም ነው፣ ጥቅሙ ብዙ ነው፣ በመጀመሪያ የእግዚአብሄር ልጅነት ምስክር ነው(ሮሜ.8፡16)፣ መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ድካም ያግዛል(ሮሜ.8፡26)፣ ሀይልን ይሰጣል(ሐስ.1፡8)፣ የአማኝ መለያ ማህተም ነው(ኤፌ.4፡30)፣ የመዳን ዋስትና ነው(ኤፌ.1፡14)፣ የተለያዩ ፀጋዎችን ይሰጣል(1ቆሮ.14)፣ በዚህም የመንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ላይ መውረድ ሰውን ሙሉ የእግዚአብሄር ልጅ ያደርጋል፡፡

ነገር ግን ቤተክርስቲያኒቷ "መንፈስ ቅዱስን መቀበል" ከሚባለው ዋነኛው የክርስትና ዕሴት ጋር በታሪክ እንጂ በተግባር አትተዋወቅም፣ ምክንያቱም፣

- የአዲስ ኪዳኑን የፅድቅ መንገድ ስላላገኘች፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በኢየሱስ ስራ ሙሉነት አምኖ ያልፀደቀ ላይ ስለማያርፍ፣
- የቤተክርስቲያንዋ ምዕመናን ከላይ እንደተመለከትነው የቁሳዊውን ፅላት ባለመተዋቸው የስጋው ፅላት ቦታውን ባለመያዙ፣ የግንባታውን ቤተመቅደስ ፋንታ የስጋው ቤተመቅደስ መተካት ባለመቻሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ሊያርፍባቸው አይችልም፣

- በቤተክርስቲያንዋ ውስጥ ቅድስና መጥፋቱና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ቅድስና የሌለውን ቦታ ስለማይወድ ነው፣ ይህም ሰይጣን በስውር በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተመለከ መገኘቱ፣ በ4.4.2 ክፍል እንደተመለከተው ጣዖታት በቅድስና ስም ተጠቅልለው በቤተክርስቲያን መገኘታቸው፣ የሰይጣን ኤጀንቶች ቤተክርስቲያንዋን መውረር ...

በነዚህ ምክንያቶች ለቤተክርስቲያንዋ ሆነ ለምዕመናኖቿ "በመንፈስ ቅዱስ መሞላት" የሚለው ቃል የመፅሀፍ ቅዱስ ታሪክ እንጂ በዚህ ዘመን ለሚኖር ለአማኝ የሚሰጥ ፀጋ አይመስላቸውም፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗም ሆነች ተከታዮቿ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላትም ከሚገኙት በረከቶች ጎድለው እንመለከታለን፡፡

### 4.2.4.2. <u>የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች</u>

"ፀጋ" ማለት አምላካዊ ስጦታ ማለት ነው፣ መንፈስ ቅዱስም አምላክ በመሆኑ ለሰዎች የተለያዩ ፀጋዎችን ይሰጣል፣ እነዚህም ፀጋዎች ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ... የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ እነዚህ ፀጋዎችም ለአማኞች ሲሰጡ እንደነበረ በመፅሀፍ ቅዱሱ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንመለከታለን (1ቆሮ.14, ሐስ.2፡4, ሐስ.2፡38, ሐስ.10፡38, ሐስ.11፡24, ሐስ.19፡6, 1ቆሮ.12፡7 ...)

በርግጥ ከላይ እንዳየነው መንፈስ ቅዱስ ከነሱ ጋር ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ፀጋዎችን መጠበቅ አይቻልም፣ በዚህም ቤተክርስቲያንዋ የፀጋ ስጦታዎች በታሪክ እንጂ በተግባር አታውቃቸውም፣ በዚህም አገልጋዮችዋ የታሪክ መምህራን ሆነው የቀሩባት ቤተክርስቲያን ሆናለች፣ ይህም መፅሀፍ ቅዱሱ፣

2ጢሞ.3፡5 "የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል ..."

በማለት የገለፃቸው አይነት ቤተክርስቲያን ሆናለች ይባሱኑ ደግሞ አሁን ባለንበት በመጨረሻው ዘመን ሐስ.2፡17 "በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ስጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትንቢት ይናገራሉ ..." ከሚለው ቃል ጋር በተቃርኖ እየሄደች ትገኛለች፡፡

በዚህም ቤተክርስቲያንዋ ከፀጋ ስጦታው ጎድላ እንዲሁም ከመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሄር እቅድ ጋር ጀርባ ለጀርባ ተቀምጣ ትገኛለች፡፡

### 4.2.4.3. ዳግም መወለድ

በቤተክርስቲያኗ “ዳግም መወለድ” የሚባለው ቃል እንግዳ ነገር ነው ነገር ግን ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ መንግስተ ሰማያት ሊገባ አይችልም፣

ዮሐ.3፡3-15 “ኢየሱስም መልሶ፡፡ እውነት እውነት እልሀለሁ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሄርን መንግስት ሊያይ አይችልም አለው … ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሄር መንግስት ሊገባ አይችልም …”

ዳግም መወለድ በዋናነት ሁለት መሠረታዊ ሀሳቦችን ይይዛል፣ ከውሃ መወለድና ከመንፈስ መወለድ፡፡

ከውሃ መወለድ የሚለው የውሀ ጥምቀትን ያሳያል፣ በቤተክርስቲያንዋ የጥምቀት ስርአት እንደሚከናወን የታወቀ ነው በ4.4.1.3 ክፍል ከተገለፁት መስተካከል ከሚገባቸው ነገሮች በስተቀረ፣ ነገር ግን ከመንፈስ መወለድ የተባለው ለቤተክርስቲያንዋ እንግዳ ነገር ነው፣ ምክንያቱም ከላይ እንዳየነው ቤተክርስቲያኒቷ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ግንኙነት ስለሌላት፡፡

በዚህም “ዳግም መወለድ” የሚባለው የክርስትና መሠረት በቤተክርስቲያኗ ተከታዮች ዘንድ አለመሟላቱን እንመለከታለን፣ ዳግም ያልተወለደ ደግሞ መንግስተ ሰማያት አይወርስም፣ በዚህም የቤተክርስቲያንዋ ተከታዮች በሙሉ መንግስተ ሰማያትን እንደማይወርሱ እንመለከታለን፡፡

## ማጠቃለያ(ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን የተተካበትን ምስጥር አለማግኘት)

ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የብሉይና አዲስ ኪዳን አንድነትና ልዩነት መለየት ባለመቻልዋ ምክንያት አሮጌው አሰራር ለአዲሱ አሰራር ቦታ ባለመልቀቁ፣ አዲሱ ኪዳን ቦታውን መያዝ አልቻለም፣ በዚህም ምዕመናኖቿ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የከፈለውን ቤዛ ማግኘት አይችሉም፡፡

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ነገሮች ምን ያህል የተያያዙ መሆናቸው ነው፣

- መንፈሳዊውን የሰውን ቤተመቅደስነት ባለማወቅ የህንፃውን ቤተመቅደስ ይገነባሉ፣ ፅላቱ የሰው ልብ መሆኑን ባለማወቅ ከእንጨት ፅላትና ታቦት ይሰራሉ፣ በዚህም የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ መሆን አልቻሉም፡፡
- ለታቦቱና ለቤተመቅደሱም አስተናጋጅ ሊቀካህን ይሾማሉ፣ በዚህም ለሀጢያት ስርየት የቆመው የሊቀ ካህኑን ኢየሱስን የምልጃ አገልግሎት ማግኘት አልቻሉም፣
- የቀኑ ሰንበት ቦታውን ባለመልቀቁ በክርስቶስ ሰንበትነት(እረፍትነት) ማረፍ አልቻሉም፣

በዚህም አዲሱ ኪዳን ባለመቆሙ የክርስቶስ ቤዛነት ለህዝቡ እንዳይታይ ተደርጎ ይገኛል፣ መጨረሻውም የነፍስ ጥፋት ነው፡፡

## 4.3. ቅድስናቸው ሳይፈተሽ ከመፅሀፍ ቅዱሱ የተቀላሉት ተጨማሪ መፅሀፍት

መፅሃፍ ቅዱስ ማለት ቅዱሳን በእግዚአብሄር መንፈስ ምሪት የፃፉት መፅሃፍት ስብስብ ነው (ዘፀ.17፡14, ዘፀ.34፡27, ዘኍ.33፡2, ዘዳ.27፡8, ኢሳ.8፡1, ኢሳ.30፡8, ኤር.30፡2, ኤር.36፡1, ኤር.36፡2, ኤር.36፡28, ሕዝ.24፡2, ዕን.2፡2, ራዕ.1፡9, ራዕ.2፡1 …)፡፡

ሁሉም የክርስትና ተቋማት የጋራ 66 መፅሀፍት የያዘ መፅሃፍ ቅዱስ ያላቸው ሲሆን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ዘንድ በነዚህ 66ቱ መፅሃፍት ላይ ተጨማሪ መፅሃፍት ተጨምረው ይገኛሉ፣ እነዚህ መፅሃፍት በኦርቶዶክስ አዋልድ(የቀኖና ልጅ) ሲባሉ፣ በካቶሊክ ዲዩትሮካኖኒካል(ሁለተኛ ቀኖና) ሲባል፣ አፖክሪፋ በማለት የሚጠሩትም አሉ፡፡

ቤተክርስቲያንዋ እነዚህ ተጨማሪ መፅሀፍት/አዋልድ/ዲዩትሮካኖን በመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥ በመጨመር በአንድ መፅሀፍ ቅዱሱ ለማሳተሟ የተለያዩ ምክንያቶች ታቀርባለች፣ ዋነኞቹም፣

1. በሌሎቹ ቅዱሳን መፅሃፍት ውስጥ የማናገኛቸው ታሪኮች በነዚህ መፅሀፍት ውስጥ ስለምናገኝ መፅሀፍቱ በመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥ ቢጠቃለሉ “ዕውቀታችንን ሙሉ ያደርጋሉ” በሚል፣
2. ዮሐ.20፡30 “ኢየሱስ በዚህ መፅሃፍ ያልተፃፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ” ስለሚል ተጨማሪ መፅሀፍትን ብናስተናግድ ችግር የለውም በሚል፣
3. ይሁ.1፡14-15 “ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ፣ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፣ በሃጢያተኝነትም ስላደረጉት ስለ ሀጢያተኛ ስራቸው ሁሉ አመፀኞችም ሀጢያተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ሀጢያተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ፡፡”

   እንደሚለው የሄኖክ መፅሀፍ ለመጨመሩ ምክንያታዊ ነው በሚል፣
4. 2ጢሞ.3፡16-17 “የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበትን መፅሃፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር

ደግሞ ይጠቅማል፡፡" በሚለው ቃል መሠረት የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበትን መፅሀፍትን መጨመሩ ስህተት ስላልሆነ በሚል ነው፡፡

እነዚህን መስፈርቶችም ከተጨማሪ መፅሀፍቱ ጋር እያነፃፀርን በዝርዝር እንመለከታለን፣ ለንፅፅሩ የምንጠቀመው በቀደሙት የሀይማኖት አባቶች የተዘጋጀውን ተጨማሪ መፅሀፍቶችን የያዘውን የ1980 መፅሀፍ ቅዱስ ነው፣ ከሱ በኋላ አቡነ ጳውሎስ ያሳተሙት የ2,000 ህትመት ከታች እንደምንመለከተው የ66ቱን መፅሀፍት ኤዲት በማድረግ የመጨመር፣ የመቀነስ፣ ቃላት የመቀየርና የማደባለቅ ስራዎች ስለተሰሩበት መፅሀፉን በእግዚአብሄር ቃልነት መቀበል አዳጋች ስለሆነ ነው፡፡

ስለዚህ ለማነፃፀሪያነት ቤተክርስቲያንዋ ከአቡነ ጳውሎስ በፊት አሳትማ ስትጠቀምበት የነበረውን የቀደመውን የአበውን የ1980 መፅሀፍ ቅዱስ እንጠቀማለን፡፡

### 4.3.1. "ዕውቀታችንን ሙሉ ያደርጋሉ" መስፈርት

ቤተክርስቲያኗ ስለ ተጨማሪ መፅሀፍቱ መጨመር ትክክለኛነት የምታስረዳው "በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ሳይነገሩ የተዘለሉ ታሪኮች በነዚህ ተጨማሪ መፅሀፍት ላይ ስለምናገኛቸው ተጨማሪ መፅሀፍቱ ከ66ቱ ጋር አብረው መቅረባቸው ዕውቀታችንን ሙሉ ያደርግልናል" በሚል ምክንያት ነው፡፡

ነገር ግን ተጨማሪ መፅሀፍቱ የተፃፉበትን ምክንያት የጎደለ ነገር ኖሮ ያንን ሙሉ ለማድረግ ሳይሆን፡-

> ዕዝራ ሱቱኤል 13፡21-46 "አሪት ጠፍታለችና የሰራሃውን ስራ ትሰራው ዘንድ ያለህንም የሚያውቀው የለም፡፡ በፊትህስ ባለሟልነት ካገኘሁ መንፈስ ቅዱስን ላክልኝና ከጥንቱ ጀምሮ በዚህ አለም የሆነውን ሁሉ ልፃፍ … መለሰልኝም … በነዚያው በአርባ ቀኖች ሀያ አራት መፅሀፍት ተፃፉ፡፡"

በማለት ተጨማሪ መፅሀፍቱ ለምንና እንዴት እንደተፃፉ መናገሩ፣ ከላይ የቀረበውን መከራከሪያ ውድቅ ያደርጋል፣ ኦሪት አለመጥፋትዋና እስከዛሬም

ድረስ መኖሯ ደግሞ በዕዝራ ሱቱኤል ላይ የተነገረውን የተጨማሪ መፅሀፍት አስፈላጊነነትን መከራከሪያ ተመልሶ ውድቅ ያደርጋል፡፡

ከመሠረቱ ስንመለከትም ይህ "ዕውቀታችንን ሙሉ ያደርጉልናል" የሚለውና መፅሀፍ ቅዱሱን በጎዶሎነት የሚመለከት መንፈስ ክርስቲያናዊ አይደለም፣

> ዮሐ.20፡31 "ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንለችሁ ዘንድ ይህ ተፅፎአል፡፡"

የሚለውን የእግዚአብሄርን ቃል የማይቀበልና መፅሀፍ ቅዱሱን ጎዶሎ አድርጎ የሚመለከት ከክርስትና የጎደለ ሰው ብቻ ነው፡፡

### 4.3.2. በዮሐ.20፡30 መስፈርት

ዮሐ.20፡30 "ኢየሱስ በዚህ መፅሃፍ ያልተፃፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ" የሚለውን ቃል ምክንያት በማድረግ መፅሀፍቱን መጨመር "መፅሀፍ ቅዱሳዊ ነው" ይባል እንጂ፣ ተጨማሪ መፅሀፍቱ በዚህ መሠረት አልተጨመሩም ምክንያቱም ይህ ክፍል የሚናገረው ስለኢየሱስ ተአምራቶች ነው ነገር ግን ተጨማሪ መፅሀፍቱ የብሉይ ኪዳን ተጨማሪ መፅሀፍት መሆናቸው ነው የተነገረው፡፡

በተጨማሪም ያንኑ ቃል ቀጥለን ስናነብ ዮሐ.20፡31 "ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንለችሁ ዘንድ ይህ ተፅፎአል፡፡" ማለቱ ደግሞ የኢየሱስ ተአምራት ተብለው እንኳን ሌላ መፅሀፍት ተፅፈው ቢመጡ ተቀባይነት እንዳይሰጣቸው ይመክረናል፡፡

ይህም ቃል ዛሬ በሐዋርያት ስም "የጴጥሮስ ወንጌል፣ የያዕቆብ ወንጌል፣ የበርናባስ ወንጌል ..." እየተባሉ እየተዘጋጁ ያሉት መፅሀፍት እንኳን የሚስተናገዱበት መንገድ አለመኖሩን ያሳየናል፡፡

### 4.3.3. በይሁ.1፡14-15 መሰፈርት

ይሁ.1፡14-15 “ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ፣ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፣ በሃጢያተኝነትም ስላደረጉት ስለ ሀጢያተኛ ስራቸው ሁሉ አመፀኞችም ሀጢያተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ሀጢያተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ፡፡”

በዚህም ቤተክርስቲያንዋ ተጨማሪ መፅሀፍቱ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አላቸው ትላለች ነገር ግን ይህንን ቃል እንደ መከራከሪያነት ማቅረብ የሚቻለው ከ15ቱ ተጨማሪ መፅሃፍት ውስጥ ለሄኖክ መፅሃፍ እንጂ ለሌሎቹ ተጨማሪ መፅሀፍት መሆን አይችልም፡፡

“መፅሀፈ ሄኖክ” ተብሎ የተጨመረውን መፅሀፍ ስንመለከት፣ መፅሀፉ እንደሚናገረው፣ ይህን መፅሃፍ የፃፈው የአዳም ሰባተኛ ልጅ፣ የያሬድ ልጅ (ሄኖክ 9፡1)፣ የማቱሳላ አባት (ሄኖክ 42፡1) በሆነውና ወደ ሰማይ በተነጠቀው(ሄኖክ 4፡1) ሄኖክ መሆኑን ይናገራል፡፡ ሄኖክም ዕውቀቱን ያገኘው መላዕክት ባሳዩት ራዕይ መሆኑን በመፅሃፉ መጀመሪያ ሄኖክ 1፡2 እና መጨረሻ ሄኖክ 42፡16 ላይ ተገልጿል፡፡ ሄኖክም ያየውን ራዕይም ለሰዎች ያስተማረው በማቱሳላ ዘመን መሆኑን(ሄኖክ 34፡35-37)፣ የሚገለጠውም በእግዚአብሄር (ሄኖክ 4፡66-69, ሄኖክ 5፡4 …) እና በመላዕክት(ሄኖክ 4፡5-7, ሄኖክ 27፡15-18) ሀይል መሆኑን ይገልፃል፡፡

ነገር ግን መፅሀፉን በዝርዝር ስንመለከተው በውስጡ ብዙ ችግሮችን እንመለከታለን፣ የመፅሀፉ መቼት ይፋለሳል እንዲሁም ከ66ቱ መፅሀፍት በተለየ ቅድስና የሌለውና በውስጡ ብዙ ውሸቶችን የያዘ መፅሀፍ ነው፣ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፣

#### 4.3.3.1. የመፅሃፉ መቼት የተፋለሰ ነው

መፅሀፈ ሄኖክ የብሉይ ኪዳን መፅሀፍ እንደሆነ ተደርጎ በብሉይ ኪዳን መፅሀፍትነቱ ቢቀርብም፣ መፅሀፉ ግን እስከ ሐሳዊ መሲህ(ሐሰተኛው ክርስቶስ) ድረስ ያለውን የመፅሃፍ ቅዱሱን ታሪክ ቀንጨብ ቀንጨብ አድርጎ የያዘ መፅሀፍ ነው(ለምሳሌ ሄኖክ ምዕራፍ 32 እስከ ሄኖክ 34፡29)፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መፅሀፉ የተፃፈው በአዲስ ኪዳን ዕውቀት እንጂ በብሉይ ኪዳን መንፈስ አለመሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ፣ በመፅሀፉ ውስጥ የአዲስ ኪዳን ቃላትን ቃል በቃል እንመለከታለን፣ ለምሳሌ፣

- ኢየሱስ
  - ክርስቶስ - ሄኖክ 13፡4
  - የአብ የባህሪ ልጅ - ሄኖክ 13፡17
  - ቀዳማዊ ቃል - ሄኖክ 17፡11
  - አስታራቂ - ሄኖክ 13፡22, ሄኖክ 13፡19፣ ሄኖክ 13፡31
  - ፈራጅ - ሄኖክ 13፡22
- አብ - ሄኖክ 13፡17
- መንግስተ ሠማያት - ሄኖክ 4፡6, ሄኖክ 13፡34
- ሐዋርያት - ሄኖክ 20፡25
- ሐዋርያው ዮሐንስ፡- ሄኖክ 33፡42

መፅሀፈ ሄኖክ ሙሉውን መፅሀፍ ቅዱስ ቀንጨብ ቀንጨብ አድርጎ መያዙ፣ የአዲስ ኪዳን ቃላትን ቃል በቃል መያዙና ሄኖክ የአበውን መፅሃፍ ሲያነብ ነበረ(ሄኖክ 29፡3) መባሉ፣ መፅሃፉ የተፃፈው በራዕይ ሳይሆን መፅሃፍ ቅዱሱን በማንበብ መሆኑና የሄኖክን መፅሀፍ የፃፈው የአዲስ ኪዳን ሰው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ይባሱኑ ደግሞ መፅሃፍ ቅዱስ ላይ ያልተፃፈውና በ234 ዓ.ም በኒቂያ ጉባኤ የተፈጠረውን "ስላሴ" የሚለውን ቃል መያዙ (ሄኖክ 13፡18-29) የሄኖክ መፅሀፍ የተፃፈው የአዲስ ኪዳን መፅሀፍት ተፅፈው ካለቁ በኋላ ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ የተፃፈ መፅሀፍ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህም መፅሀፈ ሄኖክ ስለራሱ የሚናገረውና በውስጡ የቀረቡት እውነታዎች ይፋለሳሉ፡፡

### 4.3.3.2. ከ66ቱ መፅሀፍት በተለየ ቅድስና የሌለውና በውስጡም ውሸቶችን የያዘ መፅሀፍ ነው

ቅድስናና ውሸት ተቃራኒ አሰራሮች ናቸው፣ ውሸት ከውሸት አባት ነው፣ ቅዱስ ቃላት ደግሞ ከቅዱሱ ነው፣ በዚህ የሄኖክ መፅሀፍን ማንነት ስንመለከት መፅሀፉ ቅድስና የራቀው የውሸት አባት ቃል ሆኖ እንመለከታን፣

- o "የፀሃይ መግቢያና መውጪያ ስድስት ስድስት መስኮቶች በሰማይ ላይ መኖራቸው"

  ሄኖክ 21፡5-6 "የበራ የፀሃይ መውጫ በምስራቅ ባሉ በሰማይ መስኮቶች ነው፣ መግቢያውም በምዕራብ ባሉ በሰማይ መስኮቶች ነው፡፡ ፀሃይ የሚወጣበት ስድስት መስኮቶች አየሁ ፀሃይም የሚገባበት ቦታ ስድስት መስኮቶችንም አየሁ፡፡"

  እውነታው ግን ፀሀይ መሬትን መዞርዋ እንጂ መግቢያና መውጫ መስኮት የላትም፣ ከሁሉ የሚያስቀው "የበራ" የሚለው ነው፣ ማብርያ ማጥፍያው ተነክቶ ያልበራው ፀሀይ ምን ይመስል ይሆን?

- o "ለድርቅ ምክንያት የሆነው የፀሃይ መስኮት መኖሩ"

  ሄኖክ 24፡9-10 "ዑርኤል በሰማይ ያለ ፀሃይ በሚመላለስባቸው በሰረገላዎች ዙሪያ የፀሃይ እግሮች ከነሱ የሚወጡባቸው የተከፈቱ አስራ ሁለት መስኮቶች እንዲህ አሳየኝ፡፡ በታወቁባቸው ዘመኖች በተከፈቱ ጊዜ ከነሳቸው በዚህ አለም ድርቅ ይወጣል፡፡"

- o "ፀሃይ የምትጓዘው በሰረገላ ላይ ሆና ነው"
  - ሄኖክ 21፡11-12 "ወደ ሚሄድባቸው ሰረገላዎች በወጣ ጊዜ ሰረገላዎችን የሚነዳ ነፋስ ይነፍሳል፡፡ ፀሀይም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ይገባል፡፡ ወደ ምስራቅም ለመሄድ ከምዕራብ ወደ መስዕ ይመለሳል ወደዚህም መስኮት ሊገባ ይመራል፡፡"
  - ሄኖክ 21፡55 "እንዲህ ሆኖ ይወጣል ይገባል መጉደልም የለበት በሰረገላ ሆኖ በመአልትም በለሊትም ይሮጣል እንጂ አያርፍም፡፡"

- o "ጨረቃም የፀሃይን መስኮቶች ለመግቢያና ለመውጫ መጠቀምዋ"

  ሄኖክ 21፡7 "ጨረቃም በነዚያ(በፀሃይ) መስኮቶች ይወጣል ይገባል፡፡"

- o "ኮከቦችም በዚያው በፀሃይና ጨረቃ በሚጠቀሙበት መስኮት ይገባሉ ይወጣሉ"

ሄኖክ 21፡8 "ከሰማይ ኮከቦችን የሚመሩ ኮከቦችም ከሚመራቸው ኮከቦች ጋራ በነዚያ ደጃፎች ይወጣሉ ይገባሉ፣ እኒህም መስኮቶች ስድስቱ በምስራቅ ስድስቱ ፀሃይ በሚገባበት በምዕራብ ናቸው፡፡"

- "የኮከቦችም ሰረገላ መኖሩ"

  ሄኖክ 24፡14 "የማይገቡ ኮከቦች በሚመላለሱባቸው በነዚያ መስኮቶች በበታቻቸውና በበላያቸው ሰረገላዎች ለዘላለሙ በሰማይ ሲሮጡ አየሁ፡፡"
- "ጨረቃና ፀሃይ እኩል መጠን አላቸው"

  ሄኖክ 21፡57 እና ሄኖክ 26፡3 "የሁለቱ ሁሉ የፀሃይና የጨረቃ መጠናቸው የተካከለ ነው፡፡"
- "የጨረቃ ሰረገላ የሚጓዘው በንፋስ ነው"

  ሄኖክ 22፡2 "(ጨረቃ)ክብነቱ እንደ ሰማይ ክብ ነው፣ በሚቀመጥበት በሰረገላው ነፋስ ይነፍሳል፡፡"
- "መብረቅና ነጎድጓድ የሚሄደው በንፋስ ነው"

  ሄኖክ 16፡21-23 "መብረቅና ነጎድጋድ አይለያዩም አንዱም አንዱም ሁለቱ ሁሉ በነፋስ ይሄዳሉ ... በመጡበት ጊዜ ቦታቸው ባሸዋና በድኝ መካከል ነውና መልአኩ በመካከላቸው አስተካክሎ ይከፍላል..."
- "ለነፋስ መውጫና መግቢያም አስራ ሁለት መስኮቶች አሉት"

  ሄኖክ 24፡1-11 "ነፋሶች ሁሉ መውጫ መግቢያ የሚሆኑ ነፋሶች ከነሱ የሚወጡበቸው የተከፈቱ አስራ ሁለት መስኮቶች በምድር ዳርቻ አየሁ፡፡ በዚህም ዓለም ይነፍሳሉ ... ሶስቱ በምስራቅ ሶስቱ ... በአዜብ በምትቀርበዋ የንፋስ መስኮት መልካም ዝናብ ይመጣል ... ለምስራቅ በምትቀርብ በመጀመሪያይቱ መስኮት የድርቅ ነፋስ ይወጣል ..."

  ሄኖክ 16፡35 "ዝናሙን የሚያመጣው ነፋስ ከቦታው በተናወጠ ጊዜ መላዕክት ይመጣሉ ቦታውንም ከፍተው ያወጡታል፡፡"

ይህ የጋርዮሽ ሰዎች የሚያስቡበት "የተዘረጋች ምድር፣ እንደ ጣርያ የተዘረጋ ሰማይ" በሚለው አስተምህሮ ምክንያት የመጣ ስህተት ሲሆን፣ መሀመድም በተመሳሳይ መንገድ መሳሳቱን በምዕራፍ 2 ተመልክተናል፡፡

በዚህም መፅሀፈ ሄኖክ ተብሎ የገባው መፅሀፍ መቼቱ የተዛባና ቅድስና የጎደለው በውሸት አባት የተፃፈ ከ66ቱ ቅዱሳት መፅሀፍት ጋር አብሮ መታተም የሌለበት መፅሀፍ ነው፡፡

ይህ እውነታ ለሌላውም ጊዜ ትምህርት ሊሆን ይገባል፣ አንድ መፅሀፍ ተመሳሳይ ስም ይዞ ስለመጣ ብቻ መሸወድ አይገባም፤ በመፅሀፍ ቅዱሱ ማሰባሰብ ወቅት እንደዚሁ እንደ ሄኖክ መፅሀፍ አባቶች ስማቸውን የጠቀሱላቸው ነገር ግን ትክክለኛውን ኮፒ ስላላገኙላቸው በመፅሀፍ ቅዱሱ ሳያጠቃልሏቸው የተዋቸው ብዙ ቅዱሳን መፅሃፍት እንዳሉ ማወቅ ያስፈልጋል፣ “የጦርነት መፅሀፍ”(ዘኁ.21፡14)፣ “የያሻር መፅሃፍ”(2ሳሙ.1፡18)፣ “የሰለሞን ታሪክ መፅሃፍ”(1ነገ.11፡41)፣ “የእስራኤል ነገስታት ታሪክ መፅሃፍ”(1ነገ.14፡19, 1ነገ.15፡32, 1ነገ.16፡14, 1ነገ.16፡20, 1ነገ.16፡27)፣ “የይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሀፍ”(1ነገ.15፡23, 2ነገ.15፡6)፣ “የሳሙኤል፣ የናታን የጋድ ታሪክ መፅሃፍት”(1ዜና.29፡29)፤ ነገር ግን ዛሬ ማንም ሰው ተነስቶ በነዚህ መፅሃፍት ርዕስ መፅሃፍ ቅዱሱን አመሳስሎ መፅሃፍ አዘጋጅቶ ቢያመጣ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

### 4.3.4. <u>በ2ጢሞ.3፡16-17 መስፈርት</u>

ተጨማሪ መፅሀፍቱ ከ66ቱ መፅሀፍት ጋር አብረው ለመታተማቸው የሚቀርበው ሌላው ቃል 2ጢሞ.3፡16-17 “የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበትን መፅሃፍ <u>ሁሉ</u> ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡” የሚለው ነው፡፡

ነገር ግን ተጨማሪ መፅሀፍቱ በእግዚአብሄር መንፈስ ምሪት መፃፍ አለመፃፋቸውን ከመረመርን ነገሩ ሌላ ነው፣ ይህም፣

- መፅሀፍቱ “እስራኤል የማታውቀው “የብሉይ ኪዳን” መፅሀፍት መሆናቸው፣
- የመፅሀፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ አብያተ ክርስቲያናቱና ጳጳሳቱ እንደፈለጉት “ማስተካከላቸው”፣
- የመፅሀፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚመሰክር መልኩ በመፅሃፍ ቅዱሱ ውስጥ ትክክለኛ ቦታ አጥተው መቸገራቸው፣
- የመፅሀፍቱ መቼት መምታታቱ፣
- ተረቶችና ግራ የተጋቡ ትምህርቶችን እንደ ፈጣሪ ቃል መያዛቸው፣
- እርስ በራስ እንዲሁም ከ66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ጋር መጋጨታቸው፣
- ሰይጣናዊ አሻራዎች የሚታዩበት መሆኑ፣

መፅሀፍቱ ቅድስና የራቃቸው መፅሀፍት መሆናቸውን ያሳያል፣ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 4.3.4.1. <u>እስራኤል የማታውቀው ብሉይ ኪዳን መሆኑ</u>

ብሉይ ኪዳን የወረደው ለእስራኤል ነው(ሮሜ.9፥4, ዘፀ.34፥27 ...)፣ አዲሱ ኪዳን ደግሞ ለዓለም(ማቴ.24፥14, ዮሐ.3፥16 ...)፣ ቤተክርስቲያኗ ተጨማሪ መፅሀፍቱን "የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት ናቸው" በማለት በ39ኙ የብሉይ ኪዳናት መፅሀፍት መካከል ብታስቀምጣቸውም የብሉይ ኪዳን ባለኪዳኖቹ እስራኤላውያኑ እነዚህን መፅሀፍት አያውቋቸውም።

[84] "አይሁዳውያን በ90 ዓ.ም በጀምኒያ ጉባኤ ባስተላለፉት ውሳኔ ተቀባይነት ያላቸው የብሉይ ኪዳን መጻህፍት 39 መሆናቸውን አሳውቀዋል።" [85] በዘመናዊው ሳይንስም "የዕብራውያን መፅሀፍት" የሚባሉት እነዚህ [86]በሂብሩ "ታናክ(Tanakh)"፣ በክርስትናው "ብሉይ ኪዳን" የሚባሉት 39ኙ መፅሀፍት ናቸው።

በዚህም <u>የብሉይ ኪዳኑ ባለቤቶች፣ እስራኤሎች ከ39ኙ መፅሀፍት ውጪ ያሉትን መፅሀፍት አያውቋቸውም፣ እስራኤል የማታውቃቸው መፅሀፍት ደግሞ የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት መሆን አይችሉም</u>።

መፅሀፍቱ ላይ ያሉትን ታሪኮችንም ስንመለከት አብዛኞቻቸው ከባለኪዳኗ እስራኤል ጋር አይገናኙም፣ የግሪክ፣ የኢትዮጵያና የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ዕሴቶች ይባሱኑም ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ መፃፋቸውን የሚያሳዩ አሻራዎች ይታዩባቸዋል፣ ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን፡-

- ብሉይ ኪዳን ያልተገባላት ግሪክ የፃፈችው መሆኑ፣

    [87]ብሉይ ኪዳን ለመጀመርያ ጊዜ የተፃፈው በዋናነት በሂብሩ ቋንቋ ሲሆን የተወሰኑ የዳንኤልና የዕዝራ መፅሀፍት ደግሞ በአርማይክ ቋንቋ ተፅፏል። ብሉይ ኪዳን የወረደው ለእስራኤል በመሆኑ መፅሃፉን የፃፉት ለራሳቸው በራሳቸው ቋንቋ ነው፣ በአርማይክ ቋንቋ እንኳን የተፃፉት ጥቂት የብሉይ ኪዳን ምዕራፎች እንኳን

[84] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሄር ቃል ሲመዘን**፣ ገፅ 16
[85] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Biblical languages
[86] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Hebrew Bible
[87] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Biblical languages

በዚህ ቋንቋ ሊፅፉ የቻሉት እስራኤላውያኑ ከስደት በኋላ ሲሰባሰቡ በወቅቱ በብዛት ይነገር የነበረው የአርማይክ ቋንቋ ስለነበረ ነው፣

[88]ኢየሱስም በምድር ላይ በነበረበት ወቅት በዋናነት የሚናገረው ይኸው የአርማይክ ቋንቋ ነበረ፡፡

ነገር ግን አብዛኞቹ የእነዚህ የብሉይ ኪዳን ተጨማሪ መፅሃፍት ምንጭም [89]ግሪክ ናት፣ እስራኤል የማታውቀው የብሉይ ኪዳን ያልተገባላት ግሪክ ያዘጋጀችው የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት፡፡

- ኢትዮጵያዊ አሻራዎች፣ ለምሳሌ፣

 ሲራክ 4፡6 "... እንደ አባይ ያለውን ውሃ በሃምሌ በነሃሴ እሻገራለሁ አትበል፡፡"

ይህ ኢትዮጵያዊ አፃፃፍ ነው፣ በባለ ኪዳንዋ እስራኤል ተፅፎ ቢሆን ኖሮ "የዮርዳኖስን፣ የኤፍራጠስን፣ የጢግሮስን ... ወንዝ በአዳር ወይ በኒሳን ወር አትሻገር" ባለ ነበረ፣ ምክንያቱም መፅሀፍ ቅዱሱ የእስራኤልን የወራት ስያሜ አልተረጎመም፡፡

ይባሱኑ ደግሞ በሄኖክ 21-27 የሃገራችን ካሌንደር በዝርዝር ተገልጿል፣ አለም የማታውቀው የጳጉሜ ወር እንኳን ሳትቀር መነገሩ የመፅሀፉን ኢትዮጵያዊነትን ያሳብቅበታል፣ ብሉይ ኪዳን ያልተገባላት ኢትዮጵያ የፃፈችው እስራኤል የማታውቀው የብሉይ ኪዳን መፅሃፍ፡፡

- ብሉይ ኪዳን የማያውቃቸው የካቶሊክ/ኦርቶዶክስ እሴቶች፣

 - ስርአቶች - ተዝካር(ሲራክ 7፡33)፣ የቅዳሴ ስነስርአት(ሄኖክ 4፡5)፣
 - አገልጋዮች - ባሕታዊ(ሲራክ 11፡5)፣ ደብተራ(ሄኖክ 32፡70)፣
 - ቦታዎች-ደብር(1ኛመቃብያን 19፡1-12,ሄኖክ 2፡2)፣ገዳም(ሲራክ 2፡1)
 - መላዕክት-ሩፋኤል(ጦቢት12፡15,ሄኖክ31፡7)፣ ዑራኤል(ሄኖክ 5፡37)

[88] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Language of Jesus
[89] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Deuterocanonical Books

እነዚህ በ39ኙ የብሉይ መፅሀፍት የማናገኛቸው የካቶሊክ/ኦርቶዶክስ ዕሴቶችን በተጨማሪ መፅሀፍቱ ውስጥ ስንመለከት፣ የመፅሀፍቱ ምንጭ የካቶሊክ/ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንጂ ከእስራኤል ጋር የማይገናኝ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- መፅሀፍቱ በመፅሀፍ ቅዱሱ አንድም ቦታ ላይ ያልተጠቀሰውና በኒቂያ ጉባኤ የተፈጠረውን "ስላሴ" የሚለውን ቃል (ዕዝራ ሱቱኤል 4፡5, ሄኖክ 13፡18-29 …) መያዛቸው፣ መፅሀፍቱ የተፃፉት በብሉይ ኪዳን ዘመን ወይ የአዲስ ኪዳን መፅሀፍት በተፃፉበት ዘመን ሳይሆን ከ234 ዓ.ም ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ መሆኑን ያሳያል፡፡
- መፅሀፍቱ የተፃፉት የመፅሀፍ ቴክኖሎጂ ከመጣ በኋላ በጥቅልል ወረቀቶች/ብራናዎች ሲፃፍ የነበረው በመፅሀፍ መልክ ሲሰባሰቡ 39ኙ መፅሀፍት በአንድ ላይ "የብሉይ ኪዳን" 27ቱ መፅሀፍት ደግሞ "የአዲስ ኪዳን" መፅሀፍት ተብሎ ከተሰየሙ በኋላ የተፃፉ መሆኑን የሚያሳዩ ክፍሎች አሉ፣ ይህንንም የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች አጠራር ዕዝራ ሱቱኤል 4፡20 ላይ "ብሉያትና ሀዲሳት" ሲል እንመለከታለን፡፡

በዚህም ብሉይ ኪዳን የወረደላት እስራኤል የማታውቃቸው እነዚህ የብሉይ ኪዳን መፅሃፍት ምንጭ ከግሪክ፣ ከኢትዮጵያና ከካቶሊክ/ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት መሆኑን፣ የተፃፉትም ከኒቂያ ጉባኤና የመፅሀፍ ቴክኖሎጂ ከመጣ በኋላ መሆኑን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል፣ በዚህም መፅሀፍቱ ለእስራኤል የወረደው የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት አይደሉም፣ በዚህም ተጨማሪ መፅሀፍቱን ከብሉይ ኪዳኑ መፅሃፍት ዝርዝር ውስጥ ማስገባቱ ስህተት ነው፡፡

### 4.3.4.2. <u>የመፅሀፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ አብያተ ክርስቲያናቱና ጳጳሳቱ እንደፈለጉት "ማስተካከላቸው"</u>

መፅሃፍ ቅዱስ ፈጣሪ ለሰው ልጆች መመሪያ አድርጎ ያወረደው መፅሀፍ በመሆኑ ቋሚነት ሊኖረው ይገባል፣ በዚህም 66ቱ መፅሀፍት የፈጣሪ ቃልነታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ በትውልድና በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ሳይዛነፉ በቋሚነት ይገኛሉ ነገር ግን በነዚህ 66ቱ መፅሀፍት ላይ የተጨመሩት ተጨማሪ መፅሀፍቱ በትውልድ፣ በአብያተ ክርስቲያናቱና በጳጳሳቱ ሲቀያየሩ እንለከታለን፡፡

ኦርቶዶክስ የምትለው እና ካቶሊክ የምትለው የተጨማሪ መፅሀፍት ብዛት የተለያየ ነው ይባሱኑ ደግሞ [90] "በኦርቶዶክሱ ውስጥም አንድነት የለም የኢትዮጵያው፣ የግብፁ፣ የሶሪያው፣ የህንዱ፣ የአርመኑ፣ የሩሲያውና የግሪኩ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት የተለያዩ ቁጥር ያቀርባሉ፡፡ በአለም ላይ ካሉት የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ብዙ መፅሃፍት አሰብስባ የያዘችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስትሆን ቤተክርስቲያኗ 15 ተጨማሪ መፅሀፍትን ይዛለች፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ "የመፅሃፍቱ ምንጭ ናት" ከምትባለው ከግሪክ ኦርቶዶክስ እንኳን ትበልጣለች፡፡"

ከብዛታቸው በተጨማሪም በይዘታቸውም በቤተክርስቲያናቱ መካከል ሰፊ ልዩነት እንመለከታለን፣ ለምሳሌ የመቃብያንን መፅሀፍ ስንመለከት [91] "መቃብያን የሚባሉ ስምንት መፅሀፍት አሉ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የሚታወቁ 4 ሲሆኑ በግሪክ ኦርቶዶክስ የሚታወቁትም አራት ናቸው፣ የሚያሳዝነው ደግሞ እነዚህ የኢትዮጵያና የግሪክ የመቃብያን መፅሃፍት በስም እንጂ በይዘት አይገናኙም፣ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው ሁለቱን የግሪክ መቃብያን መፅሃፍት ብቻ ነው፡፡"

---

[90] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሄር ቃል ሲመዘን**፣ ገፅ 15
[91] የኢትዮጵያ መፅሃፍ ቅዱስማህበር(2008)፣**የመፅሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት**፣ገፅ 36-37

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሱ ጋርም ስንመጣ ተጨማሪ መፅሃፍት ብዛትና አይነት በየተሿሚ ጳጳሳቱና በምሁራኖቹ የተለያዩ ናቸው፣ ምሁራኖቿ [92]"የተለያየ የተጨማሪ መፅሀፍት ብዛት ያስቀምጣሉ"፣ እነዚህን በግለሰብ ደረጃ የተሰጡትን መመሪያዎች ትተን በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የታተሙትን እንኳን ብንመለከት ብዙ ልዩነቶችን እንመለከታለን፣

| ተቁ | የተጨማሪ መፅሀፍቱ ዝርዝር | የተለያዩ የተጨማሪ መፅሀፍት ብዛት የሚናገሩ መፅሀፍት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | [93] ፍትሀ ነገስት | [94]1953 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስ | [95]የቤተክርስቲያንዋ ስርአተ አምልኮት መጽሐፍ | የ1980 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስ | የ2000 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስ |
| 1 | መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል | √ | √ | √ | √ | √ |
| 2 | መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ | √ | √ | √ | √ | √ |
| 3 | መጽሐፈ ጦቢት | √ | √ | √ | √ | √ |
| 4 | መጽሐፈ ዮዲት | √ | √ | √ | √ | √ |
| 5 | መጽሐፈ አስቴር | √ | - | - | √ | √ |
| 6 | 1ኛ መቃብያን | √ | √ | √ | √ | √ |
| 7 | 2ኛ መቃብያን | - | √ | √ | √ | √ |
| 8 | 3ኛ መቃብያን | - | √ | √ | √ | √ |
| 9 | መጽሐፈ ሲራክ | √ | √ | √ | √ | √ |
| 10 | ጸሎተ ምናሴ | - | - | √ | √ | - |
| 11 | ተረፈ ኤርምያስ | - | - | √ | √ | √ |
| 12 | መጽሐፈ ሶስና | - | - | √ | √ | - |
| 13 | መጽሐፈ ባሮክ | - | √ | - | √ | √ |

[92] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሄር ቃል ሲመዘን**፣ ገፅ 29-30
[93] ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ...(1990) **ፍትሀ ነገስት ንባቡና ትርጓሜው**፣
[94] መምህር ያሬድ ሽፈራው (2009) **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክዊ አመጣጥ**፣ ገፅ 98
[95] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሄር ቃል ሲመዘን**፣ ገፅ 29-30

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | መጽሐፈ ጥበብ | √ | √ | - | √ | √ |
| 15 | መዝሙረ ሰለስቱ ደቂቅ | - | - | √ | √ | - |
| 16 | ተረፈ ዳንኤል | - | - | √ | √ | - |
| 17 | መጽሐፈ ኩፋሌ | - | √ | √ | √ | √ |
| 18 | መጽሐፈ ሄኖክ | - | √ | √ | √ | √ |
| 19 | መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን | √ | - | √ | - | - |
| 20 | መጽሐፈ ተግሳጽ | - | - | √ | | √ |
| 21 | ተረፈ ባሮክ | - | - | - | | √ |
| 22 | የአባጎር ጥበብ | √ | - | - | - | - |
| **ተጨማሪ መፅሀፍቱ ብዛት** | | **11** | **12** | **16** | **18** | **16** |
| **ከአዲስ ኪዳን መፅሀፍት ጋር ሲደመሩ ያላቸው ብዛት** | | **77** | **78** | **82** | **84** | **81** |

*<u>የግርጌ ማስታወሻ</u>*

1. *“የቤተክርስቲያንዋ ስርአተ አምልኮ” እና “የ2000 ዓ.ም ዕትም” ላይ የተጨማሪዎቹ መፅሀፍት ብዛት እኩል እኩል 16 መፅሀፍት ቢሆኑም፣ አጠቃላይ ድምራቸው ግን የተለያየ ነው ምክንያቱ ደግሞ የ2,000 ዓ.ም ዕትም ላይ ዋናው የቀኖናው “መፅሀፈ አስቴር” ሙሉ በሙሉ ስለወጣ ነው፡፡*

2. *ፍትህ ነገስቱ የሚዘረዝረው የመፅሀፍቱን ስም ብቻ በመሆኑ በተጨማሪ ደግሞ የስም አጠራሩ ከሌሎቹ ለየት ስለሚል፣ ከአንዳንድ አመላካች ነገሮች በመነሳት ከአዲሱ አጠራር ጋር ለማዛመድ ተሞክሯል፣ በዚህም “የሰለሞን ጥበብ” የሚለው በአዲሱ አጠራር “የጥበብ መፅሀፍ” እንዲሁም “የሲራክ ልጅ የኢያሱ ጥበብ” የሚለው “መፅሀፈ ሲራክ” በሚለው ስር ተቆጥረዋል፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ የመፅሀፍቱ ብዛት ልዩነት የባሰ ይሰፋል፡፡*

የሚገርመው ደግሞ ማሻሻያዎች ሲደረጉ በየመግቢያዎቻቸው ላይ እንደሚታየው ጳጳሳቱ የአንድ ቤተክርስቲያን አባላት እንዳልሆኑ ሁሉ፣ ሁሉም ያሻሻሉት የቀደሙትን በመተቸት ነው፣ እውነታው ግን በቋንቋ ችሎታቸው፣ በቅድስና ሆነ በመፅሀፍ ቅዱስ እውቀታቸው የቀደሙት አባቶች ተተኪዎቹን ይበልጣሉ፡፡

ከሁሉ በተለየ በመፅሃፍ ቅዱስ ህትመት ታሪክ ትልቁን የድፍረት ስራ የሰሩት አቡነ ጳውሎስ ናቸው፣ አቡኑ በ2,000 ዓ.ም ባሳተሙት መፅሃፍ ቅዱሳቸው፣ “በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አትጨምር፣ አትቀንስ”(ራዕ.22፡18-19, ዘዳ.4፡2, ዘዳ.12፡32 …) የሚለውን ህግ በመጣስ በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ጨምረዋል፣ ቀንሰዋል፣ አደባልቀዋል፣ የትርጉም ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ቃላቶችን ቀያይረዋል፣ ይህ ደግሞ በእግዚአብሄር ቃል ላይ የተሰራ ትልቅ ድፍረት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

1. **<u>መጨመር</u>**

- በ1980 የታተመው መፅሀፈ ባሮክ 5 ምዕራፎችና 83 ቁጥሮች ሲኖሩት በ2,000ዓ.ም በታተመው ደግሞ የሚጨመረው ተጨምሮ 5 ምዕራፎችና 141 ቁጥሮች ይዞ፣ በአጠቃለይ 58 ተጨማሪ ጥቅሶች ተጨምረውበት መጥቷል፡፡
- በ1980 በታተመው መፅሀፍ ቅዱስ፣ መፅሀፈ ጦቢት ላይ ለመግቢያ ተብሎ በሰዎች የተቀመጠው የመግብያ ሀሳብ፣ በ2,000 ዕትም ላይ “የፈጣሪ ቃል” በማድረግ ከምዕራፍ አንድ ጋር በመቀላቀል ቁጥር ሰጥተውታል፣ በዚህም በእነዚህ ሁለቱ መፅሀፍ ቅዱሳት መካከል የሶስት ቁጥሮች መዛነፍ ተፈጥሯል፡፡

2. **<u>መቀነስ</u>**

ዋናው የ66ቱ “መፅሃፈ አስቴር” ሙሉ በሙሉ ከ10 ምዕራፎቹና ከ167 ጥቅሶቹ ጋር ከ2,000 ዓ.ም መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ተሰርዟል፡፡

3. **<u>ማደባለቅ</u>**

በቀደሙት መፅሀፍ ቅዱሳት ዋናው 66ቱ መፅሀፍትና ተጨማሪ የአዋልድ/ዲዮትሮካኖኒካል መፅሃፍት የሚቀመጡት በተለያየ ክፍል ነበረ ነገር ግን በአቡነ ጳውሎሱ መፅሀፍ ቅዱስ ተቀላቅሎ ታትሟል፣ ይህ የማደባለቅ ስራም ከዚህ ባለፈ መፅሀፍቱ ውስጥ እስከ መነካካት የደረሰ ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

| ተቁ | የመፅሀፉ ስም | በ1980 ዕትም | በ2000 ዕትም |
|---|---|---|---|
| 1 | ፀሎተ ምናሴ | ራሱን የቻለ መፅሀፍ | ከ2ዜና.33፡13 በኋላ ገብቷል |
| 2 | መፅሀፈ ሶስና | ራሱን የቻለ መፅሀፍ | ትንቢተ ዳንኤል 13ኛ ምዕራፍ ሆኗል |
| 3 | ተረፈ ዳንኤል | ራሱን የቻለ መፅሀፍ | ትንቢተ ዳንኤል 14ኛ ምዕራፍ ሆኗል |
| 4 | መዝሙረ ሰለስቱ ደቂቅ | ራሱን የቻለ መፅሀፍ | ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 3 ውስጥ ገብቷል |
| 5 | ተረፈ ኤርምያስ | ራሱን የቻለ መፅሀፍ | ተረፈ ኤርምያስ ምዕራፍ 6 ተረፈ ኤርምያስ ምዕራፍ 1 ሲደረግ፣ የቀሩት 5 ምዕራፎች ተረፈ ባሮክ ተብለዋል |

## 2. <u>ትርጉም በሚያዛንፍ መልኩ ቃላት መቀየር</u>

- **<u>ከዋናው 66ቱ መፅሀፍት</u>**

| ተቁ | ጥቅስ | የ1980 እትም | የ2000 እትም |
|---|---|---|---|
| 1 | መዝ.88፡3 | <u>ከመረጥሁት</u> ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፣ ለባሪያዬ ለዳዊት ማልሁ፡፡ | <u>ከመረጥኋቸው</u> ጋር ቃልኪዳን አደረግሁ፣ ለባሪያዬ ለዳዊት ማልሁ፡፡ |
| 2 | ኢሳ.53፡10 | እግዚአብሄርም <u>በደዌ ያደቅቀው</u> ዘንድ ፈቀደ፡፡ | እግዚአብሄር <u>ከግርፋቱ ያነፃው</u> ዘንድ ፈቀደ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | ኢሳ.53፡12 | ስለዚህ እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፣ ከሀያላን ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ ከአመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ሀጢያት ተሸከመ፣ ስለ አመፀኞችም ማለደ፡፡ | ስለዚህ እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤ ከሀያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ሀጢያት ተሸከመ፤ ስለ ሀጢያታችንም ተሰጠ፡፡" |
| 4 | ኢሳ.59፡15-16 | ወደ እሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ፣ ተደነቀም | የሚረዳም ሰው እንደሌለ ተረዳ |
| 5 | ማቴ.5፡6 | ፅድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁአን ናቸው፣ ይጠግባሉና፡፡ | ስለ ፅድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁአን ናቸው፤ እነርሱ ይጠግባሉና |
| 6 | ሮሜ.8፡33-34 | ...የሚያፀድቅ እግዚአብሄር ነው፣ የሚኮንንስ ማነው፣ ሞተው ይልቁንምከሙታን የተነሳው፣በእግዚአብሄር ቀኝ ያለው፣ ደግሞም ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡ | የሚፈርድስ ማነው፣ የሞተው፣ ይልቁንም ከሙታን ተለይቶ የተነሳው፣ በእግዚአብሄር ቀኝ የተቀመጠው፣ ደግሞ ስለ እኛ የሚፈርደው ኢየሱስ ክረስቶስ ነው፡፡ |
| 7 | ሉቃ.22፡ 32 | እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፉ ስለ አንተ አማለድሁ | እኔ ግን ሀይማኖታችሁ እንዳይደክም ስለ እናንተ ፀለይሁ |
| 8 | ዕብ.7፡22 | ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኗል | ኢየሱስ ይህን ያህል በምትበልጥና ከፍ ባለች ሹመት ተሾመ |
| 9 | ዕብ.7፡25 | ስለእነርሱ ሊያማልድ ዘወትር በህይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሄር የሚመጡትን | ዘወትር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሄር የሚቀርቡትን ሊያድናቸው ይቻለዋል፣ ለዘላለምም ህያው ነውና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ፊፅሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡ | ያስታርቃቸዋል፡፡ |
| 10 | ኤፌ.2፡16 | ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሄር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው፡፡ | በመስቀሉም በአንድ ስጋው ሁለቱን ወደ እግዚአብሄር አቀረባቸው፣ በእርሱም ጥልን አጠፋ |
| 11 | ቆላ.1፡19-20 | እግዚአብሄር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፣ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት የሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና፡፡ | ሁሉ በእርሱ ፍፁም ሆኖ ይኖር ዘንድ ወዶአልና፣ ሁሉንም በእርሱ ይቅር ይለው ዘንድ በመስቀሉ በፈሰሰው ደም በምድርና በሰማያት ላሉ ሰላምን አደረገ |
| 12 | ቆላ.1፡21-22 | እናንተ ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በበፊት የተለያችሁትን ክፉ ስራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በስጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ፡፡ | እናንተም ቀድሞ በአሳባችሁና በክፉ ስራችሁ ከእግዚአብሄር የተለያችሁና ጠላቶች ነበራችሁ፣ አሁን ግን በፊቱ ለመቆም የተመረጣችሁና ንፁኃን፣ ቅዱሳንም ያደርጋችሁ ዘንድ በስጋው ሰውነት በሞቱ ይቅር አላችሁ፡፡ |
| 13 | 1ዮሐ.2፡1 | ልጆቼ ሆይ፣ ሀጢያትንእንዳታደርጉ ይህንን እፅፍላችኋለሁ፣ ማንም ሀጢያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ፃድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ | ልጆቼ ሆይ እንዳትበድሉ ይህን እፅፍላችኋለሁ፣ የሚበድል ቢኖር ከአብ ዘንድ ጰራቅሊጦስ አለን፣ ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢያተችንን ያስተሰርይ ዘንድ ፃድቅ ነው፡፡ |

## ➢ ከተጨማሪ መፅሃፍቱ

| ተቁ | ጥቅስ | የ1980 እትም | የ2000 እትም |
|---|---|---|---|
| 1 | ኩፋሌ 4፡11 | … ሴት ልጅ ብትወልድ … ሠላሳ ስድስት ቀንም ንጽህ በሚሻው ደምዋ ትቆይ … | … ሴት ልጅ ብትወልድ … ሰድሳ ስድስት ቀንም በመንፃቷ ደም ትቆያለች |
| 2 | አስቴር 9፡16 | የቀሩትም … አይሁድ ተሰብስበው … ከሚጠሉዋቸው ሰባ አምስት ሺ ገደሉ | የቀሩትም … አይሁድ ተሰብስበው … ከሚጠሉዋቸው አስራ አምስት ሺ ገደሉ |
| 3 | ሲራክ 4፡27 | ፈጣሪ እግዚአብሄር ስላንተ ይከራከርልሀልና እስከምትሞት ድረስ በሀይማኖት አትከራከር | ፈጣሪ እግዚአብሄር ስላንተ ይከራከርልሀልና ለሞት እስክትደርስ ስለ እውነት ተከራከር፡፡ |
| 4 | ሲራክ 9፡2 | ምስጢርህን እንዳታወጣብህ ልብህን ለሴት አትስጣት | ኀይልህን እንዳታደክምብህ ለሴት ልብህን አትስጣት |
| 5 | ሲራክ 19፡9 | ከሰማ በኋላ ሀጢያትህን አይሰውርልህምና እስክትሞት ድረስ ይጠብቅሀልና ስተህ የሰራኸውን ኀጢያት አትናገር፡፡ | ቢሰማ አይሰውርልህም፣ እስክትሞት ድረስ ይጠብቁሀል |
| 6 | ሲራክ 25፡24-25 | በቤት አጠገብ ለውሀ መፍሰሻ አታብጅለት ለሴትም የልብህን ምስጢር አታውጣላት፡፡ ግብርዋ እንደ ግብርህ ካልሆነ ፍታት ከሰውነትህም ለያት | በመጀመሪያ ሀጢያት ከሴት ተገኘች፣ በእርስዋም ምክንያት ሁላችን እንሞታለን፡፡ ለውሃ መፍሰሻ አታበጅለት ለሴትም የልብህን ምስጢር አታውጣላት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | ሄኖክ 13፡19 | አስታራቂ ክርስቶስ በመላዕክት ጌታ ፊት ቆሞአልና አሰት ነገርም እንደ ጥላ ያልፋል ቆሞ የሚሰወሩበት ቦታ የለም | አስታራቂው በመናፍስት ጌታ ፊት ቆማልና አመፅ እንደ ጥላ ያልፋል መቆሚያም ቦታ የለውም |
| 8 | ሄኖክ 13፡22 | አስታራቂ ክርስቶስ በመላዕክት ጌታ አብ ፊት እሱ እንደወደደ ነውና የተሰወሩትን ነገሮች ገልጦ የሚፈርድ እሱ ነው በሱም ፊት ዋዛ ነገርን ተናግሮ መዳን የሚችል የለም | እርሱም የተሰወሩትን ይፈርዳል ከንቱ ነገርንም በፊቱ መናገር የሚችል የለም፡፡ እርሱ እንደወደደ በመናፍስት ጌታ ፊት አስታራቂ ነውና |
| 9 | ሄኖክ 13፡31 | አስታራቂ ክርስቶስ በነዚያ ወራት በዙፋኑ ይቀመጣል የመላዕክት ጌታ ሰጥቶ አክብሮታልና የተሰወረ ጥበብንም ነገር ሁሉ አስቦ ከሚናገርበት ከአንደበቱ ያወጣል | አስተራቂውም በእነዚህ ወራቶች ምድር አደራዋን ትመልሳለች መቃብርም የተቀበለችውን አደራ ትመልሳለች፡፡ |

መፅሃፍ ቅዱሱ ቅዱሳን በእግዚአብሄር ምሪት የፃፉት በመሆኑ በማንም ሰው አይታረምም፣ ማስተካከል ይቅርና ትንቢቶቹ ራሱ ዝም ተብሎ አይተረጎምም(2ጴጥ.1፡20)፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ መጨመር መቀነስ አይቻልም እየተባለ(ራዕ.22፡18-19, ዘዳ.4፡2, ዘዳ.12፡32 ...) አቡነ ጳውሎስ ባሳተሙት መፅሃፍ ቅዱሳቸው ላይ በመጨመር፣ በመቀነስ፣ በማደባለቅና በመቀየር በአጠቃላይ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አጭበርባሪ ነጋዴ ነው የሆኑበት፡፡

የሚገርመው ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ለወደፊቱም በአዲስ ኪዳኑ ላይ የሚጨመሩ መፅሃፍት ተዘጋጅተዋል እነሱም [96] "1ኛ መፅሀፈ ኪዳን፣ 2ኛ መፅሀፈ ኪዳን፣ ሥርአተ ፅዮን ሲኖዶስ፣ ትዕዛዝ ሲኖዶስ፣ ግጽው ሲኖዶስ፣ አብጥሊስ ሲኖዶስ፣ ዳድስቅሊያስ እና ቀለምንጦስ" ናቸው፡፡

ብዙ ሙስሊም ምሁራን "መፅሀፍ ቅዱሱ የፈጣሪ ቃል አይደለም ምክንያቱም እርስ በርስ ይለያያል" ብለው የሚሟገቱት ይህንን በማስረጃነት በማቅረብ ነው፣ ይህ ደግሞ፣

> ሮሜ.2፡24 "በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሄር ስም በአህዛብ መካከል ይሰደባልና ..."

የሚለው ቃል ፍፃሜ ነው፡፡

በአጠቃላይ በ66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ የተጨመሩት ተጨማሪ መፅሀፍት እንደ ፈጣሪ ቃል በብዛትና በአይነት ቋሚ አለመሆናቸውን ስንመለከት ተጨማሪ መፅሀፍቱ የማይለዋወጠው ፈጣሪ ቃል አለመሆናቸውን ያሳያል፣ መፅሀፍ ቅዱስ ስለራሱ አለመለዋወጥ ሲናገር

> ማር.16፡8 "... ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱሱን ወንጌል ከፀሀይ መውጫ እስከ ፀሀይ መጥለቂያ ድረስ በእጃቸው ላከው፡፡"

በዚህም መሠረት እነዚህ ተጨማሪ መፅሀፍት የማይለዋወጠው የእግዚአብሄር ቃል አለመሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

---

[96] መምህር ያሬድ ሽፈራው(2009)፣ **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ አመጣጥ፣** ገፅ 104-105

### 4.3.4.3. የመፅሀፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ በመፅሃፍ ቅዱሱ ውስጥ ትክክለኛ ቦታ አጥተው መቸገራቸው

ተጨማሪ መፅሀፍቱ የመፅሀፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳብቅ መልኩ በመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥ የራሳቸውን ትክክለኛ ቦታ አጥተው ሲቸገሩ እንመለከታለን፡፡

“መፅሀፈ ሄኖክ” በሁለቱም፣ በድሮዎቹም ሆነ በአቡነ ጳውሎሱ መፅሀፍ ትክክለኛ ቦታውን አጥቶ ሲቸገር ይታያል፣ ሄኖክ ከሙሴ በፊት የነበረና ያስተማረውም “በማቱሳላ ዘመን ነው” መባሉን ስንመለከት ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱ በተቀናበረበት ክሮኖሎጂ(የታሪክ የጊዜ ቅደም ተከተል) መሠረት መፅሀፉ ከኦሪታት በፊት መሆን ነበረበት ወይ ደግሞ መፅሀፉ ላይ የተፃፉት ታሪኮች የአዲስ ኪዳኑንም ታሪኮች የያዘ በመሆኑ መፅሀፉ መግባት ያለበት በአዲስ ኪዳኑ መሆን ነበረበት ነገር ግን ሁለቱም አልሆኑም፣ የ1980ው ህትመት የአዋልድ መፅሀፍት መጨረሻ ላይ ሲያስቀምጠው የ2000ው ህትመት ደግሞ ከአዋልድ መፅሀፉት 2ኛ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡

በድሮዎቹ ህትመቶች ተጨማሪ መፅሀፍቱ የዲዮትሮፒካኖኒካል መፅሃፍት ተብለው ለብቻቸው በሁለቱ የኪዳን መፅሃፍት መካከል ተቀምጠው ነበረ፣ በ2,000 ህትመት ላይ ደግሞ ከብሉይ ኪዳን መፅሀፍት ጋር ተደባልቀው መጥተዋል፣ ከማደባለቁ በላይ ደግሞ የተደባለቁበት መንገድ የመጀመርያውን ቅደም ተከተላቸውን ይዘው አይደለም፣ ለምሳሌ በቀደመው አሰራር ተጨማሪ መፅሀፍቱ መፅሀፈ ዕዝራ ሱቱኤል፣ መፅሀፈ ዕዝራ ካልዕ ... ቅደም ተከተል ሲሆኑ በተደባለቀው ውስጥ ደግሞ የአዋልድ የመጨረሻ መፅሀፍት የነበሩት መፅሀፈ ኩፋሌና መፅሀፈ ሄኖክ የተጨማሪ መፅሀፍቱ ቀዳሚና ተከታይ ሆነው መጥተዋል፣ ሌሎቹም መፅሀፍት ላይ ተመሳሳይ የቅደም ተከተል መዘበራረቅ ተፈጥሯል፡፡

በ4.3.4.2./ማደባለቅ/ ስር ተረፈ ኤርምያስ፣ ተረፈ ዳንኤል፣ መፅሀፈ ሶስና፣ የምናሴ ፀሎትና መዝሙረ ሰለስቱ ደቂቅ በሁለቱ በ1980ው እና በ2000ው ህትመት እንዴት ቦታቸው እንደተቀያየረ ተመልክተናል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት መፅሀፍቱ ቋሚ ቦታ አጥተው በየጳጳሳቱ ወዲያ ወዲህ ሲንገላቱ እንመለከታለን፤ እጅ የራሱ ቦታ አለው፣ አይን፣ ጆሮ … ሁሉም የሰውነት ክፍሎች የየራሳቸው ቦታዎች አሏቸው ነገር ግን የሰውነት አካል ያልሆነውን ተጨማሪ አካል ሰውነት ላይ ለመጨመር ብንሞክር ማስቀመጫ ቦታ ያስቸግራል፣ አሽጋሽገን ለማስቀምጥ ብንሞክር እንኳን ተለይቶ ይታወቃል፣ አሁንም እነዚህን መፅሀፍት የገጠመው ችግር ይኸው ነው፣ መፅሀፍቱ የመፅሀፍ ቅዱሱ አካላት ባለመሆናቸው በቅዱሳኑ መፅሀፍት መካከል እየተቸገሩ ይገኛሉ፡፡

66ቱ መፅሀፍት እንደዚህ አይነት ችግር ሳይገጥማቸው በዘመናትና በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ የራሳቸውን ቋሚ ቦታ መያዛቸው የ66ቱን መፅሀፍት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ሲሆን የተጨማሪ መፅሀፍቱ ትክክለኛ ቦታ ማጣት ደግሞ ተጨማሪ መፅሀፍቱ የመፅሀፍ ቅዱስ አካል አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡

#### 4.3.4.4. <u>የመፅሀፍቱ መቼት መፋለስ</u>

ተጨማሪ መፅሀፍቱ “የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት” ተብለው ይቅረቡ እንጂ በውስጣቸው የምንለከተው የአዲስ ኪዳን ይባሱኑም ከመፅሀፍ ቅዱስ መታተም በሃላ የነበሩ ታሪኮችን ነው፣ በዚህም ከላይ በሄኖክ መፅሀፍት ላይ የተመለከተውን ትተን በሌሎቹ ተጨማሪ መፅሀፍቱ ላይ ያሉትን እነዚህን ችግሮች እንመለከታለን፣ በዚህም በመጀመርያ በተጨማሪ መፅሀፍቱ ውስጥ የተደባለቁትን አዲስ ኪዳናዊ ታሪኮችን ለምሳሌ ያህል ብንመለከት፣

- ኢየሱስ
  - ክርስቶስ - ዕዝራ ሱቱኤል 5፡28-29
  - ወልድ - ተረፈ ኤርምያስ 11፡45, ዕዝራ ሱቱኤል 12፡26
  - የአብ ልጅ - ሲራክ 24፡3
  - ፈራጅ - ተረፈ ኤርምያስ 11፡46
- አብ - ተረፈ ኤርምያስ 11፡45, ዕዝራ ሱቱኤል 12፡26
- ማርያም - ሲራክ 24፡10, ዕዝራ ሱቱኤል 3፡7
- ሐዋርያት - ተረፈ ኤርምያስ 11፡52, ሲራክ 24፡2
- መንግስተ ሠማያት - 1ኛ መቃብያን 6፡11
- ቤተክርስቲያን - ሲራክ 32፡6
- መስቀል - ዕዝራ ሱቱኤል 12፡6-7, ዕዝራ ሱቱኤል 12፡35
- ሀሰተኛው ክርስቶስ - ዕዝራ ሱቱኤል 3፡6

ከነዚህ የአዲስ ኪዳን ቃላት በተጨማሪ የአዲስ ኪዳን ድርጊት ዘገባም እንመለከትበታለን፣ ለምሳሌ አንድ አረፍተ ነገር ወስደን ብንመለከት፣

> ሲራክ 24፡1-12 “ወላድ ሰውነቷን በተዋህዶ ታከብራለች … እኔ ከእግዚአብሄር አብ ተወለድኩ … <u>ካምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን አስቀድሞ</u> የህዝቡንና የአህዛቡን ስጋ አልተዋሃድሁም፡፡ ከዚህ በኋላ አረፍትን ፈለግሁ፣ እንግዴስ የማንን ስጋ እዋሃዳለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ሁሉን የፈጠረ አብ አዘዘኝ <u>ሁሉን የፈጠረ አብ</u> <u>ስጋን አዋሃደኝ …</u> በሱ ፈቃድ የከበረ <u>የማርያም ማኅፀን</u> ስጋን ተዋሃድሁ <u>በምኩራብ አስተማርሁ</u>፡፡ <u>በቤተመቅደስም እንደዚሁ</u> አስተማርኩ አብ ባስገዛኝ

<u>በኢየሩሳሌምም ወንጌልን አስተማርኩ</u>፡፡ በብዙ <u>የእግዚአብሄር አብ</u> ርስት እድል በሆኑ <u>በህዋርያት መካከል ቀዳሚነቴን አስተማርኩ፡፡</u>"

ይህ ታሪክ ምንም እንኳን ብዙ ስህተቶችን ቢይዝም በውስጡ ግን የምንመለከተው ታሪክ የአዲስ ኪዳን ታሪክ(የኢየሱስ ታሪክ) የድርጊት ዘገባ እንጂ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ወይ ትንቢት አይደለም፣ ይህም እውነታ ተጨማሪ መፅሀፍቱ የተዘጋጁት በአዲስ ኪዳን መሆኑን እንመለከታለን፡፡ ከዚህ በከፋ ደግሞ መፅሀፍቱ በመፅሀፍ ቅዱሱ አንድም ቦታ ላይ ያልተጠቀሰውና በኒቂያ ጉባኤ የተፈጠረውን "ስላሴ" የሚለውን ቃል (ዕዝራ ሱቱኤል 4፡5, ሄኖክ 13፡18-29 ...) መያዛቸው፣ መፅሀፍቱ የተፃፉት በብሉይ ኪዳን ዘመን ወይ የአዲስ ኪዳን መፅሀፍት በተፃፉበት ዘመን ሳይሆን ከ234 ዓ.ም ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ የተፃፉ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ "የጊዜ" መዛባት ችግር በተጨማሪ በ4.3.4.1 ክፍል እንደተመለከትነው መፅሀፍቱ ብሉይ ኪዳን ባልተገባላቸው ግሪክና ኢትዮጵያ መፃፋቸውን ስንመለከት መፅሀፍቱ "የቦታ" መዛባትም እንዳለባቸው እንመለከታለን፡፡

መፅሀፍቱ እነዚህን በብሉይ ኪዳን አንድም ቦታ ያልተጠቀሱና በአዲሱ ኪዳን ብቻ የተነገሩ ሀሳቦችን ከመያዝ አልፎ በአዲስ ኪዳኑም ያልተጠቀሰውን ቃል መያዛቸው እንዲሁም እስራኤላዊ ሳይሆኑ ግሪካዊና ኢትዮጵያዊ መሆናቸው መፅሀፍቱ የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት ሳይሆኑ ከአዲሱም ከብሉዩም ኪዳን ተለይተው ለብቻ መታተም የነበረባቸው መፅሀፍት መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

### 4.3.4.5. ተረቶችና ግራ የተጋቡ ትምህርቶችን እንደ ፈጣሪ ቃል መያዙ

ከላይ በ4.3.3 ክፍል እንደቀረበው "የሄኖክ መፅሀፍ" የተባለው መፅሀፍ ተረቶችና ግራ አጋቢ ትምህርቶች የፈጣሪ ቃል አድርጎ ማቅረቡን ተመልከተናል፣ ሌሎቹም መፅሀፍት የተፃፉት በአንድ መንፈስ በመሆኑ እነዚህም ጋር ተመሳሳይ ችግር እንመለከታለን፣

- **ተረት ተረቶች**

1. ፀሃይ ትሰማለች፣ አደራም ትቀበላለች
   ተረፈ ኤርምያስ 8፡18-19 "ያን ግዜ ኤርምያስ የቤተመቅደሱን መክፈቻ ይዞ ከከተማ ወደ ውጪ ወጣ:: ይህንንም መክፈቻ ፀሃይን የእግዚአብሄር ማደሪያ የቤተመቅደስ መክፈቻ ተቀበል ብሎ በፀሀይ ፊት ጣለው::"
2. ምድር ትሰማለች፣ ሰምታም ትታዘዛለች
   ተረፈ ኤርምያስ 8፡13 "ባሮክና ኤርምያስ ወደ ቤተመቅደስ ገቡ የሚያገለግሉበትን ዕቃ ሁሉ ... ለምድር ሰጧት ማድርም ያን ግዜ ተቀብላ ዋጠችው::"
3. ጨረቃ ኮከብን ትበልጣለች
   ሲራክ 43፡8 "ጨረቃስ እንደ ስሟ ናት ከከዋከብትም እንድትበልጥ ድንቅ ነው::"
   ዛሬ ላይ ፀሀይን ጨምሮ ብዙ ግዙፍ ጨረቃን ይቅርና መሬትን እንኳን የሚበልጡ ክዋክብት መገኘታቸውን ስንመለከት ቃሉ የፈጣሪ አለመሆኑን እንመለከታለን::
4. የሚናገር ይባሱኑም የሚያሾፍ ድንጋይ
   ተረፈ ኤርምያስ 11፡60 "ያን ጊዜም ያ ደንጊያ እናንተ ሰነፎች የእስራኤል ልጆች ኤርምያስን መስያችሁ በደንጊያ ስለምን ትወግሩኛላችሁ፣ ኤርምያስስ እነሆ በመካከላችሁ ቆሟል ብሎ ጮኸ::"
5. ከሰው ጋር የሚነጋገር ሀይማኖተኛ አሞራ
   ተረፈ ኤርምያስ 10፡23-32 "ባሮክም እንዲህ ያለ ፅህፈት ፅፎ ከመቃብር ቤት ወጣ ንስሩም ሀይማኖትን የምታስተምር ባሮክ ሆይ "ቸር አለህ" አለው:: ባሮክም ከሰማይ አእዋፍ ሁሉ የተመረጥክ አንተ

ትናገራለህና ባይኖችህ ብርሃን የታወቅህ ነህ … ባሮክም ደብዳቤውን ያዘ ከዚያ አቤሜሌክ ከሰጠው ከበለሱ ሙዳይ አስራ አምስቱን በለስ አምጥቶ በንስሩ አንገት ቋጠረው … ለኤርምያስ ከሱ ጋር ላሉ እስራኤላውያን ውሰድ … አእዋፍ ሁሉ ቢከቡህ ይገድሉ ዘንድ ወደው የሀይማኖት ጠላት ሁሉ ቢከቡህ በሀይማኖትህ ቀድመኻቸው ሂድ፡፡”

6. <u>ሙታንን የሚያስነሳ አሞራ</u>

   ተረፈ ኤርምያስ 11፡4-6 “ንስሩ በታላቅ ድምፅ “አምላክ የመረጠህ ኤርምያስ ሆይ ላንተ እነግርሀለሁ፣ ሄደህ ህዝቡን ሁሉ ሰብስባቸው … አለው … ህዝቡም በተሰበሰበ ጊዜ ንስሩ በሬሳው ላይ ቆመ በዚህ ሰአት ሙቱ ተነሳ፡፡”

7. <u>66 አመት መተኛት</u>

   ተረፈ ኤርምያስ 9፡1-2 “አቤሜሌክም ኤርምያስ ከላከው ቦታ በቀትር ጊዜ በለሱን አመጣ ጽፍቅ ያለች ዱርንም አገኘ ጥቂትም ያርፍ ዘንድ በጥላዋ ስር ተቀመጠ በለስ ያለባትንም ሙዳይ ተንተርሶ ስድሳ ስድስት አመት ተኛ ከመኘታውም አልነቃም፡፡ ከዚያ ዘመን በኋላ ከመኘታው ነቅቶ ተነሳ ገና ራሴን ከብደኛልና <u>እንቅልፌን አልጨረስኩም</u>ና ጥቂት ብተኛ በጎ ነገር ነው አለ፡፡”

8. <u>በምድረ በዳና በባህር ውስጥ ያሉ አለም ያላየቻቸው አውሬዎች</u>

   ሄኖክ 16፡12 እና 41 “… ስሟ ሌዋታን የሚባል ሴቲቱ አውሬ በውሀዎች ምንጮች ላይ በባህሩ ጥልቅ ትኖር ዘንድ ተፈጠረች፡፡ የማይታየውን ምድረ በዳ በደረቱ የሚይዝ ስሙ ብሔሞት የሚባል የወንዱም አውሬ ቦታው በየብስ ነው፡፡”

   ዕዝራ ሱቱኤል 4፡49-52 “(በፍጥረት ቀናት) በአምስተኛው ቀን … የፈጠርካቸው ሁለቱ እንስሳት (ብሔሞትና ሌዋታን) … አራቱ ተራሮች ባሉበት በዚያ ቦታ እሱ በውስጡ ይኖር ዘንድ ለብሔሞት ከስድስተኛው እጅ አንዱን እጅ የብስን ሰጠኸው፡፡ ሰባተኛውንም እጅ ባህሩን ለሌዋታን ሰጠኸው፣ ለምትወዳቸው ለፃድቃን ምግብ ይሆኑ ዘንድ ሌዋታንና ብሔሞትን ጠበቅሀቸው፡፡”

9. <u>እንደጎረሰ ተሰንጥቆ የሞተ ዘንዶ</u>

   ተረፈ ዳንኤል 13፡26-27 “(ዳንኤልም) ንጉስ አንተ ይህንን ዘንዶ (ንጉሱ የሚያመልከውን) ያለ ሰይፍና ያለ በትር እገድለው ዘንድ

አሰናብተኝ አለው፣ ንጉሱም አሰናበትኩህ አለው፡፡ ዳንኤልም ጠጉርና አደሮ ማር ስብ አምጥቶ አንድነት ቀቀለው ልህሉህ አደረገው ለዘንዶውም በአፉ አጎረሰው፣ ያም ዘንዶ በጎረሰው ጊዜ ተሰንጥቆ ሞተ ዳንኤልም ጣኦቶቻችሁን እዩ አለ፡፡”

10. <u>ሶስት ሺ ክንድ የሚረዝሙ ሰዎች</u>

ሄኖክ 2፡12-16 “እነሱም ፀንሰው ረጃጅሞች አርበኞች ልጆችን ወለዱ ቁመታቸውም ሶስት ሶስት ሺ ክንድ ነው ... ረጃጅሞቹ ልጆች አባት እናቶቻቸውን ይበሉዋቸው ዘንድ ወደ መብላት ተመለሱ ... እርስ በርሳቸውም ስጋቸውን ተባሉ ከሷም ደምን ጠጡ፡፡”

ሄኖክ 4፡85-86 “ከደመና የሚደርሱ ረጃጅም ሰዎችም ፈፅመው ይጠፋሉ እስበሳቸውም ይጣላሉ በዚህ ዓለም ሰውን ያጠፋሉ፡፡ በሰውም ሀዘን ያደርጋሉ እነሳቸውም የሚበሉትን እህል ምንም አያገኙም፡፡”

- <u>**ግራ የተጋቡ ትምህርቶች**</u>

1. ሲራክ 8፡12-13 “ለባለፀጋ አታበድረው ... ባለፀጋውን አትዋሰው ...”
2. ሲራክ 13፡9 “ባለፀጋ ያዘዘህን ለጊዜው እሺ በለው ...”
3. ሲራክ 16፡1 “ጥቅም የሌላቸውን ብዙ ልጆችን አትውደድ፡፡”
4. ሲራክ 26፡16 “የዋህ ሴት ለእግዚአብሄር <u>እድሉ</u> ናት፡፡”
5. ሲራክ 26፡19 “ነገር ለምትታገስ ሴት ለውጥ የላትም፡፡”
6. ሲራክ 35፡22 “በፈቃድህ ፀንቶ የሚኖረውን ልጅህን ስንኳ አትመነው፡፡”
7. ሄኖክ 41፡1-3 “ከብዙ ቀንም በኋላ ልጁ ማቱሳላ ልጁ ላሜህን ሚስት አጋባው፤ ከሱም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ <u>ሰውነቱም እንደ እንቁ ነጭ ሆነ፣ እንደ ፅጌረዳም ቀይ ነው</u> ... ዓይኖቹን በገለጠ ጊዜ ቤቱን ሁሉ እንደፀሃይ አበራ ...”

   የዚህ ህፃን ከለር ነጭ ነው? ወይስ ቀይ?
8. ሄኖክ 16፡3 “ያን ግዜ እለተ <u>እሁድ ገንዘቡ የሆነች ጌታን</u> በጌትነቱ ዙፋን ተቀምጦ አየሁ፡፡”
9. ሌላውስ ቀን ምኑ ነው?

10. ተረፈ ኤርምያስ 10፡5 "ከዚህ በኋላ የታመነ ክርስቶስ ይመጣል፣ ወደ ሬሳሽም ይመልሰሻል፣ መጠርጠር ወደ ሌለው ሀይማኖትሽ ተመልከች፡፡"
11. እስኪ ይህን ጊዜ መች እንደሆነ አስሉት፣
ዕዝራ ሱቱኤል 13፡48 "እንዳዘዘኝም አደረግሁ፣ በአራተኛው ዘመን ከሚቆጠሩ ከብዙ ሱባኤ ባምስተኛው ሱባኤ ይህ አለም በተፈጠረ ካምስት ሺህ ዘመን ኋላ ጨረቃ ሰርክ ባደረገች ጨለማዋን በአጣች በአስረኛው ቀን በሶስተኛው ወር በዘጠና አንደኛው ይህን ሁሉ ፅፎ…"
12. ጦቢት 1፡1 "እኔ ጦቢት በህይወት መኖርሁበት ዘመን በሚገባና በውነት ስራ ፀንቼ ኖርሁ፡፡"
ይህ ሰውዬ "በህይወት በኖርኩበት ዘመን" ማለቱ መፅሀፉን የፃፈው ሞቶ ነው እንዴ?

እነዚህ የተጨማሪ መፅሀፍቱ ግራ የመጋባት ችግሮች የ66ቱን መፅሃፍት ውበት እንድንደነቅና ከእግዚአብሄር የሆነና ያልሆነውን በአፃፃፉ መንፈስ ብቻ መለየት እንደሚቻል የሚረጋገጥ እውነታ ነው፡፡

#### 4.3.4.6. <u>እርስ በራሱ እንዲሁም ከ66ቱ መፅሀፍት ጋር መጋጨቱ</u>

ተጨማሪ መፅሀፍት እርስ በርስ እንዲሁም ቅድስናቸው ከተረጋገጡት ከ66ቱ መፅሀፍት ጋር ሲጋጩ እንመለከታለን፣ ይህ ደግሞ መፅሀፍቱ በአንዱ በእግዚአብሄር መንፈስ አመራር አለመፃፋቸውን ያረጋግጥልናል፡፡

##### 4.3.4.6.1. <u>እርስ በራሱ መጋጨቱ</u>

ፈጣሪ ሁሉን አዋቂ በመሆኑ ቃሉን አይለውጥም በዚህም ቃሉ እርስ በርስ አይምታታበትምም ነገር ግን የቤተክርስቲያንዋ ተጨማሪ መፅሀፍት ላይ ሊታገሱት የማይችሉት እርስ በርስ ግጭት እንመለከታለን፡-

1. **<u>ሰይጣን የተጣለበት ምክንያት</u>**

<u>ለአዳም አልሰግድም በማለቱ</u>

3ኛ መቃብያን 1፡15 "… ለሚዋረድልኝ ለአዳም አልግድም በማለቴ እግዚአብሄር ስለ አባታቸው ስለ አዳም ከማዕረጌ አዋርዶኛልና፡፡"

<u>በትዕቢቱ</u>

3ኛ መቃብያን 2፡8-9 "… በትዕቢትህና በልቦናህ ፅናት ፈጣሪህንም በማሳዘን ፈጣሪንም ባለማመስገን አንተ ከእግዚአብሄር ትዕዛዝ ወጥተህ በወነጀልህ ጊዜ… ስለ ከፉ ስራህ ከማእረግህ አዋረደህ …"

2. **<u>መንግስተ ሰማያትን ንቀው የተዉት አሉ ወይስ ማንም አላየውም?</u>**

<u>አይተው የተው አሉ(የአዳም ልጅ የሆነው የ"ሴት"ዘሮች ትተውታል)</u>

ሄኖክ 4፡69-71 "… ለደቂቀ ሴትም ሄደህ ንገራቸው … ዘላለም ፀንቶ የሚኖር መንግስተ ሰማያት ስለምን ተዋችሁ፡፡"

<u>ማንም አላየውም</u>

1መቃብያን 14፡20 "… አይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን በሰው ልቡናም ያልታሰበውን እግዚአብሄር በህይወት ሳሉ ደስ ላሰኙት ለሚወዱት ለአብርሀም፣ ለይስሀቅና ለያዕቆብ ያዘጋጀውን ይሰጣቸው ዘንድ …"

3. **<u>የመቃቢስ ልጆች ሬሳ ተቀበረ ወይስ ተሰወረ?</u>**

<u>ተቀበረ</u>

1ኛ መቃብያን 4፡7 "ምክርንም መከረ የሚያደርገውንም አጣ ከዚህም በኋላ መቃብር ቆፍሮ ያምስቱን ሰማዕታት ሬሳቸውን ቀበረ፡፡"

<u>ተሰወረ</u>

2ኛ መቃብያን 7፡9 "ይቀብራቸው ዘንድ ወደ.ልና ከዚህ በኋላ የፃድቃንን ሬሳ ወደ ጣለበት ቦታ ሂዶ ሬሳቸውን እንዳይነካ እግዚአብሄር ሰውራቸዋልና ነገር ግን አጣቸው፡፡"

4. <u>መቃቢስ ቢኒያማዊ ወይስ ሞአባዊ ነው?</u>

<u>ቢኒያማዊ</u>

1ኛ መቃብያን 2፡1 "ከነገደ ቢኒያም የተወለደው ስሙ መቃቢስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፡፡"

<u>ሞአባዊ</u>

2ኛ መቃብያን 1፡2-6 "የሶርያና የኤዶምያስ ሰዎች አማሌቃውያን የኢየሩሳሌምን አገር ካጠፉው ከሞዓቡ ሰው ከመቃቢስ ... የእስራኤልም ልጆች በበደሉ ጊዜ የሞአብ ሰው መቃቢስን አስነሳባቸው ..."

5. <u>ለሞተ ሰው የሚደረግ ስነስርአት ትርጉም አለው ወይስ የለውም?</u>

<u>ትርጉም አለው</u>

ሲራክ 7፡33 "... ለሞተ ሰውም ተዝካር ማውጣት አትተው፡፡"

<u>ትርጉም የለውም</u>

ሲራክ 17፡28 "የሞተ ሰውን ግን ንስሀ እንደ ኢምንት አለፈው ..."

6. <u>በባቢሎን ወረራ ወቅት ንዋየ ቅዱሳቱ እንዴት ሆኑ?</u>

<u>ተደበቁ</u>

ተረፈ ኤርሚያስ 8፡13 "ባሮክና ኤርሚያስም ወደ ቤተመቅደስ ገቡ፣ የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ሰጣት፣ ምድርም ያን ጊዜ ተቀብላ ዋጠችው፡፡"

<u>ተዘረፉ</u>

ዕዝራ ካልዕ 1፡54 "እግዚአብሄርን የሚያገለግሉበት ንዋየ ቅዱሳቱን ጥቃቅኑንምና ታላላቁንም ዕቃ ሁሉ የእግዚአብሄር ማደሪያ ታቦትንም ከቤተመንግስት ዕቃ ቤትም ያለውን ሳጥኑን ሁሉ ማርከው ወደ ባቢሎን ወሰዱ፡፡"

7. <u>በባቢሎን ወረራ ወቅት ቤተመቅደሱ ምን ሆነ?</u>

<u>ሰዎች እንዳይደፍሩት ተቆልፎ ተቀመጠ</u>

ተረፈ ኤርምያስ 8፡13 "የቤተ መቅደሱንም መከፈቻ ፀሃይን "የእግዚአብሄርን ማደሪያ መከፈቻ ተቀበል" ብሎ በፀሀይ ፊት ጣለው፡፡"

<u>ተቃጠለ</u>

ዕዝራ ካልዕ 1፡55 "የእግዚአብሄር ቤት ማደሪያ መቅደስንም አቃጠሉ የኢየሩሳሌምንም ቅፅሯን አፈረሱ ግንቧንም በእሳት አቃጠሉ፡፡"

**8. <u>መፅሃፈ ባሮክ የፃፈው ማነው?</u>**

<u>ባሮክ</u>

ባሮክ 1፡1-2 "የኬልቅዩ ልጅ ሴዴቅያስ የሴዴቅዩ ልጅ የማሴው ልጅ ኔርዩ የኔርዩ ልጅ <u>ባሮክ ወደ ባቢሎን የፃፈው መፅሃፍ ነገር ይህ ነው</u>፡፡"

<u>ኢኮንያን</u>

ባሮክ 1፡3-4 "ከይሁዳ ንጉስ ከኢዮአቄም ልጅ <u>ከኢኮንያን የተፃፈውን</u> ከህዝቡ ዘንድ ወደሱ የመጣውን፡፡ የባቢሎን ሰዎች የእግዚአብሄር ማደሪያ ንዋየ ቅዱሳቱ ከቤተ መቅደስ በወሰዱ ጊዜ በኢየሩሳሌም ወዳሉ ካህናት የላከውንም <u>ይህንን መፅሀፍ ባሮክ አነበበ</u>፡፡"

እነዚህ እርስ በርስ መጋጨቶች ተጨማሪ መፅሀፍቱ የእግዚአሄብር ቃል አለመሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

### 4.3.4.6.2. <u>ከ66ቱ መፅሃፍ ቅዱስ ጋር መጋጨቱ</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ተጨማሪ መፅሀፍቱ እርስ በርስ ሲጋጩ ነበረ ነገር ግን ግጭቱ በዚህ የሚያቆም ሳይሆን በቤተክርስቲያንዋ እንኳን ቅድስናቸውን ከመሰከረችላቸው 66ቱ መፅሀፍትም ጋርም ነው፣ ይህ ደግሞ ማንነታቸውን በገሀድ እንድናውቅ ያደርጋል፣

**1. <u>አዳም ከምን ተፈጠረ?</u>**

<u>ከአፈር፣ እሳት፣ ውሃና ነፋስ</u>

3ኛ መቃብያን 4፡10 "በከበሩ እጆቹ <u>ከምድር መሬትን</u> አምጥቶ <u>እሳትና ውሃ ነፋስንም</u> ጨምሮ በሱ ምሳሌና መልክ አዳምን ፈጠረው፡፡"

<u>ከአፈር</u>

ዘፍ.2፡7 "እግዚአብሄር አምላክም ሰውን <u>ከምድር አፈር</u> አበጀው..."

**2. <u>ቃየል አቤልን ለምን ገደለው?</u>**

<u>በሴት</u>

1ኛመቃቢያን 19፡1-2 "... እርሷ መልከ መልካም ነበረችና ስለ እርስዋ ከገደለው ከደግ ሰው ከአቤል ሚስት ... ልጆች ዳግመኛ ለቃየን ተወለዱለት፡፡ ወንድሙን ከገደለው በኋላ ... እርስዋን ወሰደ፡፡"

1ኛመቃብያን 23፡1-2 "... (ቃየን)በሴት ቀንቶ ወንድሙን ገደለው፡፡"

<u>እግዚአብሄር የአቤልን መስዋዕት ተቀብሎ የቃየልን ስለተወ በዚያ ንዴት</u>

ዘፍ.4፡4-8 "... እግዚአብርም ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መስዋዕቱ ግን አልተመለከተም፡፡ ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ ... ቃየንም ወንድሙን አቤልን፡፡ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው፡፡ በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሳበት፣ ገደለውም፡፡"

### 3. <u>የሰዎችና መላዕክት ጋብቻ?</u>

<u>ይቻላል</u>

ኩፋሌ 6፡9 "የአዳም ልጆች ... ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው ... የእግዚአብሄር መልአክትም ... አገቡዋቸው፣ ወንዶች ልጆችንም ወለዱላቸው እነሱም ረአይት ናቸው፡፡"

<u>አይቻልም፣</u> (መላዕክት ተፈጥሮአቸውም ከሰው የተለየ ነው፣ ሰው ቁሳዊ ሲሆን መላዕክት መናፍስት ናቸው፣ መንፈስ ደግሞ እንደ ቁሳዊው አካል ስጋና አጥንት የለውም)

- ማቴ.22፡30 "(ሰዎች) በትንሳኤ እንደ እግዚአብሄር መላዕክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም፡፡"
- ሉቃ.24፡39 "... መንፈስ ስጋና አጥንት የለውም ..."

### 4. <u>እስከ ሙሴ ያሉት ፃድቃን በአንድ መቃብር ነው የተቀበሩት ወይስ የተለያየ ቦታ?</u>

<u>አንድ ቦታ</u>

1ኛመቃብያን 10፡1-2 "ነገር ግን እንዲህ ካልሆነ የቀደሙት ሰዎች ከአዳም ጀምሮ ከሴትና ከአቤል፣ ከሴምና ከኖህ፣ ከይስሀቅና ከአብርሃም፣ ከዮሴፍና ከያዕቆብ፣ ከአሮንና ከሙሴ ጀምሮ በአባቶቻቸው መቃብር ይቀበሩ ዘንድ ነው፣ እንጂ በሌላ ቦታ ይቀበሩ ዘንድ ያልወደዱ ለምንድነው? በትንሳኤ ጊዜ ከዘመዳቸው ጋር አንድነት ሊነሱ አይደለምን፣ አጥንታቸውስ ጣኦት ከሚያመልኩ ... ጋር እንዳይቆጠር አይደለምን፣ በሌላ ቦታ ይቀበሩ ዘንድ ያልወደዱ ለምንድነው?"

<u>የተለያየ ቦታ</u>

<u>አብርሃምና ያዕቆብ፡-</u> አብርሃም የተቀበረው ከኤፍሮን በገዛው እርሻ ቦታ በሚገኘው አዲስ ባዘጋጀው የመቃብር ቦታ መሆኑን በዘፍ.23፡13-20 እና በዘፍ.50፡13 ላይ እንመለከታለን፡፡

አሮን፡- በመሪባ ውሃ ዘንድ ስላመፃችሁ ወደ እስራኤል አይገባም ብሎ እግዚአብሄር በመቆጣቱ "ወደ ሖር ተራራ ይውጣ በዚያ ይሙት ወደ ወገኖቹ ይከማች" በተባለው መሠረት በተራራው ራስ ላይ እንደሞተና አብረውት የሄዱት ሙሴና ልጁ … እዚያው ተራራው ላይ ትተውት እንደወረዱ በዘኁ.20፡23-29 ላይ ተጠቅሳል፡፡

ሙሴ፡- ሙሴ ወደ እስራኤል ምድር እንደማይገባ እግዚአብሄር በመናገሩ(ዘዳ.34፡4)፣ በሞአብ ምድር መሞቱ(ዘዳ.34፡5)፣ መቀበሩ(ዘዳ.34፡6) እና የመቃብር ስፍራውንም ማንም ሰው እንደማያውቀው(ዘዳ.34፡6) እንመለከታለን፡፡

5. ናቡከደነፆር ለምን በእግዚአብሄር ተቀጣ?

"ፀሀይን የማወጣው እኔ ነኝ" ስላለ

1መቃ.5፡3-4 "… በዚህ አለምም ፀሀይ የማወጣ ፈጣሪ እኔ ነኝ ብሎ ኮራ፣ ከትዕቢቱም የተነሳ እንዲህ አለ፡፡ እግዚአብሄርም ከሰው ለይቶ ሰባት አመት ወደ ምድረ በዳ ሰደደው፡፡"

"በታላቂቱ" ባቢሎን በመታበዩ

ዳን.4፡30 "ንጉሡም ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግስት መኖሪያ እንድትሆን ያሰራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን፣ ብሎ ተናገረ፡፡ ቃሉም ገና በንጉሱ አፍ ሳለ ድምፅ ከሰማይ ወደቀና ንጉስ ናቡከደነፆር ሆይ … ከሰዎች ተለይተህ ትሰደዳለህ … ሰባት ዘመናትም ያልፋብሃል፡፡"

6. አፍቅሮተ ነዋይ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ነው አይደለም?

መፅሀፍ ቅዱሳዊ ነው

ሲራክ 5፡1 "… ገንዘብ በቃኝ አትበል፡፡"

መፅሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም

ዕብ.13፡5 "አካሄዳችሁ ገንዘብ ያለመውደድ ይሁን፣ ያላችሁ ይብቃችሁ፡፡"፣ 1ጢሞ.6፡6-10 "ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሄርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው … የገነዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ስር ነውና፡፡"

7. ያለዝሙት ችግር መፋታት ይቻላል?

አዎን

- ሲራክ 25፡25 "ግብርዋ እንደ ግብርህ ካልሆነች ፍታት ከሰውነትህም ለያት፡፡"

- ተረፈ ኤርምያስ 11፡27-28 “ከናንተ ሴቶችን ያገባ ወንድን፣ ወንዶችንም ያገቡ ሴቶችንም ፍተናቸው አለው፣ ቃልህን የሰሙ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም መልሳቸው፣ ያልሰሙህንም ሰዎች ግን ወደሷ ይገቡ ዘንድ አትተዋቸው አለው ... ይህንንም ነገር ሲነገራቸው ያገቡ ሰዎች ... ሊፋቱም አልወደዱም፡፡”
- ሲራክ 25፡16 “ከደረቅ ሴት ጋር ከምትኖር ከምድር አውሬና ከአንበሳዎች ጋር መኖር ይሻላል

<u>ፈፅሞ የተከለከለ ነው</u>

ማቴ.5፡32 “ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ...”

8. <u>ፅላተ ሙሴ የተሰራው በምንድነው?</u>

<u>በዕንቁ ነው</u>

ኩፋሌ 1፡1 “... እግዚአብሄር፡- ከእኔ ዘንድ ወደዚህ ተራራ ውጣ፣ በፃፍከው መጠን ልብ ታስደርጋቸው ዘንድ ህጉና ስረአቱ የተፃፈባቸውን ሁለቱን የዕንቁ ፅላት እሰጥሃለሁ ብሎ ለሙሴ ተናገረ፡፡

<u>በድንጋይ ነው</u>

ዘፀ.24፡12 “እግዚአብሄርም ሙሴን ... ታስተምር ዘንድ እኔ የፃፍሁትን ህግና ትዕዛዝ የድንጋይም ፅላት እሰጥሃለሁ፡፡”

ዘፀ.31፡18 “... በእግዚአብሄር ጣት የተፃፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ፅላቶች ሰጠው፡፡”

9. <u>የያዕቆብ ልጅ የሆነው የብንያም ልጆች እነማን ናቸው?</u>

<u>ኩፋሌ 31፡21</u> “የብንያምም ልጆች <u>አስቤል</u>ና <u>ላውባኤል</u>፣ <u>ንእማን</u>ና <u>ጉአው</u>፣ <u>ራኤፍስ</u>ና <u>አብሮድዮ</u>፣ <u>አፌም</u>ና <u>ያኒም</u>፣ <u>ጋዕሞ</u>ና <u>የአም</u> ከእርሱ ጋር እነዚህ አስራ አንድ ናቸው፡፡”

<u>ዘፍ.46፡21</u> “የብንያም ልጆች <u>ቤላ</u>፣ <u>ቤኬር</u>፣ <u>አስቤል</u>፤ የቤላ ልጆችም ጌራ፣ ናዕማን፣ አኪ፣ ሮስ፣ ማንፌን፣ ሑፊም፤ ጌራም አርድን ወለደ፡፡”

10. <u>ንጉሱ አስቴር እንድትገባ መፈቀዱ የታወቀው ዘንጉን እንዴት አድርጎ በማሳየቱ ነው?</u>

(እዚህ ጋር የአስቴር መፅሃፍት በሁለቱም፣ በ66ቱ መፅሃፍ ቅዱስና በተጨማሪው መፅሃፍ፣ ስላሉ ሁለቱን ለመለየት የተጨማሪውን መፅሃፍ አስቴር አዋልድ ሲባል ሌለኛውን ደግሞ አሰቴር ቀኖና ተብሏል)

<u>ዘንጉን አንገቷ ላይ አድርጎ</u>

አስቴር(አዋልድ) 5፡2 "(ንጉሱ) የወርቁን ዘንግ አንስቶ በአንገቷ ላይ አኖረው፡፡"

<u>ዘንጉን ዘርግቶ</u>

አስቴር(ቀኖና) 5፡2 "... ንጉሱም በእጁ የነበረውን የወርቁን ዘንግ ለአስቴር ዘረጋላት፡፡"

11. **<u>በባቢሎናውያን ወረራ ጊዜ የቤተመቅደሱ እቃዎች ተዘረፉ ወይስ ከዝርፊያ አመለጡ?</u>**

<u>አመለጡ</u>

ተረፈ ኤርሚያስ 8፡13 "ባሮክና ኤርሚያስ ወደ ቤተመቅደስ ገቡ፣ የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ሰጣት፤ ምድርም ያን ጊዜ ተቀብላ ዋጠችው፡፡"

<u>ተዘረፉ</u>

2ኛዜና.36፡18-19 "የእግዚአብሄር ቤት ዕቃ ሁሉ፣ ታላቁንና ታናሹን፣ የእግዚአብሄርን ቤት መዝገብ፣ የንጉሱንና አለቆቹን መዝገብ፣ እነዚህን ሁሉ ወደ ባቢሎን ወሰደ፡፡ የእግዚአብሄርንም ቤት አቃጠሉ፣ የኢየሩሳሌምንም ቅጥር አፈረሱ፣ አዳራሾችዋንም በእሳት አቃጠሉ፣ መልካሙን እቃ ሁሉ አጠፉ፡፡"

12. **<u>በባቢሎን ወረራ ወቅት ነቢዩ ኤርሚያስ ወደ ባቢሎን ተወሰደ ወይስ እዚያው ይሁዳ ቀረ?</u>**

<u>ወደ ባቢሎን ተወሰደ</u>

ተረፈ ኤርምያስ 8፡21 "ኤርምያስም ለወገኖቹ ሲያለቅስ እያዳፉ አወጡት፤ ከህዝቡም ጋር እስከ ባቢሎን ድረስ ወሰዱት፡፡"

<u>ይሁዳ ቀረ</u>

ኤር.40፡2-6 "የዘበኞቹም አለቃ ኤርምያስን ወሰደው እንዲህም አለው ... አሁንም እነሆ በእጅህ ካለችው ሰንሰለት ዛሬ ፈታሁህ፡፡ ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎን መምጣት መልካም መስሎ ቢታይህ ና ... መልካም መስሎ ባይታይ ግን ተቀመጥ፤ እነሆ አገሪቱ ሁሉ በፊትህ ናት ... የዘበኞቹም አለቃ ስንቅና ስጦታ ሰጥቶ አሰናበተው፡፡ ኤርምያስም የአኪቃ ልጅ ጎዶሊያስ ወዳለበት ወደ ምፅጳ ሄደ፣ ከእርሱም ጋር <u>በአገሩ</u> ውስጥ <u>በቀሩት ህዝብ መካከል ተቀመጠ</u>፡፡"

13. <u>ዳንኤል አሽከር የነበረው በንጉስ ቂሮስ ወይስ በንጉስ ናቡከደነፆር ዘመን ነበረ?</u>

<u>በንጉስ ቂሮስ</u>

ተረፈ ዳንኤል 13፡1-2 "ንጉስ ዳርዮስ ሙቶ ባባቶቹ መቃብር ከተቀበረ በኋላ የፋርሱ ንጉስ ቂሮስ መንግስቱን ያዘ፡፡ ዳንኤልም የንጉስ የቂሮስ እልፍኝ የአሽከር ነበር፤ ከባለማሎቹም ሁሉ እሱ ይከብር ነበር፡፡"

<u>በንጉስ ናቡከደነፆር</u>

ዳንኤል በባቢሎን አሽከር ሆኖ ያገለገለው በልጅነቱ ሲሆን ይህም በናቡከደነፆር የንግስና ዘመን ነበረ(ዳን.1፡1-21)፣ ከዚያ ቦሃላ ዳንኤል ንጉስ ናቡከደነፆር የተጨነቀበትን ህልም ስለገለጠ፣ ዋነኛ አለቃ ተደረገ (ዳን.2፡48) ከዚያም ቀጥሎ የተነሳው ንጉስ ብልጣሶርም እንዲሁ ዳንኤልን በመንግስቱ ላይ ሶስተኛ ገዢ አደረገው(ዳን.5፡29)፣ በዳሪዮስ መንግስት ዘመንም ዳንኤል እንዲሁ ባለስልጣን ነበረ (ዳን.6፡2)፣ በቀጣዩ በቂሮስ ዘመንም ዳንኤል የተቃና ኑሮ ነበረው(ዳን.6፡28)፣ ስለዚህ የዳንኤል የአሽከርነት ዘመን በናቡከደነፆር እንጂ በቂሮስ ዘመን አልነበረም፣ ቂሮስ እንደ ዳንኤል የእግዚአብሄር አገልጋይ ነበረ(ዕዝ.6፡3፣ ኢሳ45፡1 …) እንጂ በተቃርኖ መንገድ አልነበረም፡፡

14. <u>ዳንኤል በአንበሶች ጉድጋድ የተጣለው በማን የንግስና ዘመን ነው?</u>

<u>በቂሮስ</u>

ተረፈ ዳንኤል 13፡1-29 "ንጉስ ዳርዮስ ሞቶ በአባቶቹ መቃብር ከተቀበረ በኋላ የፋርሱ ንጉስ ቂሮስ መንግስቱን ያዘ … ንጉስም እጅግ እንዳስጨነቁት ባየ ጊዜ ለንጉሱም ግድ በሆነበት ጊዜ ዳንኤልን ሰጣቸው፡፡ ወደ አንበሶች ጉድጋድ ጣሉት፡፡"

<u>በዳርዮስ</u>

ትንቢተ ዳንኤል 6፡1-6 "ዳርዮስም በመንግስቱ ሁሉ ዘንድ እንዲሆኑ መቶ ሃያ መሳፍንት በመንግስቱ ላይ ይሾም ዘንድ ወደደ … ከእነርሱ አንደኛው ዳንኤል ነበረ … የዚያን ጊዜ ንጉሱም አዘዘ፣ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጉድጋድ ጣሉት፡፡"

15. <u>ዳንኤል ወደ አናብስቱ ጉድጓድ የተጣለበት ምክንያት ምንድነው?</u>

<u>ዳንኤል የባቢሎናውያኑን አማልክትና አገልጋዮቻቸውን ስለገደለ</u>

ተረፈ ዳንኤል 13፡28 "ከዚህ በኋላ የባቢሎን ሰዎች በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቆጡ ወደ ንጉሱም በነገር ተመለሱ ቤልን(ጣዖት) ሰበረ ካህናቱንም ገደለ ዘንዶውንም ገደለ ... ንጉስም እጅግ እንዳስጨነቁት ባየ ጊዜ ለንጉሱም ግድ በሆነበት ጊዜ ዳንኤልን ሰጣቸው፡፡ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

ዳንኤል"ስግደት ወደ ንጉሱ ብቻ" የተባለውን ህግ ተላልፎ ወደ አምላኩ ስለፀለየ

ዳን.6፡11-17 "እነዚያም ሰዎች ተሰብስበው ዳንኤልን ወደ በአምላኩ ፊት ሲፀልይና ሲለምን አገኙት፡፡ ወደ ንጉስም ቀርበው ... ንጉስ ሆይ ከይሁዳ ምርኮኞች የሆነው ዳንኤል በየእለቱ ሶስት ጊዜ ልመናውን ይለምናል እንጂ አንተንና የፃፍከውን ትዕዛዝ አይቀበልም አሉት ... የዚያን ጊዜ ንጉሱም አዘዘ፣ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

16. **ንጉሱ ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ እንዲጣል የፈቀደው ለምንድነው?**

ህዝቡ የንጉሱን ቤት ለማቃጠልና ለመዝረፍ ስለዛተ

ተረፈ ዳንኤል 13፡29 "ዳንኤልን ይሰጠን ዘንድ ኑ ወደ ንጉስ እንሂድ፡፡ ይህ ካልሆነ እንገድልሃለን ገንዘብህንም እንዘርፍሃለን ቤትህን በእሳት እናቃጥላለን እንለዋለን አሉ፡፡ ንጉስም እጅግ እንዳስጨነቁት ባየ ጊዜ ለንጉስም ግድ በሆነበት ጊዜ ዳንኤልን ሰጣቸው፡፡ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

ህግህ "የማይለወጥ ነው" ብለው ስለፈተኑት

ዳን.6፡14-15 "ንጉሱም ... ያድነው ዘንድ ልቡን ወደ ዳንኤል አደረገ ... የዚያን ጊዜ እነዚያ ሰዎች ወደ ንጉሱ ተሰብስበው ንጉሱን፣ ንጉስ ሆይ ንጉሱ ያፀናው ትዕዛዝ ወይም ስርአት ይለወጥ ዘንድ እንደማይገባ የሜዶንና የፋርስ ህግ እንደሆነ እወቀው አሉት፡፡ የዚያን ጊዜ ንጉሱ አዘዘ፣ ዳንኤልንም አምጥተው ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

17. **ዳንኤል በአናብስቱ ጉድጓድ ውስጥ ስንት ቀን ቆየ?**

ሰባት ቀናት

ተረፈ ዳንኤል 13፡30 "ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት በዚያ ሰባት ቀን ተቀመጠ፡፡"

አንድ ለሊት

ዳን.6፡16-22 "... ዳንኤልን አምጥተው በአንበሶች ጉድጓድ ጣሉት ... ንጉሱም ወደ ቤቱ ሄደ ሳይበላም አደረ ... እንቅልፉም ከእርሱ ራቀ፡፡ በነጋውም ማልዶ ተነሳ፣ ፈጥኖም ወደ አንበሶች ጉድጓድ ሄደ፡፡ ወደ ጉድጓዱም ወደ ዳንኤል

በቀረበ ጊዜ በሃዘን ቃል ጠራው ... ዳንኤልም ንጉሱን፣ ንጉስ ሆይ ሺ አመት ንገስ ... የዚያን ጊዜም ንጉሱ እጅግ ደስ አለው፣ ዳንኤልንም ከጉድጓድ ያወጡት ዘንድ አዘዘ፡፡"

18. <u>ቤተመቅደስ እንዲሰራ የታዘዘው ዳዊት? ወይስ ልጁ ሰለሞን?</u>

<u>ዳዊት</u>

ዕዝራ ሱቱኤል 1፡22-23 "ዘመነ አበው አለፈ ዘመነ መሳፍንትም ተጨረሰ ስሙ ዳዊት የሚባል አገልጋይህን ለመንግስት አስነሳህ፡፡ ስምህ ሊመሰገንበት መስዋዕትህን ሊሰዋበት ቤተመቅደስ ይሰራ ዘንድ ስራ አልከው፡፡"

<u>ሰለሞን</u>

1ነገ.8፡19 እና 2ዜና.6፡9 "(እግዚአብሄርም ዳዊትን) ከወገብህ የሚወጣው ልጅህ እርሱ ለስሜ ቤትን ይሰራል እንጂ ቤት የምትሰራልኝ አንተ አይደለህም አለው፡፡"

19. <u>የመጨረሻው ቀን ይታወቃል?</u>

<u>አዎን ይታወቃል</u>

ዕዝራ ሱቱኤል 2፡37 "ይህ ዓለም በሚዛን ተመዝኗል ባህርንም በላዳን ሰፍሮታልና፣ ዘመኑንም በ8 ሺ ወስኖታልና፡፡"

<u>አይታወቅም</u>

ማር.13፡32-33 "ስለዚያች ቀን ወይ ስለዚያች ሰአት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም፡፡ ጊዜው መች እንደሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፣ ፀልዩም፡፡"

ማቴ.24፡42-43 "ጌታችሁ በምን ሰአት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ፡፡"

20. <u>መላዕክት መቼ ተፈጠሩ?</u>

<u>በስድስቱ የስነፍጥረት ቀናት</u>

ኩፋሌ 2፡5-7 "በመጀመሪያው ቀን (የተለያየ አገልግሎት ያላቸው) መላዕክት ተፈጠሩ፡፡"

<u>ከስድስቱ የስነፍጥረት ቀናት በፊት</u>

በስድስቱ የስነፍጥረት ቀናት ወቅት መላዕክቱ(መናፍስታዊ ፍጡራን) እንደነበሩ መፅሃፍ ቅዱሱ ይናገራል፡፡

ኢዮ.38፡4-7 "ምድርን በመሰረትሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ፣ ታስተውል እንደሆንህ ተናገር፡፡ ብታውቅስ መስፈሪያዋን የወሰነ፣ በላይዋስ የመለኪያ

ገመድ የዘረጋ ማነው፣ አጥቢያ ኮከቦች ባንድነት ሲዘምሩ፣ የእግዚአብሄር ልጆች ሁሉ እልል ሲሉ፣ መሰረቶችዋ በምን ላይ ተተክለው ነበር፣ የማዕዘንዋንስ ድንጋይ ያቆመ ማነው፣"

**21. ሰው የተፈጠረው ለምንድነው?**

ሰይጣን ስለወደቀ

3መቃብያን 2፡11 "አንተ(ሰይጣንን) በተመካህ ጊዜ እግዚአብሄር ክፉ ስራህን አይቶ አንተ ከሰራዊቶችህ ጋራ እግዚአብሄርን ከደሃልና ሳያጓድል ስሙን ያመሰግን ዘንድ ስላንተ ፈንታ የሚያመሰግን አዳምን ፈጠረው፡፡"

የቁሳዊው አለም "ገዥ" እንዲሆንና ገነትን "ያበጃትና ይጠብቃት" ዘንድ ነው

ዘፍ. 1፡26 "እግዚአብሄርም አለ፡፡ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባህር አሶችን የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ፡፡"

ዘፍ.2፡15 "… እግዚአብሄር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው፡፡"

**22. እግዚአብሄር አብርሃምን የተናገረው በሰይጣን ምክር ነው ወይስ በራሱ ሃሳብ ነው**

በሰይጣን ምክር

ኩፋሌ 14፡1 "ሁሉን የሚገዛ ሰይጣን መጥቶ በአምላክ ፊት ቆሞ እንዲህ አለ፣ እነሆ አብርሀም ልጁ ይስሀቅን ይወደዋል ከሁሉ ይልቅ እርሱ ደስ ያሰኘዋል በመሰዊያ ላይ መስዋዕት አድርጎ ያቀርበው ዘንድ ንገረው፡፡ ይህን ነገር ቢያደርግ አንተ ታያለህ በምትፈትነው ሁለ እርሱ የታመነ እንደሆነ ታውቃለህ አለው፡፡"

በእግዚአብሄር ሀሳብ

እዚህ ጋር ያለው ታሪክ መነሻ የሰይጣን ምክረ ሃሳብ ሳይሆን ጥልቅ መንፈሳዊ ሚስጢራትን የያዘ ታሪክ ነው፣ እግዚአብሄር አብርሀም አንድያ ልጁን እንዲሰዋ ያዘዘውና የአብርሀምን ታዛዥነት ተመልክቶ በልጁ ፋንታ በግን ያሳረደው ተምሳሌትነቱ ስለሰው ልጆች ሀጢያት ስለሚሰዋው የራሱ አንድያ ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት ተምሳሌት ነው፣ በይስሀቅ ፋንታ በጉ፣ እንደታረደው በሰው ልጅ ፋንታም ኢየሱስ ክርስቶስ መታረዱን ለማሳየት እንጂ ድንገት የመጣ የሰይጣን ምክረ ሀሳብ አይደለም፡፡

**23. <u>መንግስተ ሰማያት በብሉይ ኪዳን ተዘጋጅቶ ነበር ወይስ ኢየሱስ ነው የሚያዘጋጀው?</u>**

<u>በብሉይ ኪዳንም ነበረ አይተው የተዉትን ነበሩ</u>

ሄኖክ 4፥71 "... ዘላለም ፀንቶ የሚኖር መንግስተ ሰማያት ስለምን ተዋችሁ፡፡"

<u>አዲስ ነው የሚያዘጋጀውም ኢየሱስ ነው</u>

ዮሐ.14፥2-3 "(ኢየሱስም) ... ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፣ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፣ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛም እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኃለሁ፡፡"

1ቆሮ.2፥9 "... አይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሄር ለሚወዱት ያዘጋጀው ..."

**24. <u>አዳምና ሄዋን የተፈጠሩበት ጊዜ የተለያየ ነው? ወይስ አንድ ቀን ነው?</u>**

<u>የተለያየ ነው</u>

ኩፋሌ 4፥8 "በመጀመሪያዪቱ ሱባኤ አዳም ተፈጠረ፣ ሁለተኛይቱም ሱባኤ ሄዋንን ፈጥሮ አሳየው ..."

<u>አንድ ነው፣ በስድስተኛቀው ቀን</u>

ዘፍ.1፥2 "እግዚአብሄር ሰውን በመልኩ ፈጠረ ... ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ... ስድስተኛ ቀን፡፡"

**25. <u>ሐዋርያት ስጋዊውን ጦርነት ይዋጋሉ?</u>**

<u>አዎን ይዋጋሉ</u>

ሄኖክ 33፥58-39 "ለሐዋርያትም ታላቅ ስልጣን እስኪሰጣቸው ድረስ ደርሼ አየሁ ሐዋርያም ከውቀት ምድረ በዳ ወደ ሆኑ ወደ አህዛብ ሁሉ ሊያጠፋቸው ወጡ፡፡ በከፍታ የሚኖሩት አህዛብ ሁሉ ከፊታቸው ሸሹ፡፡"

<u>አይዋጉም</u>

ኤፌ.6፥12 "መጋደላችን ከደምና ከስጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከስልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማው አለም ገዦች ጋር በሰማያዊውም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሰራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡"

**26. <u>ሀጢያት ይበላለጣል?</u>**

<u>ይበላለጣል</u>

ሲራክ 20፥25-26 "ሀሰት ከመናገር መስረቅ ይሻላል፡፡"

ሲራክ 18፥15 "ክፉ ነገር ተናግሮ ከመስጠት በጎ ነገር ተናግሮ መንሳት ይሻላል፡፡"

አይበላለጥም

ያዕ.2፡8-13 "ህግን ሁሉ የሚጠብቅ፣ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፣ ባይዋሽ ነገር ግን ብትሰርቅ ያው ህግ ተላላፊ ሆነሀል፡፡"

**27. ቀማኛ የቀማውን ገንዘብ መልሶ ንስሃ መግባት አለበት? ወይስ የገንዘቡን አጠቃቀም መማር አለበት?**

አጠቃቀሙን ማስተማር

ሲራክ 5፡8 "... ቀምተህ ላመጣኸው ገንዘብ አትሳሳ፡፡"

ለተቀማው ሊመለስና ለራስም ንስሃ እንደሚያስፈልግ

ሚኪ.6፡10 "በውኑ በሀጢያተኛ ቤት የሃጢያት መዝገብ ፣ የተፀየፈም ውሸተኛ መስፈሪያ ገና አለ ይሆን፣"

ሐስ.8፡22 "እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ ..."

**28. የሞቱ ጻድቃንን ማመስገን ይገባል አይገባም?**

ይገባል

ይህ ሃሳብ በሲራክ መፅሀፍ ብዙ ቦታዎች ተጠቅሷል፣ "እናመስግናቸው" የሚለውም አብርሀምን (44፡19)፣ ሙሴ (45፡1)፣ አሮን (45፡6)፣ ፊንሀስ (45፡23)፣ ኢያሱ (46፡1)፣ ካሌብ (46፡7)፣ ሳሙኤል (46፡13)፣ ኤልሳዕ (48፡12-16)፣ ሕዝቅያስ (48፡17-25)፣ ኢዮስያስ (49፡1-5)፣ ሕዝቅኤል (49፡8-9)፣ ዘሩባቤል (49፡12)፣ ነህምያ (49፡13)፣ ስምዖን (50፡1-24)፡፡

ትርጉም የለውም

የሞቱትን ፃድቃን እንደ እግዚአብሄር በሁሉም ስፍራ ስለማይገኙ እነሱን ማመስገን ትርጉም የለውም፣ መፅሀፍ ቅዱሱም ላይ ስንመለከት ምስጋና የሚቀርበው ለእግዚአብሄር ብቻ ሲሆን ለሌሎች አካላት ማቅረቡም ሀጢያት ነው(ኢሳ.42፡8)፡፡

ተጨማሪ መፅሃፍቱ እንደዚህ ዋናውን መፅሃፍ ቅዱስ መጋጨታቸው የተጨማሪ መፅሀፍቱ ምንጭ ከተቃራኒው መንፈስ እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል፡፡

### 4.3.4.7. ሰይጣናዊ አሻራዎች ያለበት መሆኑ

ተጨማሪ መፅሀፍት ከእግዚአብሄር ቃላት ጋር የሚጋጩ መሆናቸውን ከላይ ተመልከተናል፣ በዚህም ምንጫቸው ከዲያብሎስ ሊሆን እንደሚችል ገምተናል ነገር ግን ግምታችንን ትክክል መሆኑን የሚያሳዩ ሰይጣናዊ አሻራዎችን በመፅሀፍቶቹ ውስጥ እንመለከታለን፣ ይህም፣

- ከ66ቱ መፅሀፍት ተቃርነው ከቁርአን ጋር የሚደጋገፉበት ቦታዎች መኖሩ፣
- ለሰይጣን ሽፋን የሚሰጥበት ቦታዎች መኖሩ፣
- የጥንቆላ አሰራር የሚያስተምርበት ቦታዎች መኖሩን

ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 4.3.4.7.1. ከ66ቱ መፅሀፍት ተቃርነው ከቁርአን ጋር የሚደጋገፉበት ቦታዎች መኖሩ

ቁርአንና መፅሀፍ ቅዱስ ተቃራኒ መሆናቸውን በምዕራፍ 2 ተመልከተናል፣ ተጨማሪ መፅሀፍቱ ቁርአንና መፅሀፍ ቅዱሱ እርስ በርስ ሲጋጩ ቁርአኑን በመደገፍ ሲናገሩ እንመለከታለን፣

- ዲያብሎስ ለአዳም አልሰግድም በማለቱ ተጣለ
  መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ዲያብሎስ የተጣለው በትዕቢቱና ራሱን ከእግዚአብሄር ጋር በማወዳደሩ ነው(ኢሳ.14፡12-16, ሕዝ.28፡2 ...) ነገር ግን ቁርአኑ ላይ ስንመለከት ዲያብሎስ የተጣለው "ለአዳም አልሰግድም በማለቱ ነው" (2፡34, 17፡61, 7፡11-13 ...) በዚህ አከራካሪ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መፅሀፍቱ የሚወግኑት ለቁርአኑ ነው፣ በዚህም 3ኛ መቃብያን 1፡15 ላይ ይህንን የቁርአኑን ታሪክ እናገኛለን፡፡
- የሰውና መላዕክት ጋብቻ
  66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ መላዕክት ከሰው ጋር ይቅርና እርስ በርሳቸው ራሱ እንደማይጋቡ ይናገራል(ማቴ.22፡30) ነገር ግን ተጨማሪ መፅሀፍቱ ከዚህ ቃል በተቃራኒ ቁርአኑ ላይ (17፡40) እንደተገለፀው ሰውና መላዕክት እንደሚጋቡ ይናገራል፣

ኩፋሌ 6፡9 "የአዳም ልጆች ... ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው ... የእግዚአብሄር መልአክትም ... አገቡዋቸው፣ ወንዶች ልጆችንም ወለዱላቸው እነሱም ረአይት ናቸው፡፡"

- <u>ምንኩስና</u>
  ተጨማሪ መፅሀፍቱ ስለ ምንኩስናና ተያያዥ ጉዳዮች ይነግሩናል ደብር(1ኛ መቃብያን 19፡1-12፣ ሄኖክ 2፡2)፣ ገዳም(ሲራክ 2፡1)፣ ባሕታዊ(ሲራክ 11፡5)፣ ለዚህ አሰራር ድጋፍ የምናገኘው 66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ሳይሆን በቁርአኑ ላይ ነው(57፡27) ፣ በ66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ አንድም ቦታ ላይ ይህንን ታሪክ አናገኘውም ይባሱኑ በ4.4.1.2 ክፍል እንደተመለከተው እነዚህ አሰራሮች ከ66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ተቃራኒ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡
- <u>ገዳም</u>
  ተጨማሪ መፅሀፍቱ ስለ ገዳም ያስተምራሉ(ሲራክ 2፡1)፣ ለዚህ ቃል ድጋፍ የምናገኘው ቁርአኑ 22፡40 ላይ ነው ነገር ግን በ66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ አንድም ቦታ ላይ ገዳም የሚል ቃል አለመኖሩና ይባሱኑ በ4.4.1.2 ክፍል እንደተመለከተው የገዳም አሰራር ከ66ቱ መፅሀፍ አንፃር ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡
- <u>ለመላዕክቱ</u>
  ተጨማሪ መፅሀፍቱ ስለ መላዕክተ አማላጅነት ያስተምራሉ፣ በ66ቱ መፅፍት አማላጅ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ በ4.1.1.2 ክፍል ተመልክተናል፣ የመላዕልት አማላጅነት አስተምህሮ ከየት እንደመጣ ስንመለከተው ቁርአኑ(53፡26) ላይ ነው የምናገኘው፡፡
- <u>ለቅዱሳን</u>
  ተጨማሪ መፅሀፍቱ ስለ መላዕክተ አማላጅነት ያስተምራሉ፣ በ66ቱ መፅፍት አማላጅ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ በ4.1.1.3 ክፍል ተመልክተናል፣ ይህ የቅዱሳን ሰማያዊ አማላጅነት አስተምህሮ ግን ክርስቲያናዊ ሳይሆን ቁርአናዊ ነው(40፡7)፣
- <u>ለሴቶች ያለው ጥላቻ</u>
  66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ገላ.3፡28 "... ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡" ቢልም ተጨማሪ መፅሃፍቱ

ግን ከዚህ በተቃራኒ ከቁርአኑ ጋር በአንድ መንፈስ ለሴቶች በዖታቸው ብቻ ያለውን ጥላቻ እንመለከትበታለን፣

- ሲራክ 42፡13 "ከልብስ ብል ይገኛል ኃጢያትም ሁሉ ከሴቶች ይገኛል፡፡
- ሲራክ 25፡21 "መቅሰፍት ናትና ጥፋትም ናትና ፅኑ ውርደትም ናትና የሴት መልከዋ አያስትህ"
- ሲራክ 42፡14 "ከሴት ቸርነት የወንድ ንፍገት ይሻላል፡፡"
- ሲራክ 25፡24"… ለሴትም የልብህን ምስጢር አታውጣላት፡፡"
- ሲራክ 9፡2 "ምስጢርህን እንዳታወጣብህ ለሴት ልብህን አትስጣት፡፡"
- ሲራክ 42፡9 "ሴት ልጅ ላባቷ የተሰወረ ቁርጥማት ናት፡፡"

ይህ ተጨማሪ መፅሀፍቱ ከቁርአኑ ጋር አንድ ሆነው ከ66ቱ ቅዱሳን መፅሀፍት ጋር መጋጨታቸው የመፅሀፍቱን ምንጭ ያሳያል፡፡

#### 4.3.4.7.2. <u>ለሰይጣን ሽፋን የሚሰጥበት ቦታዎች መኖሩ</u>

66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ሰይጣን አሳሳች፣ ክፉ … መሆኑን ይናገራል ተጨማሪ መፅሀፍቱ ግን ከዚህ በተቃራኒ ሰይጣን እንደ እግዚአብሄር፣ ቅዱሳንና መላዕክት መሆኑን የሚያሳዩ ቃላትን ይዘው እንመለከታለን፣

1. <u>ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሄር? ወይስ ሰይጣን?</u>
   <u>ሰይጣን</u>
   ኩፋሌ 14፡2 "ሁሉን የሚገዛ ሰይጣን …"
   <u>እግዚአብሄር</u>
   ራዕ. 19፡6-15 "… ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሄር …"
2. <u>ሰውን የሚጠብቀው እግዚአብሄር ወይስ ውቃቢ?</u>
   <u>ውቃቢ(ሰይጣናዊ ሀይል)</u>
   ኩፋሌ 15፡16 "መልአክ ውቃቢ ለበጎ ነገር ይጠብቅህልና …"
   <u>እግዚአብሄር</u>
   መዝ.121፡5 "እግዚአብሄር ይጠብቅሀል፡፡"
3. <u>በቅዱሳን ስም የሚሰራ የተቃርኖ መንፈስ - ህግን በልቦና መፃፍ የማን ድርሻ ነው?</u>
   <u>ሄኖክ</u>

ሄኖክ 4፡5 "ህግን በሰው ልቦና የምፅፍ እኔን ሄኖክን ..."
ሄኖክ 4፡68 "... ህግን በሰው ልቡና የምትፅፍ ሄኖክ ..."
<u>እግዚአብሄር</u>
ዕብ.10፡15-16 "ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፤ በልባቸው ህጌን አኖራለሁ በልቡናቸው እፅፈዋለሁ፡፡" እዚህ ጋር ራሱን "ሄኖክ" ብሎ የቀረበው ራሱን ከእግዚአብሄር ጋር የሚያወዳድር የእግዚአብሄር ተፎካካሪ መንፈስ ነው፣ እሱም ዲያብሎስ ነው፡፡

4. **<u>በመላዕክት ስም የሚሰራ የተቃርኖ መንፈስ</u>**

ሄኖክ 19፡1 "በዚያችም ቀን ቅዱስ ሚካኤል <u>የመንፈስ ቅዱስ እውቀቱ ወደ ሀዘን ይወስደኛል ያበሳጨኛል</u> ብሎ ለቅዱስ ሩፋኤል መለሰለት፡፡"

እዚህ ጋር በ"ሚካኤል" ስም ራሱን የሰየመው አካል፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተደጋጋፊነት ሳይሆን በተቃርኖ አሰላለፍ ያለ ሀይል ነው፣ እሱም ዲያብሎስ ነው፣ ብስጭቱም የመጣው መንፈስ ቅዱስ የዲያብሎስን ዕቅድ አስቀድሞ ለቅዱሳኑ ስለሚያሳውቅ ነው፡፡ በዚህም ዲያብሎስ በ"ሚካኤል" ስም በዚህ መፅሀፍ በኩል እንደሚሰራ እንመለከታለን፡፡

መፅሀፍ ቅደሱ ይህ አሰራር ሊኖር እንደሚችል ቀድሞውኑ በማስጠንቀቁ ግራ መጋባቶች እንዳይፈጠሩ ረድቶናል፣
2ቆ.11፡14 "ይህ ድንቅ አይደል፤ ሰይጣን ራሱ የብርሀን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል፡፡"

5. **<u>ቅዱሱን መንገድ መሳደቡ</u>**

ራዕ.13፡6 "እግዚአብሄርን ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይ የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ፡፡" ይህንን ተሳዳቢ መንፈስ በመፅሀፍቶቹ ውስጥም እንመለከተዋለን፣

- ተረፈ ኤርምያስ 7፡2 "... <u>ዋጋ የሌለውን ክርስቶስን</u> ይሸጡታል፣ ከበሽታ የሚያድነውን ጌታን <u>እንዲታመም</u> ያደርጉታል፡፡"
  ምን ማለት ነው "ዋጋ የሌለውን ክርስቶስን" ማለት? "እንዲታመም ያደርጉታል" ሲባልስ ኢየሱስ መቼ ታመመ? የታመሙትን ፈወሰ እንጂ?

- ተረፈ ኤርምያስ 8፡21 "ኤርምያስም ለወገኖቹ ሲያለቅስ እያዳፉ አወጡት፤ ከህዝቡም ጋር እስከ ባቢሎን ድረስ ወሰዱት፡፡"
  የሚገርመው ኤርምያስ በባቢሎን ምርኮ ወቅት ወደ ባቢሎን አልተወሰደም ከቀሪ ሰዎች ጋር ነው በሀገሩ የቀረው(ኤር.40፡2-6)፣ በዚህም ኤርምያስን ያዳፉት ተጨማሪ መፅሀፍቱን የፃፉትና የሚከተሉት ሰዎች እንጂ ባቢሎናውያኑ አይደሉም፡፡

በዚህም ተጨማሪ መፅሀፍቱ የተፃፉበትን መንፈስ እናስተውላለን

6. **<u>መፅሀፍ ቅዱሱ "የውሸት አባት የሚለው ሰይጣን መልአክ መስሎ መመልከቱ?</u>**

መልአክና ሰው ይለያያሉ ነገር ግን እዚህ ጋር "መልአክ ነኝ" ብሎ የቀረበው "መልአኩ" ሩፋኤል በሰው አምሳል ከመቅረቡ በተጨማሪ ሌሎች ውሸቶችንም ሲናገር እንመለከተዋለን፣

- ጦቢት 5፡1-2 "እርሱም(ልጁም) ሰውን ሊፈልግ ሄዶ መልአኩን ሩፋኤልን አገኘው ነገር ግን መልአክ እንደሆነ አላወቀም... (መልአኩም) ... <u>በገባኤል ቤት ነበርኩኝ አለ</u>፡፡"
- ጦቢት5፡12"(መልአኩም) እኔስ <u>የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ዘመድ አዛርያ</u> ነኝ አለው፡፡"
- ጦቢት 12፡19 " ... (እኔ መልአክ ነኝና) ከእናንተ ጋር አልበላሁም አልጠጣሁም ..." ቢልም ከጦቢያ ጋር መመገባቸውን ጦቢት 6፡5 እንዲሁም ጦቢት 7፡14 " ... አሳውን ጠብሰው በሉ" በማለት ሁለቱ አብረው መብላታቸውን እንመለከታለን፡፡

መፅሃፍ ቅዱስ "ምስክር በሁለት ይፀናል"(ማቴ.18፡16) እንደሚለው ይህም "መልአክ" ሶስት ጊዜ ዋሽቶ ቅድስና የሌለው ውሸታም መልአክ መሆኑን በራሱ ላይ አስመሰከረ፣ ስለዚህ ይህ መልአክ ቅዱስ መልአክ አይደለም፣ እርሱም መፅሃፉ ዮሐ.8፡44 ላይ "ሀሰተኛ የሃሰት አባት" የሚለው ዲያብሎስ ነው፣ በዚህም ሩፋኤል ተብሎ የቀረበው መልአክ ዲያብሎስ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡

በዚህም ተጨማሪ መፅሀፍቱ ቅድስና የራቃቸው የዲያብሎስ መልእክቶች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

### 4.3.4.7.3. <u>የጥንቆላ አሰራር የሚያስተምር ቦታዎች መኖሩ</u>

ጥንቆላ ሰይጣናዊ አሰራር መሆኑን መፅሀፍ ቅዱሱ ያስተምረናል፣ ይሁን እነጂ ተጨማሪ መፅሀፍቱ ውስጥ ይህ የጥንቆላ አሰራር ቅዱስ ተደርገው ሲዘገቡ እንመለከታለን፣

- ከላይ የተመለከተው ራሱን መልአኩ ሩፋኤል ነኝ ብሎ ሲሸውድ የነበረው ሰይጣን እዚህም ደግሞ የጥንቆላ ስራ ሲያሰራ እንመለከተዋለን፡፡

  <u>ጦቢት 6፡6-8</u> "... ያም ልጅ መልአኩን አንተ ወንድሜ አዛርያ የዚህ አሳ ሀሞቱና ጉበቱ ለምንድነው አለው፡፡ መልአኩም ክፉ ጋኔን ያደረበት ቢኖር ወይም የረከሰ ረቂቅ ጋኔን ያደረበት ቢኖር (የአሳውን) ጉበቱና ልቡን ለዚያ ሰው በፊቱ ያጤሱለታል ሴትም ብትሆን ያጤሱላታል ከዚያ በኋላ አይታመምም፡፡ ብልዝ ባለበት ሰው አሞቱን ደቁሰው ይኩሉታል፡፡"

  <u>ጦቢት 6፡15-17 እና ጦብያ 8፡1-3</u>"... (መልአኩም ጦቢያን) የጋኔኑ ነገር ግን አያሳዝንህ፡፡ ወደ ጫጉላ ቤት በገባህ ጊዜ የደቀቀ እጣን ከዚህም አሳ ከልቡ፣ ከጉበቱ አምጥተህ አጢስበት፡፡ ያንን ጋኔኑ በሸተተው ጊዜ ይሸሻል ለዘለአለሙ አይመለስም(አለው)፡፡

  ወደርሷም በገባ ጊዜ የሩፋኤልን ነገር አሰበ የደቀቀ እጣን አምጥቶ የዚህን አሳ ጉበቱንና ልቡን ጨምሮ አጤሰው፡፡ ያም ጋኔን መዓዛው በሸተተው ጊዜ እስከ ላይኛው ግብፅ አውራጃ ድረስ ሸሸ፡፡ ይኸም መልአክ ጋኔኑ አስሮ አጋዘው፡፡"

- <u>በቀይና በጥቁር የሚፃፈውን የጥንቆላ አሰራር</u>

  <u>ሄኖክ 19፡16-22</u> "የሙቶ አጋንንት አዝማች ... አራተኛውም ስሙ ፔንሙን ይባላል ... (ለሰው ልጆች) የተሰወረ ጥበብን ሁሉ አስተማራቸው ... በጥቁር ቀለምና በቀይ ቀለም ፅፈው <u>ሀይማኖታቸውን ሊያፀኑ</u> ሰው እንዲህ ያለ ስራ አልተፈጠረም ነበርና..."

  ፔንሙን የተባለው ሰይጣን ጠንቋዮችና ደብተራዎች የሚጠቀሙበት የጥቁርና ቀይ ቀለም አፃፃፍ ዘዴ ማስተማሩ እሱም ደግሞ እግዚአብሄር ሰዎች እንዲሰሩት ላልፈለገው ጥንቆላ (ሰው ላልተፈጠረለት ስራ) ነው

ብሎ በግልፅ መናገሩ ይህም ደግሞ ለህይማታቸው ጥቅም ነው ማለቱ አሳዛኝ ነገር ነው፡፡

እነዚህን እውነታዎች ስንመለከት መፅሀፍቱ ቅድስና የራቃቸው፣ ሰይጣን ወደ ቤተክርስቲያንዋ ተደግፎ የገባበት መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

## ማጠቃለያ(ቅድስናቸው ሳይፈተሽ …)

በአጠቃላይ ስንመለከት የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በ66ቱ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ የጨመሩት መፅሀፍ፣ ከ66ቱ የመፅሀፍ ቅዱሱ መፅሀፍት በተለየ እስራኤል የማታውቀው ብሉይ ኪዳን መሆኑ፣ ወጥ ሀይማኖታዊ መመርያ መፅሀፍት አለመሆናቸው፣ በመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥም ትክክለኛ ቦታ አጥተው መቸገራቸው፣ እርስ በርስ መጋጨታቸው፣ መቼታቸው የተፋለሰ መሆኑ፣ ከዋናው 66ቱ መፅሃፍት ጋር መጋጨታቸው፣ ተረቶች፣ ግራ የተጋቡ፣ ሰይጣናዊና ቁርአናዊ አስተምህሮቶች መያዛቸው፣ እነዚህ ተጨማሪዎቹ መፅሃፍት የእግዚአብሄር ቃላት አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ቅድስና የጎደላቸውን መፅሀፍት ከቅዱሱ ከ66ቱ መፅሀፍት ጋር መቀላቀሉ ሀጢያት ነው፣ ሀጢያቱንም በፀሃፊዎቹ ላይ ብቻ አድርጎ መመልከቱም ሌላ ስህተት ነው፣ እነዚህን መፅሃፍት ከቅዱሳኑ ጋር ቀላቅሎ ያሳተመ፣ ያከፋፈለ፣ የሸጠ፣ ቅዱሳት መፅሀፍት አድርጎ ያነበበ … በሙሉ ከተጠያቂነት አያመልጥም፡፡

ዕርኩስ ነገር ከቅዱሱ የመቀላቀል ታሪክ በመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጥ የተለመደ ታሪክ ነው፣ ምክንያቱም ሰይጣን በህይወት ስላለ፣ እንደዚሁ ደግሞ እውነታው ሲገለጥ እርኩሱን ነገር ከቅዱሱ መለየቱና ማስወገዱም የተለመደ የታሪክ ሂደት ነው(2ዜና.29፡5, 2ዜና.34፡33 …)፣ ስለዚህ እነዚህን ርኩስ ፅሁፎች ከቅዱሱ ለይቶ ማስወገድ ከቅዱሳን ይጠበቃል፡፡

## 4.4. ከዋናው መፅሀፍ ቅዱስ የሚጋጩ ትውፊቶች

[97]ትውፊት ማለት ከጥንት ጀምሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ ቃል በቃል ሲወራረድ የመጣ ዕምነት፣ ስርአት፣ ባህልና ልማድ ማለት ነው፡፡ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ያልተጠቀሱትን ስርአቶች፣ ባህሎች … ከትውፊት እንዳገኘች ትናገራለች፣ በዚህም እነዚህን ሁለት መመሪያዎች "የተፃፈውና ያልተፃፈው" የእግዚአብሄር ቃል ትላቸዋለች፡፡

ቤተክርስቲያንዋ የትውፊት አሰራሮቿንም መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ትናገራለች፡-

- መፅሀፍ ቅዱሱ ሳይፃፍ በፊት ቤተክርስቲያን በትውፊት ስትመራ ነበረ፣ ለምሳሌ ሙሴ ብሄረ ኦሪታትን፣ ሐዋርያቱም አዲስ ኪዳንን በመፅሀፍ እስኪፅፉ ድረስ ህዝቡ በቃል በሚነገረው ትምህርት(ትውፊት) ሲመራ ነበረ፣
- የወንጌሉ እውነታ በሙሉ አለመፃፉ(ዮሐ.21፡25) እና ሐዋርያቱም "መጥቼ በአፍ እነግርሃለሁ" ማለታቸው(2ዮሐ1፡12, 3ዮሐ.1፡14…)፣ በአፍ የሚተላለፈው "ያልተፃፈው የእግዚአብሄር ቃል" መኖሩን ያሳያል፣ ይህንን ቃል ደግሞ የምናገኘው በትውፊት ነው፣
- በቀደመውም ቤተክርስቲያናት በመፅሀፍ ያልተፃፉ፣ ስርአት፣ ወግ … የሚባሉ አሰራሮች ነበሩ (1ቆሮ.11፡2, 1ቆሮ.11፡16, 2ተሰ.2፡15 …)፣ ይህም ትውፊት ማለት ነው፡፡

የሚሉ መከራከሪያዎችን ታቀርባለች፣ እነዚህን መከራከሪያዎች አንድ በአንድ ብንመለከት፣ በመጀመርያ ላይ የተጠቀሰው "መፅሀፍ ቅዱሱ ሳይፃፍ በፊት ቃሉ በአፍ ብቻ ነበረ" የሚባለው ትክክል ቢሆንም ነገር ግን በቃል የነበረው በመፅሀፍ ቅዱሱ ከተፃፈ በኋላ ይህ መከራከርያ ሊሆን አይችልም፡፡

በሁለተኛ ላይ የምንመለከተውም መከራከሪያ፣ አሳማኝ መከራከርያ መሆን አይችልም ምክንያቱም ዛሬ ሐዋርያቱ በህይወት ስለሌሉ በነሱ አፍ

[97] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት፣ የሰንበት ትምህርቶች ማደራጃ መምሪያ፣ https://eotcssd.org

እንዲነገረን የምንጠብቀው ነገር የለም፣ አሁን እነሱ የሚናገሩን በመፅሀፍ ቅዱስ በኩል ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የተፃፈው ደግሞ ለመዳን በቂ መሆኑን እራሱ መፅሀፍ ቅዱሱ ይነግረናል(ዮሐ.20፡30)፣ ይህም ከሌላ ሰው አፍ የምንጠብቀው ተጨማሪ ነገር እንደሌለ ያሳየናል፡፡

በሶስተኛ ላይ የቀረበው መከራከርያ ትክክል ነው፣ በቤተክርስቲያናት ውስጥ የአሰራር ስርአቶችና ወጎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ከመፅሀፍ ቅዱሱ ቀጥሎ በስርአትና በወግ መመራቷ በመርህ ደረጃ ትክክል መሆኑን እንመለከታለን፤ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ከትውፊት ጋር በተያያዘ ትልቅ ችግር የሆነው አብዛኛው የቤተክርስቲያኗ ትውፊቶች ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጋር የሚጋጩ መሆኑ ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ደግሞ በትውፊት የሚተላለፍ ማንኛውም ስራአትና ወግ በፅሁፍ ከሚተላለፈው ከዋናው መፅሀፍ ቅዱስ ጋር ሊጋጭ እንደማይገባ ይናገራል(ማቴ.15፡3-6, ማር.7፡9 …)፣ በዚህም ትውፊት ከመፅሀፍ ቅዱሱ ከተጋጨ ትውፊቱ መስተካከል ያለበት ትውፊት ነው፡፡

በቤተክርስቲያኗ የሚታዩት መስተካከል የሚገባቸውን ትውፊቶችን ስንመለከት በሁለት ይከፈላሉ፣ እነሱም የተሳሳቱና አጋንንታዊ ትውፊቶች ናቸው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

### 4.4.1. <u>የተሳሳቱ ትውፊቶች</u>

ዋነኞቹ የተሳሳቱ ትውፊቶችም፣ ለሙታን የሚከናወነው ተዝካር፣ በገዳምና በበረሀ ከሰው ተለይቶ መኖር፣ የተሳሳተ የጥምቀት ስነስርአትንና ዝማሬን በያሬዳዊ ስልትን መገደብ ሲሆኑ፣ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 4.4.1.1. <u>ተዝካር</u>

ቤተክርስቲያንዋ ራሷን በእግዚአብሄር የፈራጅነት ወንበር ላይ በማስቀመጥ ሟቾችን “ቅዱሳንና ኃጥአን” በማለት በሁለት ትከፍላቸዋለች፣ ከዚህ በመቀጠልም “ኃጥአን” ያለቻቸውን ለሀጥያታቸው ስርየትና ነፍሳቸውን ከሲኦል ወደ ገነት ለማስገባት የተዝካር ስነስርአቶችን ታከናውናለች፡፡

ይህ ትውፊት ትክክለኛ ቢሆን ኖሮ በትጋት ሊደረግ በተገባ ነበረ፣ ከዘመድ አዝማድ ባለፈም ለሌሎች በሲኦል ላሉት ለሰው ዘሮች በሙሉ

እንኳን ሊደረግ በተገባ ነበረ ምክንያቱም አንድን ነፍስ ከሲኦል አውጥቶ ገነት ማስገባት ከተዝካር ድካምና ወጪ ጋር የማይነፃፀር ነውና ነገር ግን ይህ ምኞት እንጂ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እውነታ አይደለም፣ ምክንያቱም፡-

1. የሰዎች መዳንና በፍርድ ስር መውደቅ የተወሰነው ዛሬው ነው፣

   መፅሀፍ ቅዱስ፣ የመዳን ቀን ዛሬ ነው ይላል(2ቆሮ.6፡2) በዚህም በማን ላይ ምን አይነት ፍርድ እንዳለበት ዛሬውኑ የታወቀ ነገር ነው፣

   ዮሐ.3፡18 "በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሄር ልጅ ስላላመነ <u>አሁን</u> ተፈርዶበታል፡፡"

   ፍርዱ አሁን አልቋል ከሆነ ደግሞ እንደ ምድራዊው ፍርድ ቤት በሰማይ የይግባኝ አሰራር የለም ምክንያቱም እሱ አይሳሳትም እንዲሁም ይግባኝ የሚባልበት የበላይ አለቃ የለውም፡፡

2. በአፀደ ነፍስ የሚሰጥ ዕድል አለመኖሩ

   ዕብ.9፡27 "ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት **<u>ከእርሱ በኋላ</u>** ፍርድ ተመደበባቸው፡፡"

   በዚህም አንድ ሰው በአፀደ ነፍስ ህይወቱ ምንም የሚሰጠው ተጨማሪ እድል የለውም፡፡

የሰዎች ሀጢያት የሚቆጠረውም ሆነ የሚሰረየው ያ ሰው በህይወት እያለ ባለው እምነት እንጂ ከሞተ በኋላ የባለቤቱ አስተዋፆ በሌለበት ሌሎች በሚያደርጉለት ስነስርአት አይደለም፣ በዚህም ከሞት በኋላ ያለው ነገር የተዘጋ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም ለሞቱት ሰዎች ተብሎ ገንዘብ እየገፈገፉ በየጊዜው በመደገስ ገነት ለማስገባት መሞከር ስህተት ነው፣ በሃብት ብዛት ሆነ እጦት፣ በዘመደ ብዝሀነትና በዘመድ ማጣት፣ የፈጣሪ ፍርድ አይቀየርም፣ በመንግስተ ሰማያትም በሰለስት፣ በአርባ፣ በሰማንያ፣ በአመትና በሰባት አመት የሚደረግ የይግባኝ አሰራር የለም፣ <u>በክርስቶስ ደም ያልዳነ በተዝካር ድግስ አይድንም</u>፡፡

ስለዚህ የተዝካር ድግስ ተማምናችሁ ያላችሁ እሱን ትታችሁ የሀጢያት ስርየት ዋስትና የሆነውን ኢየሱስን ዛሬውኑ በአግባብ መያዙ ይጠቅማችኋል፣ ቤተክርስቲያንም ብትሆን ምዕመናኖቿ በተዝካር ድግስ ተማምነው እንዲሄዱ ከማድረግ መፅደቂያውን መንገድ እንዲያውቁ ብታስተምር መልካም ነው፡፡

### 4.4.1.2. <u>በገዳምና በበረሀ ለመንፈሳዊ ህይወት ተለይቶ መኖር</u>

እንደ ኦርቶዶክስ/ካቶክ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ አንድ ሰው ይህን ህይወት የሚመራው ስጋን በመጨቆን ከሀጢያትና ዓለማዊ ነገር በመራቅ ራሱን ለመንፈሳዊው ህይወት በመለየት በፆምና በፀሎት በገዳማትና በበረሀ የሚኖርበት ህይወት ነው፡፡ በዚህም በየገዳማትና ቤተክርስቲያናት የሚኖሩቱ መነኩሴ ሲባሉ በየበረሃው የሚኖሩቱ ደግሞ ባህታዊ ይባላሉ፡፡

ለዚህ አይነት ህይወት ቀጥተኛ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ባይኖርም በቤተክርስቲያኗ አካባቢ በተምሳሌትነቱ የሚነሳው ኢየሱስና ዮሐንስ ከሰው ተለይተው በረሀ የኖሩበት ኑሮ ነው፡፡

ነገር ግን ኢየሱስና ዮሐንስ ከሰው ተለይተው ወደ በረሀ የወጡት <u>ለተወሰነ አላማና ጊዜ</u> እንጂ እዚያ ሊኖሩ አይደለም፣ ከጊዜ በኋላም ለአገልግሎት ወደ ህዝብ በመውጣት የወንጌል ስብከት፣ የማጥመቅ ... አገልግሎት ሲሰሩ ነበረ፤ የምንኩስናና የባህታዊነት ህይወት ስንመለከት ግን ከዚህ ይለያል፣ ገዳምና በረሀ የሚኬደው እንደ ኢየሱስና ዮሐንስ <u>ለተወሰነ አላማ</u> እና <u>ለተወሰነ ጊዜ</u> ሳይሆን ለመኖር ነው፣ በዚህም ሁለቱ ሀሳቦች የተለያዩ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ደግሞ ይህ አይነት ህይወት ከመፅሀፍ ቅዱሱ መርህ የተቃረነ ነው፣ የመፅሃፍ ቅዱሱ እውነታ የበራለት ሰው እራሱም ብርሃን እንደሆነው(ማቴ.5፡14) ለሌሎችም ይህንኑ ብርሃን በማብራት ሌሎችን ከጨለማው አሰራር ሊያወጣ ያስተምራል እንጂ ለራሱ ሲገባው ብርሀኑን ይዞ አይደበቅም፣

> ማቴ.5፡15 "መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል፡፡"

የያዙትን ብርሀን ለሌሎች አለማብራቱ ደግሞ በራሱ ሀጢያት ነው፣ ይህንንም እውነታ በማቴ.25 ላይ በምንመለከታቸው መክሊት በተሰጣቸው ሰዎች ህይወት ውስጥ መመልከት ይቻላል፣ አንድ መክሊት የያዘው ባለማትረፉ "ያለውንም ተቀበሉት" ሲባል እንመለከታለን፡፡

ከዚህ መሠረታዊ ተቃርኖ በተጨማሪም እነዚህ ሰዎች ፅድቅን ለማግኘት የሚከተሉት አሰቃቂ "መዳኛ" መንገዶች አዲስ ኪዳናዊ የፅድቅ መንገድ አይደለም፣ ይህም ከቀላሉ በባዶ እግር መሄድ አንስቶ፣ ጨሌ ሲቆጥሩ መዋል፣ መፅሀፍትን ማነብነብ፣ በጨሌ ሰውነትን መግረፍ ... እስከ ... ከዚህ በታች የቀረቡ "የቀደምት ቅዱሳን መዳኛ መንገድ" እስከተባሉት መንገዶች ልምምድ ይደርሳል፣

- [98] "አቡነ አካለ ክርስቶስ ከአንድ ቦታ ሳይንቀሳቀስ የወይራ ዛፍ ተደግፎ ለ40 አመት በመፀለይ ከእግዚአብሄር ጋር ተገናኝቷል፡፡"
- [99] "አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለአርባ ቀን ከባህሩ በራሳቸው ቆመው ይፀልዩ ነበር ... እግራቸውንም በገመድ አስረው በታላቅ ገድል ቁቁል ተሰቀሉ ሰይጣንም ገመዱን በጠሰው፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ተቀበላቸው "ተወኝ በራሴ ልቁም" አሉት በጥርሳቸው ድንጋይ ነክሰው ሰላሳ አመት አልቅሰዋል፣ ጌታ ምሬሀለሁ ብሏቸው ጥርሶቻቸው በድንጋይ ላይ ተተክለው ቀርተዋል፡፡"
- [100]"አቡነ ተክለሀይማኖት በቁመታቸው ልክ ጉድጓድ ቆፍረው ከፊት ከኋላቸው ከቀኝ ከግራቸው ስምንት ጦር ተክለው ሱባኤ ያዙ፡፡ ከቁመት ገድል የተነሳ አንድ እግራቸው ተቆርጦ ወድቋል፣ ከዚህ በኋላ በአንድ እግራቸው ቆመው 7 አመት ኖረዋል፡፡"
- [101] "ቅዱስ ነኩቶ ለአብ በቁመቱ ልክ ጉድጓድ አስቆፍሮ በዙሪያው ጦር አበጅቶ ለአርባ አመት ሲሰግድ ነበረ፡፡"
- [102] "ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ ከመከራዋ ብዛት ከገድልዋ ጽናት ሰውነቷ ተበሳስቶ የዓሳ መመላለሻ እስኪሆን ድረስ ከባህሩ ገብታ ወደ ግራና ቀኝ ሳትል አስራ ሁለት አመት ፀልያለች፡፡ በፍፃሜ ዘመኗ በቁመቷ ልክ

[98] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፩**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ገፅ 103
[99] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፩**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ ገፅ 71
[100] Ibid, ገፅ 62
[101] Ibid, ገፅ 58
[102] Ibid, ገፅ 69

በዓት ሰርታ ከግራ ከቀኝ ከፊት ከኋላ አስራ ሁለት ጦር ተክላ ወዲህ ወዲያ ሳትል አስራ ሁለት አመት ኖራለች፡፡"

- [103] "ቅድስት አመተ ክርስቶስ ለ48 አመት ያህል ሳትንቀሳቀስ እንደ አቡነ ተክለሀይማኖት የፀለየች ሰው ናት፡፡"

በርግጥ አንዳንዶቹ ታሪኮች እውነተኛነታቸው አጠራጣሪ ነው ነገር ግን መነኮሳቱና ባህታውያኑ የሚማሩትና የሚለማመዱት የፅድቅ መንገድ ይህ መንገድ ነው ነገር ግን አዲሱ ኪዳኑ ፅድቅ የሚገኘው ለራስ ሀጢያት ዋጋ መከራን በመቀበል ሳይሆን ስለ ሰዎች ሀጢያት መከራን በከፈለው በኢየሱስ በማመን ብቻ "እንዲያው" እንደሚድኑ ይናገራል፣

- ሮሜ.3፡24 "በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል <u>እንዲያው</u> በፀጋው ይፀድቃሉ፡፡"
- ራዕ.21፡6 "አልፋና ያሜጋ የመጀመርያውና መጨረሻው እኔ ነኝ ለተጠማ ከህይወት ውሀ ምንጭ <u>እንዲያው</u> እኔ እሰጣለሁ፡፡"
- ራዕ.22፡17 "መንፈሱና ሙሽራው "ና" ይላሉ፣ የሚሰማም "ና" ይበል፣ የተጠማም ይምጣ፣ የወደደም የህይወትን ውሃ <u>እንዲያው</u> ይውሰድ፡፡"

በዚህም የምንኩስናና የባህታዊነት ህይወት የመፅሀፍ ቅዱሱ አስተምህሮ የተቃርኖ ጉዞ መሆኑና ይባሱኑም ለራስም ነፍስ መዳን የሚያሳጣ መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በርግጥ መንፈሳዊውን ነገር ከስጋዊው ነገር አስበልጦ ለመንፈሳዊ ነገር መለየት ቆራጥነትን ይጠይቃል ነገር ግን አሰራሩ ከመፅሀፍ ቅዱሱ ተቃራኒ ነው፣ ለዚህም ነው "ገዳም"፣ "ምንኩስና" የሚል ቃል መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አጥተን የመፅሀፍ ቅዱሱ ተቃራኒ በሆነው ቁርአኑ ላይ የምናገኘው፣ ምንኩስና(57፡27)፣ ገዳም(22፡40) ... በዚህም በተቃራኒው መንፈስ ሴራ ላይ መንቃቱ መልካም ነው፡፡

[103] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፩**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባኤያት)ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ ገፅ 104

#### 4.4.1.3. <u>የተሳሳተ አጠማመቅ</u>

ቤተክርስቲያንዋ የጥምቀት ስርአትን በዋናነት ውሃ በመርጨት ትፈፅማለች፣ ለዚህም የምታቀርበው፣

> ሕዝ.36፡25 "ጥሩ ውሀንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ፣ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ፡፡"

የሚለውን ቃል ነው፣ ይህ ቃል ለብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች በሚገባ መንገድ የተነገረ የትንቢት ቃል ነው፡፡

በአዲስ ኪዳን ዘመን የጥምቀት ስነስርአት የሚፈፀመው ተጠማቂውን ሙሉ በሙሉ ውሀ ውስጥ በማስገባት ነው፣ ለዚህም ነው ዮሐንስ ኢየሱስን፣ ፊሊጶስም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ለማጥመቅ ወደ ወንዝ መሄድ ያስፈለጋቸው እንዲሁም "ከውሀው ሲወጣ" የተባለው(ማር.1፡9-10, ሐስ.8፡38-39 ...)፡፡

በርግጥ ይህ የአዲስ ኪዳኑ ሰውነትን ሙሉ በሙሉ ውሀ ውስጥ በማስገባት የሚፈፀመው አጠማመቅ ዘዴ ዝም ብሎ የመጣ ሰውኛ ስርአት ሳይሆን የራሱ መንፈሳዊ ፍቺ አለው፣ ይህም፡-

> ሮሜ.6፡3-4 "... ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ህይወት እንድንመላለስ፣ <u>ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን፡፡ ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሳኤውንም በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን</u>፤"

በሚለው ቃል መሠረት ነው፣ በዚህም የጥምቀት ምሳሌ፣ ኢየሱስ ሞቶ እንደተቀበረውና እንደ ተነሳው ሰውም በጥምቀት ውሃ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ገብቶ በመውጣት ከክርስቶስ ጋር ያለውን "የህብረት ኪዳን" የሚፈፅምበት ስነስርአት ነው፡፡

ስለዚህ የአዲስ ኪዳኑ አጠማመቅ ተጠማቂውን ሙሉ በሙሉ ውሃ ውስጥ በማስገባት መከናወን አለበት፣ የቤተክርስቲያንዋ መመሪያ "ፍትሀ

ነገስት" ምዕራፍ 3 ላይ የታዘዘው ይኸው ሰውነትን ሙሉ በሙሉ ውሀ ውስጥ በማስገባት የሚፈፀመው የአጠማመቅ ስነስርአት ነው፡፡

በሌላ በኩል ቤተክርስቲያኒቱ በየአመቱ በምታዘጋጀው የጥምቀት በዓልዋ አማኙን በሙሉ ታጠምቃለች፣ ይህንንም የምታደርገው በሕዝ.36፡25 መሠረት ለሀጢያት ስርየት መሆኑን ትናገራለች፣ በርግጥ አንድ ሰው ለመጀመርያ ጊዜ ሲጠመቅ እስከዚያን ጊዜ ድስ ያለው ሀጢያቱ ይሰረይለታል ነገር ግን ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ (ኤፌ.4፡5) "ለሀጢያት ስርየት" ብሎ በየጊዜው ማጥመቁ መፅሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣ ከመጀመርያው ጥምቀት በኋላ የሀጢያት ስርየት የሚፈፀመው በንስሃና ከሀጢያት በመመለስ፣ ለበደሉን ይቅርታ በማድርግ(ሉቃ.11፡4)፣ በመመፀወት(ዳን.4፡27)፣ ለሰዎች ፍቅርን በማብዛት(1ጴጥ.4፡8) እና የእግዚአብሄርን ቤት በመቀደስ ነው(ኢሳ.27፡9) ነው፡፡

ስለዚህ ጥምቀት በትክክለኛው የአዲስ ኪዳን የአጠማመቅ ስርአትና የአንድ ጊዜ ጥምቀት ስርአት አሰራር ሊተገበር ይገባል፡፡

#### 4.4.1.4. <u>ዝማሬን በያሬዳዊ ስልት መገደብ</u>

ቤተክርስቲያንዋ፣ መዝሙር መዘመር ያለበት በያሬዳዊ ስልት (ዜማ፣ የሙዚቃ መሳሪያና እንቅስቃሴ) ብቻ መሆን እንዳለበት ትናገራለች ነገር ግን ይህ የእግዚአብሄርን ቃል ያላገናዘበ አስተምህሮ ነው፡፡

ከመነሻው መዝሙር መዘመር ያለበት በደስታ መንፈስ ነው፣

- ያዕ.5፡13 "… ደስ የሚለው … ይዘምር፡፡"
- መዝ.95፡1 "ኑ፣ በእግዚአብሄር ደስ ይበለን፤ ለአምላክ ለመድሃኒታችን እልል እንበል፡፡"

ሰው ደስ ብሎት አለማምለኩም ሀጢያት ነው፣

ዘዳ.28፡47-48 "ሁሉን አብዝቶ ስለ ሰጠህ አምላክህን እግዚአብሄርን <u>በፍስሃና በሃሴት</u> አላመለክምና በራብና በጥማት በዕራቁትነትም ሁሉንም በማጣት እግዚአብሄር ለሚልክብህ ለጠላቶችህ ትገዛለህ፤ እስኪያጠፋህም ድረስ በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር ይጭናል፡፡"

ነገር ግን ሰው ደስታውን የሚገልፀው በራሱ መንገድ ነው፣ ይህ ደግሞ ሰውየው ባደገበት ባህል፣ በሰውየው ዕድሜ፣ ፆታ … ይወሰናል፣ የዝማሬ ሞዴላችን ዳዊት ይህንን ደስታውን የገለፀው ልብሱን አውልቆ በመዘመር ነው(2ሳሙ.6፡14-23)፣ ይህ ዳዊት ደስታውን የገለፀበት የግሉ መንገድ ነው፣ በዚህም እያንዳንዱ ሰው ደስ ባለው መንገድ መዘመር አለበት በሽብሸባ፣ በጭብጨባ፣ በመዝለል፣ ብሄር ብሄረሰቦች ጋር ደግሞ ከዚህ ሌላ የራሳቸውን ደስታ የሚገልፁበት ሌላ አይነት እንቅስቃሴ ሊኖር ይችላል፡፡

እግዚአብሄር የሚወደው ይህንን ሰዎች ተፈተው በራሳቸው መንገድ የሚያደርጉትን የደስታ ዝማሬን ነው፣ በዳዊት ዝማሬ እግዚአብሄር እጅግ ተደስቶበታል ነገር ግን የዳዊት ሚስት ሜልኮል ይህንን የዳዊትን ደስታ በሰውኛ አእምሮ ተመልክታ “ለምን በዚህ መልክ ዘመርክ” በማለቷ እግዚአብሄር ሲረግማት እንመለከታለን(2ሳሙ.6፡14-23)፣ ዛሬም ዝማሬን በኛ ስልት ካልሆነ ብሎ ለመገደብ መሞከር መርገምት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ያሬዳዊው ስልት የሚጠቀመው ባህላዊውንና በሰሜን ኢትዮጵያ የሚታወቁትን የሙዚቃ መሳሪያዎችን ብቻ ነው ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱሱ ዝማሬን ከደስታ ጋር ስለሚያያይዝ እንደ እንቅስቃሴው ሁሉ የሙዚቃ መሳሪያንም አልገደበም፣ ማንም ደስ ባሰኘው የሙዚቃ መሳርያ መዘመር እንዳለበት ይናገራል፣ በመዝ.150፡1-6 ላይ እንደምንመለከተው ዳዊት በወቅቱ በእስራኤል አካባቢ የሚያውቃቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች ዘርዝሮ ከዚያም ትውልዱን በዚህ ላለመገደብ “እስትንፋስ ባለው ሁሉ” በማለት በሚመጣውም ዘመን በሚፈለሰፉት መልካም የሙዚቃ መሳሪያዎች እንኳን ላለመገደብ ሞክሯል፣ ይህም ማንኛውም ሰው ደስ ብሎት እንዲዘምር ደስታውን በሙዚቃ መሳሪያ ላለመገደብ ነው፡፡

ያሬዳዊ ስልት የሰሜን ኢትዮጵያ ስልት ነው፣ በሀገሪቱ ያለው ሌላው ህዝብ ይህንን ስልት አያውቀውም፣ ከየትኛውም ህዝብ በፊት እግዚአብሄርን የሚያውቀው የእስራኤል ህዝብ የያሬድን ስልት አያውቀውም፣ በዝማሬው መፅሃፍ ቅዱስ የመሰከረለት ከያሬድ በፊት የነበረው ዳዊት የያሬድን ስልት አያውቀውም፣ በአሁኑ ጊዜም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውጪ ጠቅላላው አለም አያውቀውም … ስለዚህ ዝማሬ በያሬድ ስልት መወሰኑ ጠባብተኝነት ነው፡፡

በዚህም ለእግዚአብሄር መቅረብ ያለበትን ዝማሬ ያሬድ በዘመረበት በሰሜኖቹ ስልት፣ ሙዚቃ መሳሪያና እንቅስቃሴ ብቻ ብሎ ዝማሬን መገደብ፣ የብሄር ብሄረሰቦችንና የፈረንጆቹን የሙዚቃ መሳሪያና የዝማሬ ስልት “ስህተት” ማለት ስህተት መሆኑና በ6.2.1 ክፍል ከተመለከቱት ከመዝሙር መራቅ ካለባቸው ዝሙታዊና አጋንንታዊ እንቅስቃሴዎች በስተቀረ ማንኛውም ሰው እንደ ዳዊት ደስ በሚለው ስልት ለአምላኩ በደስታ ሊዘምር ይገባል፡፡

## 4.4.2. አጋንንታዊ ትውፊቶች

በ4.1 ክፍል እንደተመለከትነው ሰይጣን በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም በእጃዙር አምልኮ እየተቀበለ ይገኛል ነገር ግን አልተስተዋለም እንጂ ከዚህ ስውር አሰራር በተጨማሪ ሰይጣን በቤተክርስቲያን ውስጥ ጣዖታትን አስቀምጦ እያሰገደ ይገኛል የራሱ አገልጋዮችም አሉት፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡-

### 4.4.2.1. በቅድስና ስም ተሸፍኖ ቤተክርስቲያን የገባው የስዕል ጣዖት

ቤተክርስቲያኗ የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ... ምስሎችን ለአምልኮ አገልግሎት ትጠቀማለች፣ ለዚህ የምታቀርበው [104] በ1ነገ.6፡23-35 ላይ ሰለሞን በሰራው ቤተመቅደስ ግንብ በውስጥና በውጪ በኩል ያጌጠበት የኪሩቤል፣ የዘንባባንና የፈነዳ አበባ ምስል ነው፡፡

ነገር ግን አሁን በቤተክርስቲያኗ የምንመለከተው ምስል በአይነቱም በአላማውም ከዚህ የተለየ ነው፣ ዛሬ በቤተክርስቲያኗ የምንመለከታቸው ምስሎች ሰለሞን የተጠቀማቸው የኪሩቤል፣ የዘንባባና የአበባ ምስሎችን አይደለም፣ የምንመለከተው የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን ... ምስል ነው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰለሞን ምስሎቹን የተጠቀመው ለማስጌጫነት ነው ነገር ግን በቤተክርስቲያኗዋ የምንመለከታቸው ምስሎች ጥቅም ለማስጌጫነት ሳይሆን ለአምልኮ ነው፣ በዚህም ለስዕሎቹ ይማተባል፣ ይሰገዳል፣ ይፀለያል፣ ሻማ ይበራል ... በዚህም ጉዳዩ ከሰለሞን ቤተመቅደስ ታሪክ ጋር የተለያዩ ናቸው፡፡

---

[104] ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣ **ነገረ ቅዱሳን ፩**፣ ገፅ 33

መፅሀፍ ቅዱሱ ምስል ለአምልኮ መጠቀምን አጥብቆ ይቃወማል፣ የሚቃመውም አጥብቆ በመሆኑም ምንም ክፍተት እንዳይኖር በተለያየ መንገድ በመግለፅ ነው፣

- "በሰማይም ... በምድርም"

  ዘፀ.20፡4-5 "በላይ በሰማይ ካለው፣ በታች በምድር ካለው፣ ከምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውም ምሳሌ፣ የተቀረፀውንም ምስል ላንተ አታድርግ፤ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውም..."

- በወንድም ይሁን በሴት መልክ

  ዘዳ.4፡15-18 "... የተቀረፀውን ምስል የማናቸውንም ነገር ምሳሌ፣ በወንድ ወይ በሴት መልክ የተሰራውን ... እንዳታደርጉ፡፡"

- ለሌላው ይቅርና ለእግዚአብሄር እንኳን እንዳይሳል

  ዘዳ.4፡15-18 "እግዚአብሄር በኮሬብ እሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ፡፡ እንዳትረክሱ፣ የተቀረፀውን ምስል የማናቸውንም ነገር ምሳሌ ... እንዳታደርጉ፡፡"

በዚህም ለቤተክርስቲያን ማስጌጫነት ከሚሰሩት ምስሎች ውጪ መንፈሳዊ ትርጉም ያላቸውን ምስሎች መስራቱም ሆነ አስቀምጦ መስገዱ፣ መፀለዩ፣ ሻማ ማብራቱ ..." አደጋ እንዳለው እንመለከታለን፡፡

ማርያም/መላዕክት/ፃድቃንና ኢየሱስ ፎቶ ተነስተው ቢሆን ኖሮ በቤተክርስቲያኗ ያለው የስዕል አምልኮ የእግዚአብሄርን ቃል ከዚህ በላይ በተገዳደረ ነበረ፣ በዚህም አሁን በነሱ ስም ተሰርተው ያሉት ስዕሎች በሙሉ በርግጠኝነት የነሱ አይደሉም፣ ስዕሎቹ የነሱ አለመሆኑና ከዚህም አልፎ ለስዕሎቹ አምልኮ እየቀረበ መሆኑ ደግሞ ስዕሎቹ ሳይስተዋል እየተመለኩ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

ስዕልን ለአምልኮ የመጠቀሙ ልምድ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን አጋንንታዊ መሆኑን መፅሀፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣

ራዕ.13፡14-15 "... ለአውሬውም ምስል እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል ... ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱትን ሁሉ ..."

በዚህም የስዕል አምልኮ ልምምድ የቅዱሱ መንገድ ሳይሆን የአጋንንታዊ መንገድ አሰራር ነው፡፡

አምልኮን የሚፈልጉት ሁለት አካላት ናቸው፣ እግዚአብሄርና ሰይጣን፣ እግዚአብሄር በስዕል በኩል አምልኩኝ ባለማለቱ በስዕል በኩል አምልኮን እየተቀበለ ያለው ሰይጣን መሆኑ ግልፅ ነው፣ ለዚህ ነው የሥዕል አምልኮ ልምድ "አጋንንታዊ ነው" እየተባለ፣ የስዕል አምልኮ በግልፅ በተለያየ ቋንቋ እየተከለከለ፣ በተሳለው ስዕልና በተሳዮቹ መካከል ምንም ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ የስዕል አምልኮ ለዘመናት እየተደረገ የሚገኘው፣ በዚህም በቤተክርስቲያኗ እየተከናወነ የሚገኘው የስዕል አምልኮ የጣዖት አምልኮ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 4.4.2.2. <u>"ታቦት" ተብሎ ቤተክርስቲያን የገባው ጣዖት</u>

በ4.2.3.1 ክፍል እንደተመለከትነው በታቦት በኩል የሚደረግ አምልኮ የብሉይ ኪዳን ዘመን አምልኮ መሆኑና በአዲሱ ኪዳን ፅላቱ/ታቦቱና ቤተመቅደሱ ሰው መሆኑን ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ አዲሱ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ተክቶ ባለመቆሙ ቤተክርስቲያኗ በአዲስ ኪዳኑ ዘመን የብሉይ ኪዳኑ የታቦት አምልኮ ላይ እንደምትገኝ ተመልክተናል፡፡

እውነታው በእንዲህ እያለ አሁን ቤተክርስቲያኗ የምትጠቀመውን ታቦት ምንነት ስንመለከት ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ያውም አደገኛ ስህተት ይዞ እንመለከታለን፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን ታቦት እንዲሰራ ያዘዘው እግዚአብሄር ነው፣ ያዘዘውም ዝርዝር የታቦት አሰራር ዲዛይን በመግለፅ ነው (ዘፀ.25)፣ በዲዛይኑ መሠረትም ዛሬ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን አካባቢ የሚታየው "ታቦት" እና የእግዚአብሄርን ታቦት ስናነፃፅር ፍፁም የተለያዩ ናቸው፡-

1. **<u>በመጠኑ</u>** - እግዚአብሄር ታቦት እንዲሰራ ሲያዝ የታቦቱን ልኬት በመግለፅ ነው፣

    ዘፀ.25፡10 "ከግራር እንጨት ታቦት ይስሩ፣ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን፡፡"

ይህንን የታቦት መጠን አሁን ካለው ታቦት ጋር ስናነፃፅር አሁን ያለው ታቦት የእግዚአብሄር ታቦት አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

2. <u>**በቅርፁና በመልኩ**</u> - ዘፀ.25፡10-20 "ከግራር እንጨት ታቦት ይስሩ፣ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን ... አራት የወርቅ ቀለበቶች አድርግለት፣ እነሱንም በአራቱ እግሮቹ ላይ አኑር ... መሎጊያዎችንም ከግራር እንጨት ስራ ... ለታቦቱ መሸከሚያ በታቦቱ ጎን ባሉት ቀለበቶች መሎጊያዎቹን አግባ ... ከጥሩ ወርቅም ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መክደኛ ስራ፡፡ ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ስራ፣ በስርየት መክደኛው ላይ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ ... ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ይዘረጋሉ፣ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ ..."

   በዚህም የእግዚአብሄር ታቦት ቅርፅና መልክ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፣ ይህም እውነታ ዛሬ በቤተክርስቲያንዋ ታቦት ተብሎ የተቀመጠው "ታቦት" የእግዚአብሄር ታቦት አለመሆኑን ያሳየናል፡፡

3. <u>**በይዘቱ**</u> - ዕብ.9፡4 "... ሁለንተናዋ በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት፣ በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ፅላት ነበሩ፡፡"

   በዚህም አንድ ታቦት "ታቦት" ለመሆን በውስጡ የአሮን በትር፣ <u>የድንጋዩ</u> ፅላት እና መና የያዘ የወርቅ መሶብ ሊኖር ይገባል፣ እነዚህ ሁሉ በታቦት ውስጥ የሚቀመጡት የየራሳቸው ትርጉም ስላላቸው ነው፣ ነገር ግን የቤተክርስቲያኗ ታቦት የእግዚአብሄር ታቦት ባለመሆኑ ከእነዚህ ውስጥ አንዱን እንኳን አልያዘም፡፡

4. <u>**በስሙ**</u> - እግዚአብሄር ያዘዘው ታቦት አሁን ቤተክርስቲያንዋ የምትጠቀምበት አለመሆኑን ከዲዛይኑ በተጨማሪ በስያሜው ማስተዋል ይቻላል፣ የድሮው ሙሉ ስሙ "የእግዚአብሄር የቃልኪዳን ታቦት" ነበረ(ዘዳ.10፡8, ዘኁ.14፡44, ኢያ.6፡8 ...) ነገር ግን አሁን በቤተክርስቲያንዋ የምንመለከተው "የገብርኤል፣ የሚካኤል፣ የአቦ ...

ታቦት" ነው፣ "የ..." ማለት ደግሞ ባለቤትነትን የሚያሳይ በመሆኑ አሁን ያለው ታቦት በርግጠኝነት የእግዚአብሄር አለመሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

5. <u>**በአጋፋሪዎቹ**</u> - የእግዚአብሄርን ታቦት እንዲያጥኑትና እንዲሸከሙት የተመረጡት የሌዊ ዘሮች ብቻ ናቸው፣

 1ዜና.15፡2 "... ከሌዋውያን በቀር <u>ማንም</u> የእግዚአብሄርን ታቦት ሊሸከም አይገባውም፡፡"

 አሁን የምንመለከተው ታቦት የእግዚአብሄር ታቦት ስላልሆነ የሚሸከሙት ከሌዊ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡

መፅሃፍ ቅዱሱ ሊከሰቱ የሚሉትን የስህተት አሰራሮች ቀድሞ በትንቢት ስለሚናገር ይህንን ችግር አስቀድሞ ለሰሚዎች ተናግሯል፣

 ኢሳ.45፡20 "<u>እናንተ ከአህዛብ ወገን ሆናችሁ ያመለጣችሁ</u>፣ ተሰብስባችሁ ኑ በአንድነት ቅረቡ የተቀረፀውን የምስላቸውን እንጨት የሚሸከሙና ያድን ዘንድ ወደ ማይችል አምላክ የሚፀልዩ እውቀት የላቸውም፡፡"

የሚገርመው ደግሞ እዚህ ጋር በዚህ ስህተት ውስጥ የሚወድቁት ህዝቦች ምን አይነት ህዝቦች እንደሆኑ እንኳን ያሳያል፣

- "እናንተ ከአህዛብ ወገን ሆናችሁ" ማለቱ ከእስራኤል ዘር ሃረግ ውጪ ያሉትን ያመለክታል፡፡
- "ያመለጣችሁ" የሚለው ደግሞ በክርስቶስ ስለዳኑት ክርስቲያንኖች ነው፣ እነሱም እነማንን እንደሆኑም እዚያው ምዕራፍ መግቢያው ላይ(ኢሳ.45፡14) "ኢትዮጵያ፣ ሳባና ግብፅ" መሆናቸውን አመልክቷል፡፡

በዚህም ማስጠንቀቂያው የቀረበው ከእስራኤል ዘር ውጪ ሆነው በክርስቶስ አምልጠው ነገር ግን ካመለጡ ቦሃላም የተቀረፀው የእንጨት ምስል ለሚጠቀሙ "የዘመኑ ታቦት" ተማጋቾች ለኢትዮጵያና ለግብፅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኗ አሁን የምትጠቀመው ታቦት ቅርፅ፣ መጠን፣ መልክ፣ ይዘት፣ ስያሜና አጋፋሪዎቹን ስንመለከት ታቦቱ የእግዚአብሄር ታቦት

አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡ ታቦት የሚሰራው ለአምልኮ መሆኑ፣ መመለክ የሚፈልጉት ደግሞ እግዚአብሄርና ዲያብሎስ መሆኑ፣ ይህን ታቦት ደግሞ እግዚአብሄር ያዘዘው ታቦት አለመሆኑን ስንመለከት ታቦቱ የዲያብሎስ መሆኑን እንረዳለን፣ በዚህም አሁን “ታቦት” ተብሎ የሚጠራው ትክክለኛ ጣዖት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 4.4.2.3. በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ የተቀመጡ የሰይጣን አገልጋዮች

በቤተክርስቲያኗ እንደ ደብተራ፣ ጥንቆላ፣ አስማት … ሰይጣናዊ ትውፊቶች የተለመዱ ልምምዶች ናቸው፣ ይህም ልምምድ ከቀላል ገመድ ማቆም፣ ከብቶች በአውሬ እንዳይበሉ ከማስደገም አንስቶ እስከ ደመና ጋላቢነት የሚደርስ ነው፡፡ [105] በደመና የሚኬደው “መስተጽዕነ ደመና” በሚባለው አስማት ነው፣ [106] አባ አፍፄ በደመና ተጭነው ይሄዱ ነበረ፣ በአራዊት የሚጋለበው “መስተጽዕነ አራዊት” በሚባል አስማት ነው፣ [107] አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ አንበሳ ይጋልቡ ነበረ፣ [108] አቡነ አረጋዊ ዘደብረ ዳሞ በዘንዶ ይጓዙ ነበረ፣ ዛሬ ለተለያዩ ጥቅሞች ብለው ለሊት ጅብ የሚጋልቡትም የሚጠቀሙት ይህንኑ አስማት ነው፡፡

በቤተክርስቲያኗ እነዚህም ትውፊቶች ሰይጣናዊ ተደርገው የሚወገዙ ሳይሆን በ“ቅዱሳን” መፅሀፍቶች እንኳን የሚደገፉ ናቸው፣

- ከላይ በ4.3.4.7 ክፍል እንደተመለከትነው የጥንቆላ ስራ ሀጢያት አለመሆኑንና አሰራሩ እንኳን በተጨማሪ መፅሀፍቱ ላይ የተገለፀ መሆኑ
- ሰይጣናዊ አሰራሮችን የሚያስተምሩ እንደ [109] ዐውደ ነገስት፣ መፍትሄ ስራይ፣ መልክአ ራጉኤል ባለ ጠልሰሙ፣ መልክአ እዮብ፣ ሕልመ ዮሴፍ፣ ሀተታ ዘርአያዕቆብ … የሚባሉ የቤተክርስቲያኗ “ቅዱሳን” መፅሀፍት መሆናቸውን፣

---

[105] መሪጌታ ሰረቀ ብርሀን ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም፣ ገፅ 307
[106] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፩**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባኤያት)ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ ገፅ 39
[107] መ/ር ዐስራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፩**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባኤያት)ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ፣ ገፅ 87
[108] Ibid, ገፅ 34
[109] መሪጌታ ሰረቀ ብርሀን ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም

- [110] "መፅሀፈ ቆጵርያኖስ የተባለው መፅሀፍ አስማት፣ ጥንቆላ፣ ድግምት... አሰራርን የሚያስተምር ሲሆን፣ ለትክክለኛነቱም ማርያም በድግምት "መጥቁል" የተባለውን ጠንቋይ እንዴት እንዳሸነፈችው፣ ሰለሞንም እንዴት 600 አጋንንትን ይዞ ቤተመቅደሱን እንዳሰራ ያስተምራል፡፡"

  ይህንን የሰለሞን አጋንንትን መጠቀም ታሪክ የምናገኘው መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ሳይሆን "ቅዱስ" ቁርአን ላይ ነው(34፡12, 21፡82, 27፡15-17...)

- [111]"አንተ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ በእነዚህ አስማት ኃይል ሰባ ነገስታትን በዱድያኖስ ፊት እንደ ደመሰስካቸው የእኔንም ጠላቶች እንደ እነርሱ ደምስሳቸው፡፡(ቱላዳን ዘቅዳሜ ገፅ 183)፡፡

- [112]እነዚህን አስማቶች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚካኤል ክንፍ ላይ ፃፋቸው፣ በእነዚህም አስማቶች ዲያብሎስ ከነሰራዊቱ ጨለማን ተጎናፅፎ ወደቀ፡፡(ድርሳነ ሚካኤል ገፅ 62)"

በዚህም በቤተክርስቲያኗ አገልጋዮች ዘንድ እነዚህን ሰይጣናዊ ስራዎች መስራት ትክክለኛ ይባሱኑም ወሳኝ ሆኖ ይታያል፣ ወሳኝነቱም፡-

- [113] "በምድራችን ያለው አስማት እግዚአብሄር ለኖህ ያስተማረው፣ ለሰለሞንና ለማርያም የተሰጠ፣ በሚካኤል ክንፍ ላይ የተፃፈ ... በሚል አስማተኝነትን በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ቦታ በመስጠት ... ከዚህ የተነሳም አስማትን የማያውቅ ተማሪ የእግዚአብሄር ምስጢር እንደተደበቀበት ሆኖ ሲሰማው የአስማት ልምድ የተለማመደ ተማሪ ግን የእግዚአብሄርን ምስጢር እንደተረዳ ያህል ይቆጥረዋል፡፡"

- [114] "የተንኮል ትምህርት ማለት ጥንቆላ ወይንም መፅሀፍ ገለጣ፣ ኮከብ ቆጠራ፣ ስር መማስና ቅጠል መበጠስ በዚያ አጠራር "ጥበብ" ... እንደ ግዴታም ነው፣ ምክንያቱም እርስ በርስ ጠብ ይኖራል ያን ግዜ እራስህን ለመከላከልም ሆነ ለመርታት ትንሽም እንኳን እንዳልተማርክ ከተሰማ

---

[110] መምህር ፅጌ ስጦታው(2004)፣ **ወጋገን**፣ ገፅ 32-33

[111] ፀጋአብ በቀለ(2006)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሀድሶ**፣ ቅፅ 1፣ ገፅ 38

[112]Ibid፣ ገፅ 38

[113] መሪጌታ ሰረቀ ብርሀን ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም፣ ገፅ 307-308

[114] ፀጋአብ በቀለ(2006)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሀድሶ**፣ ቅፅ 1፣ ገፅ 39

መጫወቻ ያደርጉሀል፣ በተቃራኒው ከታወቅህ ትከበራለህ … ስለዚህ መማሩ አስገዳጅ ነው፡፡ (ቀሲስ ደረጀ ገዙ፣ ቪዥን ቅፅ 1 ቁጥር 2 ጥር-የካቲት 2004 ገፅ 5)”

- [115] የገድላትና የድርሳናት ጸሀፊ ደብተራዎች አብዛኞቹ የነገስታት ፍርፋሪ የለመዱና የነገስታትን አፍ ጠብቀው የሚናገሩ፣ ለነገስታቱ መግረሬ ፀር(ጠላት እንዲገዛላቸው የሚያደርግ) ድግምትን እየደገሙ የሚኖሩ ስለነበረ ነው፡፡ በዚህም የድግምት ስራ እንጀራቸው ስለሆነ፣ ከቤተክርስቲያን አገልግሎታቸው ጋር በዚህ ሰይጣናዊ ሙያ አቀላቅለው ይኖራሉ፡፡

እነዚህ ሰይጣናዊ ትውፊቶች “ቅድስት” ቤተክርስቲያንን ሞልተዋት እንመለከታለን፣ በዚህም በቤተክርስቲያኗ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሰይጣን ቢመለክ፣ ክርስቶስ ዋጋ የከፈለበት አዲስ ኪዳን በሴራ ቢሸፈን፣ ቅድስና የጎደላቸው ተጨማሪ መፅሀፍት “ተቀድሰው” ቢገቡ፣ ከላይ የተመለከትናቸው የጥንቆላ፣ አስማት … መማርያ መፅሀፍት ቢገቡ፣ ጣዖታት በስዕልና በታቦቱ ስም ተሸፍነው ቢገቡ አያስገርምም፡፡

[115] መሪጌታ ሰረቀ ብርሀን ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም፣ ገፅ 308

## ማጠቃለያ(ኦርቶዶክስ)

የመፅሀፍ ቅዱሱን ታሪኮች ስንመለከት አንድ ተደጋጋሚ ታሪክ እንመለከታለን፣ ቅዱሱ መንገድ በጊዜ ሂደት በዲያብሎስ ሴራ የሚበረዝበትና እግዚአብሄርም በቅዱሳን አማካኝነት ተሀድሶ አስነስቶ ቤቱን የሚያፀዳበት የታሪክ ሂደት (ዘፀ.32፡20, መሳ.6፡25-30, 2ነገ.10፡26-28, 2ነገ.23፡4, 2ዜና.29፡5, 2ዜና.34 ...)፡፡

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም የምንመለከተው ችግር ትክክለኛው አስተምህሮ በጊዜ ሂደት በዲያብሎስ ሴራ የመበረዝ ችግር ነው፡፡

አብዛኞቹ የቤተክርስቲያኗ መሪዎችም እነዚህን ከላይ የተመለከትናቸውን ስህተቶች በቤተክርስቲያኗ ውስጥ መከሰታቸውን ያውቃሉ ነገር ግን እውነታውን ለመናገር አይደፍሩም፣ አንዳንዶቹ ያሉበት ስልጣንና ጥቅማ ጥቅም ስለሚያሳሳቸው ሌሎቹ ደግሞ ምስጢሩን ይፉ በማውጣታቸው የሚመጣውን መከራና ስደት ስለሚያውቁ ስህተቱን በዝምታ እየተመለከቱ ይገኛል፡፡

አንዳንድ ጥቅማ ጥቅሙ ያላሳሳቸውና ከምድራዊው ነገር ይልቅ ዘላለማዊውን ነገር የሚፈሩቱ፣ እውነቱን ሲረዱ ቤተክርስቲያኗን ጥለው ወደ ትክክለኛው አስተምህሮ ሲሄዱ እንመለከታለን፣ ይህ መልካም ቢሆንም ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ውስጥ እንደነሱ መፅሀፍትን ማግኘት፣ ማንበብና መረዳት የማይችሉ ብዙ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ባገናዘበ መልኩ ቢንቀሳቀሱ ነበረ የተሻለ የሚሆነው፣ በዚህም እውነታን ሲረዱ ጥሎ ከመውጣት በተሀድሶአዊ መንገድ እዚያው ቤተክርስቲያንዋ እንድትታደስ ቢሰሩ መልካም ነበረ፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይም ስንመለከት፣ ብዙዎቹ ቅዱሳን እውነታው ሲገለጥላቸው፣ ቤተክርስቲያናቸውን ለርኩሰት ጥለው አልወጡም፣ ቅዱሱን ከእርኩሱ ለይተው እርኩሱን ሲያስወግዱና የእግዚአብሄርን ቤት ሲያፀዱ ነበረ፣ ይህንንም እውነታ ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች ውስጥ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከነዚህ ጥቅሶች ውስጥ አንዱን በምሳሌ ሰፋ አድርገን ብንመለከት፣ በነኢዮስያስ ዘመን በሰማይ ሰራዊት(መላዕክት) ስም አምልኮ በቤተክርስቲያን

ውስጥ ሲደረግ ነበረ፣ ለኢዮስያስም እውነቱ ሲገለጥለት፣ እነዚህን በመላዕክት ስም የተቀመጡትን የአምልኮ እቃዎች ጠራርጎ አውጥቶ አቃጠለ፣

> 2ነገ.23፥4 "... ለሰማይም ሰራዊት ሁሉ የተሰሩትን ዕቃዎች ሁሉ ከእግዚአብሄር መቅደስ ያወጡአቸው ዘንድ አዘዘ፣ ከኢየሩሳሌምም ውጪ በቄድሮን ሜዳ አቃጠላቸው፡፡"

ዛሬ በቤተክርስቲያኒቷ የምንመለከተው ችግር ይህ የመላዕክት አምልኮ ጨምሮ ሌሎች ብዙ የተለያዩ አይነት አምልኮዎች መግባታቸው ነው፣ ይህም ቤተክርስቲያኗ ምን ያህል ሰፊ የእድሳት ስራ እንደሚያስፈልጋት ያመለክታል፡፡

ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው እውነቱ ሲገለጥለት ቤተክርስቲያኑን ለቆ መውጣት ሳይሆን የተረዱትን እውነት በጥበብ ለሌሎች በማካፈል፣ እነሱም ለሌሎች እንዲያካፍሉ በማድረግ፣ በተቀናጀ መንገድ በመስራት በቤተክርስቲያኗ ውስጥ አጠቃላይ ተሀድሶን በማንቀሳቀስና ከላይ የተመለከትናቸውን የስህተት ትምህርቶችንና ጣዖቶችን በሙሉ ከእግዚአብሄር ቤት በማስወገድ የእግዚአብሄርን ቤት ለእግዚአብሄር ብቻ በመቀደስ ነው፡፡

> 2ዜና.29፥5 "... ሌዋውያን ሆይ ስሙኝ ተቀደሱ፣ የአባቶቻችሁንም አምላክ የእግዚአብሄርን ቤት ቀድሱ፣ ርኩሱንም ነገር ሁሉ ከመቅደስ አስወግዱ፡፡"

በርግጥ ይህ በፀሎት፣ በጥበብና በቅንጅት ሊከናወን ይገባል፣ ቤቱን ስታድሱ ደግሞ እግዚአብሄር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋል(ኢያ.3፥5)፣ ለነፍሳችሁም የሀጢያት ስርየትን(ኢሳ.27፥9) እና ዘላለማዊውን ዕረፍትን ታገኛላችሁ(ኤር.6፥16)፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት

በዚህ ርዕስ ስር የምንመለከተው ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የተመሠረቱትን ሐዋርያት፣ የጂሆቫ እና የአድቬንቲስት አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ነው፡፡

ብዙ ሰዎች እነዚህ ሶስቱ አብያተ ክርስቲያናት በፕሮቴስታንት ስር የሚመደቡ ይመስላቸዋል ነገር ግን ሶስቱም አብያተ ክርስቲያናት ከፕሮቴስታንት በአስተምህሮ የሚለዩና እርስ በርሳቸውም የሚለያዩ የየራሳቸውን አስተምህሮ የሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በ3.2 ክፍል ስር ከተመለከትናቸው ሀይማቶችም የተለዩ ናቸው፣ ልዩነታቸውም እነዚህ ሶስቱም አብያተ ክርስቲያናት በመፅሀፍ ቅዱሱ የሚመሩ ሲሆን መፅሀፍ ቅዱሱንም ከሁሉም መፅሀፍት በላይ አድርገው ይመለከታሉ፣ በ3.2 ክፍል ስር የተመለከትናቸው ሀይማኖቶች ግን የሚመሩት መፅሀፍ ቅዱሱን ከራሳቸው ፍልስፍና ጋር በማዋሀድ ባዘጋጁት “ቅዱስ” መፅሀፍ ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ስር የነዚህን የሶስቱን ሀይማኖቶች አስተምህሮ ከመፅሀፍ ቅዱሱ አንፃር በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## 5.1. የሐዋርያት ቤተክርስቲያን "Only Jesus"

[116]"የሐዋርያት ቤተክርስቲያን (United Pentecostalism/Apostolic Pentecostal Christian) አስተምህሮት በ1914 የተጀመረ ሲሆን ቤተክርስቲያኗ ግን እንደ ቤተክርስቲያን የተቋቋመችው በ1945 ዓ.ም ነው፣ ቤተክርስቲያኗ በአሁኑ ጊዜ ከ5 ሚሊየን በላይ ተከታዮች ያሉዋት ሲሆን የቤተክርስቲያኗ ዋና ፅህፈት ቤትም በዌልደን እስፐሪንግ፣ ሚዙሪ ይገኛል፡፡"

ለቤተክርስቲያንዋ ምስረታ መነሻ የሆነው፣ ሰዎች በቡድን ሆነው መፅሀፍ ቅዱስ እያጠኑ "ትክክለኛው የውሃ ጥምቀት በማቴ.28፡19 ላይ በተገለፀው በአብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም ነው? ወይስ ሐስ.2፡38 ላይ በተመለከተው መንገድ በኢየሱስ ስም መፈፀም አለበት? በሚለው ሀሳብ ላይ በተነሳ ክርክር ነው፡፡

በዚህም ክርክር ምንም እንኳን ጥምቀት "በአብ በወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም" እንዲደረግ ቢታዘዝም ሐዋርያቱ ያጠመቁት ግን "በኢየሱስ ስም" በመሆኑ፣ "ጥምቀት መፈፀም ያለበት በኢየሱስ ስም ብቻ ነው" በሚለው ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸውና ከዚህም ድምዳሜ በመነሳት ደግሞ "አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" በማለት ከስላሴያውያኑ የተነጠለ አዲስ ሀይማኖት በመመስረት ነው፡፡

እነዚህን ሁለቱን መሠረታዊ ሀሳቦችንም ከመፅሀፍ ቅዱሱ አንፃር ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 5.1.1. "ጥምቀት መፈፀም ያለበት በኢየሱስ ስም ብቻ ነው"

ስላሴያውያን (የስላሴን አስተምህሮን የሚከተሉት ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት ...) ጥምቀት በማቴ.28፡19 ላይ በታዘዘው መሠረት በ"አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም" ሲያከናውኑ፣ የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ደግሞ ሐዋርያቶች ባጠመቁበት መንገድ(ሐስ.2፡38, ሐስ.8፡16, ሐስ.19፡5, ሐስ.22፡16 ...) "በኢየሱስ ስም" ብቻ ታጠምቃለች፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ በማቴ.28፡19 ላይ ያለውን በ"አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም" አጥምቁ የሚለውን ትዕዛዝ አትቀበልም፣

---

[116] https://en.m.Wikipedia>wiki>United Pentecostal Church International

- [117] "ጥምቀት በኢየሱስ ስም ብቻ መከናወን አለበት ... አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም ... በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማለት በኢየሱስ ስም ማለት ነው፡፡"
- [118] "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የማዕረግ ስም ነው፡፡"

ነገር ግን እነዚህ መከራከሪያዎች መቀበል ያዳግታል ምክንያቱም፣

1. ሀሳቡ እርስ በርስ ይጋጫል
   - "አብ፣ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም" ይልና ተመልሶ ደግሞ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም ማለት በኢየሱስ ስም ማለት ነው" ይላል፣
   - "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም" ይልና ተመልሶ ደግሞ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሚለው የማዕረግ ስም ነው" ይላል፣
2. ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጋር ይጋጫል
   - ማቴ.28፡19 ላይ ኢየሱስ "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ" ከሚለው ትዕዛዝ ጋር ይጋጫል፣ መቼም ኢየሱስ ይህን ትዕዛዝ ሲሰጥ "በስሜ አጥምቁ" ማለት ሲችል እንዲህ ማለቱ ተሳስቶ አይደለም፣
   - ማቴ.28፡19 "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" እያለ መፅሀፍ ቅዱሱን በመቃወም "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም ማለቱ ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጋር ይጋጫል፣
3. መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም

   "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ" ስም ማለት "በኢየሱስ ስም ማለት ነው" የሚል ቃል መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አናገኝም፣

በዚህም የሐዋርያት ቤተክርስቲያን በ"አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ስም ማጥመቅ ለመተው ያቀረበችው ምክንያት ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

[117] ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሄር መፅሀፍ ፊልጉ - መሰረታዊ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርር ማስተማሪያ**፣ ገፅ 25፣ ትምህርተ 18/ሸ/3 እና ትምህርተ 18/ቀ
[118] Ibid, 43፣ ትምህተ 23/5/በ

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ስላሴያውያን ሐዋርያቱ ባጠመቁበት መንገድ “በኢየሱስ ስም” ጥምቀትን አይፈፅሙም፣ ለዚህም ሁለት የተለያዩ መከራከሪያዎችን ያቀርባሉ፣ ይህም፣

1. “በኢየሱስ ስም ማጥመቅ” የሚባለው የስያሜ ጉዳይ ነው፣ ይህ ስያሜ የተፈጠረው ደግሞ የአዲስ ኪዳኑን ጥምቀት ከብሉይ ኪዳኑ ጥምቀት ለመለየት ነው፣ በሐስ.19፡19፡1-5 ላይ “በዮሐንስ ጥምቀት” እንደተባለው “በኢየሱስ ስም ጥምቀት” የሚባለውም የስያሜ ጉዳይ ነው፣ ይላሉ፡፡

    ነገር ግን ሐስ.2፡38, ሐስ.8፡16, ሐስ.19፡5 እና ሐስ.22፡16 ላይ ስንመለከት፣ “በኢየሱስ ስም ጥምቀት” የሚለው የስያሜ ጉዳይ ሳይሆን ሰዎች የኢየሱስን ስም እየጠሩ ተጠምቀዋል፡፡

2. በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ “በኢየሱስ ስም ተጠመቁ” የተባሉት የብሉይ ኪዳንን ጥምቀት የተቀበሉት አይሁድና የሰማርያ(የአህዛብ አይሁድ ድብልቆች) ብቻ ናቸው፣ የብሉዩን ጥምቀት ያልተቀበሉት አህዛብ “በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም” መጠመቅ አለባቸው ይላሉ፡፡

    ነገር ግን አህዛብም በኢየሱስ ስም መጠመቃቸውን በሐስ.10፡44-48 ስንመለከት መከራከሪያው ውድቅ መሆኑና በዚህም አንዳንድ ስላሴያውያን “በኢየሱስ ስም” ማጥመቅን የተዉበት አመክንዮም ትክክል አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

መፅሀፍ ቅዱሳዊውን እውነታ ስንመለከት ግን የሁለቱም ወገኖች ክርክር “ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ” መሆኑን እንመለከታለን፣ በመጀመሪያ ጥምቀት “በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መደረግ አለበት” ያለው ኢየሱስ ሲሆን ይህንንም የተናገረው ከማረጉ በፊት ነው፣ ኢየሱስ ካረገ በኋላ ደግሞ ሐዋርያቱ ጥምቀትን በኢየሱስ ስም አደረጉ፣ በዚህም ልዩነቱ ከምን መጣ? ብለን ስንመለከት፣ ከኢየሱስ እርገት በኋላ በተለወጠው ነገር ነው፣ ይህም ለውጥ ደግሞ፣

> ፊልጵ.2፡6-10 “እርሱ በእግዚአብሄር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሄር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፣ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰው ምሳሌ ራሱን ባዶ አደረገ፣ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ

የታዘዘ ሆነ፡፡ በዚህም ምክንያት ደግሞ እግዚአብሄር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም **ሰጠው**፣ ይህ በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሄር አብ ክብር ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው፡፡"

የሚለው ቃል ከኢየሱስ እርገት ቦሃላ በመውረዱ ነው፣ ከዚህም ቃል የምንረዳው ኢየሱስ ካረገ በኋላ፣ በምድር ላይ በፈፀመው ስራ ምክንያት ለስሙ ትልቅ ስልጣን መሰጠቱን ነው፣ በዚህም **ከስም አንፃር** "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" እና "በኢየሱስ ስም" መካከል ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡

ስለዚህ ጥምቀት "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" ማጥመቁም ስህተትነት የለውም፣ "በኢየሱስ ስም" ማጥመቁም ስህተትነት የለውም፣ ምክንያቱም የኢየሱስ ስምም ከሁሉም ስም በላይ እንደ ሆነው የ"አብ፣ወልድን መንፈስ ቅዱስ" ስም ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፡፡

ነገር ግን የሐዋርያት ቤተክርስቲያን በምታሳትማቸው መፅሀፍ ቅዱሶች ውስጥ ማቴ.28፡19 መሰረዟ እንዲሁም በሌሎች መፅሀፍቶቻቸው ውስጥም "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን "አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ" በማለት "ና" የምትለዋ አያያዥ ቃል ማውጣቷ ትልቅ ሀጢያት ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ የእግዚአብሄር ቃል በመሆኑ በሱ ላይ መጨመርና መቀነስ ትልቅ ሀጢያት ነው(ራዕ.22፡18-19, ዘዳ.4፡2, ዘዳ.12፡32 ...)

### 5.1.2. <u>“አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ”</u>

ቤተክርስቲያኗ፣ የኢየሱስ የስም ስልጣን ከ“አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ” ስም ስልጣን ጋር እኩል የመሆንን እውነታ በማስፋት፣ “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” የሚለው ድምዳሜ ድረስ ሄዳለች ይህ ደግሞ ትልቅ ስህተት ነው፣ በቀላሉ ከላይ በተመለከትነው በፊልጵ.2፡6-10 ላይ “ሰጠው” በሚለው ቃል ውስጥ እንኳን ሰጪ አካል መኖሩን መረዳት ይቻላል፣ ይህንን እውነታም፣ 1ቆሮ.15፡27 “ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአልና፡፡ ነገር ግን ሁሉ ተገዝቶአል ሲል፣ <u>ሁሉን ካስገዛለት በቀር</u> መሆኑ ግልጥ ነው፡፡” በሚለው ቃልም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

“አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” የሚለው አስተምህሮ ስህተት በመሆኑ ለቤተክርስቲያኗ ይህንን ሀሳብ ማስረዳት እንደ ጥምቀት ጉዳይ ቀላል አልሆነላትም፣ ይህንንም ለመወጣት ለአዕምሮ የማይያዙ ፍልስፍናዎችንና ከመፅሀፍ ቅዱሱ እንዲሁም እርስ በራሱ የሚጋጩ ትምህርቶችን ትሰጣለች፣ ከሁሉ ከባድ ፈተና የሆነባት “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” ስትል “አብና መንፈስ ቅዱስ” የሚባሉትን የእግዚአብሄር ማንነቶች የምታደርገውን ማጣቷ ነው፣ እነዚህ ስህተቶች፣ ክፍተቶችና የሀሳብ ግጭቶችም በሶስት መሠረታዊ ቦታዎች አጠቃለን እንመለከታለን፣ ይህም፣

- እግዚአብሄርና አብ ከኢየሱስ ጋር ያላቸውና አንድነትና ልዩነት አለማገናዘብ፣
- አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስን በአንድ ላይ አጠጋግቶ ኢየሱስ ማድረግ የማይቻል መሆኑ፣
- የእግዚአብሄር ስላሴነትን መሸፈን የማይቻል መሆኑን

ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 5.1.2.1. እግዚአብሄርና አብ ከኢየሱስ ጋር ያላቸውና አንድነትና ልዩነት ያላገናዘበ መሆኑ

"አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" የሚለው አስተምህሮ "እግዚአብሄር"፣ "አብ" እና "ኢየሱስ" የሚባሉትን ማንነቶች አንድነትና ልዩነት ያላገናዘበ አስተምህሮ ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

#### 5.1.2.1.1. እግዚአብሄርና ኢየሱስ

ቅዱሳን ከኢየሱስ መገለጥ በፊት እግዚአብሄርን ሲያመልኩ ነበረ፣ አብርሃም፣ ይስሀቅ፣ ያዕቆብ፣ ሙሴ፣ ኤልያስ … የሚያመልኩትን አካል ሳያውቁት ሲያመልኩ አልነበረም፣ ሲያመልኩት የነበረው "ስሜ እግዚአብሄር ነው" ያላቸውን አምላክን ነበረ፡-

- ዘፀ.6፡3 "ለአብርሀም ለይስሀቅም ለያዕቆብም … ስሜ እግዚአብሄር አልታወቀላቸውም ነበር፡፡"
- ዘሌ.19፡12 "በስሜም በሀሰት አትማሉ፣ የአምላካችሁንም ስም አታርክሱ፣ እኔ እግዚአብሄር ነኝ፡፡"
- ዘሌ.22፡2 "… የተቀደሰውን ስሜን እንዳያረክሱ ለአሮንና ለልጆቹ ንገራቸው እኔ እግዚአብሄር ነኝ፡፡
- ዘፀ.15፡3 "እግዚአብሄር ተዋጊ ነው፣ ስሙም እግዚአብሄር ነው፡፡"
- ኢሳ.51፡15 "ሞገዱም እንዲተምም ባህርንም የማናውጥ አምላክህ እግዚአብሄር እኔ ነኝ፣ ስሜም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ነው፡፡"
- ኤር.12፡16 "በበአል ይምሉ ዘንድ ህዝቤን እንዳስተማሩ፣ በስሜም፣ ህያው እግዚአብሄርን! ብለው ይምሉ ዘንድ የህዝቤን መንገድ በትጋት ቢማሩ፣ በዚያን ጊዜ በህዝቤ መካከል ይመሰረታሉ፡፡"
- ሆሴ.12፡6 "… እርሱም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ነው፣ የመታሰቢያውም ስም እግዚአብሄር ነው፡፡"

በዚህም ፈጣሪ አምላክ ስሙ "እግዚአብሄር" መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህ ስሙም የሚጠራው ለብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ ሳይሆን ለዘላለምም ነው፣

ዘፀ.3፡15 "እግዚአብሄርም … ይህ ለዘለላለሙ ስሜ ነው፣ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ መታሰቢያዬ ይህ ነው፡፡"

በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የተገለጠው ፈጣሪ ስሙ “እግዚአብሄር” መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፣ እርሱም ቅዱስ በመሆኑ ስሙ “ኢየሱስ” ሆኖ ስሜ “እግዚአብሄር” ነው ብሎ አይዋሽም፣ ትክክለኛ ስም የማይነገረው ለማጭበርበር ወይ ደግሞ በፍራቻ ነው፣ እግዚአብሄር ግን ፃድቅና ኤልሻዳይ በመሆኑ ይህንን ልናስብበት አንችልም፡፡

“እግዚአብሄር” የሚባለው ስም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተነገረው በዋናነት የሶስቱ ስላሴ(አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) የአንድነት ስም ሆኖ ነው፣ ለዚህም ነው መፅሀፍ ቅዱሱ “እግዚአብሄር” የሚለው ስም ላይ “አንድ እግዚአብሄር”(ዘዳ.6፡4, 1ጢሞ.2፡5, 1ቆሮ.12፡6 ...) ብሎ ሶስቱን ግን “ከእግዚአብሄርነት ማንነታቸው” ሳያወርድ በየስማቸውና በየምግባራቸው ለያይቶ የሚጠራው፣ በዚህም “እግዚአብሄር” የተባለውን ስምና ማንነት የገዘፈ የአንድነት ስምና ማንነት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አምላክ መጀመሪያ የለውም ነገር ግን “ኢየሱስ” የተባለው ስም የተጀመረበት ጊዜ አለው፣ ኢየሱስ የተባለው ስም የተጀመረው ከስላሴ አንዱ የሆነው “ወልድ” ስጋን ለብሶ መወለድ በመፈለጉ፣ መለኮትና ስጋው ተዋህዶ ሲወለድ፣ ለተዋህዶው ማንነት “ኢየሱስ” የሚለው ስም ተሰጠ(ማቴ.1፡21)፡፡ በዚህም “ኢየሱስ” የሚለው ስም የተሰጠበት ጊዜ ያለውና ስሙም የተሰጠው ፍፁም መለኮት ብቻ ለሆነ አካል ሳይሆን ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ሆኖ ለተወለደው ለተዋህዶው ማንነት ነው፡፡

ይህ ተዋህዶነት(ቆላ.2፡9) ያስፈለገው ደግሞ ለሰው ልጆች ሀጢያት ስርየት በመሆኑም የስሙ አሰያየም ከሀጢያት ስርየት ጋር የተያያዘ ነው፣ ይህንንም መፅሀፉ በግልፅ ኢየሱስ ማለት “የሀጢያት መድሃኒት” ማለት ነው ብሎ ይነግረናል(ማቴ.1፡21)፡፡

በዚህም “አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ” ማለት “እግዚአብሄርን” ስለ ሰው ልጅ የሀጢያት ስርየት ብሎ ከኦሪጂናል ማንነቱ ራሱን ዝቅ አድርጎ በወረደው ወልድ ተዋህዶ ማንነት የሚገድብ፣ የእግዚአብሄርን ማንነት “በሀጢያት ስርየት” ብቻ የሚገድብና ከኢየሱስ መወለድ በፊት የነበሩትን በእግዚአብሄር ስም ሲደረጉ የነበሩትን አምልኮቶች በሙሉ ባዶ የሚያደርግ የስህተት አስተምህሮ ነው፡፡

### 5.1.2.1.2. አብና ኢየሱስ

ስላሴ ማለት "አንድ ውስጥ ያለ ሶስትነት ማለት ነው"፣ ይህ በተፈጥሮ በሰው ልጅ(ነፍስ፣ መንፈስና ስጋ)፣ በፀሀይ(ሰማዩ ላይ በምትታየው፣ በብርሀንና ሀይል) ... ውስጥ ያለ የተዋህዶነት አሰራር መሆኑን በ5.1.2.3.7 ክፍል በዝርዝር ተመልክቷል፣ የፈጣሪ ስላሴነት አንድ እግዚአብሄርና አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተባሉትን የእግዚአብሄር ማንነቶች ናቸው፡፡

ኢየሱስ የአምላክና የሰው ተዋህዶ ነው ነገር ግን ይህ ተዋህዶነቱ የሰውና አምላክ ስላሴነትን አሰራር ሳይጥስ ነው፣ ይህም ኢየሱስ ስላሴነትን የያዘው ወልድ በሆነው መለኮትነት፣ ሰው በሆነው ከማርያም በወሰደው ማንነትና በዚህም ስጋ ውስጥ ከአብ በተሰጠው ህይወት ነው(ዮሐ.5፡26)፣ በዚህም ኢየሱስ የሰውና የአምላክ ተዋህዶ በመሆን የሰው-አምላክ መካከለኛነትን ቦታን ያዘ፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ኢየሱስን "መካከለኛ" የሚልበት(1ጢሞ.2፡5, ዕብ.1፡24 ...) ሌለኛው ትርጉም ይኸው እውነታ ነው፡፡

ነገር ግን ኢየሱስ በዚህ ስላሴነቱ ውስጥ ያለውን አምላክነት በሙላት መጠቀም ከመጣለት አላማ ጋር ስለማይሄድ፣ ይህን አምላክነቱን ባዶ አደረገ(ፊሊ.2፡7)፣ ከዚህ በተጨማሪም በአምላክነቱ ውስጥ የተዋሃደው ስጋዊ ማንነት በሚፈጥረው ውሱንነት ምክንያት ኢየሱስ በአብዛኛው ሲኖር የነበረው እንደ የትኛውም የሰው ልጅ ነበረ፡፡

ይህንንም እውነታ ኢየሱስ ከስጋ ካልተዋሀዱት መንፈስ ቅዱስና አብ ጋር በነበረው ልዩነትና ግንኙነት አሳይቶናል፣ በዚህም ነው "እኔ ሄጄ መንፈስ ቅዱስ ቢመጣላችሁ ይሻላችኋል"(ዮሐ.16፡7-13) ያለው በተመሳሳይ መንገድም ከአብ ጋር በነበረው ግንኙነት ውስጥ ያስመለከተን፣

➢ <u>አብ ከእሱ እንደሚበልጥ መናገሩ</u>

- ዮሐ.14፡28 "... የምትወዱኝስ ብትሆኑ <u>ከእኔ አብ ይበልጣልና</u> ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር፡፡"
- ማቴ.24፡36 "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰአት ግን <u>ከአባት ብቻ</u> በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ <u>ልጅም ቢሆን</u> የሚያውቅ የለም፡፡"
- ሉቃ.18፡19 "<u>ኢየሱስም ስለ ምን ቸር ትለኛለህ፣ ከአንዱ ከእግዚአብሄር በቀር ቸር ማንም</u> የለም፡፡"

- ዮሐ.5፡19-20 "... እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ ያየውን እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም... አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል ..."
- ዮሐ.6፡57 "ሕያው አብ እንደላከኝ እኔም ከአብ የተነሳ ሕያው እንደምሆን ..."
- ዮሐ.6፡39 "... የላከኝ አብ ፈቃድ ይህ ነው፡፡"
- ዮሐ.20፡17 "... እኔ ወደ አባቴና ... ወደ አምላኬ ... ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪ አላቸው፡፡"
- ዕብ.5፡7 "እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደ ሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን አቀረበ፣ እግዚአብሄርን ስለመፍራቱ ተሰማለት፡፡"

እነዚህ ቃላትም የአብና የኢየሱስን ግንኙነት ግልፅ ሲያደርጉል በሌላ በኩል ደግሞ የቤተክርስቲያንዋ "አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አባባል ውድቅ ያደርጋሉ፣ ይባሱኑ "አንዱን ብቻ ነው የምንይዘው" የሚለው የግዴታ ከሆነ ከኢየሱስ ይልቅ "አብ ብቻ" ቢሉ የሚሻላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

➢ **ኢየሱስ ወደ አብ መፀለዩ**

ኢየሱስ ብዙ ቦታዎች ላይ ወደ አብ ሲፀልይ ነበረ፣

- ዮሐ.17፡1-21 " ኢየሱስም ይህ ተናግሮ ወደ ሰማይ አይኖቹን አነሳና እንዲህ አለ፡፡ አባት ሆይ ... እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ አንተ የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስንም ያውቁ ዘንድ ... እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ስራ ፈፅሜ በምድር አከበርሁህ ... አባት ሆይ ... የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት ... ከአንተ ዘንድ እንደወጣሁ በእውነት አወቁ፣ አንተም እንደላከኸኝ አመኑ ... ስለዚህ እለምንሀለሁ ... እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ ... ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ ... ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከአለም እንድታወጣቸው አልለምንህም ..."

- ማቴ.27፥46 "በዘጠኝ ሰአትም ኢየሱስ፣ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡ ይህም፡፡ አምላኬ አምላኬ ፣ ስለምን ተውኸኝ፣ ማለት ነው ፡፡"
- ሉቃ.23፥34 "ኢየሱስም፣ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ፡፡"

ቤተክርስቲያኗ ኢየሱስ አእምሮ እንደሌለው ሰው "ከራሱ ጋር ሲያወራ ነበረ" እንደማትል ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

- **የኢየሱስ የአማላጅነት እውነታ**

ኢየሱስ በምድራዊ ህይወቱ ወቅት ዋናው የሰራው ስራ የማስታረቅ ስራ ነው፣ አሁን ደግሞ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ አገልግሎቱ የምልጃ አገልግሎት መሆኑን በ4.1.1.4 ክፍል ተመልክተናል ነገር ግን "አንድ አምላክ እሱም ኢየሱስ ብቻ" ከተባለ ማን ማንን ከማን ጋር? አስታረቀ፣ አሁንስ ቢሆን ማነው ማንን ከማን ጋር የሚያማልደው? የሚለው መመለስ አለበት፡፡

- **የኢየሱስ የመስካሪነት እውነታ**

- ማቴ.10፥32-33 "ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም ለሚክደኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ፡፡"
- ራዕ.3፥5 "ድል የነሳው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጎናፀፋል፣ ስሙንም ከህይወት መፅሃፍ አልደመስስም፣ በአባቴና በመላዕክቱ ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ፡፡"

እነዚህ አብ ከኢየሱስ እንደሚበልጥ መነገሩና የኢየሱስም የፀሎት፣ የማማለድና የምስክርነት አገልግሎት የቤተክርስቲያኗን "አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮ ያፈርሳል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት የቤተክርስቲያንዋ "አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮ ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጋር የሚጋጭ የስህተት አስተምህሮ ነው፡፡

### 5.1.2.2. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስን በአንድ ላይ አጠጋግቶ ኢየሱስ ማድረግ የማይቻል መሆኑ

ቤተክርስቲያንዋ "አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ" በሚለው አስተምህሮቷ ውስጥ ኢየሱስን "ብቸኛው አምላክ" ስትለው ሌሎቹን የስላሴ አካላት "አብና መንፈስ ቅዱስን" ምን ማድረግ እንዳለባት ትልቅ ፈተና ሆኖባታል፣ በዚህም አብና መንፈስ ቅዱስን በኢየሱስ ውስጥ ለማሸጋሸግ ሞክራለች፣

- [119] "አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የማይነጣጠሉ በአንድ አካል ውስጥ (በክርስቶስ ፍፁም አካል) የሚኖሩ ናቸው ... እነዚህ ሶስቱ በአካሉ ብቻ ማለትም በሰውነቱ ብቻ ተዋህደው እንጂ ለያይተን ልናያቸው አንችልም ... አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ... በአካል አይለያዩም፡፡"

- [120] "(አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) እንደ (ሰው) መንፈስ እንደ ነፍስ እንደ አካል ስለሆኑ በአንድ በክርስቶስ ሰውነት ተጠቅልለው ይኖራል፡፡"

ትላለች፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ለ"አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮም "አብና መንፈስ ቅዱስ"ን አሳንሳ ተመልክታለች፣ በዚህም፣

- [121] "አብ ማለት አባት ማለት ብቻ ነው፣ የአብ ስም ኢየሱስ ነው"

- [122]"መንፈስ ቅዱስ ማለት ረቂቅ የማይጨበጥ ቅዱስ እስትንፋስ ማለት ብቻ ነው"

ለዚህም ደግሞ የኢየሱስ ስጋ እነዚህን አምላካዊ ማንነቶች መሸከም እንዲችል ስጋውን መለኮታዊ አድርጋለች ነገር ግን ይህ አብንና መንፈስ ቅዱስን የማሳነስና የኢየሱስን አካል መለኮታዊ አካል ማድረግ ስህተት መሆኑን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

---

[119] ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሄር መፅሀፍ ፈልጉ - መሰረታዊ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህር ማስተማሪያ**፣ ገፅ 36 – 37፣ ትምህርተ 21/4

[120] Ibid, 42፣ ትምህርተ 23/5

[121] Ibid, ገፅ 41

[122] ibid, 41፣ ትምህርተ 23/3/ሀ

### 5.1.2.2.1. [123]“አብ ማለት አባት ማለት ብቻ ነው፤ የአብ ስም ኢየሱስ ነው”

ይህ የማጠጋጋት ስራ ከመፅሀፍ ቅዱሱም ከቤተክርስቲያኗም አስተምህሮ ጋር የሚጋጭ ነው፣ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው ኢየሱስ እራሱ “አብ ከኔ ይበልጣል” ማለቱ፣ በዚህም ወደ አብ ሲፀልይ የነበረ መሆኑ፣ አሁንም አማላጅ መሆኑ … ስንመለከት አብን አሳንሶ በኢየሱስ ማንነት ውስጥ ማስገባት እንደማይቻል ያሳያል፡፡

ከመፅሀፍ ቅዱሱ በተጨማሪ አስተምህሮው ከሌላ የቤተክርስቲያኗ አስተምህሮም ጋር ይጋጫል፣

> [124] “1ጢሞ.3፡16 እግዚአብሄር በስጋ እንደተገለጠ ያስረዳል፡፡ እግዚአብሄር ተጠቃሎ ስጋ ሆነ አይልም እግዚአብሄር አብ ከማርያም አልተወለደምና፡፡ እግዚአብሄር በስጋ ከመገለጡ በፊት መንፈስና ቃል ሆኖ ወይም መለኮትና ቃል ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ስለዚህ ትንቢቱ ሲፈፀም በውስጡ የነበረውን ቃሉን ስጋ አደረገውና ተገለጠበት … እግዚአብሄር አብ ስጋ ሆነ ማለት አንችልም …”

በዚህም አስተምህሮ “መንፈስ/መለኮት” በማለት የገለፁት አብ “ቃል” በሚባለው ማንነት ውስጥ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህም አብን አሳንሶ ኢየሱስ ማድረግ የማይቻል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

---

[123] ibid ፣ ገፅ 41
[124] Ibid, 45፣ ትምህረተ 24/1/

### 5.1.2.2.2. [125]"መንፈስ ቅዱስ ማለት ረቂቅ የማይጨበጥ ቅዱስ እስትንፋስ ማለት ብቻ ነው"

በርግጥ ይህ ዘዴ የማምለጫ ዘዴ ሳይሆን የመሞቻ ዘዴ ነው ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን ከሙሉ አምላክነቱ ቀንሶ "ብቻ" በሚለው ቃል ገድቦ ማስቀመጡ የማይሰረየውን ሃጢያት "መንፈስ ቅዱስን መስደብ(ማቴ.12፡31-32) ውስጥ የገባ አባባል ነው፣ እነዚህ ሰዎች ለዚህ አስተምህሮታቸውና እምነታቸው የሃጢያት ስርየት የላቸውም፡፡

ይህም መንፈስ ቅዱስን በሙሉ ማንነቱ ካለማየት የመጣ ችግር ነው፣ ሌላው ቀርቶ፣

> ኢሳ.11፡24 "የእግዚአብሄር መንፈስ፣ <u>የጥበብ</u>ና <u>የማስተዋል</u> መንፈስ፣ <u>የምክር</u>ና <u>የሃይል</u> መንፈስ፣ <u>የእውቀት</u>ና <u>እግዚአብሄርን የመፍራት</u> መንፈስ ..."

የሚለውን ቃል ሙሉውን እንኳን መውሰድ አልቻሉም ምክንያቱም ሌሎቹን ከወሰዱ ሙሉ አምላክ ሆኖ ወደ ስላሴ አስተምህሮ ይሄድባቸዋል፣ ስለዚህ ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር የምትሄደዋን "የሃይል" የምትለዋን ብቻ ለይተው አወጡ፡፡

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በኛ ቋንቋ ልንገልፀው የማንችለው ሙሉ እግዚአብሄር አምላክ ነው፡፡

- ***<u>ሙሉ አምላክ በመሆኑም፣</u>***
  - ፈጣሪ ነው - ዘፍ.1፡2, ኢዮ.33፡4, መዝ.104፡30
  - ሁሉን ያውቃል - ኢሳ.40፡13, 1ቆሮ.2፡10-11, ዮሐ.14፡26
  - በሁሉም ስፍራ ይገኛል - ኢዮ.139፡7, መዝ.139፡7
  - ሁሉን ቻይ ነው - ሮሜ.15፡19
  - ዘላለማዊ ነው - ዕብ.9፡14
  - የልብን ያውቃል - ሮሜ.8፡27
  - አይታለልም - ሐስ.5፡3-4
  - ህይወት ይሰጣል - ዮሐ.6፡63

---

[125] ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሄር መፅሀፍ ፈልጉ - መሰረታዊ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ማስተማሪያ**፣ ገፅ 41፣ ትምህርተ 23/3/ሀ

## ➢ እንደ አምላክነቱም ለሰዎች ፀጋን ይሰጣል

- ሀይልን ይሰጣል - ሐስ.1፡8
- ጥበብ፣ እውቀትና ማስተዋልን ይሰጣል-ዘፀ.31፡3,ዘፀ.35፡31,ኢሳ 11፡2
- እምነት፣ የፈውስና የተአምራት ፀጋዎችን ይሰጣል - 1ቆሮ.12፡8-9
- ትንቢት ያናግራል - ዘኁ.11፡25-26, 1ሳሙ.10፡10, 1ሳሙ.19፡20-23, ሉቃ.1፡67, ሐስ.19፡6
- ስብከትን ይሰጣል - ኢሳ.61፡1, ሚኪ.3፡8, 1ጴጥ.1፡12
- ይቀድሳል - ሮሜ.15፡15-16, 1ቆሮ.6፡11, ቲቶ3፡5
- ብፁአን ያደርጋል - 1ጴጥ.4፡14
- ያስነግሳል - መሳ.3፡10
- ይሾማል - ሐስ.20፡28
- ያድናል - ፊሊ.1፡19
- ያሳርፋል - ኢሳ 63፡14
- መገለጥ ይሰጣል - 1ቆሮ.12፡7
- ቃልን ይገልፃል - ሐስ.4፡31
- ልሳን ይሰጣል - ሐስ.2፡4, ሐስ.19፡6
- ይለውጣል - 1ሳሙ.10፡6
- አርነትያወጣል-2ቆሮ.3፡17

## ➢ ሰብአዊ ማንነት አለው

የሐዋርያት ቤተክርስቲያን “መንፈስ ቅዱስ ሀይል ብቻ ነው” ወይ “እስትንፋስ ብቻ ነው” የሚለው አስተምህሮዋ ስህተት መሆኑና መንፈስ ቅዱስ ህይወት፣ እውቀት፣ ስሜትን፣ ፈቃድን፣ ሃላፊነት … ያለው ሙሉ “ሰብአዊነት” ያለው አምላክ መሆኑን መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፣ በዚህም መንፈስ ቅዱስ፡-

- ያዝናል - ኤፌ.4፡30
- ይናገራል - ሐስ.13፡2
- ይመሰክራል - ዕብ.10፡15-16
- ይመክራል - ኢሳ.11፡2
- ይልካል - ሐስ.13፡4
- ይከለክላል - ሐስ.16፡6

- ይወቅሳል - ዮሐ.16፡8
- ይማልዳል - ሮሜ.8፡26
- ይመራል - ዮሐ.16፡13
- ያስተምራል - ሉቃ.12፡12
- ያስረዳል - ሉቃ.2፡26
- ያሳያል - ዕብ.9፡8
- ያፅናናል - ሐስ.9፡31
- ከቅዱሳን ጋር ህብረት ያደርጋል-2ቆሮ.13፡14 ...

በዚህም "አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ" የሚለውን ሀሳብ ለማጠናከር ሲባል መንፈስ ቅዱስን ከሙሉ አምላክነቱ ዝቅ ለማድረግ የተደረገው ሙከራ ስህተትም፣ ይቅር የማይባል ሀጢያትም ነው፡፡

በአጠቃላይ አብም መንፈስ ቅዱስም ወደ የትም መጠጋጋት የማይችሉና ሙሉ አምላክነት ያላቸው መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

#### 5.1.2.2.3. "የኢየሱስ ስጋ መለኮታዊ እንጂ ሰብአዊ አይደለም"

ቤተክርስቲያንዋ "አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮዋ ምክንያት ብዙ ነገሮች ተረብሸውባታል፣ ከላይ እንዳየነው አብንና መንፈስ ቅዱስን ኢየሱስ ውስጥ ለማጠቃለል ሞክራለች፣ እንደዚህ ለማድረግ ደግሞ "የኢየሱስ ስጋ እንደ ሰው ስጋ መሆን የለበትም" በማለት ስጋውን መለኮታዊ ታደርጋለች፡፡

- [126] "ክርስቶስ ከሴት ዘር የተወለደ መባል ሲገደድ ከሴት ስጋና ደም ተወለደ ማለት ሳይሆን ... ንፁህ መለኮታዊ ሰው ሆኖ ከድንግል ማርያም ማህፀን የተወለደ ማለት ነው፡፡"
- [127] "ኢየሱስ ክርስቶስ የአብርሃም ወይም የዳዊት ወይም የሴት ዘር ተቀላቅሎበት የተወለደ አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡"

[126]ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሄር መፅሀፍ ፈልጉ - መሰረታዊ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህር ማስተማሪያ**፣ ገፅ 33፣ ትምህርተ 21/2/ቸ/ሐ
[127] ibid 47፣ ትምህርተ 24/3

ነገር ግን ኢየሱስን የተዋሃደው የሰው ስጋ ያውም ከዳዊት ዘር የሆነ ስጋ እንጂ መለኮታዊ ሰውነት አይደለም፣ ይህም እውነታ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ብዙ ቦታዎች ላይ ተብራርቶ ተነግሯል፣

- <u>አብሮ አደጎቹም ሆነ ህዝቡ ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው የሚኖረው በሰው ስጋ በመሆኑ እንደ ማንኛውም ሰው ሲመለከቱት የነበረ መሆኑ፣</u>
  - ማቴ.13፡55 “ይህ የፀራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን?”
  - ዮሐ.8፡57 “አይሁድም ገና ሀምሳ አመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት፡፡”
  - ዮሐ.10፡33 “አይሁዳውያኑም፣ ስለ መልካም ስራ አንወግርህም፣ ስለ ስድብ፣ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ፡፡”
- <u>የለበሰው አካል መለኮታዊ አካል ሳይሆን ስጋዊ አካል በመሆኑ ስጋዊ የእድገት ደረጃዎችን፣ ስሜቶችንና መከራዎችን መቀበሉ፣</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተረገዘ - ማቴ.1፡18 | ደከመ - ዮሐ.4፡6 | አለቀሰ - ዮሐ.11፡35 |
| ተወለደ - ሉቃ.2፡7 | ተኛ - ማቴ.8፡24 | ተፈተነ-ማር.1፡12-13 |
| አደገ - ሉቃ.2፡52 | ተራበ - ማቴ.4፡2 | ተደበደበ-ሉቃ.22፡64 |
| ተጠመቀ-ማቴ.3፡13-17 | ተጠማ-ዮሐ.19፡28 | ተገደለ - 27፡50 ... |

- <u>የለበሰውም ስጋ የዳዊት ዘር ሀረግ መሆኑን፣</u>

ማቴ.1፡1-17 ላይ የኢየሱስ የዘር ሀረግ በዝርዝር ቀርቧል፣ በሌሎች ክፍሎችም ላይ የኢየሱስ የዘር ሀረግ “ከእስራኤል ዙፋን ከዘርህ ሰው አታጣም”(1ነገ.9፡5፣ 2ዜና.7፡18 ...) የሚል ቃል ኪዳን ከተገባለት ከዳዊት ዘር መሆኑ ተነግሯል፣

- ሮሜ.9፡5 “... <u>ከእነርሱም</u>(ከእስራኤላውያን) ክርስቶስ <u>በስጋ መጣ</u> ...”
- ሮሜ.1፡3-4 “ይህም ወንጌል <u>በስጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ</u> ... ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡”

- ሐስ.13፡23 "ከዚህም ሰው(ከዳዊት) ዘር እግዚአብሄር … ኢየሱስን አመጣው፡፡

- ራዕ.22፡16 "እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ፡፡ እኔ የዳዊት ስርና ዘር ነኝ …"

በዚህም ኢየሱስ የለበሰው ስጋ የሰው ስጋ እንጂ መለኮታዊ ስጋ አለመሆኑን እንመለከታለን፣ ይህ የሆነው ደግሞ ዝም ብሎ ሳይሆን ኢየሱስ የመጣለት ዋናው አጀንዳ በመሆኑ ነው፣ ኢየሱስ በሰው ስጋ መምጣት ያስፈለገው ስለሰው ልጆች ሀጢያት ዋጋ የሚከፍለው የሰው ልጆችን ስጋ በመልበስ በመሆኑ ነው፣

ዕብ.2፡14-17 "በህይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሀት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ነፃ እንዲያወጣ በስጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ … በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው፡፡"

ኢየሱስ የመጣው ለዚህ ትልቅ አጀንዳ በመሆኑም የመጣው በስጋ አካል ነው፡፡

ኢየሱስ የመጣው "በስጋ አካል ነው" የሚለውና "በሌላ አካል" ነው ብሎ ማመን መካከል ከባድ ልዩነት እንዳለ መፅሀፍ ቅዱሱ ይናገራል፣

- 1ዮሐ4፡2-3 "የእግዚአብሄርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሄር ነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስም በስጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሄር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው፤ ይህ እንዲመጣ ሰምታችኋልና፣ አሁንም እንኳን በአለም አለ፡፡"

- 2ዮሐ.1፡7-8 "ብዙ አሳቾች ወደ አለም ገብተዋልና እነሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ **የማያምኑ ናቸው**፣ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው፡፡ ሙሉ ደምወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሰራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡ ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖረው ሰው አምላክ የለውም፣ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት፡፡ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይንም

ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ስራው ይካፈላልና፡፡”

በዚህም አንድ ሰው አምላክ የሆነው ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የማይቀበሉትን ሰላም በማለቱ ብቻ እግዚአብሄር ካስቀመጠለት ክብር ይጎድላል፡፡

### 5.1.2.3. የእግዚአብሄር ስላሴነት ሊሸፈን የማይችል ግልፅ ነገር መሆኑ

ከላይ እንደተመለከትነው የሐዋርያት ቤተክርስቲያን የስላሴ አስተምህሮትን በመቃወም “አንድ አምላክ ኢየሱስን ብቻ” በማለት አብና መንፈስ ቅዱስን በኢየሱስ ውስጥ ሸፍና ለመሄድ ሞክራለች ነገር ግን ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው ይህ ስህተት መሆኑና፣

- እግዚአብሄርና አብ የሚባሉት ማንነቶች ከኢየሱስ በላይ የሆኑ ማንነቶች መሆኑን፣
- መንፈስ ቅዱስም ብቻውን ሙሉ አምላክነት እንዳለውና በሱ ማንነት ላይ ደግሞ ያለ ዕውቀት ቃል መናገር የማይሰረይ ሀጢያት መሆኑን፣
- የኢየሱስ አካል ሶስቱንም መለኮታዊ አካላቶች መሸከም እንዲችል መለኮታዊ ሰውነትን ማላበስ “የክርስቶስ ተቃዋሚ” እንደሚያስደርግ ተመልክተናል፣

በዚህም የ“አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ” አስተምህሮ መፅሀፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑና ለመርገምትም የሚዳርግ መሆኑን ተመልክተናል፣ ስለዚህ የመፅሀፍ ቅዱሱን ፈጣሪ አምላክን ትክክለኛ ማንነት ለማወቅ የ“ስላሴ” አስተምህሮ በጥንቃቄ መመልከት የግዴታ ይሆናል፡፡

በርግጥ እግዚአብሄር ፈጣሪ በመሆኑ ሰው ደግሞ ተፈጣሪ በመሆኑ፣ የእሱን ስላሴነት በሙላት ማወቅ አይችልም፣ ይህም በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል መኖር ያለበት ተፈጥሮአዊ ልዩነት ነው ነገር ግን እግዚአብሄር ደግሞ እንድናውቀው ባስቀመጠልን የእውቀት መጠን ማንነቱን ማወቅ እንችላለን፡፡

የሚገርመው ከስላሴ ዕውቀት ጋር በተያያዘ መፅሀፍ ቅዱሱን በጥንቃቄ ስንመለከት የስላሴ እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ ግልፅ እየሆነ የመጣ

እውቀት ነው፣ የቀድሞዎቹ ቅዱሳን ከዚህ ትውልድ በላይ ግራ ተጋብተው ነበረ ነገር ግን እንደ ሐዋርያት ቤተክርስቲያን ሳይሰናከሉበት በገባቸው መንገድ ገልፀው አልፈዋል፣ አንዳንዶቹ አንዱ በሶስት ማንነት የሚሰራበትን አሰራርን መግለፅ አቅቷቸው በነጠላ ቁጥርና በብዙ ቁጥር ሰዋሰው ሲምታቱ፣ ሌሎቹ ደግሞ በመካከላቸው የነበረውን ንግግር መግለፅ አቅቷቸው "እግዚአብሄር እግዚአብሄርን፣ ጌታዬ ጌታዬን" ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ "የእግዚአብሄር መልአክ" ብለውት ተመልሶ እሱኑ "እግዚአብሄር" ሲሉ፣ ሌሎቹ ከሶስቱ አንዱን ለይተው ባለማወቃቸው አንደኛውን ስላሴ በአገልግሎቱ "መልከ ፄዴቅ" ብለውት ሲጠሩት፣ ያዕቆብ ደግሞ "አንደኛውን" እግዚአብሄር "ስምህ ማነው እስከማለት" ሲደርስ እንመለከታለን ነገር ግን በአዲሱ ኪዳኑ "አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የሚለው ስም ተገለጠ፣ ሁሉንም በዝርዝር እንመለከታለን፣

### 5.1.2.3.1. <u>በነጠላ ቁጥርና በብዙ ቁጥር ሰዋሰው የተምታቱ</u>

ይህንን የምንመለከተው በአብርሃም ንግግርና በሙሴ ፅሁፎች ውስጥ ነው፣

- <u>**አብርሃም**</u>

ዘፍጥረት ምዕራፍ 18 ላይ በሶስት ሰው <u>ተመስለው</u> ለአብርሃም የተገለጠው/ጡት ስላሴ የሆነው እግዚአብሄር ነው፣ አብርሃም በዚህ የስላሴ ማንነት እንዴት ግራ በተጋባ ሰዋሰው እንዳናገረው/እንዳናገራቸው እስቲ እንመለከት፡-

> ዘፍ.18፡1-33 "በቀትር ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ <u>እግዚአብሄር</u> … ተገለጠለት፣ ዓይኑንም አነሳና እነሆ <u>ሶስት ሰዎች</u> በፊቱ ቆመው አየ … ወደ ምድርም ሰገደ እንዲህም አለ፣ አቤቱ <u>በፊትህ</u> ሞገስ አግንቼ እንደሆነ ባሪያህን <u>አትለፈኝ</u> ብዬ እለምናለሁ፣ <u>ጥቂት ውሀ ይምጣላችሁ</u> … <u>እነርሱም</u> ሚስትህ ሳራ ወዴት ናት <u>አሉት፣</u> እርሱም በድንኳን ውስጥ ናት አላቸው፡፡ <u>እርሱም</u> የዛሬ አመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት <u>እመለሳለሁ</u> ሚስትህ ሳራም ልጅን ታገኛለች <u>አለ</u> …
>
> ሰዎቹም ተነስተው ወደ ሰዶም አቀኑ አብርሃምም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሄደ … እግዚአብሄርም <u>አለ</u>፣ የሰዶምና ገሞራ ጩኸት እጅግ

በዝቷልና ... ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ፣ ወደ ሰዶምም ሄዱ አብርሃም ግን በእግዚአብሄር ፊት ገና ቆሞ ነበር ...”

ከዚያ ምዕራፍ 19 ላይ ሁለቱ ለሎጥ ተገለጡለት፣ ምክንያቱም አንደኛው (እግዚአብሄር) በ18፡22 አብርሃም ጋር ስለነበረ፡፡

በዚህ ውስጥ አንዱ እግዚአብሄር በሰው መልክ በሶስት ማንነት(ስላሴ) የተገለጠበት እውነታ እንመለከታለን፣ አብርሃምም በዚህ ለሰው አእምሮ ሊገባ በሚከብደው የስላሴ አሰራር በአነጋገር እንኳን ሲቸገር እንመለከተዋለን፡፡

- **ሙሴ**

ሙሴ የኦሪት መፅሀፍትን የፃፈው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው ነገር ግን ከፍጥረት ታሪክ ጋር የተገለጠለትን የእግዚአብሄርን ስላሴነት ማንነት ለመግለፅ በነጠላ ቁጥርና በሙሉ ቁጥር አነጋገር መካከል ሲቸገር ነበረ፡-

- ዘፍ.1፡26-27 “እግዚአብሄርም አለ፡፡ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤”
- ዘፍ.3፡22 “እግዚአብሄር አምላክም አለ፡፡ እነሆ አዳም ክፉውንና መልካሙን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤”
- ዘፍ.11፡6-7 “እግዚአብሄርም አለ ... ኑ እንውረድ ...”

ሙሴ ይህን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተመለከተውን እውነታ ለመፃፍ ከሰውኛ ቋንቋ በላይ ሆኖበት የቋንቋውን ሰዋሰው በመጣስ ነጠላ ቁጥርንና ብዙ ቁጥርን በማደባለቅ ሲፅፍ እንመለከተዋለን፡፡

### 5.1.2.3.2. <u>“እግዚአብሄርም ከእግዚአብሄር ዘንድ”፣ “ጌታዬ ጌታዬን” ያሉም ነበሩ</u>

የስላሴን ማንነት ባለማስተዋል ሌላ ግራ መጋባት የፈጠሩት ደግሞ ሙሴና ዳዊት ናቸው፣

- **<u>ሙሴ</u>** - “እግዚአብሄርም ከእግዚአብሄር ዘንድ አለ”

ከላይ ያየውን ታሪክ ሙሴ በዘፍጥረት ምዕራፍ 18 እና 19 ላይ ሲፅፈው በመጀመሪያ “ሶስት ሰዎች” አላቸው(ዘፍ. 18፡2)፣ መልሶ እነሱኑ መላዕክት አላቸው(ዘፍ.19፡1)፣ በመጨረሻ (ዘፍ.19፡24) ስላሴነቱን በሚያሳይ መልኩ “<u>እግዚአብሄርም ... ከእግዚአብሄር</u> ዘንድ” በማለት የስላሴን ምስጢራት በገባው መንገድ ገለጠው፡፡

- **<u>ዳዊት</u>** - “ጌታ ጌታዬን አለ”

የስላሴ ምስጢር ሙሴ እንደ ገባው “እግዚአብሄር ከእግዚአብሄር ዘንድ” እንዳለው ዳዊትም “ጌታ ጌታዬን” በማለት በገባው መንገድ ሁለቱንም ጌቶች ገለፃቸው፡፡

> ማር.12፡36 “ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ <u>ጌታ ጌታዬን</u>፣ ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው፣ አለ፡፡”

ዳዊት በተሻለ መንገድ ገልፆታል/ገልጿቸዋል፡፡

### 5.1.2.3.3. <u>አንዴ “መልአክ” ብለውት መልሰው እሱኑ “እግዚአብሄር” ያሉም ነበሩ</u>

የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች የስላሴን አሰራር እንደ እኛ በተሻለ መንገድ ባያውቁትም እውነታውን ግን ተረድተውታል፣ በዚህም ወደ ምድር ወርዶ ሲሰራ የነበረውን አንዱን ስላሴ በመጀመሪያ “መልአክ” ብለውት መልሰው እሱኑ “እግዚአብሄር” ብለውታል፣ ያዩት ሰማያዊ ማንነትም የሚናገራቸው እንደ ተላከ መልአክ ሳይሆን በራሱ ፍቃድ ሁሉንም እንደሚያደርገው እንደ እግዚአብሄር ነበረ፡-

- **አጋር**
  ዘፍ.16፥9-13 "የእግዚአብሄር መልአክም፣ ወደ እመቤትሽ ተመለሺ ከእጅዋም በታች ሆነሽ ተገዢ … እርስዋም ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሄርን ስም ዔልሮኢ ብላ ጠራች፣ የሚያየኝን በውኑ እዚህ ደግሞ አየሁትን? ብላለችና፡፡"

- **አብርሃም**

  ዘፍ.22፥11-12 "የእግዚአብሄር መልአክም ከሰማይ ጠራና አብርሃም አብርሃም አለው፣ እርሱም፣ እነሆኝ አለው፣ እርሱም በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት፣ አንድ ልጅህን ለኔ አልከለከልክምና እግዚአብሄርን የምትፈራ እንደሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ፡፡"

- **ያዕቆብ**
  ዘፍ.31፥11-13 "የእግዚአብሄርም መልአክ በህልም፡፡ ያዕቆብ ሆይ አለኝ፤ እኔም፡፡ እነሆኝ አልኩት … ሐውልት የቀባህበት በዚያም ለእኔ ስለት የተሳልህበት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ …"

- **ጌዴዎን**
  መሳ.6፥12-14 "የእግዚአብሄር መልአክ ለእርሱ ተገልጦ … እግዚአብሄርም ወደ እርሱ ዘወር ብሎ …"

- **ሆሴዕ**
  ሆሴ.12፥5-6 "(ያዕቆብ) ከመልአኩም ጋር ታግሎ አሸነፈ፣ አልቅሶም ለመነው … እርሱም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ነው፣ የመታሰቢያውም ስም እግዚአብሄር ነው፡፡"

በዚህም በአዲስ ኪዳኑ የተገለጡትን የእግዚአብሄር ስላሴነት "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ማለት ባይችሉም ከስላሴም የተገለጠላቸውን "የእግዚአብሄር መልአክ" ብለው መልሰው እሱኑ "እግዚአብሄር" ሲሉት ነበረ፡፡

### 5.1.2.3.4. ሌሎች ከሶስቱ አንዱን ለይተው ባለማወቃቸው አንዱን በአገልግሎቱ "መልከፄዴቅ" ሲሉት ነበረ

ከላይ የተመለከትነው ይህን በሰማያዊ ማንነት እየመጣ እንደ እግዚአብሄር የሚናገረውን አካል ሰዎች በተለያየ ስም ይግለፁት እንጂ ትክክለኛ ስሙ በወቅቱ አልታወቃቸውም ነበረ፣ ከቅዱሳኑ ደፈር የሚለው ያዕቆብ ስሙ ማን እንደሆነ ጠይቆት ነበረ፡-

ዘፍ.32፡29 "ያዕቆብም፣ ስምህን ንገረኝ ብሎ ጠየቀው፣ እርሱም ስሜን ለምን ትጠይቃለህ? አለው በዚያም ስፍራ ባረከው፡፡"

በርግጥ በዚያን ስፍራ ስሙን ሊነግረው አልፈለገም ምክንያቱም ቢነግረው ያዕቆብ የባሰ ብዙ ጥያቄዎች ይፈጠርበትና እንደ ሐዋርያት ቤተክርስቲያን የ"አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮት ይጀምር ነበረ፣ አንዳንዶቹ በወቅቱ ይህን ሰማያዊ ማንነት ስሙን ባይገልፅም በአገልግሎቱ ስሙ "መልከፄዴቅ" ብለው መጥራቱን መርጠዋል፣

ዘፍ.14፡18-20 "የሳሌም ንጉስ መልከፄዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅ አወጣ፣ እርሱም የልዑል እግዚአብሄር ካህን ነበረ፣ ባረከውም፣ አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሄር የተባረከ ነው፣ ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሄርም የተባረከ ነው አለውም፣ አብርሀም ከሁሉ አስራትን ሰጠው፡፡"

አብርሃም ለመልከፄዴቅ አስራት ሰጠው፣ "አስራት" የሚሰጠው ለእግዚአብሄር ብቻ ነው፣ አብርሃምም አልተሳሳተም ምክንያቱም መልከፄዴቅ ከስላሴ አንዱ የሆነው ኢየሱስ ነበረና፣

ዕብ.7፡1-3 "የሳሌም ንጉስና የልዑል እግዚአብሄር ካህን የሆነ ይህ መልከፄዴቅ አብረሃም ነገስታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፣ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አስራትን አካፈለው ... (እርሱ) <u>በእግዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ</u> ይኖራል፡፡"

"የዘላለም ካህን" የሚባለው፣ በእግዚአብሄር ልጅ የሚመሰለውና ለዘመኑ ቁጥር የሌለው ኢየሱስ መሆኑን በአዲስ ኪዳን እውቀታችን

እናውቃለን፣ በወቅቱ ቅዱሳኑ ስሙን መግለፅ ባይችሉም በአገልግሎቱ “መልከፄዲቅ” ብለውት ነበረ፡፡

### 5.1.2.3.5. በጊዜ ሂደት የስላሴ ማንነት ግልፅ እየሆነ መምጣት

በጊዜ ሂደት ውስጥ እግዚአብሄር ለሰው ልጆች ራሱን እየገለጠ ሲመጣ ሰዎች ስለ ስላሴ የተሻለ መረዳት ሲይዙ ነበረ፣ በዚህም የኋለኞቹ ነቢያት፣ የስላሴን ማንነት ከላይ ካየናቸው ቅዱሳን በተሻለ መንገድ ገልፀውታል፡፡

- ኢሳያስ

  - ኢሳ.42፡1 “(እግዚአብሄርም) እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ፣ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ፣ እርሱም ለአህዛብ ፍርድን ያወጣል፡፡”
  - ኢሳ.48፡12-16 “… እኔ ፊተኛውም ነኝ ኋለኛውም ነኝ፡፡ እጄም ምድርን መስርታለች … ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች … እኔ ከጥንት ጀምሮ በስውር አልተናገርኩም … አሁንም ጌታ እግዚአብሄርና መንፈሱ ልከውኛል፡፡”
  - ኢሳ.59፡15-21 “እግዚአብሄርም አየ … ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም፣ ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድህኒት አመጣለት … በአንተ ላይ ያለው መንፈሴ …”

እነዚህ በየጥቅሱ ውስጥ የተመለከቱት ሶስቱ ማንነቶች በአዲስ ኪዳኑ “አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ” የተባለውን የስላሴ ማንነት በብዥታም ቢሆን ማመልከት ችለዋል፡፡

- ዳንኤል

ዳንኤልም የተመለከተውም ራዕይ ተመሳሳይ ነው፣

- ዳን.2፡34-35 “እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየሁ … ምስሉን የመታ ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ ምድርንም ፈፅሞ ሞላ፡፡”

- ዳን.2፡44 "... እነዚያንም መንግስታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች ለዘላላምም ትቆማለች፡፡"
- ዳን.4፡17 "ልዑሉ በሰዎች መንግስት ላይ እንዲሰለጥን ..."

እዚህ ጋር ዳንኤል አንድ ተራራን በራዕይ ተመለከተ፣ የተመለከተውን ራዕይ ስናስተውል "ተራራው ተነቅሎ" አይደለም፣ የተራራው አንድ ክፍል የነበረ ድንጋይ ተፈንቅሎ ነው የወጣው፣ ወጥቶ ደግሞ ነገስታትን ፈጨ፣ ከዚያም ነገስታቱን ፈጭቶ እስከ ዘላለም ነገሰ፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ኢየሱስ ብዙ ቦታዎች ላይ በአለት/በድንጋይ ተመስሏል (ሉቃ.20፡17, ሮሜ.9፡32-33, ኤፌ.2፡20, 1ቆሮ.10፡4, 1ጴጥ.2፡4, 1ጴጥ.2፡6-7 ...)፣ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን በአርማጌዶን ጦርነት የዓለም መንግስታትን በማሸነፍ የራሱን መንግስት እንደሚመሰርት መፅሀፍ ቅዱሱ ይናገራል(ማቴ.21፡42-44, ራዕ.11፡15-18, ራዕ.19፡15-21 ...)፣ በዚህም ነገስታትን የሚፈጨው ከተራራው ላይ የተፈነቀለው ድንጋይ፣ ኢየሱስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም በብሉ ኪዳን ዘመን "አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የሚባለው ስም ባይገለጥ እንኳን ቅዱሳኑ የስላሴን አሰራር በጊዜ ሂደት ውስጥ፣ በተለያየ ደረጃ ማስተዋል ችለዋል፡፡

#### 5.1.2.3.6. ስላሴ በአዲስ ኪዳኑ ግልፅ መሆኑ

"ስላሴ" የሚለው ቃል የተፈጠረው መፅሃፍ ቅዱሱ ከተፃፈ ቦሃላ በኒቂያ ጉባኤ 134 ዓ.ም ነው፣ ቃሉም የተፈጠረው አንዱ እግዚአብሄር በሶስት ማንነቶቹ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ተገልፖ የሚሰራበትን አሰራርን ለመግለፅ በሚል ነው፣ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለውን በቀጣዩ 5.1.2.3.7 ክፍል የምንመለከት ቢሆንም ሶስቱም የእግዚአብሄር ማንነቶች በስላሴነት ሲሰሩ እንደነበረ ግን መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡-

- ማቴ.3፡16-17 "ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሄርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፣ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡"

- ማቴ.28፡192-20 "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው …"
- ዮሐ.14፡15-17 "ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ፡፡ እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አፅናኝ ይሰጣችኋል፡፡ እርሱም አለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ፡፡"
- ዮሐ.14፡26 "(ኢየሱስም) አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አፅናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችሃል …"
- ሐሰ.2፡32-33 "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሄር አስነሳው … ስለዚህ በእግዚአብሄር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው፡፡"
- ሐሰ.10፡38 "እግዚአብሄር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በሀይል ቀባው …"
- ዮሐ.15፡26 "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፣ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፡፡"
- 2ቆሮ.13፡14 "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሄርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ህብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡"
- 1ጴጥ.1፡1-2 "… እግዚአብሄር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው፣ በመንፈስም እንደሚቀደሱ፣ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ …"

እነኚህ የመፅሀፍ ቅዱሱ ቃላት የስላሴን አሰራር ለሚቃወሙት ከባድ ፈተና ናቸው፣ ይህንን የስላሴነት እውነታ መቀበል የማይችለው የቤተክርስቲያኗ አስተምህሮ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ እንመለከታለን፡፡

## 5.1.2.3.7. <u>ስላሴነት በተፈጥሮ ውስጥ መመልከቱ</u>

ብዙዎች ይህ የእግዚአብሄር ስላሴነት አሰራር እንግዳ ይሆንባቸዋል ነገር ግን ይህ አሰራር እንግዳ ሳይሆን በተፈጥሮ ውስጥ የተለመደ አሰራር ነው፣ ይህንን አሰራር ለመመልከት ለምሳሌ ያህል በሰውና በፀሃይ ውስጥ ያለውን ስላሴነት እንመልከት፡-

- **<u>የሰው ልጅ ስላሴነት</u>**

እግዚአብሄር የሰው ልጅን ሲፈጥር "በመልካችን" እንዳለው በመልኩ የሰውን መንፈስ ፈጠረ(ዘፍ.1፡27)፣ "እንደ ምሳሌአችን" እንዳለውም ደግሞ ሰው ስላሴነት እንዲኖረው ለተፈጠረው መንፈሳዊ አካል ስጋ አበጀለት(ዘፍ.2፡7) ከዚያ በውስጡ ነፍስን አኖረ(ዘፍ.1፡27)፣ በዚህም ሰው በስላሴ ምሳሌ ስጋ፣ ነፍስና መንፈስ ሆነ፡፡

ይህ እውነታ በአዲስ ኪዳኑም ተመልክቷል፡-

> 1ተሰ.5፡23 "የሰላምም አምላክ ራሱ <u>ሁለንተናችሁን</u> ይቀድስ፤ <u>መንፈሳችሁም</u>፣ <u>ነፍሳችሁም</u> <u>ሥጋችሁም</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈፅመው ይጠበቁ፡፡"

እዚህ ጋር እንዴት አንዱ ሰው ውስጥ ሶስት ማንነት(ስላሴነት) እንደሚገኝ እንመለከታለን፣ ይህም እውነታ የእግዚአብሄርን ስላሴነት በደንብ ለመረዳት በመጀመርያ በእጃችን ያለውን የራሳችንን ስላሴነት እንድንረዳ ይረዳናል፡፡

- **<u>የፀሃይ ስላሴነት</u>**

ፀሃይ ላይም በአንድነት ውስጥ ሶስትነትን እንመለከታለን፣ እነሱም በሰማዩ ላይ ያለችው ክብ ሆና የምትታየን አካል፣ ወደ ምድር ወርደው የሚሰሩት ብርሃንና ሀይል ናቸው፣ ሶስቱም አንድ ሆነው ነገር ግን በሶስት የተለያዩ መንገዶች የተለያዩ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ ሰማዩ ላይ ያለቸው ፀሃይ እንደ ንግስት በአከባቢው ያሉትን የተለያዩ ሃይላትን(የግራቪቲን፣ የሴነተሪፉጋል፣ የሴንትሪፔታል ... ሀይሎችን) አሸንፋ ምህዋርዋን አስጠብቃ በአካባቢው ነግሳ ትኖራለች፡፡

ብርሃንዋ ደግሞ እንደ ኢየሱስ በሚታይ መንገድ ለዓለም ያበራል፣ መፅሀፍ ቅዱሱም ኢየሱስን የዓለም ብርሃን ይለዋል(የሐ.1፥8-9, ዮሐ.8፥12…)፣ ሀይልዋ እንደ መንፈስ ቅዱስ በማይታይ መንገድ የህያዋንን የሀይል ምንጭ ሆኖ ህይወትን ተሸክሞ ይኖራል፣ በምድር ላይ ያለው ህይወታዊ ተንቀሳቃሽ ሁሉ በፀሃይ ሃይል ላይ እንደተመረኮዘው ሁሉ ህይወትም በእግዚአብሄር መንፈስ ላይ እንደተመረኮዘ መፅሀፍ ቅዱሱ "መንፈስህን ብትወስድ ፍጥረት ሁሉ በጠፋ ነበረ" (ኢዮ.34፥14-15) ይላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፀሀይ ብርሀንና የፀሀይ ሀይል ከፀሀይ ወጥተው ወደ ምድር መጥተው ስራ እንደሚሰሩት ሁሉ ከእግዚአብሄር ስላሴ ማንነት ውስጥም ኢየሱስ(ዮሐ.13፥3, ዮሐ.16፥27-28, ዮሐ.17፥8, ዮሐ.8፥42 …) እና መንፈስ ቅዱስ(ዮሐ.15፥26, ዮሐ.14፥16, ሐስ.2፥3-4 …) ወደ ምድር የወረዱት ከአብ ወጥተው ነው፡፡

በዚህ የፀሀይ ተፈጥሮ ውስጥ አንዱ እንዴት በሶስት ማንነት (ስላሴነት) እንደሚሰራ በተሻለ መንገድ እንመለከታለን፡፡

ይህን የሰው ልጅና የፀሀይ ስላሴ ተፈጥሮን በአንድ ላይ አጣምረን መመልከት ስንችል ደግሞ በእግዚአብሄር ውስጥ ያለውን ስላሴነት በተሻለ መንገድ እንረዳለን፡፡ እነኚህ ሁለቱ የሰውና የፀሀይ ስላሴነት ተፈጥሮና አሰራር የስላሴ አሰራር እንዲገባን ለምሳሌ ይቀረቡ እንጂ በሁሉም ስፍራ የሚገኘውን፣ "እኔ በአብ እንዳለሁ አብ በኔ እንዳለ" የሚለውንና "በምን ትመስሉኛላችሁ" የሚለው እግዚአብሄር ትክክለኛ መግለጫዎች አይደሉም፣ እግዚአብሄርን በራዕይ ያዩትም እነ ዮሐንስ፣ ዳንኤል … ያዩትን በሰው ቋንቋ መግለፅ አቅቶአቸው "እንደ"፣ "ይመስላል" … እንዳሉት አሁንም በ"እንደ" እና "ይመስላል" ብቻ በመውሰድ ነገር ግን በዚህ እውነታ ውስጥ አንዱ በሶስት ማንነት የሚሰራበትን እውነታ መመልከት ይቻላል፡፡

## <u>ማጠቃለያ (ሐዋርያት)</u>

ከላይ በተመለከትናቸው ምሳሌዎች በስላሴ ጉዳይ ላይ በአደናጋሪዎች ከመደናገር የሚጠብቀንን እውቀት አግኝተናል ነገር ግን የእግዚአብሄር ማንነት ሙሉ በሙሉ በሰው አዕምሮ ሊያዝ አይችልም፣ ልክ በ1.3 ክፍል እንደተመለከትነው "ጀበናን ጀበና እንደማይሰራው" ሁሉ ፈጣሪ ፍጥረታቱን የፈጠረው ከፍጥረታቱ በላይ በላቀ ማንነቱ በመሆኑ ነው፣ በዚህም ፈጣሪ በፍጥረታቱ ሙሉ በሙሉ ሊታወቅ አይችልም፣ ይህ በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል ያለ <u>ተፈጥሮአዊ ልዩነት ነው</u>፣ <u>ፈጣሪ ይቅርና ስለራሳችን ስላሴ ተፈጥሮ(ስጋ፣ ነፍስና መንፈስ) ያለን ዕውቀት ውሱን ነው</u>፡፡

ነገር ግን ይህ የሰው ልጅ የዕውቀት ክፍተት ለሐዋርያት ቤተክርስቲያን መስፋፋት የመሠረተ ድንጋይ ነው፣ በዚህም የቤተክርስቲያኗ ሰባኪዎች ለአንድ ክርስቲያን ሀይማኖታቸውን ሲሰብኩ በመጀመሪያ "በአዲስ ኪዳን ዘመን ጥምቀት ለምን በኢየሱስ ስም ብቻ ተፈፀመ?" በሚለው ጥያቄ ቀድመው ያደናብራሉ፣ ከዚያም የራሳቸውን መልስ፣ "ይህ የሆነው አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ ነው" በማለት የክርስትና መሠረት የሌለውን ሰው በቀላሉ በመማረክ ወደ ሀይማኖታቸው ይቀላቅላሉ፡፡

ይህንን ከባድ ጥያቄ ተገን በማድረግ መሠረታዊ እውቀት የሌለውን ክርስቲያን በራሳቸው መንገድ ይዘው ይሂዱ እንጂ፣ ይህ "አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮ ከላይ እንደተመለከትነው ስህተት በመሆኑ እያደር ሌሎች መቶ ጥያቄዎችን ይዞ ይመጣል፡፡ ይህም ሰይጣን ሄዋንን፣ እራሱ አደናባሪ ጥያቄ ጠይቆአት የራሱን ትንታኔ በመስጠት ከነበረችበት ገነት እንድትወጣ አድርጎ ከዚያ ከሌሎች ብዙ ተከታይ ጥያቄዎች ውስጥ የከተተበትን አጋጣሚ ይመስላል፡፡

ሌላው ከነ ሄዋን ታሪክ ጋር የሚመሳሰልበት ደግሞ ሰይጣን በገነት ውስጥ ያሉትን አዳምና ሄዋንን ታርጌት እንዳደረገው የቤተክርስቲያንዋ ታርጌትም ክርስቲያኖች ናቸው፣ የሚገርመው ደግሞ አዳምና ሄዋን በመሳሳታቸው ከገነት ከተባረሩ በኋላ ወደ ገነት መመለስ እንዳይችሉ እንደተደረገው፣ እነዚህ ከክርስትናው የወጡት ሰዎችም ወደ ክርስትናው መመለስ ሲያዳግታቸው እንመለከታለን ምክንያቱም ከላይ እንደተመለከትነው አስተምህሮታቸው የእግዚአብሄር መንፈስ ላይ በመናገር የማይሰረይ ሃጢያት

ውስጥ የሚያስገባ በመሆኑ፣ አዳም ወደ ኤደን ገነት እንዳይመለስ እግዚአብሄር መንገዱን እንደ ዘጋው የነዚህ ሰዎች መንገድም የተዘጋ ይመስላል፡፡

በዚህም ማንኛውም ሰው ከዚህ አሳሳች አስተምህሮ ራሱንና ሌሎችንም ሊጠብቅ ይገባል፣ ከላይ በ5.1.2.2.3 ክፍል እንደተመለከትነውም ዮሐንስ ይህንን አይነት አስተምህሮ የሚከተሉትን “በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ስራው ይካፈላልና፡፡” የሚል ከባድ መልዕክት የተናገረው መንገዱ መሄጃው እንጂ መመለሻው ከባድ በመሆኑ ነው፡፡

## 5.2. የይኾዋ(የጇሆቫ) ምስክሮች (Jhova Witness)

[128] "የጇሆቫ ምስክሮች ቤተክርስቲያን በ1870 ዓ.ም በአሜሪካዋ ፒትስበርግ ፔንስልቫኒያ ተመሠረተች፣ የምስረታዋ መነሻም የመስራቹ የቻርለስ ታዝ ራስልና ጓደኞቹ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን(ከታች በዝርዝር የምንመለከተው) "ነባሩ የክርስትና አካሄድ የተሳሳተ ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሱ ነው፡፡

ይህንንም በመጀመርያ በ"Herald of the Morning" በሚባል ጋዜጣ ከዚያም "Zion`s Watch Tower and Herald of Christ`s Presence" በሚባል መፅሄት በማሳተም ሰዎችን በመሰበክና በተለያዩ ቦታዎችም የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ማህበሮችን በማቋቋም ሀይማኖቱን በመመስረትና በማስፋፋታቸው ነው፣ ቤተክርስቲያንዋ በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ 8.45 ሚሊየን በላይ ተከታዮች አሏት፡፡"

ቤተክርስቲያንዋ እንደዚህ በቀላሉ ትመስረት እንጇ ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ፈታኝ ችግሮች አጋጥመዋታል፣ ከነዚህም ውስጥ ዋነኛው ችግር በቤተክርስቲያንዋ ነብያት የተተነበዩት ትንቢቶች በተደጋጋሚና በአስደንጋጭ ሁኔታ አለመፈፀማቸው ነው፣ [129] ዋና ዋናዎቹን ብንመለከት፡-

1. "የጌታ ምፅአት **በ1874 ዓ.ም** ነው፡፡" (Creation, Brooklyn: watch tower bible and tract society, 1927, 289)
2. "በመጪዎቹ 26 አመታት ውስጥ አሁን ያሉት መንግስታት እየሟሙ ያልቃሉ ... የእግዚአብሄር መንግስት **በ1914 ዓ.ም** መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ ይመሰረታል፡፡" (Studies in scriptures, Vol. 2 , Brooklyn: watch tower Bible and tract society, 1888, 98-99)
3. "ታማኝ እስራኤላውያን **በ1925 ዓ.ም** ትንሳኤ ያገኛሉ ... ከሙታንም እንደተነሱ ምልክት የሚያደርጉበት ጊዜ ነው፡፡" (Millions now living

---

[128] https://en.m.Wikipedia>wiki>Jehovah`s witnesses

[129] ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ(2016)፣ **አርዮሳውያን "የይሖዋ ምስክሮች" አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፣** ገፅ 131, 155-160

will Nevere Die, Brooklyn: Watch tower Bible and tract Society, 1920, 88-90)

4. በራዕ.7፡1-8 ላይ የተገለፀው የ144,000 ሰዎች ጉዳይ አስመልክቶ ቁጥሩ መች እንደሚሞላ የተለያዩ ትንቢቶች ተነግረዋል፣
   - በ1881 ዓ.ም፣ የቤተክርስቲያኗ መስራች ቻርለስ ታዝ ራስል (The kingdome come, p. 362)፣
   - በ1931 ዓ.ም፣ ጆርጅ ፍራንክሊን ራዘር ፎርድ (Let God be true, 1946, p. 298)፣
   - በ1935 ዓ.ም፣ ናታን ሆመር ኖር (watchtower 2007,may 1, p.30)
5. "**በ1975 ዓ.ም** የሰው ልጆች የ6,000 አመታት ኑሮ ያበቃል፡፡" (Awake, 8 october, 1894, 1675)

በነዚህ ባልተሳኩ ትንቢቶች ምክንያት ቤተክርስቲያኗ ብዙ ምዕመናኖችን አጥታለች ብዙ ችግሮችም ተፈጥሮባት ነበረ፣ በዚህም ሰበብ ቤተክርስቲያኗ አስተምህሮቶችዋን በየጊዜው ስትቀያየር ቆይታ በመጨረሻም በቤተክርስቲያኗ ምንም አይነት ትንቢት እንዳይነገር እስከማገድ ደረሰች፡፡

ቤተክርስቲያንዋ ከሌሎች ቤተክርስቲያናት የምትለይበት ብዙ አስተምህሮዎች አሉዋት፣ "የስላሴ ትምህርት ስህተት ነው፣ ዓለም ለዘላለም ናት፣ ኢየሱስ ሚካኤል ነው፣ ሰው ከሞተ በኋላ በህይወት የምትቀጥል ነፍስ/መንፈስ የሚባል ነገር የለም፣ ሲኦል የሚባል ዘላለማዊ የስቃይ ቦታ የለም፣ ኢየሱስ "ክርስቶስ" የሆነው ሲጠመቅ ነው የነገሰውም በ1914 ዓ.ም ነው፣ ክርስቶስ የተሰቀለው በአንድ እንጨት መስቀል ላይ እንጂ "†" ተደርጎ በተሰራ የመስቀል እንጨት አይደለም፣ የሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ፣ ደም መለገስና መውሰድን ሀጢያት ነው፣ በውትድርና፣ በፖለቲካ (የፓርቲ አባልነት፣ ለምርጫ አለመወዳደርና ድምፅ መስጠት) እና የሰንደቃላማ መዝሙር ላይ መሳተፍ ሀጢያት ነው" የሚሉ ናቸው፡፡

ከነዚህም ውስጥም ዋና ዋናዎቹን፡-

- “የስላሴ አስተምህሮ ስህተት ነው”፣
- “የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ በህይወት የምትቀጥል ነፍስና መንፈስ የሚባል ማንነት የለውም”፣
- የመጨረሻ ዘመን (“1914 ዓ.ም ኢየሱስ የነገሰበት አመት ነው፣ በሺሁ አመት 144,000 የጂሆቫ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ይፈርዳሉ፣ የሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ፣ ምድር ገነት ናት፣ “ነፍስ ለዘለአለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ቦታ የለም”)፣

የሚሉትንና ለነዚህ አስተምህሮዎች ድጋፍ እንዲሆን የተዘጋጀውን የቤተክርስቲያኗን “የአዲሱ አለም መፅሀፍ ቅዱስ” ይዘት እንመለከታለን፡፡

### 5.2.1. <u>“የስላሴ አስተምህሮት ስህተት ነው”</u>

የጂሆቫ ቤተክርስቲያን የስላሴን አስተምህሮት ትቃወማለች፣ ለዚህም ዋነኛ ምክንያትዋ ከላይ ሐዋርያቶች ጋር እንደተመለከትነው “እግዚአብሄር አምላክ አንድ ነው” ከሚለው መነሻ ነው ነገር ግን ከሐዋርያት በተለየ መፅሀፍ ቅዱሱ “አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ” የሚለው ውስጥ፣ አብን በቀጥታ “እግዚአብሄር ነው” ስትል ሌሎቹን የእግዚአብሄር የስላሴ ማንነቶችን ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ደግሞ አምላካዊ ማንነት በመከልከል፣ ወልድ የተባለው ኢየሱስ “መልአኩ ሚካኤል ነው” ስትል፣ መንፈስ ቅዱስን ደግሞ እንደ ሐዋርያቱ “ሰብአዊ ማንነት የሌለው የእግዚአብሄር ሀይል ነው” ትላለች፣ ሁሉንም ከመፅሀፍ ቅዱስ አንፃር ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 5.2.1.1. <u>ኢየሱስ</u>

ቤተክርስቲያኗ የአብ ወልድና መንፈስ ቅዱስን “የስላሴን አስተምህሮ” በመቃወም፣ ለአብ የፈጣሪን ቦታ በመስጠትና “ኢየሱስ አምላክ አይደለም” በማለት ኢየሱስን ከፈጣሪ ቦታ አንስታው የሚካኤል ቦታ አስቀምጣዋለች፣ ይሁን እንጂ ኢየሱስን ከአምላክነት ቦታ ማንሳቱም ሆነ በሚካኤል ቦታ ማስቀመጡ ቀላል አልሆነላትም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

#### 5.2.1.1.1. "ኢየሱስ አምላክ አይደለም"

ቤተክርስቲያኗ ኢየሱስን ከአምላክነት ቦታ ማንሳት ቀላል ስራ አልሆነላትም፣ ለዚህም ብዙ እስትራቴጂዎችን ተከትላለች፣ ይህም "ኢየሱስን ዘላለማዊ አምላክ ሳይሆን ክርስቶስ የሆነው ሲጠመቅና መንፈስ ቅዱስ ሲያርፍበት ነው" ከሚለው አንስቶ በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ የኢየሱስን አምላክነት የሚያሳዩ ቃላትን እስከ መቀየር በመሄድ ነው:-

1. [130] "ኢየሱስ በተጠመቀበት እለት የአምላክ መንፈስ ወይም ሀይል በላዩ ሲወርድበት መሪና ንጉስ እንዲሆን ተሾመ መሲህ ወይም ክርስቶስ ሆነ"፣

   ኢየሱስ ግን ሲወለድም ክርስቶስና ንጉስ እንደነበረ መፅሀፍ ቅዱሱ ይናገራል:-

   - ➢ ሳይጠመቅ በፊትም ክርስቶስ ነው፣
     - ሉቃ.2፡11 "ዛሬ በዳዊት ከተማ መድሃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነው ተወልዶላችኋልና፡፡"
     - ማቴ.2፡4 "የካህናትንም አለቆች የህዝቡንም ፃፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው፡፡"
     - ሮሜ.9፡5 "... ከእነርሱም(ከእስራኤላውያን) ክርስቶስ በስጋ መጣ..."
     - 1ዮሐ.2፡22 "ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን የሚክድ በቀር ውሸተኛ ማነው?" ይለናል፣
   - ➢ ሳይጠመቅ በፊትም ንጉስ ነው
     - ማቴ.2፡1-2 "... የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት ነው?"
     - ዕብ.7፡1-4 "የሳሌም ንጉስና የልዑል እግዚአብሄር ካህን ... የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የፅድቅ ንጉስ፣ ኋላ ደግሞ የሳሌም ንጉስ ማለት የሰላም ንጉስ ነው፣ አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍፃሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል፡፡"

[130] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 40

በዚህም "ኢየሱስ ከጥምቀቱ በፊት ክርስቶስ አይደለም፣ ንጉስ አልነበረም" ማለቱ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

2. ሊቋቋሙት ያልቻሉዋቸውን የኢየሱስን አምላክነት የሚያሳዩ የመፅሀፍ ቅዱሱን ቃላትን መቀየር፣ ለምሳሌ ዮሐ.1፥1-3 ብንመለከት፣

➢ አሪጅናሉ መፅሀፍ ቅዱስ

"በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሄር ነበረ፡፡ ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፡፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነው አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡" ይላል፣

➢ የጂሆቫ መፅሀፍ ቅዱስ

"በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም ከአምላክ ጋር ነበረ፣ ቃልም አምላክ ነበረ፡፡ እሱም በመጀመሪያ ከአምላክ ጋር ነበረ፡፡ ሁሉም ነገሮች ወደ ህልውና የመጡት በእሱ በኩል ነው፣ ያለ እሱ ወደ ህልውና የመጣ አንድም ነገር የለም፡፡"

እነዚህ ከስር የተሰመሩት ከክርስትናው መፅሀፍ ቅዱስ የተለዩት "ጋር"፣ "በኩል" እና "አምላክ" የሚሉት ቃላት የገቡበት ተልዕኮ አላቸው፣ ይህም፣

- "ጋር" የሚለው አድራጊ ባለቤትነትን ሳይሆን አጠገብነትን ያሳያል፣ በዚህም ኢየሱስ "ዋናው ፈጣሪ ሳይሆን ፈጣሪ አጠገብ ነበረ" ለማለት ነው፣
- "በኩል" የሚለው ቃል አሁንም የድርጊቱ ባለቤትነትን ሳይሆን አድራጊው ባለቤት ድርጊቱን ለማድረግ የተጠቀመበት መሆኑን ለማሳየት ነው፣
- "ቃልም እግዚአብሄር ነበረ" የሚለውን "ቃልም አምላክ ነበረ" በሚለው የተቀየረው ደግሞ "እግዚአብሄር" እና "አምላክ" የተባለውን ማንነት የተለያዩ አካላት በማድረግ "ኢየሱስ እግዚአብሄር አይደለም" ለማለት እንዲያመች የተሰራ ቅንብር

ነው፣ ለቅንብሩ አማርኛው ባይመችም በእግሊዘኛው መፅሀፍ ቅዱሳቸው ላይ ቅንብሩ በግልፅ ተመልክቷል፣

"Joh.1:1 "In the beginning was the word, and the word was with God, and the word was a god."

እዚህ ጋር "God" የሚለው ዋናው አምላክ ሲሆን "ኢየሱስ ዋናው አምላክ አይደለም" ለማለት ኢየሱስን "a god" በሚለው አነስተኛ አማልክት በሚጠሩበት ስም ጠርተውታል፣ ይህም ኢየሱስ አምላክ ቢሆንም "ዋናው አምላክ አይደለም" በሚለው ለመፍታት እንዲያመቻቸው ነው፣ ነገር ግን ኢየሱስ ዋናው አምላክ መሆኑን በብዙ የመፅሀፍ ቅዱሱ ቦታዎች ላይ ተመልክቷል፡፡

ከመነሻውም ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው ስላሴ ከሆነው የእግዚአብሄር ማንነት ወጥቶ ነው(ዮሐ.13፡3, ዮሐ.16፡28, ዮሐ.17፡8 ...) በዚህም ኢየሱስን ከዋናው አምላክ ለያይቶ መመልከት አይቻልም፣ ኢየሱስ ምንም እንኳን ለመጣለት አላማ ሲል ከአምላካዊ ማንነቱን ራሱን ባዶ በማድረጉና በተዋሃደው ስጋ ምክንያት ውሱንነቶች ቢመጡበትም፣ ኢየሱስ ግን ሙሉ፡-

- አምላክ ነው- ሮሜ.9፡5,2ጴጥ.1፡1, ቲቶ.2፡12-13,ኢሳ.9፡6,ዕብ.1፡4-6...
- እግዚአብሄር ነው - ዮሐ.1፡1-14, ማቴ.1፡23, ዮሐ.16፡30 ...
- ከአብ ጋር አንድ ነው - ዮሐ.10፡30
- ፈጣሪ ነው - ዮሐ.1፡1-14, ቆላ.1፡15-16, ዮሐ.10፡28, ዮሐ.5፡21 ...
- "ጌታ" ነው - ኢየሱስ ብዙ ቦታዎች ላይ ጌታ ተብሏል ነገር ግን የኢየሱስ ጌትነት እንደ እግዚአብሄር ጌትነት ከሌሎቹ ጌትነት የላቀ በመሆኑ "ጌታ" ለተባሉት እንኳን ጌታ መሆኑን ለማሳየት "የጌቶች ጌታ" መሆኑን ተመስክሮለታል(ራዕ.17፡14)
- ሁሉን ቻይ ነው - ዮሐ.1፡3
- ሁሉን አዋቂ ነው - ዮሐ.2፡25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.21፡17, ዮሐ.1፡48-50, ዮሐ.2፡24-25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.6፡64, ዮሐ.21፡17, ማር.2፡8 ...
- በሁሉም ቦታ ይገኛል - ማቴ.18፡20, ማቴ.28፡20 ...
- ዘላለማዊ ነው - ዕብ.13፡8, ራዕ.1፡17, ራዕ.22፡13 ...

- የልብን ያውቃል - ዮሐ.4፡29፣ ማቴ.26፡21-25 …
- ስግደትን ተቀብሏል - ስግደት የሚደረገው ለአምላክ እግዚአብሄር ብቻ ነው (ዘፀ.34፡14)፣ ኢየሱስም አምላክ እግዚአብሄር በመሆኑ ስግደትን ተቀብሏል በዚህም ሰብአ ሰገል(ማቴ.2፡11)፣ ደቀመዛሙርቱ(ማቴ.14፡33, ማቴ.28፡17 …)፣ ከለምፁ የዳነው ሰው(ማቴ.8፡2)፣ አይኑ የበራለት ሰው(ዮሐ.9፡38)፣ ከእብደት የዳነው የጌርጌሴኖኑ ሰው(ማር.5፡6) …
- ፀሎት ወደሱ የሚደረግ መሆኑ - ፀሎት የሚደረገው ለእግዚአብሄር ብቻ ነው፣ ኢየሱስም እግዚአብሄር በመሆኑ ወደሱ ፀሎት ይደረጋል(ዮሐ.14፡14)
- መስዋዕት የሚቀርብለት አምላክ መሆኑ (ማቴ.9፡13)
- ሀጢያት መሰረዩ - ከአንዱ እግዚአብሄር በቀር ሀጢያት የሚሰርይ በሌለበት(ማር.2፡7) ኢየሱስ እግዚአብሄር በመሆኑ በራሱ ሀጢያት ይቅር ብሏል(ማቴ.9፡2-6)፡፡

በዚህም ኢየሱስ የሰው ልጆችን ለማዳን ስጋ በመልበሱ በመጣበት ውሱንነት እንዲሁም ሊከፍለው ላለው ቤዛነት አምላክነቱን ባዶ ማድረጉ እንጂ ኢየሱስ እራሱ እግዚአብሄር መሆኑና ከፈጣሪ እግዚአብሄርነቱ ማውረድ የማይቻል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

#### 5.2.1.1.2. <u>“ኢየሱስ መልአኩ ሚካኤል ነው”</u>

ቤተክርስቲያኗ የስላሴን አስተምህሮ ለመቃወም ኢየሱስን ከእግዚአብሄር አምላክነቱ በማንሳት የሚካኤልን ቦታ ሰጥታዋለች፣ በዚህም “ኢየሱስ ፈጣሪ ሳይሆን ፍጡር ነው፣ የብሉይ ኪዳን ስሙም ሚካኤል ነው” ትላለች፣

- [131] “ኢየሱስ … ከአምላክ የፍጥረት ስራዎች የመጀመሪያ በመሆኑ፣ ከፍጥረት ሁሉ በኩር ተብሎአል፣ ይህ ልጅ ልዩ የሚያደርገው ሌላም ነገር አለ፡፡ “አንድያ ልጅ ነው”፡፡ ይህም በቀጥታ የተፈጠረው ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ የሚያመለክት ነው … ስለዚህ ወልድ ፍጡር ነው፣ ስለዚህ መጀመሪያ አለው ማለት ነው፡፡”

[131]Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 41-42

- [132]“ሚካኤል የሚባለው ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊትም ሆነ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ የሚጠራበት ሌላ መጠሪያ ስሙ ነው፡፡”

ነገር ግን ኢየሱስ መልአኩ ሚካኤል አለመሆኑ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፡፡

## ➢ <u>ኢየሱስ ከተፈጣሪ መላዕክት በተለየ እንደ ፈጣሪ አምላክ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ መሆኑ</u>

ተፈጣሪ መጀመሪያ አለው፣ መላዕክትም ተፈጣሪ በመሆናቸው መጀመርያ አላቸው፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፣ ዘላለማዊ የሆነው አምላክ ብቻ ነው፣ ኢየሱስ ተፈጣሪ ባለመሆኑ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ መሆኑን መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፣

- ዕብ.1፡4-6 “ስለ መላዕክትም፣ መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ ይላል፣ ስለ ልጁ ግን አምላክ ሆይ ዙፋንህ <u>ለዘላለም ይኖራል</u> … ይላል፡፡ ”
- ዕብ.7፡3 “አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍፃሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ልጅ ተመስሎ <u>ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል</u>፡፡”
- ሚክ.5፡2 “አንቺም ቤተልሄም ኤፍራታ ሆይ፣ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ <u>ከዘላለም የሆነ</u>፣ በእስራኤል ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል፡፡”
- ራዕ.1፡7-8 “እነሆ ከደመናት ጋር ይመጣል፣ አይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል … ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፡፡ <u>አልፋና ዖሜጋ</u> እኔ ነኝ ይላል፡፡”

በዚህም ኢየሱስ ከመላዕክቱ በተለየ እንደ እግዚአብሄር መጀመርያና መጨረሻ የለውም፡፡

[132] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 218

## ➢ ኢየሱስ እንደ ሚካኤል ከመላዕክት ወገን አለመሆኑ

መላዕክት እልፍ አእላፍ ናቸው፣ ዳንኤል ስለ ሚካኤል ሲናገር “ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ”(ዳን.10፡13) በማለት ሚካኤል “አለቆች” ከሚባሉት በከፍተኛ ስልጣን ላይ ከሚገኙ መላዕክት ውስጥ አንዱ መሆኑን ያሳየናል፣ መፅሀፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር “አንድያ ልጁን”(ዮሐ.3፡16) ይላል እንጂ እንደነ ሚካኤል “ከአለቆች መካከል” ወይ “ከልጆቹ መካከል” አይለንም፣ በዚህም ሚካኤል የሚገኝበት የመላዕክቱ ጎራና “አንድያ” የተባለው የኢየሱስ ጎራ የተለያየ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መፅሀፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ከመላዕክት እንደሚለይ በግልፅ እያነፃፀረ ይናገራል፣

- ዕብ.1፡4-6 “… ከመላዕክትስ፣ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፣ ደግሞም እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጄ ይሆነኛል ያለው ለማን ነው? ደግሞም በኩርን ወደ አለም ሲያስገባ፣ የእግዚአብሄር መላእክት ሁሉ ለእርሱ ይስገዱ ይላል፡፡ <u>ስለ መላዕክትም</u>፣ መላዕክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ ይላል፣ <u>ስለ ልጁ</u> ግን አምላክ ሆይ ዙፋንህ ለዘላለም ይኖራል … ይላል … ነገር ግን ከመላዕክት፣ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ ከቶ ለማን ብሎአል … ”
- ዕብ.2፡7-16 “ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሳነስኸው … ነገር ግን በእግዚአብሄር ፀጋ ስለሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሳ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን … <u>የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የመላእክት አይደለም</u>፡፡”

በዚህም ኢየሱስና መላዕክት የተለያዩ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ የስላሴ አንዱ አካል የሆነው ኢየሱስ ከእግዚአብሄርነቱ አንስቶ ሚካኤል ቦታ ማስቀመጥ የማይቻል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 5.2.1.2. መንፈስ ቅዱስ

ቤተክርስቲያኗ የስላሴ አስተምህሮትን በመቃወም ከስላሴ ውስጥ "አብን አምላክ" በማለት፣ "ወልድን ሚካኤል" ብላዋለች፣ ከስላሴ አንዱ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ምን ማለት እንዳለባት ሌላ ፈተና ሆኖባታል፣ በዚህም [133] "መንፈስ ቅዱስ ማለት በስራ ላይ ያለ የእግዚአብሄር ሀይል ነው፣ ሰብአዊ ማንነት የለውም" ብለውታል፣ አዲስ ባወጡት "የአዲስ ዓለም" መፅሀፍ ቅዱሳቸውም ላይ በቀደመው መፅሀፍ ቅዱስ ላይ የነበረውን ዘፍ.1፡2 "የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሀ ላይ ሰፍፎ ነበረ፡፡" የሚለውን ቃል በመቀየር "የአምላክም ሀይል በውሃው ላይ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡" ብለውታል፡፡

ይህም መንፈስ ቅዱስን በሙሉ ማንነቱ ካለማየት የመጣ ችግር ነው፣ ሌላው ቀርቶ፣

> ኢሳ.11፡24 "የእግዚአብሄር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የሃይል መንፈስ፣ የእውቀትና እግዚአብሄርን የመፍራት መንፈስ..."

የሚለውን እንኳን ሙሉውን መውሰድ አልቻሉም ምክንያቱም ሙሉውን ከወሰዱ መንፈስ ቅዱስ ሙሉ አምላክ ይሆንባቸዋልና ስለዚህ ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር የምትሄደዋን "የሃይል" የምትለዋን ብቻ ለይተው አወጡ፣ ነገር ግን በ5.1.2.2.2 ክፍል እንደተመለከተው መንፈስ ቅዱስ ሙሉ ሰብአዊ ማንነት ያለው ሙሉ አምላክ ነው ይባሱኑ ከሙሉ ማንነቱ ዝቅ ማድረጉ የማይሰረይ ሀጢያት መሆኑን(ማቴ.12፡32) ተመልክተናል፣ ይህም የቤተክርስቲያንዋና የምዕመናኖችዋ አሳዛኝ መጨረሻ ነው፡፡

## የስላሴ አስተምህሮ - ማጠቃለያ

የይኾዋ ቤተክርስቲያን የስላሴን አስተምህሮ በመቃወም "አንድ አምላክ አብ ብቻ" በማለቷ የስላሴ አካላት የሆኑት ኢየሱስንና መንፈስ ቅዱስን የምታደርገው ግራ ገብቷት ስህተት ውስጥ ስትገባ ተመልክተናል፣ በርግጥ የስላሴ አስተምህሮ ከመፅሀፍ ቅዱሱ መገለጦች ውስጥ ከባዱ ክፍል መሆኑን በ5.1.2.3 ክፍል በስፋት ተመልክተናል፡፡

---

[133] https://www.jw.org/bible-teachings

ከሁሉ የሚገርመው ግን የ"ስላሴ" አስተምህሮ ተቃዋሚዎች በሙሉ የተሳሳቱት በተመሳሳይ መንገድ ነው፣ የሶስቱን አምላካዊ ማንነት ለአንዱ ብቻ በመስጠት ለሁለቱ ሌላ ምደባ ይሰራሉ፣ ጂሆቫ "ኢየሱስ ሚካኤል ነው" ስትል እስልምናው ደግሞ "መንፈስ ቅዱስ ጅብሪል(ገብርኤል) ነው" ይላል፣ የሐዋርያና የጂሆቫ አብያተ ክርስቲያናት በተመሳሳይ መልኩ መንፈስ ቅዱስን "ሀይል" በማለት ችግራቸውን ለመወጣት ሞክረዋል፣ በዚህም እነዚህ ሶስቱ የስላሴን አስተምህሮ የተቃወሙት የአብርሃም ሀይማኖቶች መካከል የመንፈስ ተመሳሳይነትን እንመለከታለን፡፡

## 5.2.2. "ሰው ሲሞት በህይወት የምትቀጥል ነፍስ ወይንም መንፈስ የለውም"

የይኾዋ ቤተክርስቲያን "ሰው ከሞተ ሞተ ነው `ነፍስ` እና `መንፈስ` የሚባል ነገር የለም" ትላለች፣ [134]"ስጋችን ሲሞት በህይወት የምትቀጥል ረቂቅ አካል በውስጣችን የለችም፡፡ የማይሞት ነፍስ ወይንም መንፈስ የለንም ... ሟቾች በመሆናችን ስጋችን ሲሞት በህይወት የምንቀጥልበት ምንም አይነት መንገድ የለም ... ሰይጣን `... ሰዎች ስጋችን ከሞተ በኋላ በመንፈሳዊ አለም እንኖራለን` የሚል እምነት እንዲያድርባቸው ለማድረግ የሃሰት ሀይማኖትን መሳሪያ አድርጎ ይጠቀማል፡፡" ሲሉ በትንሳኤ ቀን ስለሚነሳው አካልም ሲናገሩ [135] "በመቃብር ውስጥ ያሉት ከሞት ሲነሱ ፈጣሪ ህይወትን መልሶ ይፈጥርላቸዋል፡፡" ይላሉ፣

ነፍስና መንፈስ የሚባሉትን ቃላት ሲፈቱም [136]"ነፍስ የሚለው ቃል ህይወትን ያመለክታል ለምሳሌ ዘፀ.4፡19 "ነፍስህን የሚሹአት ሰዎች ሞተዋል፡፡" ማለቱ ህይወቱን ለማጥፋት የሚሹ ማለት ነው" ሲሉ፣ በሌላ ትርጉሙ ደግሞ "ነፍስ ማለት ሰውን የሚያመለክት ቃል ነው፣ ይህንንም በዘፀ.16፡16 "በድንኳዋኑ ባሉት ነፍሶች ቁጥር ... ውሰዱ፡፡" የሚለው ላይ

[134] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 58-64፣ 152
[135] ibid 71
[136] ibid 208-211

ተመልክቷል” ይላሉ፤ መንፈስ ማለት ደግሞ [137] “የራሱ ስብእናና ባህሪ የሌለው የህይወት ሀይል ነው” ይላሉ፡፡

ነገር ግን መፅሃፍ ቅዱሱን ስንመለከት የነፍስና መንፈስ ትርጉም በዚህ የማይወሰንና ከዚህ ሰፋ ያለ ትርጉም ያለው መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በመጀመሪያ እግዚአብሄር የሰው ልጆችን ሲፈጥር ሶስት የተለያዩ ስራዎች ሲሰራ እናየዋለን፣ በመጀመሪያ እራሱ መንፈስ ስለሆነ “በመልካችን” እንዳለው መንፈስ የሆነውን የሰውን ማንነት በስድስተኛው ቀን ፈጠረ(ዘፍ.1፡27)፣ ይህንንም መንፈስ ከአፈር ስጋ አበጀው(ዘፍ.2፡7)፣ ከዚያ ይህንን ስጋ ህያው ነፍስ በውስጡ አደረገ(ዘፍ.2፡7)፣ በዚህም “በምሳሌያችን” እንዳለውም የሰው ልጅ ስላሴ በሆነው በፈጣሪ ምሳሌ መፈጠሩን እንመለከታለን፡፡ ይህንን እውነታም 1ተሰ.5፡23 “የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለነቀፋ ፈፅመው ይጠበቁ፡፡” በሚለው እናረጋግጣለን፡፡

በዚህም የሰው ልጅ ከስጋው በተጨማሪ መንፈስና ነፍስ የሚባሉት ማንነቶች እንዳሉት እንረዳለን፣ ስለነዚህ ማንነቶች በዝርዝር ብንመለከት፡-

#### 5.2.2.1. የሰው ነፍስ

ቤተክርስቲያንዋ ከምትሰጠው ትርጉም በተጨማሪ የሰው ነፍስ የራስዋ ማንነት ያላት፣ ዘላለማዊ የሆነችና ስጋም ሲሞት ወደ ፈጣሪ የምትሄድ መሆኑን መፅሃፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፣

➢ **ነፍስ የማትሞት፣ራሷን የቻለች ህያው ማንነት ያላት መሆኑ**

- ዘፍ.2፡7 “እግዚአብሄር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ፡፡”
- ዘፍ.9፡15 “በእኔና በእናንተ መካከል፣ ህያው ነፍስ ባለውም ስጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ …”

[137] ibid 210-211

## ሰው ሲሞት ከስጋ የምትለይ መሆኑ

- ዘፍ.35፡18 “እርስዋም ስትሞት ነፍስዋ በምትወጣበት ጊዜ ስሙን ቤን ኦኒ ብላ ጠራችው፤ አባቱ ግን ቢኒያም አለው፡፡”
- ዮና.4፡3 “አሁንም፣ አቤቱ፣ ከህይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ አለው፡፡”
- ሐስ.7፡59 “እስጢፋኖስም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር፡፡”
- 1ነገ.17፡21-22 “በብላቴናውም ላይ ሶስት ጊዜ ተዘረጋበት፣ ወደ እግዚአብሄርም፡፡ አቤቱ አምላኬ ሆይ፣ የዚህን ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጮኸ፡፡ እግዚአብሄርም የኤልያስን ቃል ሰማ፤ የብላቴናውም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እርሱም ዳነ፡፡”

## ሰው ሲሞት ነፍስ ከሰው ወጥታ ወደ ፈጣሪ የምትሄድ መሆኑን

- መክ.3፡21 “የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳት ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው፣”
- መክ.12፡7 “አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፣ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሄር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ፡፡
- ሉቃ.23፡46 “ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፡፡ አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ፡፡ ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ፡፡”
- ራዕ.6፡9 “አምስተኛውም ማህተም በፈታ ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሄር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሰዊያ በታች አየሁ፡፡”

በአጠቃላይ ስንመለከት በስላሴነት በተፈጠረው የሰው ልጅ ውስጥ ነፍስ የራሷ ማንነት ያላት፣ ስትወጣም ስጋ ሙት እንደሚሆን፣ ከስጋ ወጥታም እግዚአብሄር ወዳዘጋጀላት ቦታ እንደምትሄድ እንመለከታለን፡፡

### 5.2.2.2. የሰው መንፈስ

ስጋና ነፍስ የሆኑትን የሰው ልጆችን ማንነት ከላይ ተመልክተናል፣ ብዙዎች የሰው ነፍስና መንፈስ አንድ ይመስላቸዋል ነገር ግን ሁለቱም የተለያየ ማንነት ያላቸው ሲሆን ሁለቱን ግን ለያይቶ መግለፁ ለሰው ልጅ የተገለጠ እውቀት አይደለም፣ ለዚህም ነው መፅሀፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሄር ቃል ችሎታ ሲናገር፣ ዕብ.4፡12 "የእግዚአብሄር ቃል ህያው ነውና የሚሰራም፣ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ... እስኪለይ ድረስ ይወጋል ..." የሚለው፡፡

በዚህም ምንም እንኳን የሰው ነፍስና መንፈስ የተባሉትን ማንነቶቹን ለያይቶ መግለፅ ባይቻልም ነገር ግን ሰው ከስጋ በተጨማሪ "ነፍስና መንፈስ" የሚባሉ ሁለት የተለያዩ ማንነቶች እንዳሉት መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ እንመለከታለን፡-

- ኢሳ.57፡16 "መንፈስም የፈጠርሁትም ነፍስ ከፊቴ እንዳይዝል ለዘላለም አልጣላም፣ ሁልጊዜ አልቆጣም፡፡"
- ሉቃ.1፡47 "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፣ መንፈሴም በአምላኬ በመድሃኒቴ ሀሴት ታደርጋለች፤"
- 1ተሰ.5፡23 "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም፣ ስጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈፅመው ይጠበቁ፡፡"

በዚህም ሰው የራሱ መንፈስ እንዳለው እንገነዘባለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ቤተክርስቲያኒቷ "ስጋችን ሲሞት በህይወት የምትቀጥል የማይሞት ነፍስ ወይንም መንፈስ የለንም" የሚለው አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና የሰው ልጅ እንደ እግዚአብሄር ስሉስነት ያለውና በዚህም የሰው ልጅ ስጋ፣ ነፍስና መንፈስ እንዳለው እንመለከታለን፡፡

### 5.2.3. የመጨረሻው ዘመን

ቤተክርስቲያኗ ስለ መጨረሻው ዘመን ያላት አስተምህሮ ከሁሉም የክርስቲያን እምነት ተቋማት ይለያል፣ እነዚህም ልዩ አስተምህሮቶች፡-

- “1914 ዓ.ም ኢየሱስ የነገሰበት አመት ነው”
- “በሺሁ አመት 144,000 የጂሆቫ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ይፈርዳሉ”
- “የሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ”
- “ምድር ገነት ናት”
- “ነፍስ ለዘለአለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ቦታ የለም”

ሲሆኑ ሁሉንም ከመፅሀፍ ቅዱሱ አንፃር በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 5.2.3.1. “1914 ዓ.ም ኢየሱስ የነገሰበት አመት ነው”

እንደ ቤተክርስቲኗ እምነት [138] *“መንግስተ ሰማይ በሰማይ ያለ መስተዳድር ነው፣ የዚህ መንግስት ንጉስ ኢየሱስ ሲሆን መንግስቱን መግዛት የጀመረው ከ1914 ጀምሮ ነው፣ ከዚህም ጊዜ አንስቶ ሰይጣን ወደ ምድር ተጥሎአል፡፡”*

ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ሰይጣን ወደ ምድር የሚጣልበትና ኢየሱስ የሚነግስበት ጊዜ ገና ነው፣ እነዚህ ሁለቱ ክስተቶች የሚከናወኑት በእስራኤል ላይ የሚነሱት ሁለት ነብያት መገደልና የአውሬው መንፈስ(666) ከሚገዛበት ጊዜ በኋላ ነው፡፡

- ራዕ.11፡2-15 “... እነርሱም አርባ ሁለት ወር የተቀደሰችውን ከተማ ይረግጧታል፣ ለሁለቱ ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ ... ምስክራቸውን ከፈፀሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፍማቸዋል ይገድላቸውማል ... ከእግዚአብሄር የወጣ የህይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸው ቆሙ ... በዚያ ሰአት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ...

[138] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 74, 78, 84

<u>የዓለም መንግስት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሆነች፣ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሳል</u>፡፡”

- ራዕ.12፡5-10 “አህዛብን ሁሉ በብረት ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ልጅዋም ወደ እግዚአብሄር ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ፣ ሴቲቱም ሺ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚብሄር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች፡፡ በሰማይም ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላዕክቱ ዘንዶውን ተዋጉ፣ ዘንዶውም ከመላዕክቱ ጋር ተዋጋ፣ አልቻላቸውም፣ ከዚያ ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም፡፡ <u>ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፣</u> ወደ ምድር ተጣለ መላዕክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ፡፡ ታላቅ ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፣ አሁን የአምላካችን ማዳንና ሀይል <u>መንግስትም የክርስቶስ ስልጣን ሆነ፣ ቀንና ለሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞችን ከሳሽ ተጥሎአልና</u>፡፡”

እነዚህ ሁለቱም ጥቅሶች የሚናገሩት በአንድ ላይ ስለሚፈፀሙ ሁለት ክስተቶች፣ ይህም ስለ ኢየሱስ ንግስናና ስለ ሰይጣን ከሰማይ መጣል፣ እነዚህ ሁለቱ ክስተቶችም ከመፈፀማቸው በፊት የ666 መንፈስ ይነሳል፣ ይህ ክስተት እስካሁን አልተፈፀመም፣ በዚህ ይህ ገና የሚፈፀም ታሪክን በ1914 ዓ.ም እንደተፈፀመ ማቅረቡ ስህተት ነው፡፡

ይህ የ1914 ዓ.ም ጉዳይ መነሻ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን ብዙ እልቂትን ያመጣው የመጀመሪያው ዓለማቀፍ ጦርነት(WWI) በ1914 ዓ.ም መደረጉን መሠረት አድርጎ የተሰነዘረ ትንቢት ነው፣ ይህም ትንቢት በመግቢያ ላይ እንዳየናቸው እንደተነዙቱ የውሸት ትንቢቶች መሰረዝ ያለበት የውሸት ትንቢት ነው፡፡

### 5.2.3.2. "ከኢየሱስ ጋር የሚፈርዱት 144,000 የጂሆቫ ተከታዮች ናቸው"

[139]"*መንግስተ ሰማይ በሰማይ ያለ መስተዳድር ነው፣ የዚህ መንግስት ንጉስ ኢየሱስ ሲሆን መንግስቱን መግዛት የጀመረው ከ1914 ጀምሮ ነው ... በዚህ መንግስተ ሰማያትንም ከኢየሱስ ጋር እንዲገዙ 144,000 ሰዎች ከሃዋርያት ዘመን ጀምሮ ታማኝ ክርስቲያኖችን ሲመርጥ ቆይታል፡፡ በኛ ዘመን ያሉት የ144,000 ጥቂት ቀሪዎች በሚሞቱበት ጊዜ በቅፅበት ተነስተው ሰማያዊ ህይወት ያገኛሉ፡፡*"

የትኛውም የእምነት ተቋም "እኔ ብቻ ነኝ ትክክል" እንደሚለው፣ በቤተክርስቲያንዋ አስተምህሮ እነዚህ 144,000 ታማኝ ክርስቲያኖች "የጂሆቫ እምነት ተከታዮች ናቸው" ትላለች፣ በዚህም እነዚህ 144,000 የጂሆቫ እምነት ተከታዮች ከድሮ ጀምሮ በስጋ ሲሞቱ እየተሰባሰቡ የነበረ ሲሆን አሁንም የሚሞቱት በቅፅበት ተነስተው ይህንን ሰማያዊ ህይወት እያገኙ እንደሆነ ታስተምራለች፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በቤተክርስቲያኗ "ሰው ከሞተ በኋላ በህይወት የምትቀጥል ነፍስም ሆነ መንፈስ የለውም" በማለት እያስተማረችና ዛሬ የጂሆቫዎች መቃብር ባልተከፈተበትና ስጋቸው ወደ ሰማይ ባልሄደበትና እንደ ማንኛውም ሟች ስጋቸው በመቃብር በሆነበት እውነታ ውስጥ መሆናቸውን ስንመለከት ከመነሻው ሀሳቡ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በመቀጠል እነዚህ 144,000 ሰዎችን የመለየት ስራ የሚሰራው የአርማጌዶን ጦርነት ሊካሄድ ሲል እንጂ ከሐዋርያት ዘመን አንስቶ አይደለም፣ የሚለዩትም ከስጋዊዋ እስራኤል ዘር የሆኑት ብቻ ናቸው፣

> *ራዕ.7፡1-8 "ከዚህም በኋላ በአራቱ ምድር ማዕዘን አራት መላዕክት ቆመው አየሁ ... ሌላ መልአክም ... ለአራቱ መላዕክት በታላቅ ድምፅ እየጮኸ፡- የአምላካችንን ባሪያዎች ግንባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርንም ቢሆን ወይንም ባህርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ አላቸው፡፡ የታተሙትን ቁጥር ሰማሁ፡፡ ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ የታተሙት መቶ*

[139]Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 74፣ 78፣ 84

አርባ አራት ሺ ነበሩ፣ ከይሁዳ ነገድ አስራ ሁለት ሺ፣ ከሮቤል ነገድ አስራ ሁለት ሺ፣ ከጋድ ነገድ አስራ ሁለት ሺ፣ …"

እነዚህ 144,000 ሰዎችም ከእስራኤል ቤት ብቻ መሆኑንና ከየነገዱም ምን ያህል እንደሆኑ በግልፅ ቁጥሩን ዘርዝሮ ይነግረናል፣ በዚህም የጂሆቫ ተከታዮች እዚህ 144,000 ውስጥ የሚገቡበት አሰራር የለም፡፡

እዚህ ጋር "ከአህዛብ ወገን የሆኑቱ ፃድቃን ምን ይሆናሉ?" ለሚለው፣ አህዛብ ከጦርነቱ በፊት አስቀድሞ የሚነጠቁ (1ተሰ.4፡17) በመሆኑ፡-

ራዕ.7፡9 "ከዚህም በኋላ አየሁ፣ እነሆም አንድ ስንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከህዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፣ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባ ዝንጣፊ በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ …"

ይላል፣ በዚህም የ144,000 ሰዎችን ጉዳይ ከአህዛም ሆነ ከጂሆቫ ቤተክርስቲያን ጋር ማገናኘቱ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

#### 5.2.3.3. "ምድር ገነት ናት"

እንደ ቤተክርስቲያኗ፣

[140]"የምድር ነገስታት በክፉ መናፍስት አነሳሽነት አርማጌዶን በሚባል ስፍራ ይሰበሰባሉ፣ በዚህም መሠረት በሰብአዊው መንግስታትና በአምላክ መንግስት መካከል በዚህ ስፍራ የመጨረሻ ውጊያ ይካሄዳል፣ በዚህ ጦርነትም ክፉ ሰዎች፣ ሰይጣንና አጋንንቱ ይወገዳሉ፣ ሰብአዊ መስተዳድሮች ይጠፋሉ፣ ዘላለማዊው የአምላክ መስተዳድር ይጀምራል፣ ከዚያ በኋላ ምድር ገነት ትሆናለች፡፡"

ለዚህም አስተምህሮ ማጠናከሪያ፣

- መክ.1፡4 "ምድር ግን ለዘላለም ናት"
- መዝ.37፡29 "ፃድቃን ምድርን ይወርሳሉ በእስዋም ላይ ለዘላለም ይኖራሉ"

---

[140] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 81-85

- መዝ.104፡5 “ለዘላለም እንዳትናወጥ ምድርን በመሰረቷ ላይ መሠረታት፡፡”

የሚሉቱን ይጠቅሳሉ፡፡

እዚህ ጋር የምንመለከተው ስህተት መነሻ “ዘላለም” የሚለው ቃል ሁለት መፅሀፍ ቅዱሳዊ ትርጉሞችን ባለማወቅ የተከሰተ ሲሆን ከዚህም ስህተት የተነሳው ድምዳሜ ደግሞ የተለያዩ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ኩነቶችን በአንድ ላይ ያደራረበ የተሳሳተ ድምዳሜ ነው፣ ሁለቱንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ➢ “ዘላለም” የሚለው ቃል ሁለት መፅሀፍ ቅዱሳዊ ፍቺዎች አለማወቅ

በ4.1 ክፍል እንደተመለከተው ብሉይ ኪዳን “ስግደት” የሚለው ቃል በሁለት መንገድ እንደተጠቀመው እንደዚሁ ብሉይ ኪዳን “ዘላለም” የሚለውን ቃል በሁለት መንገድ ይፈታዋል፣ የመጀመሪያው አብዛኛው ሰው የሚያውቀው “በጊዜ አለመገደብ” የሆነው ትርጉሙ ሲሆን ሌላኛው ትርጉሙ ደግሞ “ዕድሜ ልኩን” ማለት ነው፣ ይህንን ሁለተኛውን ትርጉም ለመረዳት መፅሀፍ ቅዱሱ እንዴት እንደሚጠቀመው እስቲ እንመልከት፣

- ዘፀ.21፡6 “… ለዘላለም ባርያው ይሁን፡፡”
- 1ሳሙ.1፡22 “ሀና ግን አልወጣችም ባልዋንም፡፡ ህፃኑ ጡት እስኪተው ድረስ እቀመጣለሁ፣ ከዚያ በኋላ በእግዚአብሄር ፊት ይታይ ዘንድ፣ በዚያ ለዘላለም ይሆን ዘንድ አመጣዋለሁ አለች፡፡”
- 1ሳሙ.27፡12 “… ስለዚህ ለዘላለም ባርያዬ ይሆነኛል ብሎ ዳዊትን አመነው፡፡”
- 2ዜና.10፡7 “(ሽማግሌዎቹም ለንጉስ ሮብአም) ለዚህ ህዝብ ቸርነት ብታደርግላቸው፣ ደስም ብታሰኛቸው፣ በገርነትም ብትናገራቸው፣ ለዘላለም ባሪያዎች ይሆኑልሀል፡፡”
- መዝ.12፡7 “አቤቱ አንተ ጠብቀን፣ ከዚህችም ትውልድ ለዘላለም ታደገን፡፡”
- ዮና.2፡7 “(ዮናስም በአሳ ሆድ ውስጥ ሆኖ ሲፀልይ) ወደ ተራሮች መሰረት ወረድሁ፣ በምድርና በመወርወሪያዎች ለዘላለም ተዘጋሁ …”

ከላይ የተመለከትነው ቤተክርስቲያኗ የምትጠቅሰው "የምድር ዘላለማዊነት" ጉዳይ የተነገረውም በዚህ አውድ ነው፣ ይህም ምድር በተሰጣት ዕድሜ ውስጥ ፀንታ የምትኖር መሆንዋን ለማሳየት ነው፣ ይህ አሻሚ የሆነው የብሉይ ኪዳን አገላለፅ በአዲስ ኪዳኑ ተፈቶ እናገኘዋለን፣ አዲሱ ኪዳን ይህቺ ምድር በሌላ ምድር እንደምትተካና ይህም መቼ እንደሚሆን ጭምር ዘርዝሮ ይነግረናል፡-

- <u>አሁን ያሉት ሰማይና ምድር የሚያልፉ መሆኑ፣</u>

    - ዕብ.1፡10-12 "... አንተ ከጥንት ምድርን መሰረትህ ሰማዮችም የእጆችህ ስራ ናቸው፣ እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ፀንተህ ትኖራለህ፣ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፣ እንደ መጎናፀፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፣ አንተ ግን አንተ ነህ አመቶችህ ከቶ አያልቁም፡፡"

    - ማቴ.24፡35 "ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም፡፡"

    - ራዕ.20፡11 "ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፣ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም፡፡"

- <u>የሚያልፉትም መቼ እንደሆነ፣</u>

    - 2ጴጥ.3፡7 "አሁን ያሉ ሰማያና ምድር ግን እግዚአብሄርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል፡፡"

    - 2ጴጥ.3፡10-12 "የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፣ በዚያን ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፣ የሰማይ ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፣ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል ... ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል፡፡"

- <u>የምትተካዋ አዲሲቱዋ ሰማይና ምድር</u>
  - ራዕ.21፡1 "አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና ..."
  - 2ጴጥ3፡13 "ነገር ግን ፅድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን፡፡"

በዚህም ቅዱሳን የሚኖሩባት አዲስ፣ ንፁህ(ያልተበከለች)፣ ቅድስት(ያልተረገመችና በሰይጣን ያልተገዛችና የማትገዛ)፣ የተባረከች ... በሁለንተናዋ ፍፁም የሆነችና ፈጣሪ ለቅዱሳን በሽልማት ያዘጋጃት ምድር ትመጣለች፣ በዚህም ይህቺ "ምድር ገነት ሆና ለዘለአለም ትኖራለች" የሚለው የቤተክርስቲያንዋ አስተምህሮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- <u>**ኩነቶችን በአንድ ላይ ማደራረብ**</u>

"ምድር ገነት ትደረጋለች" የሚለው ስህተት መሆኑን የተመለከትን ቢሆንም፣ ቤተክርስቲያንዋ "ከአርማጌዶን ጦርነት በኋላ ምድር ገነት ትደረጋለች" የሚለው አባባል ደግሞ ሰፊ ኩነቶችን በአንድ ላይ የጨፈለቀ አስተምህሮ ነው፣ በአርማጌዶን ጦርነት(ራዕ.16፡16 - ራዕ.20፡3) እና ገነት መካከል ብዙ ክስተቶች ይስተናገዳሉ፣ አንኳር አንኳሮቹን ብንመለከት፣ የሺ አመት የዲያብሎስ እስርና የቅዱሳን ንግስና(ራዕ.20፡4-6)፣ ሰይጣን ከእስራት ተፈትቶ የሚቆይበትና ጊዜ(ራዕ.20፡7-9)፣ ሰይጣን ላይ የሚፈረድበት ጊዜ (ራዕ.20፡10) እና የመጨረሻው የፍርድ ቀን(ራዕ.20፡11-15) ናቸው፡፡

በዚህም ይህ የቤተክርስቲያኒቷ መለያ የሆነው "ገነት በምድር" አስተምህሮ ብዙ ታሪኮችን የዘነጋ የስህተት አስተምህሮ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 5.2.3.4. "የሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ"

እንደ ቤተክርስቲያኗ [141]"የፍርድ ቀን የሚጀምረው በምድር ላይ ያለው የሰይጣን ስርአት በአርማጌዶን ጦርነት ከጠፋ በኋላ ነው፡፡ ከአርማጌዶን በኋላ ሰይጣንና አጋንንቱ በጥልቁ ውስጥ ለሺ አመት ይታሰራሉ፡፡ በዚያን ጊዜ 144,000 ተባባሪ የሰማይ ወራሾች ፈራጆች ይሆናሉ፣ እንዲሁም ነገስታት ሆነው ከክርስቶስ ጋር ሺ አመት ይገዛሉ፡፡ የፍርድ ቀን ለ24 ሰአት ብቻ የሚቆይ በጥድፊያ የሚከናወን ነገር አይደለም፡፡ ለሺ አመት የሚዘልቅ ነው፡፡ በሺሁ አመት ጊዜ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በህያዋንና በሙታን ላይ ይፈርዳል፡፡ ፍርዱ የሚሰጠው ሰዎች ቀደም ሲል በፈፀሟቸው ድርጊቶች ላይ ተመርኩዞ አይደለም፣ ከአርማጌዶን የሚተርፉትም ሆነ ከሞት የሚነሱት ሰዎች ለዘላለም መኖር እንዲችሉ ይሖዋ በሺሁ አመት ወቅት ሊያወጣቸው የሚችላቸውን መስፈርቶች ጨምሮ ሁሉንም የአምላክ ትዕዛዛት ማክበር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ፍርድ የሚሰጣቸው በፍርድ ቀን የሚፈፅሙትን ድርጊት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በፍርድ ቀን በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ አምላክ ፈቃድ መማርና ከፍቃዱ ጋር ተስማምተው መኖር የሚችሉበት አጋጣሚ ያገኛሉ፡፡ በመሆኑም መጠነ ሰፊ የማስተማር ስራ ይካሄዳል ማለት ነው፡፡"

ይህንን መቀበሉ አዳጋች ነው፣ አስተምህሮው እርስ በራሱ እንዲሁም ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጋር ይጋጫል፡-

1. "የፍርድ ቀን" ብሎ እሱም "ሺ አመት ነው" ይላል

መፅሀፍ ቅዱሱ የፍርድ ቀንን የሚጠራው፣ የፍርድ ቀን(ማቴ.11፡24)፣ የመጨረሻው ቀን(ዮሐ.6፡54)፣ የኋለኛው ቀን(ያዕ.5፡3)፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቀን(1ቆሮ.1፡8፣ ፊልጵ.1፡6)፣ የጌታ ቀን(2ጴጥ.3፡10)፣ የእግዚአብሄር ቀን(2ጴጥ.3፡11-12) የቤዛ ቀን(ኤፌ.4፡30)፣ ታላቁ ቀን(ይሁ.1፡6) ... በማለት ሁሉንም "ቀን" በማለት ነው፣ ይባሱኑ "ቀን" ተባለ እንጂ ይህ በቅፅበት የሚደረግ ነገር ነው ምክንያቱም እግዚአብሄር ሁሉን አዋቂ በመሆኑ(1ሳሙ.2፡3)፣ ምስክር የማይፈልግና ቀድሞውኑ

[141] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 214

የተዘጋጀ መዝገብ በመኖሩ(ራዕ.20፡12)፣ አማኞች ቀድሞውኑ ተለይተው የታተሙ በመሆኑ(ኤፌ.4፡30) … ይባሱኑ የትኛውም ሰው ዛሬ ላይ ሆኖ በሱ ላይ የሚፈረደውን ፍርድ የሚያውቅበት ሁኔታ መነገሩ(ዮሐ.3፡18) ስንመለከት፣ እግዚአብሄር እንደ ሰነፍ ዳኛ ይባሱኑም ከሰነፍ ዳኛ ባነሰ “የፍርዱ ሂደት አንድ ሺ አመታት ይፈጅበታል” ማለቱ ስህተት ነው፡፡

2. “የፍርድ ቀን” ብሎ ተመልሶ ደግሞ ሰዎች <u>ፍርድ</u> የሚሰጣቸው “<u>በፍርድ ቀን</u> በሚፈፅሙት ድርጊት ነው” በማለት ሀጢያተኞች ሌላ እድል እንዳላቸው ይናገራሉ ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱሱ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ምንም ሌላ እድል እንደማይሰጣቸው ይናገራል፣

    ዕብ.9፡27 “ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት **<u>ከእርሱ በኋላ</u>** ፍርድ ተመደበባቸው፡፡”

    በዚህም ይህ “<u>አሁን ሀጢያት መስራት ችግር የለውም፣ ገነት ለመግባት ሌላ ሁለተኛ የመማርና የማመን እድል አለ</u>” የሚለው አስተምህሮ ጀርባ ሰዎችን ለሲኦል የሚመለምለው መንፈስ መኖሩን ያሳያል፡፡

3. በሺሁ አመትም(በፊተኛው ትንሳኤ) ሁሉም ሰው ከሞት እንደሚቀሰቀስ ይናገራል ነገር ግን ይህ ስህተት መሆኑና “ፊተኛው ትንሳኤ” የሚባለው ለሺ አመት ኑሮ ከሞት የሚቀሰቀሱት ቅዱሳን፣ ያውም ሰማዕታት ብቻ ናቸው፣

    ራዕ.20፡4-6 “ዙፋኖችንም አየሁ፣ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሄር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፣ ለውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺ አመት ኖሩና ነገሱ፡፡ <u>የቀሩት ሙታን ግን ይህ ሺ አመት እስኪፈፀም ድረስ በህይወት አልኖሩም</u>፡፡ ይህ የፊተኛው ትንሳኤ ነው፡፡ በፊተኛው ትንሳኤ እድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በነርሱ ላይ ስልጣን የለውም …”

በዚህም ቤተክርስቲያንዋ ምን ያህል የመፅሀፍ ቅዱሱን መንገድ እንደሳተች እንመለከታለን፡፡

### 5.2.3.5. “ነፍስ ለዘለአለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ቦታ የለም”

እንደ ቤተክርስቲያኗ አባባል [142] “አንዳንዶቹ ሀይማኖቶች አንድ ሰው አኗኗሩ መጥፎ ከሆነ ከሞተ በኋላ እሳታማ ወደ ሆነ መሰቃያ ስፍራ ገብቶ ለዘላለም ይሰቃያል ብለው ያስተምራሉ፡፡ ይህ ትምህርት የአምላክን ስም የሚያጠፋ ነው፡፡ ይሖዋ (እግዚአብሄር) የፍቅር አምላክ በመሆኑ ሰዎችን ፈፅሞ በዚህ መንገድ አያሰቃይም፡፡” ይላሉ፣

ነገር ግን ይህ ስህተት መሆኑና ስህተቱም የመጣው፣

- የእግዚአብሄርን ሙሉ ማንነት ባለማወቅ፣
- የሁሉንም ሰው ዘላለማዊነት ባለማወቅ፣
- የሲኦልን ሙሉ ትርጉም ባለማወቅ፣

መሆኑን ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፣

- **<u>እግዚአብሄርን በሙሉ ማንነቱ ባለማወቅ</u>**

ቤተክርስቲያንዋ “እግዚአብሄር ፍቅር ስለሆነ ጨክኖ ሰውን ለዘላለም በእሳት ውስጥ አይቀጣም ትላለች” በርግጥ እግዚአብሄር ፍቅር በመሆኑ ከመጀመሪያው ሲኦልን ለሰው ልጆች አላዘጋጀም፣

ማቴ.25፡41 “በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፡፡ እናንተ ርጉማን፣ <u>ለሰይጣንና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ</u> ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ (ይላቸዋል)፡፡”

ነገር ግን ሰይጣን የሰው ልጆችን አሳስቶ በራሱ የርኩሰት መንገድ ስላስገባ፣ የረከሰ ደግሞ ገነት ስለማይገባ፣ እግዚአብሄር ባዘጋጀው የፅድቅ መንገድ መሄድ ያልቻለ የሰው ልጅም ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል መግባቱ የግድ ነው፡፡

[142] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 64፣ 72 እና 212-213

እግዚአብሄር "ፍቅር" ብቻ ሳይሆን ለህግ አልገዛ የሚሉትን የሚቀጣ(ዘሌ.26፡28)፣ የሚያጠፋ እሳት(ዕብ.12፡29) ለተጎዱ የሚበቀል(ዕብ.10፡30) … በአጠቃላይ ከፍቅሩም በተጨማሪ በቁጣም የሚገለጥ አምላክ ነው፡፡ በዚህም እግዚአብሄርን "ፍቅር ነው" በሚለው ብቻ አይወሰንም፣ እግዚአብሄር በብዙ መንገድ ይገለጣል፣ ለያንዳንዱ ሰው የሚገለጠውም እንደ ሰውየው ስራ ነው፣ በትዕዛዙ የሚሄዱት ፍቅሩን ያጣጥማሉ፣ ኃጢያተኞች ደግሞ ቁጣውን ያጣጥማሉ፡፡

➢ <u>የሁሉንም ሰው ዘላለማዊነት ባለማወቅ</u>

ቤተክርስቲያኗ ሰውን በሁለት በመከፈል "ፃድቅ ለዘላለም ይኖራል ሀጢያተኛ እንዲሁ ሞቶ ይቀራል እንጂ ለዘላለም አይቀጣም" ትላለች፣ ለዚህም የምታቀርበው መከራከሪያ፣

ሮሜ.6፡23 "የሀጢያት ደሞዝ <u>ሞት</u> ነውና የእግዚአብሄር የፀጋው ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን <u>የዘላለም ህይወት</u> ነው፡፡"

የዚህ ስህተት መነሻ የነፍስን ሞት በስጋ ሞት አይን የመመልከት ችግር ነው፣ ነገር ግን የነፍስ ሞትና የስጋ ሞት የተለያዩ ናቸው፣ የስጋ ሞት ማለት የነፍስና የስጋ መለያየትና የስጋ ህልውና መቆም ሲሆን የነፍስ ሞት ማለት ደግሞ "ሁለተኛው ሞት የሚባለውና ነፍስ ከፍርድ አለማምለጥና በሲኦል ውስጥ መጣል" ማለት ነው(ራዕ.2፡11, ራዕ.20፡6, ራዕ.20፡14, ራዕ.21፡8 …)፡፡

በዚህም የስጋና የነፍስ ሞት የተለያዩ ሲሆኑ የስጋ ሞት "የስጋ ህልውናውን ማቆም" ሲሆን የነፍስ ሞት ማለት ደግሞ የ"ነፍስን ህልውና ማጣት" ሳይሆን "ነፍስ ወደ ሲኦል መጣል" ማለት ነው፣ በዚህም "የሀጢያት ደሞዝ ሞት ነው" የሚለው የነፍስ ወደ ሲኦል መውረድን ያመለክታል ምክንያቱም ነፍስ የማትሞት ህያው ተደርጋ ስለተፈጠረች(ዘፍ.2፡7, ዘፍ.9፡15…)

ነፍስ እንደ ስጋ የማትሞት በመሆንዋ ከስጋ በምትለይበት ጊዜ መኖሪያ ቦታ ያስፈልጋታል፣ በዚህም እስከ ፍርድ ቀን በጊዜያዊው መኖሪያ በገነትና በሲኦል ትቀመጣለች(ሉቃ.16፡23-24) ለዚህ ነው ኢየሱስ ሉቃ.23፡43 "አንተ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት …" ያለው እንዲሁም በሌላ ስፍራ መፅሀፉ በፍርድ ቀን "ሲኦል ነፍሳትን ሰጠች"(ራዕ.20፡13) የሚለው፡፡

## ➢ የሲኦልን ምንነት ባለማወቅ

ቤተክርስቲያኗ "ሲኦል" የሚለውንም ቃል ስትፈታ [143] "ሲኦል ቃል በቃል በአንድ የተወሰነ ስፍራ የሚገኝ ቦታን የሚያመለክት ቃል ሳይሆን ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡ አብዛኞቹ ሰዎች ሲሞቱ ወደዚህ ምሳሌያዊ ቦታ እንደገቡ ይቆጠራል፡፡"

ነገር ግን ቅዱሳን በገነት(መንግስተ ሰማያት) ለዘላለም እንደሚኖሩት ሁሉ ሀጢያተኞችም ሀጢያታቸውን ተሸክመው ለዘላለም ሲኦል(ገሀነብ) ይገባሉ፣ ይህንንም እውነታ በብዙ ቦታዎች ላይ እንመለከታለን፡-

- ሲኦል የሚባል የሀጢያተኞች ነፍስ የምትቀጣበት ቦታ መኖሩን፣
    - ማቴ.25፡41 "በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፡፡ እናንተ ርጉማን፣ ለሰይጣንና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ (ይላቸዋል)፡፡"
    - ማቴ.25፡46 "እነዚያ ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ፃድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ፡፡"
    - ሉቃ.16፡23-24 "በሲኦልም ስቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሀምን በሩቅ አየ … እርሱም እየጮኸ፡፡ አብርሀም አባት ሆይ ማረኝ፣ በዚህ ነበልባል እሰቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልአዛርን ስደድልኝ አለ …"
    - ማቴ.13፡40-42 "… በአለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል … አመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፣ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፣ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፏጨት ይሆናል፡፡"
    - መዝ.9፡17 "ሀጢያተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ፣ እግዚአብሄርን የሚረሱ አህዛብ ሁሉ፡፡"
    - ሕዝ.32፡21 "የኃያላን አለቆች በሲኦል ውስጥ ሆነው ከረዳቶቹ ጋር ሆነው ይነግሩታል፤ በሰይፍም የተገደሉት ያልተገረዙት ወርደው ተኝተዋል፡፡"

[143] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 212

- ራዕ.20፡15 "በህይወትም መፅሃፍ ተፅፎ ያልተገኘ ማንኛውም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣለ፡፡"
- መዝ.49፡15 "ነገር ግን እግዚአብሄር ይበቃኛልና ነፍሴን ከሲኦል እጅ ይቤዣታልና፡፡"

- ቅጣቱም ለዘላለም መሆኑ

- ማቴ.25፡46 "እነዚያ ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ፃድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ፡፡"
- ዳን.12፡1-2 "በዚያም ዘመን ... በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ህይወት፣ እኩሌቶቹ ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና፡፡"
- ሉቃ.3፡17 "መንሹ በእጁ ነው፣ አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል፣ ስንዴውንም በጎተራ ይከታል፣ ገለባውን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል አላቸው፡፡"
- ራዕ.20፡10፡- "... ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባህር ተጣለ፣ ለዘላለም እስከ ዘላለም ቀንና ለሊት ይሰቃያሉ፡፡"

በዚህም ሲኦል የሀጢያተኛ ሰዎች ነፍስ ለዘለአለም የምትቀጣበት ቦታ መሆኑን እንመለከታለን ስለዚህ ትክክኛውን አስተምህሮ የሚከተለውን መንገድ በጊዜ መፈለጉ መልካም ነው፡፡

### 5.2.4. አዲሱ የጂሆቫ መፅሃፍ ቅዱስ- "የአዲስ አለም ትርጉም"

ይህ መፅሃፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያንዋ በራስዋ ደንብና ስርአት ላይ ተመርኩዛ ዋናውን መፅሃፍ ቅዱስ "በማስተካከል" ያዘጋጀችው መፅሀፍ ሲሆን፣ በእንግሊዘኛ በ2013 "The new world translation" ተብሎ የታተመ ሲሆን በአማርኛ ደግሞ በ2014 ዓ.ም "አዲሱ አለም ትርጉም" ተብሎ ታትሟል፡፡

ዋናው መፅሃፍ ቅዱስ፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ መጨመርም መቀነስንም እንደማይቻል ቢናገርም (ራዕ.22፡18-19, ዘዳ.4፡2, ዘዳ.12፡32 ...) ቤተክርስቲያኒቷ ግን ይህን ተላልፋ በመፅሃፍ ቅዱሱ ላይ ብዙ ለውጥ አድርጋለች፣ በዚህም ሙሉ በሙሉ የተሰረዙ፣ በከፊል የተሰረዙና የተቀየሩ የመፅሀፍ ቅዱሱን ክፍሎች እንመለከታለን፡፡

#### 5.2.4.1. ሙሉ በሙሉ የተሰረዙ

በ"መፅሀፍ ቅዱሱ" ላይ በግልፅ እንደሚታየው ማቴ.17፡21, ማቴ.18፡11, ማቴ.23፡14, ማር.7፡16, ማር.9፡44, ማር.9፡46, ማር.11፡26, ማር.15፡28, ማር.16፡9-20, ሉቃ.17፡36, ሉቃ.23፡17, ዮሐ.8፡1-11, ዮሐ.5፡4, ዮሐ.7፡53, ሐስ.8፡37, ሐስ.15፡34, ሐስ.24፡7, ሐስ.28፡29, ሮሜ.16፡24 ... ሙሉ በሙሉ ተሰርዘው ወጥተዋል፡፡

#### 5.2.4.2. በከፊል የተሰረዙ

እነዚህ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰነው በመፃፍ ከፊሉን የመሰረዝ ስራ የተሰራባቸው ናቸው፣ ለናሙና የተወሰዱ ክፍሎች ብንመለከት፣

| ተ.ቁ | የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል | ተሰርዞ የወጣው ቃል |
|---|---|---|
| 1 | ሉቃ.1፡28 | "... አንቺ ከሴቶች መሃል የተባረክሽ ነሽ፡፡" |
| 2 | ሐስ.24፡6 | ... እንደ ህጋችንም እንፈርድበት ዘንድ ወደድን" |
| 3 | ሐስ.24፡8 | '... ከሳሾቹንም ወደ አንተ ይመጡ ዘንድ አዘዘ፤" |
| 4 | ቆላ.1፡2 | "... ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ..." |

### 5.2.4.3. የተቀየሩ

የተቀየሩትን ቃላት በተመለከተ ቤተክርስቲያኒትዋ "የተደረገው ለውጥ ጌታ፣ እግዚአብሄር ... የሚለውን በትክክለኛው የእግዚአብሄር ስም "ይኾዋ" ነው የቀየርነው" ብትልም በመፅሃፍ ቅዱሱ በዝርዝር እንደምንመለከተው የተደረገው ኤዲቲንግ ከዚህ ውጪ ብዙ ነገሮች ላይ ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

| ተ.ቁ | ጥቅስ | በኦሪጅናሉ መፅሀፍ ቅዱስ | በጂሆቫ መፅሀፍ ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዘፍ.1፡2 | ... የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሀ ላይ ሰፍፎ ነበረ፡፡ | .. የአምላክም ሀይል በውሃው ላይ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡ |
| 2 | ዮሐ.1፡18 | መቼም ቢሆን እግዚአብሄርን ያየው አንድ ስንኩዋ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው፡፡ | ... አምላክን ያየው አንድም ሰው የለም፣ ስለእሱ የገለፀልን ከአብ ጎን ያለውና አምላክ የሆነው አንድያ ልጁ ነው |
| 3 | ፊሊጽ.2፡9 | ከስም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው | ከሌላ ከማንኛውም ስም በላይ የሆነ ስም በደግነት ሰጠው |
| 4 | ሐዋ.4፡31 | ከፀለዩም በኋላ ... | ምልጃ ካቀረቡም በኋላ... |

በዚህም አሁን በቤተክርስቲያኗ የተዘጋጀው "መፅሀፍ ቅዱስ" የእግዚአብሄር ቃል አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

## ማጠቃለያ(ጂሆቫ)

የጂሆቫ እምነት ተከታዮች ከየትኛውም የክርስትና ተቋማት በላይ ስለ ሀይማታቸው ምስክርነት ሲተጉ ይታያሉ ነገር ግን "ምን ያህሉ ማህበረሰብ ወደዚህ ሃይማኖት ተቀላቀለ" ተብሎ ሲታይ ኢምንት ነው ምክንያቱም ዛሬ ወንጌል በሰማ ማህበረሰብ ውስጥ እነዚህን ከላይ ያየናቸውን ስህተቶች ይዞ ተቀባይነት ማግኘት አይቻልም፡፡ ተከታዮቻቸውም ስለ ሀይማኖታቸው ከሚሰጣቸው የ"ንቁ"፣ "መጠበቂያ ግንብ" እና መፅሃፍቶቻቸው ውጪ ስለሌላው እንዲያነቡ ስለማይፈቀድላቸው እንደ ጋሪ ፈረስ በመፅሄቶቹ ከሚሰጠው አቅጣጫ ውጪ እውነታውን ማወቅ አይችሉም፡፡

ነገር ግን ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው የሀይማኖቱ አስተምህሮ በብዙ ስህተቶችን የተሞላ ነው፣ ከሁሉ ስህተቶች ግን የከፋው በመንፈስ ቅዱስ ክብር ላይ የተሰነዘረው አስተያየት ነው፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር አይሰረየለትም፣ በዚህም የዚህ ሀይማኖት ተከታዮች እድል እንደ የሐዋርት ቤተክርስቲያን ነው፡፡

## 5.3. አድቬንቲስት(Adventism)

[144]"የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አስተምህሮ የተጀመረው በአሜሪካን ሀገር በ1830 ዓ.ም ዊሊያም ሚለር በሚባል የባፕቲስት ቤተክርስቲያን ሰባኪ ሲሆን አስተምህሮው በግልፅ መነገር የተጀመረው ግን ከ1833 ዓም ጀምሮ ነው፣ የአስተምህሮቱ መነሻም ሚለር በዳን.8፡14-16 ላይ ተመስርቶ "የኢየሱስ ዳግም መምጫ ጊዜ በ1843 እና በ1844ዓ.ም መካከል ነው" በማለት በሰራው ስሌት ነው፣ የቤተክርስቲያንዋ ስያሜ "አድቬንቲስት" የሚለው የእንግሊዘኛ ቃልም ከዚህ ጋር ተያይዞ የተሰጠ ስያሜ ሲሆን ትርጉሙም "የክርስቶስ መምጫ ቀርቧል" የሚል ነው፡፡

የሚለር ትንቢትም ከ1830 እስከ 1844 ዓ.ም ለ14 አመታት ሲጠበቅ ቆይቶ በተሰላው ጊዜ ኢየሱስ ዳግም አልመጣም፣ ትንቢቱም ባለመስራቱ በተከታዮቹ ላይ ትልቅ የሞራል ውድቀት ደረሰ፣ ከዚህ አሳዛኝ ክስተት በኋላ ሚለር "ጊዜውን እንደገና አሰላሁት" በማለት ወሩን ቀይሮ ከነቀኑ ጭምር "ኦክቶበር 22, 1844 ዓ.ም" እንደሆነ እንደገና ተነበየ፣ አሁንም ውጤቱ አሳዛኝ ሆነ፣ ቀኑም በቤተክርስቲያንዋ ታሪክ "ትልቁ አሳዛኝ ቀን" ተባለ፡፡

ከዚህም በኋላ የሚለር አስተምህሮ ተከታዮች(ሚለራውያን) መካከል ከፍተኛ ክፍፍል ተፈጠረ፣ የተወሰኑት ወደ ነበሩበት የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ሲመለሱ ሌሎች ደግሞ እንደየልዩነቶቻቸው በየፊናቸው የተለያዩ የአድቬንቲስት ስም የያዙ አብያተ ክርስቲያናትን መሠረቱ፣ በዚህም የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት፣ አድቬንት ክርስቲያን ቸርች፣ ጥንታዊቷ አድቬንት ክርስቲያን ቸርች፣ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን(ሰባተኛ ቀን) … የሚባሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተፈጠሩ፣ ከክፍፍሉ በፊት የነበረችው የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መስራቹ ሚለር ግን በነዚህ ክፍፍሎች ውስጥ ያልገባ ሲሆን እስከሞተበት ጊዜ ድረስም አብያተ ክርስቲያናቱ ወደ አንድነት እንዲመጡ ሲሰራ ነበረ፡፡

በክፍፍሉ ከተፈጠሩት አብያተ ክርስቲያናት ዋነኛዋና ዛሬ በአለም ዙሪያ ተስፋፍታ የምትገኘው "የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት" ቤተክርስቲያን ስትሆን ቤተክርስቲያኗም በ1863 ዓ.ም በነ ኤለን ጂ ኋይት መሪነት በይፋ

[144] https://en.m.Wikipedia>wiki>Adventism

ተመሠረተች፡፡ ኤለን የቤተክርስቲያኗ የጀርባ አጥንት ስትሆን ለቤተክርስቲያንዋም ከ40 በላይ መፅሃፍትንና በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ፅሁፎችን አበርክታለች፣ በዚህም ቤተክርስቲያንዋ የኤለንን መፅሀፍት "የነቢይነት ስልጣን አላቸው" በማለት መፅሀፎቹን ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጎን ለጎን ትጠቀምበታለች፣ ቤተክርስቲያኗ በአሁኑ ጊዜ 22 ሚሊየን በላይ አባላት አሏት፡፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን ታሪኮች ስንመለከት የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ምሥረታ ከየትኛውም ሃይማኖት ምሥረታ ታሪክ የተለየ መሆኑን ነው፣ ሌሎቹ ሀይማኖቶች የተመሠረቱት በነበሩበት ቤተ እምነት ውስጥ የተመለከቱትን "የስህተት" አስተምህሮ በትክክለኛ አስተምህሮ ለመተካት በሚል ነው፣ የዚህች ቤተክርስቲያን ምሥረታ መነሻ ግን ዊሊያም ሚለር "የክርስቶስ ዳግም መምጫ ጊዜ ተገለጠልኝ" በማለቱና በዚህም ሃሳቡን የሚደግፉ ሰዎች በሰሩት ስብስብ ነው፡፡

ነገር ግን በሚለር ስህተት ምክንያት ቤተክርስቲያኗ ከፍተኛ ውድቀት ውስጥ በመግባቷ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ቤተክርስቲያኗን ከመዘጋት ለማዳን የተለያየ ዘዴዎችን ተጠቀሙ፣ በዚህም በመጀመሪያ የሚለር ስህተቶች ላይ ማስተካያ ማድረግ፣ በመቀጠል ደግሞ ምዕመናኖቿ ወደ ፕሮቴስታንትና ካቶሊክ እንዳይሄዱባት እነዚህ ሁለቱ ሀይማኖቶች "በተሳሳተ መንገድ ላይ መሆናቸውን" በማስተማር ሰዎች ወደነዚህ ሀይማኖቶች እንዳይመለሱ የማድረግ አቅጣጫን ተከተለች፣ በነዚህ ዘዴዎችም ቤተክርስቲያኗ ከውድቀት ዳነች፡፡

እነዚህ መፍትሄዎች ቤተክርስቲያኗን ከመዘጋት ቢያድኗትም በውስጣቸው ብዙ ስህተቶችን ይዘዋል፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

### 5.3.1. <u>የሚለርን ስህተት "ማስተካከል"</u>

በሚለር ራዕይ አለመሳካት የደረሰውን ምስቅልቅሎሽ የማስተካከል ስራ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች በሆኑት በሂራም ኤድሰን እና ኤለን ጂ. ኋይት ተሰራ፡፡

ሂራም ኤድሰን(1806-1882) "በበቆሎ ማሳ ውስጥ ስሄድ ራዕይ አየሁ፣ ሚለር በተነበየው ቀን ኢየሱስ ተገልጦልኝ ከአንዱ የመንግስተ ሰማያት ክፍል

ወደ ሌለኛው ሲሄድ አየሁት፣ ስለዚህ ሚለር ቀኑን አልተሳሳተም ነገር ግን ሚለር ያላስተዋለው ኢየሱስ ያደረገው እንቅስቃሴ ወደዚህ ምድር ሳይሆን ወደ ሁለተኛ የመንግስተ ሰማያት ክፍል ነው" በማለት አከራካሪውን ጉዳይ ማንም ሰው ማረጋገጥ ወደማይችለው ቦታ አርቆ አስቀመጠው፡፡

ኤለን ጂ. ኋይትም "እኔም ራዕይ ተመልክቻለሁ" በማለት የሄራም ኤድሰንን ራዕይ የሚያጠናክር ቃል ተናገረች "ኢየሱስ ወደዚህ ሁለተኛው ክፍል የሄደው "የፍርድ ምርመራ" ለማድረግ መሆኑንና ይህም ለወደፊት ለፍርድ ሲመጣ ለመፍረድ እንዲያመቸው የሰዎችን መዝገብ ለመመልከት ነው" አለች፡፡

እነዚህ አስተምህሮቶች ለመፅሀፍ ቅዱሱ እንግዳ ሲሆኑ ይባሱኑም ከመፅሀፍ ቅዱሱ ጋር የሚጋጩና የኢየሱስን ክብር የሚነኩ አስተምህሮቶች ናቸው፣ ይህም፣

- ኢየሱስ ለሚፈርደው ፍርድ እንደ የሰው ዳኛ ገና "መዝገብ ቤት ገብቶ ይመረምራል" ማለቱ ስህተት ነው፣ ምክንያቱም ኢየሱስ፣
    - በአምላክነቱ ሁሉን አዋቂ በመሆኑ የመዝገብ ምርመር ውስጥ የማይገባ መሆኑ፣

      ዮሐ.2፡25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.21፡17, ዮሐ.1፡48-50, ዮሐ.2፡24-25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.6፡64, ዮሐ.21፡17, ማር.2፡8 ...

    - የሚተላለፈው ፍርድም ኢየሱስ ይቅርና ማንኛውም ሰው ዛሬውኑ በራሱ ላይ ሊያውቅ የሚችል መሆኑ፣

      ዮሐ.3፡18 "በእርሱ የሚያምን አይፈረድትም፣ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሄር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል፡፡"

    - የሚፈረድበትና ነፃ የሚሆነው ከፍርድ በፊት ቀድሞውኑ የተለየና የታተመ በመሆኑ፣

      ኤፌ.4፡30 "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሄር መንፈስ አታስዝኑ፡፡"

በዚህም ኢየሱስ ምንም የመዝገብ ጥናት የማያስፈልገው መሆኑና በዚህም "የምርመራ ጊዜ" የተባለው ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- ኢየሱስ ወደዚህ ስራው ገባ ከተባለው ከ1844 እስከ ዛሬ 2019 ድረስ ለ175 አመታት እዚያው መዝገብ ቤት ውስጥ እንደ ሰነፍ ዳኛ "እያጠና ነው" ማለቱ ክርስቶስን የሚሳደብ ለወንጌሉም እንግዳ የሆነ አስተምህሮት ነው፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ከተነገረው ሃሳብ ውጪ እንግዳ አስተምህሮ ማስገባት በራሱ መርገምት ነው፣

ገላ.1፡8-9 "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን፣ አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን፡፡"

በዚህም "ስህተትን ስህተት" ማለቱ ሲሻል ስህተትን በሌላ "መልካም" ስህተት መሸፈን ውጤቱ የከፋ ነው፡፡

የሚገርመው ደግሞ ሶስቱንም የቤተክርቲያኒቱን መሪዎች ለስህተት የዳረገው ከመነሻው ሰው ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበትን ቀን ሊያውቀው የማይችል መሆኑን አለመረዳታቸው ነበረ፣

- 1ተሰ.5፡1-2 "ወንድሞች ሆይ፣ ስለ ዘመናትና ወራት ምንም እንዲፃፍላችሁ አያስፈልጋችሁም፤ የጌታ ቀን፣ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና፡፡"
- ማቴ.24፡36-42 "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰአት ግን ከአባት በቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም፣ የኖህ ዘመን እንደነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፡፡ በዚያች ወራት ከጥፋት ውሃ በፊት ኖህ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፣ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደነበሩ፣ የጥፋት ውሀ መጥቶ ሁሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፣ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ

እንዲሁ ይሆናል... ጌታችሁ በምን ሰአት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ፡፡”

ተመሳሳይ ሀሳቦችም ሉቃ.12፡39, ራዕ.3፡3, ራዕ.16፡15 ... ላይ ተመልክቷል

በዚህም የኢየሱስ ዳግም መምጫ ቀን የሰው ልጅ ሊያውቀው አይችልም፣ በዚህም ሚለር “የኢየሱስ ዳግም መምጫ ቀን” ብሎ የሰራው ስሌት በምንም ዘዴ ሊስተካከል አይችልም፡፡

### 5.3.2. ካቶሊክን ማንቋሸሽ

ፕሮቴስታንት ከካቶሊክ በመውጣቷና ከዚያም አድቬንቲስት ከፕሮቴስታንት ወጥታ ይህን ውርደት መከናነቧ በነማርቲን ሉተር ለተወገዘችው ካቶሊክ የአድቬንቲስት ስህተት ትልቅ ማሾፊያ ሆነ፣ ለዚህም የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ራስዋን ከካቶሊክ ነቀራ ለመጠበቅና አባላቶቿም ወደ ካቶሊክ እንዳይፈልሱባት ለመጠበቅ ዘዴ ቀየሰች፣ ዘዴውንም በአስተምህሮት ላይ እንዳታደርግ ከመጀመሪያው ማርቲን ሉተር በካቶሊክ አስተምህሮ ላይ ጠንካራ ሂሶች ስለሰነዘረ በአስተምህሮ ካቶሊክን መንቀፍ አመቺ አልሆነም፣ በዚህም በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ ጭፍን የስም ማጥፋት ዘዴን ተከተለች፣ በዚህም፣

- መፅሀፍ ቅዱሱ “አውሬው” የሚለው መንፈስ ባልተገለጠበት ጊዜ ጳጳሱን “አውሬው ናቸው”፣
- የካቶሊክ ቤተክርስቲያንንም መፅሃፍ ቅዱሱ የሚያወግዛት “አዲሲቱ ባቢሎን ናት”፣
- ሰንበትን በእሁድ ቀን የሚያከብር “የአውሬው ምልክት የተቀበለ ነው”፣

የሚሉ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ስራዎችን በካቶሊክ ቤተክርስቲያ ላይ ሰራች ነገር ግን መፅሃፍ ቅዱሱ የሚያስጠነቅቀው አውሬም ሆነ “አዲሲቱ ባቢሎን” የተባለችው ከተማም ሆነ የአውሬው ምልክት የተባሉት በምዕራፍ 7 ላይ እንደተመለከተው በወቅቱ ያልተገለጡ መሆኑና መንፈሱ ሲገለጥም የሚሰራው ለሰባት አመታት/አንድ ሱባኤ(ዳን.9፡27) እንጂ ለዚህን ያህል ክፍለ ዘመናት አለመሆኑን ስንመለከት በወቅቱ በካቶሊክ ላይ የተሰነዘረው ጥቃት ተራ አሉባልታ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

### 5.3.3. ከፕሮቴስታንት በአስተምህሮ ተለይቶ መገኘት

ቤተክርስቲያኗ ከምስረታዋ ከፕሮቴስታንት የወጣችበት ምክንያት "የኢየሱስ መምጫ ቀን" ላይ በተፈጠረ የህሳብ ልዩነት ቢሆንም ክርስቶስ በተባለው ቀን ባለመምጣቱ ምክንያት የቤተክርስቲያኗ አባላት ጠቅልለው ወደ ፕሮቴስታንት እንዳይመለሱ፣ ቤተክርስተያኒቷ ከፕሮቴስታንት የሚለያትን የተለየ ዶክትሪን በማስቀመጥ የልዩነት መስመር ማኖር እንዳለባት ተመለከተች፡፡

በዚህም ከፕሮቴስታንት ጋር የልዩነት መስመር ሊሰሩ የሚችሉ "የፕሮቴስታንት ስህተቶች" መፈለግ የግዴታ ሆነ ነገር ግን የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በወቅቱ በተሀድሶ የተመሠረተች አዲስ ቤተክርስቲያን ስለነበረች ለትችት የማትመች ሆነች፣ ነገር ግን ከተደረጉት ጥናቶች "የፕሮቴስታን ስህተት" ተብሎ ጎልቶ የወጣው "ፕሮቴስታንት የሰንበት ቀንን አታከብርም" የሚለው ሆነ፣ በዚህም የ"ሰንበትን ማክበር" ጉዳይ ቤተክርስቲያኗ ከፕሮቴስታንት የምትለይበት ዋነኛ መለያ ሆነ፣ በዚህም ከፕሮቴስታንት የተለየችና የተሻለች መሆኗን ለማሳየት የቤተክርስቲያንዋ ስም "ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን" እስከ ማለት ተደረሰ፡፡

ሁለተኛው "ፕሮቴስታንትን በአስተምህሮ መለየት" ተብሎ የገባው አስተምህሮ "እግዚአብሄር የፍቅር አምላክ በመሆኑ ሰዎችን በሲኦል እሳት ውስጥ አይቀጣም" የሚለው ሆነ፣ በዚህም [145] "ነፍስ ለዘለአለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ቦታ የለም" [146] "በዘሌ.16፡21-22 ላይ እንደተገለፀው ፍየል (Escape goat)፣ በመጨረሻውም ቀን ሀጢያተኛ ሰው ለዘላለም ሲሞት፣ ሀጢያቱ ደግሞ በሰይጣን ላይ ተረድጎ ሰይጣንም የሰውየውን ሀጢያት ተሸክሞ ወደ ሲኦል ይወርዳል" የሚለው ሀሳብ ተነሳ ነገር ግን ይህ መፅሀፍ ቅዱሱን ለያዘው ህብረተሰብ እምብዛም አሳማኝና እትኩሮት የሚስብ ነገር አልነበረም፣ በ5.2.3.5. ክፍልም እንደቀረበው ይህ አስተምህሮ መፅሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣ በዚህም ጠንከር ያለው የልዩነት መስመርን፣ የሰንበት ጉዳይ ሆነ፣ ቀጥለን በሰፊው እንመለከታለን፡፡

---

[145] Ellen G. White, **The Great controversy**, chapter 33, page 531-550
[146] ibid, Chapter 23, page 422

ከመነሻው ታሪክ ስንነሳ "ሰንበት" ማለት "ዕረፍት" ማለት ነው፣ በስነ ፍጥረት ታሪክ ፈጣሪ የስድስቱን ቀናት የፍጥረት ስራው ሰርቶ ያረፈው በሰባተኛው ቀን ነው፣ በዚህም ፈጣሪ በሰባተኛ ቀን እንዳረፈው ሰዎችም በዚህ ቀን እንዲያርፉ አዘዘ፣

- ዘፀ.20፡11 "እግዚአብሄር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባህርንም፣ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና፤ ስለዚህ እግዚአብሄር የሰንበት ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም፡፡"
- ዘፀ.20፡8 "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡"
- ዘፀ.35፡3 "በማደሪያዎቻችሁ ውስጥ በሰንበት ቀን እሳትን አታንድዱ፡፡"

በዚህም የሰንበት ቀን ምንም ስራ የማይሰራበት የተቀደሰ የእረፍት ቀን ነው፣ ያላከበረውም፡-

ዘፀ.31፡14 "ስለዚህ ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን ጠብቁ ፣ የሚያረክሰው ሰው ሁሉ ፈፅሞ ይገደል፣ ስራንም በእርሱ የሰራ ሰው ሁሉ ከህዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ፡፡"

የሚደረሰ ትልቅ ቅጣት አለው፡፡

ነገር ግን እነዚህ "የሰንበትን ቀን ቀድሰው፣ አክብረው፣ በዚያን ቀን አትስራ ..." የሚሉት ጥቅሶች በሙሉ የሚጠቀሱት ከብሉይ ኪዳን ብቻ ነው፣ አዲስ ኪዳኑን ላይ እነዚህን ትዕዛዞች አንመለከትም፣ ኢየሱስም ሆኑ ሐዋርያቱ በሰንበት ቀን ሲሰሩ ነበረ(ማቴ.12፡1-5, ማቴ.12፡10-12 ...) በዚህም አይሁዶች ዮሐ.9፡16 "... ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሄር አይደለም አሉ፡፡"፣ ሌሎቹ ደግሞ  በዘፀ.31፡14 ህጋቸው መሠረት ዮሐ.5፡16 "ስለዚህ በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበረ ሊገድሉትም ይፈልጉት ነበረ፡፡"

ይባሱኑ ኢየሱስና ሐዋርያቱ "የቀኑ ሰንበት ቀርቷል" ብለው አስተማሩ፣

- ማቴ.12፡12 "... ስለዚህ በሰንበት መልካም መስራት ተፈቅዶአል አላቸው፡፡
- ዕብ.4፡9 "እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሄር ህዝብ ቀርቶላቸዋል፡፡"

የሰንበት ትዕዛዝ የተሰጠው በዋናው አስርቱ ትዕዛዛት ነው፣ ኢየሱስ ደግሞ "ህግን ልሽር አልመጣሁም" እንዳለው ህጉን አልሻረም ነገር ግን በ4.2 ክፍል እንደተመለከተው አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ሲተካ ብዙ ቃላቶች አተረጓጎም ከፍ ተደርገዋል፣ ከነዚህም አንዱ የሰንበት ትርጉም ነው፣

> ቆላ.2፡16-17 "እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፡፡ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው፡፡"

በዚህም በብሉይ ኪዳን ቀን የነበረው ሰንበት፣ በአዲሱ ኪዳን፣ ህጉ ሳይሻር የሰንበቱ ትርጉም ወደ ክርስቶስ ከፍ ተደረገ፣ በዚህም በአዲስ ኪዳን ዘመን ሊታረፍበት፣ ሊቀደስ፣ ሊከበር … የሚገባው ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን ተመለከተ፡፡

በዚህም ቤተክርስቲያኗ በፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ላይ ያነሳችው ትችት ትክክል አለመሆኑና የቤተክርስቲያንዋ መለያ እስኪሆን የደረሰው "ሰባተኛው ቀን" ጉዳይም የአዲሱ ኪዳን እውቀት ጎዶሎነት ያሳየ እውነታ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

## ማጠቃለያ(አድቬንቲስት)

በመግቢያው ላይ እንደተመለከትነው የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በሁሉም በተረጋገጠ በሚለር ውሸቶች ነው፣ ውሸቱም ደግሞ መፅሃፍ ቅዱሱ "ምስክር በሁለት ይፀናል" እንደሚለው ሁለት ጊዜ ተከሰተ፡፡

ሚለር ሁለቴ በመዋሸቱ ምክንያት በአድቬንቲስትነት የተሰባሰበው ማህበረሰብ ወደ ሌሎች ሀይማኖቶች እንዳይሄድ እነ ኤለን ጂ. ኋይትና ሂራም ኤድሰን ደግሞ የሚለርን ውሸት በሌላ ሁለት ውሸቶች ለመሸፈን ሞከሩ፣ በርግጥ በውሸት የተጀመረ በእውነት ይጨርሳል ተብሎ አይታሰብም፣ ምክንያቱም መነሻው የውሸት አባት ነውና፡፡

በዚህም አዕምሮ ያለው ሰው በነዚህ የሚለር፣ ኤድሰንና ኤለን ሰንሰለታማ ውሸቶች መሠረት ላይ በቆመች ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ሳይታለል በጊዜ ሚለር ወደወጣበት ፕሮቴስታንት ቢመለስ መልካም ነው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. ፕሮቴስታንት

መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ አንድ የታሪክ ድግግሞሽ አለ፣ ሰይጣን የስህተት ትምህርቶችን ወደ ቤተክርስቲያን በማስገባት ሰዎችን ከትክክለኛው መንገድ ሲያስወጣ የነበረበትና እግዚአብሄር ደግሞ ቅዱሳንን ተጠቅሞ ተሀድሶን ሲያንቀሳቅስ፣ በሰይጣን የገቡትን እርኩሰቶችን ጠራርጎ ሲያወጣና ቤቱን ሲያድስ የነበረበት ተደጋጋሚ የታሪክ ሂደት(ዘፀ.32፡20, መሳ.6፡25-30, 2ነገ.10፡26-28, 2ነገ.23፡4, 2ዜና.29፡5, 2ዜና.34 ...)፡፡

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ምን ያህል የስህተት ትምህርቶች እንደገቡ በምዕራፍ አራት ተመልክተናል፣ እግዚአብሄር አሳሳች ትምህርቶች እንዲስተካከሉ ተሀድሶ ሲያስነሳ እንደነበረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ ፒተር ዋልዴስ፣ ጆን ዋይክሊፈ፣ ጃን ሁስ፣ ማርቲን ሉተር ... የመሳሰሉ ጠንካራ የሀይማኖት መምህራኖችን በተሀድሶ መንፈስ አስነሳ፡፡

ከነዚህ ውስጥም [147]በጀርመን ሀገር በነማርቲን ሉተር የተነሳው የተሀድሶ እንቅስቃሴ 95 የተሀድሶ ነጥቦችን በማንሳት በ1517 ዓ.ም የመጀመርያዋን የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን መሰረተ፣ ቤተክርስተያኗም በኦርዶክስ/ካቶሊክ ያለውን ግሳንግስ ጥላ ኢየሱስ በከፈለው ዋጋ ቀለል ብሎ በመጣው አዲስ ኪዳን መሰረት አምስት የዕምነት መርሆችን (Five Solae)[148] ይዛ ተነሳች፣ እነሱም መመሪያ መፅሀፍ ቅዱስ ብቻ(Sola Scriptura)፣ አምልኮ ለእግዚአብሄር ብቻ(Soli Deo gloria)፣ ድነት በፀጋ(Sola Gratia)፣ በዕምነት(Sola Fide) እና በኢየሱስ ክርስቶስ(Solus Cristos) ብቻ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህ የዕምነት መሰረቶችም ግልፅና አሳማኝ በመሆናቸው በአብዛኛው ክርስቲያን ዘንድ በአንዴው ተቀባይነት አገኙ፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ያለ ምንም ጦርነት በአንድ ጊዜ ከአለም ጥግ እስከ ጥግ ተዳረሰች፣ ቤተክርስቲያኗ

---

[147] https://en.m.Wikipedia>wiki>Protestantism

[148] https://en.m.Wikipedia>wiki>Protestantism/Five Solae

በተለይ በአሜሪካ ላይ ያመጣችው መንፈሳዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ በአለም ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ ይዟል፣ ቤተክርስቲያኗ በአሁኑ ጊዜ ከ800 ሚሊየን እስከ አንድ ቢሊየን የሚገመቱ አባላት እንዳሏት ይነገራል፡፡

በዚህ ምዕራፍም የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንን በስፋት የምንለከት ሲሆን፣ በዚህም፣

- ፕሮቴስታንት ህይማኖት ስር የሚመደቡ አብያተ ክርስቲያናት፣
- በፕሮቴስታንት ላይ እየተነሱ ያሉ ትክክኛና የተሳሳቱ ሂሶች፣
- በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል እየታየ ያለ ክፍፍል፣
- የቤተክርስቲያኗ ድክመቶች፣

በስፋት እንመለከታለን፡፡

## 6.1. <u>በፕሮቴስታንት ህይማኖት ስር የሚመደቡ አብያተ ክርስቲያናት</u>

የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በነማርቲን ሉተር ኪንግ መሪነት በተነሳ የተሀድሶ እንቅስቃሴ ስትመሰረት እንቅስቃሴው ግልፅና አሳማኝ ስለነበረ ህይማኖቱ ያለመስራቾቹ መሪነት በየቦታው እንደ ሰደድ እሳት ተቀጣጠለ፣ በዚህም በአውሮፓና በአሜሪካ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ስር የሚመደቡ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተቋቋሙ በዚህም ሉትራኒዝም፣ አንግሊካኒዝም፣ ካልቪኒዝም፣ ሜቶዲዝም፣ ፕሪስብቴሪአኒዝም … የሚባሉ አብያተ ክርስቲያናት በየሀገራቱ እየተፈጠሩ ሄዱ፡፡

በሀገራችን በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በዋናነት በሶስት ይከፈላሉ፣ እነሱም ወንጌላውያን፣ መካነ ኢየሱስና ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡

“ወንጌላውያን” የሚባሉት በ“የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት” ስር የታቀፉት ሙሉ ወንጌል፣ ቃለ ህይወት፣ መሠረተ ክርስቶስ፣ የህይወት ብርሀን … የሚባሉ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ የመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን እንደ ወንጌላውያኑ ቀደምት የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ብትሆንም ቤተክርስቲያኗ ህፃናትን ማጥመቋ፣

ጥቀትን በውሀ በማበስ ማከናወኗ፣ የቅስና ሹመት መስጠቷ ... ብዙውን ጊዜ ከወንጌላውያኑ ተለይታ እንድትታይ አድርጓታል፡፡ “ባለራዕይ” የሚባሉት በግለሰቦች “ራዕይ” የተመሠረቱት “የኢትዮጵያ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ህብረት” ስር የሚገኙት ከደርግ መንግስት ውድቀት ቦሀላ የተመሰረቱ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡

መካነ ኢየሱስን ጨምሮ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ስር የሚገኙት አብያተ ክርስቲናያት የተለያዩበት ዋነኛ ምክንያት ሚሽነሪዎች ተሀድሶውን ወደ ኢትዮጵያ ሲያስገቡ አመጣጣቸው ከተለያዩ ሀገሮች በመሆኑና በተሰማሩበት ክፍለ ሀገርም የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን በመመስረታቸው ሲሆን ከዚያም በኋላ እንደነ ሙሉ ወንጌል ያሉት ደግሞ በሀገር ውስጥ የበቀሉ ሲሆን እነሱ ደግሞ “የሚሽነሪዎቹ አስተምህሮ ትክክለኛ ወንጌል ቢሆንም ካሪዝማቲክ(የፀጋ ስጦታ) መንገድ የተከተለ አይደለም” በማለት ቤተክርስቲያንን በካሪዝማቲኩ መንገድ የመሠረቱ ናቸው ነገር ግን በሂደት ሁሉም በሚሽነሪዎች የተመሠረቱት ይህንኑ መንገድ ተቀላቅለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ስር የሚመደቡት በግለሰቦች “ራዕይ” የተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፣ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እጅግ ብዙ ሲሆኑ በየጊዜውም ቁጥራቸው እየጨመረ ይገኛል፣ የመብዛታቸው ምክንያትም ከአስተምህሮ ልዩነት ወይ ከሚሺነሪዎች ልዩነት ወይ ከካሪዝማቲክነት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ሳይሆን “በተቀበሉት ራዕይ”፣ በነበሩበት ቤተክርስቲያን በደረሰባቸው መገፋት ወጥተው፣ ለኪራይ ሰብሳቢነት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በሚል(ከታች በ6.3 ስር በዝርዝር እንመለከተዋለን) እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ነው፡፡

## 6.2. <u>በፕሮቴስታንት ላይ የሚቀርቡ ሂሶች(ትችቶች)</u>

በፕሮቴስታንት ላይ እየተሰጡ ያሉት ሂሶች በዋናነት የሚያተኩሩት ከመዝሙርና ቤተክርስቲያኗ ከተከተለችው የካሪዝማቲክ(የፀጋ) አገልግሎት ይህም አዲስ ቋንቋ(ልሳን)፣ ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ጋር በተያያዘ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ትክክለኛ የሆኑትንና የተሳሳቱ ሂሶችን ለያይተን እንመለከታን፡፡

### 6.2.1. መዝሙር

ከመዝሙር ጋር በተያያዘ በፕሮቴስታንት ላይ የሚቀርበው ሂስ "መዝሙሮቻቹ ያሬዳዊውን ስልት አይከተሉም፣ በዚህም መዝሙሮቹ ከመዝሙርነት ይልቅ ዘፈን ይመስላሉ" የሚል ነው፡፡

- የተሳሳተ ሂስ

መዝሙርን በሰሜን ኢትዮጵያው ያሬዳዊ ስልት መገደቡ ጠባብተኝነት ይባሱኑም መርገምት መሆኑን 4.4.1.4 ክፍል ተመልክተናል፣ በዚህም መዝሙርን ያለ ያሬዳዊ ስልት "ውግዝ ከም አርዮስ" የሚባለው የተሳሳተ ሂስ ነው፡፡

- ትክክለኛ ሂስ

አንዳንድ ዘማሪያን በታወቁ ዘፈኖች ዜማና ክላሲካል መዘመራቸው ስህተት ነው፣ ይህ ተለይቶ መወገዝ አለበት፣ ለሰይጣን በቀረበ የመስዋዕት ዕቃ ለቅዱሱ ማቅረብ ስህተት ነው፣ መስዋዕቱም መልካም መዓዛ እንደሌለው እንደ ቃየል መስዋዕት ነው፡፡

- ለወደፊት ሊስተዋል የሚገባ

በ4.4.1.4 ክፍል እንደተመለከተው ሰው በውስጥ በመንፈሱ ባስደሰተው መንገድ መዘመሩ ችግር የሌለው መሆኑ እንዳለ ሆኖ ለወደፊቱ ጥንቃቄ ሊደረጉባቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ፣ ይህም ለአእምሮ የማይመቹ(ሮሜ.12፡1)፣ የሀጢያትና የሰይጣን ተፅዕኖዎች ያሉባቸው አዘማመሮች ከመዝሙር ሊርቁ ይገባል፣ እነዚህም የአዘማመር አይነቶች በአብዛኛው በአርኩሳኑ መናፍስት አካባቢ ያሉት እስታየሎች፣ የመራቢያ አካላትና መቀመጫ ተኮር ዳንሶች፣ የወንድና የሴት ፍቅረኞች ከሌላው ሰው ተለይተው የሚደንሱት ዳንሶችና የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው፡፡

ይህንን ወደ ሀገራችን አውርደን ስንመለከተው ደቡብና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ አካባቢ ያሉት መቀመጫ አካል ተኮር እንቅስቃሴዎች፣ ኦሮሚያ ውስጥ የምናየው በዛር የተያዘች ሴት የምታደርገው አይነት እራስን እንደ እንዝርት የማሾር እንቅስቃሴ፣ አማራ አካባቢ ያለው የእባብ አንገት እንቅስቃሴ አይነት እስክስታ፣ ትግራይ አካባቢ ያለው የአንድ ወንድ አንድ

ሴት ለብቻ ተነጥለው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደዚሁም በውጪ ሃገር ባህል ተፅዕኖ ምክንያት ወደ ሃገራችን እየገቡ ያሉ ዝሙታዊ ዳንሶች፣ እጅን የኮብራ እባብ እንቅስቃሴ አስመስሎ የሚከናወኑ ዳንሶች፣ እንደ እባብ ከእግር አንስቶ እስከራስ ድረስ የሚደረግ ዝግዛጋማ ዳንሶች፣ የመንዙማና የቃልቻ ቤት የድቤ አመታቶችና ዜማዎች ... በሙሉ ከዝማሬ ሊርቁ የሚገቡ ነገሮች ናቸው፣ ከነዚህ በተጨማሪም ቢያንስ ከመዝሙርና ከቤተክርስቲያን አካባቢ ዝሙታዊ አለባበሶችም ሊርቁ ይገባል፡፡

ስለዚህ ትክክለኛውን፣ ስህተቱንና ለወደፊት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡትን የዝማሬ እስታየሎች ተለይተው ሊታወቁ ይገባል፡፡

### 6.2.2. <u>የካሪዝማቲክ መንገድ (መንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች - አዲስ ቋንቋ(ልሳን)፣ ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ...)</u>

በፕሮቴስታንቱ አካባቢ የምንመለከተው የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ ላይ ብዙ ሂሶች ሲሰጡ ይታያል፣ ከነዚህ ሂሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆኑት፣ የተሳሳቱትንና ለወደፊት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡትን ለይተን እንመለከታለን፡፡

#### 6.2.2.1. <u>አዲስ ቋንቋ (ልሳን)</u>

“ልሳን” ማለት አዲስ ቋንቋ ማለት ነው፣ ከልሳንም ጋር በተያያዘ እንደ መዝሙሩ የተሳሳቱ ሂሶች፣ ትክክለኛ ሂሶችና ለወደፊቱ ጥንቃቄ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ነገሮችን እንመለከታለን፡፡

- <u>የተሳሳቱ ሂሶች</u>

ከልሳን(አዲስ ቋንቋ) ጋር በተያያዘ የሚሰጡቱ ሂሶች በዋናነት ልሳን መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ባለማወቅ ነው፤ ይህንንም ከስር መሠረቱ ብንመለከት፣ በመጀመሪያ እግዚአብሄር የሰው ልጅን ሲፈጥር በመጀመሪያ በራሱ መልክ መንፈስ የሆነውን የሰውን ማንነት በስድስተኛው ቀን ፈጠረ(ዘፍ.1፡27)፣ ከዚያ ይህን መንፈስ ከአፈር ስጋ አበጀው(ዘፍ.2፡7)፣ ከዚያ በዚህ ስጋ ውስጥ ህያው ነፍስ አደረገ(ዘፍ.2፡7)፣ ይህ የስነ ፍጥረት ታሪክ ነው፣ በመጀመሪያ “ፈጠረ” ከዚያ “አበጀው” ከዚያ “እስትንፋስ እፍ” አለበት፣ በዚህም ሰው በስላሴ ምሳሌ ስጋ፣ መንፈስና ነፍስ ሆኖ ተፈጠረ፡፡

አብዛኛው ክርስቲያን ስለ ስጋና ነፍስ ማንነቱ እንጂ ስለ መንፈስ ማንነቱ ብዙም አያውቅም ነገር ግን መንፈስ የሆነችው የሰው ማንነት መንፈስ በመሆኗ ዓለሟ መንፈሳዊው ዓለም ነው፣ መንፈስ ከሆነው እግዚአብሄርም ጋር(ዮሐ.4፡24) በልሳን ትነጋገራለች(1ቆሮ.14፡2)፣ በልሳን ፀሎትም ታቀርባለች(1ቆሮ.14፡14) …

በርግጥ ይህ ስጦታ የሚገለጠው ሰዎች ትክክለኛው የዕምነት መስመር ውስጥ ሲገቡ ነው፣

> ማር.16፡17 "ያመኑት እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል … በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ …"

በዚህም ይህን አዲስ ቋንቋ መናገር የማይችሉት በሙሉ ትክክለኛውን እምነት ያልያዙና መንግስተ ሰማያትን የማይገቡ(ዮሐ.3፡3) ሰዎች ናቸው፣ በዚህም ልሳን የሚባለው አዲስ ቋንቋ የሚያስወግዝ ሳይሆን ትክክለኛ መንገድ ላይ መሆንን የሚያሳይ እውነታ ነው፡፡

- ትክክለኛ ሂሶች

ከልሳን ጋር በተያያዘ ትክክለኛ ሂሶችም ሲሰጡ እንመለከታለን፣ እነዚህም ቀድሞውኑም በመፅሀፍ ቅዱሱም እንዲስተካከሉ የተነገሩና አሁንም ሳይስተካከሉ የቀሩ ናቸው፣ እነሱም፣

- 1ቆሮ.14፡23 "እንግዲህ ማህበር ሁሉ ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ፡፡ አብደዋል አይሉምን?"
- 1ቆሮ.14፡27 "በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ቢበዛ ሶስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም፤"
- 1ቆሮ.14፡19 "ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማህበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ፡፡"

እነዚህ ዛሬም የሚስተዋሉና መስተካከል ያለባቸው ችግሮች ናቸው፡፡

- <u>ለወደፊቱ ሊስተዋል የሚገባ</u>

ከትክክለኞቹ ልሳናት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ሰዎች አግባብ ያልሆነ ሂስ ሲሰጡ እንመለከታለን፣ ከነዚህ ከመንፈስ ጋር የሚገናኙ አሰራሮች ላይ ያለ ዕውቀት ሂስ መስጠት አደጋው የከፋ ነው፣

- ማቴ.12፡32 “በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ አለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም፡፡”
- ዕብ.10፡28-29 “የሙሴን ህግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሶስት ቢመሰክሩበት ያለ ርህራሄ ይሞታል … የፀጋውንም መንፈስ ያከፋፋ እንዴት የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል፡፡”

ስለዚህ ከመንፈስ ቅዱስ አሰራር ጋር በተያያዘ ያለ ዕውቀት ሂስ ከመስጠት ዝም ማለቱ የተሻለ ነው፣ እግዚአብሄር በቅድስናው ላይ ለሚናገሩት ምህረት የለውም፣ መንፈስ ቅዱስ ላይ የተናገረ ፍርዱ ሲኦል መሆኑን አሁኑኑ መረዳት አለበት፣ ስለዚህ እውነታ እስኪገባን ድረስ አስተያየት ከመስጠት መቆጠቡ የተሻለ ነው፡፡

### 6.2.2.2. <u>ሌሎች የፀጋ ስጦታዎች - ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ …</u>

- <u>የተሳሳቱ ሂሶች</u>

የፀጋ ስጦታ የሌለባቸው አብያተ ክርስቲያናት በነዚህ ፕሮቴስታንት አካባቢ በሚታዩት የፀጋ ስጦታዎች ላይ የተለያዩ ሂሶችን ሲሰጡ ይታያል፣ ይህ ስህተት ሲሆን ከስህተትም አልፎ ከላይ እንደተመለከትነው የማይሰረይ ሀጢያት ነው፡፡

- <u>ትክክለኛ ሂሶች</u>

ከትንቢት ጋር በተያያዘ “ሰዎች በሚሰሙት ትንቢት በመያዝ ሀሳባውያን፣ ሰነፍና ብቸኛ እየሆኑ ይገኛሉ” የሚባለው ሂስ ትክክለኛ ሂስ ነው፡፡

ይህ ሂስ በአብዛኛው የሚመለከተው የክርስትናን አስተምህሮ በሂውማኒቲ አስተምህሮ ቀይጦ የመጣውን የብልፅግና ወንጌልን ነው፣ በብልፅግና ወንጌል አስተህሮ ሰዎች የሚባረኩት ሰርተው ሳይሆን በተአምራዊ

መንገድ በሚወርድ ሀብት ነው የሚል፣ አምልኮቱም የፉከራ፣ የሽለላና “የእምነት ልምምድ” በሚባለው ሰዎች ከተነገራቸው ትንቢት ጋር በሀሳብ የሚያስዋኝ አምልኮ ነው፡፡

ማንም ሰው እግዚአብሄር “መኪና እሰጥሃለሁ” ስላለ የሰው መኪና ሲመኝ፣ በሀሳብ ቁጭ ብሎ መሪ እያዞረ፣ ነዳጅ እየሰጠ … መቃዠት የለበትም፡፡ መፅሀፍ ቅዱሱ “እግዚአብሄር ለእያንዳንዱ የእምነት መጠን እንዳካፈለው እንደ ባለአእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው በላይ አልፎ እንዳያስብ ይመከራል(ሮሜ.12፡3)፣ ሰው በተሰጠው ትንቢት የሚለወጠው የእግዚአብሄርን ጊዜ በመጠበቅ፣ በመፀለይና በ1.4.2 ክፍል እንደተመለከተው ጠንክሮ በመስራት ብቻ ነው፡፡ መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ “እባርክሀለሁ” ተብለው በሀብት የተባረኩትን ሰዎችን ሀብት ስንመለከት ሀብታቸው በተአምራዊ መንገድ የወደቀላቸው ሳይሆን በያዙት ስራ ላይ እግዚአብሄር በሰራው የማባዛት ስራ ነው፣ ሩት በረከትዋ ጋር ለመድረስ በመጀመርያ ነዶ ለቃሚነትን በአግባቡ መፈፀም እንደነበረባት ሁሉ ማንኛውም አማኝ ዛሬ ላይ የያዘውን ስራ በርትቶ ይዞ ነው ከተነገረው በረከት ጋር የሚገናኘው፡፡

“ትንቢት” ማለትም በህይወት ውስጥ በሆነ ጊዜ የሚደረስበት ራዕይ እንጂ የዛሬ ጉዳይ አይደለም፣ ራዕይም የሚነገረው ሰው ባለበት ሁኔታ ተስፋ ሳይቆርጥ በያዘው ነገር እንዲበረታ እንጂ በምኞት ባህር ሰጥሞ ከህይወት ሩጫና ውድድር ገለልተኛ እንዲሆን አይደለም፣ ሰው የተነገረውን ትንቢት ብቻ እያየ በስንፍና የዛሬውን በርትቶ አለመያዙ በራሱ ከተነገረው መንገድ እንኳን ያወጣዋል፣

ምሳ.19፡3 “የሰው ስንፍና መንገዱን ታጣምምበታለች …”

በሌላ በኩል ደግሞ ሊስተዋል የሚገባው ነገር ትንቢት ህግ አይደለም፣ የተነገረውም ትንቢት ሊሻር ይችላል(1ቆሮ.13፡8)፡፡

በዚህም የትኛውም አማኝ የተነገረውን ትንቢት በልቡ ይዞ፣ ዛሬ ላይ በህይወቱ ውስጥ ያሉትን ዕድሎች አሟጦ በመጠቀም፣ ማግኘት ያለበትን ጥቃቅን ጥቅሞችን ሳይንቅ፣ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ራስን በማስተካከል፣ ከማህበረሰቡ ጋር ተሳስሮ በመኖር፣ በ1.4.2 ክፍል በቀረበው የመፅሀፍ

ቅዱሱን የጠንካራ ሰራተኛነት መርህ በመኖር፣ ከሌላው በተሻለ መልክ ራስን ከነባራዊው ሁኔታ ጋር አመሳስሎ በአሸናፊነት መራመድ ይገባዋል፡፡

ሌላው ከፀጋ ስጦታ አጠቃቀም ጋር እየተፈጠረ ያለው ችግር በቤት ለቤት በሚደረጉት ፀሎቶች ነው፣ ይህም አገልጋዮች እንደ በዓል ነቢያት(1ነገ.18፡25-39) በከባድ ድምፅ ጎረቤትና ሰፈሩን የሚረብሹበት፣ አንድ ሚርተኛ ወይ ቡዳ ወይ ... በራዕይ ተመልክተው ያለ ጥበብ በመናገር ቤተሰቡን ከጎረቤቶቹ በሙሉ የሚያጣሉበት፣ ለአማኙ የመጣውን የትንቢት ቃል አማኝ-አህዛቡ ሁሉ እየሰማ በመናገር፣ ያዕቆብ ህልሙን ለወንድቹ በመናገሩ የገባበት አይነት ችግር ውስጥ ሰዎች እንዲገቡ በማድረግና ዕንቁዎቻቸውን በዕርያ ፊት በመጣል የሰዎችን ማህበራዊ ህይወት እንዲጎዳ ሲያደርጉ ይታያል፡፡ ከፈውስም ጋር በተያያዘ የፈውስ አገልግሎት ላይ በአደባባይ "ከኤች አይ ቪ፣ ጉበት ... በሽታ ተፈወስክ" ከማለት ለሰውየው በግሉ መንገሩ ብልህነት ነው፣ ሰውየው በፈለገበት ጊዜ ይመስክር ነገር ግን ባዩት መገለጥ የራስን ዋጋ ከፍ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ ስህተት ነው፣ በዚህም አገልጋዮች በራዕይና በመገለጥ ከማገልገሉ ጎን ለጎንም በጥበብም ማገልገል ይገባቸዋል፡፡

- <u>ለወደፊቱ ሊስተዋል የሚገባ</u>

ከሁሉም የሀይማኖት ተቋማት በተለየ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰፊ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን (ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ...) እንመለከታለን፣ ይህ ደግሞ እየሆነ ያለው ስር ሳይምሱ፣ ቅጠል ሳይበጥሱ፣ የጅብ ቅንድብ ... ሳይሉ መፅሀፍ ቅዱሱ እንደሚያዘው "በኢየሱስ ስም" ስልጣን መሆኑ የፀጋውን ቅዱሳዊነት ያረጋግጣል፣ ይህም ቤተክርስቲያኒትዋን ከየትኛው የዕምነት ተቋም በተለየ በትክክለኛው የእግዚአብሄር መንገድ ላይ ያለች መሆንዋን ያሳያል፡፡

የሚገርመው ደግሞ አብዛኞቹ የእምነት ተቋማት እነዚህ የፀጋ ስጦታዎች መኖራቸውን ያውቃሉ ነገር ግን እውቀታቸው በታሪክ እንጂ በተጨባጭ አይደለም፣ በዚህም እነዚህ የእምነት ተቋማት ከኔትዎርክ ውጪ የሚሰሩ የድሮውን ታሪክ ብቻ የሚያወሩ "የታሪክ አስተማሪዎች" ሆነዋል፣ 2ጢሞ.3፡5 ላይ የምንመለከተው "የአምልኮት መልክ አላቸው ሀይሉን ግን ክደዋል፡፡" የሚባሉት አይነት ሆነዋል፣ ይህ ደግሞ እየሆነ ያለው "ፀጋው ይበዛል"

በተባለበት በመጨረሻ ዘመን(ሐስ.2፡17-18) መሆኑን ስንመለከት በአሁኑ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ(ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ …) በተጨባጭ የሌላት ቤተክርስቲያን "ቤተክርስቲያን" መባል የሌለባት ከመስመሩ ውጪ ያለች መሆንዋን እርግጠኛ መሆን አለባት፡፡

በርግጥ ፕሮቴስታንት ጋር የምንመለከታቸው እነዚህ ፀጋዎችም መቶ በመቶ የጠሩ አይደሉም፣ ሀሰተኞችም ተደባልቀው እየሰሩ ይገኛሉ፣ ይህም ችግር በነኤርምያስ ዘመን እንደነበረው አይነት ችግር ነው (ኤር.28) ነገር ግን የፀጋ ስጦታ ከሌላት እያላት ከስህተቶችና ከአሳሳቾች ጋር የምትንደፋደፈው የተሻለች ናት ምክንያቱም ያለው ችግር የመደባለቅ ጉዳይ እንጂ ከመስመር ውጪ የመሆን ችግር አይደለም፡፡

በረሀ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ምንጭን ሳየዩ ከርቀት፣ ጭው ካለው በረሀ መካከል የበረሀ ምንጭ(Oasis) ያለበትን ቦታ ለይተው ያውቃሉ፣ አረንጓዴ ዛፎች በተሰበሰቡበት ምንጭ ይገኛል፣ እነዚህ ዛፎች ውስጥ ከታች በ6.3 ስር እንደምንመለከተው መልካምም መጥፎውም ይኑርበት እንጂ ምንጩ እዚያው ጋር ነው ያለው፣ እንደዚሁ ጥሩም መጥፎም ሰዎች ይሰብሰቡበት እንጂ የትኛውም ሰው ትክክለኛው የመንፈሳዊው ህይወት ምንጭ የቱ ጋር እንዳለ ጭው ካለው መንፈሳዊ በረሀ ውስጥ መለየት መቻል አለበት፡፡

ስለዚህ ማንም ሰው መጥፎው ዛፍ የራሱን ቅጣት እንደሚሰጠው አውቆ፣ በረሀውንና ምንጩን ለይቶ ሊመለከትና ከበረሀው ወደ ምንጩ ሊጠጋ ይገባዋል፡፡

### 6.3. በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል እየተፈጠረ ያለ ክፍፍል

ለዘመናት ሠላም የነበረችው የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን የመስፋፋት ምዕራፍ ውስጥ ስትገባ ቤተክርስቲያኗን የሚከፋፍሉ አሰራሮች ብቅ እያሉባት ይገኛል፣ ይህም ችግር እየመጣ ያለው በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል በሚታየው በሁለት የተቃርኖ አሰራሮች ምክንያት ነው፣ ይህም ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት ለቀቅ ያለ አሰራርና ወንጌላውያኑ(መካነየሱስን ጨምሮ) የተከተሉት አሳሪ አሰራር ምክንያት ነው፡፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናትም በዚህ ልዩነቶቻቸው ምክንያት በተለያዩ ህብረቶች "የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረትና የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ህብረት" በማለት በተለያየ ቡድን እስከ መደራጀት፣ መፎካከርና እርስ በርስ መናቆር ደርሰዋል፡፡

በዚህ ልዩነት ላይ ደግሞ አንዳንድ የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት መስራቾች፣ ልክ የአሜሪካዋ የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ከተመሠረተች በኋላ በገጠማት ፈተና አባላቶቿ ወደ ፕሮቴስታንት እንዳይኮበልሉ በማለት "ከፕሮቴስታንት በአስተምህሮ ተለያይቶ መታየት" በሚል ከፕሮቴስታንት የሚለዩዋትን አስተምህሮዎች እንደሰራችው፣ እነዚህ መሪዎችም በሁለቱ ቡድኖች መካከልም የልዩነት መስመር የሚያደርጉ አስተምህሮዎች እያስገቡ ይገኛሉ፣ በዚህም "የብልፅግና ወንጌል፣ አምስቱ የአገልግሎት ቢሮዎች፣ የኢየሱስ ስጋ ከማርያም አይደለም፣ ኢየሱስ በወርሀ ስጋው አምላክነት አልነበረበትም፣ የዳነው በፀጋ ነው ስለዚህ ሀጢያት ብንሰራም ችግር የለውም…" የሚሉ ኢ-ፕሮቴስታንታዊ አስተምህሮዎችን እያስገቡ ይገኛሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ባለራዕይ ቤተክርስቲያን ላይ ያለው የአንድ ሰው የበላይነት አሰራር አብዛኛው ቦታ ላይ የቤተክርስቲያን ልቅነት እየፈጠረ ሲሆን ወንጌላውያኑ ጋር ያለው ጥብቅ አሰራር ደግሞ የወንጌል ስርጭቱንም ቆልፎ ይዞታል(ከታች በዝርዝር እንመለከታለን)፡፡

በዚህ ቤተክርስቲያን በተለያየ ቡድን መደራጀት፣ መፎካከር፣ እርስ በርስ መናቆር፣ አዳዲስ አስተምህሮዎች መግባት፣ የቤተክርስቲያን ልቅነትና ከመጠን በላይ ጥብቅነት ምክንያት የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ለሁለት ልትከፈል የምትችልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡

ልዩነቱን ከመሠረቱ ስንመለከተው፣ በሁለቱም ቡድኖች መካከል ያለው ልዩነት መነሻ በዋናነት ልክ በፖለቲካው "ሀገር የምታድገው በገብያ መር ስርአት ነው" የሚለው ካፒታሊዝምንና "ሀገር የምታድገው በዕዝ የኢኮኖሚ ስርአት ነው" የሚለውን የሶሻሊዝም ሽኩቻ ጋር የሚመሳሰል ሽኩቻ ነው፡፡

በፖለቲካው መስክ እነዚህ ጫፍ የወጡ ፍልስፍናዎች እንዳሉ ሆነው ሁሉም ሀገራት ግን የሚመሩት ሁለቱንም ፍልስፍናዎች አዋህደው በ"ቅይጥ የኢኮኖሚ ስርአት" እንደመሆኑ መጠን፣ በቤተክርስቲያናቱ መካከልም ለሚታየው ችግር መሠረታዊ መፍትሄ የሚገኘው ሁለቱን አካሄዶች በማዋሀድ ቅይጥ አካሄድን በማስፈን ነው፣ ይህንን ቅይጥ መንገድ ከመመልከታችን በፊት በቅድሚያ የሁለቱን ቡድኖች ጠንካራና ደካማ ጎን እንመልከት፣

- <u>ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት</u>

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በደርግ ዘመን በጭንቅ ውስጥ ተመሥርተው በጭንቅ ውስጥ ያለፉ አብያተ ክርስቲያናት እንደመሆናቸው መጠን አደረጃጀታቸውም እንደዚሁ ጥብቅ ነው፣ አሁንም የሚከተሉት አሰራር እንደዚያው ዘመን ጥብቅ አሰራር ነው፣ በዚህም፣

- አሰራሩ ለአጭበርባሪዎች ምንም ክፍተት የማይሰጥ መሆኑ፣
- አሰራሩ "ገብያ መር" መርህን የተከተለ ባለመሆኑ አዳዲስ ሰዎችም ገብቷቸው አምነው ወደ ክርስትና እንዲቀላቀሉ ማድረጋቸውና ያመኑትም በትክክለኛ መንፈሳዊ እድገት ውስጥ እንዲያልፉ ማድረጋቸው፣
- የትኛውም አገልጋይ ህዝቡን መስሎ እንዲኖር ማድረጋቸው፣

የሚያስመሰግናቸው ሲሆን ነገር ግን ይህ አካሄዳቸው ደግሞ ሌሎች የጎንዮሽ ችግሮች አሉበት፣

- ጥብቅ ቢሮክራሲው መሪዎችን የደንብና የመመሪያ ባርያዎች በማድረግ እንደ ባለራዕዮቹ መሪዎች በባለቤትነት ስሜት አዳዲስና ከአካባቢው ጋር የሚመጥኑ አካሄዶችን ፈጥረው እንዳይንቀሳቀሱ ይዟቸዋል፣ ይህ ደግሞ ወንጌል ሊሄድ በሚገባበት ፍጥነት እንዳይሄድ አድርጓል፣

- አንድን ሰው ወደ አገልጋይነት ለማሳደግ የተቀመጡት መስፈርቶች እጅግ አድካሚ በመሆናቸው ይህ አሰራር በተለየ ቅባት የሚነሱ ወጣቶች ወደ አገልግሎት አንገታቸውን ማስገባት እንዳይችሉ አድርጓል፣ በዚህም ከእግዚአብሄር ፀጋ ጋር መተላለፍ እየተፈጠረ ይገኛል፣
- በስራና በተለያዩ ምክንያቶች ከሌላ ስፍራ የሚመጡትን አማኞች ለመቀበል "ክሊራንስ አምጣ፣ በኛ ቤተክርስቲያን መርህ ተምረህ ካልተጠመቅክ …" የሚሉ መስፈርቶችን ማስቀመጣቸው ብዙዎችን በቤተክርስቲያን እንዳይጠለሉ አድርጓል፣
- አዲስ ቤተክርስቲያን ለመትከል የተቀመጠው መስፈርትና ቅድመ ሁኔታ የህዝብ መብዛትና የከተማ መስፋፋትን ግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ በርቀት ያሉ ምዕመኖቻቸው አማካይ ቦታ ቤተክርስቲያን ወደሚከፍቱ ባለራዕይ አብያተክርስቲያናት እንዲኮበልሉ አድርጓል፣

እነዚህ ችግሮች ደግሞ አብያተ ክርስቲያናቱ መስራት የሚቻላቸውን ያህል እንዳይሰሩና ከባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ሌላ የግጭት ግንባር እንዲፈጥሩ አድርጓል፡፡

- <u>ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት</u>

ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት በካፒታሊዝሙ "ገበያ መር" እስትራቴጂ፣ ቤተክርስቲያን ያልተከፈተበት አማካይ ቦታ በመመልከት ቤተክርስቲያን መከፈታቸው፣ በቀላል መስፈርቶች ሰዎችን ወደ አገልጋይነት ማምጣታቸው፣ ከሌላ ስፍራ የሚመጡ ምዕመናንን "ክሊራንስ፣ እኛ አስተምረንህ ካላጠመቅንህ …" ሳይሉ መቀበላቸው፣ አገልግሎታቸውም የህዝቡን የልብ ትርታ ብቻ በመመልከት በትንቢትና ፈውስ ላይ ብቻ ማተኮራቸውና ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያናቸው እንዲመጡ ሰፊ ራስን የማስተዋወቅ ስራ መስራታቸው፣ ወንጌል በሳተላይት ዲሽ እንዲሰራጭ ማድረጋቸው … ብዙ የተዳከሙና ግራ የተጋቡ አማኞችን በማነሳሳት ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመለሱ ያደረገ ሲሆን አሰራራቸውም ለአጠቃላይ የፕሮስታንት ማህበረሰቡ ትልቅ መነሳሳት ፈጥሮ ይገኛል፤ በተለይ ደግሞ

ጀማሪ መስራቾች ቤተክርስቲያናቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉት ትጋት ለሌሎችም ክርስቲያኖች ትልቅ መነሳሳትን ፈጥሯል፡፡

ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያለውን ችግር ስንመለከት፣ ከመነሻው "ባለራዕይ" ከሚለው ስያሜ ይነሳል፣ ስያሜው እንደ መፅሀፍ ቅዱሱም እንደ አመራር ሳይንሱም የተሳሳተ ስያሜ ነው፣

መፅሀፍ ቅዱሱ፣

> ነሳሙ.9፡9 "<u>ዛሬ ነብይ የሚባለው ቀድሞ ባለራእይ ይባል ነበርና</u> አስቀድሞ በእስራኤል ዘንድ ሰው እግዚአብሄርን ለመጠየቅ ሲሄድ፣ ኑ ወደ ባለራእይ እንሂድ ይል ነበር፡፡"

በዚህም በክርስትናው ባለራዕይ ማለት ከፈጣሪ የሚወርድለትን ራዕይ የሚመለከት ነብይ ማለት እንጂ ቤተክርስቲያን መስራች ማለት አይደለም፡፡

በአመራር ሳይንሱም ብንሄድ ባለራዕይ የሚሆነው ባለቤት ነው፣ የቤተክርስቲያን ባለራዕይ የቤተክርስቲያን ባለቤት የሆነው እግዚአብሄር እንጂ ሰው አይደለም፣ ያስቀመጠውም ራዕይ(vision) "የሰው ልጅ ሁሉ እንዲድን ወንጌል ለዓለም ማድረስ" የሚል ሲሆን እያንዳንዱ አገልጋይ የሚገኘው በዚህ ራዕይ ስር በተቀመጠው በታላቁ ተልዕኮ(Mission) ውስጥ ሚሽነሪ በመሆን እንጂ በራዕይ ባለቤትነት አይደለም፣ ማቴ.28፡19-20 ላይ "ሂዱና" የሚለው ቃልም የዚሁ እውነታ አመላካች ቃል ነው፣ ዛሬ እያንዳንዱ አገልጋይ እየሰራ ያለው ስራ የተጀመረው ስራ ላይ የመጨመር ስራ እንጂ አዲስ የሚጀምረው ስራ አይደለም፣ ይህ ትውልድ ይቅርና የፕሮቴስታንት ተሀድሶን እንኳን ወደ ሀገራችን ያስገቡት ሚሽነሪዎች ናቸው፡፡

አንዳንዶቹ ከዚህ ሀሳብ ጋር ላለመጋጨት በማለት የቃሉን አተረጓጎም ለወጥ በማድረግ "ባለራዕይ" የሚለውን ቃል "ይህንን ቤተክርስቲያን በዚህ ቦታ እንድተክል ራዕይ ተሰጥቶኝ ነው" በሚለው ሲተረጉሙ ይሰማል ነገር ግን አብዛኞቹ ባለራዕዮቹ ቤተክርስቲያናቸውን የሚመሠርቱት በአካባቢው ሌላ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በስራ ላይ እያለች መሆኑ እያታወቀ፣ የሚከፍቱበት ቦታም በገበያ መር እስትራቴጂ ብዙ አማኞችን ማግኘት በሚችሉበት በትላልቅ ከተሞች አማካይ ቦታዎች እየተፈለገ መሆኑና "በዚህ ቦታ እንድከፍት ራዕይ ተሰጠኝ" የሚለውን አልፈው በሌሎች ቦታዎችም

ቅርንጫፎችንም እየከፈቱ የሚሄዱበትን እውነታ ስንመለከት ለወጥ የተደረገው አተረጓጎም አሳማኝ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

ነባራዊውን እውነታ ስንመለከት የአብዛኞቹ ምስረታ ምክንያት ከእግዚአብሄር በመጣ ራዕይ ሳይሆን፣

- አገልጋዮች በተለያየ ምክንያት ከክፍለ ሀገር ወደ ትላልቅ ከተሞች ሲመጡ በአካባቢው ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ማገልገል አለመቻላቸው፣
- አገልጋዮች በላያቸው ላይ ትልቅ ፀጋ ሲገለጥ በሽማግሌዎች ስር ከመመራት "የራሴን በራሴ" ከሚል ስሜት በመነሳት፣
- ሰውን በስጋ አይን በሚመዝኑት በእነኤልያብ የተገፉ ዳዊቶች(1ሳሙ.17፡28)፣
- አገልጋዮች በነበሩበት ቤተክርስቲያን የሚያገኙት የኢኮኖሚ ጥቅማ ጥቅም አነስተኛ በመሆኑ ኢኮኖሚያቸውን ለማሻሻል፣
- ከላይ የተመለከቱት መስራቾች በቀላሉ ቤተክርስቲያን አቁመው "ፅዳ" ያለ ህይወት መጀመራቸውን በመመልከት "ማን ከማን ያንሳል" በሚል ስሜት በሚነሱ አገልጋዮች ነው፣

ይህም እውነታ "የእግዚአብሄር ራዕይ" ከሚባለው በላይ "የግለሰብ ራዕይ" የሚለውን እውነታ ያጎላል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናትን አሰራር ስንመለከት ደግሞ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የቤተክርስቲያን ዋናው ተልዕኮ "ታላቁ ተልዕኮ"(ማቴ.28፡19-20) አካል አለመሆናቸውን እንመለከታለን፣ ይህም፡-

- አብያተ ክርስቲያናቱ ያለባቸውን ከፍተኛ ወጪ ለመሸፈን በሚከተሉት "ገብያ መር እስትራቴጂ" ቤተክርስቲያን የሚከፍቱት ሰፊ ገብያ(ብዙ አማኝ) ማግኘት በሚችሉበት ትልልቅ ከተማ አማካይ ቦታዎች ላይ በመሆኑ አብያተ ክርስቲያናቱ በደሃው ሰፈር፣ በሀገሪቱ ገጠራማ ክፍልና በአዳዲስ የወንጌል ግምባሮች አለመገኘታቸው፣ አብያተ ክርስቲያናቱ ወንጌል የማስፋት ስራ አካል አለመሆናቸውን ያመለክታል፡፡

- አብያተ ክርስቲያናቱ የተመሠረቱት በአንድ ሰው ራዕይ ሆኖ የቤተክርስቲያኗም ባለቤት ይህ ግለሰብ መሆኑ፣

  - በመስራቹ ስር የሚሰሩት አገልጋዮች ከተከታይነት ይልቅ በግለሰብ ተቀጣሪነት መንፈስ እንዲሰሩና እነሱም የሰውን ከመከተል የራሳቸውን ቤተክርስቲያን የሚተክሉበትን መንገድ እንዲከተሉ ያደርጋቸዋል፣ ይህ እውነታ ደግሞ ባለራዕዩ ተከታይ ማፍራት እንዳይችል ያደርገዋል፣ ተከታይ ማፍራት ያልቻለ ባለራዕይ ደግሞ ራዕዩን ማሳካት አይችልም፡፡

  - ቤተክርስቲያንን የግለሰብ ድርጅት በማድረግ ቤተክርስቲያን እንደ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከመቆም ይልቅ ህልውናዋ በአንድ ሰው ላይ እንዲመሠረት አድርጓል፣ በዚህም ባለራዕይ ያለና የሌለ ቀን የቤተክርስቲያኗ ገፅታ የተለያየ ነው፤ ባለራዕዩ ውጭ ሀገር ቢሄድ፣ ቢታመም፣ ከክርስትናው ቢወድቅ፣ ቢሞት … ቤተክርስቲያኗም አብራ እንደባለራዕዩ ትሆናለች፡፡

  እነዚህ እውነታዎች ደግሞ መፅሀፍ ቅዱሱ የሚያወግዘው "የእከሌ ቤተክርስቲያን"(1ቆሮ1፡11-13) አሰራር ማሳያ ነው፡፡

- አብያተ ክርስቲያናቱ በሚከተሉት "ገበያ መር" እስትራቴጂ በፈውስና ትንቢት ላይ ብቻ ማተኮራቸው ምዕመናኖቻቸው ፅኑ ክርስቲያናዊ መሠረት እንዳይኖራቸው አድርጓል፣ ይህም ደግሞ፣

  - ምዕመኑ ከእግዚአብሄር ጋር ያለውን ግንኙነት በ"ሰጥቶ መቀበል" መርህ እንዲመሠረት፣ በዚህም ምዕመኑ የተነገረው "ትንቢት" ሆነ "ፈውስ" ሳይፈፀም ሲቀር ወይንም ሲዘገይ ዋናውን ነገር ይህም "የነፍስን መዳንና የእግዚአብሄር ልጅነትን" እንደዋዛ ጥለው ሲወጡ ይታያል፡፡

  - ወንጌልን በዕውቀት መመስከር የማይችሉ ክርስቲያኖችን እየፈጠረ ይገኛል(1ጴጥ.3፡15)፣

እነዚህም እውነታዎች ደግሞ ሆሴ.4፡6 "ህዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል …" የሚለው ቃል ማሳያ ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናቱ ወንጌልን ወደ አዲስ ስፍራ የማስፋት ስራ የሚሰሩ አለመሆናቸው፣ የሚሰሩትንም ስራ ከመስራቹ ሁኔታ በላይ አስፍተን የሀገራዊው ሆነ የአለማቀፋዊው የወንጌል ስራ አካል ማድረግ የማይቻል መሆኑና ባሉበት ሁኔታም ከነሱ ጋር ያሉት ምዕመናኖች ፅኑ ክርስቲያናዊ መሠረት የሌላቸው መሆኑን ስንመለከት፤ የባለራዕይ ቤተክርስቲያናት የ"ታላቁ ተልዕኮ" አካል አለመሆናቸውንና በዚህም የነዚህ የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አደረጃጀት መፅሀፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በላይ ደግሞ ትልቅ ችግር የሆነው እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ድጋፍ የሚያደርግላቸው የበላይ መዋቅር የሌላቸው መሆኑ፣ በሚመርጡትም ማዕከላዊ ቦታ ምክንያት ባለባቸው ከፍተኛ የቤት ኪራይ፣ ቤተክርስቲያኗ አዲስ እንደመሆኗ ለቤተክርስቲያኗ ዕቃ ግዢ የሚያስፈልገው ከፍተኛ ወጪ፣ ለአገልጋዮች ደሞዝ፣ ራስን ለማስተዋወቅ፣ በኮንፍራንሱ ለሚጋበዙ ትልልቅ አገልጋዮች የሚከፈለው ትልቅ ገንዘብ፣ ለትልልቅ እስፒከሮች፣ ኪቦርዶችና ሳዎንድ ሲስተሞች ግዥ/ኪራይ የሚወጣው ወጪ፣ ከዚህም ባለፈ ከሌሎች ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት እኩል ለመሆን ቻናል ለመክፈት ወይ የአየር ሰአት ለመግዛት የሚያደርገው ሩጫ፣ ቻናል የከፈቱትም ይህን ብዙ ሚሊየን ብር የሚያስወጣን ወጪ ለመሸፈን የሚያደርጉት ሩጫ፣ ለችግር ጊዜ ዋስትና እንዲሆን ዛሬ ላይ ትልቅ ካፒታል ለማከማቸት የሚደረገው ሩጫ፣ ላልተሰቀለው ስጋዊ ማንነት ምቾት የሚደረገው የሀብት ማካበት ሩጫ … አብያተ ክርስቲያናቱን ከፍተኛ የገንዘብ ሀሳብ ውስጥ ከቷቸዋል፡፡

በዚህም አብዛኞቹ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ወጪያቸውንና ፍላጎታቸውን ለመሸፈን መፅሀፍ ቅዱሱ ከሚያዘው የገቢ ምንጮች በመውጣት ያላቸውን ፀጋ በመሸቀጥ ከታች የምንመለከታቸው ሀጢያት የሆኑ የኪራይ ሰብሳቢነትና የዝርፍያ የገቢ ማሰባሰብያ ስራዎችን ሲሰሩ እንመለከታለን፣ ይህም፣

- የተፀለየበት መፅሀፍ ቅዱስ፣ ጨው፣ ዘይት፣ ውሃ፣ ብር፣ እስክሪብቶ፣ ቲሸርት፣ ኮፍያ … ንግድ፣
- ገስት ሀዎስ፣ በልዩ ክፍያ "እጅ ጭኖ መፀለይ"፣ ልዩ የባለሀብቶች ፕሮግራም፣ የኮንትራክተሮች ፕሮግራም፣ የዲያስፖራ ፕሮግራም፣

የነጋዴዎች ፕሮግራም ... የተለያዩ ገንዘብ መሰብሰብያ ገብያ መር ፕሮግራሞች፣

- “የፍቅር ስጦታ” (ይህ የገቢ አይነት ሰው ብር በፖስታ በመያዝ መድረክ ላይ በመውጣት ተፀልዮለት የሚሰጠው አይነት ስጦታ ነው፣ ያልሰጠ አይፀለይለትም፣ በጉባኤውም አይባረክም)፣

  አሰራትና መባ መፅሀፍ ቅዱሳዊ በመሆናቸው ለቤተክርስቲያን ሲሰጡ የራሳቸው አሰጣጥ ስነስርአት አላቸው፣ ይህ አዲስ የተፈጠረው አሰራር ግን መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም ይባሱኑ አሰራሩ ማቴ.6፡2-6 ላይ የተነገረውን ማስጠንቀቂያ ችላ ያለ በመሆኑ የሰጪው ስጦታ በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡

- ስሙ የማይታወቀው የስጦታ አይነት፣ ይህም ነብዩ ለዚያ ሰው ለይቶ ትንቢት እንዲያመጣለት በነብዩ እጅ፣ ኪስ ወይንም በጉባኤው ፊት ለፊት በተዘጋጀ ቦታ ላይ ተነስቶ ገንዘብ የማስቀመጥ አሰራሮች ...

እነዚህ አሰራሮች በአሰራር ደረጃ “በነፃ ያገኛችሁትን በነፃ ስጡ” ከሚለው ቃል በተቃራኒ ያሉ አሰራሮች ሲሆኑ አገልጋዮቹም እንደ ጆቶኒ ሳንቲም ካልገባላቸው በቀር ማንንም ከፈጣሪ ፀጋ ጋር የማያገናኙ እየሆኑ ያለበትና አብያተ ክርስቲያናቱም ህጋዊ የዝርፊያ ማዕከላት እየሆኑ የሚገኙበትን እውነታ እየተመለከትን እንገኛለን፡፡

ይህ በቤተክርስቲያን ስም የግል የዝርፊያ ማዕከላትን መክፈት በሁሉም ሀገራት እየተስፋፋ ያለ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ፈተና ነው፣ [149] “አሜሪካዊው ኢኮኖሚስት ቶማስ ሼይቨሊ ባደረጉት ጥናት፣ ቤተክርስቲያንና አጋር አገልግሎቶች (ሚኒስተሪ) መክፈት፣ “አዋጭ የቢዝነስ ዘርፍ” እየሆነ እንደመጣ ተናግረዋል፡፡” የጀርመን ድመፅ ራዲዮ እንግሊዘኛ ፕሮግራም በ15/04/2018 በሰራው ዘገባ [150]“ጋና ውስጥ የቸርች ቢዝነስ እያደገ ያለና የብዙ አገልጋዮችን ሻንጣዎቻቸውን በገንዘብ እየሞላ ያለ አዋጭ ቢዝነስ ሆኗል” ይላል፣ [151]ኮንጎ ውስጥ አንድ ሰውን ከአጋንንት ነፃ ለማድረግ ከ24-27

---

[149]**ማቴቴስ መፅሄት**, ግንቦት 2003, ገፅ 10

[150] http://p.dw.com/p/2w3TK

[151]ፀጋአብ በቀለ(2009)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ**፣ ቅፅ 2፣ ገፅ. 273

ፓዎንድ የሚያስከፍሉ አገልጋዮች እንዳሉ፣ በሀገራችንም [152]ቤተክርስቲያን መከፈት ቀረጥ የማይከፈልበት በአቋራጭ የሚያበለፅግ ንግድ እየሆነ እንደመጣ እየተመለከትን እንገኛለን፡፡

ኪራይ ሰብሳቢነቱን ቀደም ብለው የጀመሩቱ ፀጋቸውን በመቸርቸር ግዙፍ ካፒታሊስቶች ሲሆኑና በካፒታላቸውም የሚታመኑ በቤተክርስቲያን የተቀመጡ ጣዖታት እየሆኑ ይገኛሉ፣ በዚህም አገልጋዮቹ በሀገራቸው የቢሊየነሮች ዝርዝር ውስጥ የገቡ፤ የግዙፍ ኢንቨስትመቶች ባለቤቶች፤ ግዙፍ የንግድ መርከቦች ያሏቸው፣ አማራጭ የግል ፕሌን ያላቸው፤ ከፊት ለፊታቸው ምንጣፍ እየተዘረጋላቸውና አበባ እየተጎዘጎዘላቸው የሚሄዱ፤ በማርያም፣ ኢየሱስ ... ስም የስዕል ጣዖታትን እንደሚጠቀሙት ክርስቲያኖች፣ ሰዎች የነሱንም ገናናነት እንዲመሰክሩ ፎቶግራፋቸውን በልብስ፣ በኮፍያ ... አሳትመው እንዲለብሱና በመኪኖቻቸው እንዲለጥፉ የሚያደርጉ፤ ሰው ሲያያቸው የሚንበረከክላቸው፣ ጫማቸው ላይ የሚሰግድበትና በእንብርክክ እየሄደ ዕቃ የሚያቀብላቸው፤ “ለባለቤቴና ለልጄ አልተነሳችሁም” ብሎ ሰዎችን ከቤተክርስቲያን የሚያባርሩ፤ ሰው መሬት ላይ እየተነጠፈላቸው ላዩ ላይ የሚሄዱ፤ እንደ እግዚአብሄር “ባንተ ቸርነት፣ ባንተ ጥበቃ ...” የሚባልላቸው በአጠቃላይ በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን የተቀመጡ ዘራፊዎችና ጣዖታት ሆነዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥም በኪራይ ሰብሳቢነቱ መንገድ እየሄዱ ያሉት ዛሬ ላይ መልቲ ሚሊየነሮች ናቸው፣ በቦዲ ጋርድ እንጂ አይንቀሳቀሱም፣ በዚህ ዳቦ በልቶ ባልጠገበ ህዝብ መካከል የሚይዙት “አለ” የተባለ መኪና ነው፣ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ኢንቨስትመንት እየሞካከሩ የሚገኙም አሉ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንኳን በ13/10/2011 ባስተላለፉት መልዕክት መሪዎቹን “... የሀብትና የስልጣን እሽቅድምድም እንኳንስ ለሰማይ ለምድር አይጠቅማችሁም ... የስልጣን ጥማታችሁ ከኛ ከፖለቲከኞቹ የባሰ እየሆነ ነው... እንዴት ያለ ርህራሄ የአውቶቢስ የሚከፍለው ከሌለው ምዕመን ሰብስባችሁ መኪና ትገዛላችሁ ... የሚያስፈልጋችሁ መነጋገር ሳይሆን ንስሀ

[152] ፀጋአብ በቀለ(2009)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ**፣ ቅፅ 2፣ ገፅ. 224

ነው ...” ብለዋቸው ነበረ ነገር ግን ሰዎቹ የሚመሩት [153]በብልፅግና ወንጌል መርህ ስለሆነ ማንም በዚህ በኢየሱስና በሐዋርያቱ መንገድ “መቸገር” አይፈልግም፡፡

በዚህም ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰው ለነሱ ቢዝነስና ክብር እስኪመስል እየደረሰ ይገኛል፣ አላወቁም እንጂ፣

> ማቴ.7፡22-23 “በዚያን ቀን ብዙዎች፣ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፣ የዚያን ጊዜም፣ ከቶ አላወቅኋችሁም፣ እናንተ አመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባችኋለሁ፡፡”

የሚለው ቃል የተነገረው <u>ላላመኑት ወይ ለተራው ክርስቲያን አይደለም</u> ነገር ግን በተለየ ቅባት ስለተነሱትና አጋንንት ስለሚያወጡ፣ ተአምራት ስለሚያረደርጉት ነገር ግን ከነሱ የማይጠበቅ አኗኗር ስለሚኖሩት ዋናዎቹ አገልጋዮች እንጂ፡፡

ከታሪክ እንደምንማረው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ምስረታ የእግዚአብሄር የተሀድሶ ሀሳብ ቢሆንም ሰዎች ግን በዚህ የተሀድሶ መስመር

---

[153] “የብልፅግና ወንጌል” ማለት ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ የተፈጠረ አዲስ አስተምህሮ ነው፣ አስተምህሮውም የሚያተኩረው አገልጋዮች እንዴት የአዲስ ኪዳኑን ፀጋ ተጠቅመው ብሉይ ኪዳናዊ “በረከትን” ማጋበስ እንደሚችሉ የሚያስተምር ወደ ኋላ የዞረ አስተምህሮ ነው፡፡

ብሉይ ኪዳን የወረደው አምልኮዋ ቁሳዊ(ታቦት፣ ቤተመቅደስ ...)፣ በረከቷ ቁሳዊ፣ ጠላቶቿ ስጋዊያን ለሆኑት፣ 12ቱ የያዕቆብ ዘሮች ለመሠረቷት ስጋዊዋ እስራኤል ነው፤ አዲስ ኪዳን ደግሞ የወረደው አምልኮዋቸው፣ በረከታቸው፣ ጠላቶቻቸው ... መንፈሳዊ ለሆኑት በ12 ሐዋርያት መሠረት ላይ ለተመሠረቱት መንፈሳዊ እስራኤላውያን ነው፡፡

ይሁን እንጂ የብልጽግና ወንጌል አስተምህሮ በአዲስ ኪዳኑ መንፈሳዊ ፀጋ ምድራዊ ሀብትን ለማካበት የሚሰራ፣ በሁለቱ ኪዳኖች መካከል የተወዛገበ አስተምህሮ ነው፡፡ በአስተምህሮውም ብልፅግና የሚመጣው ጠንክሮ በመስራት ሳይሆን ከምዕመናኑ አስራት፣ መባ ... በመሰብሰብ፣ “ስጡ ይሰጣችኋል” የሚለው ቃል “ስጡኝ ይሰጣችኋል” በማድረግ ነው፣ ውጤቱም በኢየሱስና በሐዋርያቱ ህይወት ያልተመለከትነው ይባሱኑም መፅሀፉ የሚያወግዘው አይነት ሀብታምነት ነው፡፡

በዚህም አስተምህሮቱ በሁለቱ ኪዳናት መካከል የተቸገረ፣ የፈጣሪን ቃል አጣሞ ለግል ጥቅም ያዋለና ውጤቱም ሀጢያት የሆነ አስተምህሮ ነው፡፡

ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት የሆናቸው በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረው የእግዚአብሄርን ነገር የመሸቀጥ ችግር ነበረ “መንግስተ ሰማያት መግቢያ ትኬት” የሚለው የኪራይ ሰብሳቢነት ስራ፣ በአሁኑ ጊዜ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ለሰይጣን ሴራ ባለመመቸቷ ሰይጣን በፕሮቴስታንት በኩል የተነሳውን ተሀድሶ ወደ ነበረበት ቦታ ለመመለስ እየሰራ ያለው ቤተክርስቲያኗ ወደ ኪራይ ሰብሳቢነት ይህም “የእግዚአብሄርን ነገሮች መሸቀጥ” እንድትመለስ በማድረግ ነው፡፡

በዚህም በኢትዮጵያም ይሁን በዓለማቀፍ ደረጃ እየተመለከትን የምንገኘው ኪራይ ሰብሳቢነት በቤተክርስቲያኒቷ ላይ የተነሳ አደገኛ አጋንንታዊ ሴራ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፣ ሰይጣን ነፃነት ነፍጓት ማፍረስ ያቃተውን ቤተክርስቲያን አሁን ደግሞ ከአቅሟ በላይ ነፃነት ሰጥቷት በልቅነት ሊጥላት እየሰራ ይገኛል፡፡

ከዚህ ኪራይ ሰብሳቢነቱ ችግር በላይ ደግሞ አንዳንድ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት የፕሮቴስታንት ማህበረሰቡን አንገት የሚያስደፋ የወንበዴ ስራዎችንም ሲሰሩ ይታያሉ፣ ከነዚህ ውስጥ የስም አጥፊዎችን ወሬ ትተን ከታማኝ ምንጮች የሚሰሙትን ጥቂቶቹን ብንመለከት፣ አገልጋዩ እንደሌለ እየታወቀ ሰዎችን ገስት ሀዎስ አስገብቶ ብዙ ሺ ብሮች ማስከፈልና አገልጋይም እያለ ሰዎች ብራቸውን ከፍለው ሳይፀለይላቸው መቅረት፣ አዳዲስ አማኞችን “እንፀልይላችኋለን” በማለት ብዙ ሺ ብሮች መቀበል፣ ከሰዎች ብር ተበድሮ መካድ፣ በቻናል ላይ ለሚለቀቅ ማስታወቅያ ክፍያ ተቀብሎ መካድ፣ “እፀልይበታለሁ” ብሎ የአትሌቶችን ሽልማት ተቀብሎ መካድ፣ የመድፈር ወንጀሎች፣ ተከፍሏቸው በሚመጡ ሰዎች የውሸት የፈውስና የትንቢት ድራማ መስራት፣ የሰዎችን መረጃ ከሌላ ቦታ ለሚመጣ አገልጋይ ቀድሞ በመንገር ይህንን መረጃ ትንቢት አስመስሎ እንዲነገር ማድረግ፣ የውሸት “ጌታን መቀበል” ወከባዎች፣ መፅሀፍ ቅዱሳዊውን አሰራር ባልተከተለ መንገድ በፈለጉት ሹመት “ፓስተር፣ ነብይ፣ ሐዋርያ …” እያሉ መሿሿም፣ በተለያየ መንፈስ(ግብረሰዶም፣ ዮጋ …) ለሚሰሩ ከውጪ ሀገር ለሚመጡ አገልጋዮች ፍቃድን ማከራየት፣ ከዚህ ባለፈም በቤተክርስቲያናቸው አርማ ውስጥ 666 በሚስጥር የተቀመጠባቸው፣ በአጋንንታዊው ሀይል የሚሰሩ፣ አስቂኝና አሳፋሪ ስሞችና ማስታወቂያዎች በመጠቀም በማህበራዊ ሚዲያዎችና በተለያዩ

መድረኮች ሀይማኖቱን ማላገጫ ያስደረጉ ... ብዙ ጉዶችን እየተመለከትን እንገኛለን፣ ነገሮች በዚህ ከቀጠሉም ከዚህ የባሱ ብዙ ጉዶችን እንሰማለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት አንድ ግለሰብ እንደፈለገው የሚያሽከረክረው የባለራዕይ ቤተክርስቲያን አደረጃጀት የታላቁ ተልዕኮ አካል መሆን የማይችል፣ አደረጃጀቱ በሚፈጥረው ክፍተትም ቤተክርስቲያንን የዝርፊያ፣ የወንበዴ ዋሻ፣ የሰይጣን መገልገያ፣ የፕሮቴስታንቱ ውርደት የሚያደርግና በአጠቃላይ ቤተክርስቲያንን ወደ ውድቀትና "የተከፋፈለች መንግስት ትፈርሳለች" ቃል እየገፋ ያለ ችግር ነው፤ በዚህም ይህ ችግር በጊዜ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል፣ ይህ ደግሞ መከናወን ያለበት ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ ሳይወጡ በተለይ ብቅ እያሉ ያሉቱ ኢ-ፕሮቴስታንታዊ አስተምህሮዎች በክፍፍሉ መካከል ገብተው ክፍፍሉን መልክ ሳያሲዙት በፊት መሆን አለበት፡፡

በዚህም ቤተክርስቲያንን ለኪራይ ሰብሳቢነትና ለልቅነት እያጋለጠ ያለውን በአንድ ሰው የሚሽከረከረው የባለ ራዕይ አደረጃጀት እንዲሁም እንደ ሶሻሊዝም አሳሪ አሰራርን በመከተል የወንጌሉን እንቅስቃሴ ያፈነውን የወንጌላውያኑን አሰራር በመቀየር እንደ ቅይጥ ኢኮኖሚው(Mixed Economy) ለዚህ ጊዜ ተስማሚ የሆነ ቅይጥ አደረጃጀት መከተሉ የግድ በሆነበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት አንድ ማድረግ ጉዳቱ የሰፋ ነው፣ ለዚህም ሁለት የመፅሀፍ ቅዱስ መርሆችን ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው፣ ይህም

- ይስሐቅ አማራጭ የውሀ ምንጭ ጉድጓድ በመቆፈሩ ምክንያት ጠላቶቹ አንዱን ሱደፍኑበት እሱ ሌላውን ሲጠቀም ነበረ፣ በዚህም አንዷን ቤተክርስቲያን ዘረኝነት፣ ቢሮክራሲ ... ቢደፍናት ሌላው አልፎ ይሰራል፣ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ለሰይጣን አፈና እንዳትመች ያደረጋትም መብዛትዋ ነው፣
- በነገ.19፡16-17 እንደተመለከተው "ከአዛሄልም ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ ኢዩ ይገድለዋል ከኢዩ ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ ኤልሳዕ ይገድለዋል" መንፈስ አብያተ ክርስቲያናቱ በተለያየ ዘዴ የሚሰሩት የወንጌል ማስፋፋት ስራ ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ያደርጋል፣

ከነዚህ መፅሀፍ ቅዱሳዊ መርሆች በመነሳት አንዱ ቤተክርስቲያን ለብቻው የሚቆምበት አሰራርን መደገፍ ባይቻልም፣ ከላይ እንደተመለከትነው ብዙ ችግር ያለበትና ብዙ ክፍተት የሚፈጥረውን በአንድ ሰው የሚሽከረከረውን የባለራዕይ ቤተክርስቲያን አሰራርን ማስቀረት ግን ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ችግር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

በዚህም ሁሉም ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ባሉበት ቦታና ሁኔታ ወደ ወጡበት እናት ቤተክርስቲያን ወይንም ወደ ፈለጉት የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን(መካነየሱስን ጨምሮ) እንዲመለሱ እንደዚሁም ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናቱም በውስጣቸው ያለውን ችግር በማስተካከል (ከታች ተመልክቷል) እነዚህን ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናትን ምንም ጉዳት በማይደርስባቸው ሁኔታ መቀበል በሚችሉበት መንገድ ሊዋሀዱ ይገባል፡፡

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ማስተካከል የሚገባቸው ነገር፣

- የየትኛውም ቤተክርስቲያን፣ ህብረት፣ አጥብያ … መሪዎች በባለቤትነት ስሜት በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ ከአሳሪ ደንብና መመርያ ነፃ ማድረግ፣
- አዲስ ቤተክርስቲያን፣ ህብረት፣ አጥብያ … ለመክፈት የተቀመጡትን መስፈርቶችና ቅድመ ሁኔታዎችን ቀለል ማድረግ፣ የከተሞች መስፋፋትን ግምት ውስጥ በማስገባት ቤተክርስቲያንን ተደራሽ ማድረግ፣ የትኛውም አማኝ ልቡ በተነሳሳበት ቦታ ላይ ቤተክርስቲያን መትከል ቢፈልግ በቤተክርስቲያኗ አሰራርና ደንብ እንዲሰራ ፍቃድ መስጠት፣ መከታተልና መደገፍ፣
- የእግዚአብሄርን ቅዱስ አሰራር መቀበል፣ ኤልያብ እያለ ዳዊት ሲቀባ ዳዊትን አለመግፋት ቢያንስ እንደ ሳዖል የዳዊትን ቅባት መርምሮ ዳዊትን ወደ አገልግሎት ማሳለፍ፣
- ሰዎችን ወደ ተለያየ አገልግሎት ለማሳደግ የሚከተሉትን ጥብቅ አሰራርም ቀለል ማድረግ፣

- ከሌላ ስፍራ የሚመጡ አማኞች ላይ መስፈርት አለማብዛት፣ የዚያን ሰው ማንነት ማጣራት ካስፈለገ እንኳን በአብያተ ክርስቲያናት ህብረት በኩል ባላቸው የመረጃ ስርአት የሰውየውን ማንነት ማጣራት፣
- በሰፈር የሚቀራረቡ ሰዎች ተሰባስበው በራሳቸው መንገድ አገልጋይ ጠርተው ለሚያደርጉት አምልኮ እውቅናና ድጋፍ መስጠት፣
- አገልጋዮች በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲደግፉ በትርፍ ጊዜያቸውና ፍቃድ እየወሰዱ የፈለጉበት ቦታ ሄደው ማገልገል እንዲችሉ ማመቻቸትና ምዕመኑ ለቤተክርስቲያን የሚያደርገውን ድጋፍና አክብሮት በማቴ.10፡40-42, ማር.9፡41 … መንፈስ ለአገልጋዮችም እንዲያደርግ ማስተማር፣

በዚህም ወንጌላውያኑ ጥብቅ አሰራራቸው በተወሰነ መጠን ለቀቅ በማድረግ ያፈኑትን ወንጌል የሚፈታበትንና ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናቱን የሚያስተናግዱበትን አሰራርና መዋቅር መፍጠር አለባቸው፡፡

እዚህ ጋር አንዳንድ የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አመራሮች ከነበራቸው ስልጣንና ጥቅማ ጥቅም አንፃር ውህደቱ እንዳይሳካ የሚያንገራግሩ ወይ የማይመቹ ውሳኔዎችን የሚያሳልፉ ከሆነ ወይ “እኛ በቅድስና እየሰራን ነው ሌላው ራሱን ያስተካክል” በማለት ለዘራፊዎቹና ለወንበዴዎቹ ሽፋን የሚሰጡ ከሆነ በነሱ ስር ያለው ህዝብ ከላይ የተመለከትናቸውን ችግሮችንና በዚህ የተሀድሶና የአንድነት ጥሪ የሚፈጠረውን የቤተክርስቲያን ቅድስናና አንድነት በማስተዋል፣ እንደ ኢየሱስ በ“የቤትህ ቅናት ይበላኛል”(ዮሐ.2፡17) መንፈስ የአንድነት ጥሪውን በግሉ ስኬታማ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በዚህም እንደ ሶሻሊዝሙና ካፒታሊዝሙ ፅንፍ ለፅንፍ የቆሙትን ሁለቱን አሰራሮች አዋህዶ፣ ዘራፊዎችን፣ ወንበዴዎችን፣ እርኩሶችን … ከቤተክርስቲያን ክልል በማውጣት፣ ሀገሪቱ የተሰጧትን የተስፋ ቃሎችን በቅድስናና በአንድነት እንድትቀበል ማድረግ የሁሉም አማኝ ግዴታ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአንዳንድ ሀገራት ላይ የምንመለከተው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ዝቅጠት በኛ ሀገር ላይ ሊደገም አይገባም፣ ሀገሪቱ ከእግዚአብሄር ጋር ብዙ

ፕሮግራሞች አሏት፣ ከዚህ ቦሀላ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን "ከተከፋፈለች መንግስትነት"፣ ከዘራፊዎች፣ ከወንበዴዎችና ከእርኩሶች ተላቃ በቅድስናና በአንድነት እግዚአብሄርን የምታመልክበት፣ በቁስ በሊና በኩል የተተነበየውን ተሀድሶ የምትቀበልበት፣ እግዚአብሄር ከ3,000 አመታት በፊት በነብዩ ዳዊት በኩል ለሀገሪቱ የተናገረውን "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች"(መዝ.68፡31) ቃል ፍፃሜ የምትቀበልበት፣ ኢትዮጵያ ለእግዚአብሄር የምትሰግድበት(መዝ.72፡9)፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ለእግዚአብሄር ምልጃና ቁርባን የሚያቀርቡበት(ሶፎ.3፡10) ብሎም ህዝቦቿ ለኢየሱስ ዳግም ምፅአት የሚዘጋጁበት ጊዜ ሊደረግ ይገባል፡፡

ፈጣሪ ለኢትዮጵያ ያዘጋጀው የክብር ጊዜ እጅግ ድንቅ እንደሆነ፣ ሌላው ይቅርና እስራኤል እንኳን ኢትዮጵያ ላይ በሚገለጠው የእግዚአብሄር እጅ የምትገረምበት ጊዜ እንደሚመጣ መፅሀፉ ይናገራል፣

> አሞ.9፡7 "የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ እናንተ ለኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሄር ..."

ነገር ግን ሀገሪቱ እነዚህ የተስፋ ቃሎቿ ጋር የምትደርሰው እንደዚህ ተወዛግባ ሳይሆን ወደ "Law and Order" በመመለስ ነው፡፡

## 6.4. በቤተክርስቲያኗ የሚታዩ ድክመቶች

በ6.2 ክፍል እንደቀረበውም ቤተክርስቲያኗ በትክክለኛ መንገድ ላይ በመሆኗ የእግዚአብሄር እጅ በሷ ላይ እየሰራ እንደሆነ ተመልክተናል ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያኗ እየኖረች ያለችው የእግዚአብሄርን እጅ ፈፅሞ አይተው ከማያውቁት ከሌሎቹ ሀይማኖቶች ተመሳስላ ነው፣ ይህ ደግሞ ትልቅ ድክመት ነው፡፡ ይህ ድክመትም እየታየ ያለው በእያንዳንዱ ምዕመን፣ በአብያተ ክርስቲያናቱና በአብያተ ክርስቲያናቱ ህብረት ነው፣ ሁለቱንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 6.4.1. የምዕመናን ድክመት

ምዕመኑ ጋር ያለው ድክመት ጠንካራ ሀይማኖተኛነትን ለሌላ ጊዜ ፕሮግራም ማድረግና የምስክርነት ስራ የሁሉም አማኝ ስራ አድርጎ አለመመልከት ነው፣ ሁለቱንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፣

#### 6.4.1.1. ጠንካራ ሀይማኖተኛነትን ለሌላ ጊዜ ፕሮግራም ማድረግ

አብዛኛው አማኝ በሀይማኖቱ ጠንካራ ሆኖ በሰማያዊው ቤት የክብርን አክሊል መጎናፀፍ እንዳለበት ያምናል ነገር ግን ይህንን የጠንካራ ሀይማኖተኘነት ጊዜ ፕሮግራም የሚያደርገው ለሌላ ጊዜ ነው፡፡ ይህ የህይወት መርህ የተሳሳተ የህይወት መርህ መሆኑን መፅሀፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣ ፈጣሪ ሰዎችን የሚፈልገው አሁን ባሉበት በጉብዝና ወቅት (መክ.12፡1, 2ቆሮ.6፡2 …) እንዲያመልኩትና እንዲያገለግሉት ነው፡፡

ነባራዊው እውነታም ከሰዎች ፕሮግራም ጋር አብሮ የማይሄድበት ጊዜ እንዳለ መገንዘቡም አስፈላጊ ነው፣ ማንም ሰው የሚሞትበትን ቀን አያውቅም “የጌታ ቀን እንደ ሌባ ናት” የሚለው ቃል ሌላው መገለጫም ይኸው እውነታ ነው፣ የምትቀጥለዋ ሰአት ምን እንደሆነች ማንም አያውቃትም፣ በራሳቸው ምድራዊ ፕሮግራም ላይ እያሉ የሞቱ ሰዎች ከመሞታቸው አንድ ቀን በፊት ሊሆን ያለውን ባወቁ ኖሮ ጊዜዋን እንዴት እንደሚያሳልፏት አስቡ ይህንን ባለማወቃቸው ግን ስማቸው ከአንዱ መዝገብ ወደ ሌላው መዛወሩን ሳያውቁ ሄደዋል፣

ኤር.17፡13 "አቤቱ፣ የእስራኤል ተስፋ ሆይ፣ የሚተዉህ ሁሉ ያፍራሉ፤ ከአንተም የሚለዩ የህይወትን ውሀ ምንጭ እግዚአብሄርን ትተዋልና በምድር ላይ ይፃፋሉ፡፡"

ሲኦል የአንድ ቀን፣ የአንድ ሳምንት፣ የአንድ … መዋያ ቦታ አይደለም፣ ሲኦል ቁጥር አያውቅም፣ ለዚህም ነው መፅሀፍ ቅዱሱ ደጋግሞ የሚያስጠነቅቀው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ሰዎች ይህ የህይወት መርሀቸው "የቃየን መስዋዕት" አለመሆኑን መመርመር አለባቸው "ቃየን ከሰብሉ እንዳደረገው እኔም ከጊዜዬ እያደረኩ ይሆን እንዴ?" ብለው ራሳቸውን መመርመር አለባቸው፣ እግዚአብሄር ቃየንን ሲረግመውም "ኮብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ" እንዳለው እነዚህ ሰዎችም ቤተክርስቲያንን ትተው የሚኮበልሉበት አሰራር ደግሞ ተጨማሪ መመሳሰልን ይፈጥራል፣ በዚህም በቃየል መንገድ ከመሄድ ከዛሬ ጀምሮ ከነአቤል ጋር መስዋዕት ማቅረቡ ብልህነት ነው፡፡

ብዙ ቦታዎች ላይ ኢየሱስ ስለ ክርስትና ምንነት ሲያስረዳ የወይን እርሻን በምሳሌነት በመውሰድ ነው(ሉቃ.13፡7, ዮሐ.15፡1-5, ማቴ.21፡33, ማቴ.7፡16 …)፣ ስለ ወይኑ ማሳና ስለ ገበሬውም ሲናገር፣

- ዮሐ.15፡1 "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፣ ገበሬውም አባቴ ነው፡፡"
- ዮሐ.15፡5 "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፣ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ …"፣
- ማቴ.3፡10 "አሁንስ ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል፣ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል፡፡

ከነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የምንረዳው የወይኑ እርሻ ክርስትና ሲሆን ገበሬው ደግሞ እግዚአብሄር ነው፣ ገበሬው የወይኑን ሁኔታ በጥንቃቄ ይከታተላል፣ ራሱን መለወጥ አቅቶት ፍሬ የማያፈራውን ቅርንጫፍ አይሳሳለትም ቆርጦ ይጥለዋል፣ የሚገርመው ደግሞ ገበሬው ምሳሩን(መጥረቢያውን) ያስቀመጠው በዛፉ ስር ነው፡፡

እዚህ ጋር "ይቆርጣል" የሚለው ቃል የተነገረው በመንፈሳዊ ትርጉሙ ነው፣ በዚህም "ይቆረጣል" ሲል "የተሰጠው ዕምነት ከውስጡ ሟምቶ እንዲጠፋ ይደረጋል" ማለት ነው፣ በዚህም እነዚህ ሰዎች በውስጣቸው

የነበረው ጨዉ ሚምቶ ያልቅና ሳያስተውሉት ክርስትና “ውሀ ውሀ” ብሏቸው ክርስትናቸውን ይተዋሉ፣ ገበሬውም ቆርጦ አይተወውም ይህንን ቅርንጫፍ በእሳት ያቃጥለዋል፣ ይህም ሲኦል ነው፡፡

ይህ ቃል የተነገረው ላላመኑት አይደለም ነገር ግን አምነው በክርስትና መበርታት ላልቻሉ ደካማ ክርስቲያኖች እንጂ፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት አንድ ሰው ካመነ በኋላ በክርስትናው ጠንክሮ አለመሄዱ ሀጢያት መሆኑ ይባሱኑም ከክርስትና የሚያስቀርጥና ሲዖል የሚያስገባ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

### 6.4.1.2. የወንጌል ምስክርነት የሁሉም አማኝ ስራ አድርጎ አለመመልከት

አብዛኛው አማኝ የመፅሀፍ ቅዱሱን ቃል ያምናል ነገር ግን “ፍቅር” የተባለው የክርስትና መሠረት ባለመረዳት ሌሎች ሰዎች ከሲኦል እንዲድኑ የምስክርነትን ስራ “ስራዬ ነው” ብሎ ቦታ አይሰጠውም፡፡

ስለ ክርስቶስ አዳኝነት የማይመሰክር ሰው እራሱም የተሰጠው መዳን እንኳን እንደሚወሰድበት መፅሀፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፣ ማቴ.25፡14-30 ላይ ስንመለከት፣ አንድ መክሊቱን ያልነገደባትና ያላተረፈባት ሰው በመጨረሻው ዘመን “ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት … የማይጠቀመውንም ባሪያ በውጪ ወዳለው ጨለማ አውጡት …” እንደሚባል ይናገራል፡፡

በተጨማሪም ማቴ.10፡32 “… በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፡፡” እንደሚለው ስለ ኢየሱስ የሚመሰክር የኢየሱስን ምስክርነት ያገኛል የማይመሰክረው ደግሞ ምስክርነቱን አያገኝም፣ የእሱ ምስክርነት የሌለው ደግሞ መጨረሻው ሲኦል ነው፡፡

በዚህም ምስክርነት፣ አምኖ ከመዳን ቀጥሎ ያለ ስራ ነው፣ ይህንን የምስክርነት ስራ ደግሞ በስፋት የሚሰራ የከበደ ሽልማት ይጠብቀዋል፣ መንግስተ ሰማያት የሚገቡት አማኞችም ሽልማታቸው አንድ አይነት አይደለም፣

1ቆሮ.15፥41-42 “የፀሃይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብት ክብር ሌላ ነው፤ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያያልና፡፡ <u>የሙታን ትንሳኤም እንደዚሁ ነው</u>፡፡”

እዚህ ጋር “ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ኮከብ” የሚለው ቃል የሚናገረው ስለተፈረደባቸው ሰዎች አይደለም፣ በብርሀን አካላት ስለተመሰሉት የፀደቁ ሰዎችና መካከላቸው ስለሚኖረው የማንነት ልዩነት ነው፣ ይህ የማንነት ልዩነት ደግሞ ዘላለማዊ የማንነት ልዩነት ነው፣ ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ ዘላለማዊው ማንነቱ ምን እንደሚመስል የሚገነባው በስጋው ወራት በሚሰራው አገልግሎቱ ነው፡፡

በዚህም እያንዳንዱ ሰው በስጋው በሚያደርገው ትጋት መንፈሳዊ ማንነቱን እየገነባ እንደሆነ በመረዳት በአገልግሎቱ ሊተጋ ይገባዋል፡፡

### 6.4.2. <u>የአብያተ ክርስቲያናቱና የህብረቱ ድክመት</u>

በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትና ህብረታቸው ጋር ያለውን ችግር ስንመለከት ሀገራዊ ስራዎችን ማቀናጀት አለመቻልና ሀይማኖታዊ በዓላትን ወደ መታሰብያነት በመቀየር የኢየሱስን አዳኝነት በጉልህ የሚታይበትን ሁኔታ መፍጠር አለመቻል ናቸው፣ ሁለቱንም ቀጥለን እንመለከታለን፣

#### 6.4.2.1. <u>ቅንጅታዊ ስራ አለመኖር</u>

አብያተ ክርስቲያናቱና ህብረታቸው ካላቸው አቅም፣ ልምድና ጠንካራ አደረጃጀት አንፃር፣ በተናጠልም ይሁን በህብረት ተቀናጅተው መተግበር የሚገባቸው ሀገራዊ ስራዎች አሉ፣ እነዚህም፡-

- መፅሀፍ ቅዱሱን በተለያየ የሀገራችን ቋንቋዎች ተርጉሞ በማሳተም ለሁሉም ማዳረስ በሚቻልበት መንገድ ላይ መፅሀፍ ቅዱስ ከሚያሳትሙ አካላት ጋር መስራት፣ መፅሀፍ ቅዱሱንም በኦዲዮና የተለያዩ አገልግሎት በሚሰጡ አፕሊኬሽኖች ማዘጋጀት፣
- ከጥንት ጀምሮ ሲወጡ የነበሩትን አሁንም በተበታተነ መንገድ እየወጡ ያሉትን መዝሙሮችን፣ ጋዜጦችን፣ መፅሄቶች፣ መፅሃፍት ... በማዕከላዊነት የሚሰባሰቡበትና ህዝቡ የሚያገኝበትን ላይብረሪ፣

ዌብሳይት፣ ሱቆች … ማደራጀት፣ ቀደምት መዝሙሮች ለአሁኑ ትውልድ በሚያመች መልኩ በዘመናዊ መሳሪያ አድሶ ማቅረብ፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ በእግዚአብሄር መንፈስ ምሪት ስለተዘጋጀ እንደማያረጀው ሁሉ እነዚህ ስራዎችም "አርጅተዋል" ተብለው ሊተው አይገባም፣ እንደ አለማዊው ዝም ብለው ስላልመጡ ዝም ተብለው ሊረሱ አይገባም፣ ለሌላውም ትውልድ ሊደርሱ ይገባል፡፡

- በሀገሪቱ ውስጥ ከእድሜ፣ ከአእምሮ፣ ከወላጅ ማጣት፣ ከመበለትነት … ጋር ተያይዞ ያሉትን ችግሮች የሚረዱ ለረጂውም ሆነ ለተረጂውም ተደራሽ ድርጅቶችን ማቋቋም፣ በዚህም አማኙ "ተርቤ አላበላችሁኝም…" በሚለው ቃል ሳይጠየቅ፣ "ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ" ከሚለው ቃል ጋር ሳይጋጭ፣ ከገቢው በቋሚነት የሚቆርጠውን መድቦ መቁረጥ የሚችልበትን፣ ችግረኞችም ከነችግራቸው በአደባባይ ሳይበተኑ በተለያየ መንገድ ይህም፣ በፀሎት፣ በህክምናና በሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች መረዳት የሚችሉበትን መንገድ በማመቻቸት የረጂውንም፣ የተረጂውንም ሆነ የሀገርን ጥቅም ያማከሉ አሰራሮችን መዘርጋት፣
- አብያተ ክርስቲያናትን እንዲሁም ምዕመኑን እርስ በርስ የሚያገናኝና መረጃ የሚሰጥ ማዕከላዊ የሆነ የቴሌቪዥን፣ የዌብሳይት፣ የማህበራዊ ሚዲያ እንዲሁም የጂ.አይ.ኤስ. የመረጃ ስርአት ማደራጀት፣

በዚህም አብያተ ክርስቲያናቱና ህብረቱ ምንም እንኳን በተለያየ አደረጃጀት የተደራጁ ቢሆንም አላማቸው አንድ እንደመሆኑ መጠን እነዚህን አሰራሮች ተጠቅመው አማኙን፣ ራሳቸውምንም ሆነ ሌላውን ማህበረሰብ እርስ በርስ በማስተሳሰር የተቀናጀ ማዕከላዊ አሰራርን ማስፈን አለባቸው፡፡

### 6.4.2.2. በዓልን ወደ መታሰቢያነት መቀየር አለመቻል

አዲሱ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ሲተካ ከተተካኩት ውስጥ አንደኛው "በአል" ነው፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን በዓል ቀን የነበረበት አሰራር በአዲሱ ኪዳን በአል ኢየሱስ ሆነ(ቆላ.2፡16-17)፣ ልክ የቀን ሰንበት በክርስቶስ ሰንበትነት(ዕረፍትነት) እንደተተካው፡፡

ይሁን እንጂ ሰዎች በዓል ብለው የለዩትና በካሌንደር ስራ የሚዘጋበት ቀን በመኖሩ እነዚህን ቀናት ምክንያት በማድረግ ከቀናቱ ጋር ተያይዘው ያሉትን ታሪኮች ለአዲስ ኪዳናዊ ስራ ማዋሉ አስፈላጊ ነው፣ በዚህ በተለምዶ "በዓል" ተብለው በተሰየሙት ቀናት ከመብላት፣ መጠጣቱ፣ መልበሱ፣ መገባበዙ … በላይ ቀኑን ሰበብ አድሮጎ በቀኑ የተፈፀመውን የኢየሱስ አዳኝነት ስራ ገላጭ በሆነ መልክ ለሰዎች የሚመሰከርበት፣ እግዚአብሄር የሚከብርበት፣ የፕሮቴስታንት አንድነት የሚንፀባረቅበት፣ ደከም ያሉ አማኞችም ራሳቸውን የሚያዩበት … ቀን እንዲሆን በማድረግ የበዓል ቀናቱን በአዲስ ኪዳናዊ መንገድ መቅረፅ(Shape) ማድረግ አስፈላጊ ነው፣ በዚህም፡-

1. <u>ገና</u>

ገና ኢየሱስ የተወለደበት ቀን በመሆኑ ኢየሱስ በስጋ የመጣው ለምን እንደሆነ በሚያስረዳ መልኩ፣ ኢየሱስ የአለም ብርሀን መሆኑን፣ የሰው ልጆችን ለማዳን ራሱን ዝቅ አድርጎ በማርያም ማህፀን አድሮ በከብት በረት መወለዱን <u>ሁሉም</u> ሊገነዘብ በሚችል መልኩ ቀኑ መታሰብ አለበት፡፡

በዚህም መታሰቢያው ከዋዜማው ጀምሮ የነማርያም ቤተሰብና እረኞቹ የነበሩበትን ድባብ በሚያሳይ መልኩ መጀመር አለበት፣ በዚህም በዋዜማው ቀን ህፃናት የእረኛ ወይንም ባህላዊ ልብስ በመልበስ፣ ጅራፍ ወይንም ዱላ በመያዝ፣ ቤተሰብም ለህፃናቱ እረኞች ወደ መስክ ይዘውት የሚሄዱት ባህላዊውን ሙልሙል ዳቦ በማዘጋጀት፣ ህፃናቱም የህይማኖት አባቶችና አገልጋዮች ቤት በመሄድ የ"እንኳን አደረሳችሁ" ፖስት ካርድ፣ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ አበባ፣ የአበባ ስዕል፣ ፍራፍሬ … የመሳሰሉ ስጦታዎችን የሚሰጡበት፣ ስጦታ የሚበረከትላቸውም በቤታቸው ህፃናቱን የሚባርኩበትና የሚፀልዩላቸው ቀን በማድረግ ቀኑ ሊታሰብ ይገባል፡፡

በቤት ወይ በቤተክርስቲያን አካባቢም እንደ ግርግም አይነት በመስራት ሳር መሬት ላይ ጎዝጉዞ ወደ አመሻሽ ላይም የእረኞች እሳት አይነት ችቦ፣ ደመራ፣ እንጨት … በማንደድ ወይንም የብርሀን አካላት በማብራትና በመተኮስ፣ እጣንና ከርቤ በማጤስ ከጎረቤት ወይንም ዘመድ አዝማድ ጋር የወላድ ገንፎ በመብላት፣ ቡና በመጠጣትና በዝማሬ ዋዜማው ሊታሰብ ይገባል፡፡

በገና ጠዋት ቤት ውስጥ የሳር ጉዝጓዝ፣ ለልደት በሚቆረስ ኬክ/ድፎና ስንተኛ የልደት አመት እንደሆነ በሚያሳይ ፅሁፍ፣ ጌጦችና ሻማ በማብራት ስነስርአት የኢየሱስ ልደት ትክክለኛ የልደት በአል ተደርጎ ሊታሰብ ይገባል፣ በዚያን ቀን ህፃናቱም የበአል ልብስ በመልበስ ለጎረቤትና ለዘመድ አዝማድ የ“እንኳን አደረሳችሁ” ፖስት ካርድ፣ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ አበባ፣ የአበባ ስዕል፣ ፍራፍሬ … የሚያበረክቱበትና ይህ ስጦታ የተበረከተላቸውም ህፃናቱን ኬክ፣ዳቦ፣ ፍራፍሬ፣ ከረሜላ፣ ቸኮሌት … በመጋበዝ ህፃናቱን ባርከው የሚሸኙበት ቀን በማድረግ ቀኑ ሊታሰብ ይገባል፡፡

የገናን በዓል በዚህ መልክ ሲታሰብ አማኝ አህዛቡ በሙሉ የክርስቶስን መወለድ እውነታና ዓላማ ላይ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

## 2. <u>የፋሲካ ሳምንት</u>

ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት ቀድሞ ባለው ሳምንት ውስጥ ብዙ ጉልህ ክንውኖች ተከናውነዋል፣ እነዚህን ክንውኖቹንም በተግባር በማሰብ፣ ለአህዛብ ገላጭ በሆነ መልክ ቀናቱን ለምስክርነት ስራ ማዋል አስፈላጊ ነው፣ በዚህም፣

- <u>ሆሳዕና (ዕሁድ)</u>

በሆሳዕና ቀን ኢየሱስ ራሱን ዝቅ አድርጎ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ህፃናቱ ደግሞ የኢየሱስን ጌትነትና ንጉስነት ያወደሱበት፣ ኢየሱስን የባረኩበት፣ አዋቂዎች ደግሞ ዘንባባና የተለያየ ነገር እያነጠፉ ኢየሱስን እንደ ንጉስ አክብረው የተቀበሉበት ቀን ነው፡፡

ስለዚህ፣ በዚህ ቀን የኢየሱስ ጌትነት፣ ስራ … በአደባባይ የሚነገርበት ቀን በማድረግ መታሰብ አለበት፣ በዚህም መታሰቢያው የኢየሱስን ጌትነት፣ አዳኝነት … አጉልቶ በሚመሰክር መልኩ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የመዘምራን

ቡድኖችና በመንገድ ላይ ካርኒቫል(ከተቻለ በማርሽ ባንድ፣ በትርኢቶች ... በማጀብ) ... በዋና ዋና መንገዶች ላይ በማቅረብ ሊከናወን ይገባል፡፡ ፕሮግራሙ ከየት ተጀምሮ የትና የት በመሄድ እንደሚከናወን፣ የት ቦታ ላይ የማጠቃለያ ፕሮግራም እንደሚዘጋጅ በአብያተ ክርስቲያናቱ ህብረት ሊመራ ይገባል፡፡

በዚህም ቀን ኢየሱስ በሆሳዕና ቀን የተናገረውን "ሰላም እራሱ ኢየሱስ መሆኑን" (ሉቃ.19፡42) በማወቅ፣ እያንዳንዱ አማኝ ሰላሙን ክርስቶስን መያዙን ለማሰብና ለመመስከር የሰላም ምልክት የሆነውን ዘንባባ በመያዝ፣ በዘንባባ የሚሰሩ ኮፊያዎችን፣ ቀለበቶችን፣ አምባሮችን ... በመጠቀም፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በቤታቸው ውስጥ፣ በጎበናቸው፣ በመኪናቸው ... ላይ በማሰር መታሰብያውን ሊያከናውኑ ይገባል፡፡

➢ <u>**የፅዳት ቀን(ሰኞ)**</u>

ይህ ቀን ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊት ከእግዚአብሄር ቤተመቅደስ ውስጥ የሚሸቅጡትን ያባረራቸው ቀን ነው፡፡

አማኝም የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ቀን ማንኛውም አማኝ ቂም፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ አለማዊነት፣ ጣዖት ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት ... ነፃ መሆኑን ራሱን የሚፈትሽበትና ቤተመቅደሱን የሚያፀዳበት ቀን መሆን አለበት፣ በዚሁ መንፈስም፣ ለምዕመኖች በሚመች መልኩ፣ ከሰአት በኋላ የግቢ የሰፈር፣ ከተቻለ ከተማ አቀፍ የፅዳት ዘመቻ በማድረግ ቀኑ መታሰብ አለበት፡፡

➢ <u>**የፍሬ ቀን(ማክሰኞ)**</u>

ይህ ቀን መታሰብ ያለበት፣ ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ርቦት ከበለስ የሚበላውን ፍሬ ፈልጎ ስላላገኘባት ረግሟት የሄደበት ቀን በማሰብ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ፣ በዚህ ቀን የትኛውም አማኝ ለእግዚአብሄር ያፈራውን የመንፈስ ፍሬ ይህም ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት(ገላ.5፡22)

እንዲሁ እግዚአብሄርን ወደ መምሰል(1ጢሞ.4፡7) እንዴት እያደገ እንዳለና ወንጌልን ለስንት ሰው እንደመሰከረ ያለፈበትን ጊዜያት የሚገመግምበትና ለወደፊቱም እንዴት እንደሚንቀሳቀስ ዕቅድ የሚያወጣበትና እንደ በለሷ ፍሬ ጠፍቶበት እንደማይረገም ራሱን የሚመለከትበት ጊዜ በማድረግ ቀኑ ሊታሰብ ይገባል፡፡

- <u>**የሽቶ ቀን(ሮብ)**</u>

ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊት ማርያም የተባለች ሴት መጥታ እግሩን ሽቶ ቀባችው፣ ድርጊቷም "መታሰቢያነቱ ለትውልድ ነው(ማቴ.26፡13)" በተባለው መሠረት በዚህ ቀን ሰዎች ለቤተሰባቸውና ለትዳር አጋራቸው የሽቶ ስጦታ በማበርከት የሚያስቡት ቀን ሊደረግ ይገባል፡፡

- <u>**የእስራት ቀን(ሐሙስ)**</u>

ኢየሱስ አርብ ሊሰቀል ሀሙስ ዕለት ታሰረ፣ ስለዚህ በዚህ ቀን የሚለበሰው በተለምዶ የእስረኛ ልብስ ተደርጎ የሚወሰደውን ቢጫ ልብስ (ሙሉ ወይንም ግማሽ ቢጫ ልብስ) ሲሆን በዚህን ቀን የሚበላውም ምግብ እስረኛ እንደሚበላው አይነት ተራ ምግብ (ለምሳሌ ሽሮ፣ ፍርፍር፣ የሱፍ ፍትፍት፣ ቲማቲም …) ይሆናል፣ ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊትም የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበው ሁሉ አመሻሽ ላይ በቤተክርስቲያንና በቤተሰብ ደረጃ እርስ በርስ የእግር መተጣጠብ ስነስርአት ሊታሰብ ይገባል፡፡

- <u>**የይቅርታ ቀን(አርብ)**</u>

አርብ እለት ኢየሱስ ስለ ሰዎች ሀጢያት ዋጋ የከፈለበት ቀን በመሆኑ ስለ ሀጢያት ስርየት የፈሰሰውን ደሙን ለማስታወስ የሚለበሰው ሙሉ ወይንም ግማሽ ቀይ ልብስ ሲሆን ኢየሱስ በራሱ ላይ የተሸከመውን የእሾህ ጉንጉን በማሰብም በራስ ላይ የቄጠማ፣ ዘንባባ፣ ሳር፣ ክር፣ ጨርቅ … በማሰር ቀኑ ሊታሰብ ይገባል፡፡ ኢየሱስ ከተገደለበት ዘጠኝ ሰአት በኋላ እንደ ባህላችን የሀዘን ንፍሮ በመመገብና ወደ መዝናኛ ቦታዎች ባለመሄድ ሞቱ ሊታሰብ ይገባል፡፡

ቀኑ የሰው ልጆች የሀጢያት ይቅርታ ያገኙበት ቀን በመሆኑም በዚህም ቀን "በደላችንን ይቅር በለን እኛን የበደሉንን ይቅር እንደምንል" በሚለው

መንፈስ ቀኑ በግለሰብ ሆነ በሀገር ደረጃ የይቅርታና የእርቅ ቀን መደረግ አለበት፣ በዚህም ሰዎች የበደሉትን፣ የተጣሏቸው ወይንም የተቀየሟቸው ሰዎች ካሉ ስልክ ደዋውለው ይቅር የሚባባሉበት ቀን በማድረግ፣ መንግስትም ባለው አሰራር እስረኞችን በይቅርታ የሚፈታበት ቀን ሆኖ ሊታሰብ ይገባል፡፡

➢ **<u>የሀዘን ቀን(ቅዳሜ)</u>**

ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ የቆየበት ቀን በመሆኑ እለቱ የሚታሰበው ሙሉ ወይንም ግማሽ ጥቁር ልብስ በመልበስና ወደ መዝናኛ ቦታዎች ባለመሄድ ነው፡፡

በዚህ ቀን እያንዳንዱ አማኝ እራሱም አንድ ቀን እንደሚሞትና እንደሚቀበር ቆም ብሎ የሚያስብበትና ስጋዊው ሞቱም ሳይመጣ እራሱ ለዓለማዊነት መሞቱንና ለዘላለማዊው መንፈሳዊ ነገር መለየቱን የሚመለከትበት ቀን መሆን አለበት፡፡

➢ **<u>የትንሳኤ ቀን(እሁድ)</u>**

የትንሳኤ ቀን፣ ምህረት የወረደበት፣ የክርስትና ዘመን መለወጫ ቀን በመሆኑ፣ አማኙ በሙሉ አዲሱን የክርስትና አመት መጀር ያለበት ከፈጣሪ ጋር ያለውን ቃል ኪዳን በማደስ ስጋ ወደሙን በመውሰድ ሊሆን ይገባል፣ በዚህም ጠዋት 12፡00 ሰአት ላይ በቤተክርስቲያን በሚደረግ ስነስርአት ወይንም በቀጥታ የቴሌቪዥ/ሬዲዮ/ኢንተርኔት ስርጭት የቅዱስ ቁርባን ስነስርአት ሊፈፅም ይገባል፡፡

እሁድ የትንሳኤው ቀን ስለሆነ የሚለበሰው ነጭ ልብስ ሲሆን ቀኑም በትንሳኤ አእምሮ፣ በትንሳኤ ልቦናና በትንሳኤ መንፈስ ሊታሰብ ይገባል፡፡

ከአለባበስ ጋር በተያያዘ አቅም የሌላቸው፣ ዩኒፎርምና የስራ ልብስ አስገዳጅ በሚሆንባቸው ቦታዎች … በዚያን ቀን የሚለበሰው ልብስ ቀለም የሆነ ክር፣ ፈትል፣ ጨርቅ … የተመቻቸውን በእጃቸው ላይ አስረው ማሰብ ይችላሉ፣ በተጨማሪም ከላይ "የፅዳት ቀን፣ የፍሬ ቀን፣ የይቅርታ ቀንና ለ"ዓለምና ለስጋዊ ፍላጎቶች መሞት" የሚባሉት እዚህ ጋር የቀረቡት ለመታሰብያነት እንጂ የእያንዳንዱ አማኝ የየእለት ተግባር መሆን አለበት፡፡

አንዳንድ ሰዎች በሌሎች የአዘቦት ቀናትም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለሰራው ስራ መታሰቢያ የመስቀሉን ምልክት በሀብል፣ በቀለበት … መልክ አሰርተው ሲይዙ ይታያል ነገር ግን እዚህ ጋር ጥንቃቄዎች ሊደረጉ ይገባል ምክንያቱም ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ዘንድ የተሰራው ስህተት እዚህም ጋር መደገም የለበትም፣ ይህም:-

- “የመስቀልን ምልክት መሸከም” ለመታሰቢያነት እንጂ ሉቃ.9፡23 “… በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ <u>መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ</u>፡፡” የሚለው ቃል ትርጉም አለመሆኑን በተረዳ መልኩ መሆን አለበት፣ የዚህ የሉቃ.9፡23 ትርጉም በ1ጴጥ.2፡21-24 የተብራራው ለክርስትና ተብሎ ስለሚከፈለው ዋጋ መሆኑን በተረዳ መልኩ ሊተገበር ይገባል፣ ለአንድ ተግባር ተብሎ የትኛውም ቃል መሸፈን የለበትም፣ እያንዳንዱ ቃል የአምላክ ቃል ናትና፡፡
- በየመንገዱ የሚሸጡት ቅዠት የሚያባርር፣ ሰይጣን የሚያባርር … የሚባሉ የተደገመባቸው አጋንንታዊ አሰራሮችን ባለመጠቀም፣
- መስቀልን ጣዖት የሚያደርገውና ለመስቀል የሚደረገው አምልኮ(መስቀል መሳም፣ ለመስቀል መስገድ …) በራቀ ሁኔታ መከናወን አለበት፡፡

በዚህም መስቀልን ለመታሰብያነት የምትጠቀሙ “ሳሩንም ገደሉንም” እያያችሁ መሄድ አለባችሁ፡፡

እነዚህ ስምንቱን የፋሲካ ቀናት በዚህ መልክ በመታሰባቸውም አብዛኛው አማኝ ራሱን እንዲመለከት ሲያደርግ አህዛቡም የኢየሱስን ስራ እንዲገነዘብ ያደርጋል፣ ይህ ደግሞ ትልቅ ምስክርነት ነው፡፡

### 3. <u>የዘመን መለወጫ</u>

ክርስቲያናዊው ዘመን መለወጫ ፋሲካ እለት ቢሆንም በሀገሪቱ ከወቅቶች መፈራረቅ ጋር ተያይዞ በብሄር ብሄረሰቦችም ሆነ እንደ ሀገር ዘመን መለወጫ በአል የሚከበረው በመስከረም ወር ነው፣ ማንኛውም ክርስቲያን ከሚኖርበት ማህበረሰብ ባህል ጋር መፅሀፍ ቅዱሱን በማይፃረር መልኩ መሳተፍ እንዳለበት ሁሉ፣ ለየትኛውም ብሄር ሳያዳላ ሀገራዊውን የዘመን

መለወጫ ቀን መስከረም አንድ በዘመን መለወጫነት ከማህበረሰቡ ጋር ማክበር ይገባዋል፡፡

በዚህም ለአዲስ አመት የተጀመረው ሙሉ የጳጉሜ ፆም ፀሎት እንዳለ ሆኖ በጳጉሜ መጨረሻ ቀን ፆም ፀሎቱ ካለቀ በኋላ አጠቃላይ የራስ ግቢ፣ የሰፈር፣ የቤትክርስቲያን አካባቢ ከተቻለ ከተማ አቀፍ የፅዳት አገልግሎት የሚሰራ ሲሆን መስከረም አንድ ቀን ቄስ ቶለሳ ጉዲና ያወጁት የእስታዲየም የአጠቃላይ ቸርቾች የህብረት ፕሮግራም እንዳለ ሆኖ ነገር ግን እያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት ወደ እስታዲየም የሚመጡት በተበታተነ መልኩ ሳይሆን ከየቸርቾቻቸው መዘምራኖቻቸውንና ምዕመናኖቻቸውን ይዘው በዋና ዋና መንገዶች እየዘመሩ መሆን አለበት፡፡

የዚህ ቀን ፕሮግራም በአብያተ ክርስቲያናቱ ህብረት መመራት ያለበት ሲሆን ከ12 ሰአቱ የአዲሱ አመት ብስራት የመድፍ ተኩስ ስነስርአት በኋላ የአብያተ ክርስቲያናቱ ህብረት በሚያዘጋጃቸው የሀይማኖት አባቶች በቀጥታ የቴሌቪዥን፣ የሬዲዮ፣ የኢንተርኔት ... ስርጭት ሀገርን፣ መንግስትን፣ ፓርቲዎችን፣ ህዝቡን፣ ሠራተኛውን ... በመባረክና ለደቂቃዎችም "ኢትዮጵያ ለእግዚአብሄር ትሰግዳለች" በሚለው ቃል መንፈስ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድ ጊዜ ለእግዚአብሄር የሚሰግድበት ጊዜ መደረግ አለበት፡፡

በአጠቃላይ "በአላት" ተብለው በተሰየሙት ቀናት የኢየሱስ ስራዎችን በአግባቡ የሚመሰከርበት፣ እግዚአብሄር የሚከብርበት፣ የፕሮቴስታንት አንድነት የሚታይበት፣ አማኞችም ራሳቸውን የሚያዩበት ቀን ... በማድረግ ማሰቡ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት እንመለከታለን፡፡

እነዚህን ቀናት በዚህ መልክ በመታሰባቸው ከሚገኘው መንፈሳዊ ጥቅም በተጨማሪ ሀይማኖታዊ ስነስርአቶችን ከመንፈሳዊው ነገር ጋር ጨምሮ መያዙ ሌሎች መሠረታዊ ጥቅሞች እንዳሉት ከጥንታውያኑ ሀይማኖቶች ልምድ መመልከት ይቻላል፡፡ ግዙፎቹ ጥንታውያን ሀይማኖቶች በግዝፈትና በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ፀንተው ሊቆሙ የቻሉት ምዕመናኖቻቸው ጋር ባለው መንፈሳዊ እውቀት ሳይሆን በሀይማኖታዊ ስርአቶቻቸው ነው፣ አብዛኛው ምዕመን ስለሀይማኖቱ አስተምህሮ ምንም ሳያውቅ ነው ለሀይማኖታዊ በዓል ብቻ ሀይማኖተኛ የሚሆነው፣ ይህ ችግር እንደ ችግርነቱ መመልከቱ ተገቢ ቢሆንም እዚህ ጋር ያለውን ልምድ ከነባሩ መንፈሳዊ

አሰራር ጋር መቀመሩም አስፈላጊ ነው፣ በሀይማኖታቸው ደከም የሚሉ ሰዎች በዓልን እንኳን ሰበብ አድርገው ራሳቸውን በሀይማኖቱ አውድ ውስጥ አስገብተው መንቀሳቀሳቸው አሁን ካለው “በእምነት የደከመ ጠፋ” ሁኔታ የተሻለ ነው፡፡

ፕሮቴስታንቱ አካባቢ ሁሉም ነገር መንፈሳዊ ብቻ በመሆኑ፣ በሀይማኖት ደከም ያሉ ሰዎች የሚስተናገዱበት ቦታ የለም፣ አንድ ሰው በሀይማኖቱ ደከመ ማለት ወይ በፖለቲካው መንፈስ ወደ ብሄር ሀይማኖት ይሄዳል ወይ በፍልስፍና መንፈስ ወደ ኤቲዝምና ሂውማኒዝም ይሄዳል፣ ይህ ኪሳራ ደግሞ የአንድ ሰው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ሰው በኋላም ያለው ትውልድ ኪሳራ ነው፡፡ ዛሬ ላይ የፕሮቴስታንት ሀይማኖት ተሀድሶ የተንቀሳቀሰባቸው ሀገሮች ላይ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት፣ ሀይማኖቷ የአንድና ሁለት ትውልድ ጉዳይ ብቻ ናት፣ ሌላውን ትውልድ በኤቲዝም፣ ሂውማኒዝም … ውስጥ ነው የሚገኘው፡፡ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በተሀድሶ በመመስረቷ አማኞቿ የሌሎች ሀይማኖት ተቋማትን ድክመት በዝርዝር ስለሚያውቁ እራሳቸው በሚደክሙበት ጊዜ ወደ ሌላ ሀይማኖት አይሄዱም፣ ቤተክርስቲያኗ ጋር ደግሞ ሰነፎችን የሚያስተናግድ ሜዳ ባለመኖሩ ደካማውን አማኝ የሚጠብቀው “ደከመ ጠፋ” የሆነው የፍልስፍናው ሜዳ ብቻ ነው፡፡

በዚህም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ይህንን ነባራዊ ሂደት በመመልከት ሀይማኖታዊ ስርአቶችን ከመንፈሳዊ ጥቅም በተጨማሪ የደካማ አማኞች መሰባሰቢያ ሜዳ መሆኑን በመገንዘብ፣ ቤተክርስቲያኗ በትውልድ መካከል ያላትን ህልውናና ግዝፈት የምታስጠብቅበት ሌላው መንገድ መሆኑን በመገንዘብ መፅሀፍ ቅዱሱን የማይቃረኑ ሀይማኖታዊ ስርአቶችን ከመንፈሳዊው ነገር ጋር በአግባቡ ልትተገብር ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ(ፕሮቴስታንት)

መፅሀፍ ቅዱሱ ደስ በሚል መልኩ ግልፅ አድርጎ ሰዎች ከዘላለማዊው ሞት የሚድኑት በኢየሱስ ላይ ባላቸው እምነት ብቻ መሆኑን ይናገራል፣ የሚገርመው ከላይ በተመለከትናቸው ስድስቱ ምዕራፎች ውስጥ ሁሉም ሀይማኖቶች በኢየሱስ ላይ ያለቸው እምነት ፈፅሞ የተለያየ ነው፣ ይህ እውነታ ደግሞ ትክክለኛዋ ሀይማኖት የትኛዋ ናት? የሚለውን መመመለስ እንድንችል ረድቶናል፣

- አይሁድ - "ኢየሱስ አልተወለደም ገና ይወለዳል"
- ሙስሊም- "ኢሳ ተወልዷል ነገር ግን እንደኛው ሰው ብቻ ነው"
- ሐዋርያት - "ኢየሱስ ፍፁም አምላክ እንጂ ሰውነት የለውም"
- ጂሆቫ - "ኢየሱስ መልአኩ ሚካኤል ነው"
- ስላሴያውያን (ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት፣ አድቬንቲስት ...) - "ኢየሱስ የሰውና የአምላክ ተዋህዶ ነው"

የሚገርመው ደግሞ "ተዋህዶ ነው" ብለው አንድ የሚመስሉት ስላሴያውያን ተመልሰው ደግሞ በአገልግሎቱ ላይ የተለያየ አቋም አላቸው፡-

- ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ - "ኢየሱስ አሁን ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም"
- አድቬንቲስት - "ኢየሱስ አሁን የምርመራ ፍርድ እየሰራ ነው"
- ፕሮቴስታንት - "ኢየሱስ አሁን አማላጅ ነው የፍርድ ጊዜ ገና ነው"

ይህ ሁሉም ሀይማኖቶች በኢየሱስ ማንነትና አገልግሎት ላይ የተለያየ እምነት መያዛቸው ትክክለኛዋን ሀይማኖት የትኛዋ እንደሆነች መለየት እንድንችል ረድቶናል፣ በዚህም ከላይ በቀረቡት የስድስት ምዕራፎች ጉዟችን የፕሮቴስታንት ሀይማኖት ኢየሱስን በትክክለኛ መንገድ የተረዳች ትክክለኛዋ ሀይማኖት መሆኗን ተመልክተናል፡፡

እያንዳንዱ ሰው ትክክለኛዋን ሀይማኖት ከመለየቱ ስራ በመቀጠል፣ መፅሀፉ "የገነትና የሲኦል መለያ" የሚያደርገውን "በኢየሱስ ማመን" የተባለውን የገነት መግቢያ ቁልፍ ከመሄዱ በፊት በትክክል መያዙን ማረጋገጥ አለበት፣ ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ከስር መሰረቱ ብንመለከት፣

የሰው ልጅ በሀጢያት በመውደቁ ምክንያት ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል እየጎረፈ በመሆኑ ፈጣሪ ለሰው ልጅ በማዘን መጀመሪያ ወደ አሰበለት የገነት ህይወት ለመመለስ አሰበ፣ በዚህም ኋለኛውን አዳም(ኢየሱስ ክርስቶስን) ወደ አለም ላከው፣ ኢየሱስም ሰዎች ዋናውን "የሃጢያት ዋጋ ሞት ነው" ህግ አልፈው ገነት መግባት እንዲችሉ፣ ስለ ሰው ልጆች ሀጢያት በምትካቸው በመስቀል ላይ ዋጋ ከፈለ፣ በዚህም ሰዎች እንዲያው በዚህ በኢየሱስ ስራ አምነው ከሀጢያት ኩነኔ ድነው ገነት የሚገቡበት መንገድ ተዘጋጀ፡፡

"በኢየሱስ ማመን" የሚለው ሃሳብ በዋናነት አራት ተከታታይነት ያላቸውን የኢየሱስ ማንነትና አገልግሎቶች ናቸው፣ ይህም የኢየሱስ ኦሪጂናል ማንነት፣ በምድር ላይ የሰራው ስራ፣ አሁን እየሰራ ያለውና ለወደፊት በሚሰራው ስራዎቹ ማመን ማለት ነው፣ ይህም፣

- ኢየሱስ ማን እንደሆነ? ኢየሱስ ጌታ መሆኑን፣
- ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ ምን ሰራ? የሰው ልጆችን የሀጢያት ዋጋ እራሱ በመስቀል ላይ ከፈሎላቸው ከሲኦል አዳናቸው፣
- ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ምንስ እየሰራ ነው? ሰዎች በየዕለት ሀጢያታቸው እንዳይያዙ እያማለደ ይገኛል፣
- ኢየሱስ ለወደፊቱ ምን ይሰራል? ይፈርዳል፡፡

ስለዚህ የትኛውም ሰው ከሲኦል ለመዳን በነዚህ አራቱ የኢየሱስ ማንነትና አገልግሎቶች ማመን አለበት፣ እነዚህ አራቱ ቁም ነገሮች ሰፋ ያለ ትንታኔ ቢኖራቸውም በዋናነት ግን "በኢየሱስ ማመን" የተባለው ትዕዛዝ አራቱ ዋልታዎች ናቸው፣ በዚህም እያንዳንዱ ሰው በእነዚህ አራቱ የእምነት ዋልታዎች ላይ መመስረቱን ከመሄዱ በፊት ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ቤተክርስቲያንም በምድር ላይ እነዚህን ስራዎች አቀናጅታ የምትሰራ ተቋም እንደመሆኗ መጠን፣ ሰዎች እነዚህን አራቱን "ኢየሱስን ማመን" መስፈርቶች ሲያሟሉ፣ በተሰጣት ሀይማኖታዊ ስነስርአት ውስጥ ታሳልፋቸዋለች፣ በዚህም የትኛውም አዲስ አማኝ በነዚህ በአራቱ የዕምነት ዋልታዎች ሲቀበል ወደ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በመሄድ የቤተክርስቲያኗን ሀይማኖታዊ ስነስርአቶች መፈፀም አለበት፣ እነዚህም ስርአቶች አማኙ ከእግዚአብሄር ጋር ቃል ኪዳን የሚገባበት፣ የክርስቶስ ተከታይ መሆኑን በጥምቀት የሚያረጋግጥበትና የክርስቶስ አካል ለመሆኑ ቅዱስ ቁርባን የሚቀበልበት ስነስርአቶች ናቸው[154]፡፡

ማንም ሰው በኢየሱስ በማመንና እነዚህን ሀይማኖታዊ ስነስርአቶችን በመፈፀሙ በመንፈሳዊ ማንነቱ ላይ የሚሆነው ነገር በብርሀንና በጨለማ መካከል ያለ ልዩነት ነው፣ ለዚህም ነው መፅሀፍ ቅዱሱ አንድ ሰው ይህንን ድርጊት ሲፈፅም "በእግዚአብሄር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል" የሚለው(ሉቃ.15፡10)፡፡

---

[154]እምነቱ ገብቷችሁ ነገር ግን ሶስቱን ሀይማኖታዊ ስነስርአቶች መፈፀም ያልቻላችሁ፣ የመጀመርያውንና ዋናውን "ከእግዚአብሄር ጋር የሚደረገውን ቃል ኪዳን" ለብቻችሁ በመሆን በጥሞና የሚከተለውን ቃል ኪዳን መፈፀም ትችላላችሁ፣ "በሰማያት ያለኸው እግዚአብሄር ሆይ፣ እውነቱን እንድረዳ ስለረዳኸኝ አመሰግንሀለሁ፣ አሁን እውነቱ ገብቶኝ ሰይጣንንና ዓለማዊነትን ክጄ አንተን ልከተል ወስኛለሁ፣ ተቀበለኝ፣ ሀጢያቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፣ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ፣ ስለኔ ሀጢያት በመስቀል ላይ እንደሞተ፣ አሁንም ስለኔ እንደሚያማልድ፣ ለፍርድም እንደሚመለስና እኔንም ከፍርድ እንደሚያድነኝ አምኛለሁ፣ በዚህ እምነቴም ስላፀደከኝ፣ ልጅህ ስላደረከኝ፣ በከበረው መዝገብህም ስለፃፍከኝ አመሰግንሀለሁ፣ በጌታ በኢየሱስ ስም፣ አሜን"፡፡

ከዚህ ቃል ኪዳን በኋላ ባሉበት ሆነው መፅሀፍ ቅዱሱን በመጀመርያ አዲሱን ኪዳን ከዚያም ብሉይ ኪዳንን በማንበብ፣ የቤተክርስቲያን ቻናሎችን በመከታተል፣ በአቅራቢያዎ የሚገኙ አማኞችን በማፈላለግ ህብረት ያድርጉ፣ በተመቾት ጊዜም የተቀሩትን ሁለቱን ሀይማኖታዊ ስነስርአቶች በቤተክርስቲያን ተገኝተው ይፈፅሙ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## 7. መጪው የአንድ ዓለም አንድ ሀይማኖትና አንድ መገበያያ ስርአት

የስነፍጥረት አጀማመር፣ የአዳም መሳሳትና ከገነት መባረር፣ የኖህ ዘመን የጥፋት ውሃ፣ የእስራኤላውያን ከግብፅ ሀገር ባርነት በተአምራዊ እጅ መውጣት፣ የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የተከናወኑ አንኳር ታሪኮች ናቸው፣ ከነዚህ ተርታ የሚሰለፍ ሌላ አንኳር ታሪክ ደግሞ ከፊት ለፊታችን ተቀምጧል፣ የዓለም ሀይማኖቶችን በሙሉ አንድ በማድረግ ዓለም በአንድ ሀይማኖት እንድትኖር የሚያደርግ በከፍተኛ መንፈሳዊ ሀይል ተሞልቶ የሚነሳ ሰው ታሪክ፡፡

ይህም ሰው በመናፍስታዊ ሀይል እገዛ "እኔ ክርስቶስ ነኝ" በማለት(ሉቃ.21፡8) አለምን ለሰባት አመታት(ለአንድ ሱባኤ) ይገዛል(ዳን.9፡27, ዳን.11፡36, 2ተሰ.2፡4, ራዕ.13፡4 ...)፣ መፅሀፍ ቅዱሱ ይህንን ሰው "የጥፋት ልጅ"(2ተሰ.2፡3)፣ "ሀሰተኛው ክርስቶስ"(ማቴ.24፡24)... ሲለው በሰውየው ላይ የሚያድረውን መንፈስ ደግሞ "አውሬው"(ራዕ.11፡7, ራዕ.19፡20) ይለዋል፤ በሚገርም መልኩ ደግሞ ይህንን ሰው ሁሉም ሀይማኖቶች እየጠበቁት ይገኛሉ፡፡

እስልምና ይህን ሰው "ኢማም መኽዲ" ይለዋል፣

> የአቡ ዳውድ ሱና 4283-4286) "ለጊዜው አንድ ቀን ሲቀረው አላህ ከዘሬ ሰው ይልካል ... በአለም ላይ እኩልነትና ፍትህ ያሰፍናል፣ አለም ላይ ለሰባት አመታት ይነግሳል ... በነዚህ አመታት እስልምና በአለም ላይ ይነግሳል፡፡"

ይህ ከመፅሀፍ ቅዱሱ የሀሰተኛው ክርስቶስ ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ታሪክ ነው፣ ንግስናው ሰባት አመታት መሆኑና "ለጊዜው አንድ ቀን ሲቀረው" የሚለውም ከኢየሱስ መምጫ በፊት መሆኑ ተመሳሳይ ታሪክ መሆኑን ያሳያል፤ ቁርአኑም 97፡1 "እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው፡፡ መወሰኛይቱም ለሊት ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ፣ መወሰኛይቱ ለሊት ከሺ ወር በላጭ ናት ... እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት፡፡" ይላል፣ እዚህ ጋር "እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት" የሚለው መፅሀፍ ቅዱሱ "ብርሀን" የሚለው ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ

መሆኑን ያሳያል፣ በዚህም የዚህ መንፈስ አሰራር የሚሰራው ያ ጎህ እስኪቀድ ድረስ ብቻ ነው፡፡ መፅሀፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን "አውሬ" የሚባል መንፈስ እንደሚነሳ ይናገራል በተመሳሳይ መንገድም ቁርአኑም በመጨረሻው ዘመን የቁርአንን አንቀፅ የምትናገር አውሬ እንደምትመጣ ይናገራል(27፡82)፣ በርግጥ አውሬ እንደ ሰው አይናገርም ነገር ግን ቁርአኑ የሚናገረው በመንፈሳዊ ትርጉም ነው፡፡

[155] አንዳንድ የሂንዱ ሀይማኖቶች "ክሪሽና" ይሉታል፣ "ካልኪ" ብለው የሚጠሩ የህንድ ሀይማኖቶችም አሉ፣ [156] "ካልኪ" ማለት [157] "ቪሽኑ" ለመጨረሻ ጊዜ በስጋ የሚወለድበት ማንነት ነው፣ [158]ቡድሂስቶች "ሚየትራ" ይሉታል፣ "ሚየትራ" ማለት ... "ቡድሃ" ለአምስተኛ ጊዜ ሲወለድ የሚገለፅበት ስም ነው፣ [159] "ከሚየትራ በኋላም አለም በሰባት ፀሀዮች እንድትጠፋ ይደረጋል" ይላሉ፣ ይህ ስለ መጨረሻው ቀን የተነገረው አነጋገር ከፊል መፅሀፍ ቅዱሳዊ ነው፣

> ኢሳ30፡26 እግዚአብሄርም የህዝቡን ስብራት በጠገነ ዕለት፣ መቅሰፍቱ የቆሰለውንም በፈወሰ ዕለት፣ የጨረቃ ብርሀን እንደ ፀሀይ ብርሀን፣ <u>የፀሀይም ብርሀን እንደ ሰባት ቀን ብርሀን ሰባት እጥፍ ይሆናል</u>፡፡"

በ3.2.6 ክፍል የተመለከትነው "የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ" ሀይማኖትም በፊናው እየጠበቀ ይገኛል፣ እንደ ሀይማኖቱ አስተምህሮ [160]ዓለም ልትገባበት እያለች ያለችው የ"አኩዋረስ ዘመን" ነው ይላል፣ ዘመኑም የሚመሠረተው እንዴት እንደሆነ የተለያየ ሃሳብ ያላቸው

---

[155] ግደይ ገ/ኪዳን(2007)፣ **የኢሉሚናቲ የቁጥጥር ዘዴዎች**፣ ገፅ 53

[156]https://en.m.Wikipedia>wiki>end time

[157] በሂንዱዎች እምነት አለምን የሚያስተዳድሩት ሶስት አማልክት ናቸው፣ ብራህማ(የሚፈጥር)፣ ቪሽኑ(የሚያድን) እና ሺቫ(የሚቀጣ)፣ ቪሽኑ አለምን ለማዳን የሚሰራው በተለያየ መንገድ ደጋግሞ በመወለድ ነው፣ ቪሽኑ ለ10ኛ ጊዜ ሲወለድ ካልኪ በሚባል ማንነት ሲሆን የሚመጣውም ከባህር ነው፣ የሚወለደውም አለም ለመጥፋት ጫፍ ላይ ስትደርስ አለምን ለማዳን ነው፡፡

ካልኪ አለም ልትጠፋ ስትል የሚወለድ መሆኑና የሚመጣውም ከባህር መሆኑ ከፊል መፅሀፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው(ራዕ.13፡1)፡፡

[158]ግደይ ገ/ኪዳን(2007)፣ **የኢሉሚናቲ የቁጥጥር ዘዴዎች**፣ ገፅ 53

[159]https://en.m.Wikipedia>wiki>end time

[160] https://en.m.Wikipedia>wiki>New age movement

ሲሆኑ አንዳንዶች በሰዎች “human agency” እንደሆነ ሲናገሩ፣ ሌሎች ደግሞ “non human forces such as spirits or extra terrestrials” ሲሉ ሌሎች ደግሞ ምጡቅ በሆነ ሰው “aquarum conspiracy” ነው ይላሉ፣ ስለ ዘመኑም ሲናገሩ “በዚያ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ፍፁም በሆነ ሰላም፣ ደስታ፣ ፍቅር፣ መትረፍረፍ... ውስጥ ይኖራሉ” ይላሉ፡፡

ይህንን ዋነኞቹ ሀይማኖቶች በጉጉት የሚጠብቁት ሰው በዘመናዊ ፊልሞችም እየተተነበየ ይገኛል፣ በዚህም ማንም የማይችለው አስገራሚ ሀይልና ጥበብ ያለው፣ ከአለም ውጪ የሚመጡትን ሀይላት የሚከላከል፣ ሰዎች ሊወዱትና ሊከተሉት የሚገባውን ልዩ ሰው የተለያዩ ፊልሞች በአኒሜሽንና በገፀባህሪ ሲሰሩ እንመለከታለን፣ በርግጥ 1.4.2.3/3 ክፍል እንደተመለከተው ኢየሱስ ከሰራዊቱ ጋር በደብረ ዘይት ተራራ የሚወርደው የዓለምን ሰራዊት ለመግጠም ነው፣ በዚህም የፊልሙ ትንቢት ግማሽ እውነታነት አለው፣ የፊልም ኢንደስትሪው ይህንን ሰው በተለያየ ስም ይጥራው እንጂ ይሄ ልዕለ ስብዕና ያለውና “ድንቅ” የተባለለት ሰው እንደሚመጣ ሁሉም የሚስማማበት ሀቅ ነው፡፡

መፅሃፍ ቅዱሱ በዚህ ሰው ጥበብና ችሎታ እንዳንገረም ቀድሞ አስጠንቅቋል ራዕ.13፡13-15 “እሳትንም ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል ...” ስለ ሃይሉና ብርታቱም ሲናገር ራዕ.13፡7 “ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፡፡” በዚህም ብቃቱ 2ተሰ.2፡4 “እኔ እግዚአብሄር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በቤተ መቅደስ እስከሚቀመጥ ድረስ፣ አምላክ ከተባለው ሁሉ፣ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው” በማለት ራሱን “እግዚአብሄር” እስከማለት እንደሚደርስ ይናገራል፡፡

የሚገርመው ደግሞ ስለዚህ ሰው መፅሀፍ ቅዱሱ፣ ሌሎች ሀይማኖቶችም ሆኑ ዘመናዊው ፊልሞች በጉጉት የሚጠብቁት ሆኖ፣ ከመፅሀፍ ቅዱሱ በስተቀረ ሁሉም አድናቆታቸውን የሚቸሩት መሆኑን ስንመለከት እነዚህ አካላት የተለያየ ስም ይያዙ እንጂ ዞረው ዞረው በክርስትና ተቃዋሚ መንፈስ የሚመሩ አንድ ቡድኖች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በዚህ ምዕራፍም ይህን መንፈስ ለመቀበል እየተደረጉ ያሉትን አለማቀፋዊ ቅድመ ዝግጅቶችና ሀገራዊ አሰራሮች፣ መንፈሱ ሲገለጥ የሚከተለው አሰራር፣ የቁጥጥር እስትራቴጂና የመንፈሱ መጨረሻ ምን እንደሚሆን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## 7.1. <u>የዓለም ቅድመ ዝግጅቶች</u>

ዓለም በግሎባላይዜሽን ሂደት አንድ መንደር እየሆነች ትገኛለች፣ በዚህም ሂደት ሀገራት በቴክኖሎጂው እገዛ በማህበራዊው፣ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው ዘርፍ ጠንካራ ትብብሮሽና ውህደትን እየፈጠሩ ወደ አንድነት እየሄዱ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየሄደች ያለችበትን እውነታ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂው በቁጥጥሩ ስር እያስገባ ይገኛል፣ ከተራው የፅሁፍ አገልግሎትና የማህበራዊ ሚዲያዎች አንስቶ የዓለምን ስርአት ተቆጣጥረው እስከሚገኙት የቴሌኮምኒኬሽን፣ መብራት ሀይል፣ ባንክ፣ ኢንሹራንስ እስከ ጅምላ ጨራሽ ኒውክለር ቦንቦች፣ የኒውክለር ሃይል ማመንጫዎች፣ ሚሳኢሎችና የሳተላይት ሲስተሞች በኮምፒውተር አሰራር ቁጥጥር ስር ወድቀው ይገኛሉ፣ በዚህም ዓለም ሳይስተዋል በአንድ ስርአት ስር እየወደቀች ትገኛለች፡፡

ይህ ደግሞ የራሱን የጎንዮሽ ጉዳት አለው፣ ለምሳሌ እንኳን ብንመለከት፣ በመንፈሳዊ ሀይል የሚንቀሳቀሰውን ልዩውን ሰው ለጊዜው ትተን፣ በአንድ የሶፍትዌር አምራች ድርጅት በሚሰራ የኮምፒውተር ፕሮግራም ብቻ ይህን በአንድ ስርአት ውስጥ የወደቀውን ዓለም በቀላሉ በቁጥጥር ስር ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፣ ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ እንኳን “Ransom ware” የተባለው ቫይረስ፣ “ዊኪ ሊክስ” የተባለው ሚስጢር ፈልፋይ ለጥቂት ቀናትም ቢሆን ዓለምን እንዴት በአንድ እግር እንዳስቆሙ ማስታወስ ይቻላል፣ እንደዚሁ ደግሞ ከዚህ የተራቀቀ የሁሉንም ኮምፒውተር ስርአቶች የሚቆጣጠር ቫይረስ በአንዱ ግለሰብ ወይ ድርጅት ቢለቀቅ ይህ አካል በቀላሉ ዓለምን መቆጣጠር ይችላል፣ ይህን ሰው ንጉስ አይደለም “አምላካችሁ ነኝ፣ ባትሰግዱልኝ …” ቢል አብዛኛው ሰው ይህን ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም፡፡

በዚህም ማንም ዓለምን መግዛት የፈለግ አካል ይህን ዓለም በአንድ ስርአት ውስጥ እየገባች ያለችበትን ሂደት ይጠቀምበታል፣ ከላይ የተመለከትነው በመናፍስታዊ ሀይል የሚንቀሳቀሰው ሰውም ሌላ ምንም ትግል ሳይፈጥር ይህንኑ ሲስተም በቀላሉ በመያዝ ዓለምን በቀላሉ መግዛትና ማሰገድ ይችላል፣ በዚህም አሁን ዓለም በአንድ ስርአት ውስጥ እየወደቀች ያለችበት ሁኔታ ከላይ ለተመለከትነው ሀይል እየተሰራ ያለ ቅድመ ዝግጅቶች ነው፡፡

ከዚህ አጠቃላይ አለማቀፋዊው ቅድመ ዝግጅትም ወረድ ብለን ይህንን ስርአት እየመሩ ያሉት መሪዎች በሀገራቸው ውስጥ እያካሄዱ ያሉትን ነገር ስንመለከት ደግሞ መሪዎቹ በጥብቅ መናፍስታዊ ትስስር ሂደቱን በአንድ መንፈስ እየመሩት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

መሪዎቹ በምን አይነት መንገድ ሀገራቸውን እያመቻቹ እንደሆነ ለመመልከት እንዲያመቸን በመጀመሪያ መንፈሱ የሚፈልገውን አሰራር ለይተን እንመልከት፣ መንፈሱ የእግዚአብሄር ተቃራኒ መንፈስ እንደመሆኑ መጠን ተቃራኒ አሰራሮችን ይከተላል፣ በዚህም በዋናነት ለመፅሀፍ ቅዱሱ፣ ለእስራኤልና ለተፈጥሮአዊው አሰራር ተቃራኒ አሰራሮችን ይከተላል፡፡ እዚህ ጋር ለተፈጥሮአዊ አሰራር ተቃራኒነት(ኢ-ተፈጥሮአዊነት) ማለት ከተፈጥሮአዊ አሰራር ተቃራኒ የሆኑ አሰራሮች ናቸው፣ ይህም ውርጃ፣ ግብረ ሰዶማዊነት(Homosexuality)፣ ከተፈጥሮው ፆታ በተቃራኒ ሌላ ፆታ መሆን(Trans Gender)፣ በትዳር ውስጥ በፈጣሪ እንዲሁም በተፈጥሮ የተቀመጠውን የትዳር መዋቅር በመተው ባልና ሚስትን በአንድ ስልጣን ላይ እኩል አድርጎ ማስቀመጥ … በአጠቃላይ በፈጣሪና በስነተፈጥሮ ተቀምጠው ያሉ ህጎችን መቃወምና እነዚህን ኢተፈጥሯዊ አሰራሮችን ማበረታታትና ለሙብታቸው መቆምን ያጠቃልላል፡፡

በመሪዎች መካከል ያለውን መናፍስታዊ ትስስር ለመመልከት ለምሳሌ ያህል ዋናዎቹን የአለም ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ መሪዎችን አሜሪካን፣ የአውሮፓ ህብረትንና ቫቲካንን የምንመለከት ሲሆን አካሄዱን ተጨባጭ በሆነ መልኩ ለመገንዘብ እንዲረዳንም በሀገራችን ላይ ያለውንም አሰራር እንመለከታለን፡፡

## 1. አሜሪካ

የአሜሪካ መንግስት የሚመራው በሁለቱ በዲሞክራትና ሪፐብሊካን ፓርቲዎች ነው፣ ሁለቱ ፓርቲዎች ፍፁም ተቃራኒ በመሆናቸው የሚሰሩዋቸው ስራዎችም ተቃራኒ ናቸው፣ ይህ ተቃርኖም የመጣው ከጀርባቸው ባለው ተቃራኒ መንፈስ ነው፣ ይህንን ተቃርኖ በቀላል ምሳሌ በኦባማና በትራምፕ መካከል ባለው ልዩነት እንመልከት፡፡

አባማ በስልጣን ዘመኑ ግብረ ሰዶማዊነትን(የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ) ህጋዊ አደረገ አለማቀፉ ማህበረሰብም እንዲቀበለው ብዙ ተፅዕኖ አደረገ፣ ውርጃን በሀገሩና በዓለማቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ፈንድ ሲያደርግ ነበረ፣ መፅሃፍ ቅዱሱ "እስራኤላውያን ከአለም ሁሉ ይሰበሰባሉ" እንደሚለው ለዚህም ትንቢት ማስፈፀሚያ የእስራኤል መንግስት የሚሰራውን የአዳዲስ ቤቶች ግንባታ ከለከለ፣ እስራኤልን የሚጎዳውን የ"two state solution" እና የኢራን የኒውክለር ውል አንቀሳቃሽ ነበረ፣ በ2.3.2.4 ክፍል የተመለከተውን ቁርአናዊ የሽብር ስራ ለመሸፋፈን ድርጊቱን "Violent Extremism" በማለትና በስልጣን ዘመኑም በነዚህ ሀይላት ላይ እርምጃ እንዳይወሰድ ሲያደርግ የነበረ ሲሆን ትራምፕ እነሱን የሚጠራበትን "Radical Islamic Terrorism" አባባልን ሲቃወም ነበረ፣ በቤተመንግስት ውስጥ በክብር ሲቀመጥ የነበረውን አስርቱን ትዕዛዛት ከቤተመንግስቱ እንዲወጣ አደረገ፣ "የኦባማ የጤና ፖሊሲ" በሚል መፅሃፍ ቅዱሱ የሚከለክለውን በግምባርና በቀኝ እጅ ውስጥ ቺፕስ እንዲቀበር የሚያዘውን ህግ አፀደቀ፣ ሀገራችን ሲመጣ እንኳን ስንቶች እየተገደሉና እየተሰቃዩ ባለበት ሁኔታ "ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ የሰፈነባት ሀገር ናት" አለ፣ ለክርስትና ትልቅ ቦታ የሚሰጠውን አሜሪካዊነት እንዲበረዝ የግሎባላይዜሽንንና የአሜሪካን ድንበር ክፍት የማድረግን አሰራር ሲከተል ነበረ፡፡

ትራምፕ ደግሞ ሲመረጥ ከኦባማ በተቃራኒ የሆሞሴክሹዋል ህጉን በተቻለው መንገድ ጫና አደረገበት፣ የውርጃ በጀቶችን በተቻለው መጠን ቆራረጠ፣ በግምባርና በቀኝ እጅ ላይ የሚተከለውን አሰራር ይዞ የመጣውን የኦባማ የጤና ፖሊሲን እንዲሰረዝ ታገለ፣ ኦባማ ከቤተመንግስቱ ያስወጣውን

አስርቱ ትዕዛዛት ወደ ቤተመንግስቱ መለሰ፣ [161]መፅሀፍ ቅዱስ ሆስፒታሎች ውስጥ ተመልሶ እንዲታደል አደረገ፣ የወያኔን መንግስት ሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አወገዘ፣ ኦባማ ያዘጋጀውን የኢራን የኒውክለር ውል በመሰረዝ ኦባማ ያነሳውን ማዕቀብ መልሶ አስቀመጠ፣ አሜሪካ በሪፐብሊካን ስትመራ እስልምናው ሀገራት አካባቢ ትዕቢት ውስጥ የገቡትን ሀገራት በሀይል ስታስተካክል እንደነበረው ትራምፕም በአሁኑ ጊዜ ትዕቢት ውስጥ የገባቸውን ኢራን ለማስተካከል እየሰራ ይገኛል፣ በ2.3.2.4 ክፍል የተመለከተውን ቁርአናዊ የሽብር ስራ በግልፅ "Radical Islamic Terrorism" ሲል የኦባማን የመሸፋፈን አባባል "Violent Extremism" ሲቃወምና በነዚህ ሀይላት ላይ በተከተለው አሳሪ አካሄድ ከአለም ላይ ድምፃቸው እንዲጠፋ አደረገ፣ የእስራኤል የሰፈራ ቤቶችን ግንባታ ፈቀደ፣ በእስራኤል ሰባኛ አመት ምስረታ በአል ቀን ላይ የኢየሩሳሌም የእስራኤልን ዋና ከተማነት አረጋገጠ፣ ለእስራኤል ወታደራዊ እስትራቴጂ ጉልህ ሚና የሚጫወተውን የጎላን ኮረብታዎች የእስራኤል አካል መሆናቸውን አወጀ ...

እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ፊት ለፊት እንደዚህ ተቃራኒ ሆነው ይታዩ እንጂ የጀርባ አጥንታቸው የፓርቲያቸው ርዕዮተ ዓለም ነው፣ በዚህም ሁለቱ ፓርቲዎች በምን አይነት መንፈስ እየተነዱ እንዳለና የየትኛው መንፈሳዊ ጎራ አሰራር እንዲሰፍን እየሰሩ እንዳለ መመልከት ይቻላል፣ በዚህም እያንዳንዱ አሜሪካዊ አሰላለፉን ሊያስተውል ይገባል፡፡

ስለዚህም የትኛውም ክርስቲያን ከዲሞክራቲክ ፓርቲ ጋር ያለውን ህብረት ማቆም አለበት፣ ከመቅሰፍትዋ እንዳይቀበል ከሀጢያትዋ ባይተባበር መልካም ነው(ራዕ.18፡4)፡፡

---

[161] የአሜሪካው ምክትል ፕሬዚዳንት፣ Mike pence, August/29/2019, facebook ገፃቸው ላይ ያስነበቡት ፅሁፍ ነው፡፡

## 2. የአውሮፓ ህብረት

የአውሮፓ ህብረት ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑት የምዕራብ አውሮፓ ሀገራት ከላይ የተመለከትነውን የኦባማን መንገድ ይከተላሉ፤ በተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ፣ በውርጃ፣ በእስራኤል ፍልስጤም ጉዳይ፣ በኢራን የኒውክለር ጉዳይ፣ በግሎባላይዜሽንና የስደተኞች ጉዳይ፣ በሽብርተኝነት ጉዳይ ላይ ከኦባማ ተመሳሳይ አቋም አላቸው፡፡

በህብረቱ ውስጥ የምስራቅ አውሮፓ ሀገራት ተፅዕኖ ፈጣሪነት ባይኖራቸውም የትራምፕ ፖለቲካ መስመርተኛ ናቸው፣ በዚህም የክርስትናን ዕሴቶችና የእስራኤል አጋሮች ሲሆኑ እስልምናን “አሸባሪ ሀይማኖት ነው” እስከማለት የደረሱም ይገኛሉ፡፡

ከምዕራብ አውሮፓውያኑ እንግሊዝ ተፅዕኖ ፈጣሪዎቹ ሀገራት የአውሮፓ ህብረትን እያስኬዱበት ያለው መንገድ አልተመቻትም፣ በዚህም ህዝቡ በብሬግዚት ውሳኔ ከህብረቱ ለመውጣት ውሳኔ ላይ ደርሷል፣ በርግጥ ህዝቡ ከአውሮፓ ለመገንጠል ውሳኔ ላይ ይድረስ እንጂ ትስስሩ መናፍስታዊ በመሆኑ ብሬግዚት በቀላል የሚከናወን ነገር አልሆነም፣ ጠቅላይ ሚስትሯ፣ ቴሪሳ ሜይ፣ ይህንን ማስፈፀም አቅቷት ስልጣንዋን ለቃለች፣ ተተኪው ቦሪስ ጆንሰንም ይህንን ጉዳይ ለማስፈፀም እንዴት እንደተቸገረ ተመልክተናል፡፡

የብሬግዚት ምርጫ ሲካሄድ በነበረበት ወቅትም ያለውን አለማቀፋዊ መንፈሳዊውን ትስስር በግልፅ በሚያሳይ መልኩ ብሬግዚት በትራምፕና በእስራኤል ሲደገፍ በተቃራኒው ደግሞ ኦባማ፣ የኢትዮጵያ መንግስት፣ ቫቲካን ... የመሳሰሉት የብሬግዚት እንቅስቃሴ ተቃዋሚዎች ነበሩ፣ በዚህም በአለማቀፍ ደረጃ ያለውን መናፍስታዊ ትስስር እንመለከታለን፡፡

## 3. ቫቲካን

ኢየሱስ ተቀምጦ ሳለ ወሬ ነጋሪዎች አንድ ነገር በጆሮው ሹክ አሉት፣ “ከዚህ ቦታ አምልጥ ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋል አሉት” ኢየሱስ ግን ከወትሮው በተለየ አነጋገር ፣

ሉቃ.13፡32 “... ሄዳችሁ ለዚያች ቀበሮ፣ እነሆ ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ በሽተኞችንም እፈውሳለሁ፣ በሶስተኛውም ቀን እፈፀማለሁም በሉአት (አለ)፡፡”

እዚህ ጋር ይህ የኢየሱስ እንግዳ አነጋገር የመጣው፣ የታቀደበትን ሴራ በመንፈሱ ስለሚያውቅ ነው ነገር ግን “ቀበሮ” ያለው ማንን ነው? የሚለውን ለማወቅ የሮማን ታሪክ ከስር መሠረቱ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

[162] “እንደ ሮማውያን አባባል ሮም የተመሠረተችው ሮሙለስና ሬሙስ በተባሉ ሁለት ሰዎች ነው፣ እነዚህ ሁለቱ ሰዎች በህፃንነታቸው ቲበር በሚባለው ወንዝ ውስጥ በተጣሉ ጊዜ፣ በአካባቢው የነበረች ቀበሮ እነዚህን ህፃናት ከውሀው አውጥታ ወደ ቤትዋ በመውሰድ አጥብታ ታሳድጋቸዋለች፣ ህፃናቱም ካደጉ በኋላ በአካባቢው የተመለከታቸው እረኛ ህፃናቱን ይወስዳቸዋል፣ እነዚህ ወንድማማቾችም ካደጉ በኋላ ታላቅ ህዝቦች በመሆን ያሁኗን ሮም መሠረቷት፡፡” ይላሉ

ለዚህም መታሰቢያነት በኢጣልያን “The capitolina Wolf” የሚባል አንድ ቀበሮ ሁለት ህፃናትን ስታጠባ የሚያሳዩ ሀውልቶች ይሰራሉ፣ ታሪኩ እውነትም ይሁን ውሸት ህዝቡ ግን በዚያን ወቅት በቀበሮ ባለውለታነትና እናትነት ያምን ነበረ፣ ኢየሱስም ህዝቡን የጠራው ህዝቡ ራሱን በሚመለከትበት መንፈስ ነው “ለዚያች ቀበሮ” ያለው፡፡

ያቺ ቀበሮ ዛሬም የአለም አንደኛ የሀይማኖት መሪ በሆነችው በቫቲካን በኩል በጎቹ ላይ አድብታለች፡፡

[163] ቫቲካን ማለት በ44 ሄክታርና በ1,000 የህዝብ ብዛት በሮም ከተማ ውስጥ የምትገኝ የራሷ መንግስት፣ ባንዲራና ብሄራዊ መዝሙር ያላት ሉአላዊ

---

[162] https://en.m.Wikipedia>wiki>The capitolina Wolf

[163] https://en.m.Wikipedia>wiki>Vatican City

ሀገር ናት፣ ሀገሪቱም የምትመራው የአለም ካቶሊክ ሀይማኖት መሪና የሮማው ጳጳስ ሆነው በሚሾሙት ሰው ነው፡፡ ይህቺ ከአለም የመጨመረሻ ትንሿ ሀገር የ1.3 ቢሊየን ተከታይ ያላት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሪ በመሆኗ ያላት የፖለቲካ ጉልበት ከሀያላኑ ሀገራት ጋር የሚስተካከል ነው፡፡

የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጥንታዊ ቤተክርስቲያን ስትሆን እንደ ጥንታዊነቷም በጊዜ ሂደት ውስጥ ብዙ የተሳሳቱ ትምህርቶች ወደ ቤተክርስቲያኗ እንደገቡ በምዕራፍ 4 በዝርዝር ተመልክተናል፣ ሁለቱም ኦርቶዶክስና ካቶሊክ አስተምህሮ ከሞለ ጎደል ተመሳሳይ በመሆኑ ሁለቱም በተመሳሳይ የስህተት መንገድ ላይ የሚገኙ ቢሆንም የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግን ከስህተቱም አልፋ በግልፅ የጥልቁ መንፈሳዊ አሰራር ውስጥ ገብታለች፡፡

በዚህም ቤተክርስቲያኗ ዛሬ ላይ የሰይጣን እጆች ወደ ክርስትና ማስገቢያ ቀዳዳ ሆናለች፣ የሰይጣንን እቅዶች የክርስትና ካባ የሚደረብላቸው በዚች ቤተክርስቲያን ነው፣ ዛሬ በቤተክርስቲያኗ የሆሞሴክሹዋል(ወንድ ለወንድ/ሴት ለሴት ጋብቻ) ህጋዊ ጋብቻ ተደርጎ ተፈቅዷል፣ ቤተክርስቲያኗ ብዙ ታዋቂ ግብረሰዶም ቀሳውስት አሏት፣ ብዙ ህፃናትም በግብረ ሰዶማውያኑ ቀሳውስት ተደፍረዋል፡፡ በፖለቲካው መስክም ከቅዱሱ በተቃራኒው ተሰልፋለች፣ የእስራኤል - ፍልስጤም ጉዳይ ላይ እስራኤልን የሚጎዳው የሁለት ሀገሮች መፍትሄ(two state solution) ደጋፊ ስትሆን ይህንኑ የሚያጠናክር የፍልስጤምን ነፃ ሀገርነት ስምምነት ከፍልስጤማውኑ የነፃነት ድርጅት(PLO) ጋር ተፈራርማለች፣ የኢየሩሳሌም የእስራኤል ዋና ከተማነትን ትቃወማለች፣ አባማ ያዘጋጀው እስራኤልን የሚጎዳው የኢራን የኒውክለር ውል ትደግፋለች፣ የግሎባላይዜሽን ደጋፊ ስትሆን በዚህም የትራምፕን "አሜሪካ ትቅደም" እና የአሜሪካን ድንበር ለስደተኞች ዝግ የማድረግ ፖሊሲን ትቃወማለች፣ ብሬግዚትን ትቃወማለች፣ የወደፊቱ ሀሰተኛው ክርስቶስ የሚመራው "አንድ ዓለም አንድ ሀይማኖት" መርህ በመቀበል ሀይማኖታትን አንድ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች፡፡

በዚህም በአሁኑ ጊዜ ቫቲካን ያለችበትን መንፈስ ማስተዋል ይቻላል፡፡

## 4. ኢትዮጵያ

ከላይ የተመለከትነው የመንፈስ አሰራር ኢትዮጵያ ላይም እየሰራ ይገኛል፣ ገዢው ፓርቲ ከላይ ከተመለከትናቸው መናፍስታዊ አሰራሮች ጋር መስመርተኛ በመሆኑ ተመሳሳይ አሰራሮችንና አቋሞችን በሀገር ውስጥና በዓለማቀፍ ጉዳዮች ላይ እያራመደ ይገኛል፡፡

ከዓለማቀፍ እውነታ ብንነሳ እስራኤልን የሚጎዳውን "የእስራኤልና የፍልስጤም ሁለት ሀገር መፍትሄ" (two State Solution) ከመደገፍ አልፎ ፍልስጤም ሀገር ሳትሆን እንደ አንድ ሀገር አዲስ አበባ ላይ ኤምባሲ ከፍቶላታል፣ የኢየሩሳሌምን የእስራኤል ዋና ከተማነትን ይቃወማል፣ ኦባማ ያዘጋጀውና እስራኤልን የሚጎዳው የኢራን የኒውክለር ውል ይደግፋል፣ ከአሜሪካው ዲሞክራት ፓርቲ ጋር ፍቅር በፍቅር ሲሆን ከሪፐብሊካን ፓርቲ ጋር ግን ተቃራኒ ነው፣ በዚህም ትራምፕ እንዳይመረጥ በፓርቲው የዲያስፖራ ማህበረሰብ በኩል ብዙ ዘመቻዎች ሲያካሄድ ነበረ፣ ለትራምፕ ተቃራኒዋ ሂላሪ የምርጫ ዘመቻ ወጪ በነህላሙዲን በኩል የገንዘብ ድጋፍ ሲያስደርግ ነበረ፡፡

በሀገር ውስጥም ውርጃን ህጋዊ ያደረገ ሲሆን በዚህም በመንግስት ጤና ተቋማት በኩል [164] በአመት 221,533 ህፃናትን እንዲሁ በሜሪስቶፕስ በኩል በአመት 504,000 ህፃናትን፣ እንደዚሁ በብሉስታር በኩልም ተመሳሳይ መጠን ውርጃ ይከናወናል፣ በዚህም በአመት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያንን በውርጃ እንዲገደሉ በማድረግ ሀገሪቱን በውርጃ በአፍሪካ አንደኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧት ይገኛል፡፡ ሆሞሴክሹዋሊቲን በግልፅ ባይፈቅድም ሲከለከል ግን አይታይም ይባሱኑ በማረሚያ ቤቶች እንዲስፋፋና በፆታና ስነተዋልዶ ትምህርቶች በሚሰጡት ድርጅቶች በኩል የሆሞሴክሹዋሊቲን ማበረታቻ ትምህርቶችና ልምምዶች ሲሰጡ በዝምታ እየተመለከተ ይገኛል፡፡

---

[164] የኢትዮጵያ ጉባኤ እግዚአብሄር ቤተክርስቲያን፣ **የጊዜው ድምፅ** (መፅሄት)፣ 2010፣ ቁጥር 8፣ ገፅ 37

ፓርቲው በሚከተለው ሰይጣናዊ አሰራር ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በሀገሪቱ ላይ ብዙ ሰይጣናዊ ስራዎችን ሲፈፅም ቆይቷል፣ "ተቃዋሚ" ባላቸው ዜጎች ላይ ምን አይነት ሰይጣናዊ ስራዎች ሲሰራ እንደነበረ፣ ሀገሪቱ እንዴታድግ ሀብቷ እንዴት ሲዘረፍና ሲያባክን እንደነበረ፣ ለዚህና ለቀጣዩ ትውልድ ምን ያህል ዕዳ እንዳስቀመጠ፣ የ2010 "ለውጥ" ሲጀመር ጨልፈው ሲያሳዩን በነበሩ ዶክመንተሪ ፊልሞች አሳይተውናል፤ በሀሰተኛ መረጃ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት መቶ ሺዎች እንዲያልቁ አድርጓል፤ ፓርቲው በሚከተለው "ከፋፍለህ ግዛ" ቀመር ምክንያት በተፈጠሩ ግጭቶች ብዙዎች አልቀዋል፣ ከቄያቸው ተሰደዋል፣ የአካል ጉዳተኛ ሆነዋል፣ የሀገር አንድነት አደጋ ውስጥ ገብቷል፣ ለቀጣይ ትውልድ እንኳን የቤት ስራ አስቀምጧል ...

ባንዲራና አርማ የተለያዩ ነገሮች ሆነው ሳለ በሀገሪቱ ባንዲራ ላይ በህገ መንግሥቱ ያልተደነገገውን ዓለማቀፋዊውን ሰይጣናዊ አርማ አስቀምጧል፣ [165] በክብ ውስጥ የተቀመጠ አምስት ጎን ያለው ኮከብ ማለት አለማቀፋዊ የሰይጣን ምልክት ነው፣ የ666 መንፈስ አካል የሆነው የኢሉሚናቲ ሃይማኖትም ለአርማው የሚጠቀመው ይህንኑ አርማ ነው፣ ትርጉሙም የፍየል ሁለቱ ቀንዶች፣ ሁለቱ ጆሮዎችና ፂሙ ሲሆን ያው መፅሃፉ ኢየሱስን "በጉ" እንደሚለው ሀሰተኛውን ክርስቶስ ደግሞ በፍየል እንደሚመሰለው ነው፡፡

የሚገርመው ደግሞ ይህ አርማ በባንዲራውና ከህገመንግስቱ አንስቶ ባሉት ህጎች ላይ ጎልቶ ተቀምጧል፣ "ኢትዮጵያ" ሲባል በዋናነት የሚታየው ባንዲራዋ ነው፣ በዚህም ባንዲራዋ ግንባርዋ ነው፣ ሀገሪቱ የምትተዳደረው በህግ ነው፣ በዚህም ህጉ የሀገሪቱ ቀኝ እጅ ነው፣ በዚህም ፓርቲው በራዕ.13፡16-18 ላይ የተገለፀውን የአውሬውን ምልክት በሀገሪቱ ግንባርና ቀኝ እጅ ላይ አስቀምጦ ይገኛል፤ ከዚህ በተጨማሪም ሶስት የቀለም እስትራይፖችን ከክብ ቅርፅ ጋር የሚቀናበርበት አሰራርም በራሱ "አእምሮ ያለው ይቁጠረው" የተባለው የ666 ቁጥር አንዱ የአፃፃፍ ስልት ነው፡፡

---

[165] https://en.m.Wikipedia>wiki>satanism

አሁን የመጣው "የለውጥ ቡድንም" እነዚህን ሰይጣናዊ ትሩፋቶች እንዳለ ይዞ ይባሱኑ የፓርቲውን ስም "የስሙ ቁጥር(ራዕ.13፡17-18)" አድረጎ አምጥቷል፣ ይህንንም እውነታ ለማስተዋል የኢትዮጵያ የብልፅግና ፓርቲ የሚለው "epp" ገልብጠን ከጀርባው ስንመለከተው በግልፅ "666" ቁጥር ነው፣ በዚህም መሪዎቹ የህይማኖት ካባ ደርበው ቢታዩም ከጀርባቸው ያለው ይኸው መንፈስ ነው፡፡

በዚህም ገዢው ፓርቲ የታሰረበትንና ሀገሪቱንም ያሰረበትን መንፈስ ማስተዋል ይቻላል፤ ፓርቲው ሀይል አግኝቶ ሀገሪቱ ላይ መቀመጥና መቆየት የቻለው በአባላቱ፣ ደጋፊዎቹና መራጮቹ ነው፣ በዚህም ብዙ ሰው በሰይጣን ማስመሰያዎች በመታለል ሳያስተውል የጥልቁን መንፈስ አገልጋይ ሆኖ እየሰራ ይገኛል፣ በዚህም ማንም ፓርቲዋን ከሚጠብቀው መቅሰፍት እንዳይቀበል ከሀጢያትዋ ባይተባበር መልካም ነው(ራዕ.18፡4)፡፡

<u>ማጠቃለያ (በመሪዎች መካከል እየተሰራ ያለው መናፍስታዊ ትስስር)</u>

አሁን የሚታየው የግሎባላይዜሽን ሂደት፣ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂ ሁሉንም ነገር በአንድ ዕዝ ስር የማስገባት ሂደት፣ የእስራኤል፣ ፍልስጤምና ኢራን ጉዳዮች ላይ እስራኤልን የሚጎዱ አቋሞች፣ የውርጃና ግብረ ሰዶማዊነት አካሄዶች … የመንፈሱ መንገድ ጠራጊዎች ናቸው፣ ልክ ዮሐንስ ለክርስቶስ መምጫ መንገድ ሲያመቻች እንደነበረው ማለት ነው፡፡

በዚህም እያንዳንዱ ክርስቲያን ቢያንስ እነዚህን "ህሰተኛ ዮሐንስ" አሰራሮችንና ፓርቲዎችን ባለመደገፍ፣ አባል ባለመሆንና በምርጫ ጊዜም እነሱን ባለመምረጥ መንፈሳዊ ቡድንተኝነቱን ሊለይና ከመቅሰፍትዋ እንዳይቀበል በሀጢያትዋ ባለመተባበር(ራዕ.18፡4) ራሱን ሊለይ ይገባል፡፡

## 7.2. <u>መንፈሱ በሙላት ሲገለጥ የሚከተለው አሰራር</u>

መንፈሱ ዛሬ ላይ ከላይ እንደተመለከትነው በነገስታት በኩል ግልፅ ባልሆነ መንገድ ውስጥ ለውስጥ እየሰራ ቢሆንም፣ እንደዚሁ በአንዳንድ ሰዎች በኩል ኢሉሚናቲ፣ ሳታኒዝም … በሚሉ መንፈሳዊ ስሞች ጥቂት እንቅስቃሴዎችን ቢጀምርም፣ መንፈሱ ግን በግልፅ በአለም ላይ በአሸናፊነት የሚሰራበት የራሱ ዘመን አለው፣ ይህም ለሰባት አመታት(አንድ ሱባኤ) ሲሆን(ዳን.9፡27) በዚህ ሰባት አመት ሁለተኛው መንፈቅ ላይ(42

ወራት/1260 ቀናት) መንፈሱ በአለም ላይ ይነግሳል(ዳን.11፡36, ራዕ.13፡5-7)፣ እስራኤልን ይወርራል(ራዕ.11፡2, ራዕ.13፡5)፣ በእስራኤል ላይ የሚነሱትን ሁለቱን ነብያት ይገድላል(ራዕ.11፡3-10)፣ ወደ እግዚአብሄር የሚደረገውን አምልኮ ያስቀራል(ዳን.11፡31)፣ "እግዚአብሄር እኔ ነኝ" በማለት(2ተሰ.2፡4) ብቻውን የሚመለክበት(ራዕ.13፡4) ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ይህንንም የሚያደርገው ከላይ የተመለከትናቸውን ሁኔታዎችን እያመቻቹለት በሚገኙት "ሀሰተኛ ዮሐንሶች" በመጠቀምና ቀጥሎ በምንመለከታቸው በግለሰቦች ሰውነት ውስጥ በሚቀበር ረቂቅ ቁስና ድርጅቶችንም ደግሞ የራሱን ምልክትና አርማ እንዲጠቀሙ በማድረግ ሁሉንም ሰውና አሰራር በራሱ ቁጥጥር ውስጥ በማስገባት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

1. <u>በግለሰቦች ላይ በሚቀበር ምልክት</u>

መንፈሱ በግልፅ መስራት ሲጀምር የአለምን ህዝብ የሚቆጣጠረው በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ እንዲቀበር በሚያደርገው አሰራሩ(ቴክኖሎጂው) ነው፣

> ራዕ.13፡16 "ታናናሾችም ታላላቆችም ባለጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎች ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ(ያደርጋል)"

በወቅቱ ራዕዩን የተቀበለው ዮሐንስ የተመለከተውን ራዕይ በወቅቱ በነበረው ሰውኛ ቋንቋ ችግር የሚገልፅበት ቃል ባለመኖሩ፣ በገባው መንገድ "ምልክት" ብሎ ገልፆታል፣ ቴክኖሎጂው አሁን በሙከራ ላይ በመሆኑ አሁንም አንድ ቋሚ ስም አልያዘም፣ በዚህም አሁንም በተለያየ ስም እየተጠራ ይገኛል፣ RFID Chips, Bio chips, micro chips … ለዚህም ቀለል ባለ ቋንቋ ለጊዜው "ቺፕስ" ብለን እንጠራዋለን፡፡

ይህ ቺፕስ በአነስተኛ መጠን ተሰርቶ በሰውነት ውስጥ የሚቀበር የመረጃ ስርአት የኤሌክትሮኒክ ቁስ ሲሆን ቺፕሱም ወደ ሰው ውስጥ እንዴት ሊገባ እንደሚችል ሳይንቲስቶች ብዙ ጥናት እያደረጉ ሲሆኑ ከሁሉ ጎልተው እየወጡ ያሉት ግኝቶች ቺፕሱ በቀላሉ እንደ መድሃኒት በመርፌ፣ በንቅሳት መልክ በመንቀስ ወይ በጨረር ማስገባት እንደሚቻል እየተነገረ ይገኛል፡፡

ቺፕሱንም አንባቢ መሳርያዎች በቀላሉ ማንበብ እንዲችሉ መቀበር ያለበት በቀኝ እጅ ወይንም በግምባር ላይ መሆን እንዳለበት እየተነገረ ይገኛል፣ ይህም በራዕዩ ላይ የተገለፀው እውነታ ነው፡፡ ስርአቱ ይህንን የሚቀበረውን ቺፕስ ለማንበብ የሚጠቀመው የ"Computer እና RFID scanner" ቴክኖሎጂ ጥምርታን ሲሆን፣ እነኚህ ስሞች ደግሞ ከታች በቀረበው የማስያ ፎርሙላ መሠረት "የአውሬው ቁጥር" የተባለውን 666 ቁጥር መምጣታቸው የሚያስገርም ነገር ነው፡፡

ይህ አሰራር ላይ ላዩን ሲታይ ብዙ ጥቅሞች አሉት፣ ይህም በዋናነት የገንዘብ ኖት፣ የባንክ ደብተር፣ መታወቂያ፣ የመንጃ ፍቃድ፣ የህክምና ታሪክ፣ የትምህርት ማስረጃ ... በአጠቃላይ የወረቀት ዶክመንቶችን ሸክም የሚያስቀር፣ በፎርጅሪ፣ ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ቃጠሎ ... ምክንያት የሚመጡ ችግሮችን የሚያስቀርና ሰዎች ግብይትን በቀላሉ መንገድ እንዲፈፅሙ የሚረዳ "ቴክኖሎጂ" ነው፣ ነገር ግን ዋናው ስራው ከላይ የተመለከትነው ዓለምን በአንድ ስርአት ውስጥ እያስገባው ያለው መንፈስ ግለሰቦችንም በዚሁ ቁጥጥር ስር የሚያስገባበት አሰራር ነው፣ ከዚህ የከፋው ደግሞ ምልክቱን መቀበል የሰይጣን መንግስት ሙሉ አባልነት የሚረጋገጥበት አሰራር ነው፡፡

መፅሀፍ ቅዱሱ በዚያን ወቅት የሚኖሩት ቅዱሳን ይህንን ምልክት በመቀበል የሰይጣን መንግስት አባል እንዳይሆኑ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

2. <u>ድርጅቶች በሚጠቀሙት አርማና የንግድ ምልክት</u>

መንፈሱ በሙላት በሚሰራበት ወቅት ድርጅቶች ለአርማ ወይንም ለንግድ ምልክታቸው የአውሬውን ምልክት ወይንም የስሙን ቁጥር እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል፣

> ራዕ.13፥17-18 "<u>የአውሬው ምልክት</u> ወይም <u>የስሙ ቁጥር</u> ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል፡፡ አእምሮ ያለው የአውሬውን <u>ቁጥር</u> ይቁጠረው፤ <u>ቁጥሩ</u> የሰው <u>ቁጥር</u> ነውና፣ <u>ቁጥሩም</u> ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው፡፡"

እዚህ ጋር "የአውሬው ምልክት" የሚለው በራዕ.13፥1 ላይ በቀጥታ የተመለከተው "አስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ያለው አውሬ" የሚለውን ምስል አንስቶ ሰይጣን የሚመሰልበት የእባብ፣ ዘንዶ፣ ጊንጥ ... ምስሎች እንዲሁም

ጥርሳቸው፣ ጥፍራቸው ... የጎሉ አውሬዎች፣ እስከ የእስራኤላውያን የውርደት ምልክቶች፣ የግብፅ ፒራሚድ፣ የናዚ አርማ ... ምስሎች የሚደርስ ነው፡፡

"የስሙ ቁጥር" የሚለው የአውሬው አሃዛዊ መገለጫ ሲሆን ይህም የአውሬው ቁጥር "666" ጋር ግንኙት ያለው ቁጥር ነው፣ መፅሀፍ ቅዱሱ "አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው፣ ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና" ይላል እንጂ ሙሉ መረጃውን አይሰጥም ምክንያቱም ቁጥሮቹ በተለያዩ ዘዴ የሚቀናበሩ በመሆኑና ማንም አእምሮ ያለው ሰው ከቅንብሩ ውስጥ ቁጥሩን ማንበብ የሚችል በመሆኑ ነው፤ ዛሬ ላይ ሰዎች ለራሳቸውና ለድርጅታቸው ስኬት ሲሉ ከመናፍስታዊው አሰራር ጋር እየፈጠሩት ባለው ህብረት ቁጥሩን በድርጅቶቻቸው አርማዎችና የንግድ ምልክቶች በተለያየ ቅንብር እያሳዩን ይገኛሉ፣ ዋነኞቹን የቅንብር ዘዴዎች ብንመለከት፣

1. ቁጥሩን በቀጥታ፣ በተለያየ አቅጣጫ ወይም በተለያየ ዘዴ በማደራረብ በመፃፍ፡- 666፣ 999 ...
2. ቁጥሩን ከምልክቶች፣ ከአርማዎች ... ውስጥ በማንበብ፣ ለምሳሌ
    - አንዱን ስድስት በተለያየ ዘዴ በሶስት ቀለሞች፣ መስመሮች ... በመስራት፣
    - የእስፕሪንግ ጥቅልል በማስመሰል የተያያዙ ስድስቶችን በመስራት፣
    - ሶስት ስድስትን እንዲፈጥሩ አንድ ዜሮን የሚጋሩና በዙርያቸው በተለያየ ዘዴ የተቀናበሩ ሶስት መስመሮች፣ ጭረቶች፣ ቅንፎች ጥቅልሎች፣ ሬክታንግሎች፣ ቀለሞች ... በመስራት፣
    - ሶስት ስድስቶችን እንዲፈጥሩ ሶስት ዜሮዎችን በተለያየ መንገድ በአንድ ጭረት በማገናኘት፣
    - ሶስት ጎን፣ ሶስት ቀለም ... ሶስት ነገሮችን በተለያየ ዘዴ ከስድስት ጎን፣ ስድስት ቁጥር፣ ስድስት ቀለም ... ጋር በማጣመር፣
    - ሶስት ስድስት ጎን ያለውን ፖሊጎን(Hexagon) በተለያየ ዘዴ በመሳል፣ አንዱን ሄክሳ ጎን በሶስት ቀለማት በመቀባት ...

3. መነሻው ባይታወቅም አንዳንዶች "የስሙ ቁጥር" የሚለውን፣ የእንግሊዘኛ ፊደሎችን በቁጥር በመተካት ሲያሰሉ ይታያሉ፣

በዚህም ከA-Z ያሉትን የእንግሊዘኛ ቃላትን በስድስት ብዜት ቁጥር በመተካት (A=6, B=12, C=18, D=24, E=30, F=36, G=42, H=48, I=54, J=60, K=66, L=72, M=78, N=84, O=90, P=96, Q=102, R=108, S=114, T=120, U=126, V=132, W=138, X=144, Y=150, Z=156)፣ ከዚያም የተፈለገውን ቃል የፊደላት ቁጥሮችን በመደመር ውጤቱን ያሰላሉ፣

ለምሳሌ "Computer" የሚለውን ቃል በዚህ ዘዴ ብናሰላ፣

C=18, o= 90, m=78, p= 96, u= 126, t= 120, e= 30, r= 108

18+90+78+96+126+120+30+108

= 666

በዚህ ዘዴ፣ Computer, mark of beast, RFID scanner ... ድምራቸው 666 ይመጣል፣ የዚህን ዘዴ አሰራር መነሻ ማረጋገጥ ባይቻልም በዚህ ስሌት 666 የመጡትን ስንመለከት ከ666 መንፈስ ጋር የሚገናኙ ናቸው፣ "The result explains the path" በሚባለው አባባል የውጤቱ ትክክለኛነት የስሌቱን ትክክለኝነት ሲያሳይ እንመለከታለን፡፡

በዚህም መፅሀፍ ቅዱሱ "አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው" የተባለውን ማስተዋል ይችላል፡፡

### 7.3. <u>የመንፈሱ የቁጥጥር እስትራቴጂ</u>

ከላይ እንደተመለከትነው አለም በግሎባላይዜሽን ሂደትና በኮምፒውተር ቴክኖሎጂ እገዛ አንድ መንደር እየሆነች ትገኛለች፣ በዚህም ሁሉም ነገር በአንድ ስርአት ውስጥ እየተጠቃለለና የመንፈሱ አሰራር አለምን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል አመቺ ሁኔታዎች እየተፈጠሩለት ይገኛል፡፡

ነገር ግን ስለ መንፈሱ አሰራር መፅሀፍ ቅዱሱ አስቀድሞ ስላስጠነቀቀና በቴክኖሎጂው እንግዳነት ምክንያት ቺፕስ በሰውነት ውስጥ የማስገባቱ ሂደት ቀላል ሂደት አይሆንም፣ በዚህም መንፈሱ ሰዎች አሰራሩን አካብደው እንዳያዩ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል፣ ዘዴዎቹም

- <u>ማለማመጃዎች</u>

ሰዎች ገንዘብ የሚያክልን ነገር በትንሽ ማይክሮ ቺፕስ ማስቀመጥ ላያምኑ ስለሚችሉ ወደዚህ ቴክኖሎጂ ከመገባቱ በፊት፣ ሰዎች ብዙ ብር እንዴት በቀላሉ በግብይት ካርድ በመያዝ መገበያየት እንደሚችሉ ያለማምዳል፡፡

- <u>ስነልቦናዊ አካሄዶች በመጠቀም</u>
    - አሰራሩን መንፈሳዊ ሳይሆን ቴክኖሎጂያዊ በማስመሰል፣ ይህንን የሚቃወሙ ሰዎች ቴክኖሎጂ ያልገባቸው "መሀይሞች" በማስመሰል፣
    - የግብይት ስርአቱ "የዘመናዊነት" ምልክት በማድረግ ይህንን ያልተቀበሉ ሰዎች "ፋራዎች" በማስመሰል፣

- <u>አጋጣሚዎችን በመጠቀም</u>

አሰራሩን የሚመሩት፣ ሰዎች ይህንን ምልክት እንዲቀበሉ የተለያዩ አጋጣሚዎችን እየፈጠሩና እየተጠቀሙ ይገኛሉ፣ አባማ ሰዎች የጤና ኢንሹራንስ ለማግኘት ማስቀበር እንዳለባቸው ህግ አውጥቷል፣ የአለም አንደኛው ሀብታም ቢል ጌትስም የኮሮና ቫይረስ ክትባት ያገኙና ያላገኙ ሰዎችን ለመለየት ሰዎች ምልክቱን እንዲቀበሉ በማለት ሀሳብ ሲያቀርብ ነበረ፣ በዚህ ሰዎች በተለያየ አጋጣሚ ለጤና መድህን፣ ለክትባት... ሲሉ ይህንን ምልክት እዲቀበሉ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡

- <u>አስገዳጅ ሁኔታዎችን በመፍጠር</u>
    - መግዛትም መሸጥን በዚህ ዘዴ ብቻ በመገደብ ምልክቱን የማይቀበሉ ከገብያው፣ ከኢኮኖሚው፣ ከማህበራዊ ህይወት ... እንዲነጠሉ በማድረግ ምልክቱን እንዲቀበሉ ማስገደድ፣
    - ሰዎች የሚከፈላቸውን ክፍያ እንዲሁም በባንክና በቁጠባ ተቋማት ያስቀመጡትን ገንዘብ ማግኘት የሚችሉት በዚህ ስርአት በማድረግ ምልክቱን እንዲቀበሉ ማስገደድ፣

መፅሀፍ ቅዱሱ ግን አስቀድሞ ሁሉንም በዝርዝር ስላስጠነቀቀ ምልክቱን በመቀበል ለሚመጣው ኪሳራ ሀላፊነቱ የባለቤቱ ነው፡፡

## 7.4. የአሰራሩ መጨረሻ

አሁን የዚህ መንፈስ አሰራር ውስጥ ለውስጥ እንጂ በግልፅ አልተጀመረም፣ ከመንገድ ጠራጊዎቹ "ሀሰተኛ ዮሐንሶች" በስተቀር ዋናው መንፈስ አልተገለጠም ነገር ግን ጊዜው እየደረሰ እንደሆነ ከላይ ከተመለከትነው አለማቀፋዊና ሀገራዊ ትስስሮሽ፣ ቴክኖሎጂያዊ ትስስሮችና የግብይት ልምምዶች ማስተዋል ይቻላል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው የመንፈሱ አሰራር አንዱ መገለጫው ለእስራኤል ያለው ጥላቻ ነው፣ ይህ ሂደት በ1.4.2.3/3 ክፍል እንደተመለከትነው በአለም ላይ እየተከናወነ ያለ ሂደት ነው፣ ግለሰቦች፣ ሀገራት፣ ቀጠናዊና አለማቀፋዊ ህብረቶች በእስራኤል ላይ ያላቸው ጥላቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፣ ይህም ጥላቻ እየጨመረ በመሄድ ከዓለም የተውጣጣ "ማን እርሱን ሊዋጋ ይችላል" የሚባል ጦር(ራዕ.13፡4) በሀሰተኛው ክርስቶስ(መኽዲ/ክርሺና/ሚየትራ/ካልኪ/ልዕለ ሰው) መሪነት እስራኤልን ለ42 ወራት ይወራል(ራዕ.11፡2, ራዕ.13፡5 ...)፡፡

በዚህ እስራኤል መፈናፈኛ በሚያሳጣው ከአቅም በላይ በሚሆን ችግር መካከል በሚነሱት ሁለቱ ነብያት(ራዕ.11፡3-7) ምክንያት እስራኤል የገደለችውን ኢየሱስን ትቀበላለች፣ ከከበባትም ጭንቅ የተነሳ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ታነሳለች፣ በዚህም ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ እስራኤልን ሊረዳ ይገለጣል(ዘካ.14፡1-4, ማር.13፡3-37)፣ በዚህም በሀሰተኛውና በእውነታኛው ክርስቶስ መካከል ውጊያ ይካሄዳል(ራዕ.19፡15-21)፣ ኢየሱስም ይህንን የዓለምን ሰራዊት በመደምሰስ፣ መንፈሱንና አጠቃላይ ዲያብሎስን ለሺ አመት በማሰር ለእስራኤል ብሎም ለአለም ሰላምን ያወርዳል(ራዕ.20፡3)፣ በዚህም የመንፈሱ አሰራር መቋጫ ያገኛል፡፡

# ማጠቃለያ

ከላይ በቀረቡት እውነታዎች የሰው ልጆችን የሀይማኖት ልዩነት ምክንያትና ልዩነቱን መፍታት የሚቻልበትን መንገድ ከስር መሠረቱ፣ አምላክ አለ? ወይስ የለም? ከሚለው ተነስተን የየሀይማኖቶቹን ፍልስፍና ፈትሸን ትክክለኛዋ ሀይማኖት የትኛዋ እንደሆነች ለይተን ተመልክተናል፡፡

በዚህም የኢአማኒያን "ፈጣሪ አምላክ የለም" የሚለው ፍልስፍና የተሳሳተ ፍልስፍና መሆኑና ፈጣሪ አምላክ መኖሩን፣ ዋናውንም ፈጣሪ የሚያመልከው ሀይማኖትም የሚገኘው (በመቅድም ክፍል እንደተመለከተው) በጂኦግራፊ/በብሄር በማይወሰኑትና የአንዱ ዋናው አምላክ ተከታዮች በሆኑት በአብርሃም ሀይማኖቶች ውስጥ መሆኑን፣ ከአብርሃም ሀይማቶች ደግሞ የቁርአን፣ ሞርሞን ... መንገድ የስህተት መንገድ መሆኑንና ትክክኛው የመፅሀፍ ቅዱሱ መንገድ መሆኑን፣ መፅሀፍ ቅዱሱንም ከያዙት አብያተ ክርስቲያናት ጥንታውያኑ ኦርቶዶክስና ካቶሊክ በቆይታቸው ውስጥ በገቡባቸው የስህተት ትምህርቶች ከትክክለኛ መንገድ የወጡ መሆኑን፣ አዳዲሶቹ የሐዋርያት፣ ጂሆቫና የአድቬንቲስት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በተሳሳተ ፍልስፍና የተመሠረቱ መሆኑን ነገር ግን አሁን ባለችበት አቋሟ በተሀድሶ የተመሠረተችው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በትክክለኛ መንገድ ላይ መሆኗን ተመልክተናል፡፡

እዚህ እውነታ ጋር ለመድረስ ተነበው ይቅርና ተገልጠው እንኳን የሚያልቁ የማይመስሉ የየሀይማኖቶችን መመርያ መፅሀፍትን፣ በግለሰቦች የተፃፉትን የሀይማኖትና የፍልስፍና መፅሀፍትን፣ ተጓዳኝ መፅሄቶችን፣ ቪሲዲዎችና ድረ ገፆችን በመጎብኘት፣ ከተለያዩ የሀይማኖት ሰዎች ጋር በመወያየት በብዙ አመታት ጥናት በተሰበሰቡ እውነታዎች መሆኑ አስረጂ አያስፈልገውም፤ ይህንን ሁሉ መንገድ መሄድ ያስፈለገውም አንዷን የእውነት መንገድ መልሶ ከማቆም፣ ሰዎች በሀይማኖት ልዩነት ምክንያት እየደረሰባቸው ካለው ችግርና በነፍስም ሊቀበሉት ከሚሉት መከራ ለመታደግ ነው፡፡ በዚህም ይህን የሰው ልጆች ዋና ልዩነት ችግር እንዲቀረፍ፣ አንድ እውነተኛ መንገድ ብቻ እንዳለችው ሁሉ ሁሉም ሰው ወደዚህች መንገድ እንዲመለስና ለዘላለማዊ ህይወቱ የሚመኛትን ገነት እንዲወርስ ሁሉም ይህንን እውነታ ለሌሎች በማዳረስ የድርሻውን እንዲወጣ አሳስባለሁ፡፡

# አባሪ(Annex)

## አባሪ - 1 (Annex-I) - የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች ምህፃረ ቃል

### ብሉይ ኪዳን

1. ዘፍ. - ኦሪት ዘፍጥረት
2. ዘፀ. - ኦሪት ዘፀአት
3. ዘሌ. - ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ዘኍ - ኦሪት ዘኍልቁ
5. ዘዳ. - ኦሪት ዘዳግም
6. ኢያ. - መፅሀፈ ኢያሱ
7. መሳ. - መፅሀፈ መሳፍንት
8. ሩት. - መፅሀፈ ሩት
9. 1ሳሙ.-መፅሀፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ
10. 2ሳሙ. - መፅሀፈ ሳሙኤል ካልዕ
11. 1ነገ. - መፅሀፈ ነገስት ቀዳማዊ
12. 2ነገ. - መፅሀፈ ነገስት ካልዕ
13. 1ዜና.-መፅሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
14. 2ዜና.-መፅሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ
15. ዕዝ. - መፅሀፈ ዕዝራ
16. ነሀ. - መፅሀፈ ነህምያ
17. አስ. - መፅሀፈ አስቴር
18. ኢዮ. - መፅሀፈ ኢዮብ
19. መዝ. - መዝሙረ ዳዊት
20. ምሳ. - መፅሀፈ ምሳሌ
21. መክ. - መፅሀፈ መክብብ
22. መኃ.-መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን
23. ኢሳ. - ትንቢተ ኢሳያስ
24. ኤር. - ትንቢተ ኤርምያስ
25. ሰቆ. - ሰቆቃወ ኤርምያስ
26. ሕዝ. - ትንቢተ ሕዝቅኤል
27. ዳን. - ትንቢተ ዳንኤል
28. ሆሴ. - ትንቢተ ሆሴዕ
29. አሞ. - ትንቢተ አሞፅ
30. ሚክ. - ትንቢተ ሚክያስ
31. ኢዩ. - ትንቢተ ኢዩኤል
32. አብድ. - ትንቢተ አብድዩ
33. ዮና. - ትንቢተ ዮናስ
34. ናሆ. - ትንቢተ ናሆም
35. ዕን. - ትንቢተ ዕንባቆም
36. ሶፎ. - ትንቢተ ሶፎንያስ
37. ሀጌ - ሀጌ
38. ዘካ. - ትንቢተ ዘካርያስ
39. ሚል. - ትንቢተ ሚልክያስ

### አዲስ ኪዳን

1. ማቴ. - የማቴዎስ ወንጌል
2. ማር. - የማርቆስ ወንጌል
3. ሉቃ. - የሉቃስ ወንጌል
4. ዮሐ. - የዮሐንስ ወንጌል
5. ሐስ. - የሐዋርያት ስራ
6. ሮሜ. - ወደ ሮሜ ሰዎች
7. 1ቆሮ. - 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
8. 2ቆሮ.-2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
9. ገላ. - ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ኤፌ. - ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ፊልጵ. - ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ቆላ. - ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. 1ተሰ.- 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች
14. 2ተሰ.-2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች
15. 1ጢሞ. - 1ኛ ወደ ጢሞቲዎስ ሰዎች
16. 2ጢሞ. - 2ኛ ወደ ጢሞቲዎስ ሰዎች
17. ቲቶ. - ወደ ቲቶ
18. ፊልሞ. - ወደ ፊልሞና
19. ዕብ. - ወደ ዕራውያን
20. ያዕ. - የያዕቆብ መልዕክት
21. 1ጴጥ. - 1ኛ የጴጥሮስ መልዕክት
22. 2ጴጥ.-2ኛ የጴጥሮስ መልዕክት
23. 1ዮሐ. - 1ኛ የዮሐንስ መልዕክት
24. 2ዮሐ.- 2ኛ የዮሐንስ መልዕክት
25. 3ዮሐ. -3ኛ የዮሐንስ መልዕክት
26. ይሁ. - የይሁዳ መልዕክት
27. ራዕ. - የዮሐንስ ራዕይ

## <u>አባሪ-II(Annex-II)</u> - <u>የቁርአን ምዕራፎች</u>

1. አል ፈቲሀ
2. አል በቀራህ
3. አል አእራፍ
4. አል ዒምራን
5. አል ማኢዳህ
6. አል ዓንአም
7. አል አዕራፍ
8. አል አንፋል
9. አል ተውባህ
10. የኑስ
11. ሁድ
12. ዩሱፍ
13. አል ረዕድ
14. ኢብራሂም
15. አል ሒጂር
16. አል ነህል
17. አል ኢስራዕ
18. አል ከህፍ
19. መርየም
20. ጣሀ
21. አል አንቢያ
22. አል ሐጅ
23. አል ሙዕሚኑን
24. አል ኑር
25. አል ፉርቃን
26. አል ሹአራዕ
27. አን ነምል
28. አል ቀሶስ
29. አል አንከቡት
30. አል ሩም
31. አል ሉቅማን
32. አል ሰጅዳህ
33. አል አህዛብ
34. ሰብእ
35. አል መላይካ (አል ፈጢር)
36. ያሲን
37. አል ሳፋት
38. ሷድ
39. አል ዙመር
40. አል ጋፊር
41. ፉሲለት
42. አል ሹራ
43. አል ዙኽሩፍ
44. አል ዱኻን
45. አል ጀሲያህ
46. አል አህቃፍ
47. ሙሀመድ
48. አል ፈትህ
49. አል ሑጅራት
50. ቃፍ
51. አል ዛሪያት
52. አል ጡር
53. አል ነጂም
54. አል ቀመር
55. አል ረህማን
56. አል ዋቂዓህ
57. አል ሐዲድ
58. አል ሙጀደላ
59. አል ሐሽር
60. አል ሙምተሒናህ
61. አል ሶፍ
62. አል ጁሙዓህ
63. አል ሙናፊቁ
64. አል ተጋቡን
65. አል ጠላቅ
66. አል ተህሪም
67. አል ሙልክ
68. አል ቀለም
69. አል ሓቃህ
70. አል መዓሪጅ
71. ኑህ
72. አል ጂን
73. አል ሙዘሚል
74. አል ሙደሲር
75. አል ቂያማህ
76. አል ደህር
77. አል ሙርሰላ
78. አል ነበዕ
79. አል ናዚዓት
80. ዐበሰ
81. አል ተከዊር
82. አል ኢንፊጣር
83. አል ሙጠፊፉን
84. አል ኢንሺቃቅ
85. አል ቡሩጅ
86. አል ጣሪቅ
87. አል አዕላ
88. አል ጋሺያህ
89. አል ፈጅር
90. አል በለድ
91. አል ሸምስ
92. አል ለይል
93. አል ዱሓ
94. አል ኢንሺራሕ
95. አል ቲን
96. አል ዐለቅ
97. አል ቀድር
98. አል በይናህ
99. አል ዘልዘላህ
100. አል ዓዲያት
101. አል ቃሪዓሕ
102. አል ተካሱር
103. አል ዓስር
104. አል ሁመዛህ
105. አል ፊል
106. አል ቁረይሽ
107. አል ማዑን
108. አል ከውሰር
109. አል ካፊሩን
110. አል ነስር
111. አል ለሐብ
112. አል ኢኽላስ
113. አል ፈለቅ
114. አል ናስ